# ዜና ጳጳሳት

# ኢትዮጵያውያን

«ዜና ሕይወቶሙ ወዕረፍቶሙ ለብፁዓን ወቅዱሳን
አበው ኢትዮጵያውያን»

ዲያቆን መርሻ አለኸኝ

አዲስ አበባ፤ 1996 ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ALL RIGHTS RESERVED

ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ ታርሞና ተስተካክሎ የተፈቀደ ነው።

የአዘጋጁ አድራሻ

ፖስታ ሣጥን ቁጥር – 12418

Email:– mershing@yahoo.com

## መታሰቢያነቱ

1ኛ. ሚያዝያ 27 ቀን 1994 ዓ.ም ከምንወደውና ከሚወደን ቤተ ሰቦቹ ከዚህ ዓለም በሞት ለተለየው ለአባቴ አቶ አለኸኝ መንግሥቴ፤

2ኛ. ትምህርታቸውን፣ ምክራቸውንና ጸሎታቸውን ስንፈልግ ሳለ በድንገት ጥቅምት 30 ቀን 1996 ዓ.ም ከሞት ለተለዩን ደግ አባታችን ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ይሁንልኝ።





«መልካም ስም ከብዙ ባለጠግነት ይበልጣል» /ምሳሌ 22÷1/፡
«መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ» /ማቴ.5÷16/።

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ «ስምና ሥራ» የሚሉት ቃላት «መልካም» በሚል ቅጽል ወይም አጎላማሽ ቃል በመገለፃቸው ትርጉማቸው ጎልቶ ይታያል። የሰው ልጅ «አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ» እንደ ተባለው /ዘፍ. 3÷19/ ከተወሰነ ዕድሜ በኋላ ከሥጋዊ ዓለም ይለያል። ለዘሩ፣ ለትውልዱ በዓለም ላይ የሚቀረው ስሙና ሥራው ነው። ስም የሚያስጠራ ሥራ ካልሠራ ግን ሰውዬው ሲያልፍ ወዲያው ይረሳል፡ አስታዋሽ አይኖረውም። ፈጣሪውንም አያስመሰግንም፡ አያስከብርም። ቤተ ሰቡንም አያኮራም።

በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊው ዓለም መልካም ሥራ ማለትም እግዚአብሔርን የሚያስከብር፣ አገርን ወገንን በአጠቃላይ የሰውን ልጅ

www.ethiopianorthodox.org



«መልካም ስም ከብዙ ባለጠግነት ይበልጣል» /ምሳሌ 22፥1/፡
«መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ» /ማቴ.5÷16/።

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ «ስምና ሥራ» የሚሉት ቃላት «መልካም» በሚል ቅጽል ወይም አጎላማሽ ቃል በመገለፃቸው ትርጉማቸው ጎልቶ ይታያል። የሰው ልጅ «አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ» እንደ ተባለው /ዘፍ. 3÷19/ ከተወሰነ ዕድሜ በኋላ ከሥጋዊ ዓለም ይለያል። ለዘሩ፣ ለትውልዱ በዓለም ላይ የሚቀረው ስሙና ሥራው ነው። ስም የሚያስጠራ ሥራ ካልሠራ ግን ሰውዬው ሲያልፍ ወዲያው ይረሳል፡ አስታዋሽ አይኖረውም። ፈጣሪውንም አያስመሰግንም፡ አያስከብርም። ቤተ ሰቡንም አያኮራም።

በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊው ዓለም መልካም ሥራ ማለትም እግዚአብሔርን የሚያስከብር፣ አገርን ወገንን በአጠቃላይ የሰውን ልጅ

www.ethiopianorthodox.org

የሚጠቅም መልካም ዓላማን፣ እምነትን፣ ፍቅርን፣ ሰላምን ወዘተ. የሚያራምድ ሥራ የሠሩ ሰዎች ታሪካቸው፣ ገድላቸው፣ ዜናቸውና ትምህርታቸው ይጻፋል፡፡ በልዩ ልዩ መንገድ ይገለፃል፡፡

መነሻችን «የአበው ስምና ሥራ ሲዘከር» የሚል ነውና በመንፈሳዊው ዓለም የሆነውንና የተደረገውን ስንመለከት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ታሪክና በሌሎች ድርሳናት የአበው ስምና ሥራ ተጽፎ በዝርዝር ተገልፆ እናገኛለን፡፡ በበሉይ ኪዳን የአብርሃም፣ የሙሴ፣ የዳዊት ወዘተ. በሐዲስ ኪዳን የሐዋርያትና የተከታዮቻቸው፣ በሌሎች ድርሳናት የጻድቃን የሰማእታት ስምና ሥራ በሰፊው ተዘርዝሮ ይገኛል፡፡ ዓላማው ግልጽ ነው፡፡ ተተኪው ትውልድ ያለፉትን አበው መልካም ስምና ሥራ አውቆ ከአርአያነታቸውና ከምሳሌነታቸው እንዲማር፣ እንደነሱ እግዚአብሔርን እንዲያከብርና ለሀገሩ ለወገኑ የሚጠቅም መልካም ሥራን እንዲሠራ ለማነሣሣት ነው፡፡

ከዚህ መሠረታዊ ዓላማ በመነሣት የመንፈስ ቅዱስ ልጃችን ዲያቆን መርሻ አለኸኝ በሞተ ሥጋ ተለይተው በዐፀደ ነፍስ የሚገኙ የአበው ኤጲስ ቆጶሳትን፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትንና ቅዱሳን ፓትርያርኮችን ታሪክ፣ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ሥራቸውን፣ ተጋድሎአቸውን የሚያዘክር መጽሐፍ ጽፎ አቅርቧል፤ በመልእክታችን መነሻ ላይ «የአበው ስምና ሥራ ሲዘከር» ያልነው ለዚህ ነው፡፡

በታሪክ እንደ ተመዘገበው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለ1600 ዓመታት በውጭ ሀገር ተወላጅ ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት ስትተዳደር ብትኖርም፣ ከንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ከ1921 ዓ.ም ወዲህ ግን ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትን ሊቃነ ጳጳሳትንና ቅዱሳን ፓትርያርኮችን በማሾምና በመሾም መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቷን ስታበረክት ኖራለች፡፡ በዚህም ወሰብአ ኢትዮጵያሰ ኢይሤሙ ሊቀ እማእምራኒሆሙ /ኢትዮጵያውያን ከሊቃውንቶቻቸው መካከል ኤጲስ ቆጶሳትን አይሹሙ የሚለው የግብፃውያን ገደብ ተነስቷል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአርቆ ተመልካቹ በዓፄ ኃይለ ሥላሴ ከፍተኛ ጥረትና በአበተዋይና ደጋግ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጸሎትና ትጋት መንፈሳዊ ብቃትና አስተዳደራዊ ዕውቀት ያላቸው አበው ኢትዮጵያውያን ከኤጲስ ቆጶስነት ወደ ሊቀ ጵጵስና ከሊቀ ጵጵስና ወደ ፓትርያርክነት መዓርግ እንዲሸጋገሩ ተደርገው በአመራራቸው እነሆ ቤተ ክርስቲያናችንን አሁን ካለችበት አስተማማኝ ደረጃ አድርሰዋታል፡፡

እነዚህ ብፁዓን፣ ቅዱሳን አበው እያንዳንዳቸው «ሠናየ ገድለ ተጋደልኩ በድርየኒ ፈጸምኩ ወሃይማኖትየኒ በቀብኩ፤ እንክሰ ጽኑሕ ሊተ አክሊለ ጽድቅ ዘየዐስየኒ እግዚአብሔር ... » መልካሙን ገድል ተጋደልሁ፤ ሩጫዬን ጨረስሁ፤ ሃይማኖትንም ጠበቅሁ፤ እንግዲህስ እግዚአብሔር የሚሰጠኝ የጽድቅ አክሊል ይጠብቀኛል /2ኛ ጢሞ. 4÷7 - 8/



በማለት ከምድራዊ ሕይወት ወደ በማይ ሕይወት ተሸጋግረው በአፀደ ነፍስ ይገኛሉ፡፡ የእነዚህን አባቶች ስምና ሥራ በአንድ ጥራዝ አዘጋጅቶ ለንባብ እንዲበቃ ማድረጉ ጠቀሜታው ብዙና ከፍ ያለ ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ታሪካቸው በአሁኑና በሚመጣው ትውልድ እንዲታወቅ ያደርጋል፡፡ ዛሬ «ዜና አበው፣ ሃይማኖተ አበው፣ ገድለ ሐዋርያት፣ ገድለ ሰማዕታት» እያልን የምንማርባቸውና የምናስተምርባቸው መጻሕፍት የሚያገለግሉን ተጽፈው ስለቆዩን ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የቤተ ክርስቲያናችንን የጽሑፍ እንቅስቃሴ ያጠናክራል፡ ወደ ፊትም ያራምዳል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ጥናትና ምርምር በቤተ ክርስቲያናችን ጸሐፊዎች ዘንድ እንዲስፋፋ ያደርጋል፡፡

ስለዚህ «የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል» /መዝ. 111 ÷ 6/ እንደ ተባለው ወደ ዘላለም ዕረፍት የተሸጋገሩት የጻድቃን አበው ኤጲስ ቆጶሳት፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ቅዱሳን ፓትርያርኮች ዜና ሕይወትና ዕረፍት በአንድ መጽሐፍ ተበብስቦ መቅረቡ በጣም የሚደገፍ ቅዱስ ተግባር ነውና ጸሐፊው በብዙ ድካም አዘጋጅቶ ስላቀረበ «እግዚአብሔር ይባርክህ ይቀድስህ» እንላዋለን፡፡ አንባብያንም ዝግጅቱን በማንበብ ከአባቶች ሥራና ታሪክ በመማር ለበለጠ ሥራ እንዲነሣሡ፣ ክርስቲያናዊ ሃይማኖታቸውን አጽንተው እንዲይዙ መልእክታችንን እናስተላልፋለን፡፡ አምላከ ቅዱሳን እግዚአብሔር ከብፁዓን፣ ቅዱሳን አባቶቻችን ረድኤት ያሳትፈን፡፡

አባ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

www.ethiopianorthodox.org

# ምስጋና

ይህን የብፁዓን አባቶቻችንን ዜና ሕይወት የሚያትት የመጀመሪያ ክፍል መጽሐፍ ከዓመት በፊት ለማዘጋጀት ሳስብ በመጀመሪያ ያማከርኳቸው ነፍሳቸውን በገነት ያኑርልንና ባለፈው ዓመት በሚያሳዝን ድንገተኛ ሁኔታ በሞት የተለዩንን ታላቅ አባት ብፁዕ አቡነ ማቴዎስን ነበር። ብፁዕነታቸው በተለመደው ርኃታ የተመላበት የማዳመጥ ጥበባቸው እሳቤን ከተረዱ በኋላ ያሰብኩትን ሥራ ሙሉ በሙሉ እንደ ሚቀበሉት፣ ለተግባራዊነቱም ለምጠ ይቃቸው እንዳንድ ታሪካዊ ነጥቦች እስከ ሚያውቁት ድረስ መልስ በመስጠት ከጎኔ እንደ ሚቆሙ ገልጸው ምስጋናን ከቡራኬ ጋር ቸሩኝ። ብፁዕነታቸው ምንም እንኳን ከብዙ ድካምና ምርምር እንዲሁም ውይይት በኋላ ዛሬ ለዚህ የበቃውን ይህን መጽሐፍ ጥቂት የመጨረሻ የሕይወት ዘመናቸውን በዝምታ ካሳለፉባት ቤታቸው ሔጄ አበርክቼላቸው፤ የመከሩኝ ምክር ተግባራዊ መሆኑን በማየት የማይጠገበውን ምርቃታቸውንና ጸሎታቸውን ለማግኘት ባልታደልም፤ የአባታዊ ምክራቸውን ፍሬ በሀጸደ ነፍስ ከሚኖሩበት ዓለም ሆነው እንደ ሚያዩልኝ በማመን የልጅነት ምስጋናዬን በታላቅ አክብሮት እቀርባለሁ።

ይህ መጽሐፍ ሕይወታቸውን በሙሉ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በመስጠት የኖሩ፤ በመጨረሻም ለታላቁ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን በመብቃት ለቅዱስ ወንጌል በመላ ሀገሪቱ መዳረስ፣ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መጠበቅ ደፋ ቀና በማለት ሩጫቸውን እየጨረሱ ያለፉ ብፁዓን አባቶችን ዜና ሕይወት የሚያቀርብ በመሆኑ በአንድ ቦታ ተወስኖ የሚሠራ አልነበረም። በመሆኑም ከበርካታ አባቶች እና ወንድሞች ጋር በእያንዳንዱ አባት ዙሪያ ውይይት አድርጌያለሁ። በዚህ ረገድ ሐሳቤን በመረዳት ብዙ የቤተ ክርስቲያናችን አባቶችና ደቀ መዛሙርት የሚያውቁትን ታሪክ በመተረክ፣ የጽሑፍ ማስረጃዎችን በመስጠትና የጻፍኩትን በመተቸት ከፍተኛ ርዳታ አድርገውልኛል። በለዚህ ዝግጅቴን በመደገፍ ለተባበሩኝ ሁሉ ከፍተኛ ምስጋናዬን እቀርባለሁ። በተለይ በቃላት ውስጥ የፊደላትን ኹነኛ ቦታ፤ በሀረፍተ ነገሮችም ውስጥ የቃላትን አገባብና ትርጉም በእጅጉ በመጠንቀቁ ለወጣት ጸሐፍያን አርአያ የሚሆኑን ሊቀ ትጉኃን ኃይለ ጊዮርጊስ ዳኜ የመጽሐፉን ረቂቅ በጥንቃቄ በማንበብ፣ በረጅም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቱ በዚህ መጽሐፍ ዜና ሕይወታቸው የቀረበላቸውን አባቶች በቅርብ የሚያውቀውንና የሰማውን ለጽሑፍ በሚያመች መልኩ በመንገር፣ እንዲሁም የብፁዓን አባቶችን ፎቶ ግራፎች በማፈላለግ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ስላደረገ



ከፍ ያለ ምስጋናዬን እቀርባለሁ። እግዚአብሔር ዕድሜውን አርዝሞ የምንጠቀምበት ያድርግልን። እንደዚሁም በአባቶች ሕይወት ዙሪያ የጠየኳቸውን ሁሉ በመመለስ ለተራዱኝ ሊቀ መዘምራን መልከ ጼዴቅ፣ ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ፣ መምህር ታዬ አብርሃም፣ ቀሲስ ጌታቸው ደጀኔ፣ መምህር ዓሥራት ደስታ፣ አቶ አብርሃ ገ/ሕይወት፣ አቶ ገ/መስቀል ዲሜጥሮስ የቤተ ክርስቲያን አምላክ ዋጋቸውን ይክፈልልኝ እላለሁ። የመጽሐፉን ረቂቅ በኮምፒዩተር በመጻፍ የተባበሩኝ ወ/ት ርብቃ ኃ/ማርያም፣ ወ/ት ጽዮንና በተለይ በመጀመሪያዎቹ ወራት ረቂቁን በማረም እብሮኝ የደከመው አቶ አሱላ ጥላሁን ውለታቸውን አልረሳውም።

የዚህ መጽሐፍ ጥንካሬ መሠረቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ በሚገባ ታርሞና ተስተካክሎ መፈቀዱ ነው። የጉባኤው አባላት አባቶቼ መጽሐፉን በማረም ከጠቀሙኝ ባልተናነሰ በሚያርሙባቸው ጊዜያት አልፎ አልፎ በመካከላቸው በመገኘት የማስተዋልን፣ ያለመሰልቸትንና በአንድ ጉዳይ ላይ በቂ ጊዜ ሰጥቶ በመወያየት የተሻለውን የመያዝን አስፈላጊነት በሚገባ ተምሬያለሁ። የሊቃውንት ጉባኤ አባላት አባቶቼ ላደረጉልኝ ትብብር ሁሉ አመሰግናቸዋለሁ። ሌሎች ወንድሞቼም እንደኔ ቢጠቀሙባቸው መልካም ነው እላለሁ።

የመጽሐፉ ዝግጅት ከተጠናቀቀ በኋላ ከእያንዳንዱ አባት የሕይወት ታሪክ ጋር ፎቶ ግራፍ ለማውጣት እንድችል በጠየኩት ጊዜ ሁሉ ከጎኔ ሆኖ ለተባበረኝ ወንድሜ አቶ ሙሉጌታ በቀለ አምላክ እበው ዋጋውን ይክፈለው።

በመጨረሻም በተለመደው ደገኛ ተግባሯ ሥራው ከተጀመረ አንሥቶ ከጎኔ ሳትለይ ስታበረታታኝ የነበረችዋን ባለቤቴን ወ/ሮ ሉሊት መኰንንን በእጅጉ ላመስግናት እወዳለሁ።

ከላይ በጠቀስኳቸው አባቶቼ፣ ወንድሞቼና እኅቶቼ ጥረት የመጨረሻው ምዕራፍ የደረሰው የዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ሩቅ ሀገር ባለው ወንድሜ ወልደ ትንሣኤ /በትውልዱ ኢትዮጵያዊ አይደለም/ የገንዘብ ድጋፍ ለኅትመት ባይበቃ ኖሮ እኔም ለማመስገን ፤ እነሱም ለመመስገን ባልበቁ ነበር። ከአንድ እብራክ የወጡ ወንድማማቾች ሊረዱዱ በተቸገሩበት በዚህ ወቅት በጥቂት ቀናት ትውውቅ ምኞቴን ተረድቶ በፍጹም ፈቃደኝነት የመጽሐፉን የኅትመት ወጭ በመሸፈን ከእኔ አልፎ ቤተ ክርስቲያናችንን የረዳውን ይህንን ወንድሜን በእጅጉ አመስግነዋለሁ። እግዚአብሔር ከውጭ ወደ ቤቱ እንዳስገባው በቤቱ አቆይቶ ለመንግሥቱ ያብቃው።

ዲ/ን መርሻ አለኸኝ

www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ

የአዘጋጁ ማስታወሻ ........................................................ 11

ቅድመ ምዕራፍ

አባ ሰላማ «ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዘኵሉ ኢትዮጵያ»... 14

ምዕራፍ አንድ

1.ማዕዶተ ጵጵስና ........................................................ 19

ምዕራፍ ሁለት

2. ዜና ፓትርያርኮች ........................................................ 41
- 2.1. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ /1884 - 1963 ዓ.ም./ ...... 41
- 2.2. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ካልአይ ፓትርያርክ /1902 - 1971 ዓ.ም./........ 50
- 2.3. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሣልሳይ ፓትርያርክ /1910 - 1980 ዓ.ም./....... 61

ምዕራፍ ሦስት

3. ዜና ጳጳሳት
- 3.1. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቀዳማዊ /1875 - 1928 ዓ.ም/.................................... 72
- 3.2 ብፁዕ አቡነ አብርሃም ቀዳማዊ /1861 - 1931 ዓ.ም/ .................................. 81
- 3.3. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ቀዳማዊ /? - 1929 ዓ.ም/ ............................................ 87
- 3.4. ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ቀዳማዊ /1871 - 1947 ዓ.ም/ .................................... 94
- 3.5. ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ቀዳማዊ /1868 - 1925 ዓ.ም/........................................ 100
- 3.6 ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ቀዳማዊ /1875 - 1948 ዓ.ም/ .................................... 104
- 3.7. ብፁዕ አቡነ ሰላማ ቀዳማዊ /1865 - 1935 ዓ.ም/........................................ 109
- 3.8. ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ቀዳማዊ /1862 - 1939 ዓ.ም/.................................... 112

ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን

- 3.9. ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ቀዳማይ /1837 - 1940/............................................... 115
- 3.10. ብፁዕ አቡነ ማትያስ ቀዳማይ /1860 - ?/................................................ 118
- 3.11. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ቀዳማይ /1878 - ? /.................................................. 121
- 3.12. ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ቀዳማይ /1888 - 1980 ዓ.ም/...................................... 127
- 3.13. ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ቀዳማይ /1889 - 1970 ዓ.ም/...................................... 132
- 3.14. ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ቀዳማይ /1888 - 1957 ዓ.ም/...................................... 136
- 3.15. ብፁዕ አቡነ ማርቆስ ቀዳማይ /1889 - 1971 ዓ.ም/ ...................................... 139
- 3.16. ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ቀዳማይ /1882 - 1958 ዓ.ም/ .................................... 144
- 3.17. ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ቀዳማይ /1872 - 1958 ዓ.ም/ .................................. 148
- 3.18. ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ቀዳማይ /1888 - 1974ዓ.ም/ ...................................... 152
- 3.19. ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ካልአይ /1900 - 1900 ዓ.ም/........................................ 158
- 3.20. ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ካልአይ /1885 - 1959 ዓ.ም/ ...................................... 165
- 3.21. ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ካልአይ /18887 - 1983 ዓ.ም/ .................................... 168
- 3.22. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ካልአይ /1901 - 1961 ዓ.ም/ ...................................... 176
- 3.23. ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ ቀዳማይ /1888 - 1968 ዓ.ም/.................................. 183

www.ethiopianorthodox.org

3.24. ብፁዕ አቡነ ሰላማ ካልአይ
/1898 - 1970 ዓ.ም/ .................................. 186
3.25. ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ቀዳማይ
/1892 - 1979 ዓ.ም/ .................................. 190
3.26. ብፁዕ አቡነ አብርሃም ካልአይ
/1905 - 1995 ዓ.ም/ .................................. 195
3.27. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ሣልሳይ
/1903 - 1995 ዓ.ም/ .................................. 199
3.28. ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ቀዳማይ
/1911 - 1991 ዓ.ም/ .................................. 204
3.29. ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ቀዳማይ
/1878 - 1953/ .......................................... 209
3.30. ብፁዕ አቡነ እንድርያስ ቀዳማይ
/1906 - 1987 ዓ.ም/ .................................. 212
3.31. ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ሣልሳይ
/1904 - 1991 ዓ.ም/ .................................. 219
3.32. ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ቀዳማይ
/1924 - 1967 ዓ.ም/ .................................. 223
3.33. ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ካልአይ
/1896 - 1975 ዓ.ም / .................................. 226
3.34. ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ካልአይ
/1919 - 1996 ዓ.ም/.................................... 229
3.35. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ሣልሳይ
/1921 - 1993 ዓ.ም/ .................................. 235
3.36. ብፁዕ አቡነ ሰላማ ሣልሳይ
/1931 - 1996 ዓ.ም/ .................................. 239
3.37. ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልአይ
/1932 - 1982 ዓ.ም/ .................................. 245
3.38. ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ካልአይ
/1922 - 1993 ዓ.ም/.................................... 251
3.39. ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ካልአይ
/1921 - 1981 ዓ.ም/.................................... 256



3.40. ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ካልአይ
/1920 - 1981 ዓ.ም/ .................................. 260
3.41. ብፁዕ አቡነ በርናባስ ቀዳማዊ
/1917 - 1980 ዓ.ም/ .................................. 264
3.42. ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ቀዳማይ
/1911 - 1989 ዓ.ም/.................................... 268
3.43. ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ
/1917 - 1996 ዓ.ም/ .................................. 272
3.44. ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት
/1938 - 1983 ዓ.ም/ .................................. 275
3.45. ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ሣልሳይ
/1903 - 1995 ዓ.ም/ .................................. 278
3.46. ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ሣልሳይ
/1936 - 1990 ዓ.ም/ .................................. 281
3.47. ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ካልአይ
/1938 - 1991 ዓ.ም/ .................................. 285
3.48. ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ቀዳማይ
/1933 - 1991 ዓ.ም/.................................... 288
3.49. ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ካልአይ
/1932 - 1992 ዓ.ም/.................................... 292
3.50. ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ሣልሳይ
/1937 - 1995 ዓ.ም/.................................... 295
ምዕራፍ አራት
4. አባሪ .......................................................... 299

www.ethiopianorthodox.org

# የአዘጋጁ ማስታወሻ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ተሹሞ ከመጣው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ አባ ሰላማ ጀምሮ ለ 1600 ዓመታት ከግብፅ ተቀብተው በሚመጡ ግብፃ ውያን ጳጳሳት እና ሊቃነ ጳጳሳት ስትመራ ቆይታለች። ይሁን እንጂ በ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በንጉሥ ሐርቤ ገብረ ማርያም /1117 - 1157 ዓ.ም/ የተጀመረውና ቤተ ክርስቲያኗ በዕውቀት ከአብራኳ በሚገኙ ልጆቿ ትመራ የሚለው ክርክር ከዘጠኝ መቶ ዓመታት በኋላ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውጤት አግኝቶ ግንቦት 21 ቀን 1921 ዓ.ም የመጀመሪያዎቹ አራት ኢትዮጵያውያን አበው ሊቃውንት መዓርገ ጵጵስናን ለማግኘት ቻሉ። ምንም እንኳን በኢትዮጵያ በኩል ጥረቱ ቀላል የሚባል ባይሆንም ከዓመታት በኋላ ደግሞ ጥር 6 ቀን 1942 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሊቀ ጵጵስናውንም መንበር ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ተረክባ የራሷን ልጅ አስቀመጠች። በመጨረሻም የተቀዳጀችው ነጻነት ፍጹም ሊሆን ሰኔ 21 ቀን 1951 ዓ.ም የራሷን መንበረ ፓትርያርክ አደላድላ የምታውቀውንና የሚያውቃትን ልጇን ሠየመች።

መጽሐፍ ቅዱሳዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያን የዘመናት ትግሏ ውጤታማ ሆኖ የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያ ውያን አባቶች ጳጳሳት ተብለው ከተሾሙበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት ይበቃሉ ያለቻቸውን አበው እየመረጠች በመሾም ወንጌልን የመስበክ ደገኛ ተግባሯን ስትወጣ ቆይታለች። አሁንም በብቃት በመወጣት ላይ ትገኛለች። ወደ ፊትም ትቀጥላለች።

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ቤተ ክርስቲያናችን ራሷን በራሷ የማስተዳደር ነጻነት ከተቀዳጀችበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት በጵጵስናና ሊቀ ጵጵስና ከዚያም ከፍ ባለ በፓትርያርክነት ተሹመው፣ አስቀድሞ የመረጣቸው አምላክ የፈቀደላቸውን ዕድሜ ያህል አገልግ ሎታቸውን በትጋት ሰጥተው ሐዋርያው «መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ ፥ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል» /2 ጢሞ 4 ፥ 7-8/ ባለው መሠረት መልካሙን ገድል ተጋድለው ያለፉትን ጳጳሳት፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ፓትርያርኮች ዜና ሕይወት ማዘከር ነው። በሌላው ዓለም እንኳን ብፁዓን ተብለው በከፍተኛ መንፈሳዊ መንበር በመቀመጥ ሲያገ ለግሉ የቆዩ አባቶች ቀርቶ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ በሚያመዝን ሙያ ተሠማርተው ያለፉ ሰዎች የሕይወት ታሪክ በጥንቃቄና በትጋት በሚጻ ፍበት በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያናችን በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ተሠማርተው ያለፉ ልጆቿን ዜና ሕይወት ጽፎ በማቆየቱ ረገድ ገድል

www.ethiopianorthodox.org

በተሰኘው ነባር የሥነ ጽሑፍ ሀብቷ የጻፈችላቸው ቅዱሳን ልጆቿ እንዳሉ ሆነው ብዙ የተራመደች አትመስልም።

ምንም እንኳን የሁሉም ተመዝግቦ ይገኛል ባይባልም፣ በአባቶች የሕይወት ታሪክ ዙሪያ በሚያርፉበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያኗ ልሳናት በሆኑ የኅትመት ውጤቶችና የዓርብ ቀን መታሰቢያቸውን በማስመልከት በሚዘጋጁ መጽሔቶችና በራሪ ጽሑፎች ላይ የአንዳንድ አባቶች ዜና ሕይወት በአጭር በአጭሩ ተዘግቦ ይገኛል። እነዚህ መዛግብት በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ወቅት በምንጭነት ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ አበርክተዋል። ለዚህም ጊዜው በሚጠይቀው መሠረት ግልጋሎት ላይ የዋሉት መዛግብት በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ተዘርዝረዋል። ይሁን እንጂ የዚህ መጽሐፍ ዓላማ በተበታተነ ሁኔታ በኅትመቶቹ ከተሠሩት ሰፋ ያለና ዝግጅቱም በመጽሐፍ መልክ እንደ መሆኑ በጋዜጦቹና በመጽሔቶቹ ከተገለጠው የበለጠ በርካታ መረጃዎች እንዲካተቱበት ሆኗል። ይኸውም ከተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት፣ የአባቶች የቅርብ ዘመዶችና ለቤተ ክርስቲያኗ ቅርበት ካላቸው ምሁራን ጋር ከተደረጉ ውይይቶች እንዲሁም ከበርካታ ሰነዶች የተገኙ መረጃዎች በመጽሐፉ እንዲካተቱ በመደረጉ ነው። በዓላማም ረገድ ይህ መጽሐፍ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አገልግለው ያለፉ ብፁዓን አባቶችን ዜና ሕይወት ከማስተዋወቅ ባለፈ በቤተ ክርስቲያኗ የጽጽስና ታሪክ ከየት ተነሥቶ የት እንደ ደረሰ፣ ቤተ ክርስቲያኗ ለረጅም ዘመናት ተነፍጓት የቆየውን ራሷን በራሷ ልጆች የማስተዳደር መብት እንድትጎናጸፍ የተደረጉ ትግሎች፣ በዚህ ረገድ ተመዝግበው የሚገኙ መዛግብት፣ መብቷን ከተጎናጸፈች በኋላም በዚሁ በጽጽስና ሹመት ዙሪያ የተከሰቱ አንዳንድ ውጫዊና ውስጣዊ ችግሮች፣ የተወሰዱ የመፍትሔ ርምጃዎች እና የመሳሰሉትን ታሪካዊ እውነታዎች በማቅረብ ዘርፉን በሚመለከት በኢትዮጵያና ቤተ ክርስቲያኗ ታሪክ ጥናት ለተሰማሩ ምሁራን መጠነኛ መረጃ ይሰጣል ተብሎ ታስቧል።

ከመጽሐፉ ርእስ ለመረዳት እንደ ሚቻለው ይህ መጽሐፍ የርእስ ጉዳዩ የመጀመሪያ ክፍል ነው። ቀጣዩ ክፍል አሁን በጸሎታቸው፣ በቡራኬያቸውና በትምህርታቸው እየገለገሉን ያሉ አባቶቻችን ዜና ሕይወት ነው። ምንም እንኳን እኔ እንዲህ ነኝ ብሎ ስለ ራስ ደግ ደጉን መተረክ አባቶቻችን የሚሹት ባይሆንም ሁለተኛው ክፍል ከዚህ በተሻለ ሁኔታ ሰፋ ያለና መረጃ ጠገብ እንደ ሚሆን ተስፋ አለኝ። ያድርስን። የአባቶቻችን አምላክ እንደ ፈቀደ ይህን የመጀመሪያ ክፍልም ሆነ ወደ ፊት ይታተማል ብዬ የማስበውን ሁለተኛውን ክፍል ወደ እንግሊዝኛ ተርጓሚ ምዕራባውያን ስለ አባቶቻችን እንዲያነቡ አደርጋለሁ የሚል ተስፋ አለኝ።



መጽሐፉ አራት ምዕራፎች አሉት። የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከግብፅ ተሹመው በሚመጡ ግብፃውያን አባቶች መመራቷ አቁሞ ከራሷ ሊቃውንት በተሾሙ አባቶች እንድትመራ፣ ምእመናኗም ቋንቋዋን፣ ትምህርቷንና ባሕሏን በሚገባ በሚያውቁ ሊቃውንት እንዲማሩ ከ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተለያዩ ነገሥታት ያደረጉትን ጥረትና በመጨረሻም እንዴት ሙሉ በሙሉ ነጻነቷን እንደ ተቀዳጀች የቀረበበት ምዕራፍ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በተከታታይ በፓትርያርክነት ተሹመው በመልካም አስተዳደራቸው ቤተ ክርስቲያኗን አገልግለው ያረፉ ሦስት ቅዱሳን አባቶች ዜና ሕይወት የቀረበበት ነው። ሦስተኛው የመጽሐፉ ምዕራፍ ግንቦት 1 ቀን 1921 ዓ.ም ከተሾሙት አራት ብፁዓን አባቶች ጀምሮ በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት እስከ ተለዩት ብፁዕ አቡነ ሰላማ ድረስ ቤተ ክርስቲያናቸውን አገልግለው ያለፉትን 50 ብፁዓን አባቶች ዜና ሕይወት የቀረበበት ነው። በዚህ ምዕራፍ ፋሺስት ኢጣልያ ሕዝቡን የያዙ መስሎት «ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ጳጳሳት መሾም ይችላሉ ብሎ» በዋጀ ባስነገረ ጊዜ ከየክፍሉ በተሰባሰቡ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ምርጫ፣ በነበሩት አባቶች የተሾሙትን አንዳንድ አባቶች የሕይወት ታሪክም ለማካተት ተሞክሯል። የእነዚህ አባቶች ዜና ሕይወት የተካተተበት ምክንያት ነጻነት ከተመለሰ በኋላ ምንም እንኳን በተለይ ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጋር የነበረውን ግንኙነት ላለማበላሸት ለጊዜው ከአገልግሎት ታግደው ቢቆዩም ወደ ኋላ ብዙዎቹ ሥልጣናቸው ስለተመለሰላቸውና የመጽሐፉ አዘጋጅ በባልያን ጊዜ የነበረው ሹመት ትክክለኛ ወይም ቀኖናዊ ነበር ብሎ ስለሚያምን ነው። ታሪካቸው ያልተካተተላቸው አባቶች የቀሩት ምንጭ ስለጠፋ ነው። የብፁዓን አባቶች ዜና ሕይወት በዚህ መጽሐፍ የቀረበው በተሾሙበት ዘመን ቅደም ተከተል ነው።

ሁለት ዓመታት በወሰደው የመጽሐፉ ዝግጅት ወቅት የተገኙት መረጃዎች ተቀናብረው ይህ መጽሐፍ ለዚህ ቢበቃም በሐዲት ሊገኙ ያልቻሉ መረጃዎች ሊኖሩ እንደ ሚችሉ አይጠረጠርም። በመሆኑም የመጽሐፉ አንባቢዎች ያልተካተቱ የሚሏቸው መረጃዎች ካሉ ቢልኩልኝ ወደ ፊት መጽሐፉ እንደ ገና ሲታተም ለማካተት ይሞከራል። ይህ ይሆን ዘንድ በመጽሐፉ ዜና ሕይወታቸውን ላዘከርላቸው የሞከርኳቸውን ብፁዓን አበው በቅርብ የሚያውቁና በሕይወታቸው ዙሪያ የተጻፉ መረጃዎች ያሏቸው አንባብያን በመጽሐፉ መጀመሪያ በተገለጠው አድራሻ እንዲልኩልኝ ከአክብሮት ጋራ እጠይቃለሁ።

አዘጋጁ

www.ethiopianorthodox.org

# ቅድመ ምዕራፍ

## አባ ሰላማ

## «ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዘኵላ ኢትዮጵያ»

ሀገራችን ኢትዮጵያ ምንም እንኳን ክርስትናን የተቀበለችው ባኮስ /አቤላክ/ በተባለው የኢትዮጵያ ንግሥት የህንደኬ በጅሮንድ አማካኝነት በ1ኛው መ.ክ.ዘ ቢሆንም እስከ 4ኛው መ.ክ.ዘ. ድረስ የኤጲስ ቆጶስነት መንበር አላገኘችም ነበር:: ከ4ኛው መ.ክ.ዘ. አጋማሽ እስከ 5ኛው መ.ክ.ዘ. መጀመሪያ ድረስ የኖረው ሩፊኖስ የተባለ የቤተ ክርስቲያን የታሪክ ጸሐፊ ይህንን ታሪክ እንደ ሚከተለው ዘግቧል::

ሜሮጵዮስ የተባለ አንድ ጢሮሳዊ ክርስቲያን ነጋዴ /ፈላስፋም ነበረ የሚሉ አሉ/ ፍሬምናጦስና ኢዴስዮስ የተባሉ ዘመዶቹን በማስከተል ከሀገሩ ተነሥቶ ወደ ሕንድ አቅጣጫ በጀልባ ጉዞውን ጀመረ:: በጉዞውም ወደ አፍሪካ የባሕር ጠረፍ በመምጣት በቀይ ባሕር ወደብ ውኃ ለመጠጣትና እግረ መንገዱንም ሀገር ለማየት ጀልባውን ጠረፍ ላይ አቆመ:: ነገር ግን እሱ እንዳሰበው ሳይሆን በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ ሰዎች በጀልባቸው ላይ አደጋ ጥለው እራሱንና የጀልባዋን ቀዛፊዎች እዚያው ገድለው ሀብታቸውን ዘረፏቸው::

ባላሰቡት ሁኔታ ከሜሮጵዮስ የተለዩት ወጣቶቹ ወንድማማቾች ፍሬምናጦስና ኢዴስዮስ ቋንቋውንና ባሕሉን በማያውቁት ሀገር ብቻቸውን በመቅረታቸው እያዘኑና እያለቀሱ ከዛፍ ሥር ተቀምጠው ይጸልዩ ጀመር:: እነዚህን ወጣቶች በማየታቸው የተገረሙት መንገደኞች ከዚህ ቦታ አንሥተው በወቅቱ የአክሱም ንጉሥ ለነበረው ታዜር «ይኸውና ምርኮ አመጣንልህ» በማለት አስረከቧቸው::

ንጉሡም ወጣቶቹ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ያድጉ ዘንድ ፈቃዱ ሆነና ከልጆቹ አብርሃና አጽብሐ ጋር አንድ ላይ ማደግ ጀመሩ:: ከዓመታት በኋላ በአእምሮ መብሰላቸውን በጥበብም ማደጋቸውን የተመለከተው ንጉሥ ታዜር ፍሬምናጦስን በጅሮንድ ኢዴስዮስን ደግሞ ጋሻ ጃግሬው አድርጎ ሾማቸው:: ወጣቶቹም ሹመቱን በመቀበል በቤተ መንግሥቱ በማገልገል ላይ እንዳሉ



ንጉሡ ሀረፈ:: በዚህ ጊዜ ግሪካውያኑ ወጣቶች ነፃ ወጣን በማለት ወደ ሀገራቸው ሊሔዱ ተነሡ:: ነገር ግን መንግሥቱን በሞግዚትነት የተረከበችው ንግሥት አሕየዋ /ሶፊያ/ ልጆቿ ኢዛናና ሳይዛና /በኋላ አብርሃና አጽብሐ/ አድገው ዙፋኑን እስኪረከቡዋት ድረስ በአስተዳደር እንዲረዱዋት ለመኗቸው:: እነሱም ጥያቄዋን ተቀብለው ጉዞዋቸውን በመተው በዚያው በቤተ መንግሥቱ በአማካሪነት ሲያገለግሉዋት ቆዩ::

ከዓመታት በኋላ ታናሽ ወንድሙ ወደ ሀገሩ በመሔዱ ብቻውን የቀረው ፍሬምናጦስ ለክርስትና እምነቱ ቀናኢ ስለነበር አስቀድሞ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ተሰብኮ በአክሱምና አካባቢዋ የነበረው የክርስትና እምነት የሚስፋፋበትን መንገድ ዘወትር ያስብ ነበር:: ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ሃይማኖት ብቻ እንጂ ክህነት፣ ቁርባን ወዘተ. የመሳሰሉትን ምሥጢራት የሚፈጽምላቸው ካህናትን የሚሾምላቸው ኤጲስ ቆጶስ በለሌላቸው ያዝኑ እንደነበር ተመለከተ:: ይህን የሕዝቡን ሐዘን ለማቆምም የበኩሉን ጥረት ለማድረግ ወስኖ ጉዳዩን የአባታቸውን መንግሥት ለተረከቡት አብርሃና አጽብሐ ማስረዳቱን ቀጠለ::

ነገሥታቱም ጉዳዩን ሙሉ በሙሉ በመቀበል ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ሲያሰላስሉ በፍሬምናጦስ ምክር ከአንድ ውሳኔ ላይ ይደርሳሉ:: እነሱም ፍሬምናጦስን የእኛን ቋንቋና ባህል የእነሱንም ቋንቋና ባህል ከአንተ ሌላ የሚያውቅ የለምና አንተ ወደ እስክንድርያ ሄደኽ ክህነትንና ቁርባንን አምጣልን ብለው እሱን ወደ እስክንድርያ ሰደዱት:: ፍሬምናጦስ ወደ እስክንድርያ የተላከው እንደ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ነው እንጂ፣ ትውልድ ሀገሩን ወክሎ እንዳልተላከ መገንዘብ ይገባል::

ፍሬምናጦስ እስክንድርያ የደረሰው እለ እስክንድሮስ አትናቴዎስን አስከትሎ በጉባኤ ኒቅያ ለመካፈል በሔደበት ወቅት ነበረና እስኪመለሱ ድረስ በዚያው ትምህርተ ቤተ ክርስቲያንን እየተማረ በትዕግስት መጠበቅ ግድ ሆነበት::

እለ እስክንድሮስ በጉባዔ ኒቅያ በአትናቴዎስ አፈ ጉባዔነት አርዮስን ረትቶ ከተመለሰ በኋላ ወዲያው ስላረፈ በመንበሩ አትናቴዎስ ተተካ:: ፍሬምናጦስም የተላከበትን ህቢይ ጉዳይ ለሐዋርያዊው ቅዱስ አትናቴዎስ አቀረበ:: አትናቴዎስ ስለ ኢትዮጵያውያን ሃይማኖት በሚገባ ከተረዳ በኋላ ለፍሬምናጦስ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አስተምሮ «ኤጲስ ቆጶስ ዘአክሱም ወዘኵላ ኢትዮጵያ» ብሎ በትብዓትና በአንብሮተ እድ ሹሞ ላከው::ፍሬምናጦስ ጵጵስናውን ተቀብሎ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰ በኋላ:-

www.ethiopianorthodox.org

- የወንጌልን ትምህርት በስፋት ለሕዝቡ የሚያዳርሱ፣ የሚያጠምቁና የሚያቁርቡ ካህናትንና ዲያቆናትን ሾመ።
- በአብርሃ አጽብሐ አማካኝነት አያሌ አብያተ ክርስቲያናትን አሳነፀ።
- በዘመኑ የኢትዮጵያ ግዛት ወደ ነበሩት ኑብያ፣ አኑኖ እና መርዌ አምስት ቆምሳትን በመላክ ትምህርተ ወንጌል እንዲሰበክ፣ ቤተ ክርስቲያን እንድትስፋፋ አደረገ።
- ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሱርስት፣ ከዕብራይስጥና ከግሪክ ወደ ግእዝ እንዲተረጎሙ አደረገ።
- የሳባውያንን የፊደል አቀማመጥ በመለወጥ ከግራ ወደ ቀኝ የመጻፍንና የማንበብን ዘዴ ያስተማረው እርሱ ነው።

በዚህም መሠረት ክርስትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖ በ350 ዓ.ም እንዲታወጅ አድርጓል። ኢትዮጵያውያን ይህንን ታላቅ አባት በሃይማኖቱና በምግባሩ ስለወደዱት «አቡነ» /አባታችን/ የሚለውን መዓርግ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰጡት ለእርሱ ነው። በብርሃናዊ ሥራውም «ከሣቴ ብርሃን» /ብርሃን ገላጭ/ ብለውታል።

አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የተባለው ፍሬምናጦስ በኢትዮጵያ ክርስትና እንዲስፋፋ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ በመውጣትና በመውረድ የሚገባውን ሁሉ ከፈጸመ በኋላ ሐምሌ 26 ቀን ዐረፈ።

ይህ ታላቅ አባት የኢትዮጵያውያን ባለውለታ፣ የወንጌልን ፋና ይበልጥ እንዲበራ ያደረገ፣ መንበረ ጵጵስናን ያስገኘልን፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ለኢትዮጵያውያን የወጠነልን እና አያሌ አብያተ ክርስቲያናትን ያስተከለልን ነውና ዘወትር ልናስበው በዓሉንም ልናከብርለት ይገባናል።

ይህ ቅዱስ አባት ቤተ ክርስቲያኑ በሚገኝበት ትግራይ ውስጥ በተንቤን እንዳባ ሰላማ ባንዳንድ ቦታዎች ካልሆነ በቀር በአብዛኛው የሀገራችን ክፍል ዓመታዊ ክብረ በዓሉ እምብዛም ትኩረት አይሰጠውም።

ኤፍ.ጂ. ሆልዊክ የተሰኘ ጸሐፊ እንደ ገለጠው በጥንታዊቷ ሉዩሲያና /Louisiana/ /በዩናይትድ ስቴት ግዛት/ በ1787 ዓ.ም እ.ኤ.አ. የአካባቢው ሰዎች በከፍተኛ ድምቀት የቅዱስ ፍሬምና ጦስን በዓል ሲያከብሩ መመለከቱንና እነርሱም ከዚህ ከአፍሪካ በባርነት የሄዱ ጥቁሮች መሆናቸውን ማረጋገጡን ጽፎ ነበር።



አባ ሰላማ የሮማ ቤተ ክርስቲያን በኦክቶበር 27፣ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በኖቬምበር 30 በዓሉን ሲያከብሩለት የሾመችውና የላከችው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ግን ፈጽማ ከበዓላት ቀኖናዋ አውጥታዋለች። አቡነ ሰላማ የቀደሰበት በግሪክ ቋንቋ የተጻፈ ቅዳሴና የባረከበት የእጅ መስቀሉ ዛሬም በተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። የብፁዕ አባታችን ረድኤት አይለየን። አሜን።

በ4ኛው መ.ክ.ዘ. በቅዱስ ፍሬምናጦስ የተጀመረው የአስከንድሪያ ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶሳትን ሾሞ ወደ ኢትዮጵያ የመላክ ሥልጣን እስከ 20ኛው መ.ክ.ዘ. ቆይቶ 119 የሚሆኑ ግብፃውያን አባቶች ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ በሊቀ ጵጵስና ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ከቅዱስ ፍሬምናጦስ /አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን/ በኋላ ሥልጣኑን ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያውያን እስከ ሚረከቡ ድረስ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን እየተሾሙ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በሊቀ ጳጳስነት ያገለገሉ ግብፃውያን አባቶች በም ዝርዝር የሚከተለው ነው።

1. አቡነ ሚናስ
2. አቡነ ጴጥሮስ
3. አቡነ ማቴዎስ
4. አቡነ ማርቆስ
5. አቡነ ዮሐንስ
6. አቡነ ገብርኤል
7. አቡነ ዮሐንስ 2ኛ
8. አቡነ ገብርኤል
9. አቡነ ሚናስ 2ኛ
10. አቡነ ሚካኤል
11. አቡነ ይስሐቅ
12. አቡነ ስምዖን
13. አቡነ ጴጥሮስ 2ኛ
14. አቡነ ሚካኤል 2ኛ
15. አቡነ ገብርኤል 3ኛ
16. አቡነ ዮሐንስ 3ኛ
17. አቡነ ሚካኤል 3ኛ
18. አቡነ ሚካኤል 4ኛ
19. አቡነ ስምዖን 2ኛ
20. አቡነ ዮንሐንስ 4ኛ
21. አቡነ ማርቆስ 2ኛ
22. አቡነ አብርሃም
23. አቡነ ቄርሎስ
24. አቡነ ዮሐንስ 5ኛ
25. አቡነ ሚካኤል 5ኛ
26. አቡነ ስምዖን 3ኛ
27. አቡነ ጴጥሮስ 3ኛ
28. አቡነ ማቴዎስ 2ኛ
29. አቡነ ያዕቆብ
30. አቡነ ፊቅጦር
31. አቡነ ቄርሎስ 2ኛ
32. አቡነ ቆዝሞስ
33. አቡነ ዮስጦስ
34. አቡነ ሚካኤል 6ኛ
35. አቡነ ገብርኤል 4ኛ
36. አቡነ ሚካኤል 7ኛ
37. አቡነ ማቴዎስ 3ኛ
38. አቡነ ዮሳብ
39. አቡነ ዮሴፍ
40. አቡነ ቆዝሞስ 2ኛ

www.ethiopianorthodox.org

41. አቡነ ፊላታዎስ
42. አቡነ ጴጥሮስ 4ኛ
43. አቡነ ዮሐንስ 6ኛ
44. አቡነ ፊቅጦር 2ኛ
45. አቡነ ዮስጦስ 2ኛ
46. አቡነ በርምያ
47. አቡነ ሚካኤል 8ኛ
48. አቡነ ገብርኤል 5ኛ
49. አቡነ ሚናስ 3ኛ
50. አቡነ ዮሐንስ 7ኛ
51. አቡነ ዮሐንስ 8ኛ
52. አቡነ አብርሃም 2ኛ
53. አቡነ ማርቆስ 3ኛ
54. አቡነ መቃርስ
55. አቡነ ሚካኤል 9ኛ
56. አቡነ ማቴዎስ 4ኛ
57. አቡነ ሚካኤል 10ኛ
58. አቡነ ገብርኤል 6ኛ
59. አቡነ ዮሐንስ 9ኛ
60. አቡነ ቄርሎስ 3ኛ
61. አቡነ ሚናስ 4ኛ
62. አቡነ ማቴዎስ 5ኛ
63. አቡነ ሚካኤል 11ኛ
64. አቡነ ገብርኤል 7ኛ
65. አቡነ ማርቆስ 4ኛ
66. አቡነ ገብርኤል 8ኛ
67. አቡነ ማቴዎስ 6ኛ
68. አቡነ ዮሐንስ 10ኛ
69. አቡነ ሚናስ 5ኛ
70. አቡነ ማርቆስ 5ኛ
71. አቡነ ክርስቶዶሉ
72. አቡነ ዘካርያስ
73. አቡነ ፊላታዎስ 2ኛ
74. አቡነ ሰንትዮስ
75. አቡነ ገብርኤል 9ኛ
76. አቡነ ዮሐንስ 11ኛ
77. አቡነ ሚካኤል 12ኛ
78. አቡነ ገብርኤል 10ኛ
79. አቡነ በርተሎሜዎስ
80. አቡነ ማቴዎስ 7ኛ
81. አቡነ ዮሐንስ 12ኛ
82. አቡነ ማርቆስ 6ኛ
83. አቡነ ይስሐቅ 2ኛ
84. አቡነ ክላድያኑ
85. አቡነ ጴጥሮስ 5ኛ
86. አቡነ ማቴዎስ 5ኛ
87. አቡነ ስምዖን 4ኛ
88. አቡነ ዮሳብ 2ኛ
89. አቡነ ሚካኤል 13ኛ
90. አቡነ ማቴዎስ 9ኛ
91. አቡነ ማርቆስ 7ኛ
92. አቡነ ጴጥሮስ 6ኛ
93. አቡነ ስምዖን 5ኛ
94. አቡነ ማርቆስ 8ኛ
95. አቡነ ሚካኤል 14ኛ
96. አቡነ ዮሐንስ 13ኛ
97. አቡነ ክርስቶዶሉ 2ኛ
98. አቡነ ሲኖዳ
99. አቡነ ማርቆስ 9ኛ
100. አቡነ ክርስቶዶሉ 3ኛ
101. አቡነ ዮሐንስ 14ኛ
102. አቡነ ዮሳብ 3ኛ
103. አቡነ መቅርዮስ 2ኛ
104. አቡነ ቄርሎስ 4ኛ
105. አቡነ ሰላማ 2ኛ
106. አቡነ አትናቴዎስ
107. አቡነ ጴጥሮስ 7ኛ
108. አቡነ ማቴዎስ 10ኛ
109. አቡነ ቄርሎስ 5ኛ



# ምዕራፍ አንድ

## ማዕዶተ ጵጵስና[1]

*መሰብለ ኢትዮጵያ ኢይሢሙ ባዕሌሆሙ ሊቀ ጳጳሳተ እማእምራኒሆሙ፣ ወኢበሥምረተ ርእሰሙ:: እስመ ጳጳሰሙ ይከውን እምታሕተ እዴሁ ለበዓለ እስክንድርያ ወውእቱ ዘይደልዎ ይሢም ባዕሌሆሙ ሊቀ እምኀቤሁ፡ ዘውእቱ መትሕተ ሊቀ ጳጳሳት::*

*የኢትዮጵያ ሰዎች ከሀዋቂዎቻቸው ወገን፣ በራሳቸውም ፈቃድ ሊቀ ጳጳሳትን ለራሳቸው አይሹሙ:: ጳጳሳቸው ከእስክንድርያው በዓለ መንበር ሥልጣን በታች ነውና:: ከሊቀ ጳጳሳት በታች የሆነውን ሊቀ ጳጳስ ከእርሱ ወገን ሊሾምላቸው የሚገባውም እርሱ ነው::*

/ፍትሐ ነገሥት፣ አንቀጽ 4፣ ቁጥር 50/

አያሌ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና በቤተ ክርስቲያኗ ታሪክ ላይ ምርምር ያደረጉ ምሁራን ይህን የፍትሐ ነገሥት አንቀጽ «ቀኖና ማጥበቂያ አንቀጽ» እያሉ ይጠሩታል:: ሊቃውንቱ በተለይ የትርጓሜ መጻሕፍት መምህራን ምንም እንኳን አንቀጹ የተካተተበትን ታላቅ የሕግና የሥርዓት መጽሐፍ ተቀብለው በአንድምታ የትርጓሜ ጥበባቸው የረቀቀውን አጉልተው፣ የራቀውን አቅርበው በማመስጠር ቢያስተምሩትም ከተጠቀሰው አንቀጽ ላይ ሲደርሱ አንድም ብለው ሳይተረጉሙት ያልፉ ነበር:: ነገር ግን፤ ምንም እንኳን በሙሉ ልብ «ግብፃውያኑ በስርዋጽ ያስገቡት ተንኮል ያዘለ አንቀጽ ነው» ብለው በድፍረት ባይተቹትም፤ አልፎ አልፎ «ይህ እንኳን ስሕተት ይመስላል» እያሉ የአንቀጹን የግዮት «ቀኖና አጥባቂነት» ለደቀ መዛሙርታቸው ይገልጹ ነበር::

[1] ይህ ምዕራፍ የአሌክሳንድርያ ቤተ ክርስቲያን ለ1600 ዓመታት ያህል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ሹማ በምትልከው ሊቀ ጳጳስ አማካይነት ስታስተዳድርበት የነበረው አካሄድ አቁሞ በምትኩ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ክራሷ አብራክ በተከፈሉ፣ በምእመናኗ ቋንቋ በሚናገሩ ኢትዮጵያውያን አባቶች ትመራ ዘንድ የተደረገውን ትግልና ውጤት የሚያተርብ በመሆኑ ይህ ርዕስ ተሰጥቶታል::

www.ethiopianorthodox.org

ይህ ሲባል ግን የመጣውን ቅጣት ሁሉ ለመቀበል ቆርጠው እንቀጹን በመጥቀስ በድፍረት «ይህ እኛን ኢትዮጵያውያንን ለመግዛት፣ ሀብታችንንም ለማጋዝ ሲሉ በ7ኛው መ.ክ.ዘ. ግብፆች በፍትሐ ነገሥት ውስጥ እንዲካተት ያደረጉት አንቀጽ ነው» በማለት የተቃወሙ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አልነበሩም ለማለት አይጠ ደለም:: በየዘመኑ የተነሡ በጣም ጥቂት ቆራጥ ሊቃውንት ነበሩና:: ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ሊቃውንት በዘመኑ ቤተ ክርስቲያኗ ትመራ የነበረው በግብፃውያኑ አባቶች ስለ ነበር በግዝት አፋቸውን እንዲይዙ፣ ከዚያም ባለፈ ወንበራቸውን እንዲያጥፉ፣ ከምእመናንም እንዲለዩ ይደረጉ ነበር:: በዚህም የተነሣ በተጠቀሰው ዓይነት ጉዳዩ በጣም በተበታተነና በአነስ ሁኔታ በቤተ ክርስቲያኗ አንዳንድ ሊቃውንት ይነሣ ካልሆነ በስተቀር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደ አንዲት መንፈሳዊት ተቋም ጉዳዩን አንሥታ ተቃውሞዋን ሳታሰማ ቆይታለች::

ከዚህ በተሻለ ግን በሀገሪቷ ላይ በየጊዜው የነገሡ ነገሥታት የነበረውን ሒደት በመቃወም ድምፃቸውን ሲያሰሙ ቆይተዋል:: እንዳንድ የታሪክ መዛግብት እንደ ሚገልጹት የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ የሆነው ሶርያዊው አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን በግብፃውያኑ ተሹሞ ከመጣ ጀምሮ ጉዳዩን በመቃወም «ቁጥራቸው እጅግ ብዙ ለሆነው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በራሳቸው ቋንቋ ተዟዙረው የሚያስተምሯቸው ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳትና ጳጳሳት ያስፈልጓቸዋል» ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ ድምፁን ያሰማው የኢትዮጵያ ንጉሥ ቅዱስ ሐርቤ /1060 - 1077 ዓ.ም/ ነበር::

በ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነግሦ የነበረውና ከነገደ ዛጉዌ የሆነው ንጉሥ ሐርቤ የነገሠበት የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመን ቁጥር ብዙ፣ ሀገሩም ሰፊ እንደ ሆነ በማየት ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳትን ይሾምለት ዘንድ በወቅቱ ለነበረው ግብፃዊ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ /አባ ሚካኤል ይባል ነበር/ ጥያቄ አቀረበ:: ሊቀ ጳጳሱ ግን ፍላጎቱ እንደ ንጉሡ የሰብከተ ወንጌል ነገር ሳይሆን ሀገሪቱ በመንበረ ማርቆስ ሥር እንድትቆይ ማድረግ ስለ ነበር የንጉሡን ጥያቄ በእሺታ አልተቀበለም:: በምትኩ ጉዳዩን በግሉ ለመወሰንና ተግባራዊ ለማድረግ እንደ ማይችል ገልጦ ከፓትርያርኩ /ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ገብርኤል ይባሉ ነበር/ ጋር ልምክር በሚል ወደ ካይሮ ሔደ::

በወቅቱ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ላይ ተሹሞ የነበረው ፓትርያርክም የፍትሐ ነገሥቱን «ቀንበር ማጥበቂያ አንቀጽ» በመጥቀስ «ሦስት መቶ በሥራ ስምንቱ ሊቃውንት ኒቅያ ላይ ጉባኤ



ሠርተው ያሳለፉትን ውሳኔና ትእዛዝ መተላለፍ ነው» በሚል የንጉሡን ጥያቄ ሳይቀበል ቀረ:: ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያው ንጉሥ ጥያቄ አበው የደነገጉትን ሥርዓት የጣሰ በመሆኑ እምላከ አበው እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ላይ እንደ ተቆጣ አድርጎ መናገርና ማስነገር ጀመረ:: የንጉሡን ጥያቄ ለማፈን ያስወራውን አሉባልታም የእርሱ አባቶች ቀንበር ማጥበቂያውን አንቀጽ በፍትሐ ነገሥት ስርዋጽ ገብቶ እንዲጻፍ እንዳደረጉ ሁሉ፤ እርሱም በወቅቱ የነበረውን ሥልጣን ተጠቅሞ የቅዱሳንን ዜና ሕይወትና ተጋድሎ ዘግቦ በያዘው ስንክሳር መጽሐፍ ላይ በስርዋጽ ገብቶ እንዲጻፍ አድርጓል:: የአሉባልታው ታሪክም እንደ ሚከተለው ይነበባል:-

.. .. ..

*ደግሞ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ማን እንደ ጻፈው ያልታወቀ ጽሑፍ እናገኛለን:: እንዲህም ይላል:: በዚህ አባት በአባ ገብርኤል ዘመን በቅዱስ ሐርቤ ዘመነ መንግሥት አባ ሚካኤልም ለኢትዮጵያ ጳጳስ ሁኖ በነበረበት ጊዜ::*

*የኢትዮጵያ ንጉሥ ሐርቤ ለኢትዮጵያ አገሮች ኤጲስ ቆጳሳትን ይሾም ዘንድ አባ ሚካኤልን አዘዘው:: አባ ሚካኤልም ያለ ሊቀ ጳጳሳቱ ትእዛዝ ሌሎች ኤጲስ ቆጳሳትን መሾም አልችልም ብሎ ለንጉሡ መለሰለት::*

*ስለዚህም የኢትዮጵያ ንጉሥ ወደ አባ ገብርኤልና ወደ ግብፅ ንጉሥ እየለመነና እየማለደ ንጉሡ አባ ገብርኤልን እንዲአዝለት፤ አባ ገብርኤልም ለአባ ሚካኤል እንዲፈቅድለትና በተጨማሪ ሌሎች ኤጲስ ቆጳሳትን አሰቀድሞ በሾሟቸው ላይ እንዲሾም እንዲህ መልእክትን ላከ::*

*የግብፅ ንጉሥም የኢትዮጵያን ንጉሥ ፈቃዱን ሁሉ ይፈጽምለት ዘንድ አባ ሚካኤል እንዲፈቅድለት አባ ገብርኤልን አዘዘው::*

*ከዚህ በኋላ መኳንንቱ ወደ ግብፅ ንጉሥ ዘንድ ገብተው እንዲህ አሉት:: በኢትዮጵያ ኤጲስ ቆጳሳት ቢበዙ ደፍረው ጳጳሳትን ይሾማሉ:: ከዚያ በኋላ ከኛ ወደ እኛ አይመጡም::*

*ንጉሡም ይህን በሰማ ጊዜ ይህን አባት አባ ገብርኤልን እንዲህ አዘዘው:: ከእንግዲህ በኢትዮጵያ አገር ኤጲስ ቆጳሳትን እንዳይሾም ለኢትዮጵያ ንጉሥ*

www.ethiopianorthodox.org

*የውግዘት ደብዳቤ ላከ አለው::*

*ሊቀ ጳጳሳቱም የግብፅ ንጉሥ እንዳዘዘው ላከ:: የውግዘቱ ደብዳቤም ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ደርሶ በተነበበች ጊዜ የንጉሡ እዳራሽ ተቃጠለ:: በኢትዮጵያ እገርም ረኃብና ቸነፈር ሆነ:: ዝናብም ተከለከለ:: ችግርም ሆነ:: የኢትዮጵያ ንጉሥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላልፎአልና::*

*ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ንጉሥ ተመልሶ ተጸጸተ:: ወደ ግብፅም ይህን አባት አባ ገብርኤልን እንዲእዝለትና ከግዝቱ ይፈታው ዘንድ እየለመነ መልእክትን ላከ:: የግብፅ ንጉሥም እዘዘለት::*

*አባ ገብርኤልም የመፈቻና የቡራኬ ደብዳቤ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ እየባረከ ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ላከ::*

*ይህች የበረከት ደብዳቤ ወደ ኢትዮጵያ እገር ደርሳ በተነበበች ጊዜ እግዚአብሔር መዓቱን ከላያቸው እርቆ ይቅርታውን ሰጣቸው:: ዝናብም ወረደላቸው:: ቸነፈርም ተወግዶ ታላቅ ደስታ ሆነ:: ይህም በዘመኑ ሆነ::*

/ስንክሳር፣ ሚያዝያ 10/

የንጉሥ ሐርቤ ጥያቄ በዚህ ዓይነት ውጤት ሳያመጣ ተዳፍኖ፣ በምትኩ ግብፃውያን የመረጡትን እየላኩ ከሀገሪቷ ማግኘት ያለባቸውን ጥቅም ሲያገኙ ቆዩ::

«ያለ እኛ ሀገሪቷም ሆነች ቤተ ክርስቲያኗ አይቀኑም» ይሉ የነበሩት ግብፃውያን በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በተደረገው የመስቀል ጦርነት የተነሣ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ባለመቻላቸው፣ እንደ እነሱ አባባል፣ አገሪቷ ካለ ጳጳስ ቆይታለች:: ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይልቁንም በወቅቱ የታላቁ ገዳም የደብረ ሊባኖስ ገዳም ዕጨጌ የነበሩት ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በኢትዮጵያውያን መምህራንና ሊቃውንት ተመርጠው በመንበረ ጵጵስናው ላይ በመሾም አገሪቷን በመባረክ፣ ተዘጋጅተው ለቀረቡትም ዲቁናና ቅስና ሲሰጡ ቆይተዋል::

ጦርነቱ ከተጠናቀቀ በኋላም የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ስድስተኛውን የኢትዮጵያ ጳጳስ በላከች ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበሩን አልለቅም አላለችም:: በማስተዳደር ረገድ መንፈሳዊና አእምሮአዊ ብቃታቸውን በተግባር ያሳዩት ጻድቁ አቡነ ተክለ



ሃይማኖት ለዓመታት ተግተው ያገለገሉበትን መንበረ ጵጵስና ለመጣው አዲስ ግብፃዊ ጳጳስ ክአክብሮት ጋር አስረክበዋል::

ከንጉሥ ሐርቤ ቀጥሎም በየጊዜው መንበረ ሥልጣኑን የያዙ የኢትዮጵያ ነገሥታት ምንም እንኳን አዎንታዊ መልስ ባያገኙም ጥያቄያቸውን በግብፅ ለነገሡ የእስላም ነገሥታት ሊያነሡ ቆይተዋል:: ለምሳሌ ዓፄ ዓምደ ጽዮን /1304 - 1305/ ለመሐመድ ኢብን ካላሁን፣ ዓፄ ይስሐቅ በ1423 ዓ.ም ለሡልጣን ባርሳቤይ፣ ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ በ1443 ዓ.ም ለሡልጣን ካግማህ፣ ዓፄ እስክንድር በ1481 ዓ.ም ለሡልጣን ካይትባይ ያቀረቧቸው ጥያቄዎች ይጠቀሳሉ::

ወደ 19ኛው መ.ክ.ዘ. ስንመጣም ሀፄ ዮሐንስ አራተኛ /1871-1881/ ይህንኑ ለረጅም ዘመናት መልስ ሳያገኝ የቆየ ጥያቄ ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን አቅርበዋል:: ዓፄ ዮሐንስ ኢትዮጵያውያን በቋንቋቸው ወንጌል ይሰብክላቸው ዘንድ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የራሷን አንድ ሊቀ ጳጳሳትና በርከት ያሉ ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጳሳት እንድትሾምላቸው በዘመኑ ለነበሩት የእስክንድርያው ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስ አምስተኛ ጥያቄ አቀረቡ:: ይሁን እንጂ የንጉሡን ጥያቄ ፓትርያርኩ ሳይቀበሉ በምትኩ በኢትዮጵያ የሚኖሩትን ኤጲስ ቆጳሳት ቁጥር ወደ ሦስት ከፍ በማድረግ ከአንድ ሊቀ ጳጳሳት ጋር ሾመው ላኩ:: በዚህም መሠረት በ1874 ዓ.ም አቡነ ጴጥሮስ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ፣ አቡነ ማቴዎስ የሸዋ ኤጲስ ቆጳስ፣ አቡነ ሉቃስ የጐጃም ኤጲስ ቆጳስ፣ አቡነ ማርቆስ የበጌ ምድር ኤጲስ ቆጳስ ሆነው በመሾም መጡ::

ጉዳዩ በዚህ ተደምድሞ የሀፄ ዮሐንስ አራተኛ ዘመነ መንግሥት በሀፄ ምኒልክ ተተካ:: በዚህም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ /በ1910 ዓ.ም ሀርፈው እቲሳ ተ/ሃይማኖት ሳይ ተቀብረዋል/ ወደ ትግሬ ሀገረ ስብከት ተዛውረው በምትካቸው በሸዋ ተሹመው የነበሩት ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ /1874 - 1919/ መንበረ ጵጵስናውን ያዙ:: እኒህ አባት በሸዋ ኤጲስ ቆጳስነት ለ8 ዓመታት፣ በኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳትነት ለ37 ዓመታት የተሾሙ ሲሆን ኅዳር 25 ቀን 1919 ዓ.ም ሀርፈው አዲስ አበባ ያኔ መካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ይባል በነበረው የዛሬው በዓለ ወልድ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል::

ይሁን እንጂ ሊቀ ጳጳሳቱ ከማረፋቸው አንድ ዓመት በፊት የጀመረው የኢትዮጵያውያን ሊቃውንትና መምህራን የሹመት ጥያቄ ካረፉ በኋላም እየተጠናከረ መጣ:: የኢትዮጵያውያኑ ጥያቄ በወቅቱ በአማርኛ ቋንቋ እየተዘጋጁ ይታተሙ የነበሩትን «አእምሮ»ና «ብርሃንና ሰላም» የተሰኙ ጋዜጦችንም ሽፋን እያገኘ፣ ሊቃውንቱም

www.ethiopianorthodox.org

በጎትመቶቹ ሐሳባቸውን እየገለጹ ሔዱ:: እየዋለ እያደረም የሊቃውንቱ ጥያቄና ክርክር ከመጠናከሩ የተነሣ ወደ ሰድብና ዘለፋ እስከ መሔድ በመድረሱ በሊቀ ጳጳሱ ከሳሽነት ለእስራትም የተዳረጉ ኢትዮጵያውያን ነበሩ ይባላል:: ይህ የኢትዮጵያውያኑ ሊቃውንት፣ መኳንንትና ሠራዊት ክርክርና ፍትሐዊ ጥያቄ በጋዜጦቹ አማካይነት ወደ ቤተ መንግሥቱ ገብቶ ተደማጭነትንና ተቀባይነትን አገኘ::

በወቅቱ በልዑል አልጋ ወራሽነት መዓርግ ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ የነበሩት ራስ ተፈሪ መኰንን /በኋላ ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ/ እንደ ቀደሙት ነገሥታት በጥያቄው ተገቢነት በማመን እጀንዳው የቤተ መንግሥቱ እንዲሆን አደረጉ:: በዚህም ጉዳዩን በመጀመሪያ ለግርማዊት ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ፤ ቀጥሎም ለመሣፍንቱ፣ መኳንንቱና ሊቃውንቱ በማቅረብ ሰፊ ውይይት አደረጉበት:: በውይይቱም ከልዑል እልጋ ወራሹ ጀምሮ ሁሉም የጥያቄውን ተገቢነት በማመናቸው በልዑል አልጋ ወራሽ ፊርማ «ባረፉት የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ምትክ ሌላ ሊቀ ጳጳሳት ተሹሞ እንዲመጣ፣ ከእርሱም ጋር በሀገሪቱ ወንጌል ይስፋፋ ዘንድ የሚያስፈልጉ በርከት ያሉ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ይሾሙልን ዘንድ ፈቃዳችሁ ይሁን» በሚል ለወቅቱ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ለብፁዕ እቡነ ቄርሎስ አምስተኛ ደብዳቤ ተላከ::

ደብዳቤው የደረሳቸው የግብፅ ፓትርያርክም ብቻቸውን በጉዳዩ ውሳኔ ሊያሳልፉበት እንደ ማይችሉ፤ በመሆኑም በጥያቄው ላይ የሚመክር ጉባኤ ጠርተው ውሳኔ እንዲሰጥበት እንደ ሚያደርጉ በመግለጽ ለልዑል እልጋ ወራሽ መልስ ሰጡ::

አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪም ሆኑ ኢትዮጵያውያን ፓትርያርኩ በገቡት ቃል መሠረት ጉባኤ የሚጠሩበትንና ውሳኔ የሚያስጡበትን ቀን በመጠባበቅ ላይ ሳሉ የግብፅን ቤተ ክርስቲያን ለ52 ዓመታት ከዘጠኝ ወራት የመሩት ፓትርያርክ ከዚህ ዓለም በሞት እንደ ተለዩ ተሰማ:: የፓትርያርኩን ዕረፍት በማስመልከትም ኢትዮጵያ የተሰማትን ኀዘን በመግለጽ፤ ወዲያውም የቀረበው ጥያቄ መልስ እንዲያገኝ በሚል አዲስ አበባ ላይ ሰባት ጊዜ መድፍ እንዲተኮስ ተደረገ::

በዕድሜ ጠገቡ ፓትርያርክ ሞት የተነሣ የቀረበውን ጉዳይ የሚያስፈጽም እዲስ ፓትርያርክ ባለ መሾሙ የኢትዮጵያ ጥያቄ ለአንድ ዓመት ከአምስት ወር ያህል ሊዘገይ ግድ ሆነ:: ከዚያም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ ታኅሣሥ ሰባት ቀን 1921 ዓ.ም 19ኛው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው እንደ ተሾሙ በቴሌ ግራም ለልዑል አልጋ ወራሹ ተገለጠ:: ልዑል አልጋ ወራሹም በጉዳዩ የተሰማቸውን ደስታ ለፓትርያርኩ ገልጸው ቀደም ሲል



ያቀረቡት ጥያቄ አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጠው የሚያሳስብ ቴሌግራም ላኩ:: ይኸውም በአቡነ ማቴዎስ ምትክ አንድ ሊቀ ጳጳስ ተሹሞ እንዲላክ፤ እርሱም አዲስ አበባ ሲደርስ ከኢትዮጵያ መምህራን እየመረጠ ጳጳሳትን እንዲሾም የሚል ጥያቄ ነበር::

ይሁን እንጂ አዲሱ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ጥያቄውን ሙሉ በሙሉ ባለመቀበል የሚከተለውን ቴሌ ግራም ለልዑል እልጋ ወራሹ ላኩ::

*ግርማዊነትዎ የላከውን መልእክት ለማን::*

*በግብፅ ቤተ ክርስቲያንና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን መልካም ወዳጅነት አጠንክሮ ለማኖር ስለ ገለጡልን ልባችን በደስታ ተነካ:: ለግርማዊነትዎና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፤ ለሕዝብዎም ተድላ እንዲሆን ስለ ራሳችን ስለ ግብፅም ሕዝብ ሆነን የምንመኘውን መልካም ምኞታችንን በደስታ እናቀርባለን::*

*ለግርማዊነትዎ በማንኛውም ነገር የሚስማማ መልካም ባሕርይ ያለው አንድ ጳጳስ ለመሾም ከዚህ ቀድሞ መፍቀዳችንን እንደ ገና እናረጋግጣለን:: የቤተ ክርስቲያኑ ሕግ የሚፈቅድልን ቢሆን ኖሮ ይህንኑ ሊቀ ጳጳስ ሌሎች ጳጳሳትን ለመሾም እንዲችል አድርገን ብንሾመው ደስ ይለን ነበር:: ይህ በተለይ የቤተ ክርስቲያንን ሕግ የሚያውክ ስለሆነ ብፁዕ ፓትርያርክ ሱራል በዮሴፍ ፓሻ ሱሌይማን በኩል ያስታወቁንን አሳብ እናረጋግጣለን:: ጳጳስ ብለን እንድንሾማቸው ብፁዕ ዕጨጌን ግርማዊነትዎ ይላኩልን:: ከሊቀ ጳጳሱም ጋራ እንድነት ሆነው በኢትዮጵያ በየክፍሉ ላለው ሥራ የሚረዱ ሁለት የግብፅ ጳጳሶችን እንሾማለን:: በኢትዮጵያ ልጆችና በናታቸው በግብፅ ቤተ ክርስቲያን መካከል እስካሁን ሳያልቅ የቆየውን ነገር ሁሉ ለሁለቱም ወገን ጥቅም የሚሆንና ለግርማዊነትዎም ደስ በሚያሰኝ መንገድ ለመጨረስ ቁርጥ የሆነ አሳባችን መሆኑን እናረጋግጣለን:: ሁለቱንም አገሮች የሚያስተሳስረው የፍቅር ማሰሪያ እየጠበቀ እንዲሔድ እንደ ግርማዊነትዎ ሐዋርያዊ ቡራኬያችንን ለግርማዊት ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊነትዎ ለቤተ ዘመዶቻችሁም ለቤተ ክርስቲያን ልጆቻችን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንሰጣለን::*

www.ethiopianorthodox.org

ልዑል እልጋ ወራሽ ተፈሪም የፓትርያርኩን የአቡነ ዮሐንስን ቴሌግራም ከተመለከቱ በኋላ ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ምላሽ በቴሌ ግራም አስተላለፉ::

*ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ዮሐንስ፤ ቴሌ ግራምዎ ደረሰን:: መልካም ባሕርይ ያለው አንድ ሊቀ ጳጳስ ለመሾም እርሱ ከእኛም ለአንዱ ለዕጨጌ ጳጳስነት ለመስጠት መፍቀድዎን የሚያስታውቅ አሳብ ግን እኛ እንዳሰብነው የትምህርት ችግራችንን የሚያቀልልን አልሆነም:: የሚጨመሩትንም ሁለቱ ግብፆች መቼም ቋንቋችንን አያውቁትምና ፈቃድዎ ሆኖልን ዛሬ ለጊዜው በቋንቋችን ከሚያስተምሩ ሊቃውንት መርጠን የሚያስፈልገንን ያህል ከመልእክተኞቻችን ጋራ በደንልዎ ስለ ቤተ ክርስቲያኑ ሥርዓት የሚከለከል ሕግ ከተገኘ እኛም ያስፈልገናል ያልንበትን ምክንያት አስታውቀው እርስዎም የቤተ ክርስቲያኑ ሕግ የሚከለከልበትን ሥርዓት አስረድተዋቸው የሚመጣው ሊቀ ጳጳስ ከዚህ ለመሾም የማይቻል ነው ከተባለ እነዚህን መርጠን የምንሰድልዎን ሰዎች ከዚያው ተሹመው ከሊቀ ጳጳሱ ጋራ አብረው ይምጡልን::*

*ይህንንም ፈቃድዎን አለመጋፋታችን እስከ አሁን ጸንቶ የኖረው ያባትና የልጅነት መተማመን እንዳ ይጉድል ብለን ነው እንጂ የእኛም የሕዝባችንም ፈቃድ ግን ያው ቀድሞ እንደላክንብዎ ቃል መሆኑን እንዲ ያውቁልን እንለምንዎታለን::*

ንጉሥ ተፈሪ ቴሌግራሙን ከላኩም በኋላ የቴሌግራሙ ውይይት ፍሬ እንደ ማያመጣ በማሰብ በወቅቱ የትምህርት ሚኒ ስቴር ዲሬክተር በነበሩት በአቶ ሣህሌ ጸዳሉ የሚመራ ልዑክ ወደ ምድረ ግብፅ ላኩ:: ልዑኩም ይዞት በሔደው አጀንዳ ዙሪያ ከፓትርያርኩ ጋር ሰፋ ያለ ክርክር አደረገ:: በዚህም ፓትርያርኩ አስቸኳይ የሲኖዶስ ጉባኤ ጠርተው ከተወያዩ በኋላ ከአንድ ግብፃዊ ሊቀ ጳጳሳት ጋር አምስት ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳት እንዲ ሾሙ ፈቀዱ:: ፓትርያርኩም ውሳኔውን በሚከተለው ቴሌ ግራም ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ አስተላለፉ::

*ሐዋርያዊ ቡራኬያችን ለግርማዊነትዎ ይሁን:: ከኢትዮጵያ መምህራን አምስት ሰዎች ተመርጠው*



*ጳጳሳት ሆነው አምስት የኢትዮጵያ ኤጲስ ቆጳሳት ሹመት እንዲሾሙ ፈቅደናልና አምስት መነኮሳት እንዲልኩልን እንለምናለን::*

ግርማዊ ንጉሥም በፍጥነት በሚከተለው ቴሌ ግራም የተሰማቸውን ደስታ ገለጹ::

*በሣህሌ ጸዳሉ በኩል ባስታወቅንዎ ጉዳይ ከቡራ ኬዎ ጋር በላኩልን ምላሽ ደስ ብሎናል:: መነኮሳቱንም እንደ ሚያስፈልግ አድርገን እንልካለን:: እግዚአብሔር ቅዱስነትዎን ይጠብቅ::*

ከዚህ በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱና ግር ማዊ ንጉሥ ተፈሪ ነገሩ ይዋል ይደር ሳይሉ የኢትዮጵያ የዘመናት ጥያቄ መልስ ማግኘቱን ሊቃውንቱን፣ መሣፍንቱንና መኳንንቱን በመሰብሰብ አሳወቁ:: የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በጠየቁት መሠረትም በትምህርትና በምግባር የተመሰከረላቸውን መምህራን እንዲመርጡ ትእዛዝ አስተላለፉ::

በትእዛዙ መሠረትም ቤተ ክህነቱና ቤተ መንግሥቱ በአንድ ነት ጉባኤ በማድረግ መዓርገ ጵጵስናው ይገባቸዋል የተባሉ ዐሥር መምህራን ተመረጡ:: ይህም ለግርማዊትና ግርማዊ ተገለጠ:: ይሁን እንጂ ለምርጫ የተሰበሰቡት ሊቃውንት በነበራቸው ችኮላና ጉጉት ምክንያት አምስት መምረጥ ሲገባቸው ዐሥር መርጠው ነበር:: የግብፅ ቤተ ክርስቲያን በጠየቀችው መሠረት የተመራጭ ሊቃውንቱን ቁጥር ወደ አምስት ለማውረድ እንደ ገና ሊቃውንቱን ጉባኤ መጥራቱ ጊዜ ስለ ሚወስድ ከተመረጡት ዐሥር መምህራን አምስቱ በዕጣ እንዲለዩ ተወሰነ:: ቀድሞ ከዐሥሩ ውስጥ ተመርጠው ዕጣ ሳይወጣላቸው በመቅረቱ ከቀሩት አባቶች በስም ሊታወቁ የቻሉት መልአከ ገነት ወልደ ሐና፣ አለቃ ወልድ ተክሌ፣ አለቃ ወልደ ትንሣኤ የተባሉት አባቶች ብቻ ናቸው::

በዚህም መሠረት በዕጣው ላይ ለበባት ቀናት በቤተ ክርስቲያን ጸሎትና ሱባኤ ከተያዘበት በኋላ ዕጣው ወጥቶ አምስቱ መምህራን ተለዩ:: እነርሱም ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ መምህር ደስታ፣ መምህር ኃይለ ማርያም፣ መምህር ወልደ ኪዳንና መምህር ኃይለ ሚካኤል ናቸው::

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ በኋላ ከተመረጡት መምህራን አራቱ በወቅቱ የገንዘብ ሚኒስቴር በነበሩት በክቡር በጅሮንድ ዘለቀ አግደውና የትምህርት ሚኒስትር ዲሬክተር በነበሩት በክቡር አቶ ሣህሌ መሪነት ግንቦት 2 ቀን 1921 ዓ.ም ከአዲስ አበባ በባቡር ተሳፍረው ወደ ጅቡቲ ሔዱ::

ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በወቅቱ ባጋጠማቸው ሕመም የተነሣ ወደ ካይሮ ሊሔዱ አልቻሉም:: ነገር ግን በ1922 ዓ.ም ፓትርያርኩ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት በመጡ ጊዜ ጥር 1 ቀን 1922 ዓ.ም ሥርዓተ ቅብዓታቸውን እዚሁ አዲስ አበባ በመታሰቢያ ቤት በአታ ለማርያም ገዳም ሳዊሮስ ብለው በመሠየም ፈጽመውላቸዋል:: ፓትርያርኩ በዚህ አፊሴላዊ ጉብኝታቸው ወቅት የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራልን የመሠረት ድንጋይ አስቀምጠው እንደ ነበር ይነገራል::

ለታላቁ ሹመት የታጩት አራት አባቶችና ሌሎች ልዑካን ከጅቡቲም ግንቦት 5 ቀን በመርከብ ተሳፍረው ወደ ካይሮ ሔዱ:: በካይሮም ለ20 ቀናት ከቆዩ በኋላ ግንቦት 25 ቀን 1921 ዓ.ም ከግብፃዊው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ጋር መምህር ደስታ - አቡነ አብርሃም፤ መምህር ኃይለ ማርያም - አቡነ ጴጥሮስ፤ መምህር ወልደ ኪዳን - አቡነ ይስሐቅ፤ መምህር ኃይለ ሚካኤል - አቡነ ሚካኤል ተብለው በፓትርያርኩ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ አንብሮተ ዕድ በካይሮ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ተሾሙ::

ኢትዮጵያውያኑ አባቶች በተጠቀሰው ቀን ከተሾሙ በኋላ ፓትርያርኩ አቡነ ዮሐንስ ለግርማዊት ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ቴሌ ግራም አስተላለፉ::

*ዛሬ በግንቦት 25 ቀን አባ ቄርሎስን ሊቀ ጳጳሳት አድርገን፤ አራቱን የኢትዮጵያ መምህራን ጳጳሳት አድርገን ስማቸውንም ጴጥሮስ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ሚካኤል ብለን ቀብተን ሹመናቸዋል::*

የቴሌ ግራሙን መልእክት የተቀበሉት ግርማዊትና ግርማዊም ወዲያውኑ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል በቴሌ ግራም ወደ ፓትርያርኩ ላኩ::

*ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ዮሐንስ፤ የሊቀ ጳጳሱንና የጳጳሳቱን መሾም ስላስታወቁን እናመሰግን ዎታለን:: ይኸውም ነገር በቅዱስነትዎ ዘመን መፈጸሙ*



*የኢትዮጵያና የግብፅ ቤተ ክርስቲያንን አንድነት እያጸና የሚሔድ መሆኑን ያስረዳልናል:: እግዚአብሔር ፓትርያ ርክነትዎን ይባርክ::*

ግብፃዊው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስና አራቱ ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳት ከላይ በተገለጠው መንገድ መዓርገ ጵጵስና ከተቀበሉ በኋላ ተመሳሳይ የባቡርና የመርከብ የመልስ ጉዞ በማድረግ ሰኔ 21 ቀን 1921 ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ:: ለ1600 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያውያን ነገሥታትም ሆኑ አባቶች ሲታገሉለት የነበረው የኢትዮጵያውያን መሾም ጉዳይ እግዚአብሔር በፈቀደው በዚያ ዘመን ሊፈጸም ያዩ ኢትዮጵያውያን፤ ለተሾሙት ብፁዓን አባቶች ወደ ኢትዮጵያ ምድር ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ በየቦታው ከፍተኛ አቀባበል ያደርጉላቸው ነበር:: ለምሳሌ ድሬዳዋ ሲደርሱ ከከተማውና በአካባቢው ከተሰበሰቡት ኢትዮጵያውያን በተጨማሪ ለዚሁ በቤተ መንግሥቱ ትእዛዝ ከአዲስ አበባ በተላኩ ሊቃውንትና ታላላቅ ባለሥልጣናት አማካይነት የሞቀ አቀባበል ተደርጎላቸዋል:: ድሬዳዋን አልፈው ሞጆ ሲደርሱም በወቅቱ የሀገር ግዛት ሚኒስትር የነበሩት ደጃዝማች ወ/ጻድቅ እና የመሳሰሉት ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት አቀባበል አድርገውላቸዋል::

እነዚህ የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን ብፁዓን አባቶችና በሊቀ ጳጳስነት ተሹመው የመጡት ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ ከሃያ ቀናት በላይ ተጉዘው አዲስ አባባ ባቡር ጣቢያ ሊደርሱ ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃ/ሥላሴ ከሕዝባቸው ጋር በመሆን ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል:: በማግሥቱም ትልቅ በዓል ተደርጎ ለክብራቸውም 25 ጊዜ መድፍ ተተኩሶላቸዋል::

ኢትዮጵያውኑ አባቶች ለአንድ ዓመት ያህል ከቤተ መንግሥቱ ሳይርቁ ሥነ አስተዳደር እንዲ ለማመዱ ከተደረገ በኋላ ቀደም ያሉት ነገሥታትም ጭምር ያልሙት የነበረው የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በሀገሪቱ የመስፋፋት ነገር እውን ሊሆን በቤተ መንግሥቱ ሀገረ ስብከት እየተከፈለ ተሰጣቸው:: */የሹመታቸውን ደብዳቤ በአባሪ 1 ይመለከቷል/::*

ኢትዮጵያውያኑ ጳጳሳትም በየተመደቡበት ሀገረ ስብከት በመሠማራት ሕዝባቸውን በትጋት መባረክና ማስተማር ጀመሩ:: ይሁን እንጂ ሕዝቡ ለአባቶቹ ያሳይ የነበረው ፍቅር ብዙም ሳይዘልቅ፣ የአባቶች የስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ ገና በመጀመር ላይ ሳለ ሀገራችንን በግፍ ሊወር በመጣው የኢጣልያ ፋሺስት ጦር ተደናቀፈ:: ቀደም ባለው የሀገሪቷ ታሪክ እንደ ሆነው በ1928 ዓ.ም ኢትዮጵያ በተወረረች ጊዜም ብሔራዊት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስ

www.ethiopianorthodox.org

ቲያን ግንባር ቀደም ተጠቂ ነበረች:: በርካታ አብያተ ክርስቲያናቷ ወድመዋል:: ከመቼውም ጊዜ በበለጠም ሀብቷ ተዘርፏል:: ኢትዮጵያውያን ነገሥታትና ሕዝብ ባደረጉት ሰፊ ትግል ለመጀመሪያ ጊዜ ተሹመው የሀገሪቱ ሕዝብ በስስት ከሚያያቸው የመጀመሪያዎቹ ጳጳሳቷ መካከል ሁለቱ በግፍ ተረሸነውባታል::

የጉዳዩን መካረር ያዩት የወቅቱ ግብፃዊ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ወደ ሮማ ሔጀ ከዱቼ ሙሶሎኒ ጋር ስለ ጉዳዩ ልምክር በሚል ብፁዕ አቡነ አብርሃምን ተጠባባቂ ሊቀ ጳጳሳት አድርገው በመሾም ሔዱ:: ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያን ግብፃዊው አቡነ ቄርሎስ ሰላምን ይዘውልን ይመለሳሉ ብለው በጉጉት ቢጠብቋቸውም ከሮማ ሊመለሱ ያመሩት ቀኑ ወደ ጨለመበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይሆን ወደ ሀገራቸው ወደ ግብፅ ነበረ::

የአቡነ ቄርሎስን ወደ ሮማ መሔድ አስመልክቶ አንዳንድ የታሪክ መዛግብት ለየት ያለ ሐሳብ ያሰፍራሉ:: ይኸውም ሊቀ ጳጳሱ ወደ ሮማ ያቀኑት ሙሶሎኒ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት ለመሆናቸው ዕውቅና እንዲሰጣቸው ለመማጸን ነበር የሚል ነው:: እነዚህ የታሪክ መዛግብት ሊቀ ጳጳሱ ወደ ኢትዮጵያ ሳይመጡ በዚያው ወደ ሀገራቸው የሔዱበትን ምክንያት ሲገልጹ ሙሶሎኒ ለጥያቄያቸው አዎንታዊ ምላሽ ስላልሰጣቸው እንደሆነ ያትታሉ::

የሆነው ሆኖ በዚህ ዓይነት ብፁዕ አቡነ አብርሃም ተጠባባቂ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው የመከራውን ዘመን ሲገፉ የኢጣልያ መንግሥት በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የፈጸመውን ግፍ ለማስረሳትና በዚህም እሷን መሳሪያ አድርጐ በየቦታው የእግር እሳት የሆኑበትን ኢትዮጵያውያን አርበኞችን ለማሥታገስ ሲል በ1930 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ሊቀ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጳሳት መሾም ትችላለች በማለት ዐወጀ:: ይህ ዐዋጅ ወደ ተግባር ይለወጥ ዘንድም ከሸዋ፣ ከጎጃም፣ ከጎንደር፣ ከወሎና ከትግሬ አስራ አምስት አስራ አምስት ሊቃውንት ወደ አዲስ አበባ መጥተው ጉባኤ እንዲሆን ትእዛዝ አስተላለፈ:: ምንም እንኳን ኢትዮጵያውያኑ ሊቃውንት የዐዋጁ መንፈስ ምን እንደ ሆን በሚገባ የተረዱት ቢሆንም አጋጣሚውን ለመጠቀም በመፈለግ ኅዳር 21 ቀን 1930 ዓ.ም ከየክፍሉ የተውጣጡ መምህራንና ሊቃውንት አዲስ አበባ ላይ ጉባኤ አደረጉ::

ጉባኤውም በተለያዩ ነጥቦች ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ ቀደም ሲል ወደ ግብፅ ሔደው የተሾሙት ብፁዕ አቡነ አብርሃም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት እንዲሆኑ፣ እርሳቸውም ሌሎች ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጳሳትን እንዲሾሙ የሚል ታሪካዊ ውሳኔ አሳልፎ ተጠናቀቀ:: በውሳኔውም



መሠረት በዚያው ቀን ጉባኤው የሚገባውን ጸሎት ካደረሰ በኋላ ብፁዕ አቡነ አብርሃም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው ተሾሙ:: ብፁዕነታቸውም በዚያው ቀን የሚከተሉትን ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶስ ሾሙ::

- ንቡረ ዕድ ተክለ ሃይማኖት ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ዮሐንስ ብለው፣ ዕጨጌና የሸዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ፣
- መምህር ገብረ አምላክ ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ማርቆስ ብለው፣ የኤርትራ ሀገረ ስብከት ጳጳስ፣
- መምህር ገብረ አምላክ ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ማቴዎስ ብለው፣ የወሎ ሀገረ ስብከት ጳጳስ፣
- መምህር ገብረ ኪዳን ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ገብርኤል ብለው፣ የጐንደር ሀገረ ስብከት ጳጳስ፣
- መምህር አካሉ ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ሉቃስ ብለው፣ የወለጋ ሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጳስ::

ኢትዮጵያውያን ችግር ባጋጠማቸው ጊዜ በአቡነ ቄርሎስ አማካይነት ሀገሪቷን እሳት ላይ ጥላ የሸሸችው የግብፅ ቤተ ክርስቲያንም ይህንን ውሳኔና ሹመት በሰማች ጊዜ ድርጊቱንም ሆነ የድርጊቱን አስፈጻሚ አቡነ አብርሃምን አወገዘች:: ከውግዘትም ጋር ሕዝቡ ከእሳቸውም ሆነ እሳቸው ከሾሟቸው አባቶች መስቀል እንዳይሳለም ጥሪ አቀረበች:: ነገር ግን ብፁዕ አቡነ አብርሃምም ሆኑ የተሾሙት አባቶች እንዲሁም ሊቃውንቱና ምእመኑ ለውግዘቱ ቦታ ሳይሰጡ አገልግሎታቸውን ቀጠሉ:: ከዓመት በኋላ ሐምሌ 14 ቀን 1931 ዓ.ም ሽምግልና ተጫጭኗቸው የነበሩት ብፁዕ አቡነ አብርሃም ዐረፉ:: በመሆኑም በእርሳቸው ቦታ የሚተካውን ሊቀ ጳጳሳት ለመምረጥ ከየክፍሉ የተውጣጡት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን መስከረም 1 ቀን 1932 ዓ.ም እንደ ገና ጉባኤ አደረጉ:: በጉባኤው መጨረሻም ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ መንበረ ሊቀ ጵጵስናውን ተረክበው እንዲያገለግሉ፣ እርሳቸውም ሌሎች ጳጳሳትን እንዲሾሙ በሙሉ ድምፅ ውሳኔ አስተላለፈ:: ብፁዕ አቡነ ዮሐንስም በጉባኤው ውሳኔ መሠረት የሚከተሉትን ጳጳሳት ሾሙ::

- ሊቀ ሊቃውንት ገብረ አብ ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ፊልጶስ ብለው፣ የሊቀ ጳጳሳት ዮሐንስ ጸሐፊ፣
- መምህር ገብረ ጊዮርጊስ ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ጎርጎርዮስ ብለው፣ የወሎ ጳጳስ፣

www.ethiopianorthodox.org

- መምህር ሣህሌ ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ማትያስ ብለው፣ የሸዋ ጳጳስ፤
- መምህር ተክለ ማርያም ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ አትናቴዎስ ብለው፣ የጎጃም ጳጳስ፣
- መምህር ወልደ አረጋይ ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ቄርሎስ ብለው፣ የኤርትራ ጳጳስ::

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ከነዚህም በተጨማሪ ከአምስት ወራት በኋላ በጥር ወር 1932 ዓ.ም አባ ኃይሉ ሚካኤል ይባሉ የነበሩትን ብፁዕ አባ ዘካርያስ ብለው፣ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ አድርገው ሾሙ::

በዚህ ዓይነት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጳጳሳትና የኤጲስ ቆጶሳት ቁጥሯን ወደ ሀሥር አሳድጋ በተሰመደ ተግባሯ በጠላት ወረራ ይሳቀቁ እና ይንገላቱ የነበሩትን ኢትዮጵያውያን ስታጽናና ስትመክር ቆየች::

እግዚአብሔር በአምስቱ የመከራ ዘመናት በየቦታው የፈሰሰውን የንጹሐን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ደም ጩኸት፣ እንዲሁም በየዋሻው ዘግተው የሚጸልዩትን አባቶችና እናቶች ጸሎት ሰምቶ በ1933 ዓ.ም ሀገሪቷ ከወራሪው ኃይል ነጻ ወጣች:: ንጉሡም ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ:: በዚህ ጊዜ የሁለቱን ወዳጅ ሀገሮች (የግብፅንና የኢትዮጵያን) ፖለቲካዊ ግንኙነት ስመጠበቅ በሚል ምንም እንኳን የእንዳንዶቹ አባቶች ቆይቶ ቢመለስላቸውም በወረራው ወቅት የተሾሙት አባቶች በየሀገረ ስብከታቸው ያለ ምንም ሥራ እንዲቀመጡ ሆነ:: የቤተ ክህነቱንም ሥራ በወቅቱ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ዕጨጌ የነበሩት ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ እንዲመሩት ተደረገ::

ከዚህ በኋላ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ተቋርጦ የቆየው የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት እንዲቀጥል ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ አቀረቡ:: በጥያቄውም መሠረት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን በወረራው ወቅት ሸሽተው ወደ ሀገራቸው በሔዱት አቡነ ቄርሎስ የሚመራ አንድ ልዑክ ወደ ኢትዮጵያ ላከች:: ከሊቀ ጳጳሱ ጋር የመጡት ሰዎች ሚ/ር ሳዲቅ ጋሻ ዋህቢ፣ ሚ/ር ሜሪት ጋሊ ቤዲ፣ ፋርግ ሚካኤል ሙሳ ቤዲ ይባሉ ነበር:: ልዑኩ በቤተ መንግሥቱ ከተወከሉ ኢትዮጵያውያን ጋር ከተወያየ በኋላ የኢትዮጵያን «ግዝቱ ይነሣልን» ጥያቄ ይዞ ወደ ካይሮ ተመለሰ:: በዚህ ጊዜ አቡነ ቄርሎስ አዲስ አበባ ቀሩ:: ጉዳዩን መስመር ለማስያዝ በሚልም በወቅቱ የሊቀ ጳጳሳትነቱን ቦታ ይዘው የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ



የመንበረ ሊቀ ጳጳሱን ግቢ እንዲለቁ ተደርጎ ግብፃዊው ሊቀ ጳጳሳት በዚያ እንዲቀመጡ ተደረገ::

በአቡነ ዮሳብ ተጠባባቂ ፓትርያርክነት ይመራ የነበረው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ሰኔ 14 ቀን 1934 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጥቶ የነበረው ልዑክ ይዞት በሔደው ጥያቄ ላይ ውይያት ካደረገ በኋላ አንድ ውሳኔ አስተላለፈ:: ውሳኔውም ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ተላከ:: ይሁን እንጂ ተላለፈ የተባለው ውሳኔ ለኢትዮጵያውያኑ አርኪ አልነበረም:: በዚህ የተነሣም ውይይቱ ለጊዜው ተቋረጠ::

ከወራት በኋላ ጥር 27 ቀን 1936 ዓ.ም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መቃርዮስ 114ኛ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው ሲሾሙ በራሳቸው በአዲሱ ፓትርያርክ ጥያቄ ግዝቱን አስመልክቶ ተጀምሮ የነበረው ውይይት እንዲቀጥል ተደረገ:: በመሆኑም በፓትርያርኩ የተወከለ በጉዳዩ ላይ መክሮ የሚመለስ በአቡነ ጢሞቴዎስ የሚመራ አንድ ልዑክ ወደ ኢትዮጵያ መጣ:: ከአቡነ ጢሞቴዎስ ጋር የመጡት ሰዎች ጊምዲ ቤይ አብዱል መሊክ፣ እስክንድር ቤይ አሳብረና አስአድ ማርቆስ ቤይ ይባሉ ነበር::

ልዑኩም ከሰኔ 9 - 21 ቀን 1936 ዓ.ም በዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ይመራ ከነበረው የኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት ተወካዮች ልዑክ ጋር ከተወያየ በኋላ በስድስት አንቀጾች የቀረቡትን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ጥያቄዎች ይዞ ወደ ካይሮ ተመለሰ:: */የውይይቱን ሙሉ ቃለ ጉባኤ በአባሪ 2 ይመለከቷል/::*

ልዑኩ ካይሮ እንደ ደረሰ ጥያቄዎቹን ለፓትርያርኩ አቀረበ:: ፓትርያርኩም ደብዳቤውን ከተመለከቱ በኋላ ኢትዮጵያውያኑ ሊቃውንት በስድስት ነጥቦች ወስነው ባቀረቧቸው ጥያቄዎች ላይ አከራካሪ የሆነ መልስ ያዘለ ደብዳቤ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ላኩ:: */የደብዳቤውን ሙሉ ቃል በአባሪ 3 ይመለከቷል/::* ንጉሠ ነገሥቱም ፓትርያርኩ በደብዳቤያቸው የጠየቋቸው ጥያቄዎች መልስ ያገኙ ዘንድ ጥያቄውን ወደ አቀረበው መንፈሳዊ ጉባኤ እንዳ ስተላለፉትና መልሱን ከጉባኤው እንዲጠብቁ የሚገልጽ ደብዳቤ ላኩላቸው:: የፓትርያርኩን ጥያቄ ከንጉሡ የተቀበለው መንፈሳዊ ጉባኤም ሳይውል ሳያድር ጥያቄ የተነሳባቸውን አንቀጾች በማብራራት ለፓትርያርኩ በቀጥታ ላከ:: */የደብዳቤውን ሙሉ ቃል በአባሪ 4 ይመለከቷል/::*

የመንፈሳዊ ጉባኤው ማብራሪያ የደረሳቸው ፓትርያርክም ጉዳዩን ለሲኖዶስ አቅርበው ከተወያዩበት በኋላ የጉባኤው ሂደት የተዘገበበትን ቃለ ጉባኤ እና ያስተላለፈውን ውሳኔ ለመንፈሳዊ

www.ethiopianorthodox.org

ጉባኤው ላኩ። ቀድሞ በመከራ ዘመን የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ባደረገችው ፈትን የማዞር ድርጊት፤ ከነጻነትም በኋላ ግዙቱን ላለማንሳት እየሰጠችው ባለው ሐላፊነት የጎደለው መልስ፤ ከዚያም በላይ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ባስተላለፈው ውሳኔ ክፉኛ ያዘነው የመንፈሳዊ ጉባኤውም በመደበኛ አማካሪዎቹ አማካይነት አዲስ አበባ ላይ ሰፊ ውይይት ያዙ። በጉዳዩ ላይ በስፋት ከተወያየበት በኋላም ሐምሌ 6 ቀን 1937 ዓ.ም አንድ ከባድ ውሳኔ አሳለፈ። ይኸውም «የግብፅ ቤተ ክርስቲያን እየተደረገ ባለው ውይይት ያሳለፈችውን ግዝት ታንሣ። ከአሁን በኋላም የግብፅን ቤተ ክርስቲያን እምነት ባንለውጥም ከግብፅ ምንም ዓይነት ሊቀ ጳጳሳትን አንፈልግም። በቋንቋችን የሚናገርና የሚያስተምር ሊቀ ጳጳሳት እንፈልጋለን» የሚል ነበር። የውሳኔው ሙሉ ቃል በዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ እንዲፈረምበት ከተደረገ በኋላ ለንጉሠ ነገሥቱ ተላከ።

ከወራት በኋላም ኅዳር 9 ቀን 1938 ዓ.ም ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤው እንደ ገና ተሰበሰበ። በዚህም መሠረት ባለፉት ጊዜያት የተደረጉትን ውይይቶችና የተከናወኑትን ድርጊቶች ሪፖርት በመስማት በሐምሌ የአማካሪዎች ጉባኤ ያስተላለፈውን ውሳኔ በመቀበል ተጨማሪ የውሳኔ አሳቦችንና ማሳሰቢያዎችን በማስተላለፍ ተበተነ።

በዚህ የሊቃውንቱ ቁራጥ በቋም የተነሣም በችግር ጊዜ ወደ ሀገራቸው ሸሽተው ሔደው የነበሩትና በኢትዮጵያውያን አባቶችና ሊቃውንት እንዲሁም አርበኞች ደም ሰላም ከመጣ በኋላ ተመልሰው መጥተው የነበሩት አቡነ ቄርሎስ ኢትዮጵያን ለቀው ሔዱ። ከላይ በተገለጠው ዓይነት የተላለፈው የመንፈሳዊ ጉባኤው የመጨረሻ ውሳኔ የደረሰው ቤተ መንግሥትም በጉዳዩ ላይ ከመከረ በኋላ ከመንፈሳዊ ጉባኤው አቋም ለየት ያለ አሳብ አቀረበ። ይኸውም ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋር በዚህ ዓይነት ከምንለያይ ለተጨማሪ ውይይት ጊዜ መስጠት ይኖርብናል የሚል ነበር። ቤተ መንግሥቱ ይህንን አሳቡንም በዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስና በሌሎች ወኪሎቹ አማካይነት ለመንፈሳዊ ጉባኤው ገለጸ።

የሊቃውንቱ ጉባኤ ምንም እንኳን «እስከ መቼ እንወያያለን?» በሚል በተወሰነ ደረጃ የቤተ መንግሥቱን ጥያቄ ላለመቀበል ተቃውሞ ቢያሰማም፤ በመጨረሻ ግን «ይሁን፤ ጥቂት ጊዜ ይሰጥ» በሚል ተስማማ። አቋሙ እንዳልተቀየረ፣ ጥያቄው ተግባራዊ ይሆን ዘንድብቻም ተጨማሪ ጊዜ እንደ ሰጠ በማግለጽ እንደ ገና በዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ፊርማ ለቤተ መንግሥቱ አቀረበ። በቀረበው ደብዳቤ የሚከተለው አሳብ ተካቶበታል።



*... መላው ጉባኤ ለኢትዮጵያ የሚገቡት ነገሮች እንዲሰጡ፤ ሊቀ ጳጳሳትም ከኢትዮጵያ ተወላጆች ውስጥ እንዲመረጥ ማስፈለጉን ተስማምቶበታል። ይኸውም አሳብ በመንግሥታችን ወገን የተደገፈ ስለሆነ መንግሥታችን መልእክተኞችን ልኮ አሳቡን ለማስፈጸም የሚከናወንለት ከሆነ ጉባኤው ተቃዋሚ አይደለም፤ ስለዚህ የቤተ መንግሥታችን አሳብና ምኞት መልእክተኞቹን ልኮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጠየቀችውን ሁሉ ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ተጠባባቂ ወይም ከጉባኤው ጋር በሰላም ለመጨረስ ስለሆነ ይህንኑ በቶሎ ከፍጻሜ እንዲያደርስላት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስተያን ግርማዊነትዎን በጸሎት እየደገፈች ትለምናለች፤ ነገር ግን ግርማዊነትዎ መልእክተኞችን ልኮ ከአሁን በፊት በዚሁ ነገር ቤተ ክህነት የደከመችውን ያህል በነገሩ ደከመውበት ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ተጠባባቂ ወይም ከጉባኤው ፍሬ ያለው ምላሽ ያልተገኘ እንደ ሆነ ግርማዊነትዎ የተስማማ እንደሆነ ባለመጠራጠር እናምናለን።*

ቤተ መንግሥቱም ይህንን የመሰለ ጠንካራ ማሳሰቢያ ከቤተ ክርስቲያኗ ሊቃውንት ከተቀበለ በኋላ በጉዳዩ ላይ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋር መክረው የኢትዮጵያን ጥያቄ ያስፈጽሙ ዘንድ ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤልንና ብላታ መርሥዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስን ጥር 1 ቀን 1938 ዓ.ም ወደ ካይሮ ላከ። ልዑኩ ወደ ዚያ ሲሔድ ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ለፓትርያርኩ የተጻፈ ደብዳቤ ይዞ ነበር። ጉዳዩ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ዘንድ ተጠናክሮ መቀጠሉን የሰማው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ግን ኢትዮጵያውያኑ ልዑካን ካይሮ ከመድረሳቸው በፊት አንድ ውሳኔ አሳለፈ። ይኸውም ከሚሾሙት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ጋር ሁለት የግብፅ ጳጳሳትም ተሹመው ወደ ኢትዮጵያ ይምጡ የሚል ነበር።

ክባድና ታሪካዊ ተልዕኮ ይዘው የሔዱት ሁለቱ ልዑካንም ካይሮ እንደ ደረሱ ውሳኔው ተገለጸላቸው። ይሁን እንጂ በቀረበላቸው ውሳኔ ባለ መስማማት ክርክራቸውን ቀጠሉ። ከብዙ ክርክርና ውይይት በኋላም የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያን ጥያቄ እንደ ተቀበለች፤ በጥያቄው መሠረትም የኢትዮጵያውያኑ አባቶች ሹመት በግንቦት ወር ከሚደረገው የአዲሱ ፓትርያርክ ሹመት ጋር እንደሚፈጸም፤ ስዚያም አምስት አባቶች ተመርጠው እንዲላኩ ለልዑካኑ ተገለጸላቸው።

በውሳኔውም መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃው

www.ethiopianorthodox.org

ንት በዕውቀትና በምግባር የተመሰከረላቸውን አምስት ሊቃውንት መርጠው በፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤልና በብላታ መርሥዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ መሪነት ሚያዝያ 28 ቀን 1938 ዓ.ም ወደ ካይሮ ላኩ። የግብፅ ቤተ ክርስቲያን አስቀድማ በገባችው ቃል ኪዳን መሠረት የግብፅ 115ኛ ፓትርያርክ ከሆኑት አቡነ ዮሳብ ጋር ግንቦት 2 ቀን 1938 ዓ.ም ሊሾሙ ወደ ካይሮ የገሠገሡት አባቶች በሰላም ገብተው ዝግጁነታቸውን ገለጡ። ነገር ግን ባልጠበቁት ሁኔታ በግብፆች የተዘጋጀና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ነጻነቷን እንዳታውጅ የሚያደርግ ሰነድ ቀረበላቸው። ሰነዱም የሚሾሙት ጳጳሳት ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ሌላ ኤጲስ ቆጶስ እንዳይሾሙ የሚያግድ ሲሆን ኢትዮጵያውያኑ አባቶች ከመሾማቸው በፊት እንዲፈርሙበት ይጠይቃል።

የግብፆችን ተንኮል በሚገባ የተረዱት አባቶችም ሲኖዶሱ ያሳለፈውን ውሳኔ ባለመቀበል ተቃውሞአቸውን በፊታውራሪ ታፈሰ ፊርማ ለተጠባባቂ ፓትርያርኩ አሳወቁ። ወዲያውኑም ሲኖዶሱ ያቆያቸውን ውሳኔ በተጠባባቂ ፓትርያርኩ በኩል ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንዲላክ አደረጉ። ንጉሠ ነገሥቱም ውሳኔውን በሚገባ ከመረመሩ በኋላ ኢትዮጵያ የማትስማማባቸውን ነጥቦች በዝርዝር በማስቀመጥ ኢትዮጵያውያኑ ልዑካን ከፓትርያርኩ ጋር ይወያዩባቸው ዘንድ ለፊታውራሪ ታፈሰ ላኩላቸው። ይህንን እንዳደረጉም ለፓትርያርኩ በደብዳቤ አሳወቁ። የንጉሡ ደብዳቤ የደረሳቸው ተጠባባቂ ፓትርያርክም ለንጉሡ የመልስ ደብዳቤ ከጻፉ በኋላ ከልዑካኑ ጋር የጋራ ስብሰባ አድርገው ተወያዩ። ከውይይቱም በኋላ ኢትዮጵያውያኑ አባቶች አዲሱ ፓትርያርክ ከመሾማቸው በፊት ሊሾሙ አይቻልም ከሚል ውሳኔ ላይ ስለ ደረሱ እና አንዳንድ ተጨማሪ ግልጽ ያልሆኑ አሳቦች ስለ ነበሩ ተጠባባቂ ፓትርያርኩን በመሰናበት ከወራት ፍሬ ቢስ ቆይታ በኋላ ሐምሌ 29 ቀን 1938 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ። በዚህ የተነሣ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋር የነበረው ግንኙነት ለሁለት ዓመታት ያህል ተቋረጠ። ይህንን በያሉበት ሆነው የሰሙት ኢትዮጵያውያኑ ሊቃውንትና መምህራን ምንም እንኳን እንዳ ለፉት ዓይነት ጉባኤያት አድርገው ባይወያዩም በያሉበት ሆነው ድምፃቸውን ሲያሰሙ ቆዩ።

የሊቃውንቱ ድምፅ ከፍ እያለ እንደ ገና ጉባኤ ወደ መጥራት አዝማሚያ ሲደርስ ሐምሌ 9 ቀን 1940 ዓ.ም የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አቡነ ዮሳብ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ አንድ መልእክት ላኩ። መልእክቱም የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያውያኑን አባቶች ለመሾም መወሰኗን የሚገልጥ ነበር። በዚህም መሠረት ከሁለት ዓመታት በፊት ተመርጠው ይሾሙ ዘንድ ወደ ካይሮ ሔደው የነበሩት አምስት አባቶች እንደ ገና ወደ ካይሮ ሔዱ።



እንደ ደረሱም ኢትዮጵያውያኑ በተስማሙበት አንድ ፕሮቶኮል ላይ ፈርመው ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም ካይሮ ላይ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ እጅ ተቀብተው ጳጳሳት ሆኑ። ከተፈራረሙበት ፕሮቶኮል ውስጥ «አንድ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳሳት ከመሾሙ በፊት አሁን በአፈሴል ሲቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ተብለው የሚታወቁት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ማረፍ አለባቸው» የሚል ይገኝበታል።

ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም ሥርዓተ ሢመት ተፈጽሞላቸው ሐምሌ 22 ቀን 1940 ዓ.ም አዲስ አበባ የገቡት ኢትዮጵያውያን አባቶች የሚከተሉት ነበሩ።

1. ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ፡- አቡነ ባስልዮስ፤
2. መምህር ገሪማ ወልደ ኪዳን፡- አቡነ ሚካኤል፤
3. ሊቀ ሥልጣናት መልእክቱ ወልደ ማርያም፡- አቡነ ቴዎፍሎስ፤
4. መምህር ዘፈረ ብርሃን ገብረ ጻድቅ፡- አቡነ ያዕቆብ፤
5. መምህር ጌታሁን ወልደ ሐዋርያት፡- አቡነ ጢሞቴዎስ፤

ከሦስት ዓመታት በኋላ ግብፃዊው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ ሲያርፉ ቀደም ሲል በተፈረመው ፕሮቶኮል መሠረት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ በብፁዕ አቡነ ዮሳብ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው ተሾሙ። ይህም ለዘመናት እልህ አስጨራሽ ክርክር ላደረገችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ቤተ መንግሥት ከፍ ያለ ደስታን ፈጠረ።

ብፁዕነታቸው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው በተሾሙ ጊዜ የያኔው አለቃ መሐሪ ትርፌ /በኋላ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ/ የሚከተለውን ዋዜማ ቅኔ ተቀኙተውላቸው ነበር።

*ይግባዕ ተኀፊሮ ዘበኒቅ.ዖ ቀነጸ ነዳዮ አእምሮ መንፈስ*
*ባስልዮስ አምጣነ ገዘማ ለሥርዋዕ በለስ*
*እስከነ በጎዳግ ይጸሐፍ ሥርዋዐ ዚአሁ ሐዲስ*
*ከመስ ኢንበል በመጽሐፍ ቅዱስ*
*ሥርዋፅነ ማኀበቅት ወርእስ።*

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ይህንን ታላቅ መዓርግ ተቀብለው ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ከፍ ያለ አቀባበል ተደረገላቸው። በነበራቸው ሥልጣንም ነሐሴ 28 ቀን 1943 ዓ.ም ተመርጠው የቀረቡ አምስት አባቶችን ጳጳሳት አድርገው ሾሙ። በዚህ ዕለት የተሾሙት አባቶችም የሚከተሉት ነበሩ።

1. መምህር ዘፈረ ብርሃን፣ አቡነ ታዴዎስ ተብለው፤ የጐሬ ጳጳስ፣
2. ጸባቴ ተክለ ጊዮርጊስ፣ አቡነ ገብርኤል ተብለው፣ የወሎ ጳጳስ፣
3. ሊቀ ሊቃውንት ገብረ እብ፣ እቡነ ፊልጶስ ተብለው፣ የኢየሩሳሌም ጳጳስ፣
4. መምህር ገብረ አምላክ፣ አቡነ ማርቆስ ተብለው፣ የኤርትራ ጳጳስ፣
5. መምህር ገብረ ጊዮርጊስ፣ አቡነ ጎርጎርዮስ ተብለው፣ የከፋ ጳጳስ፣

ከላይ ከተጠቀሱት እባቶች ውስጥ በኤርትራ የተሾሙት መምህር ገብረ አምላክ በጠላት ወረራ ዘመን በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት መራጭነት በብፁዕ አቡነ እብርሃም ከተሾሙት አባቶች አንዱ ሲሆኑ በዚህኛውም ያው ጳንቆላቸው ተሹመዋል። እንዲሁም በቁጥር 4 እና 5 የተቀመጡት አባቶች ብፁዕ አቡነ አብርሃም ካረፉ በኋላ ብፁዕ እቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ሲሆኑ መስከረም 1 ቀን 1932 ዓ.ም የሾሟቸው ነገር ግን ከላይ በተገለጠው ዓይነት ስሁለቱ ሀገራት ፖለቲካዊ ግንኙነት ሥምረት ሲባል ከሥራ ታግደው የቆዩና በዚህኛው ዓመት ሹመታቸው የጸናላቸው ናቸው።

ከእራት ዓመታት በኋላ የትግሬ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ እቡነ ይስሐቅ ነሐሴ 3 ቀን 1947 ዓ.ም ዐረፉ። በዚህም የተነሣ ሐምሌ 21 ቀን 1948 ዓ.ም በወቅቱ የእክሱም ንቡረ ዕድ የነበሩት ንቡረ ለድ ገብረ መስቀል በብፁዕ እቡነ ባስልዮስ እንብሮተ ዕድ እቡነ ዮሐንስ ተብለው ተሹመው የትግሬ ጳጳስ ሆኑ።

በዚህ ዓይነት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደ ፍላጐቷና እንደ ሕዝቧ ጥያቄ ኤጲስ ቆጳሳትንና ጳጳሳትን እየሾመች ለአገል ግሎት በማሠማራት የስብከተ ወንጌል አገልግሎቷን ማስፋፋቷን ቀጠለች። ይህ በእንዲህ እንዳለም በ1948 ዓ.ም በግብፅ ቤተ ክርስ ቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አባላት መካከል መስየየት ተከስተ። በዚህም የተነሣ ፓትርያርኩን በተቃወሙ እባላት ምክንያት የግብጽ ቤተ



ክርስቲያን ፓትርያርክ የነበሩትና የሁለቱን አኀት አብያተ ክርስቲያ ናት ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ያደረሱት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ ከመንበረ ፓትርያርክነታቸው ተነሡ። የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ድርጊት በመቃወም ድምፅዋን አሰማች። አንድ በጉዳዩ መክሮ የሚመለስ ልዑክም ወደ ካይሮ ላከች። ይሁን እንጂ ፓትርያርኩን ከመንበራቸው ባወረዷቸው አባቶች እምቢታ የተነሣ ልዑኩ ያለ ውጤት ተመለሰ።

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነገሩን አቅልላ ባለማየትና በግብፅ ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ጉዳይ ያላትን ቦታ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሰባት አባላት ያሉት የብፁዓን ጳጳሳት ልዑክ ወደ ካይሮ ላከች። ልዑኩም በቀጥታ ፓትርያርኩ ተቀምጠ ውበት ወደ ነበረው ገዳመ ቍስቋም በመውረድ በፓትርያርኩ ወገን ከነበሩት ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጳሳት ጋር በመሆን በሁኔታው ላይ ሰፊ ውይይት አደረገ። በውይይቱ መጨረሻም ፓትርያርኩ ወደ መንበራቸው እንዲ መለሱ የሚል የጋራ ውሳኔ እሳለፉ። በውሳኔውም መሠረት ኢትዮጵያውያኑ ጳጳሳት ከግብፃውያኑ ጳጳሳት ጋር በመሆን ፓትርያርኩን ይዘው ወደ ካይሮ ሲሔዱ ፓትርያርኩ ወደ መንበራቸው መመለስ እንደማይችሉ ተገለጸላቸው። ኢትዮጵ ያውያኑ እባቶች ከዚህ በኋላ ምንም ሊያደርጉ እንደማይችሉ በመገን ዘባቸው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልዑኳ ካለ ፍሬ ከተመለስ በኋላ ጉዳዩን በርቀት እየተከታተለች መፍትሔ የሚገኝበትን መንገድ ስታፈላልግ ፓትርያርኩ አቡነ ዮሳብ ኅዳር 4 ቀን 1949 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት እንደ ተለዩ ተሰማ። በዚህም መሠረት በእርሳቸው መንበር የሚተካውን ፓትርያርክ ለመምረጥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መራጭ ወኪሎችን እንድትልክ ሀቃቤ መንበር ሆነው በተመረጡት አቡነ አትናቴዎስ አማካይነት ግብዣ መጣላት። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በፓትርያርክ ምርጫ ላይ ያላት አግባብ በግልጽ ያልተወሰነ በመሆኑ፤ ባለፉት ፓትርያርክ ላይም ያደረጋችሁት አድራጐት ጥሩ ባለመሆኑ እናዝናለን» በማለት ግብዣ ውን እንደ ማይቀበለው አሳወቀ።

የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አቡነ ቄርሎስን 116ኛ ፓትርያርክ አድርጐ ሾመ። በዚህ የተነሳም በኢትዮጵያና በግብፅ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የነበረው ግንኙነት ተቋርጦ ቆየ። ነገር ግን ከጥቂት ጊዜያት በኋላ አዲሱ ፓትርያርክ ባልተጠበቀ ሁኔታ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን መዓርግ ወደ ፓትርያ ርክነት ደረጃ ከፍ ለማድረግ ያሰቡ መሆናቸውን የሚያትት ደብዳቤ

www.ethiopianorthodox.org

አስይዘው ሦስት ጳጳሳትንና አራት ምእመናንን ወደ እዲስ አበባ ላኩ።

መልእክተኞችም አዲስ አበባ ላይ ከቤተ ክህነትና ከቤተ መንግሥት ሰዎች ጋር ሰፊ ውይይት ሲያደርጉ ከሰነበቱ በኋላ ወደ አንድ ስምምነት በመድረስ የውል ስምምነት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ተፈረመ። በስምምነቱም መሠረት በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት የነበሩት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሰኔ 21 ቀን 1951 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ተቀብተው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው ተሾሙ። በሥነ ሥርዓቱም ላይ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተገኝተው ነበር።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ለእርሳቸውም ሆነ ለሀገራችን የመጀመሪያ የሆነውን ሥልጣነ ፓትርያርክነት ይዘው ሐምሌ 4 ቀን 1951 ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ። በዚህም ወቅት 21 ጊዜ መድፍ ተተኮሰ፤ በአዲስ አበባ የሚገኙ አድባራትና ገዳማትም በደወል ድምፅ ደስታቸውን አሰሙ። ምእመናንም በእልልታ አጀቧቸው።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ ነጻነቷን ዐውጃ፣ ከራሷ ልጆች ለዚህ ታላቅ አደራና ሐላፊነት የሚበቁትን እየመረጠች፣ ለአገልግሎትም እያሰማራች ሕዝቧን በማስተማርና በመባረክ ላይ ትገኛለች።



# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ዜና ፓትርያርኮች

### 2.1. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ቀዳማይ ፓትርያርክ /1884 - 1963 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የአጥቢያው መሪ ጌታ ከነበሩት አባታቸው ከደብተራ ወልደ ጻድቅ ስሎሞን፤ ከእናታቸው ከወይዘሮ ወለተ ማርያም ባዩ /በኋላ አማሆይ/ በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት፣ በመርሐ ቤቴ አውራጃ ሚዳ ሚካኤል ከተባለው ቦታ መጋቢት 14 ቀን 1884 ዓ.ም ተወለዱ:: እንደ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በዓርባ ቀናቸው ኮሶ ማርያም በተባለች በአጥቢያቸው ቤተ ክርስቲያን ተጠምቀው ገብረ ጊዮርጊስ ተብለው ስመ ክርስትና ተሠየሙ:: አባታቸው ባደረባቸው ሕመም ገና ከመወለዳቸው በፊት በማረፋቸው ወዲያውኑ ከመነኮሱት እናታቸው ጋር በክብካቤ አደጉ:: ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስም በዚያው በትውልድ ቀዬአቸው በምትገኘው አመልሳ ኮሶ ማርያም በተባለቸው ደብር ግብረ ዲቁና ተምረው ከግብፃዊው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ማቴዎስ መዓርገ ዲቁና ከተቀበሉ በኋላ በዚያው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግሉ ቆዩ::

ዕድሜያቸው 14 ዓመት ሲሆንም ወደ ፊት ለሚጠብቃቸው ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የትምህርት እና የሥነ ምግባር ዝግጅታቸውን ሊቀጥሉ ወደ ታላቁ ገዳም ደብረ ሊባኖስ ሔዱ:: በዚያም ሁለተኛውን ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርት /ጸዋትወ ዜማ/ ተምረው አጠናቀቁ:: በመቀጠልም የቅኔና የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርታቸውን ከመምህር ገብረ ኢየሱስ ተምረው በሁለቱም ተመረቁ:: ከዚህም ጋር የቅዳሴውን ትምህርት አባ ገብረ ሕይወት ከተባሉት አባት በሚገባ ተማሩ::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በተማሪነት ዘመናቸው በምግባራቸው እጅግ ትሑት እና ለትልቅ ለትንሹ ታዛዥ ስለ ነበሩ በመምህሮቻቸውና በጓደኞቻቸው እጅግ ፍቅርን የሚቸሩና የሚከበሩ ነበሩ::

ቅዱስነታቸው በዚህ ዓይነት ትምህርታቸውን በማስፋፋት፡ በገዳሙ ውስጥም በረድዕነት እየገለገሉ ሥርዓተ ገዳምን ሲማሩ ከቆዩ በኋላ ነሐሴ 24 ቀን 1905 ዓ.ም ልክ በሃያ አንድ ዓመታቸው በዚያው በደብረ ሊባኖስ ገዳም ሥርዓተ ምንኩስና ተፈጸመላቸው:: በዓመቱ በ1906 ዓ.ም ደግሞ ከግብፃዊው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ማቴዎስ መዓርገ ቅስና ተቀበሉ:: ቅዱስነታቸው ሥልጣነ ክህነት ከያዙ በኋላ በዚያው በገዳሙ የደከሙ አባቶችን በመርዳት፣ ሥርዓተ ገዳሙን በመጠበቅና በማስጠበቅ ለዓመታት ሲያገለግሉ ቆዩ:: ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከደብረ ሊባኖስ ተነሥተው ወደ ዓባይ ሸለቆ በመውረድ ዋሻ ሚካኤል በተባለ ቦታ ለሦስት ወራት ዘግተው በብሕትውና ቆዩ::

ከዚህ በኋላ በ1909 ዓ.ም በመጋቢት ወር በፍጹም



ብሕትውና ሊጸልዩ ከቆዩበት ዋሻ መንፈስ እግዚአብሔር አነሳሥቷቸው በርካታ ባሕታውያን በምናኔ ይኖሩበት ወደ ነበረው የመናገሻ ጋራ በመውጣት በዚያ የተባሕትዎ ሕይወታቸውን ቀጠሉ:: ከዚህም ጋር በጋራው የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ስለ ነበር በዚያ የቤተ መቅደስ አገልግሎትም እየሰጡ በትጋት ማገልገል ጀመሩ:: ይህ ደገኛ ተግባራቸው አብረዋቸው በሚኖሩት ባሕታውያንና በአካባቢው ምእመናን ዘንድ እየታወቀ ቅዱስነታቸውም በአገልግሎታቸው እየበረቱ ይህም ከአካባቢው አልፎ እስከ ቤተ መንግሥቱ ደረሰ:: በዚህ የተነሣም በ1910 ዓ.ም በግንቦት ወር ወደ ቤተ መንግሥት ተጠሩ:: ጥሪውን አክብረው ሲቀርቡም ግርማዊት ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ በመናገሻ ጋራ ላይ ያሉ ባሕታውያን በተበታተነ ሁኔታ መኖራቸውን አቁመው በማኅበር እየኖሩ ለሀገር ለወገን እንዲጸልዩ መፈለጋቸውን፣ ለማኅበሩ መመሥረት እንዲረዳም በጋራው ላይ የእመቤታችንን ቤተ ክርስቲያን ሊያሠሩ እንዳሰቡ፣ በሚመሠረተው ገዳምም ሆነ ቤተ ክርስቲያን ላይ በአልቅና እንደ ሚሾሟቸው፤ እስከዚያ ድረስ ግን ባሕታውያኑን በማሰባሰብ ሊያስተምሩ እና ሲመክሩ እንዲቆዩ አሳሰቧቸው::

ቅዱስነታቸውም የንግሥቷን ሐሳብ በሙሉ ፈቃደኝነት ተቀብለው ባሕታውያኑን እያስተማሩ ባለው የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ማኅበሩን መመሥረት ጀመሩ:: በዚህ እንቅስቃሴ ላይ እያሉም ንግሥቷ ያሠሯት የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን በመጠናቀቋ በ1916 ዓ.ም የገዳሟ መምህር ሆነው ተሾሙ:: ቅዱስነታቸው ይህን የመሰለውን የትሩፋት ሥራ ለመሥራት ዕድላቸው በለሆነ የቤተ መቅደሱን አገልግሎት በትጋት ከመስጠት ጋር ራሳቸውም ቅዳሴ ከማስተማር ጋር ሌሎች ጉባኤያት በገዳሙ እንዲዘረጉ፣ ማኅበረ መነኮሳትና ባሕታውያኑም ገዳሙን በማልማት እንዲተጉ ማድረጋቸውን ቀጠሉ:: በዚህ ዓይነት አገልግሎታቸውን በብቃት በማበርከት ላይ ሳሉ የካቲት 27 ቀን 1924 ዓ.ም ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ቤተ መንግሥት ጠሯቸው:: ንጉሡም ለምግባራቸውና ለአገልግሎታቸው ያላቸውን አድናቆት በመግለጽ፤ የመናገሻ ማርያም ገዳምን መምህርነት እንደ ያዙ የአዲስ አበባ መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤልን ደብር አለቅነት ሾሟቸው::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስም ሹመቱን በትሕትና ተቀብለው ሁለቱንም ቅዱሳት መካናት በትጋት ማስተዳደር ጀመሩ:: ይሁን እንጂ በዚህ ዓይነት ለሁለት ዓመታት ከቆዩ በኋላ በ1925 ዓ.ም ኅዳር ወር የከተማው ኑሮ ሲኖሩት ካሰቡት የትኅርምት ሕይወት ጋር ሊጣጣምላቸው ባለመቻሉ ግርማዊነታቸውን ከልመና ጋር አስፈቅደው የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ሹመታቸውን በማ

www.ethiopianorthodox.org

ሰረከብ ወደ መናገሻ ገዳም መምህርነታቸው ሙሉ በሙሉ ተመለሱ::

ቅዱስነታቸው በመናገሻ ተቀምጠው ቤተ ክርስቲያናቸውን እያገለገሉ በጾምና በጸሎት እየተጉ መኖር ፍላጎታቸው ቢሆንም ብዙም ሳይቆዩ እግዚአብሔር ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ሔደው እንዲያገለግሉ ፈቅዷልና መጋቢት 12 ቀን 1926 ዓ.ም በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ራይስ ሆነው ተሾሙ::

ብፁዕ ውቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በመናገሻ ማርያም ገዳም የጀመሩት አገልግሎትና በዚያ ያሉ ማኅበረ መነኮሳት ፍቅር ቢያስቅ ቃቸውም፤ ንጉሡ ከመከሯቸው ምክርና ከጣሉባቸው አደራ ታላቅነት ጋር የተሾሙበት ቦታ ቅድስና ስለ ከበዳቸው ሹመቱን በአኩቴት ተቀብለው ወደ ኢየሩሳሌም ሔዱ:: በዚያም መቀመጫቸውን ከታላ ቁ የኢትዮጵያ ገዳም ዴር ኤል ሡልጣን ገዳም አድርገው የተሾሙብ ቸውን ዘጠኝ የኢትዮጵያ ገዳማት በሚገባ ሲያስተዳድሩ ቆዩ::

ከሁለት ዓመታት በኋላ ቅዱስነታቸው የካቲት 11 ቀን 1929 ዓ.ም ከግርማዊነታቸው በተጻፈ የቴሌግራም መልእክት በአስቸ ኳይ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ተጠሩ:: ቅዱስነታቸው ጥሪውን በመቀበል ከ10 ቀናት የባቡርና የመኪና ጉዞ በኋላ የካቲት 21 ቀን አዲስ አበባ ገብተው ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀርበው እጅ ነሡ:: ከዚያም ማረፊያ ተሰጥቶአቸው ለሦስት ቀናት ከቆዩ በኋላ ለዕጨጌነት መዓርግ ታጭተው ኖሮ አዲስ አበባ በገቡ በአራተኛው ቀን /የካቲት 24/ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወርኃዊ መታሰቢያ ዕለት በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ «ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ዘነበረ በመንበረ ተክለ ሃይማኖት» ተብለው የታላቁ የደብረ ሊባኖስ ገዳም 59ኛ እጨጌ ሆነው ተሾሙ::

ይሁን እንጂ ቅዱስነታቸው በታላቁ መንበር ተቀምጠው አገልግሎታቸውን ገና ከመጀመራቸው ወራሪው የኢጣሊያ ጦር በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በኩል ኢትዮጵያን በግፍ መውረሩ ተሰማ:: ይህን የሰሙት ግርማዊ ጃንሆይም መኳንንቱንና መሣፍንቱን አስከት ለው ወራሪውን ኃይል ለመመከት ወደ ማይጨው ቢወርዱ ቅዱስነ ታቸውም ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጋር የቃል ኪዳኑን ታቦት ይዘው ወደ ማይጨው ጦርነት ወረዱ::

ምንም እንኳን ከንጉሡ ጀምሮ በግንባሩ የነበሩት መላው የኢትዮጵያ አርበኞች በቆራጥነት ቢዋጉም ጠላት በተጠቀመበት የመርዝ ጋዝ የተነሣ በማይጨው ጦርነት ድል ለኢትዮጵያውያን ልትሆን አልቻለችም:: በዚህ ጦርነት የቅዱስነታቸው በቅሎ ከጠላት በተተኮሰ ጥይት ተመትታ እንደ ነበር ይነገራል::

በዚህ ጊዜ የጠላት ጥይትና የመርዝ ጋዝ የበለጠ ብዙ ሰው



ከሚፈጅ ወደ ኋላ መመለሱ የተሻለ እንደ ሆነ የቤተ ክህነቱም ሆነ የቤተ መንግሥቱ ባለሥልጣናት ሐሳባቸውን ለንጉሡ ቢያቀርቡም ንጉሡ እዚሁ እሞታለሁ ብለው እንቢ አሉ ይባላል:: ይሁን እንጂ በንጉሡም ሆነ በቤተ ክህነቱ ከፍተኛ ተሰሚነት የነበራቸው ቅዱስነታቸው፤ ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ ምክሩን በእሺታ ተቀብለው ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ አድርገዋል ይባላል:: ንጉሠ ነገሥቱ ሐሳቡን ተቀብለው እንዲመለሱም አውግዣለሁ ብለው ነበር ይባላል::

በዚህ ዓይነት ንጉሡና ተከታዮቻቸው የበላይነትን ማግኘት ባለመቻላቸው ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ቅዱስነታቸውም አብረው ተመለሱ:: አዲስ አበባ እንደ ደረሱም በነበራቸው ቅርበት በአገር ውስጥ መቆየታቸው ጉዳት እንጂ ጥቅም እንደ ሌለው ይልቁንም ወደ ውጭ ሔደው ለኃያላኑ መንግሥታት በሀገራቸውና ሕዝባቸው የተፈጸመባቸውን የግፍ ተግባር እንዲያስረዱ በመምከር ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ ከሀገር እንዲወጡ አደረጉ:: እርሳቸውም ስደተኛውን ታቦት ይዘው አብረው ወጡ:: ግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ከኢትዮጵያ እንደ ወጡ ያመሩት ወደ ኢየሩሳሌም ነበር:: በዚያም ጥቂት ቆይታ አድርገው ወደ ታላቋ ብሪታንያ ሲሔዱ ቅዱስነታቸው ከእቴጌ መነንና ንጉሡን ተከትለው ከሔዱ ሌሎች መኳንንትና መሣፍንት እንዲሁም ታማኝ ወታደሮች ጋር በዚያው ቀሩ::

ንጉሡ ወደ ለንደን ከሔዱ በኋላ ቅዱስነታቸው ከእቴጌና ሌሎች መኳንንት ጋር በመሆን ከጸሎት ጀምሮ ለኢትዮጵያ ነጻነት መመለስ መሆን ያለበትን ሁሉ ማድረግ ጀመሩ:: በዚህም ለንደን በሚገኙት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና በሀገር ውስጥ ከጠላት ጋር የሞት ሽረት ትግል እያደረጉ ባሉት አርበኞች መካከል ሆኖ መረጃ የሚያቀብል አንድ የ«ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ማኅበር» እንዲ ቋቋም አደረጉ:: በተጨማሪም ንጉሡም ባሉበት የሀገሪቱን ችግር ለዓለም ሕዝብ እንዲያሰሙ፡ ሀገር ቤት ያሉት አርበኞችም «ተጋድሎአችሁ ለሃይማኖታችሁ፣ ለሀገራችሁ፣ ለባንዲራችሁ ነው:: በዚህም ብታልፉ ሰማዕታት ናችሁ:: በጉንፋንና በወረርሽኝ የምትወሰድ ነፍሳችሁን ለሀገራችሁ አትንፈጓት:: በርቱ!!» የሚሉ ደብዳቤዎች በራሳቸው እጅ እየጻፉ ወደ ኢትዮጵያ ይልኩ ነበር:: ለንደን ላይ ሀገራቸው ኢትዮጵያ በግፍ መወረሯን በቻሉት መንገድ ሁሉ ለዓለም ማኅበረሰብ ሲያሰሙ የነበሩት ንጉሠ ነገሥቱም በኢየሩሳሌም ይገኝ የነበረውን ታቦተ መድኃኔ ዓለምን /ስደተኛው መድኃኔ ዓለም - በአዲስ አበባ ምስካዬ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም የሚገኝ/ ከቀዳሲያን ካህናት ጋር ወደ ለንደን እንዲ ልኩላቸው ለቅዱስነታቸው ላኩባቸው::

www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስነታቸውም ሳይውሉ ሳያድሩ ታቦተ መድኃኔ ዓለምን በአባ ሐና ጅማ አማካይነት ከአምስት ካህናት ጋር ላኩላቸው:: ይህ ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም የሔደው በ1895 ዓ.ም በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ትእዛዝ መምህር ፈቃደ እግዚእ የተባሉ መምህር በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ገዳማት ራይስ ሆነው ሲሔዱ እንደ ነበር ይነገራል::

ኢትዮጵያ ከአምስት ዓመታት ወረራ በኋላ በብሪታንያ ርዳታ ነጻ እንደ ምትወጣ ከስምምነት ላይ ሲደረስ ንጉሡ ከብሪታንያ ገሥግሠው ሱዳን ደረሱ:: ይህን የሰሙት ቅዱስነታቸው፣ ሰኔ ዘጠኝ ቀን 1932 ዓ.ም ከክቡር ፊታውራሪ ብሩና ከሌሎችም ታላላቅ መኳንንት ጋር ከኢየሩሳሌም ተነሥተው ወደ ሱዳን በመጓዝ ከግርማዊነታቸው ጋር ተገናኙ:: በሱዳን ቆይታ ካደረጉ በኋላ ንጉሡ በድል አድራጊነት ወደ ኢትዮጵያ ጉዟቸውን ሲጀምሩ ቅዱስነ ታቸውም አብረው በመጓዝ ጥር 12 ቀን 1933 ዓ.ም ብዙዎች የተ ሠውላት ሰንደቅ ዓላማችን አሜድላ ላይ በግርማዊነታቸው ስትተከል ጸሎተ ቡራኬ አድርገዋል ይባላል:: ከዚያም በኋላ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ሳይለዩ ከአሜድላ ጀምረው ተጉዘው ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ::

ነጻነት ተመልሶ ቤተ መንግሥቱ ሀገሪቱን የመገንባት መርሐ ግብር አውጥቶ ሲንቀሳቀስ ቅዱስነታቸውም በነበራቸው የዕጨጌነት ሥልጣንና ሓላፊነት ቤተ ክርስቲያኗን መልሶ የመገንባት እንቅስቃሴ ያቸውን ቀጠሉ:: በዚህ ረገድ በተለይ የሚጠቀሰው ሥራ በ1936 ዓ.ም ከንጉሡ ጋር በነበራቸው ቅርርብ ቤተ ክርስቲያኗ በወረራው ከደረሰባት ጉዳት እንድታገግም እና ለኢትዮጵያውያን የምትሰጠው አገልግሎት እንደ ቀድሞው የተሟላ እንዲሆን ከቤተ መንግሥቱ ርስት ጉልት እንድታገኝ አድርገዋል::

ቅዱስነታቸው ከዚህም ጋር በጦርነቱ ከፉኛ ወደ ተጎዱት አብያተ ክርስቲያናት ሔደው እየጎበኙና ካህናቱንና ምእመናኑን በምክር እያረጋጉ እንዲሁም የፈረሱት እንዲጠገኑ፣ የወደሙት እንዲ ተኩ ገንዘብ በመርዳት ሰፋ ያለ እንቅስቃሴ አድርገዋል:: በተለይ በ1935 ዓ.ም ቤተ ክርስቲያኗ ከነበራት ርስትና ጉልት የሚገኘው ገንዘብ በቀጥታ ወደ ቤተ ክርስቲያኗ ካዝና እንዲገባ መንግሥትን በማስፈቀድ በገንዘቡ በየአውራጃውና ወረዳው መምህራን እንዲቀጠ ሩና አብነት መምህራን ድጎማ እንዲያገኙ አድርገዋል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ከነጻነት በኋላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት በጋራ ሆነው ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋር ባደረጉት ሰፊና ረጅም ውይይት እንዲሁም ክርክር በሁለቱ አብያተ



ክርስቲያናት ታሪክ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ካይሮ ሔደው ከተሾሙት ኢትዮጵያውያን አባቶች አንዱ በመሆን ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም «ብፁዕ አባ ባስልዮስ ጳጳስ ዘሸዋ ወለጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ» ተብለው በእስክንድርያው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ እንብሮተ ዕድ ተሾሙ:: በወቅቱ ኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳቱም ከእኔ ይሁን ብላ የነበረ ቢሆንም፣ ይህ መሆን ያለበት በሕይወት ካሉት ከኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ግብፃዊው አቡነ ቄርሎስ ዕረፍት በኋላ ነው የሚል ስምምነት ተደርሶ ነበር:: ከአራት ዓመት በኋላ ግን አቡነ ቄርሎስ እንዳረፉ ሲሰማ ቀደም ሲል በተደረገው ስምምነት መሠረት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ወደ ካይሮ ሔደው ጥር 6 ቀን 1943 ዓ.ም በአቡነ ዮሳብ አንብሮተ እድ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው ተሾሙ::

በሊቀ ጳጳሳትነት ቤተ ክርስቲያንን በሰፋት ሲያገለግሉ የቆዩት ቅዱስነታቸው በእርሳቸው መልካም አስተዳደርና በቤተ መንግሥቱ ድጋፍ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ነጻነቷን እንድታውጅ በመፍቀዷ ከ11 ዓመታት የሊቀ ጵጵስና አገልግሎት በኋላ ሰኔ 21 ቀን 1951 ዓ.ም ብፁዕ ወቅዱስ ተብለው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው ተሾሙ::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በዘመነ ሥልጣናቸው ለቤተ ክርስቲያኗ ሰፋ ያለ አገልግሎት አበርክተዋል:: ቤተ ክርስቲያኗ በልማት እንቅስቃሴዋ እንድትጠናከር፣ ከዓለም ዐቀፉ ማኅበረሰብ ጋር የሠመረ ግንኙነት እንዲኖራት፣ ምእመናን በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንዲተዳደሩ፣ ቀደም ሲል ሥርዓት ሳልተሠራላቸውም ሥርዓት እንዲሠራላቸው በማድረግ /ለምሳሌ:- የልቅሶ ሥርዓት/፣ በቅዱስ ሲኖዶስ በብቃት እንድትመራ በማድረግ ሰፋ ያለ አገልግሎት አበርክተዋል::

ስብከተ ወንጌል አገልግሎት መፋጠንም በ1948 ዓ.ም የስብከተ ወንጌል ድርጅትን ከማቋቋም ጋር በዘመነ ፓትርያር ክነታቸው አስራ ሰባት የሚደርሱ ኤጲስ ቆጶሳትን በመሾም፣ የቤተ ክርስቲያኗንም አህጉረ ስብከት ዓሥራ ስድስት በማድረስ ታላቅ ሥራን ሠርተዋል::

ቅዱስነታቸው የቤተ ክርስቲያኗ ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲፋጠን ከፍተኛ ፍላጎት ስለ ነበራቸው ማንም ይሥራው ማን እኔ ሳልፈቅድና ሳልመክርበት በሚል ስሥራ እንቅፋት እንዳልነበሩ በቅርብ የሚያውቋቸው ሊቃውንት ይመሰክራሉ:: በዚህ የተነሣ ከእሳቸው ጋር በነበሩ የቤተ ክህነቱ ሠራተኞች በርካታ የልማት ሥራዎች ተሠርተዋል:: በዚህ ረገድም ዛሬም ቤተ ክርስቲያኗን እያገለገሉ ያሉ ብዙዎቹ ሕንፃዎችና መኖሪያ ቪላዎች የተሠሩት

www.ethiopianorthodox.org

በእሳቸው የአገልግሎት ዘመን ነው። ቅዱስነታቸው ሥራው ተጠናቅቆ ለቡራኬ ሲጠሩ ከቦታው ድረስ በመገኘት አባታዊ ቡራኬያቸውን ሰጥተው ሠራተኞቹን አመስግነውና እድንቀው ሽልማት ለሚገባው ሽልማት ሰጥተው ይመለሱ ነበር።

ወቅቱ በሚጠይቀው አስተዳደር መሠረት ሹመት፣ ርስትና ጉልት ወዘተ. ፈልገው ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነቱ መጥተው ለረጅም ጊዜያት ደጅ ሲጠኑ የሚቆዩ ሊቃውንት ነበሩ። ታዲያ እነዚህ ደጅ ጠኚዎች እንዳይቸገሩ ቅዱስነታቸው በየጊዜው ግብር እያደረጉ ይመግቡ፣ ማረፊያ እንዲያገኙም ያደርጉ ነበር ይባላል። በተለይ ቅዱስነታቸው ከምንም በላይ ለቅድስናና ለሊቅነት ከፍተኛ ቦታ ይሰጡ ስለ ነበር በአካባቢያቸው በቅድስናቸውም ሆነ በሊቅነታቸው ለተመሰከረላቸው አባቶች ርስት ጉልት እንዲሰፈርላቸው ያደርጉ ነበር ይባላል። በዚህ ረገድ በተለይ ደብረ ጽጌ ላይ ዛሬም ሲዘከር የሚኖር ሥራ እንደ ሠሩ ይነገራል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በቤተ መንግሥቱ በነበራቸው ከፍተኛ ተቀባይነት የተነሣ በመኳንንቱና መሣፍንቱ፣ በልዑል ታቱና ወይዛዝርቱ መካከል የሚፈጠርን ማንኛውንም ዓይነት ቅራኔ በቀላሉ ይፈቱና ዕርቅ ይመሠርቱ ነበር ይባላል። በተለይ ከፖለቲካዊ ቅራኔ በመለስ ማንም ንጉሠ ነገሥቱ ግንባራቸውን መለሱብኝ የሚል ባለ ሥልጣን ምልጃን ሲሻ ሮጦ የሚመጣው ወደ እሳቸው ነበር ይባላል።

ቅዱስነታቸው ከቤተ መንግሥቱ ጋር የነበራቸውን ቅርርብና ታማኝነት በይፋ የመሰከረ ድርጊት የፈጸሙት በ1953 ዓ.ም የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ወቅት ነበር ይባላል። በጄኔራል መንግሥቱ ንዋይና ግርማሜ ንዋይ የተመራው የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ተፋፍሞ ቤተ መንግሥቱ በተናጋበት ጊዜ ቅዱስነታቸው ከመንበረ ፓትርያርክናቸው ሆነው «ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዓፄ ኃይለ ሥላሴ የማትገዛ እውግዝሃለሁ፤ ጠብ መንጃህን ጣል» የሚል መልእክት ያዘለ ደብዳቤ ጽፈው በከተማዋ በሄሊኮፍተር እንዲበተን አድርገው ነበር። ይህንን ውግዘታቸውን ተከትሎም ሁሉም ባይሆን መፈንቅለ መንግሥቱን ይደግፉ የነበሩ የክቡር ዘበኛ አባላት ጠብ መንጃቸውን ጥለዋል ይባላል። በዚህ ጊዜ መፈንቅለ መንግሥቱን ይመሩ የነበሩት ሰዎች «ከጄኔራሎቹ የበለጠ እኛን የጎዳን ይህ መነኩሴ ነው» ብለው ነበር ይባላል። መፈንቅለ መንግሥቱ ከከሸፈ በኋላም እንቅስቃሴውን ይደግፉ የነበሩ ሰዎችና ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ቅራኔ የነበራቸው አካላት ቅዱስነታቸውን የቤተ መንግሥቱ ቀኝ እጅ አድርገው ይመለከቷቸውና ይጠሏቸው ነበር ይባላል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በቤተ ክህነቱም ሆነ በቤተ መንግሥቱ በነበራቸው ላቅ ያለ አገልግሎት የተነሣ የግርማዊ



ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴን የመጀመሪያ የክብር ኮከብ ኒሻን ተሸልመዋል። ይህ ኒሻን ቅዱስነታቸው ባረፉ ጊዜ ወደ ቤተ ክህነት ሳይሆን ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመልሶ እንደ ገባ ይነገራል።

ቅዱስነታቸው በሕይወታቸው የመጨረሻዎቹ ዓመታት በነበረባቸው ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ የስኳር ሕመም የተነሳ ዓይናቸውን ታውረው አልጋ ላይ ዋሉ። በእርግጥ የዓይናቸው መታወር ምክንያት ጣና ገዳማትን ሊጎበኙ ወደ ዚያው በሔዱ ጊዜ በባሕር ላይ በጀልባ ሲጓዙ የውኃ ነጸብራቅ ዓይናቸውን ስለ ጎዳቸው ነው ይባላል። ቤተ ክርስቲያኗም ሆነች ቤተ መንግሥቱ የሚቻለውን ሕክምና ሁሉ አግኝተው ጤናቸው እንዲመለስ ከፍተኛ ጥረት ቢደረግም ፈውስን ሊያገኙ አልቻሉም። በመጨረሻም ለተመሳሳይ የሕክምና አገልግሎት ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው ከተረዱ በኋላ ይዘዋቸው የሔዱት አባቶች እንመለስ ቢሉ «እኔ ከእንግዲህ ወደ ኢትዮጵያ አልመለሰም፤ እዚሁ እቀበራለሁ» በሚል እንቢታቸውን ገልጸው ለጥቂት ጊዜ እዚያው ቆዩ። ነገር ግን ይህንን የሰሙት ንጉሠ ነገሥቱ በእንደራሴነት ያገለግሉ የነበሩትን ብፁሰ /በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ/ አቡነ ቴዎፍሎስን በአማላጅነት ልከው አስመጧቸው።

ይሁን እንጂ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ብዙም ሳይቆዩ ሰኞ ጥቅምት ሁለት ቀን 1963 ዓ.ም ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት በተወለዱ በ79 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ዜና ዕረፍታቸው እንደ ተሰማ በመላ ሀገሪቱ 12 ብሔራዊ የኀዘን ቀናት ታውጆ ሰንብቷል። ሥርዓተ ቀብራቸውም ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ እና ብፁዓን አባቶች እንዲሁም መኳንንቱና መሣፍንቱ በተገኙበት ፈደል ቆጥረው ባደጉበት የደብረ ሊባኖስ ገዳም ጥቅምት 4 ቀን 1963 ዓ.ም ተፈጸመ። የቅዱስነታቸው በረከት ከሁላችን ጋራ ይሁን። አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## 2.2. ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ

## ካልአይ ፓትርያርክ

## /1902 - 1971 ዓ.ም/





ሊቀ ሥልጣናት መልአክቱ ወልደ ማርያም ይባሉ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በቀድሞው የጎጃም ጠቅላይ ግዛት፣ በደብረ ማርቆስ አውራጃ፣ በማቻከል ወረዳ፣ ደብረ ገነት ኤልያስ በሚባል ታላቅ ደብር ሚያዝያ 16 ቀን 1902 ዓ.ም ተወለዱ:: የአባታቸው ስም አቶ ጀንበሬ ውቤ፤ የእናታቸው ስም እመት ዘር ትሁን አደላሁ ይባል ነበር::

በወላጆቻቸው ክብካቤ በመንፈሳዊ የልጆች አስተዳደግ ሥርዓት ያደጉት ቅዱስነታቸው ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በተወለዱበት አጥቢያ በደብረ ኤልያስ ከአያታቸው ከወ/ሮ ሙሉ ነሽ ወዳጄ ነህ ጋር እየኖሩ ከመሪ ጌታ ረዳኸኝና ግራ ጌታ ሣህሉ ዘንድ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን በሚገባ ተማሩ:: ከዚያም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ከነበሩት ግብፃዊው አቡነ ማቴዎስ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ዲቁናቸውን ከተቀበሉ በኋላ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ገይማ ጊዮርጊስ በሚባለው ቤተ ክርስቲያንና በደብረ ኤልያስ በዲቁና ሲያገለግሉ ቆዩ:: ከማገልገልም ጋር በዚያው ፈደል ቆጥረው ዜማ በዘለቁበት ታላቁ ደብር /ደብረ ኤልያስ/ ከታላቁ ሊቅ ከመምህር ገብረ ሥላሴ ቅኔ ከነአገባቡ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ:: ትምህርታቸውንም በመቀጠል ከተጠቀሱት መምህር ውዳሴ ማርያምን፣ ቅዳሴ ማርያምንና የወንጌል ትርጓሜን በሚገባ አሔዱ::

ቅዱስነታቸው በተማሪነታቸው የነበራቸውን ቀለም የመ ቀበል ፍጥነት መምህሮቻቸውና ባልንጀሮቻቸው ያደንቁ ነበር ይባላል:: የጸዋትወ ዜማ ትምህርታቸውን በአጭር ጊዜ ካጠናቀቁ በኋላ ቀጥሎ የሚመጣው የቅኔ ትምህርትም በመደበኛ መልኩ የሚጠይቀውን ያህል ጊዜ አልወሰደባቸውም ነበር:: ስቀስም ብሩህ የነበረው አእምሮአቸው ቅኔን በአጭር ጊዜ እንዲቀኙ አስቻላቸው:: በቅኔ ስለ ነበራቸው ልዩ ስጦታ የትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው በአያሌው ያደንቋቸው ነበር:: በደብረ ኤልያስ ማኅሌት በሚቆሙበት ሰዓት የሚቀኙ ተማሪዎች ወይም መሪ ጌቶች እሳቸው ካሉ ይፈሩ ነበር ይባላል:: ከፍርሃታቸውም የተነሣ ቅዱስነታቸው ዓይናቸውን ገለጥ አድርገው ያዩአቸው እንደ ሆነ ቅኔው ጭራሹኑ ይጠፋቸው ስለ ነበር «አባክህ መልአክቱ፣ ስንቀኝ አትየን፤ ይጠፋብናል» ይሏቸው እንደ ነበር ስለ እሳቸው የተጻፉ መዛግብት ያስረዳሉ::

ቅዱስነታቸው እንዲህ መሪ ጌቶችንም ጭምር የሚያስፈራ ዕውቀት እንደ ነበራቸው ሁሉ ማንኛውንም ትምህርት ለመማር የፈጠኑ፤ የተማሩትንም በተግባር የሚያሳዩ ብልህ አባት እንደ ነበሩ

www.ethiopianorthodox.org

## 2.2. ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ

## ካልኣይ ፓትርያርክ

## /1902 - 1971 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

ይነገራል:: አንድ ጊዜ የደብረ ኤልያስ ቤተ ልሔም በማፍሰሱ ሳር ታጭዶ ከመጣ በኋላ ለጊዜው የሚከድን ባለ ሞያ ጠፋ:: በዚህ ወቅት ተማሪ መልእክቱ እኔ እከድነዋለሁ ብለው ቤተ ልሔሙን አሳምረው ከፍክፈው ስለ ከደኑት ቤቱ ለብዙ ዓመታት ሳያፈስ ኖሯል ይባላል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በዚህ ዓይነት በመምህሮ ቻቸውና በጓደኞቻቸው ተፈቅረውና ተከብረው እየተማሩ ለዓመታት ከቆዩ በኋላ የወደ ፊት የትምህርት ሕይወታቸውን በሚመለከት አንድ አሳብ መጣላቸው:: ይኸውም ምንም እንኳን ከወላጆቻቸውና ካሳደጓቸው አያቶቻቸው ጀምሮ እስከ መምህሮቻ ቸውና ባልንጀሮቻቸው ድረስ የሚፈልጉት የቅዱስነታቸውን በዚያው መቆየትና ጉባኤ ዘርግቶ ማስተማር ቢሆንም፤ ቅዱስነታ ቸው ወደ ሌላ ቦታ ሔደው ዕውቀታቸውን ለማስፋፋት ወሰኑ:: በመሆኑም ይህን ከፍተኛ የመማር ፍላጎት የወለደውን ውሳኔያቸ ውን ለማንም ሳያዋዩ በ1920 ዓ.ም በአንድ ቀን ሌሊት ጠፍተው በእግራቸው ወደ ሸዋ ገሠገሡ:: ከዚያም የቀረኝን ትምህርት አገኝበታለሁ ወዳሉት አዲስ ዓለም ማርያም ሔደው በወቅቱ በዚያ ያስተምሩ የነበሩትን ንቡረ ዕድ ሐዲስ ተክሌን /በኋላ አቡነ ዮሐንስ/ እጅ ነሥተው የጉባኤው አባል ሆኑ::

ቅዱስነታቸው አዲስ ዓለም ደርሰው ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተማሪዎች ይጐርፉላቸው ከነበሩት ንቡረ ዕድ ሐዲስ ተክሌ ጋር ቢተዋወቁ ንቡረ ዕድ «ታላቅ ሰው መጣ» አሉ ይባላል:: ወደ ጉባኤ ገብተው የቅዱስነታቸውን ትምህርት ተቀባይ ነት ካዩም በኋላ ከሌሎች ተማሪዎቻቸው ለይተው ምግብና መኝታ እንዲዘጋጅላቸው አድርገው በማስቀመጥ የልጅ ያህል እያቀረቧቸውና ለሥራም እያዘዟቸው መኖር ጀመሩ:: ቅዱስነ ታቸው በተማሪነታቸው ብስክሌት መንዳት ተምረው ስለ ነበር ንቡረ ዕድ ለአንዳንድ ጉዳዮች ወደ አዲስ አበባ ሲልኳቸው በብስክሌት እየተመላለሱ ጉዳይ ይፈጽሙላቸው ነበር ይባላል:: ተሹመው አዲስ አበባ ከመጡ በኋላም ብስክሌቷ አብራቸው እንደ ነበረችና በመጨረሻ ግን ለአንድ ወዳጃቸው እንደ በጡአት ይነገራል::

ከላይ እንደ ተገለጠው ቅዱስነታቸው ከደብረ ኤልያስ ተነሥተው ወደ አዲስ ዓለም የመጡት ወላጆቻቸውንም ሆነ መምህሮቻቸውን ሳያስፈቅዱና ሳይሰናበቱ በመሆኑ በቅዱስነታቸው ከአካባቢው መሰወር ያላዘነና ያልተጨነቀ አልነበረም:: በተለይ በአጠገባችን ተቀምጠ አይዞአችሁ ይለናል፣ ብናረጅ ይጦረናል፣



ብንሞት ይፈታናል፤ ይጸልይልናል ባሉት የመጀመሪያ ልጃቸው መጥፋት በእጅጉ ያዘኑት አባታቸው አቶ ጀንበሬ ውቤ ይሔዱበ ታል ባሉት ቦታ ሁሉ ማፈላለጋቸውን ተያይዘውት ነበር:: ታዲያ አቶ ጀንበሬ ጉዳዩን ሲያጠያይቁ ልጃቸው ያለበትን ቦታ ዐወቁ:: በዚህም በእጅጉ ተደስተው ወደ አዲስ ዓለም በመሔድ ከተገናኙ በኋላ «ወደ ሀገራችን እንሒድ፣ ይህንን ያህል የተስደድክበትን ዕውቀትም እዚያው ታገኘዋለህ» ብለው ቅዱስነታቸውን ጠ የቁአቸው:: ቅዱስነታቸው ግን የአባታቸውን ሐሳብ እንደ ማይቀ በሉት በአክብሮት በመግለጽ «አባቴ ሆይ፤ አሁን ፍትሐ ነገሥቱ ንም ሐዲሳቱንም ጨርሼ በመክለስ ላይ እገኛለሁ:: ከለሳውን ከጨረስኩ በኋላ እመጣለሁ» በማለት ሐሳባቸውን ገለጹላቸው:: አቶ ጀንበሬም ምንም እንኳን ከዓመታት ልቅሶ እና ኀዘን በኋላ ያገኟቸውን ልጃቸውን ትተው ለመሔድ ቢቸገሩም ባስረዷቸው ሐሳብ በመስማማት፤ የጀመሩትን ትምህርት ሲጨርሱ ግን ወደ ጎጃም እንዲመጡ ከተማኅፅኖ ጋር አደራ ብለው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አዲስ ዓለም ላይ በዚህ ዓይነት ትምህርታቸውን ሲያደላድሉ ከቆዩ በኋላ በ1930 ዓ.ም ወደ ደብረ ሊባኖስ በመውረድ መዓርገ ምንኩስናን ተቀበሉ:: ብዙም ሳይቆዩ ከአቡነ አብርሃም መዓርገ ቅስናን ተቀበሉ:: ቅዱስነታቸው ከዚህ በኋላ ከጎጃም ሸዋ ድረስ መጥተው ወደ ሀገራቸው ይሔዱ ዘንድ የለመኗቸው፤ በዚህም ከቅዱስነታቸው አንደበት የተስፋ ቃል ይዘው የተመለሱት አባታቸውም ሆኑ እናታቸው እንዲሁም ወዳጅ ዘመዶቻቸው ተስፋ ይቆርጡ ዘንድ መንኵሰው የተነሡትን ፎቶ ግራፍ አንዳንድ ቅጂ ለወላጆቻቸውና ለዘመዶቻቸው ላኩ ይባላል::

የቅዱስነታቸውን መመንኮስ ከፎቶ ግራፋቸው ያዩት ሁሉ በውሳኔያቸው ተደስተዋል:: ትምህርትም አግኝተዋል:: በተለይ አባታቸው ፎቶ ግራፉ እንደ ደረሳቸው ምንም እንኳን ለወዲያው በእጅጉ ቢደነግጡም «እንግዲህ ትላንት የወለድኩት ልጄ እንደዚህ ዓለሙን ንቆ የእንጦንስን ቆብ በመጫን ራሱን የክርስቶስ ሙሽራ ሲያደርግ እኔ ለምን በዓለም እደክማለሁ!?» በማለት ቤት ንብረታቸውን ትተው መንነዋል:: የአቶ ውቤ አድራሻ ለዓመታት ሳይታወቅ ቆይቶ በመጨረሻ በቤተ በዎቻቸው ፍለጋ እዚያው ጎጃም ውስጥ ሥርወ ኢየሱስ ከተባለ ገዳም ገብተው አባ ወልደ ማርያም በመባል ከቆዩ በኋላ በዚያው ማረፋቸው ተረጋገጠ::

የአባታቸውን ዜና ዕረፍት የሰሙትና በወቅቱ የመንበረ

www.ethiopianorthodox.org

ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሊቀ ሥልጣናት የነበሩት ቅዱስነታቸው ለአባታቸው ከነበራቸው ጽኑዕ ፍቅር የተነሣ በእጅጉ አዝነው እንደ ነበር በአሳቸው ሕይወት ዙሪያ የተጻፉ መዛግብት ይመሰክራሉ:: በዚህ ከባድ ኀዘናቸው የተነሣም ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ቤታቸው ድረስ በመሔድ አስተዛዝነዋቸዋል:: የአባታቸውን የመጨረሻ ሕይወት ለማስታወስም የአባታቸውን ስም ከጀንበሬ ወደ ወልደ ማርያም ቀይረው ይጠሩበት ነበር ይባላል::

የኢጣልያ ጦር ሀገራችንን በወረረ ጊዜ ቅዱስነታቸው በጣም ይወዷቸው ከነበሩትና በወረራው ጊዜ ከተሾሙት ኤጲስ ቆጶሳት አንዱና ኋላም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት ከነበሩት መምህራቸው ሐዲስ ተክሌ ዘንድ ስላልተለዩ በፈጣን የመማር ችሎታቸው የጣልያንኛና የእንግሊዝኛ ቋንቋን ተምረው እንደ ነበር ይነገራል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ኢትዮጵያ በኢጣልያ በተወረረችባቸው ዓመታት የቋንቋውን ትምህርት እየተማሩ የመምህራቸውና ከአቡነ አብርሃም ቀጥሎ ሊቀ ጳጳስ ተብለው ተሹመው የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ አርዌ ብርት ያዥ /ጸሐፊያቸውም ነበሩ ይባላል/ እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ዲያቆናት ሆነው እንደ ነበር ይነገራል::

ኢትዮጵያ ነጻነቷን ከተጎናጸፈች በኋላ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ የንቡረ ዕድ ሥልጣናቸውን እንደያዙ በአዲስ ዓለም ማርያም ገዳም እንዲቀመጡ ሲደረግ ቅዱስነታቸውም ወደዚያው በመሔድ ትምህርታቸውን ሲያጠናክሩ ቆዩ::

አዲስ ዓለም ላይ ጥቂት እንደ ቆዩም በቤተ መንግሥቱ ሙሉ ፈቃድ 1935 ዓ.ም በነበራቸው ትምህርት ወደ አዲስ አበባ ቢመጡ ብዙ ሊሠሩ እንደ ሚችሉ በለ ታመነበት ያኔ መካነ ሥላሴ ይባል ለነበረው ደብር መምህር ሆነው ተሾሙ:: ቆይቶም በ1938 ዓ.ም የመካነ ሥላሴ ደብር «መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል» ተብሎ በሊቀ ሥልጣናት ማዓርግ እንዲተዳደር ሲደረግ ቅዱስነታቸውም «ሊቀ ሥልጣናት አባ መልአክቱ» ተብለው ማስተዳደር ጀመሩ::

ቅዱስነታቸው በተቀበሉት ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን በአግባቡ በመጠቀም ሐላፊነታቸውንም በብቃት በመወጣት ለካቴድራሉ መልካም አስተዳደራዊ መዋቅርን ዘርግተዋል::



ከዚህም በተጨማሪ የካቴድራሉን ማኅበረ ካህናትና ምእመናንን በማስተባበርም ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን አከናውነዋል:: ይህ መልካም አርአያነት ያለው ተግባራቸውም በቤተ መንግሥቱም ሆነ በቤተ ክህነቱ እየታወቀ መጣ:: በዚህም በ1940 ዓ.ም ለመዓርገ ጵጵስና ተመርጠው ከተሾሙት አምስት አባቶች አንዱ ሆኑ::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በነበራቸው የቋንቋ ችሎታና የአርቆ አስተዋይነት ሀብት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ለዘመናት ተጭኖ የኖረው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የጫነት ቀንበር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተበብሮ እንዲወድቅ በማድረግ በታሪክ መዝገብ በወርቃማ ቀለም የተመዘገበ አስተዋጽኦ አበርክተዋል:: ጉዳዩን በሚመለከት በተለያዩ ጊዜያት ወደ ግብፅ በመሔድ ከአባቶች ጋር የተወያዩትን ልዑካን በመምራት ታሪክ የማይረሳውን ሥራ ሠርተዋል::

ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም በካይሮ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ እንብሮተ ዕድ ከተሾሙት አባቶች አንዱ የሆኑት ቅዱስነታቸው የቅድስት ሥላሴ ሊቀ ሥልጣናትነታቸውን ሳይተው «ጳጳስ ዘሐረር» ተብለው እስከ 1951 ዓ.ም አገልግለዋል:: ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በ1951 ዓ.ም የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው ከተሾሙ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በ1952 ዓ.ም የሊቀ ጵጵስናውን መንበር ተረከቡ::

በተመሰከረላቸው የአስተዳደር ብቃት ሀገረ ስብከታቸውን ከማስተዳደር ጋር ከ1943 ዓ.ም እስከ 1963 ዓ.ም ድረስ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ እንደ ራሴ በመሆን አገልግለዋል::

ቅዱስነታቸው በእነዚህ የአገልግሎት ዓመታት በፊና ለዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን መሠረት የጣሉ ሀበይት ሥራዎችን ሠርተዋል:: በነበራቸው ሠርቶ የማሠራት ጥበብና ችሎታ ወቅቱ የሚጠይቃቸው አስተዳደ ራ ዊ መዋቅሮች በቤተ ክህነቱ እንዲዘረጉ፣ መመሪያዎችና ደንቦችም እንዲወጡ በማድረግ የቤተ ክርስቲያኗ ሁሉን ዐቀፍ አገልግሎት እንዲጠናከር አድርገዋል:: ባህላዊና ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችን አቀናጅተው መርተዋል:: በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ በብከተ ወንጌል እንዲስፋፋ አድርገዋል:: በተለይ ቤተ ክርስቲያኗ ከቤላው ዓለም ጋር ያላት

www.ethiopianorthodox.org

ግንኙነት የተጠናከረ ይሆን ዘንድ የቤተ ክርስቲያኒቱን የውጭ ግንኙነት መርሕ በመቅረጽና በመተግበር ታሪካዊ አስተዋጽኦ አድርገዋል::

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በዘመነ እንደ ራሴነታቸው ከሠሯቸው ዐበይት ተግባራት የሚጠቀሰው የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደራዊ መዋቅር እንዲሻሻል በማድረግ በቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር ምእመናን ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችሏቸውን የሰበካ ጉባኤ ማደራጃና የሰንበት ት/ቤቶች ማስተባበሪያ የተሰኙት መምሪያዎች እንዲዘረጉ፤ በተጨማሪም የቅርስ ምዝገባና ጥበቃ መምሪያና የቤተ ክርስቲያኗ ልማትና ክርስቲያናዊ ተራድዖ ኮሚሽን እንዲዋቀሩ አድርገዋል:: በትምህርቱ መስክም በ1935 ዓ.ም የተቋቋመው የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ት/ቤት /አሁን ኮሌጅ/ የበላይ አስተዳዳሪና የቦርድ ሰብሳቢ በመሆን ት/ቤቱ እንዲጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርገዋል:: በሀገረ ስብከታቸውም በሐረርና በቁልቢ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ሁለት ዘመናውያን ት/ቤቶችን አቋቁመው በርካታ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች በመንፈሳዊና በዘመናዊ ትምህርት እንዲገነቡና ሀገራቸውን እንዲሁም ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲረከቡ አድርገዋል:: ምንም እንኳን ብዙዎቹ ተመልሰው የሠሯቸውን ኀመመልከት ባይታደሉም ተማሪዎች በሀገር ቤት በተከፈቱላቸው መንፈሳውያን ት/ቤቶች ከመማራቸው በተጨማሪ ወደ ውጭ እንዲሔዱና ከፍተኛ የነገረ መለኮት ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ አድርገዋል::

የቅዱስነታቸው የዘወትር ዓላማ ስብከተ ወንጌልና ትምህርተ ወንጌል ይስፋፋና ይጠናከር ዘንድ ነበረና በ1958 ዓ.ም የስብከተ ወንጌል ማስፋፊያ ፕሮግራም አውጥተው በአዲስ አበባና በተለያዩ አህጉረ ስብከት በመዘዋወር የስብከተ ወንጌል ድርጅት የሚባለውን አቋቁመዋል:: አስፋፍተዋልም:: ወደ ኋላ በጠቅላይ ቤተ ክህነቱ መምሪያ እንዲሁም በየአጥቢያው የተቋቋመው የሰበካ ጉባኤ ምንጩ ይኸው የቅዱስነታቸው እንቅስቃሴ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ የነገው የቤተ ክርስቲያን ተረካቢ ትውልድ ዝግጁ ሆኖ ይገኝ ዘንድ የወጣቶችን ማዕከላዊ ጽ/ቤት በመንበረ ፓትርያርኩ መሥርተው በየደብሩ ቅርንጫፍ የወጣቶች መንፈሳውያት ማኅበራት እንዲቋቋሙና የሰንበት ትምህርት እንዲስፋፋ አድርገዋል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ግንቦት 1 ቀን 1963 ዓ.ም በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ተተክተው በመንበረ ፓትርያርክነቱ ከተቀመጡም በኋላም ቀድሞም ቢሆን ሙሉ ተሳታፊ የነበሩበትን የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የበለጠ በማጠንከር ልዩ ልዩ ጠቃሚ ተግባራትን አከናውነዋል:: ቤተ ክርስቲያኗ በሰሜን



አሜሪካና በካሪቢያን ደሴቶች እምነቷን እንድታስፋፋና እንድ ታስተምር፣ አብያተ ክርስቲያናትም እንዲቋቋሙና እንዲታነፁ፣ የራሷን ካህናት እየላከች ሐዋርያዊ ሥራ እንድ ትሠራ አድርገዋል::

በሀገር ውስጥም በ1964 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን እንዲቋቋም አድርገዋል:: ይህ የልማት ኮሚሽን ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ካህናትን በተለያዩ ልማት ነክ ሥራዎች በማሠልጠንና በያሉበት የሀገሪቱ ክፍሎች በሚካሔዱ የልማት ሥራዎች እንዲ ባተፉ በማድረግ፣ የበጎ አድራጎት ሥራዎችንና የምግብ ለሥራ ፕሮ ግራሞችን በማካሔድ፣ በሀገሪቱም ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ሥራዎች በመሳተፍ በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ጠቃሚ አገልግሎቶችን እያበረከተ ይገኛል::

ከዚህም በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የተቃና ይሆን ዘንድ የተለያዩ አስተዳደራዊ ደንቦችንና መመሪያዎችን በፊር ማቸው አጽድቀው ሥራ ላይ እንዲውሉ አድርገዋል:: ከእነዚህም ውስጥ «ቃለ ዐዋዲ» የተሰኘውና የተለያዩ ደንቦችን ያካተተው ዐቢይ የቤተ ክርስቲያኗ የአስተዳደር ደንብ ተጠቃሽ ነው:: ከዚህም ጋር ጥቅምት 15 ቀን 1965 ዓ.ም ዛሬም ቢሆን ቤተ ክርስቲያኗ እየተገ ለገለችበት ያለውን የሰበካ ጉባኤ ደንብ፣ ግንቦት 1 ቀን 1965 ዓ.ም የቤተ ክርስቲያኒቱን ንዋያተ ቅድሳትና መጻሕፍት አመዘጋገብና አጠባበቅ ደንብ፣ ታኅሣሥ 16 ቀን 1967 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅን ሥልጣንና ተግባር የሚወስን ደንብ አውጥተው ሥራ ላይ አውለዋል::

ቅዱስነታቸው በነበራቸው የሰከነና የአርቆ አስተዋይነት ችሎታ ቤተ ክርስቲያናችን በመንግሥት ችሮታ ታገኘው የነበረው ገቢ አንድ ቀን እንደ ሚቀር በመረዳት ቀደም ቢል ከታነፁት ጋር አከራይታ የምትጠቀምባቸውን ሕንጻዎች በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ቦታዎች አሠርተዋል:: ከሚከራዩ ሕንፃዎችም በተጨማሪ አዲስ አበባ ላይ የሚገኘውን የጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራልን አሳንፀዋል:: በተጨማሪም ፊደል ቆጥረው ያደጉበትንና በምስራቅ ጎጃም የሚገኘውን የደብረ ገነት ኤልያስ ቤተ ክርስቲያንን በዘመናዊ መልክ አሳድሰዋል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በዚህ በተጠቀሱትና ባልተጠ ቀሱት በርካታ አገልግሎቶች ተጸምደው ሳለ በ1966 ዓ.ም የንጉሡ ዘውዳዊ መንግሥት በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መንግ ሥት ተተካ:: የወጠኗቸውን የቤተ ክርስቲያን ልማቶች ሳይፈጽሙ፣ ያሰቧቸውን የሥራ ዕቅዶች ወደ ተግባር ሳይለውጡ የካቲት 9 ቀን 1968 ዓ.ም ከመንበረ ፓትርያርክነታቸው ወርደው ለእስር ተዳረጉ::

www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስነታቸው በእስር በታላቁ ቤተ መንግሥት በዙፋን አዳራሽ ምድር ቤት ውስጥ ታላላቅ የዘውድ መንግሥት ባለሥልጣናት ታስረውበት ወደ ነበረው አንድ ቀዝቃዛ ክፍል ውስጥ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የነበረውን የቅዱስነታቸውን ሁኔታ ከቅዱስነታቸው ጋር የቅርብ ትውውቅና የሥራ ግንኙነት የነበራቸው አቶ አበራ ጀምበሬ የዓይን እማኝነታቸውን «የእስር ቤቱ አበሳ» በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሐፍ እንደ ሚከተለው ተርከውታል፡፡

*«. . . በታላቁ ቤተ መንግሥት ታስረው የነበሩ የቀድሞ መንግሥት ባለ ሥልጣኖች ንጹሕ አየር ለማግኘት፣ በፀሐይ አካላቸውን ለማሞቅ፣ የተሳሰሩ እግሮቻቸውን ለማፍታታት በዙፋን አዳራሽ አጠገብ በሚገኝ በሽቦ በታጠረ ጠባብ ክልል ውስጥ ይንከላወሳሉ፡፡ ቀኑ መጋቢት ሦስት ቀን 1968 ዓ.ም ከእኩለ ቀን በኋላ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ታላቁ መንፈሳዊ አባት ሁለት እጆቻቸው በአንድ ላይ በሠንሠለት ታስረው እየተገፈተሩ ያለ መጫሚያ በባዶ እግራቸው ሲመጡ የተመለከቱት እነዚያ እስረኞች ባሉበት ክው ብለው ቀሩ፡፡ በዚህ ወቅት ነበር አንዱ እስረኛ ልቡ ተነክቶ «እዲዮስ የኢትዮጵያውያን ሰብአዊነትና መንፈሳዊነት» ያለው፡፡*

*«. . . የኢትዮጵያ ሕዝብ ግብረ ገብነትና መንፈሳዊነት በእነዚህ ጋጠ ወጦች አይለካም» አለ ሌላው በድርጊቱ መብገኑን ሁኔታው እየነገረበት፡፡ «ካህኑን እንደ ፖለቲከኛ፣ መንፈሳዊ አባቱን እንደ ወንጀለኛ የሚመለከት ወታደራዊ ቡድን በዚህች ቅድስት አገር መነሳቱ ያሳዝናል፡፡ መንፈሳዊ አባት በግፍ ሲንገላታ ከማየት መሞት ይመረጣል» አለ ሌላው በመበሳጨት፡፡*

*«የአደፈ ሸርአማ ቀሚስ እንደ ለበሱ ከቀኝም፣ ከግራም፣ ከኋላም ሳንጃ የተሰካበት ጠብ መንጃ ተደግኖባቸው ወደ ዚያች የፖለቲካ እስረኞች መቀየጃ ቅጥር ግቢ ሲገቡ መንፈሳዊው አባት «የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» በማለት ግፍ ለሚፈጽሙባቸው የሚጸልዩ እንጂ የተበሳጩና የተሸበሩ አይመስሉም ነበር፡፡*

*«እስረኛው ከድንጋጤው ገና ሳይላቀቅ፣ ምን እንደ ሚልና እንደ ሚያደርግ አሰላሰሉ ሳይጨርስ፣ ከቆመበት ሳይላወስ ነበር ከአንድ ትንሽ ክፍል ውስጥ አስገብተው የቆለፉባቸውና እግራቸውን በእግረ ሙቅ፣*



*እጃቸውን በሠንሠለት ጠፍረው ከአልጋ ጋር ያሠሯቸው፡፡ 'ይህን አዚመኛ ቄስ ተጠንቅቃችሁ ጠብቁ' በማለት ለወታደሮቹ ጥብቅ ትእዛዝ ሰጥቶ የዘቡ አዛዥ ከአጥሩ ወጥቶ ሔደ፡፡*

*«መንፈሳዊው አባት የታሰሩባት ክፍል በማግሥቱ የአሳሪዎች ምልልስ ታየባት፡፡ ሹማምንት በመፈራረቅ ጉበኟት፡፡ ፈንጠር፣ ፈንጠር፣ ቀበጥበጥ ብለው እንዳልገቡ ተሰፋ ቆርጠው ሲወጡ ተስተዋሉ፡፡ ይህ ሁሉ ምልልስ፣ ይህ ሁሉ ጋጋታ የተከሰተው ከአንድ ክፍል ውስጥ እግር እጃቸው ከአልጋ እግር ጋር የታሰረው መንፈሳዊ አባት ምግብ አልበላም ብለው በመወሰናቸው ነበር፡፡ ሻለቃ ዳንኤል አስፋውና ሌሎች የእስር ቤቱ ኃላፊዎቹ የሚመጣላቸውን ምግብ እንዲመገቡ ለማድረግ ቢሞክሩም ቆራጡ አባት አልተበገሩም፡፡ ከዚህ በኋላ ነበር ምግብ አልበላም በማለት ማስቸገራቸውን በመግለጽ ሻለቃ ዳንኤል ለደርግ የፀጥታ ጥበቃ ኮሚቴ ሊቀ መንበር ባቀረበው ማስታወሻ ግርጌ ላይ «ምግብ እንዲ ገባላቸው አድርጉ እንጂ ቢበሉ ባይበሉ የራሳቸው ጉዳይ ነው» ሲል ሻለቃ ተካ ቱሉ ምልክት ያደረገው፡፡*

*«እኒያ አባት በዚያች መስኮት በሌላት ጠባብ ክፍል ምግብ ብቻ ሳይሆን ንጹሕ አየርም ሳያገኙ ሰባት ቀን ጦማቸውን ውለው አደሩ፡፡ ከዚያ በኋላ ነበር ሌሎች እስረኞች አግባብተው ምግብ እንዲበሉ እንዲያደርጉ ለአንድ ቁጥር ኃላፊ ትእዛዝ በመስጠት አሳሪዎቻቸው ከሰው እንዲቀላቀሉ ያደረጉት፡፡ እግር እጃቸው ከብረት ተላቅቆ ከመንፈስ ልጆቻቸው ጋር ተቀላቀሉ፡፡ ለጸሎት እንዲያመቻቸው በዙፋን አዳራሽ መግቢያ ዋና በር ደረጃ ሥር የሚገኘው ጉሮኖ ለእርሳቸው መኝታ ተለቀቀላቸው፡፡ በአንድ ቁጥር ክፍል ውስጥ የሚገኙት እስረኞች በተለይም ብርጋዴር ጄኔራል ሳሙኤል በየነ ሀቅማቸው በፈቀደ መጠን የሚጉድላቸውን እሟልተውና አንጥፈው ተቀበሏቸው፡፡ ምግብ ሲያቀርቡላቸው ግን «እግዚአብሔር ይስጣችሁ፤ አልበላም» የሚል ሆነ መልሳቸው፡፡ የደረቀ ጉሮሮአቸውን በውኃ እያጉመጠመጡ ብቻ ምግብ ሳይበሉ፣ ውኃ ሳይጠጡ መጾሙን ቀጠሉ፡፡ ጠንካራነታቸውን አስመሰከሩ፣ የመንፈስ ብቻ ሳይሆን አካላዊ ምግባቸውም ጾም ጸሎት ሆነ፡፡ የዕለት ተዕለት ሁኔታቸውም ለሌሎች እስረኞች መንፈሳዊ ጽናትን ሰጠ፡፡»*

www.ethiopianorthodox.org

*ይሁንና ፋሲካ በዋለ በማግሥቱ ከእስረኞች መካከል በዕድሜ የገፉት እንደነ ደጅ አዝማች ሐረጉት ግባይ ያሉት አጥብቀውና አስጨንቀው ስለ ለመኗቸው አሀል ሊበሉ መቻላቸውን አብረዋቸው ታስረው ከነበሩት ለማረጋገጥ ተችሏል:: /የእስር ቤቱ አበሳ በታላቁ ቤተ መንግሥት፣ ከ1966 እስከ 1974 ዓ.ም፣ አበራ ጀንበሬ ገጽ 9-12/::*

ቅዱስነታቸው በዚህ ዓይነት ለ28 ወራት ከአራት ቀን በመራር ኀዘንና ጸሎት ከቆዩ በኋላ ሐምሌ 7 ቀን 1971 ዓ.ም በሰሜን አዲስ አበባ ወረዳ 12 ቀበሌ 22 ወደ ሚገኘው የልዑል ራስ ዓሥራተ ካሳ ቤት ተወስደው በሚያስቅቅ ሁኔታ በገመድ ታንቀው ተገደሉ:: አስከሬናቸውም የእርሳቸውን ዓይነት የሞት ጽዋ ከተቀበሉ ሰዎች ጋር በዚያው ቅጽር ግቢ ተቀበረ::

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ዐጽም ከ13 ዓመታት በኋላ እሚሚታቸውንና የት እንደ ተቀበሩ በዐይኑ ባየ በወቅቱ የደርግ የደኅንነት ክፍል ወታደር ጥቆማ ወጥቶ ሐምሌ 4 ቀን 1984 ዓ.ም በጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል በክብር ዐረፈ:: በዚህ ወቅት ከላይ በአጭሩ የተገለጠውን የመከራ ጽዋዕ ተቀብለው ያለፉት ቅዱስ አባት በቤተ ክርስቲያኗ ቅዱስ ሲኖዶስ «ሰማዕት» ተብለው እንዲጠሩ የተላለፈው ውሳኔ በንባብ ተሰምቷል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቅዱስነታቸው «ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ» ተብለው ይጠራሉ:: ለቅዱስነታቸው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ዐጽማቸው ባረፈበት ካቴድራል ሐውልት ቆሞላቸዋል:: የቅዱስነታቸው ረድኤትና በረከት ከሁላችን ጋር ይሁን:: አሜን::



# 2.3. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሣልሳይ ፓትርያርክ /1910 - 1980 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

## 2.3. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት
## ሣልሳይ ፓትርያርክ
## /1910 - 1980 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

አባ መልአኩ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መስከረም 10 ቀን 1910 ዓ.ም የንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ታማኝ ወታደር ከነበሩት አባታቸው ከወ/ር ወልደ ሚካኤል አዳሙና ከእናታቸው ከወ/ሮ ዘውዲቱ ካሣ በቀድሞው ጎንደር ጠቅላይ ግዛት ማኅደረ ማርያም ተብላ በምትታወቀው ገዳም አካባቢ ጋዝን በምትባል ቦታ ተወለዱ:: ወላጅ አባታቸው ወ/ር ወልደ ሚካኤል እናታቸውን ወ/ሮ ዘውዲቱን ያገኟቸው ለውትድርና አገልግሎት ከጎንደር ወደ ጎጃም መጥተው ዘርዘር በተባለው አካባቢ በቆዩበት ጊዜ ነበር:: የቅዱስነታቸው ወላጆች በዚህ ዓይነት ከተዋወቁ በኋላ አባታቸው የጎጃሙን ተልእኮ አጠናቀው ወደ ጎንደር ሲመለሱ ወ/ሮ ዘውዲቱንም ይዘው ተጓዙ:: ጎንደር ደርሰው ጥቂት ከቆዩ በኋላ የሁለቱ ፍሬ የኾኑት ቅዱስነታቸው ተገኙ::

ወ/ር ወልደ ሚካኤል ምንም እንኳን ባልታሰበ ሁኔታ ካገኟት የትዳር ጓደኛቸው ዓይናቸውን በዓይናቸው ለማየት ቢታደሉም ባደረባቸው ሕመም የተነሣ ልጃቸው ገና ዕርጥብ አራስ ሳሉ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: ባለቤታቸውን ተከትለው ወንዝ በመሻገር ወደ ማያውቁት ሀገር የሔዱት ወ/ሮ ዘውዲቱ አራስ ልጃቸው በመጠኑ ጠንከር እስኪሉ በዚያው ቆይተው ልጃቸውን በመያዝ የባለቤታቸውን ዘመዶች ተሰናብተው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ:: ገና በአራስነታቸው ወላጅ አባታቸውን ያጡት ቅዱስነታቸውም ዘርዘር ሚካኤል በተባለ የእናታቸው ሀገር ማደግ ጀመሩ:: ለድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ እዚያው ከእናታቸው ጋር ሆነው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ጀመሩ:: ነገር ግን በዚህ ምድር በፈተና ጸንተው ለማየዊውን ቤታቸውን በሚገባ ሠርተው ሊሔዱ የተፈቀደላቸው ቅዱስነታቸው ገና ፊደል እንኳን ሳይለዩ ወላጅ እናታቸውም በሞት ተለዩአቸው::

የወላጅ አባታቸውን መልክ በልጅነት አጃቸው ለመዳሰስ፣ በከንፈራቸው ለመሳም፣ በዓይናቸው በይተው በአእምሮአቸው ለመሣል ያልታደሉት ቅዱስነታቸው ይባስ ብሎ እናታቸውን ሲያጡ ተደናገጡ:: ምንም እንኳን የእናታቸው ዘመዶች አይዞህ ቢሏቸውም ከእነርሱ እንደ አንዱ ሆነው በግብርና እንዲሠማሩ ለማድረግ ስለ ነበረ ቅዱስነታቸው እናታቸው በሞት ከተለዩአቸው በኋላ በአካባቢው ሊቆዩ አልፈለጉም:: በመሆኑም ከዘርዘር ዘመዶቻቸውን ተሰናብተው ጎንደር ወደ ሚገኙት የአባታቸው ዘመዶች ተጓዙ:: ጉዟቸውን አጠናቀው ማኅደረ ማርያም አካባቢ በምትገኘው ጋዝን ከተባለች ቦታ ደርሰው የመማር ፍላጎታቸውን ለዘመዶቻቸው ገለጹ:: የድሃ አደጉን ሕፃን አሳብ የተረዱት ዘመዶችም በእዚያው አካባቢ ታዋቂ መምህር ለነበሩት መሪ ጌታ ወርቅነህ ሰጧቸው:: በዚያም ፊደል ከቆጠሩ በኋላ ወደ ደብረ ታቦር ተሻግረው እናቲቱ ማርያም በተባለችው



ደብር ያስተምሩ ወደ ነበሩት አለቃ ቀለመ ወርቅ ዘንድ ሔደው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ:: ከዚህም በኋላ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ::

ከዚያም ወደ ማኅደረ ማርያም ተመልሰው በዲቁና ሲያገለግሉ ቆዩ:: ወላጆቻችውን በሞት በመነጠቃቸው ብቸኝነት የተሰማቸው ቅዱስነታቸው ቀጣይ ሕይወታቸውን በቤተ ክርስቲያን ትምህርት አጎልምሰው በትኅርምትና እግዚአብሔርን በማገልገል ሊኖሩ ወሰኑ:: በውሳኔያቸው መሠረትም ቅኔ ሊማሩ ከጓደኛቸው ጋር ከማኅደረ ማርያም ተነሥተው ወደ ጎጃም ተመለሱ:: በዚያም በእናታቸው ሀገር አጠገብ ወደ ሚገኘውና የረዝ ሚካኤል ወደ ተባለው ቦታ ሔደው መምህር ልሳነ ወርቅ ከተባሉ መምህር ዘንድ ቅኔንና ዜማን ለስምንት ዓመታት ያህል ተማሩ:: በሚማሩ በትም ጊዜ የእናታቸው ዘመዶች በልብስና በምግብ መጠነኛ ድጋፍ ያደርጉላቸው ነበር ይባላል::

የዜማውንና የቅኔውን ትምህርት በሚገባ ካጠናቀቁ በኋላ በተማርኩት ደግሞ ጥቂት ላገልግል በማለት ወደ ደብረ ታቦር ሔዱ:: ይሁን እንጂ ወዲያውኑ የኢጣልያ ፋሺስት ጦር ኢትዮጵያን በግፍ በመውረሩ እንዳሰቡት በሰላም ሊያገለግሉ አልቻሉም:: በመሆኑም የአገልግሎት አሳባቸውን በመተው ራቅ ወዳለ ቦታ ሔደው በብሕትውና እየኖሩ ለመማር ወሰኑ:: ይህንን ውሳኔያቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚሔዱበትን ሀገር ለመወሰን ሲያወጡ ሲያወርዱ እና የጓደኞቻቸውን ምክር ሲጠይቁ አንድ ጓደኛቸው በደቡብ ኢትዮጵያ ወላይታ አካባቢ አጎቱ በመንግሥት ሥራ ተሠማርቶ እንደ ሚኖር፣ አካባቢው በ13ኛው መ.ክ.ዘ. ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የተጋደሉበት፣ እንደ ደብረ መንክራት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዓይነት ታላላቅ ገዳማት እንዳሉበት፣ ቦታው በጥምቀት የቅድስት ሥላሴን ልጅነት ያላገኙ ሰዎች የሚበዙበት በመሆኑ ለብሕትውናና ለአገልግሎት የሚመች መሆኑን መክሮ አብረው ቢሔዱ ለጊዜው አጎቱ ቤት እንደ ሚያርፉ ይነግራቸዋል:: ቅዱስነታቸውም የጓደኛቸውን አሳብ ተቀብለው በ1926 ዓ.ም ሁለቱም ወደ ወላይታ ጉዞአቸውን ጀመሩ::

አድካሚ ከሆነው ከብዙ ቀናት የእግር ጉዞ በኋላ ወላይታ ደርሰው ከጓደኛቸው አጎት ቤት ዐረፉ:: አካባቢውን እስከ ሚላመዱ በእንግድነት ከቆዩ በኋላም ዝናው ከጎንደር ስቦ ወዳ መጣቸው ደብረ መንክራት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ገቡ:: እግዚአብሔር እንደነ ጻድቁ አቡነ ዜና ማርቆስና ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በአካባቢው ሥራ እንዲሠሩ መርጧቸዋልና ወደ ገዳሙ ሲገቡ በቦታው ረዘም ላለ ጊዜ የቆዩትን አለቃ ደስታ የተባሉትን ባሕታዊ አገኙ:: ከእርሳቸ

www.ethiopianorthodox.org

ውም ጋር በአንድ በአት ተወስነው መኖር ጀመሩ::

ቅዱስነታቸው በደብረ መንክራት ገብተው ጥቂት ከቆዩ በኋላ የገዳሙ አበ ምኔት ከነበሩት መምህር ወልደ ኢየሱስ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ በተለይም የማር ይስሐቅንና የመጻሕፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ በጥልቀት ተማሩ:: ቅዱስነታቸው ከመማር ጋር በነበራቸው የቁም ጽሕፈት ችሎታ በመምህራቸው ታዝዘው ቅዱሳት መጻሕፍትን እየጻፉ ለገዳሙ ማኅበር እንዲዳረስ አድርገዋል:: በዚህ ዓይነት የቅዱሳት መጻሕፍትን ምሥጢር ሊመረምሩና ሥርዓተ ገዳምን ሲያጠኑ ከቆዩ በኋላ በዚያው መዓርገ ምንኩስናን ተቀበሉ:: ከዚያም ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከግብፃዊው ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ መዓርገ ቅስናን ተቀብለው ወደ በአታቸው ተመለሱ::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ገዳማቸው ከተመለሱ በኋላ በጾም በጸሎት፣ በስጊድና በትኅርምት በገድልና በልዩ ልዩ ትሩፋት ተወስነው እስከ 1940 ዓ.ም ድረስ በአታቸውን አጽንተው ቆዩ:: ይህም የተባሕትዎ ጊዜ ከፈጣሪያቸው ከእግዚአ ብሔር ልዩ ጸጋና በረከት የተቀበሉበትና ለወደ ፊት ዓላማቸው ሁሉ መመሪያ ያገኙበት ወቅት ነበር::

በዚህ ዓይነት ለዓመታት በፍጹም ትኅርምት እና ተጋድሎ እንደ አባቶቻቸው እግዚአብሔርን በጸሎት ከለመኑ በኋላ በ1940 ዓ.ም በአታቸውን በዚያው ገዳም አድርገው በአውራጃው ልዩ ልዩ ቦታዎች በመዘዋወር ማስተማር ጀመሩ:: ቅዱስነታቸው በሚያስ ደንቅ ሁናቴ በአውራጃው ውስጥ በሚገኙት ሰባት ወረዳዎች እየተዘ ዋወሩ ሲያስተምሩ ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ዘንድ በአካባቢው እንዲንቀሳቀሱ የፈቃድ ደብዳቤ ከማግኘታቸው በስተቀር የተቆረጠላቸው ደመወዝ የተሰፈረላቸው እህል አልነበረም:: በቅዱስነታቸው ትምህርት ከ300,000 /ሦስት መቶ ሺህ/ በላይ የሆኑ ኢ አማንያን አምነው እንደ ተጠመቁና የክርስቶስ ተከታዮች እንደ ሆኑ ይነገራል:: በጣዕመ ስብከታቸው ይህንን ያህል ምእመን ካፈሩም በኋላ ምእመናኑ እየተሰበሰቡ የሚጸልዩባቸውና ምሥጢራተ ቤተ ክር ስቲያንን የሚቀበሉባቸው በሁሉም ወረዳዎች 65 አብያተ ክርስ ቲያናትን አሠርተዋል:: እንዲሁም ልጆቻቸው መንፈሳዊውንና ሥጋ ዊውን ትምህርት የሚማሩባቸውን 24 ትምህርት ቤቶችን አቋቁ መዋል::

ቅዱስነታቸው ከዚህም በተጨማሪ በወላይታ ሶዶ ከተማ በደብረ መንክራት ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም አካባቢ 11 ክፍል የድኩማን ቤት በማሠራት ራሳቸውን ለመርዳት የማይችሉ ድኩማን ምግብ፣ ልብስና መጠለያ እንዲያገኙ በማድረግ ሐዋርያዊ ግዳጃቸውን ተወጥተዋል:: እንዲሁም በዚሁ ከተማ ውስጥ ከ400



ያላነሰ ሕዝብ በአንድ ጊዜ መያዝ የሚችል «የወጣቶች የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አዳራሽ» የተሰኘ መሰብሰቢያ አዳራሽ አሠርተው በአገልግሎት ላይ ይገኛል:: ከዚህም ሌላ አንድ ክሊኒክ በዚሁ ከተማ ውስጥ አቋቁመው ሕዝቡ እንዲጠቀምበት አድርገዋል:: እንደዚሁም ከከተማው ወጣ ብሎ በሚገኘው ቆንቶ በተባለው ቀበሌ በ1954 ዓ.ም ባሠሩት አዳራሽ የቃጫና የልዩ ልዩ ጥበብ እድ ሥራዎችን በማቋቋም የአካባቢው ችግረኞች እየሠሩ ራሳቸውን እንዲረዱ አድርገዋል::

ስብከተ ወንጌልንም በተመለከተ አካባቢው በመናፍቃን የተያዘ ስለ ነበር ባቋቋሙት ማኅበር አማካይነት ሰባክያንን በመቅጠ ር አባላቱም በፈቃዳቸው በአገልግሎቱ እንዲሠማሩ በማድረግ ሰፋ ያለ አገልግሎት አበርክተዋል:: ቅዱስነታቸው ባቀናጁት የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ተሳታፊ ከነበሩት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የያኔው ዲያቆን መርሐ ጽድቅ /የዛሬው ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ሊቀ ጳጳስ/ አንዱ ነበሩ::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከላይ በመጠኑ የተዘረ ዘሩትን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሥራዎች የሠሩት በቤተ መንግሥቱ ዕውቅና የነበረውንና በአካባቢው የሚገኙ ሰባት አውራጃዎች ተወካዮ ችን በአባልነት የያዘ «የመገበሪያ ቦርድ» የተሰኘ አካል በማቋቋም የአካባቢው ሕዝቦች ገንዘብ እንዲያዋጡ በማድረግ፣ ከዚህም ጋር የአካባቢውን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማፋጠንን ቀዳሚ ዓላማው ያደረገውን «ብርሃነ ሕይወት» የተሰኘ ግብረ ሠናይ ድርጅት አቋቁ መው ነበር::

በዚህ ዓይነት ሰፊ አገልግሎት ላይ ተጸምደው ቤተ ክርስ ቲያን የሰጠቻቸውን ሓላፊነት በመወጣት ላይ ሳሉ ንጉሣዊው መንግሥት በወታደራዊው የደርግ መንግሥት ተተካ:: በመሆኑም እንደ ቀድሞው ሁሉ ከሕዝቡ ገንዘብ ማሰባሰብ አልቻሉም:: በዚህ የተነሣም የልማት አገልግሎታቸው እንዳይቋረጥ ወደ አዲስ አበባ እየመጡ ከቤተ ክርስቲያኗና ከምእመናን መለመን ጀመሩ:: በዚህ ዓይነት በተወሰነ ደረጃ እየተንቀሳቀሱ እያለ ደርግ ሁለተኛውን የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን አሳግባብ አሰረ:: ከቤተ ክርስቲያኗ ቀኖና ውጪም ሌላ ፓትርያርክ እንዲ መረጥ አዘዘ:: ራሱ ባቋቋመው አስመራጭ ኮሚቴ አማካይነት ከየክ ፍሉ ለፓትርያርክነት እንዲመረጡ የሚፈለጉ አባቶች እንዲጠቆሙ አደረገ:: በመጨረሻም የማጣሪያ ምርጫ አድርጎ ከተጠቆሙት አባቶች ውስጥ አምስቱ ብቻ እንዲቀሩ ካደረገ በኋላ ከ565 ወረዳ ዎች ሁለት ሁለት ተወካዮች እንዲላኩና በአምስቱ አባቶች ላይ የፓትርያርክነት ምርጫ ድምፅ እንዲሰጡ ጥሪ አደረገ:: በእጩነት

www.ethiopianorthodox.org

የቀረቡት አምስት አባቶች አቡነ እንድርያስ /በወቅቱ የቤጌምድርና ስሜን ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ/፣ ብፁዕ አቡነ ሰላማ /በወቅቱ የጋሞ ጎፋ ሊቀ ጳጳስ/፣ አባ ተወልደ ብርሃን ወ/ሥላሴ ዘቢዘን /በወቅቱ የደብረ ቢዘን ገዳም አበምኔት/ ፣ አባ ዮሐንስ ከሐሊ ዘኢየሩሳሌም፣ አባ መላኩ ወ/ሚካኤል ዘደብረ መንክራት ተክለ ሃይማኖት ነበሩ:: ባላሰቡት ሁኔታ ለዚህ ታላቅ ኃላፊነት መታጨታቸውን የሰሙት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መንበሩ ለእኔ አይገባም ብለው ተቃውመው እንደ ነበር ይነገራል:: በዚህ የተነሣ ቅዱስነታቸው ቤተ ክህነት ውስጥ በምትገኝ አንዲት ክፍል ውስጥ ተቀምጠው በዘበኛ እንዲጠበቁ ተደርጎ እንደ ነበር ይነገራል::

ምንም እንኳን ከተጠበቀው 1130 ወኪሎች 909 ብቻ ቢገኙም በተገኙት ወኪሎች አማካይነት ምርጫው እንዲከናወን ተደርጎ ከደብረ መንክራት አቡነ ተክለ ሃይማኖት የመጡት አባ መላኩ ከጠቅላላው 909 ወኪሎች 317 ድምፅ በማግኘት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሦስተኛው ፓትርያርክ ሆነው ተመረጡ:: የቅዱስነታቸው ሹመት እውን ይሆን ዘንድ ሐምሌ 11 ቀን 1968 ዓ.ም መዓርገ ጵጵስና ተቀበሉ:: ስማቸውም ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተብለው ተሠየሙ:: በኋላም ነሐሴ 23 ቀን 1968 ዓ.ም በቅዱስ ሲኖዶስ «አባ ተክለ ሃይማኖት ሣልሳዊ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ» ተብለው ተሾሙ::

የቅዱስነታቸውን የአመራረጥ ሒደት የሰሙት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን፣ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት እንዲሁም የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ጉባኤ አንድን ፓትርያርክ በኃይል ከመንበሩ አንሥቶ ሌላ ፓትርያርክ መሾም አይገባም ሲሉ በመቃወም ለሹመቱ ዕውቅና እንሰጥም በማለት መግለጫ አውጥተው ነበር::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዚህ ዓይነት የቤተ ክርስቲያኗን ታላቅ ሐላፊነት ከተረከቡበት ጊዜ ጀምሮ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ ድረስ ያለውን የሰውና የገንዘብ ኃይል በማሰባሰብ ጊዜው የሚጠይቀውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ግዴታ ይፈጽሙ ጀመር:: ቅዱስነታቸው የሥራቸው መጀመሪያ ያደረጉት ቀደም ሲል በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ መሠረቱ ተጥሎ የነበረውን የቃለ ዐዋዲ ደንብ በማሻሻልና አንዳንድ ሁኔታዎችን ከወቅቱ ጋር እንዲሔዱ በማድረግ ሰበካ ጉባኤያት በማዕከል በሚቋቋመው መምሪያ እንዲመሩ ሆነው በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ እንዲቋቋሙና ምእመናን በቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ነበር::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት



ዘኢትዮጵያ ስለ ስብከተ ወንጌል መስፋፋትና መጠናከር ከጥንት ጀምሮ በነበራቸው ጽኑዕ ዓላማ ሰበካ ጉባኤን በማጠናከር አዳዲስ ሰባክያንን በመምረጥና በማሠልጠን ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋና እንዲጠናከር አድርገዋል::

ቅዱስነታቸው የነገዪቱ ቤተ ክርስቲያን ተረካቢዎች የዛሬ ሕፃናት መሆናቸውን ስለ ሚያውቁ ለሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ከፍ ያለ አመለካከትና ትኩረት ነበራቸው:: ቀደም አድርገው በየአንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤት እንዲቋቋም በሰጡት መመሪያ መሠረት በየአህጉረ ስብከቱ በርካታ የሰንበት ት/ቤቶች ተቋቁመው ሰፋ ያለ አገልግሎት እንዲ ያበረክቱ አድርገዋል:: በአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት በተቋቋሙት የሰንበት ት/ቤቶች እየተዘዋወሩ ለሚያስተምሩ መምህራን መጓጓዣ ይሆን ዘንድ ከወር ደመወዛቸው በየወሩ 730 ብር ይሰጡ ነበር::

አብነት ትምህርት ቤቶች ለቤተ ክርስቲያኗ ቀጣይ አገ ልግሎት ወሳኝ እንደ ሆኑ የተገነዘቡት ቅዱስነታቸው ከዘመኑ መለወጥ ጋር የሕዝቡ ኑሮም ስለ ሚለወጥ ለዘመናት በአካባቢያቸው ከሚኖሩ ምእመናን ቁራሽ ለምነው ሲማሩ የኖሩት ተማሪዎችና መምህራን እንዳይቸገሩ በማሰብ በየዓመቱ በመንበረ ፓትርያርክ በሚደረገው አጠቃላይ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ እንዲወሰን አድርገው ለበርካታ የአብነት መምህ ራ ን የወር ደመወዝ እንዲመደብላቸው፣ ተማሪዎችም ተመሳሳይ ድጎማ እንዲደረግላቸው አድርገዋል:: ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርትን በሚመለከትም ለተወሰኑ ዓመታት ሥራውን አቁሞ የነበረውን የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በ1974 ዓ.ም እንደ ገና ተከፍቶ ሥራውን እንዲጀምር አድርገዋል::

ቅዱስነታቸው ቤተ ክርስቲያኗ በካህናቷ አማካይነት መንፈሳ ዊውንም ሆነ ማኅበራዊውን አገልግሎት ለኅብረተሰቡ በተሟላ ሁኔታ መስጠት እንድትችል በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ በድስት የሚሆኑ የካህናት ማሠልጠኛዎች እንዲቋቋሙና ሥራቸውን እንዲጀምሩ አድርገዋል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በዘመነ ፓትርያርክናቸው ለቤተ ክርስቲያኒቱ ዕድገትና ሐዋርያዊ ተልእኮ ለስብከተ ወንጌልም መስፋፋት የጳጳሳት ቁጥር መጨመር አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ በተለያዩ ጊዜያት 28 ኤጲስ ቆጶሳትን ሹመዋል:: በሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር ለማበራከት በተደረገው ከፍተኛ ጥረትና የም እመናንንም መንፈሳዊ ፍላጎት ለማሟላት ሲባል ምእመናን በሚኖ ሩበት አካባቢና በየአቅራቢያቸው በርከት ያሉ አዳዲስ አብያተ ክር

www.ethiopianorthodox.org

ስቲያናት እንዲቋቋሙላቸው አድርገዋል፡፡

ልማትን በሚመለከትም ቅዱስነታቸው በሚሰጡት መመሪያ በድርቅ የተጎዱ ወገኖች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ያለ ምንም የሃይማኖት ልዩነት ኢትዮጵያውያን የሚገለገሉባቸው የእህል ወፍጮ ቤቶችና ዳቦ ቤቶች እንዲቋቋሙ አድርገዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የውኃ ጉድጓዶችን በማስቆፈርና መጋቢ መንገዶችን በማሠራት፤ በልዩ ልዩ ገዳማትና አድባራት የጨርቃ ጨርቅ ሽመና፣ የሹራብ ሥራ፣ የከብትና የንብ ርባታ፣ የአዝርእትና አትክልት ልማት፣ ችግኝ ማፍላትና የደን ዛፍ መትከል፣ የወንበርና ጠረጴዛ፣ የመስቀል ቅርጻ ቅርጽ ወዘተ የሚሠሩባቸውን ጎጆ ኢንዱስትሪዎች ተቋቁመው አገልግሎት እንዲሰጡ አድርገዋል፡፡

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለዚህ ክፍተኛና የመጨረሻ የፓትርያርክነት ሐላፊነት በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ በምእመናን ከመመረጣቸው በፊት «ለድሆችና ለድሃ አደጎች ፍረዱ፤ ለችግረኛውና ለምስኪኑ ጽድቅን አድርጉ፤ ብቸኛውንና ችግረኛውን እርዱ» በሚለው ቃል በመመራት በትምህርተ ወንጌል ምእመናንን በማስተባበር ደኻ አደጎችንና ድኩማንን ሰብስቦ መርዳትና ማስተማር በገዳም ይፈጽሙት ከነበረው ምግባር ትሩፋት ዋናው ክፍል ነበር፡፡ ቅዱስነታቸው በፓትርያርክነቱ የቅድስና መንበር ላይ ከተቀመጡ ወዲህም ቢሆን ይህን የተቀደሰ ዓላማ ዋና ተግባራቸው አድርገው በመያዝ የሃይማኖትና የብሔር ልዩነት ሳያደርጉ ከየአቅጣጫው እያሰባሰቡ በምግበ ሥጋና በምግበ ነፍስ የሚረዷቸው ድኻ አደጎችና ድኩማን እጅግ ብዙዎች ነበሩ፡፡ በተለይም በሀገራችን የድርቅ ችግር ከተከሰተ ወዲህ ቅዱስነታቸው ከየሥፍራው ሰብስበው የሚረዷቸው ወላጅ አልባ ሕፃናት ከቁጥር በላይ ነበሩ፡፡ ይህንን የቅዱስነታቸውን ምግባረ ሠናይ ከያሉበት ሆነው የሚሰሙ ወልዶ ማሳደግ ያቃታቸው ችግረኞች ምእመናንም ልጆቻቸውን ወደ መንበረ ፓትርያርኩ በማምጣት ለቅዱስነታቸው ሲያስረክቡ ወይም ለማስረከብ ደጅ ሲጠኑ ማየት የተለመደ ነበር፡፡

ቅዱስነታቸው ደኻ አደጎችን መርዳት ከቤተ ክርስቲያን ዐበይት ዓላማዎች አንዱ በመሆኑ በተሾሙ ማግሥት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ማእከል ተከፍቶ እጓለ ማውታ እንደ ማንኛውም የኅብረተሰብ ልጆች ሥርዓትና መልክ ባለው ሁኔታ ክብካቤ እየተደረገላቸው እንዲያድጉ አድርገዋል፡፡ በዚህም ረገድ በሰጡት መመሪያ በእርሳቸው ዘመነ ፓትርያርክነት በየሀገረ ስብከቱ የተቋቋሙ የቤተ ክርስቲያኗ የእጓለ ማውታ ማሳደጊያዎች 36 ደርሰው ነበር፡፡ በእነዚህ ማእከላት አድገውና ተምረው ለደረጃ የበቁት ኢትዮጵያውያን ዛሬ በልዩ ልዩ



ሞያዎች ተሠማርተው ሀገርንና ወገንን በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

በውጭ እህጉር ለሚገኙ የቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን መንፈሳዊ አገልግሎትን ለማሟላትና እንዲሁም በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርትና እምነት እምልኮተ እግዚአብሔርን ለመፈጸም ለሚፈልጉ የውጭ አህጉር እማንያን ቤተ ክርስቲያን በማቋቋምና አገልጋዮችንም በመላክ ለቤተ ክርስቲያናችን ክፍተኛ የሆነ ታሪክ አስመዝግበዋል፡፡ ለዚህም ድርጊት በምዕራብ ጀርመን፣ በጅቡቲና በኬንያ የተቋቋሙት አብያተ ክርስቲያናት በግንባር ቀደም ከሚጠቀሱት መካከል ናቸው፡፡

ቅዱስነታቸው ለዘመናት የምእመናን ጥያቄዎች ሆነው ሲያነጋግሩ የነበሩ ጉዳዮችን በማድመጥ ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ እንዲያሳልፍባቸው በማድረግ በኩል የሚጠቀሱ ሥራዎችን ሠርተዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ከሰባቱ አጽዋማት አንዱ የሆነው የልደትና የጥምቀት ጾመ ገሐድ ፣ ጾመ ነቢያት የሚገባው በየዓመቱ ኅዳር 15 እንደ ሆነና ዓሣ በጾም ወራት እንደማይበላ ያስወሰኗቸው ውሳኔዎች ይጠቀሳሉ፡፡

እንደ ሚታወቀው እሳቸው በሥልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ በሀገሪቱ የነበረው ርእዮተ ዓለም ከእምልኮተ እግዚአብሔር ጋር የሚሔድ አልነበረም፡፡ በዚህ የተነሣም ብሔራዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ፈተናዎች ተጋርጠውባት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በቅዱስነታቸው ጥበብና ትዕግሥት በሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የደረሰው በእኛዋ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሳይደርስ ፈተናውን እንድታልፍ ማድረጋቸው በሰፊው የሚነገር እውነታ ነው፡፡

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከሢመተ ፓትርያርክነት በፊትም ሆነ በመዋዕለ ሢመታቸው በትግሀ ጸሎት በገድል በትሩፋት የተፈተነ መንፈሳዊ ሕይወት የነበራቸው፣ ክፍቅረ ንዋይ የነጹ፣ ለተቸገሩት የሚሰጡትን ርዳታና በጎ አድራጎትም ማንም በአፍአ እንዲናገር የማይፈልጉ፣ የዚህንም ምክንያት ሲያስረዱ «እናት ለልጆችዋ የምትሰጠውን ሁሉ ሀገር ይወቅልኝ ትላለችን?» ሲሉ በተደጋጋሚ ይናገሩ የነበሩ፣ ሠርቶ የማሠራትና በየጊዜውም አዳዲስ የሥራ መቀቅሮች እንዲከፈቱ የማበረታታት ልምድ ያላቸው ደግ አባት እንደ ነበሩ በቅርብ የሚያውቋቸው ሁሉ ይናገራሉ፡፡

ቅዱስነታቸው እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሀገረ ሙላድ እያላቸው ተወልጄ ያደግሁበት ቦታ ይህ ነው ብለው ከመናገር ይልቅ በፍጹም ኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ ያምኑ ነበር፡፡ የካህነ እግዚአብሔር መልከ ጼዴቅን አሠረ ፍኖት በመከተል እንደ

www.ethiopianorthodox.org

አብርሃም እበ ብዙኃንነትን እጉልተው በማሳየት ሁሉን እኩል በመመልከት ብቃታቸው ብዙዎችን ሲያስገርሙ የኖሩ አባት ነበሩ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መቼም ቢሆን አልጋ ላይ ተኝተው የማያውቁ ፍጹም ተጋራሚ አባት እንደነበሩ በቅርብ የሚያውቋቸው ሁሉ ይመሰክሩላቸዋል። በዚህ ረገድ በብዙ ሰዎች አንድ የሚነገር ታሪክ አላቸው። በአንድ ወቅት ቅዱስነታቸው ፓትርያርካዊ ጉብኝት ለማድረግ ሌሎች ብፁዓን አባቶችን አስከትለው ወደ ሮማንድ ይጓዛሉ። በዚያም ያረፉት በካርዲናሉ መኖሪያ ቤት ነበር። ለቅዱስነታቸው ክብር ሲባል የተሰጣቸው ክፍል የካርዲናሉ ክፍል ነበር። ታዲያ ቅዱስነታቸው እሺ ብለው ሲመሽ ወደ ክፍሉ ይግቡ እንጂ አልጋው ላይ አይተኙም ነበር። ጠዋት ግን አልጋውን የተኙበት ለማስመሰል የተነጠፈውን ብርድ ልብስም ሆነ አንሶላውን ያመስቃቅሉት ነበር። አንድ ቀን ምሽት በአጋጣሚ የካርዲናሉ ሠራተኛ ዕቃ ለማውጣት ወደ ክፍላቸው ስትገባ አልጋው እንደ ተነጠፈ፣ ቅዱስነታቸው ከመሬት ላይ ተኝተው ታገኛቸዋለች። እርስዋም በእጅጉ ደንግጣና ተደንቃ ለካርዲናሉ ነገረችው። ካርዲናሉም የብፁዕ ወቅዱስ እቡነ ተክለ ሃይማኖትን ቅድስናና ትኅርምት አድንቆ ጉብኝቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ በራሱ መኪና ራሱ እየነዳ ሲያገለግላቸው ሰንብቷል ይባላል።

ቅዱስነታቸው በአመጋገብም በኩል ቢሆን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ከበሶ ወይም የተቀቀለ ድንች በስተቀር ሌላ ነገር ቀምሰው አያውቁም ይባላል።

ቅዱስነታቸው በጾም፣ በጸሎት፣ በቀዊምና በስግደት ተወስነው ቤተ ክርስቲያናቸውን ሲያስተዳድሩ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ ሰፊ አገልግሎትና ተጋድሎ ሲፈጽሙበት የቆዩበትን የደብረ መንከራት አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ገዳም በመጎብኘት ላይ ሳሉ በድንገት ታመሙ። ወደ አዲስ እበባ ባስቸኳይ መጥተው በዳግማዊ ምኒልክና የጦር ኃይሎች ሆስፒታል በሕክምና ሲረዱ ቢቆዩም ሊድኑ አልቻሉም። በመሆኑም ከዐሥራ ሁለት ዓመታት የፓትርያርክነት አገልግሎት በኋላ ግንቦት 28 ቀን 1980 ዓ.ም በተወለዱ በ 70 ዓመት ዕድሜያቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ቅዱሰነታቸው መላ ዘመናቸውን በጾም፣ በጸሎትና በስጊድ ያሳለፉ ከመሆናቸው ጋር ባደረባቸው ሕመም የተነሣ ነፍሳቸው ከሥጋቸው ስትለይ የሰውነታቸው ክብደት 25 ኪሎ ግራም ደርሶ እንደ ነበር ይነገራል። አስከሬናቸውም በመንበረ ፓትርያርኩ እርፎ ሊሲቱን ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጸሎተ ፍትሐቱን ሲያደርሱ እደሩ። በማግሥቱም ግንቦት 29 ቀንም በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም ጸሎተ ቀጥሎ ሥርዓተ ቀብራቸው ግንቦት 30 ቀን 1980 ዓ.ም



ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ የየመምሪያው ኃላፊዎችና ሠራተኞች፣ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት አድባራትና ገዳማት አለቃዎች፣ የሰንበት ት/ቤቶች አባላትና ምእመናን እንዲሁም የመንግሥት ባለ ሥልጣናት በተገኙበት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በክብር ተፈጽሟል። የቅዱስነታቸው አገልግሎት ሲዘከር ይኖር ዘንድ አስከሬናቸው በክብር ባረፈበት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የመታሰቢያ ሐውልት ቆሞላቸው ዛሬም ይገኛል። የቅዱስነታቸው ረድኤት እና በረከት ከሁላችን ጋር ይኑር። እሜን።

www.ethiopianorthodox.org

# 3.1. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቀዳማዊ «ጳጳስ ዘምሥራቅ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ኢየሱስ ሞዓ» /1875 - 1928 ዓ.ም/





ጴጥሮስ የሚለውን ስመ ጵጵስና ከማግኘታቸው በፊት መምህር ኃይለ ማርያም ይባሉ ነበር። ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቀዳማዊ በ1875 ዓ.ም. በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሰላሌ አውራጃ ፍቼ ከተማ ተወለዱ። የልጃቸውን የዕውቀት ብልጥግና ለማየት የጓጉት ወላጆቻቸው ዕድሜያቸው ገና ለትምህርት ሳይደርስ ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመውሰድ ሲጋ አእምሮአቸውን በዕውቀት ያንፁላቸው ዘንድ ባሕታዊ ተድላ ለተባሉ መምህር አደራ ሰጧቸው።

ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስም የወላጆቻቸው ሕልም እውን ይሆን ዘንድ በንጹሕ አእምሮአቸው እንደ ጥንታዊው የቤተ ክርስቲያኗ ሥርዓተ ትምህርት ከንባብ እስከ ቅኔ ያሉትን ትምህርቶች እዚያው በተወለዱበት አካባቢ በሚያስገርም ሁኔታ በአጭር ጊዜ አጠናቀቁ። በኋላም የቅኔ ትምህርታቸውን ለማስፋፋት በምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ወደ ሚገኘው የቅኔ ትምህርት ቤት ዋሸራ ተሻገሩ። በዚያም በውስጣቸው በስንቁት የመማር ፍላጐት እየታገዙ ደብረ ሊባኖስ ላይ መሠረቱን የጣሉት የቅኔ ትምህርት በመቀጠል ለመምህርነት የሚያበቃውን ትምህርት ፈጽመው በመምህርነት ተመረቁ።

ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ፈደል ቆጥረው ያደጉበትን ገዳም ለቀው ዓባይን እንዲሻገሩ ያደረጋቸውን የቅኔ ትምህርት በአጥጋቢ ሁኔታ ቢያጠናቅቁም ወደ ሸዋ አልተመለሱም። ትምህርት ገና በሕፃንነታቸው የወላጆቻቸውን ፍቅር ሳያጣጥሙ የመነኑለት ነውና እንደ ቅኔው ሁሉ የዜማውንም ትምህርት በሚገባ ለመማር ከቅኔው ዐውድማ ጎጃም ወደ ዜማው አዝመራ ጎንደር ተሻገሩ። በዚያም እንደ ቅኔው ሁሉ እስከ ማስመስከር ባይደርሱም የዜማውን ትምህርት በአጥጋቢ ሁኔታ ተማሩ።

ብፁዕነታቸው አሁንም «ያወጣኸኝ አገሬ መልሰኝ ወደ አገሬ» አላሉም። ከፍተኛውን የትምህርት ደረጃ አላዳረሱምና። ገና በሕፃንነታቸው ከወላጆቻቸው ለይቶ ወደ ታላቁ ገዳም ደብረ ሊባኖስ፣ ከዚያም ወንዝ አሻግሮ ወደ ጎጃም፣ ቀጥሎም ወደ ጎንደር የወሰዳቸው የትምህርት ፍቅር በመጨረሻ ወደ ወሎ አደረሳቸው። በወቅቱ ወሎ ቦሩ ሜዳ ከተባለው ቦታ ላይ ወንበር ዘርግተው የመጻሕፍትን ምሥጢር በየዓይነቱ ሲመግቡ ወደ ነበሩት ስመ ጥርው መ/ር እካለ ወልድ ዘንድ በመሔድ ዋና ዋናዎቹን የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርቶች ማለትም ብሉያትን፣ ሐዲሳትንና ሊቃውንትን በብቃት አሔዱ።

ከዚህ በኋላ በ1900 ዓ.ም. እንደ እርሳቸው ሁሉ ዕውቀትንና ጥበብን ፍሰጋ የገቡትን ደቀ መዛሙርት ለማስተማር እዚያው ወሎ አማራ ሳይንት በተባለው ቦታ ወደ ሚገኘው ምስካበ ቅዱሳን ገዳም

www.ethiopianorthodox.org

## 3.1. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቀዳማይ

## «ጳጳስ ዘምሥራቀ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ኢየሱስ ሞዓ»

## /1875 - 1928 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

በመሔድ ወንበር ዘረጉ:: በዚያው ቦታ ለዘጠኝ ዓመታት ያህል ቅኔንና መጻሕፍትን አሰተማሩ::

ገና ከሕፃንነታቸው ጀምሮ በተገለጠው ዓይነት በመንፈሳዊ ትምህርት እየተኮተኮቱ ያደጉት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ራሳቸውን በእግዚአብሔር ቃል በሚገባ ከገነቡ በኋላ በ1909 ዓ.ም. ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመሔድ ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጸሙ:: ብዙም ሳይቆዩ መዓርገ ቅስናን ተቀብለው ከወንበሩ አገልግሎት ጋር የቤተ መቅደ ሱን ተልዕኮም ደርበው ያዙ::

ሥርዓተ ምንኩሰናንና ቅስናን በተቀበሉ በዓመታቸው በ1910 ዓ.ም. መምህር ኃይለ ማርያም ተብለው በያኤው ወላሞ ወረዳ በሚገኘው ደብረ መንክራት ምሁር ኢየሱስ ገዳም በመምህርነት ተሾሙ:: በዚያም የተሰጣቸውን ሐላፊነት ለሰድስት ዓመታት ከተወጡ በኋላ በ1916 ዓ.ም. እንደ ገና በዝዋይ ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ገዳም በመምህርነት ተሾሙ:: በዝዋይም የመምህር ነት ተግባራቸውን ለሦስት ዓመታት ያህል በአጥጋቢ ሁኔታ ካከናወኑ በኋላ በ1919 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ መምህርና በቤተ መንግሥት የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ እበ ንስሐ ሆኑ::

የግብፅ ቤተ ክርሰቲያን ምንም እንኳን ለጊዜውም ቢሆን የሊቀ ጵጵስናውን መንበር አለቅም ብትልም፤ ከአንድ ሺ ሰድስት መቶ ዓመታት በኋላ የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርሰ ቲያን በሰውቀት መንፈሳዊ ክእርስዋ ተወልደው በዕቅፏ ውስጥ ባደጉ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንድትመራ ፈቃዷን ስትገልጽ በትምህር ታቸውና በስነ ምግባራቸው የተመሰከረላቸው አምስት ኢትዮጵያ ውያን አባቶች ተመርጠው ነበር:: ከተመረጡትም አባቶች አንዱ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮሰ ነበሩ::

በዚህም መሠረት ብፁዕነታቸው ከሌሎች አባቶች ጋር ግን ቦት 18 ቀን 1921 ዓ.ም. በእስክንድርያው መንበረ ማርቆስ ቤተ ክር ሰቲያን መዓርገ ጵጵስናን ተቀበሉ:: ወደ አገራቸው ከተመለሱ ከዓመት በኋላም «አቡነ ጴጥሮሰ ጳጳስ ዘምሥራቀ ኢትዮጵያ ተላዌ እሠሩ ለአቡነ ኢየሱሰ ሞዓ» ተብለው በያኤው መንዝና ወሎ ሀገረ ሰብከት ተሾሙ:: */የሹመት ደብዳቤያቸውን በአባሪ አንድ ይመለከቷል::/*

ብፁዕ አቡነ ጴጥሮሰ ቤተ ክርስቲያን በእደራነት የሰጠ ቻቸውን ሐላፊነት ለመወጣት ሕዝበ ክርስቲያኑን በጸሎታቸው እየደገፉ፣ በትምህርታቸው እያበረቱ በማስተዳደር ላይ እንዳሉ በ1928 ዓ.ም. አረመኔው የኢጣልያ ፋሺስት በግፍ ሀገራችንን



ለመውረር ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት በማለት ባሕርን አቋርጦ መጣ:: ቅድስት ቤተ ክርሰቲያን በህገር በመጣ ወራሪቀጥተኛ ተጠቂ ናትና ሊቃውንቷ፣ ገዳማትና አድባራቷ እንዲሁም ንዋያተ ቅድሳቷ በወራሪው የኢጣልያ ኃይል ይጨፈጨፉና ይቃጠሉ ገቡ:: ይህ ግፍ በዕውቀት ከትኩታ ባሳደገቻቸው ቅድስት ቤተ ክርሰቲያን ላይ ቢፈጸም ያዩት ብፁዕነታቸው ወራሪውን ኃይል ከኢትዮጵያውያኑ አርበኞች ጋር በመሆን በጸሎት ሊዋጉት ወሰኑ::

በመጀመሪያ የወቅቱ የሀገሪቱ መሪ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ከአረመኔው ፋሺስት ጦር ጋር በመፋለም ላይ የነበረውን አርበኛ ለማበረታታት ወደ ማይ ጨው በሔዱ ጊዜ ብፁዕነታቸው ተከትለው ሔዱ:: ይሁን እንጂ ንጉሡም ሆኑ ብፁሰነ ታቸው ከሠራዊቱ ጋር ተቀላቅለው ብዙም ሳይቆዩ የጠላት ጦር በመርዝ የታገዘ ጥቃት በሰፉት በመክፈቱ የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ኋላ እንዲያፈገፍግ ሆነ:: በዚህም የተነሣ ንጉሡ ወደ አዲስ አበባ ቢመለሱ ብፁዕነታቸውም አብረው ተመለሱ:: እዚሁ እሞታለሁ ብለው እንቢ ያሉት ንጉሡ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ከሌሎች አባቶች ጋር የብፁዕነታቸው ሚና ቀላል እንዳልነበር ይነገራል::

ይሁን እንጂ በጠላት የግፍ ጥቃት ክፉኛ ያዘኑት ብፁሰነ ታቸው በአዲሰ አበባ ለመቀመጥ አልፈቀዱም:: በታላቁ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ተሰባስበው የቤተ ክርሰቲያን አምላክ እግዚአብሔር በኢትዮጵያውያን ላይ የመጣውን ችግር እንዲያሥታግስ በጸሎት እየለመኑ ወደ ነበሩት አባቶችና አርበኞች በመሔድ ለሀገርና ለነጻነት መሞት ቅዱስ ተግባር መሆኑን በመስበክ ሁሉም እንዲጋደሉ ማሳሰብ እና ማትጋት ጀመሩ:: ምንም እንኳን ድልን ባይቀዳጅም በእርሳቸው ስብከት የተነሣሡት አርበኞችም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ጠላትን ወግተዋል:: በዚህ ጊዜ ብፁሰነታቸውም አብረው ነበሩ::

ብፁዕነታቸው የነበሩበት የአርበኞች ጦር ወደ አዲስ አበባ ቢመጣም ድልን ላለመቀዳጀቱ ምክንያቱ የመረጃ ልውውጥ ክፍተት እንደ ነበረ ይነገራል:: ይኸውም «የሰላሌ አርበኞች» ተብሎ የሚታወቀው፣ በነደጃዝማች አበራ ካሣ ይመራ የነበረውና በደብረ ሊባኖስ ጫካዎች ውስጥ መሽጎ የነበረው አርበኛ ጦር በሸንኮራ በኩል ከነበረውና በደጃዝማች ፍቅረ ማርያም ይመራ ከነበረው አርበኛ ጦር፣ በምዕራብ በኩል ከነበረውና በደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሰ ይመራ ከነበረው አርበኛ ጦር ጋር በአንድ ጊዜ ተንቀሳቅሶ አዲስ አበባ ላይ ወንበሩን አደላድሎ የተቀመጠውን የግራዚያኒን ጦር ሊወጋ ይነጋገራል:: ይሁን እንጂ በሰምምነቱ መሠረት ሦስቱም የጦር ኃይል ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብሎ ወደ አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

ቢንቀሳቀስም በሦስቱም አቅጣጫ በአንድ ጊዜ ባለ መድረሉ በጠላት ላይ ያደረሰው ጉዳት ቀላል የሚባል ባይሆንም፤ በተናጠል እየተመታ ወደ መጣበት ተመለሰ። በመጀመሪያ በኮተቤ በኩል የደረሰው የደጃማች ፍቅረ ማርያም ጦር ነበር። ይህ ጦር የካ ሚካኤል ላይ ሲደርስ ተመትቶ ተመለሰ። የጠላት ጦር የደጃዝማች ፍቅረ ማርያምን ጦር ወደ መጣበት መልሶ ወደ አዲስ አበባ ሲመለስ የደጃዝማች ባልቻ ጦር በባቡር ጣቢያ በኩል መጣሁ አለ። እሱንም መትቶ መለሰ። በመጨረሻ ደግሞ የደጃዝማች አበራ ጦር በእንጦጦ በኩል አድርጎ መጣ። እሱም በጠላት ጦር ተመትቶ ተመለሰ። በዚህ ዓይነት ሦስቱም ኃይሎች በአንድ ጊዜ ባለ ማጥቃታቸው ወደ የመጡበት ሲመለሱ ከሰላሌ አርበኞች ጋር የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ጠላት ከኢትዮጵያውያኑ ነጥቆ አገሬ ከተማዬ ብሎ በመቀመጥ በመላ ሀገሪቱ የሚያካሒደውን ጭፍጨፋ የሚመራበትንና ትእዛዝ የሚያስተላልፍባትን የአዲስ አበባ ከተማ ትተው ለመሔድ አልፈቀዱም። በመሆኑም «ብቻል ጠላት በኢትዮጵያውያን ላይ እያደረሰ ያለውን ግፍ በቅርብ ርቀት ሆኖ የሚመለከተውን ሕዝብ በማትጋት በጠላት ላይ እንዲነሣ አደርገዋለሁ፤ ካል ሆነ ደግሞ እዚሁ እሞታለሁ» ብለው ከአርበኞች ተነጥለው በአዲስ አበባ ቀሩ።

ይሁን እንጂ ጠላት በመላ ከተማዋ ባሠማራቸው በርካታ ባንዳዎች መካከል ብፁዕነታቸው እንዳሰቡት ሲንቀሳቀሱ አልቻሉም። በመጨረሻ እዚሁ ከተማ ተሰውሬ መኖር አልፈልግም፤ ወደ ገጠርም ፊቴን አልመልስም በማለት ሐምሌ 22 ቀን 1928 ዓ.ም. በወቅቱ የኢጣልያ እንደራሴ ለነበሩት ለራስ ኃይሉ እጃቸውን ሰጡ። ራስ ኃይሉም ወዲያውኑ ለግራዚያኒ አሳልፈው ሰጧቸው።

ብፁዕነታቸው በተጠቀሰው ቀን እጃቸውን ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ በጠላት የጥይት አሩምታ በሰማዕትነት እስካለፉበት ጊዜ ድረስ የነበረውን ሒደት ኮርየሬ ዴላሴራ የተባለው ጋዜጣ ወኪልና የምሥራቅ አፍሪካ ዜና መዋዕል አዘጋጅ የነበረው ፖጃሌ የተባለ ጋዜጠኛ እ.ኤ.አ ሰኔ 15 ቀን 1936 ዓ.ም. አዲስ አበባ በነበረ ጊዜ በብፁዕነታቸው ላይ የተሰጠውን ፍርድና የተፈጸመውን ግድያ ባየውና በተመለከተው መንገድ እንደ ሚከተለው ጽፎ ነበር።

«ሐምሌ 22 ቀን 1928 አቡነ ጴጥሮስ ተይዘው ወደ ግራዝያኒ ቀረቡ። በዚህ ጊዜ አቡነ ቄርሎስ የተባሉት «ግብፃዊ ጳጳስ ቀርበው ለእስክንድርያው መንበረ ፓትርያርክ ምክር ቤት ሳታሰማ በአቡነ ጴጥሮስ ላይ አንዳች ነገር ማድረግ አይገባህም» ሲሉ ለግራዝያኒ ነገሩት። ምክንያቱም ይላሉ አቡነ ቄርሎስ፤ «አቡነ ጴጥሮስ ታላቅ ሰው ናቸው። በመሠረቱ ሲያዙ ባልተገባ ነበር። ከተያዙም ደግሞ ልትገድላቸው ትችላለህ። ነገር ግን በእርሳቸው ላይ



የምታደርገውን ነገር ሁሉ ለእስክንድርያው መንበረ ፓትርያርክ ምክር ቤት ሳታሰማ ምንም ማድረግ አይገባህም» አሉት።

አቡነ ቄርሎስ ይህን ማለታቸው በዲፕሎማቲክ ደረጃ ለዓለም ለማሰማትና የአቡነ ጴጥሮስን ሕይወት ለማትረፍ አስበው እንደ ነበር ግልጥ ነው። ነገር ግን ግራዝያኒ ይህ የአቡነ ጴጥሮስ የሞት ፍርድ እንኳንስ እስከ ግብፅ ከአዲስ አበባ ውጭ እንኳ ከመሰማቱ በፊት በግማሽ ቀን እንዲፈጸም ትእዛዝ አስተላለፈ። በእርግጥ ምንም እንኳን ከመገደል ባያመልጡም ብፁዕነታቸው እንደ ተያዙ ንቡረ ዕድ ተክለ ሃይማኖት /ሐዲስ ተክሌ/ና ሌሎች ሲቃውንት ወደ አቡነ ጴጥሮስ ዘንድ በመሔድ ግልደዋቸው ነበር ይባላል።

«ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቁመታቸው ረዘም፣ ፊታቸውም ዘለግ ያለ፣ መልካቸው ጠየም ያለ፣ ዐዋቂነታቸውና ትሕትናቸው ከገጻቸው የሚነበብ ሲሆን በዚህ ጊዜ ለብሰውት የነበረው ልብሰ ጵጵስና ጥቁር ካባ ያውም በጭቃ የተበከለ ነበር። በዚህ ሁኔታ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ወደ ችሎት ቀረቡ። ለፍርድም የተሠየሙት ዳኞች ሦስት ሲሆኑ እነዚህም ጣሊያኖችና የጦር ሹማምንት ናቸው። የመካከለኛው ዳኛ ኮሎኔል ነበር። የቀረበባቸውም ወንጀል ሕዝብ ቀስቅሰዋል፣ ራስዎም ዐምፀዋል፣ ሌሎችንም እንዲያምፁ አድርገዋል የሚል ነበር። ዳኛውም «ካህናቱም ሆኑ የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስም የኢጣሊያንን መንግሥት ገዢነት አምነው አሜን ብለው ሲቀበሉ እርስዎ ለምን ዐመፁ? ለምን ብቻዎን አፈንጋጭ ሆኑ?» ሲል ጠየቃቸው።

«አቡነ ጴጥሮስም የሚከተለውን መለሱ። «አቡነ ቄርሎስ ግብፃዊ ናቸው፤ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የሚገዳቸው ነገር የለም። እኔ ግን ኢትዮጵያዊ ነኝ። ሐላፊነትም ያለብኝ የቤተ ክርስቲያን አባት ነኝ። ስለዚህ ስለ ሀገሬና ስለ ቤተ ክርስቲያኔ አቆረ ቆራለሁ። ከዚህ በቀር ለእናንተ ችሎት የማቀርበው ነገር የለኝም። ለፈጣሪዬ ብቻ የምናገረውን እናገራለሁ። እኔን ለመግደል እንደ ወሰናችሁ ዐውቃለሁ። ስለዚህ በእኔ ላይ የፈለጋችሁትን አድርጉ። ግን ተከታዮቼን አትንኩ» አሉ።

«ይህንንም ብለው በጥይት ተደብድበው ሲገደሉ እንዲያይ ተጋብዞ ለተሰበሰበው ሕዝብ የሚከተለውን ሕያው መልእክት አስተላለፉ፦ «አረማዊ የሆነው የፋሺስት መንግሥት ቤተ ክርስቲያንን ለማቃጠል፣ ሕዝበ ክርስቲያንን ለመግደል፣ ሃይማኖትን ለማጥፋት፣ ታሪካችንን ለማበላሸት የመጣ ነው፤ እንጂ በጎ ለመሥራት እውነተኛ ፍርድ ለመስጠት ስላልመጣ ለዚህ ለግፈኛ አትገዙ። ስለ ውድ ሀገራችሁ፣ ስለ ቀናች ሃይማኖታችሁ ተከላከሉ። ነጻነታችሁ ከሚረክስ ሙታችሁ ስማችሁ ሲቀደስ ታላቅ ዋጋ ያለው

www.ethiopianorthodox.org

ክብር ታገኛላችሁ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዚህ ለጠላት እንዳይገዛ አውግዠለሁ፤ የኢትዮጵያ መሬት ጠላትን ብትቀበል የተረገመች ትሁን:: በፈጣሪዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የተገዘተች ትሁን::»

ጋዜጠኛው ይቀጥላል:: «እኒህ ጳጳስ ሐቀኛ ነበሩ:: ነገር ግን ለኢጣሊያ ለጋስዮን ታዝዞ የመጣው አስተርጓሚ ዳኞች የሚሉትን ብቻ ከማስተርጐም በቀር ጳጳሱ የሚናገሩትን ሐቀኛ ንግግር አላስተረጐመም:: እኔ እንኳን የሰማሁት በአዲስ አበባ ለሠላሳ ዓመት የኖረው የእቴጌ ሆቴል ሐላፊ የነበረው የግሪክ ዜጋ ማንድራኮስ አጠገቤ ተቀምጦ ስለ ነበር የተናገሩትን ሁሉ ስለ ገለጠልኝ ነው:: እኔ እንደ ሰማሁት ፍርዱን ለመስማት በብዛት የተሰበሰቡት ጣሊያኖችና ታዝዞ የወጣው የአዲስ አበባ ሕዝብ ሐቀኛ የሆነውን ንግግራቸውን ቢሰሙ ኖሮ ልባቸው ይነካ ነበር» ይላል::

«ሆኖም አስተርጓሚው በጳጳሱ ላይ ተጽዕኖ ስላሳደረባቸው እውነተኛ ንግግራቸው ሳይገለጥ ቀረ:: ቀጥሎም ብፁዕነታቸው በፍርድ ችሎት ላይ እንዳሉ ሕዝቡ ሁሉ ስለ ርሳቸው አያዝን ባለ መስቀላቸውን አውጥተው እየጸለዩ ሕዝቡን ባረኩ:: ወዲያው የሞታቸው ፍርድ ሲሰማ ሕዝቡ በኢጣልያ የእጅ ሰላምታ ዓይነት እጁን እንዲያነሣ ታዘዘ:: በዚያን ጊዜ አቡነ ጴጥሮስ የሞታቸው ሰዓት መድረሱን ሀውቀው ሰዓታቸውን ከኪሳቸው አውጥተው ተመለከቱ:: በዚህ ጊዜ ሁሉ ምንም ፍርሃት አይታይባቸውም ነበር:: የሞታቸውን ፍርድ ያነብ የነበረው ኢጣሊያዊ ዳኛ ግን ይንቀጠቀጥ ነበር:: ታላቅ ፍርሃትም በፊቱ ላይ ይታይ ነበር::

«ይሙት በቃ የተፈረደባቸው ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በችሎት ፊት ለብዙ ሰዓታት ቆመው ስለዋሉና ደክሞአቸው ስለ ነበር ለመቀመጥ ፈልገው ዳኛውን በትሕትናና በፈገግታ ጠየቁት:: እንዲቀመጡም ፈቀደላቸው:: በመጨረሻም የሞታቸው ፍርድ ከተነበበ በኋላ የፈረዱባቸውን ዳኞች ጸልየው በመስቀላቸው ባረኩዋቸው:: ብፁዕነታቸው እስከ መቃብር አፋፍ ድረስ የፍርሃትና የድንጋጤ ምልክት ያይደለ ክልብ የሆነ ፍጹም ቆራጥነት ይታይባቸው ነበር::

«የሀገራቸው በጠላት መወረር፣ የሕዝባቸው መገደልና መታሰር፣ የቤተ ክርስቲያናቸው መደፈር እስከ ሞት ያደረሳቸው እኒህ እውነተኛ ጳጳስ ለመገደል ሲወሰዱ ጥይት አልፎ ሌላ ሰው እንዳይጐዳ ግንብ ይፈለግ ጀመር:: ሩቅ ባለ መሔድ ከመካነ ፍትሑ 10 ሜትር ርቆ ግንብ ያለው መግደያ ቦታ ተገኘና ወደ ዚያ ተወሰዱ:: ከገዳዮቹም አንዱ «ፊትዎን ለመሸፈን ይፈልጋሉን?» ሲል ጠየቃቸው:: «ይህ የአንተ ሥራ ነው» ሲሉ ብፁዕነታቸው መለሱ:: ከመግደያውም ቦታ እንደ ደረሱ ወንበር ቀረበላቸውና ፊታቸውን ወደ ግንቡ ጀርባቸውን ወደ ሕዝቡ አድርገው እንዲቀመጡ ሆኑ::



«ከዚያ በኋላ ስምንት ወታደሮች በስተ ጀርባቸው ሃያ ርምጃ ርቀው ተንበርክከው በተጠንቀቅ ቆሙ:: ወዲያው አዛዡ «ተኩስ» በማለት ትእዛዝ ሲሰጥ ስምንቱም ተኩሰው መቱዋቸው:: ግን በስምንት ጥይት ሳይሞቱ ቀሩ:: መሞታቸውንና አለመሞታቸውን ለማረጋገጥ ዶክተር ተጠራ:: ዶክተሩም እንዳልሞቱ አረጋገጠ:: ከዚያም ሌላ ወታደር በሦስት የሽጉጥ ጥይት ራስ ቅላቸውን መትቶ ገደላቸው:: ብፁዕነታቸው የተገደሉበት ቦታ መኻል አዲስ አበባ ዛሬ መታሰቢያ ሐውልታቸው ቆሞ በሚገኝበት ቦታ አካባቢ ነው::

«የብፁዕነታቸው አስክሬን ማንም አንዳ ይወስደው በአስቸኳይ ክአዲስ አበባ ውጭ ማንም በማያውቀው ቦታ በምሥጢር እንዲቀበር ተደረገ:: በዚያች ሌሊት በአዲስ አበባ ውስጥ በየቤቱ ልቅሶና ዋይታ ሆነ::» /<u>ትንሣኤ</u>፣ ቁጥር 58፣ 1978 ዓ.ም./::

ይህ ጋዜጠኛ የሰጠው ምስክርነት የኢትዮጵያን ሕዝብ ጀግንነት ሲያረጋግጥ ይኖራል:: የብፁዕነታቸውን በድን በተመለከተ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች ቅዱሳን መላእክት የጻድቃንን በድን አያመጡ እንደ ሚያስቀምጡበትና በውስጡ የሚቀመጥ አስክሬን እንደ ማይፈርስ ወደ ሚነገርለት አቡነ መልከ ጸዴቅ ዋሻ /ሰሜን ሸዋ/ መላእክት ወስደው እንዳስቀመጡትና በዚያ እንደ ታዩ ይናገራሉ::

ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በአደባባይ በተሰበሰበ ሕዝብ ፊት የሰማዕትነት ጽዋቸውን ሲቀበሉ ክሕዝቡ ጋር ሆና ታይ የነበረች አንዲት ክድጃ የምትባል የእስልምና እምነት ተከታይ ሴት በብፁዕነታቸው ፍፁም አባታዊ ቆራጥነት ተማርካ የእኒህን አባት እምነት አከተላለሁ ብላ በመጠመቅ ክርስቲያን ሆናለች ይባላል::

በተጨማሪም ደራሲና ጋዜጠኛ ጳውሎስ ኞኞ «አቡነ ጴጥሮስ እንዴት ሞቱ?» ሲል ሙሴ ፓይላክን ጠይቆአቸው እርሳቸውም የሚከተለውን ተናግረዋል:: «አቡነ ጴጥሮስ የተገደሉ ዕለት እዚያው ነበርኩ:: መጀመሪያ በእጃቸው ይዘውት የነበረውን መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ተሳለሙት:: ቀጥለውም በያዙት መስቀል አማትበው ሕዝቡን ባረኩ:: የኪሳቸውንም ሰዓት አውጥተው ካዩ በኋላ መልሰው ክኪሳቸው ከተቱት:: ወዲያው ወታደሮች በሩምታ ተኩሰው ገደሉዋቸው:: ይህ እንደ ሆነ አስገዳዩ ኮሎኔል ተመልካቹን ሕዝብ አጨብጭቡ ብሎ አዘዘና ተጨበጨበ::

ማታ ክአስገዳዩ ኮሎኔል ጋር ተገናኝተን ስንጫወት «በዚህ ቄስ መገደል እኮ ሕዝቡ ተደስቷል» አለኝ:: «እንዴት?» ብለው «አላየሀም ሲያጨበጭብ» አለኝ:: እኔም «ባታውቀው ነው እንጂ የሕዝቡ ባሕል ሲናደድም ያጨበጭባል» አልኩት:: «እንዴት?»

www.ethiopianorthodox.org

ቢለኝ እጄን እያጨበጨብኩ አሳየሁት:: እሱም አሳየኝ:: «ከዚህ በኋላ የሆነው ቢሆን እኔ ትልቅ ማስታወሻ አግኝቼአለሁ» ብሎ አቡነ ጴጥሮስ ሲገደሉ ይዘውት የነበረውን መስቀልና መጽሐፍ ቅዱስ፣ የኪስ ሰዓታቸውን ጭምር አሳየኝ:: መጽሐፍ ቅዱሱ መሐል ለመሐል በጥይት ተሰንጥቋል:: መስቀሉም ልክ በመሐከሉ ላይ ጥይት በስቶት ወጥቷል:: የኪስ ሰዓታቸውንም እንዳየሁት እንደዚሁ ጥይት በስቶታል» ብለው ያዩትን መስክረዋል::» /ዝኒ ከማሁ./::

የብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ጥብአት ማለትም ለሀገራቸውና ለእምነታቸው እስከ መጨረሻዋ ሰዓት ድረስ መስክሮ ማለፍ ምክንያቱ በልጅነታቸው ከቅኔ መምህራቸው የሰሙት የአደራ ቃል እንደሆነ ይነገራል:: አለቃ ተጠምቆ የተባሉ ቅድስናን ከሊቅነት አስተባብረው የያዙ መምህራቸው አንድ ቀን ብፁዕነታቸውን ጠርተው «ኃይለ ማርያም፤ አንተ ወደ ፊት ጳጳስ ትሆናለህ:: በዚያ ጊዜ አረመኔ በዚህች ሀገር ይሠለጥናል:: ታዲያ ያኔ አንተ ለነፍስህ ሳትሰቀቅ በሰማዕትነት እለፍ:: ሰማዕትነት ክፍልህ ነው:: አደራ» ብለዋቸው ነበር ይባላል:: ይህንን የመምህራቸውን የአደራ ቃል የያዙት ብፁዕነታቸው እስከ መጨረሻው ለነፍሳቸው ሳይፈሩ፣ እንዲትም ቀን ሳይሸሹ ከላይ በቀረበው ሁኔታ የሰማዕትነት ጽዋቸውን ሊቀበሉ ችለዋል::

ጠላት ድል ተደርጎ ሀገራችን ነፃነቷን ከተቀዳጀች በኋላ የብፁዕነታቸውን አኩሪ ታሪክ ትውልድ ቢያዘክርላቸው እንዲኖር መታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ በግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት አጋጋቢነት ሐምሌ 16 ቀን 1938 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ እምብርት ሐውልት ቆሞላቸዋል:: ከድል በኋላ የብፁዕነታቸው ሐውልት ተመርቆ የቤተ መንግሥቱም ሆኑ የቤተ ክህነቱ ባለሥልጣናት የአበባ ጉንጉን ከሐውልቱ ሥር ቢያስቀምጡ ከቤተ ክህነት ካስቀመጡት አባቶች አንዱ በ1921 ዓ.ም አብረዋቸው የተሾሙት ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ነበሩ:: የሐቀኛው አባታችን በረከት ይደርብን:: አሜን::



## 3.2. ብፁዕ አቡነ አብርሃም ቀዳማዊ

## «ጳጳስ ዘምዕራብ ኢትዮጵያ ተሳዌ አሡሩ ለአቡነ ሐራ»

## /1861 – 1931 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

# 3.2. ብፁዕ አቡነ አብርሃም ቀዳማዊ

## «ጳጳስ ዘምዕራብ ኢትዮጵያ ተሳዬ አሡሩ ለአቡነ ሐራ»

## /1861 – 1931 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ አቡነ አብርሃም በጎጃም ሀገረ ስብከት በሞጣ አውራጃ ልዩ ስሙ አሽመን ከተባለው ቦታ ሐምሌ 5 ቀን 1861 ዓ.ም. ተወለዱ:: ለድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በምሥጢረ ጥምቀት ልጅነትን ባገኙባትና አጥቢያቸው በሆነችው የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊደል እና የቃል ትምህርቱን ተምረው ዳዊት ደገሙ::

ከወላጆቻቸው ሳይርቁ በእማረ ሁናቴ የጀመሩትን ትምህርት በመቀጠል በአካባቢያቸው ወደ ሚገኙ የዜማና የቅኔ ትምህርት ቤቶች በመዘዋወር ጸዋትወ ዜማንና ቅኔን በአግባቡ ተማሩ:: በመቀጠልም በወቅቱ በጎጃም ክፍለ ሀገር ስመ ጥር የመጻሕፍት ትርጓሜ ቤት ከነበረው ሞጣ ጊዮርጊስ ብሉያቱንና ሐዲሳቱን አጠኑ:: መጻሕፍተ ሊቃውንቱንና መነኮሳቱንም በሚገባ አጠናቀቁ::

ብፁዕነታቸው የተማሯቸኩት ትምህርት ይበቃኛል ሳይሉ ዕውቀታቸውን ለማስፋፋት ወሎ ቦሩ ሥላሴ ወደ ነበሩት ስመ ጥርው መ/ር አካለ ወልድ ዘንድ ሔዱ:: ጎጃም የተማሩትን እንደ ገና እንደ አዲስ በመጀመር አራቱንም ጉባኤያት በሚገባ በመከለስ ዕውቀታቸውን አስፋፉ:: የብፁዕ አቡነ አብርሃምን ሊቅነት ያዩ የመ/ር አካለ ወልድ ተማሪዎች ከመማር ጐን ለጐን ጉባኤ ዘርግተው እንዲያስተምሩ ጥያቄ አቀረቡ:: መምህር አካለ ወልድም የተማሪዎቻቸውን ጥያቄ ተቀብለው ቁጥሩ ከበዛው ተማሪያቸው በመክፈል የተወሰኑ ተማሪዎች ለብፁዕነታቸው ሰጧቸውና እየተማሩ ማስተማር ጀመሩ:: ብፁዕነታቸው ለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ምሥጢር ከምሥጢር አገናኝተው፣ የራቀውን አቅርበው፣ የረቀቀውን አፍታተው ሲያቀርቡ እንኳን ተማሪዎቻቸው ታላቁ ሊቅ መ/ር አካለ ወልድም ይደነቁ ነበር ይባላል::

ቦሩ ሥላሴ ከላይ በተገለጠው ሁኔታ እያስተማሩ ረዘም ላለ ጊዜ ከመምህር አካለ ወልድ ዘንድ ከተማሩና የምስክር ወረቀታቸውን ከያዙ በኋላ ወደ ተወለዱበት አካባቢ ጎጃም በመሔድ ጉባኤያቸውን አስፋፍተው ማስተማር ጀመሩ:: የዘረጉት ጉባኤ ዕለት ከዕለት እየሰፋና እየጐለበተ በመምጣት ላይ ሳለ እንደ አባታቸው አብርሃም አበ ብዙኃን ሊያደርጋቸው ያሰበ እምላክ በስውር ጥበቡ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ አደረገ::

ከጎጃም ተነሥተው ወደ አዲስ አበባ የመጡት ብፁዕ አቡነ አብርሃም ሳይውሉ ሳያድሩ በአዲስ አበባው መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በእልቅና ተሾሙ:: ብፁዕነታቸው በዚያ ጊዜ የንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ የጸሎት መጻሕፍት አንባቢና አሳላሚ ሆነው ያገለግሉ ነበር:: ከተሾሙም በኋላ ሊቅነታቸውን የሰሙ የመጻሕፍት ተማሪዎች ከክፍለ ሀገርም ሆነ ከአዲስ አበባ በመሰብሰብ ስለ ከበቧቸው ጉባኤያቸው ከሙሉውም ጊዜ



በበለጠ ሁኔታ እየሰፋ መጣ:: በዚህም ሐዲስ ለሚማረው ሐዲስ፣ ብሉይ ለሚማረው ብሉይ፣ ሊቃውንት ለሚማረው መጻሕፍተ ሊቃውንት፣ መነኮሳት ለሚፈልገው መጻሕፍተ መነኮሳት በየዓይነቱ በሚያጠግብ ሁኔታ ያስተምሩ ጀመር:: ለተማረው ዕውቀት መንፈሳዊን ከመመገብ ጋርም ዐቅማቸው የፈቀደውን ያህል ለተራበው እያጐረሱ፣ ለተጠማው እያጠጡ፣ ለታረዘው እያለበሱ ተማሪዎቻቸውን ይንከባከቡ ነበር ይባላል::

በዚህ ዓይነት ለተወሰኑ ዓመታት የቆዩት ብፁዕ አቡነ አብርሃም በቤተ ክርስቲያኗና በሀገሪቱ መንግሥት በ1921 ዓ.ም. በተደረገው የእጩ ጳጳሳት ምርጫ ከተመረጡት አባቶች አንዱ ሆኑ::

በዚህም ብፁዕነታቸው ግንቦት 18 ቀን 1921 ዓ.ም. በካይሮ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች ሦስት ወንድሞቻቸው ጋር መዓርገ ጵጵስናን ተቀበሉ:: ወደ ሀገራቸው ከተመለሱም በኋላ «አባ አብርሃም ጳጳስ ዘምዕራብ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ሐራ » በሚል ተሠይመው በጎጃም፣ በጎንደርና በሜን አህጉረ ስብከት ተሾሙ:: /*የሹመት ደብዳቤያቸውን በአባሪ 1 ይመለከቷል*/::

ከሕፃንነታቸው ጀምሮ ለትምህርት ሲሉ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ የኖሩት ብፁዕ አቡነ አብርሃም ቅዱሳት መጻሕፍትን አብዝተው ከመመርመራቸው የተነሣ ዓይናቸውን፣ ትጎርምት ከማብዛታቸው የተነሣም አንጀታቸውን በተለያዩ ጊዜያት ያማቸው ነበር:: ይሁን እንጂ የሚደርስባቸው ሥጋዊ ፈተና እንቅፋት ሳይሆንባቸው ሕማሙ ጠንቶባቸው አልጋ ላይ እስኪውሉ ድረስ ሕዝበ ክርስቲያኑን ከማስተማር፣ ሥራቸውንም ከመሥራት አልታቀቡም ነበር:: በዚህ ሁሉ ደገኛ ተግባራቸው የተነሣ ምእመናን «አማናዊው አብርሃም» እያሉ ይጠሯቸው ነበር ይባላል::

ብፁዕነታቸው ቃለ እግዚአብሔርን ለሕዝበ ምእመናን በማዳረስ በኩል ላቅ ያለ አስተዋጽኦ ያበረከቱ አባት ነበሩ:: ከዚህም ውስጥ የሚጠቀሰው በዐውደ ምሕረት ቃለ እግዚአብሔርን ለምእመናን መስበክ በመጀመር የከፈቱት አዲስ የአገልግሎት መስመር ነው:: ብፁዕነታቸው ይህንን አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት ቃለ እግዚአብሔር በቅዳሴ ጊዜ ተነበ በአጭሩ ከሚተረጎም በስተቀር በባለፉን ለስብከተ ወንጌል በፊ መርሐ ግብር ይዘው ምእመናንን አያስተምሩም ነበር:: የዐውደ ምሕረት ስብከተ ወንጌል አገልግሎት በብፁዕነታቸው ከተጀመረ በኋላ ግን ይኸውና ዛሬ ድረስ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን ዘወትር በሠርክ በዐውደ ምሕረት እየተሰባሰቡ ቃለ እግዚአብሔርን ይማራሉ::

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ አቡነ አብርሃም የሀውደ ምሕረትን የስብከተ ወንጌል አገልግሎት እንዲያከናውኑ የነፍስ ልጃቸው የነበሩት ንግሥተ ንገሥታት ዘውዲቱ ትልቅ ድጋፍ እንዳደረጉላቸው ይነገራል። እንደ ሚታወቀው ንግሥተ ንገሥታት ዘውዲቱ ለቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ካህናት ይሰጡት ከነበረው አክብሮትና ከብካቤ እንዲሁም ሥልጣን የተነሣ የእሳቸው ዘመን «ዘመነ ካህናት» ተብሎ ይጠራል።

ከላይ እንደ ተገለጠው ብፁዕነታቸው በነበራቸው ዕውቀትና ቅድስና በንግሥቷ ዘመን በቤተ መንግሥቱ ላቅ ያለ ከብርና ሥልጣን ካገኙት አባቶች አንዱ ነበሩ። የንግሥቷ አበ ነፍስ በመሆናቸው በቤተ መንግሥቱ አካባቢ በነበረው መንፈሳዊ እንቅስቃሴና በሚወጣው መመሪያ ትልቅ ተሳትፎ ነበራቸው። ታዲያ በዚህ መዓርግና አገልግሎት ላይ ሳሉ ንግሥቷ ከዚህ ዓለም በሞት ይለያሉ። በዚህ የተነሣ ምንም እንኳን በንግሥቷ ሞት መላው የኢትዮጵየያ ሕዝብ ይልቁንም በንግሥቷ እንክብካቤ ለከፍተኛ ሹመትና መዓርግ የበቁት ሊቃውንት በእጅጉ አዝነው ነበር። ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ደግሞ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ነበሩ ታዲያ ብፁዕነታቸው ዘወትር ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ይህንን ሐዘናቸውን ይገልጹ ነበር ይባላል። አንድ ቀን እንደ ተለመደው በዐውደ ምሕረት ቃለ እግዚአብሔርን ለምእመናን ሲያሰሙ ያስተማሩበት ርዕስ «አንከሰ ጸርሐት ቤተ ክርስቲያን ፤ እንግዲህስ ቤተ ክርስቲያን ትጮኻለች» የሚል ነበር። በዚህ ርዕስ በነበራቸው የጣዕመ ስብከት ጸጋ በቃለ እግዚአብሔር እያዋዙ ንግሥተ ንግሥታቷ አዝነውና ተጎሳቁለው ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ቤተ ክርስቲያን እንደምታዝን፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያንና ልጆቿ ያደረጉትን በጎ ሥራ ሁሉ ቆጥሮ ነፍሳቸውን በአብርሃም፣ በይስሐቅና በያዕቆብ አጠገብ እንዲያበቀምጥ ቤተ ክርስቲያን በእጅጉ እንደ ምትጸልይ ያስተምራሉ። ይህንኑ ትምህርታቸውን በሌሎች ጉባኤያትም ይደጋግማሉ። በዚህ ጊዜ ብፁዕነታቸው ስለ ንግሥተ ንገሥታቷ መሞት የተሰማቸውን ሐዘንና ስለ አሟሟታቸው ሁኔታ በዐውደ ምሕረት እየገለጹ እንደሆነ ንጉሡ ይሰማሉ። ንጉሡም ወዲያውኑ ብፁዕነታቸውን አስጠርተው «ምነው በንግሥተ ንግሥታቷ ማረፍ ይኸንን ያህል አዘኑ? እኛስ ክርስቲያኖች አይደለንም እንዴ? እንደዚህ ሊሆኑ አይገባም» አሏቸው። ብፁዕነታቸውም የንጉሡን አባባል ባለመቀበል «ሐዘንተኛ እንደ ቢጤቱ ነው የሚያለቅሰው። በተሰማው መንገድ ሊያለቅስ ይችላል እንጂ በዚህ መንገድ አልቅስ፤ በዚያ መንገድ አታልቅስ አይባልም» አሏቸው ይባላል።

ብፁዕነታቸው በተለይ በሀገረ በብከታቸው ጎጃም ሕዝቡ ቃለ ወንጌል በሰፊው እንዲሰማ፣ የአብነት ትምህርት ቤቶች እንዲስፋፉ፣



ሊቃውንትም ርበት ጉልት እንዲያገኙ ስፊ ጥረት ያደርጉ ነበር ይባላል። በወቅቱ በአካባቢው የቅብዐት ትምህርት በስፋት ነበረና የቅብዐት ሊቃውንትን ጥልቅ በሆነ ዕውቀታቸው በቃልም በመጣፍም ይረቷቸውና ያስረቷቸው እንደ ነበር ይነገራል። በዚህ ከተደበቱት የተዋሕዶ ሊቃውንት መካከል አንዱ በቅኔ ሊያወድሳቸው የሚከተለውን ሐረግ ሊቀኝ፤ በጅምሩ የተደሰቱት ብፁዕነታቸው ወደ ሁለተኛው ሐረግ ሳይሔድ «በቃ በቃ፤ ይኸው ይበቃል ታበለሽዋለህ» አሉት ይባላል። በመሆኑም እስከ ዛሬ ድረስ በርካታ ሊቃውንት የሚያውቋት ከዚህ በታች የተጻፈችዋን ስንኝ ብቻ ነው።

*አ አብርሃም ነድዐ የቅብዐት ማቅለሜ*

ታዲያ አንረታም ያሉት የቅብዐት መምህራንም ለተበረከ ተላቸው ቅኔ መልስ ይሆን ዘንድ በሚከተለው ሐረግ የሚጀምር ቅኔ ዘርፈዋል ይባላል።

*ቅብዕ እስመ ያለፍእ ለአብራም አነዳ*

ብፁዕነታቸው በጎጃም ባበረከቱት ስፊ አገልግሎት ዛሬ ድረስ በአካባቢው አረጋውያን ዘንድ ስማቸው አልተረሳም። ከላይ እንደ ተገለጠው በነበራቸው ሊቅነት የቅብዐትን ሊቃውንት ከመርታታቸው በተጨማሪ በነበራቸው የተቸገረን የመርዳት ጸጋ በገንዘባቸው እየረዱ ብዙዎችን አስተምረው ለወግ ለመዓርግ አብቅተዋልና።

ብፁዕነታቸው የኢጣልያ ወራሪ ጦር ሀገራችንን በግፍ በወረረ ጊዜ በሊቃውንት ተመርጠው ግብፃዊው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ ትተውት የሔዱትን መንበረ ጵጵስና ኅዳር 21 ቀን 1930 ዓ.ም በመረከብ በሊቀ ጳጳሳትነት እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው በቅንነትና በትጋት አገልግለዋል። በተሾሙበት ዕለትም እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ ውሳኔ ሌሎች አምስት ጳጳሳትንና አንድ ኤጲስ ቆጳስን ሹመዋል። እነሱም እቡነ ዮሐንስ ጳጳስ ዘሸዋ፣ አቡነ ማርቆስ ጳጳስ ዘኤርትራ፣ አቡነ ሰላማ ጳጳስ ዘሐረር፣ አቡነ ገብርኤል ጳጳስ ዘጎንደር፣ አቡነ ማቴዎስ ጳጳስ ዘወሎና አቡነ ሉቃስ ጳጳስ ዘወለጋ ናቸው። በምዕራፍ አንድ እንደ ተገለጠው በዚህ የተነሣ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን አላግባብ አውግዛቸው ነበር።

በመጨረሻ ብፁዕነታቸው በዚህ ዓለም ከአንድ መንፈሳዊ አባት የሚጠበቀውን ካከናወኑ በኋላ ሐምሌ 24 ቀን 1931 ዓ.ም. ስኞ ከጠዋቱ ልክ በአንድ ሰዓት ተኩል ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

www.ethiopianorthodox.org


ሐምሌ 26 ቀን 1931 ዓ.ም. ለሊቀ ጳጳሳት ዕረፍት የሚገባው ጸሎተ ፍትሐት ከተደረገ በኋላ ሥርዓተ ቀብራቸው አዲስ አበባ በሚገኘው የቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቤተ መቅደስ መንበር አጠገብ ተፈጸመ:: የብፁዕነታቸው በረከት ይደርብን:: አሜን::



## 3.3. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ቀዳማዊ

### «ጳጳስ ዘአዜበ ኢትዮጵያ ተሳዊ አሠሩ ለአቡነ ዜና ማርቆስ»

/1870 – 1929 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

# 3.3. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ቀዳማዊ

## «ጳጳስ ዘአዜበ ኢትዮጵያ ተሳዌ አሡሩ ለአቡነ ዜና ማርቆስ»

## /1870 – 1929 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

መዓርገ ጵጵስናን ከመቀበላቸው በፊት አባ ኃይለ ሚካኤል ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በቀድሞው ቤጌምድር ጠቅላይ ግዛት አፈረ ዋናት ልጫ መስቀለ ክርስቶስ በተባለ ቦታ ተወለዱ። በዚያው በተወለዱበትም አካባቢ ግንድ አጠመም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በጥምቀት እንደ ገና ሲወለዱ ስመ ጥምቀታቸው ኃይለ ሚካኤል ተባለ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በትውልድ ሀገራ ቸው ግንድ አጥም ሚካኤል በተባለው ቤተ ክርስቲያን ከነበሩት መሪ ጌታ ዋሴ ከተባሉ አስተማሪ የመጀመሪያ ደረጃ የቤተ ክህነት ትምህርታቸውን አጠናቀቁ። ከዚያ በኋላ ከግብፃዊው አቡነ ጴጥሮስ መዓርገ ዲቁና ተቀብለው በዚያው በትውልድ ሀገራቸው ዘገበ ጽዮን በተባለ ቤተ መቅደስ በዲቁና አገለገሉ።

ብፁዕነታቸው ትምህርታቸውን በመቀጠል እዚያው ጎንደር መካነ ሰማዕት ቅዱስ ገላውዴዎስ ቤተ ክርሰቲያን ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ወደ ነበሩት መሪ ጌታ ተድላ ዘንድ ሔደው ጸዋትወ ዜማን፣ ማኅደረ ማርያም ከነበሩት መ/ር ወልደ ሩፋኤልም ድጓ በሚገባ ተማሩ።

የዜማ ትምህርታቸውን በተገለጠው ሁኔታ ያጠናቀቁት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል መጻሕፍትን ለመማር በነበራቸው ፍላጐት የተነሣ ወደ ጎንደር ከተማ በመሔድ ከመ/ር ተስፋዬ ዘንድ የብሉ ያትንና የሐዲሳትን ትርጓሜ በሚገባ ተማሩ። በጎንደር የጀመሩትን የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርት የበለጠ መማር እንዳለባቸው ሕሊናቸው ስላነሣሣቸው በወቅቱ ስመ ጥር ወደ ነበሩትና ቀደም ሲል ታሪካቸው የቀረበላቸው አባቶች መምህር ወደ ነበሩት መምህር አካለ ወልድ ዘንድ ተሻገሩ። በዚያም ሐዲሳቱን በሚገባ በማስፋፋትና ቅኔን ከነምሥጢሩና አገባቡ ጠንቅቀው ለቅኔ መምህርነት በቅተዋል።

መንፈሳዊውን ትምህርት ከዳር ለማድረስ ቆርጠው የተነሡት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ከቦሩ ሥላሴ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር ሰፊ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት መ/ር ወልደ ጊዮርጊስ ዘንድ የዓሥራ አራቱን ቅዳሴያት ዜማ በጥንቃቄ ተማሩ። በዚህ ጊዜ በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ግብፃዊው አቡነ ማቴዎስ መዓርገ ቅስናን ተቀበሉ።

በዚህ ሁሉ ሒደታቸው፣ ትምህርታቸውና ግብረ ገብነታቸው በሰዎች ዘንድ ስለ ተመለከረ ይህም በቤተ መንግሥቱ በመለማቱ ለመኳንንቱ፣ ለመሣፍንቱና ለወይዛዝርቱ አበ ነፍስ ለመሆን በቁ። ሞያቸውና ግብረ ገብነታቸው የበለጠ ከዕለት ወደ ዕለት እየተጠ ናከረና እየተመሰከረ በመሔዱም ከአበ ነፍስነት አገልግሎት አልፎ



ወደ ቤተ መንግሥቱ በመግባት የምክር ድጋፍ እንዲያደርጉ ተሾሙ።

ከንጉሡ ቤተ መንግሥት በሚወጣው ሕግና መመሪያ በቀ ጥታ ተሳታፊ በመሆን በማገልገል ላይ የነበሩት ብፁዕነታቸው ከዚያ ከፍ ላለውና ለትምህርታቸውና ለማንነታቸው ተስማሚ የሆነ ቦታ ተመርጠላቸው የዜና ማርቆስና የዝቋላ ገዳማት አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ። የተሰጣቸውን ሐላፊነት በብቃት እየተወጡ ጥቂት ዓመ ታት ከቆዩ በኋላ እንደ ገና በአዲስ አበባው ደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራ ኤል፣ ቀይቶም በማኅደረ ማርያም በአልቅና ተሹመው ለምእመናኑ ትምህርት በመስጠት፣ ካህናትን በማትጋት ሲያገለግሉ ቆዩ።

በኮፕትና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ለረጅም ዘመናት ዘልቆ የነበረው የጵጵስና ሹመት ክርክር ተፈጽሞ ኢትዮጵያውያን ወደ ጵጵስና ሹመት መድረክ እንዲቀርቡ በተደረገ ጊዜ ለታላቁ ሹመት ከተመረጡት አባቶች ብፁዕ አቡነ ሚካኤል አንዱ ሆኑ። ከሌሎች አባቶች ጋር ወደ ካይሮ በመሔድም ግንቦት 18 ቀን 1921 ዓ.ም. መዓርገ ጵጵስናን ተቀበሉ።

አቡነ ሚካኤል ተብለው ወደ ሀገራቸው የተመለሱት ብፁዕነ ታቸው ከዓመት በኋላ «አባ ሚካኤል ጳጳስ ዘአዜበ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ዜና ማርቆስ» ተብለው በኢሲባቡርና በከፋ ጠቅላይ ግዛቶች ተሾሙ።

ዕድሜያቸውን በሙሉ በትምህርትና በትኅርምት ያሳለፉት ብፁዕነታቸው የዘወትር ዓላማቸው ምእመናንን ማስተማር ነበረና በተሰጣቸው ሀገረ ስብከት የሚገኙ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸውን በመንፈሳዊ ትምህርትና ምክር ያጠናክሩ፣ ተወዳጅ የነበረውንም ሐዋርያዊ ተልዕኮአቸውን ያፋጥኑ ጀመር። በዚህ ተግባራቸው እርሳ ቸውም እየተደበቱና እግዚአብሔርን እያመሰገኑ፣ ምእመናንም በብፁዕነታቸው ትምህርተ ወንጌል እየረኩ ቅድስት ቤተ ክርስቲያ ናቸውን እያወቁ ለሰባት ዓመታት ቆዩ።

ምንም እንኳን በቂ ናቸው ባይባልም ያሉት አራት አባቶች ኢትዮጵያን ተከፋፍለው ለረጅም ዘመናት በቋንቋው የሚናገር አባት አጥቶ የቆየውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከካህናቱና ሲቃውንቱ ጋር በመተባበር እውነተኛውን የወንጌል ትምህርት እያስ ተማሩ ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር በማስተዋወቅ ላይ ሳሉ በ1928 ዓ.ም. ግፈኛው የኢጣልያ ፋሽስት ጦር ኢትዮጵያን በግፍ ወረረ። ወረራ ውም ከሰሜኑና መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍል አልፎ ከእሳቸው ሀገረ ስብከት ደርሶ መንበረ ጵጵስናቸው የነበረበት የጎሬ ከተማ ኮሎኔል ማሊታ በተባለ የጦር አዛዥ በሚመራ የጦር ኃይል እጅ ወደቀ። በዚህ ጊዜ

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕነታቸው መንበረ ጵጵስናቸውን ለቀው ሰምቢ ወደ ተባለች የገጠር ቀበሌ በመሔድ በፍጹም አባትነት፣ ስሜትና ወኔ «ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን ብቻ እንጂ የሌላ አይደለችም» በማለት የሀገረ ስብከታቸው ሕዝብ ባሕር አቋርጦ ሊወረው በመጣው ጠላቱ ላይ እንዲነሣ መሰበክና መቀስቀስ ጀመሩ።

ብፁዕነታቸው ምንም እንኳን የመንፈስ ወንድማቸው የሆኑትን የብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቀዳማዊን አኩሪ ሰማዕትነት ሰምተው ቢደሰቱም፤ በአንጻሩ በጊዜው ከጠላት ጦር ጋር የተስማሙ አባቶች በፋሺስቱ ወራሪ ኃይል ተልከው ለምልጃ ስለመጡባቸው አዝነው ነበር ይባላል። አቶ ታደሰ ሜጫ የተባሉ አርበኛ «ጥቁር አንበሳ በምዕራብ ኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ ስለ ገነት ጦር ትምህርት ቤት ምሩቃንና «ጥቁር አንበሳ» ተብሉ ይታወቅ ስለነበረው ሠራዊት ተጋድሎ በጻፉት ታሪክ ውስጥ ብፁዕነታቸው በወቅቱ ስለነበራቸው ቆራጥ አቋም የሚከተለውን ምስክርነት ሰጥተውላቸዋል። «... ጎሬ በገባን ጊዜ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በከተማው እንደ ሚገኙ ሰማን። መልእክታችንን ለከቡር ራስ እምሩ አድርሰን ወደ ተሰጠን ሠፈር ከመመለሳችን በፊት የጥቁር አንበሳን ሰላምታ ይዘን ወደ ብፁዕነታቸው መኖሪያ ሔድን። እርሳቸውም ከተቀበሉንና ቃለ ቡራኬ ከሰጡን በኋላ ከዋነኞቹ መልእክተኞች ጋር ተነጋግረው የማበረታቻ ቃላቸውንም ወደ ጥቁር አንበሳ ጦር እንዲያደርሱላቸው አሳስበው በቡራኬ አሰናበቱን። እኛ ወደ ጥቁር አንበሳ ጦር እንድናደርስላቸው አሳስበው በቡራኬ አሰናበቱን። እኛ ወደ ጥቁር አንበሳ ጦር ከተመለስን በኋላ ራስ እምሩም ጎሬን ለቀው ወደ እኛ በመጡ ጊዜ ብፁዕነታቸው በዚያው ያሉትን ምእመናን ለነጣቂ ተኩላ ጥዬ አልሔድም በማለት መንፈሳዊ ተግባራቸውን በቆራጥነት ያከናውኑ ነበር።»

ስለ እኚሁ ታላቅ የሀገርና የቤተ ክርስቲያን አባት ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ የኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ጽኑ ወዳጅ የነበሩት ስዊድናዊ ኮሎኔል ካውንት ካርል ጉስታፍ በንሮዝን የሚከተለውን የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል። «ፎከር የምትባለውን አውሮፕላን እያበረርኩ በጎሬ አቅራቢያ አረፍኩ። በምዕራብ ኢትዮጵያ የነበሩትን ስደተኞች አግኝቼ በራስ እምሩ ይመራ ለነበረውም ጦር መገናኛ ከፈትኩ። ጎሬ እንዳረፍኩ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል አስጠሩኝ። 'በርግጥ አንተ ዘመዶችህን ከድተህ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማገልገል ወስነሃልን? ክርስቲያን ነኝ ብለሸኛል። ለዘመዶችህ ሳታዳላ ለዚች ለተጨነቀች ሀገር ከልብህ ለመሥራት መወሰንህን መስቀሌን በመምታት ማልልኝ' ሲሉኝ የሀገር ፍቅር እንዳቃጠላቸው ተሰማኝ። 'ጓደኞቼ በዕለት



ጥቅም እየተደለሉ ለጠላት ማደራቸውን ስሰማ በጣም አዘንኩ። ሌላው የልብ ጓደኛዬ አቡነ ጴጥሮስ ግን ለጠላት አልገዛም ብለው ለመሥዋዕትነት መቃረባቸውን ስለሰማ በጣም ደስ አለኝ። ይህ ነው መሐላን ማክበር። እኔም የምከተለው የጴጥሮስን ፈለግ ነው።' ብለው አጫወቱኝ። ቆራጥነታቸውን ሳደንቅ ፋሺስት ንጹሐንን ለምን እንደሚገድል በማሰብ በጣም ተገረምኩ። ምስቀላቸውን መትቼ ከጎሬ ተመለስኩ። ወደ ሎንዶን ከሔድኩ በኋላ ጳጳሱ ተገድለው ጎሬም በጠላት መያዟን ስሰማ በጣም አዘንኩ። አቡነ ሚካኤል ከማልዘንጋቸው ቆራጥ ኢትዮጵያውያን አንዱ ናቸው። በነጻነት ጉዳይ ኢትዮጵያውያን የተለየ አቋም አላቸው። ቋንቋ ፈጽሞ አያግዳቸውም። አይበግራቸውም።ሁሉም በሀገራቸው ጉዳይ ቀልድ እንደማያውቁ የጎሬው ጳጳስ የአቡነ ሚካኤል ጥንካሬ በሚገባ አስረድቶኛል። የጳጳሱ ድፍረትና የሀገር ፍቅር ምን ጊዜም አይረሳኝም።»

ይህ የብፁዕነታቸው ስብከት ለወራሪው ኃይል ትልቅ እሳት ሆነ። ይህንንም በተረዳ ነገር ያወቀው ፋሺስት ፈቃደኛ ከሆኑ ሕዝቡ «መንግሥቴ የጣልያኑ ፋሺስት መንግሥት ነው» ብሎ ይቀበል ዘንድ እንዲሰብኩ፤ ካልፈቀዱ ግን መሰበካቸውን እንዲያቆሙ ለሁለተኛ ጊዜ በደብዳቤ ጠየቃቸው። ሰውም ልኮ አስጠየቃቸው። ብፁዕነታቸው ግን በዓላማ መጽናትን ያውቁበታልና ከእውነተኛው የሀገር ፍቅር ዓላማቸው እንደ ማያፈገፍጉ፣ እስከ መጨረሻውም ደማቸውን አፍስሰው ለውድ ሀገራቸው ቤዛ ለመሆን የማይቀዘቅዝ ስሜት እንዳላቸው በሙሉ ልብ አረጋግጠው ላኩበት።

ይህንን የብፁዕ አቡነ ሚካኤልን ጽናት የተረዳው ፋሺስትም የብፁዕነታቸውን ዐቋም በማረጋገጥ ያሰበውን ለመተግበር በሌሎች ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ላይ እንደ ፈጸመው ሁሉ በእርሳቸውም ላይ የግድያ ርምጃ ለመፈጸም ወሰነ። ብፁዕነታቸውም ለጠላት በአንደበታቸው ባረጋገጡለት መሠረት በሀገረ ስብከታቸው ከአውራጃ ወደ ወረዳ እየተዘዋወሩ ሕዝቡ የተባበረ ክንዱን በጠላት ላይ እንዲያነሣ ከውግዘት ጋር መስበካቸውን ቀጠሉ። በስብከት ጉዞ ላይ እንዳሉ እዚያው ሰምቢ ቀበሌ አጠገብ ከሚገኝ ጫካ ውስጥ በጠላት ጦር ተከብበው በቆራጥነትና በአርበኝነት ሲዋጉ አንድ ሌሊት ካደሩ ሁለት አርበኞች ጋር ተማረኩ።

ከዚያም ከኮሎኔል ማልታ ፊት ቀርበው ሕዝብን ከማነሣሣት ሥራቸው ተቆጥበው የማረጋጋት ሥራ ለምን እንደማይሠሩ በሕዝብ ፊት ጠየቃቸው። ቆራጡ ብፁዕ አቡነ ሚካኤልም በጠላት እጅ መውደቃቸው ምንም ሳያስፈራቸው የፋሽስትን በኢትዮጵያ የበላይ ነት ወይም አስተዳዳሪነት መንበር መቀመጥ በፍጹም ዕውቅና የማይ ሰጡትና የማይቀበሉት መሆኑን፣ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን ብቻ

www.ethiopianorthodox.org

መሆንዋን፣ ይህንንም ሐቅ አሰመመሰከር፣ ሕዝቡንም ለትግል አለ ማስተባበር ፍጹም ኃጢአት መሆኑን በድፍረት ዘርዝረው አሰረዱ:: «እኔ የማምነው በአንድ እግዚአብሔር ነው:: የምቀበለውም የነጻነታችን ምልክት የሆነውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ብቻ ነው:: ኢጣሊያ የሚባል ገዥ አላውቅም:: ለፋሺስት ኢጣልያ የተገዛ እንደ አርዮስ የተረገመ ይሁን:: እንኳንስ ሕዝቡ ምድሪቱም እንዳትገዛላቸው እውግዜአለሁ::» በማለት በዚያ ለተሰበሰበው ሕዝብና ሠራዊት ውግዘታቸውን አሰሙ::

ይህንን ቆራጥነታቸውን ከእንደበታቸው የተረዳው ፋሺስትም በሰጡት ቁርጠኛ መልስ ተናዶ እርሳቸውንና አብረዋቸው የተያዙትን ቀኝ አዝማች ይነሡና ግራ አዝማች ተክለ ሃይማኖት ይባሉ የነበሩ አርበኞችን ለሰምንት ቀናት ያህል ሌሊት በውርጭ ቀን በፀሐይ ሲያሰቃያቸው ሰነበተ:: በመጨረሻም ኅዳር 21 ቀን 1929 ዓ.ም. ከተያዙት ሁለት አርበኞች ጋር በጥይት ተደብድበው እንዲሞቱ ፍርድ እሰተላለፈ:: ትእዛዙ ተግባራዊ ሲሆን ከጎሬ ቤተ ክርሰቲያን በታች እሮጌው ቄራ አጠገብ ጉድጓድ ተቆፈረ:: በጉድጓዱ ዳር አብረዋቸው በተያዙ ሁለት ሰመ ጥር አርበኞች /ቀኛዝማች ይነሱና ግራዝማች ተክለ ሃይማኖት/ መካከል ብፁዕነታቸው እንዲቆሙ ተደረገ::በዚሀን ጊዜ እቡነ ሚካኤል ሰጥቂት ደቂቃዎች ጸሎት እንዲያደርጉ ጠይቀው ተፈቀደላቸው:: ጸሎታቸውን አድርበው ቢያበቁ መሰቀላቸውን ግንባራቸው ላይ «ብል እንግዲህ የፈለከውን አድርግ» አሉ:: በዚህ ጊዜ የወታደሮቹ አዛዥ የተኩሰ ትእዛዝ ሰጠ:: ከእነ አቡነ ሚካኤል ፊት ለፊት በተርታ ተሰልፈው በመንፈሳዊው አባትና በአርበኞቹ ላይ ጠብ መንጃቸውን ያነጣጠሩት የጠላት ወታደሮች አንድ ላይ በአሩምታ ተኮቡ:: ብፁዕነታቸውና ሁለቱ አርበኞች በተተኮሱባቸው ጥይቶች ተመትተው ወደቁ:: በዚህ ዓይነት ብፁዕነታቸው ኅዳር 24 ቀን 1929 ዓ.ም. በሰማዕትነት ዐረፉ:: አቶ ወልደ አብ የተባሉ ሀገር ወዳድ የአካባቢው ነዋሪ ሰው የብፁዕነ ታቸውን አሰከሬን ምንም እንኳን ከወደቀበት ጉድጓድ አንሰተው ወደ ቤተ ክርሰቲያን ወሰደው መቅበር ባይችሉም እዚያው በወደቀበት ጉድጓድ በሌሊይ ሔደው በአግባቡ እንደ ቀበሯቸው ይነገራል::

ከዚህ በኋላ የአካባቢው የጠላት ጦር ዋና አዛዥ የነበረው ኮሎኔል ማልታ በጎሬ ከተማና በአካባቢው በሚገኙት አብያተ ክርሰቲያናት የሚያገለግሉትን ካሀናት በሙሉ ሰብስቦ ገለፃ አደረገላቸው:: «አቡነ ሚካኤል የተገደሉት ለኃያሉ የኢጣሊያ መንግሥት አልገዛም በማሰታቸው ነው:: ሕዝቡም እንዳይገዛ በማውገዝ በእንቢተኛነታቸው ጸንተው በፈጸሙት የአመጽ ሥራ ነው::» አለና ስለዚህ «አቡኑ መገደላቸው ተገቢ ነው? ወይስ ተገቢ አይደለም?» ቢል ካሀናቱ በአፋጣኝ አሰተያየታቸውን እንዲበጡ



በማዘዝ አፈጠጠባቸው:: ካሀናቱም ለዚህ አስቸጋሪ ጥያቄ ወዲያውኑ መልሰ ሰመሰጠት ተቸገሩ:: ይሀም የሆነበት ምክንያት «እቡኑ መገደላቸው ተገቢ አይደለም» ካሉ እነርቡም የሚጠብቃቸው ዕድል ሞት ነው:: «የአቡኑ መገደል ተገቢ ነው» እንዳይሉ ደግሞ ለአገርና ለነጻነት መቆርቆርና መታገል ወንጀል አለመሆኑን እንደውም የተቀደሰ ተግባር እንደሆነ ያውቃሉና:: ካሀናቱ በቀረበላቸው ጥያቄ ላይ ተወያዩ:: ከመካከላቸውም አነጋገር ይችላሉ ብሰው የሚያም ኑባቸውን አለቃ ቢረሳው የተባሉትን አባት መርጠው እንዲመልሱ አደረጉ:: አለቃ ቢረሳውም ለኮሎኔል ማልታ «እናንተም ደግ ገደላችሁ፤ እርሳቸውም ደግ ሞቱ» በማለት መልሰ ሰጡ:: የአሰቃ ቢረሳውን መልስ ምስጢር ያልተረዳው ጣሊያናዊው ኮሎኔል የወሰደውን እርምጃ የደገፉለት መሰሎት በመደሰት «አለቃ ቢረሳውን አቡን አድርጌ ሾሜዋለሁ» ብሎ የሟቹን ጳጳስ መሰቀልና መቋሚያ በሽልማት እንዲሰጣቸው አዘዘ::

ጠላት ከሀገር ከወጣ በኋላ በ1935 ዓ.ም የብፁዕነታቸው ሀጽም ከነበረበት አልባሌ ሥፍራ ተለቅሞ በክብር በሳጥን ከተደረገ በኋላ በጎሬ ደብረ ገነት ቅድሰት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀምጧል::

ሀገሪቷ ነፃነቷ ተመልሶ ንጉሡ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ በ1934 ዓ.ም መታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ በሰማዕትነት ባለፉበት ጎሬ ከተማ አንድ ት/ቤት እንዲቆም አደረጉላቸው:: በዘመነ ደርግም ብፁዕ ወቅዱሰ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በጎሬ ከተማ መታሰቢያ የሚሆን ሐውልት ሊያቆሙላቸው ቀን ቆርጠው፣ ዜና ሕይወታቸውን ለማዘከር ጽሑፎች ተዘጋጅተው፤ እንደ ነገ ሊሔዱ እንደ ዛሬ ማታ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ከደርግ ጽ/ቤት ተደውሎ እንዳይሔዱ ተብለው ሐሳባቸውን ተግባራዊ ሳያደርጉ ቀርተዋል ይባላል:: የብፁዕ አቡነ ሚካኤል ረድኤት አይለየን:: አሜን::

www.ethiopianorthodox.org

## 3.4. ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ቀዳማይ

## «ጳጳስ ዘሰሜን ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ሳሙኤል»

## /1871 - 1947 ዓ.ም/





ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ከአባታቸው ከመሪ ጌታ ክንፉና ከእናታቸው ከወ/ሮ ፈረደ እሸቴ በ1871 ዓ.ም. በወሎ ሀገረ ስብከት ዋግ አውራጃ ተወለዱ። ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስም እዚያው ከቤተሰቦቻቸው ሳይርቁ ዞብል ሠፈረ ማርያም ከተባለው ቦታ ከነበሩት አለቃ ተድላ ዘንድ ከፊደል ጀምረው ንባብና ዳዊት ተማሩ። የጀመሩትን ትምህርት በመቀጠልም ጾዋትወ ዜማ፣ ቅኔ፣ ውዳሴና ቅዳሴ ማርያም እንዲሁም የፍትሐ ነገሥትንና የዳዊትን ትርጓሜ ተማሩ። በዚሁ ጊዜ ቁም ጽሕፈትንም በሚገባ ተማሩ።

ከዚህ በኋላ ራሳቸውን ለመንግሥተ ሰማያት ጃንደረባ በማድረግ ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ አባ ኢየሱስ ሞዓ ገዳም በመግባት መጽሐፈ መነኮሳትን ካጠኑ በኋላ ወደ ዝመዶ ማርያም ገዳም በመሔድ ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጸሙ። ከዚያም ዕውቀታቸውን ለማበልፈፋት ወደ ቦሩ ሜዳ ሔደው አለቃ መርሻ ከተባሉ የዜማ ሊቅ ድጓን ተምረው አስመሰከሩ። መሪ ጌታ ላቀው ወደ ተባሉ መምህርም በመጠጋት የቅኔ ትምህርታቸውን አጠናከሩ።

ከዚህ በኋላ ወደ ወልዲያ በመሔድ ለአምስት ዓመታት ያህል ዜማ ሲያስተምሩ ቆዩ። ነገር ግን የብፁዕነታቸውን ትምህርትና ግብረ ገብነት በአንክሮ ሲከታተሉ የነበሩ አለቃ ተድላ የተባሉ አባት እርሳቸውም እንደ ሌሎቹ ወደ አራት ዓይናው ሊቅ መ/ር አካለ ወልድ ዘንድ በመሔድ ዕውቀታቸውን እንዲያደላድሉ መከሯቸው። ብፁዕነታቸውም የአለቃ ተድላን ምክር በፍጹም እሺታ ተቀብለው ወደ መምህር አካለ ወልድ ወረዱ። በዚያም የብሉያትንና የሐዲሳትን፣ የሊቃውንትንና የመጽሐፈ መነኮሳትን ትርጓሜ አጠናቀው ተማሩ። በነበራቸውም የተደነቀ የቁም ጽሕፈት ሞያ ሃይማኖተ አበውን፣ መጽሐፈ ኢሳይያስን፣ እረኃዊ መንፈሳዊን፣ ፊልክስዩስን፣ ማር ይስሐቅን ንባቡን ከነትርጓሜው በግእዝ ቋንቋ በእጃቸው ጻፉ።

ከመምህር አካለ ወልድ ዘንድ ለመጻሕፍት ትርጓሜ መምህርነት የሚያበቃ የምስክር ወረቀት ከያዙ በኋላ ወደ ላስታ በመሔድ እያስተማሩ የነአኩቶ ለአብንና የገነተ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ማስተዳደር ጀመሩ። በዚያ ቆይታቸው በርከት ያሉ ሊቃውንትን አስተምረው ለሴተ ክርስቲያን አበርክተዋል። ከዚያም በ1911 ዓ.ም ወደ ሸዋ መጥተው ደብረ ሊባኖስ አጠገብ ያለውን የጫጋል መድኃኔ ዓለምን ገዳምና ገነተ ኢየሱስን አቅንተዋል።

ብፁዕነታቸው በዚህ ላይ እንዳሉ የስገሌ ጦርነት ተደረገ። ጦርነቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ብፁዕነታቸው በንግሥተ ንገሥታት ዘውዲቱ ጥሪ ወደ አዲስ አበባ መጡ። ከዚያም በአንኮበር ቅዱስ ሚካኤል ደብር በአስተዳዳሪነት ተሹመው ለጥቂት ዓመታት

www.ethiopianorthodox.org

# 3.4. ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ቀዳማይ

## «ጳጳስ ዘሰሜን ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ሳሙኤል»

/1871 - 1947 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

አገለገሉ። በኋላም ወደ አዲስ አበባ በመመለስ በግቢ ገብርኤል ገዳም ተሹመው እያገለገሉ በሚገባ አጠንክረው የተማሩትን መዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ 1ኛ. የሃይማኖት፣ 2ኛ. የተስፋ፣ 3ኛ. የትምህርት፣ 4ኛ. የምስጋና፣ 5ኛ. የደስታ፣ 6ኛ. የልመና፣ 7ኛ. የታሪክ ፤ በማለት በሰባት በመክፈል ለተጠቃሚ በሚመች መልኩ በብራና ላይ በቁም ጽሕፈት ጽፈው በገዳሙ እንዲቀመጥ አድርገዋል።

በ1921 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዕውቀት መንፈሳዊ ወልዳ ተክባክባ ካሳደገቻቸው ሊቃውንት ልጆቿ ለጵጵስና መዓርግ ከመረጠቻቸው መካከል ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ አንዱ ሆኑ።

ብፁዕነታቸው በካይሮ መንበረ ማርቆስ ቤተ ክርስተያን የጵጵስናን መዓርግ አግኝተው ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ «ጳጳስ ዘሰሜን ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ሳሙኤል» ተብለው በትግራይ ሀገረ ስብከት ተሾሙ። ብፁዕነታቸው ወደ ትግራይ ከሔዱ በኋላ የተቀበሉትን የሐዋርያነት ተግባር በማስፋፋት ያላመኑትን ሰብከው ወደ አሚነ ሥላሴ ማምጣትና ያመኑትንም ማጠናከር ጀመሩ።

ብፁዕነታቸው የተሰጣቸውን ሐላፊነት ካህናትን በማስተባበር በብቃት እየተወጡ ሳለ በ1928 ዓ.ም. ፋሺስት ኢጣልያ ሀገራችንን ለመውረር መጣ። በዚህ ጊዜ ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ዓድዋ ዓዲ አቡን ነበሩ። በወቅቱ የአካባቢው ልዑል የነበሩት ራስ ሥዩም የኢጣልያ ፋሽስት መረብን ሳይሻገር ዳዕር ተኸሊ ከተሰለፉት አሽከሮቼ ጋር ሆኜ ደሜን አፈሳለሁ ብለው ተነሡ። ይህንንም በአካባቢያቸው የነበሩት ብፁዕነታቸው ሰሙ። እንደ ሰሙም አርቆ አስተዋይ ናቸውና በፍጥነት ወደ ልዑል ራስ ሥዩም ገሥግሰው በመሔድ እንዳሉት ወደ ጦር ግንባር እንዳይሔዱ፤ ሔደው ቢሞቱ ግን ጉዳት እንጂ ጥቅም እንደ ሌለው በአጽንዖት መከሯቸው።

ራስ ሥዩምም ወደ ዚያው ሳይሔዱ አሽከሮቻቸው ዳዕሮ ተኸሊ በተባለ ቦታ ላይ የተሰለፈውን ጦር ድል አድርገው እንደ አባረሩት ተሰማ። በዚህ ጊዜ ራስ ሥዩም ጠላት ኃይሉን አጠናክሮ እንደሚመለስ ስለ ገመቱ ሌላ ኃይል ጨማምረው ወደ ተንቤን ተዛወሩ። ብፁዕ አቡነ ይስሐቅም አብረው ሄዱ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ራስ ሥዩም በተለያዩ ዐውደ ግንባሮች ከጣሊያን ፋሺስት ጦር ጋር ተፋልመዋል። ብፁዕነታቸውም እስከ ግንባር ድረስ ከልዑሉና ከሠራዊታቸው ጋር በመገኘት የማጽናኛ ቃል ይሰጡ ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን ምሽት ልዑል ራስ ሥዩም ከሠራዊቶቻቸው ጋር ያገኙትን ድል በማስመልከት ድግስ አድርገው እየተደሰቱ ሳለ ጠላት ኃይሉን አስተባብሮ እየመጣ እንደ ሆነ ሰሙ።



ከደረሰው መረጃ እንጻር የጠላት ጦር ጠንከር ያለ ስለ ነበር ይህንኑ ለሠራዊታቸው ገልጠው ዝግጅት እንዲያደርጉ አሳሰቡ። ሠራዊቱም ማሳሰቢያውን ተቀብሎ ከአሁን አሁን ጠላት ደርሶ ጥቃት ይከፍታል በማለት በፍጥነት መዘጋጀት ጀመረ። ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ በሠራዊቱ መካከል ቆመው እንድ ጊዜ ሠራዊቱ እንዲረጋጋ ካደረጉ በኋላ የሚከተለውን ንግግር አደረጉ፡-

*«ልጆቼ ሆይ አድምጡኝ። ዝም በሉ። ነገር ግን ዝም እንድትሉ የምመክራችሁ የጀግንነታችሁን ወኔ ለማብረድና ለማቀዝቀዝ አይደለም። ከዚህ ቀደም በፈጸ ማችሁት ተጋድሎ ያስገኛችሁት ድል አድራጊነት ከፎከ ራችሁለት በላይ ልዩና የሚገመት በመሆኑ ወደ ፊትም የምታጉድሉት ነገር ስለ ማይኖር ለአገራችሁ ታማኞች ናችሁ፤ አሁን ወደ ጠላት ግንባር የመሔጃችን ጊዜ ስለ ደረሰ እኔም አንድ መሣሪያ አለኝና ያንን ሳስታጥቃችሁ እፈልጋለሁ። መሣሪያ ያልኳችሁም አሁን የምናገረው ቃል ነው።*

*እነሆ ይህች የምትመጣው ሌሊት የጸሎተ ሐሙስን ሌሊት ትመስላለች። ይኸውም የመከራ ሌሊት በመሆኑ ነው። ወርቅ በእሳት ተፈትኖ ጥራቱን እንደ ሚያሳይ እናንተም የዚህችን ሌሊት ፈተና ወጥታችሁ ሃይማኖታችሁንና የሀገር ፍቅራችሁን ሊታስመሰክሩ የተጠየቃችሁባት የጌታችሁንም እምነት አጉልታችሁ የምታሳዩበት በመሆኗ ነው። ይህች ሌሊት ይሁዳ ጌታውንና ፈጣሪውን አሳልፎ የሰጠባት ሌሊት ናት። ይህች ሌሊት ግን እናንተ ስለ ጌታችሁ ራሳችሁን አሳልፋችሁ ለሞት ለመስጠት የተዘጋጃችሁባት ናት። ያቺ ሌሊት ሐዋርያት ጌታቸውን ጥለው የሸሹባት ናት። ይህች ሌሊት ግን ይህ እንዳይደረግ ቃል የገባችሁባት ናት። መጥፎ ለድል እንዳይገጥማችሁ እግዚአብሔር ይርዳችሁ። ሃይማኖታች ሁና አንድነታችሁ የጸና ይሁን።»*

ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ይህንን ከተናገሩ በኋላ ከሠራዊቱ ጋር አብረው ወደ ጦር ግንባር ዘመቱ። በሀገር ፍቅር ስሜት የነደደው፣ በብፁዕነታቸው ምክርና ቡራኬ የተነሣሣው የልዑል ራስ ሥዩም ሠራዊት ጠላትን ድል አድርጎ ወደ መጣበት መለሰው። ነገር ግን አንድ በደስታው ላይ ጥላ ያጠላ ጉዳይ ተፈጠረ። ብፁዕ አቡነ ይስ ሐቅ በጠላት ተማረኩ።

ጣልያን ፋሺስት ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ

www.ethiopianorthodox.org

ምእመኑንና ሠራዊቱን በማትጋት እሾህ ሆነውበት የነበሩትን ብፁዕ አቡነ ይስሐቅን እንደ ያዘ ለግዞት ወደ ናኩራ ወሰዳቸው:: ከናኩራም ወደ ሮማ ናፖሊ ከተማ ወሰዳቸው::

በዚያው ለሁለት ዓመታት በግዞት ከቆዩ በኋላ በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው በተሾሙት ኢትዮጵያዊው ብፁዕ አቡነ አብርሃም አማላጅነት ወደ አገራቸው ወደ ኢትዮጵያ ተመል ሰው አዲስ አበባ ከተማ ከብፁዕነታቸው ጋር ተቀምጠው ማገ ልገል ጀመሩ::

አቡነ አብርሃም ካረፉ በኋላም ዕጨጌ ተብለው የደብረ ሊባኖስን ገዳም እንዲያስተዳድሩ ተደርገው ለአንድ ዓመት እንዳገለ ገሉ ወራሪው የፋሺስት ጦር ድል ተመትቶ የሀገሪቱ ነጻነት ተመለሰ::

በዚህ ጊዜ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በኢጣልያ ፋሺስት አስገዳጅነት የተሾሙትን ጳጳሳት እንዳይሠሩ አውግዞ ቀድሞ ከእስክ ንድርያ የተሾሙት ጳጳሳት እንዲሠሩ ፈቅዳ ስለ ነበር ከቀድሞዎቹ ጳጳሳት አቡነ ይስሐቅ ስለ ተገኙ የጵጵስናውን ሥራ እርሳቸው እንዲሠሩ ተደረገ:: በመሆኑም ከ1937 ዓ.ም ጀምሮ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ እስከ ተሾሙበት 1941 ዓ.ም ድረስ መኖሪያቸው አዲስ አበባ ሆኖ በጎንደር፣ በጎጃም፣ በትግራይ፣ በኢሉባቦር እየተ ዘዋወሩ የሐዋርያነት ተግባራቸውን አከናወኑ::

ከዚያም በ1941 ዓ.ም ወደ ወሎ ሀገረ ስብከት ተዛውረው በሊቀ ጳጳስነት አገልግለዋል:: በመጨረሻም ወደ ጥንት ሀገረ ስብከ ታቸው ወደ ትግራይ ተመልሰው ዓድዋ አዲ አቡን ተቀመጡ:: በዚ ያም የተለያዩ መንፈሳውያት ተግባራትን ሲያከናውኑ ከቆዩ በኋላ ባደረባቸው ድንገተኛ ሕመም ምክንያት አሥመራ ሐኪም ቤት ሲታከሙ ቆይተው በ1947 ዓ.ም ነሐሴ 4 ቀን በተወለዱ በ78 ዓመ ታቸው ዐረፉ:: የቀብራቸው ሥነ ሥርዓትም በርእሰ አድባራት ወገዳማት አክሱም ጽዮን ማርያም ተፈጸመ::

በሥርዓተ ቀብራቸው ከተገኙት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ የነበሩት አለቃ ልሣነ ወርቅ ወ/ዳዊት በወቅቱ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ት/ቤቶች ጠቅላይ ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ የሚከተለውን መወድስ ሰጥተው ነበር::

ደቂቀ ስቆቃው ኀሥም ለዘተሠወረ፡ በሐቅለ ሞተ ዓቤል
ይስሐቅ ለእመ ይትረከብ ዳኅናነ
ለረኪበ ድኁን አብርሃም እንዘ የሐሥሥ ተሰፋሁ
እምኀበ አልቦ እስመ ተረክበ፡ በግዕ ዐዳ ለይስሐቅ ቤዛሁ፡



ባሕቱ ዘይተግሁ
ለኃሚሥቱ ረከቡ፣ ውስተ ቤተ አብርሃም ምሥዋሪሁ::
የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን:: አሜን::

www.ethiopianorthodox.org

# 3.5. ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ቀዳማይ

## «ጳጳስ ዘደቡብ ኢትዮጵያ ወዕጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት»

## /1868 - 1925 ዓ.ም/





ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ በቀድሞው የቤጌምድር ጠቅላይ ግዛት ደራ አቡነ ሐራ በሚባለው ቦታ ሚያዝያ 19 ቀን 1868 ዓ.ም ተወለዱ:: በወላጆቻቸው ቤት በክብካቤ አድገው ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በአጥቢያቸው የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ተማሩ:: ከዚያም በ1880 ዓ.ም ወደ ጎጃም ተሻግረው በወቅቱ የጎጃም ጳጳስ ከነበሩት ከግብፃዊው አቡነ ሉቃስ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ::

ከዚህ በኋላ ወደ ትውልድ ሀገራቸው ተመልሰው በጥምቀት ክአብራክ መንፈስ ቅዱስ ክማኅፀነ ዮርዳኖስ ሲወለዱ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተብለው የተሠየሙበትን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በዲቁና እያገለገሉ ለዓመታት ቆዩ:: ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በመጀመሪያ ወደ ሬማ መድኃኔ ዓለም ገዳም፣ ቀጥሎም ወደ አቡ ሥላሴ ገዳም በመሔድ ትምህርታቸውን እየተማሩና ሥርዓተ ገዳም እያጠኑ ረዘም ላሉ ዓመታት ቆዩ::

ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ በሕይወት ዘመናቸው ሳይፈጽሙት በሞት እንዳይጠሩ ወደ እግዚአብሔር ዘንድ አብዝተው የሚጸልዩበት አንድ ሕልምና ፍላጎት ነበራቸው:: ይኸውም በሕፃንነታቸው ፈደለ ሐዋርያ ሲያነቡ ጀምሮ ስሟን እየጠሩ ቅድስትነቷን በአእምሮአቸው ሲሥሏት የኖሯትን ኢየሩሳሌምን መጎብኘት፣ ቅዱሳት መካናቷንም መሳለም ነበር:: ብፁዕነታቸው በተለይ ዕድሜያቸው እየጨመረ ሲሔድ ቅድስት ሀገርን የመጎብኘት ፍላጎታቸው እየጨመረ በመምጣቱ በ1900 ዓ.ም ወደ ደብረ ታቦር ሔደው ራስ ጉግሳ ወሌንና ወ/ሮ ዘውዲቱ ምኒልክን ደጅ መጥናትን ቀጠሉ::

በዚህ ዓይነት ከራስ ጉግሣና ወ/ሮ ዘውዲቱ ጋር የተዋወቁት ብፁዕነታቸው መልካም መልስ በማግኘታቸው ከእነሱ ጋር ለወራት ያህል ቆዩ:: መቼ ጸሎቴ ተበምቶ ወደ ኢየሩሳሌም እሸኝ ይሆን እያሉ በመጣባበቅ ላይ ሳሉ ዓፄ ምኒልክ መታመማቸው ተሰማ:: በዚህም የተነሣ ልጃቸው ወ/ሮ ዘውዲቱ አባታቸውን ለማስታመም ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ ኢየሩሳሌም ስደዱኝ እያሉ ደጅ ሲጠኑ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስም ተከትለው መጡ:: በዚህም ንጉሡ ዓፄ ምኒልክን በጸሎታቸው የታወቁ አባቶች ጸሎት እያደረጉ ጠበል እንዲያጠምቋቸው በተደረገ ጊዜ ብፁዕነታቸው አንዱ በመሆን ሲያጠምቁ ቆዩ:: ይሁን እንጂ ንጉሡ በዚህ ዓለም ይኖሩበት ዘንድ የተሰጣቸው ዘመን ዐልቆ ኖሮ ዐረፉ:: የንጉሡን ሞት ተከትሎም ልጅ ኢያሱ መንበሩን ለመያዝ ሲሉ የዓፄ ምኒልክ ልጅ ዘውዲቱ ቤተ መንግሥቱን ለቀው እንዲወጡ አዘዙ:: ዘውዲቱም በታዘዙት መሠረት ግቢውን ለቀው ፋሊ ወደ ተባለ ቦታ ወረዱ:: በዚህ ጊዜ

www.ethiopianorthodox.org

# 3.5. ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ቀዳማይ

## «ጳጳስ ዘደቡብ ኢትዮጵያ ወዕጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት»

/1868 - 1925 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

ያኔ መምህር ተድላ ይባሉ የነበሩት ብፁዕነታቸውም አብረዋቸው ወረዱ።

ይሁን እንጂ በ1909 ዓ.ም ልጅ ኢያሱ የማዘዝ ሥልጣናቸውን ተነጥቀው ወ/ሮ ዘውዲቱ ንግሥተ ንግሥታት ተብለው ተሾሙ። በዚህ ጊዜ በንግሥቷ የስደት ዘመን ሁሉ አብረው የተቸገሩት ብፁዕነታቸው እንደ ውለታ ተቆጥሮላቸው የአቡነ ሐራንና የወለተ ጴጥሮስን ገዳማት መምህርነት ተሾሙ። በዚህ ሹመታቸው ለአንድ ዓመት ያህል ካገለገሉ በኋላ ታኅሣሥ 27 ቀን 1910 ዓ.ም መልአከ ገነት ተብለው የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ።

ከንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ ቀረብ ብለው የተሾሙበትን ደብር ለአራት ዓመታት ያህል በብቃት ካስተዳደሩ በኋላ በውስጣቸው ይዘውት የነበረውን የዘመናት ሕልም እውን የሚያደርጉበት ቀን ደረሰ። በ1914 ዓ.ም ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው ቅዱሳት መካናትን ተሳለሙ። በዚያውም ወደ ግብፅ ወርደው በዚያ ያሉ ገዳማትን ጎብኝተው ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ።

ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ከኢየሩሳሌምና ግብፅ ከተመለሱ በኋላም በዚያው በቀድሞው የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪነታቸው ሊያገለግሉ ቆዩ። በኋላም ኅዳር 17 ቀን 1917 ዓ.ም ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተብለው የታላቁ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ዕጨጌ ሆነው ተሾሙ። በዕጨጌነታቸውም ሰፊ አገልግሎትን ሲያበረክቱ ቆይተዋል። ካበረከቷቸው ዐበይት አገልግሎቶች ውስጥ ዕጨጌ ከሆኑ ከአንድ ዓመት በኋላ መስከረም 8 ቀን 1918 ዓ.ም መንፈሳዊ ጉባኤን አቋቁመው የቤተ ክርስቲያን የወደ ፊት ጉዞ ቀና እንዲሆን የጣሉት መሠረት ተጠቃሽ ነው።

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከ1600 ዓመታት በኋላ በ1921 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ተመርጠው ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙ በተፈቀደ ጊዜ ብፁዕነታቸው ከአምስቱ አንዱ ሆነው ተመረጡ። ይሁን እንጂ በ1921 ዓ.ም ተመራጮቹ አባቶች ወደ ግብፅ ሔደው መዓርጉን በተቀበሉ ጊዜ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ባጋጠማቸው ሕመም የተነሣ አብረው ሊሔዱና ለሹመቱ ሊደርሱ አልቻሉም ነበር። አንዳንድ አባቶች እንደሚሉት ግን ብፁዕነታቸው ወደ ግብፅ ያልወረዱት ሹመቱን ስላልፈለጉት ነበር።

ይሁን እንጂ አባቶች ወደ ግብፅ ሔደው መዓርጉን ባገኙ በዓመቱ የወቅቱ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ በራስ ተፈሪ ግብዣ ለጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ መጡ። በዚህም ጊዜ የቤተ መንግሥቱም ሆኑ የቤተ ክህነቱ



ባለሥልጣናት ከዓመት በፊት ከሌሎች አባቶች ጋር ወደ ካይሮ ተጉዘው ሥልጣኑን ለመቀበል ባይችሉም ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሹመቱ ስለ ሚገባቸው ፓትርያርኩ ወደ ኢትዮጵያ እንደ መጡ ሾመዋቸው ቢሔዱ የሚል የይሁንታ ሐሳብ አቀረቡ። ሐሳቡ ተቀባይነት አግኝቶም ጥር 20 ቀን 1922 ዓ.ም በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት በአታ ለማርያም ገዳም «አባ ሳዊሮስ ጳጳስ ዘደቡብ ኢትዮጵያ ወዕጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ» ተብለው ተሾሙ። /የሹመታቸውን ደብዳቤ በአባሪ አንድ ይመለከቷል/።

ብፁዕነታቸው ምንም እንኳን በደቡቡ የሀገራችን ክፍል ቢሾሙም መቀመጫቸው አዲስ አበባና ደብረ ሊባኖስ ነበር። ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ ብፁዕነታቸውን ያቀርቧቸው ስለ ነበር የረጅም ጊዜ ሕልማቸው የነበረውን የባዓታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያንን ሕንፃ ግንባታና በአገልጋይ ካህናት መጠናከር አደራውንና ሐላፊነቱን የሰጧቸው ለብፁዕነታቸው ነበር ይባላል። በተለይ ለቤተ ክርስቲያኗ የሚሆኑ አገልጋይ ካህናትን፣ በየዕውቀት መስኩ የሚያስተምሩ ሊቃውንትን የመምረጡን ተግባር ሙሉ በሙሉ ለብፁዕነታቸው ሰጥተዋቸው ነበር። ይሁን እንጂ የንግሥተ ንግሥታቷ ሐሳብና ፍላጎት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ የሆነው በኋላ በቦታው በተሾሙ አባቶች ነው።

ቤተ ክርስቲያንን ለረጅም ዓመታት በማገልገል የቆዩት ብፁዕነታቸው ሹመቱን ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ቢያገኙም ብዙም ሳይቆዩ ከጎንደር ጀምሮ አስከትለዋቸው ለወግ ለመዓርግ ያበቋቸው ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ዐረፉ። በዚህ የተነሣ አሳቸውም እንደ ሌሎች የንግሥቷ ቀራቢ አባቶች ከቤተ መንግሥቱ ያገኙት የነበረው ክብካቤ ተቋረጠ። በዚህ ሁሉ የተነሣ ብፁዕነታቸው ሁሉንም ትተው ባልቻ አባ ነፍሶ በሰጧቸው ቦታ ላይ /ራሳቸው ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ ናቸው የሰጧቸው የሚሉም አሉ/ የማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያንን አሠርተው በዚያው ግቢ መኖሪያቸውን አደረጉ። የቤተ ክርስቲያኗን ስም ማኅደረ ስብሐት ብለው የሠየሟት እሳቸው እንደ ሆኑ ይነገራል። ይሁን እንጂ ብዙም ሳይቆዩ ባደረባቸው የአንድ ወር ተኩል ሕመም ጳጉሜን 2 ቀን 1925 ዓ.ም ከዚህ ሥጋዊ ዓለም በሞት ተለዩ። ሥርዓተ ቀብራቸውም ባሠሯት የልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን መቅደስ ውስጥ ተፈጸመ። ብፁዕነታቸው በየዓመቱ ጳጉሜን 2 ቀን በማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ይዘከራሉ። ብፁዕነታቸው በቤተ ክርስቲያንዋም ዘወትር ሲዘከሩ ይኖሩ ዘንድም የቤተ ክርስቲያንዋ ሰንበት ት/ቤት «ተክለ ሳዊሮስ» ተብሎ ይጠራል። የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን። አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

# 3.6. ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ቀዳማይ ሊቀ ጳጳስ

## /1875 - 1948 ዓ.ም/





ሐዲስ ተክሌ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት እነዋሪ በመባል በሚታወቀው ቦታ መጋቢት 12 ቀን 1875 ዓ.ም ተወለዱ:: ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስም በወላጆቻቸው አማካይነት በየተራ ወደ አዲስ ዓለም ደብረ ጽዮንና ደብረ ሊባኖስ ገዳማት ተወስደው የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን በሚገባ ተማሩ::

ትምህርታቸውን በመቀጠልም ለሁለተኛ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርት ወደ ጎንደር ተሻግረው በቤተ ልሔም ቁም ዜማን፣ በጎንደር ከተማ ደግሞ አቋቋምን በሚገባ ተማሩ:: ለሦስተኛ ደረጃ ትምህርትም ከጎንደር ወደ ጎጃም በመመለስ ዋድላ ላይ ቅኔን ከነአገባቡ በመማር በመምህርነት ተመረቁ:: ቀጥሎም ከጎጃም ወደ ጎንደር በመመለስ ከታወቁት ሊቅ ከመምህር ተክለ ማርያም ትርጓሜ ሐዲሳትን ከአለቃ ዘዮሐንስም ፍትሐ ነገሥትን ተማሩ:: የሐዲሳቱንም ትርጓሜ በሚገባ አሔዱ:: የትርጓሜውን ትምህርት በመቀጠልም ወደ ደብረ ታቦር በመሔድ በዘርፉ ከታወቁት ሊቅ ከአለቃ ተስፋ ዘንድ የሃይማኖተ አበውን ትርጓሜ በሚገባ አጠኑ::

ከትርጓሜው ትምህርት ሐዲሱን በሚገባ አስፋፍተው በመምህርነት በመመረቃቸው ሐዲስ ተክሌ የሚል ስያሜ የተሰጣቸው ብፁዕነታቸው በትምህርት በኖሩበት በዚያው በጎንደር የሐዲሳትንና የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ጀመር:: በማስተማር አገልግሎት ላይ እንዳሉም ወደ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም በመሔድ ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጸሙ::

እንደ አባቶቻቸው ሕይወታቸውን በተባሕትዎ ሊኖሩ ቃልኪዳን ፈጽመው፣ ጉባኤያቸውን ከዕለት ወደ ዕለት እያስፋ የተቀመጡት ሐዲስ ተክሌ ባሳሰቡትና ባልጠበቁት ሁናቴ በጎንደር ከተማ በምትገኘው የልደታ ደብር በአስተዳዳሪነት ተሾሙ:: ሹመቱን በአኩቴት ተቀብለው አጋጣሚው በፈጠረላቸው መልካም ሁናቴ በመጠቀም ደብሩን ከማስተዳደር ጋር ጉባኤያቸውን አስፋፍተው ማገልገል ጀመሩ::

ይሁን እንጂ በተሾሙባት ደብር ጥቂት እንዲቆዩ በራስ ጉግሣ አማካይነት ወደ ደብረ ታቦር ተዛውረው በቂ የወር ደሞዝ ተመድበላቸው ሐዲሳትን፣ ፍትሐ ነገሥትንና ቅኔን እንዲያስተምሩ ተደረጉ:: ብፁዕነታቸው ጉባኤያቸውን አስፋፍተው ለራስ ጉግሣም በመንፈሳዊውም ሆነ በአስተዳደራዊው ተግባር ረገድ በምክር ሊያገለግሉ ከቆዩ በኋላ በ1918 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ከግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ ዘንድ የቅስናና የቁምስና መዓርግ ተቀበሉ:: በዚያውም ፈቃድ ጠይቀው ወደ ቅድስት ሀገር

www.ethiopianorthodox.org

ኢየሩሳሌም በመሔድ በዚያ ያሉ ቅዱሳት መካናትን ተሳልመው ተመለሱ::

ከኢየሩሳሌም ከተመለሱም በኋላ በዚሁ በአዲስ አበባ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር ተቀምጠው ለጥቂት ጊዜያት ከአስተማሩ በኋላ በአንኮበር ቅዱስ ሚካኤል ደብር በመምህርነት ተሹመው ያስተምሩ ጀመር:: በሁለተኛውም ዓመት ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው «መልአከ ብርሃን» ተብለው በአዲስ አበባ መካነ ሥላሴ ደብር ተሾሙ::

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በቦታው በአስተዳዳሪነት ለሦስት ዓመታት ካገለገሉ በኋላ የትምህርትን መንገድ አንድ ብለው በጀመሩባት አዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ማርያም «ንቡረ ዕድ ተክለ ሃይማኖት» ተብለው ተሾሙ:: ወደዚያ ከሔዱ በኋላም ከማኅበረ ካህናቱ ጋር በመስማማት አገልግሎታቸውን በስፋት ቀጠሉ:: ካከናወኗቸው ተግባራት መካከል በአክሱም ሥነ ሥርዓትና ክብር በዳግማዊ ምኒልክ የተገደመው የአዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን መተዳደሪያ ደንብ በቤተ መንግሥትም ሆነ በቤተ ክህነት ሳይሰጠው በውዝፍ ቆይቶ ስለ ነበር የደብሩን አቅዋምና አስተዳደር የሚያመለክት ደንብ እንዲደራጅ ማድረጋቸው በቀዳሚነት ይጠቀሳል:: ብፁዕነታቸው ገዳሚን ከማስተዳደር ጋር አንደ ጊዜውም ሁኔታ የዳኝነቱን ሥራ አያካሒዱ የተሰመደ ጉባኤያቸውን በሰፊው ዘርግተው ያስተምሩ ጀመር:: የሐዲሳትና የፍትሐ ነገሥት ደቀ መዛሙርታቸውንም በማስተማር ብቻ ሳይሆን በምግብና በልብስ ይከባከቧቸው ስለ ነበር የተማሪው ቁጥር በእጅጉ ጨምሮ እንደ ነበር ይነገራል::

ግፈኛው የኢጣልያ ፋሽስት ሀገራችንን እስከ ወረረበት ጊዜ ድረስ በአዲስ ዓለም የንቡረ ዕድነት ሥልጣን ላይ ከቆዩ በኋላ በ1929 ዓ.ም. የጣልያን ወራሪ ኃይል ሕዝቡን ያረጋጋሁ መስሎት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በራሷ የራሷን ጳጳሳት እንድትሾም ፈቅጃለሁ ብሎ ከአምስቱ ጠቅላይ ግዛቶች የተመረጡ ሊቃውንት አዲስ አበባ ላይ ጉባኤ ሊያደርጉ ለጵጵስና ከተመረጡት አባቶች አንዱ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ነበሩ:: በዚህም ከነበሩባት አዲስ ዓለም ገዳም ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው ከሌሎች የተመረጡ አባቶች ጋር ኅዳር 21 ቀን 1930 ዓ.ም. በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ አብርሃም አንብሮተ ዕድ «ጳጳስ ዘሸዋ፣ እጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ» ተብለው ተሾሙ::

ምንም እንኳን በጣልያን ትእዛዝ ቢሆንም የአዲስ አበባው የሊቃውንት መንፈሳዊ ጉባኤና ብፁዓን አባቶች በተገለጠው ዓይነት ሥልጣን ስሚገባው ሥልጣንን እየሰጡ ሕዝቡን ማረጋጋት ቢጀምሩም በተፈጸመባቸው የግፍ ወረራ የተበሳጩት ኢትዮጵያውያን



አርበኞች በከተማም ይሁን በገጠር ወራሪውን ኃይል ጤና ይነሱት ጀመር:: ይልቁንም ቀድሞ አቡነ ጴጥሮስ በአዲስ አበባ፣ አቡነ ሚካኤል በኢሉባቦር ከወራሪው የፋሺስት ጦር ጋር ተናንቀው በሰማዕትነት ሲያልፉ፣ በሀገሪቱ የሚዘንመውን መከራ ተሰቅቀውና አግሬ አውጭኝ ብለው ወደ ሀገራቸው ሸሽተው በሔዱት በወቅቱ የሀገሪቱ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው ሲያገለግሉ በነበሩት ግብፃዊው አቡነ ቄርሎስ መንበር ላይ ተሾመው የነበሩት ብፁዕ አቡነ አብርሃም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ዉሳኔ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆኑ::

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳስ በነበሩባቸው ጥቂት ዓመታት ከጣልያን መንግሥት ጋር በስምምነት ይሠሩ ነበር ይባላል:: ይሁን እንጂ ብፁዕነታቸው ለወራሪው መንግሥት ይሰጡት የነበረውን ርዳታ አስመልክቶ ሁለት ዓይነት አስተያየቶች ይሠነዘራሉ:: አንዳንድ ሰዎች «ብፁዕነታቸው ቤተ ክርስቲያኗ እንደ ተቋም ድጋፍ እንድታደርግ ሲያደርጉ ወራሪውን መንግሥት በመንግሥትነት አምነው ተቀብለው ነበር» ሲሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ «ከመምህርነታቸው እንሥቶ ጳጳስ እንዲሆኑ፣ ከዚያም በሊቀ ጵጵስናው መንበር ያስቀመጣቸው ራሱ ወራሪው መንግሥት በመሆኑ የመቃወምም ሆነ የማውገዝ ኃይል አልነበራቸውም» ይላሉ:: ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ብፁዕነታቸው ከነበረው ወራሪ መንግሥት ጋር በሰላም ቆይተዋል:: ምናልባትም ሕዝቡን ከማሳመን አንጻር ወራሪው መንግሥት የቤተ ክርስቲያኗን ነጻነት አስከብሮ የራሷ ልጆች የሆኑ አባቶችን በመሾም ያደረገው ተንኮል ሳይሰምርለት የቀረ አይመጠ ስልም::

ብፁዕነታቸው በዚህ ሁኔታ በታላቁ የሐላፊነት መንበር ላይ ተቀምጠው በማስተዳደር ላይ ሳሉ ጠላት ድል ተነሥቶ ከሀገሪቷ ወጣ:: ነገር ግን ኢትዮጵያ ባሕር ተሻግሮ በመጣ ወራሪ ኃይል በተጠቃች ጊዜ አናውቅሽም ብላ የሔደችው የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያ በልጆቿ መሥዋዕትነት ነጻነቷን ከተቀዳጀች በኋላም ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በወረራው ጊዜ የሾሟቸው ጳጳሳትና ሊቀ ጳጳሳት በሥልጣናቸው እንዳይሠሩበት የውግዘት ቃሏን አሰተላለፈች::

በዚህ የተነሣም አቡነ ዮሐንስ ከሊቀ ጵጵስና መንበራቸው ወርደው አዲስ አበባ በቅዱስ ሁራኤል ቤተ ክርስቲያን እያስተማሩ እንዲቀመጡ ተደረገ:: ይሁን እንጂ ለጊዜው የኢትዮጵያ መንግሥት የግብፅ ቤተ ክርስቲያንን ጥያቄ ተቀብሎ በወቅቱ የተሾሙትን ሊቀ ጳጳሳትና ጳጳሳት ከአገልግሎት ቢያገላቸውም የቤተ ክርስቲያኗ ሊቃውንት የመብታችን ይከበር ጥያቄ ግን ተጋግሎ ቀጠለ:: በመሆኑም ደረጃ በደረጃ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን መሪዎች በራሷ

www.ethiopianorthodox.org

የመምሪጥና የመሾም ሙሉ መብቷን አገኘች፡፡ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስም ከላይ በተገለጠው ሁኔታ የተነጠቀ ሥልጣናቸው ተመለሰላቸው፡፡ ይሁን እንጂ ከዕድሜያቸው መግፋት የተነሣና ከማስተዳደሩ የበለጠ ቢያስተምሩ መልካም እንደሆነ ስለ ታመነበት ከሥልጣናቸው ጋር በአዲስ ዓለም ማርያም ገዳም በንቡረ ዕድነት እንዲያስተዳድሩና በዚያው እንዲቀመጡ ተደረገ፡፡

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በአዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ማርያም በንቡረ እድነቱ መዓርግ ላይ ሆነው ጉባኤያቸውን አስፋፍተው በማስተማር ላይ ሳሉ በተወለዱ በ73 ዓመት ዕድሜያቸው ሰኔ 3 ቀን 1948 ዓ.ም. ዐረፉ፡፡ ሥርዓተ ቀብራቸውም በዚያው በአዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተፈጸመ፡፡ የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን፡፡ አሜን፡፡



# 3.7. ብፁዕ አቡነ ሰላማ ቀዳማይ ጳጳስ

## /1865 - 1935 ዓ.ም/

ብፁዕ አቡነ ሰላማ በ1865 ዓ.ም. የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ቄስ ገበዝ ከነበሩት አባታቸው ቄስ ገበዝ ገብረ ሥላሴና የአክሱሙ ባላባት የንቡረ እድ ተክሌ ልጅ ከነበሩት የሕግ ሚስታቸው በአክሱም ተወለዱ፡፡

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ በዚያው በአክሱም ጽዮን ደብር ፊደል ቆጠሩ፡፡ የንባብ ትምህርታቸውንም ዳዊትን በሚገባ አንብበው አጠናቀቁ፡፡ ትምህርታቸውን በመቀጠልም ዜማንና ቅኔን ከየመምህራኑ በመዘዋወር ከተማሩ በኋላ ከአቡነ ሉቃስ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ፡፡ በዲቁናቸው በዚያው በአክሱም ጥቂት ካገለገሉ በኋላ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ዕድል ሀብተ ንጽሕ መሆኑን ስለ ተረዱት ከግብፃዊው አቡነ ማቴዎስ የቅስናን መዓርግ ተቀበሉ፡፡ ከዚያም በትግራይ ወደ ሚገኘው የአቡነ ሳሙኤል ገዳም ደብር ዓባይ ወርደው በተወለዱ በ24 ዓመታቸው መነኮሱ፡፡ በዚያው ገዳምም የቅዳሴ ዜማ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ፡፡

ብፁዕ አቡነ ሰላማ በመነኮሱ በአራት ዓመታቸው በ1893 ዓ.ም. የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አባት ልዑል ራስ መኮንን ትግሬን ይዙ በነበረበት ጊዜ ከእርሳቸው ፈቃድ ጠይቀው ስንቅም ተቀብለው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋዌው ወራት ድንቅ ድንቅ ተአምራትን ያሳየባቸውን ቅዱሳት መካናት ለመሳለም ወደ ኢየሩሳሌም ሔዱ፡፡ ከዚያም ወደ ግብፅ ወርደው በዚያ ያሉ ገዳማትን በመጎብኘትና በመሳለም ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ከአቡነ ቄርሎስ የቁምስና መዓርግ ተቀብለው ወደ አክሱም ተመለሱ፡፡

ብፁዕነታቸው ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ አክሱም ጽዮን ማርያም ላይ ጉባኤያቸውን ዘርግተው፤ ዝማሬና መዋሥዕት ቅዳሴም እያስተማሩ ብዙ መምህራንን በማፍራት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል ጀመሩ፡፡ ከማስተማርም ጋር በተሰጣቸው ሀብተ ክህነት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ማዕጠንተ ወርቅ ይዘው እየቀደሱ ያገለግሉ ነበር፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ አቡነ ሰላማ በዚህ ዓይነት ሲያስተምሩና ለቤተ ክርስቲያን ማኅቶት ሆነው ሲኖሩ ሀገሪቷንም ሆነ ሕዝቧን ክፉኛ ያወከው የኢጣልያ ወራሪ ኃይል ወደ ኢትዮጵያ ገባ:: የፋሺስት ወረራ የጀመረው ብፁዕነታቸው በሚያገለግሉበት ትግራይ አቅጣጫ በመሆኑ እንደ ሌላው የአካባቢው ሕዝብ እርሳቸውም ገና ከጅምሩ የመከራው ገፈት ቀማሽ ሆኑ:: ይኸውም ወራሪው የኢጣልያ ጦር ብፁዕነታቸው በአካባቢው አስተዳደርም ሆነ ሕዝብ ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነት ቀደም ሲል ተረድቶት ኖሮ ሰቃና መሣሪያ ደብቀው አስቀምጠዋልና ያምጡ በሚል ብዙ ፈተና አድርሶባቸዋል:: ነገር ግን ብፁዕ አቡነ ሰላማ በደረሰባቸው መከራ ሁሉ ሳይደናገጡ ለሀገሪቷ ነጻነት መመለስ ይጸልዩ ነበር::

የኢጣልያ ፋሺስት ኃይል በመጨረሻ በኢትዮጵያ ሕዝብና አብያተ ክርስቲያናት ላይ ያደረሰውን የግፍ ጭፍጨፋ ለማሰረሳትና በሕዝቡም ተቀባይነት ለማግኘት ሲል አንድ መሠሪ ሀዋጅ ሀወጣ:: ይኸውም «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለረጅም ዘመናት ስትና ፍቀው የነበረው ነገር እውን ሆነ» በሚል «ቤተ ክርስቲያኗ በራሷ ከራሷ ሊቃውንት ጳጳሳትንና ሊቀ ጳጳሳትን እንድትመርጥና እንድ ትሾም ፈቅጃለሁ፤ ለተግባራዊነቱም በሚያስፈልገው ሁሉ ድጋፌን እቸራለሁ» የሚል ነበር:: የዐዋጁ ተግባራዊነት በተቃረበ ጊዜ ብፁዕ አቡነ ሰላማ ሳይወዱ በግድ ከቦታቸው ተይዘው ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ተደረገ:: ከዚያም በወቅቱ በአዲስ አበባ የተሰበ ሰበው ጉባኤ ሊቃውንት ደግነታቸውንና ንጽሕናቸውን መስክሮ በብፁዕ አቡነ አብርሃም አንብሮተ እድ ኅዳር 24 ቀን 1930 ዓ.ም. «ዳግማዊ ሰላማ ጳጳስ ዘቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያዊት ኦርቶዶክሳዊት» ተብለው ተሾሙ:: በወቅቱ የተሰጣቸው ሀገረ ስብከትም ሐረር ነበር::

ለዚህ ታላቅ መዓርግ የበቁት ብፁዕ አቡነ ሰላማም ወደ ተሰ ጣቸው ሀገረ ስብከት በመሔድ የሐዋርያነት ተግባራቸውን መፈጸም ጀመሩ:: በወረራው የተነሳ የታሰሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን እንዲ ፈቱ፣ በጦርነቱ የፈረሱና የተቃጠሉ አብያተ ክርስቲያናት እንዲ ሠሩ፣ ገና የወንጌልን ብርሃን ሳያዩ በአረማዊነት የነበሩ በርካታ ሰዎችንም በማስተማር በጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ እንዲ ወለዱ አድርገዋል::

ብፁዕ አቡነ ሰላማ በዚህ ዓይነት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሰጠቻቸውን ሐላፊነት በብቃት በመወጣት ላይ ሳሉ የነገሩትን የማይረሳ፣ የለመኑትን የማይነሣ አምላክ የእርሳቸውንም ሆነ የኢትዮ ጵያውያንን ኀዘንና ልቅሶ ተመልክቶ ለአምስት ዓመታት ኢትዮጵ ያንና ኢትዮጵያውያንን ሲያውክ የነበረው የኢጣልያ ወራሪ ኃይል ድል ተመትቶ የሀገሪቱ ነጻነት ተመለሰ:: ብፁዕነታቸው በተገኘው



ነጻነት ተደስተው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ የሀገረ ስብከታቸውን ምእመናን እያስተማሩ በዚያው ቆዩ::

ለጥቂት ዓመታት ታውኮ የነበረው የኢትዮጵያ ሰላም ተመልሶና ጸንቶ በሀገሪቱ ጠቅላይ ግዛቶች የነበረው ሁኔታ ከተረጋጋ በኋላም ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አባታቸው ልዑል ራስ መኰንን ያቀኑትን ሀገር ሊጐበኙ ወደ ሐረር ወረዱ:: በዚህ ጊዜ ብፁዕ አቡነ ሰላማ ወደ ንጉሡ ቀርበው እግዚአብሔር የሚወዱትን ሕዝብ ለሳም መልሶ፤ እርሳቸውንም ከሔዱበት በሰላም አምጥቶ ከሀገራቸውና ከሕዝባቸው ጋር ስላገናኛቸው የተሰማቸውን ደስታ ገለጡ:: ቀጥሎም ዕረፍታቸው ተወልደው ባደጉባትና ከዲቁና ጀምሮ ባገለገሉባት አክሱም መሆኑን በመንፈስ ቅዱስ ሰሰ ተረዱ ንጉሡን «ከነጻነቴ ጋር ብሩህ ፊትዎን ለማየት፣ ጥዑም ቃልዎን ለመስማት እግዚአብሔር ካበቃኝ እንግዲህ ደክሜያለሁና የምፈልገው ነገር የለኝም፤ ወደ ጥንቱ በታዬ ይመልሱኝና ከበአቴ ሆኜ እግርር ፀሮ፤ ዕቀብ ንግሦ እያልኩ ዳዊት እንድደግም ይፍቀዱልኝ» በማለት አባታዊ ተማኅፅኖ አቀረቡ::

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም የብፁዕነታቸውን ልመና ተቀብለው የወደዱት እንዲሆን ፈቀዱላቸው:: በሁኔታው በእጅጉ የተደሰቱት ብፁዕ አቡነ ሰላማም ጃንሆይን አመስግነው ወደ ጥንት መካናቸው አክሱም ጽዮን ሔዱ:: በዚያም ለአንድ ዓመት ከአምስት ወር ዳዊት ደግመው እናታቸውን ጽዮን ማርያምን ደጅ ሲጠኑ ቆዩ::

በመጨረሻም ነሐሴ 15 ቀን 1935 ዓ.ም. ጸሎታቸውን አድርሰው ተቀምጠው ከካህናቱና ደቀ መዛሙርታቸው ጋር እየተጫ ነጋገሩ ባለ ያለ ሕማምና ያለ ፃእር ነፍሳቸው ከሥጋቸው ተለየች:: አስከሬናቸውም ከብፁዕ ዕጨጌ ቴዎፍሎስና ከአባታቸው ከቄሰ ገበዝ ገብረ ሥላሴ መቃብር ጋር በታላቅ ክብር ሀረፈ:: የብፁዕነታቸው በረከት ይደርብን:: አሜን::

www.ethiopianorthodox.org

# 3.8. ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ቀዳማዊ ጳጳስ

## /1862 - 1939 ዓ.ም./

ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ከአባታቸው ከመምሬ ሱበንዮስ እና ከእናታቸው ከወለተ ጻድቃን በቀድሞው የኤርትራ ክፍለ ሀገር፣ አካለ ጉዛይ አውራጃ፣ ከንን ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ከሚባለው ቦታ ተወለዱ።

በተወለዱ በሰባት ዓመታቸው በወቅቱ በነበረው ደንብ መሠረት የቤተ ክርበቲያንን ትምህርት ይማሩላቸው ዘንድ አባታቸው መምሬ ሱበንዮስ ወደ ደብረ ዳሞ ወበደው በወቅቱ የደብረ ዳሞ አበ ምኔት ለነበሩት መምህር ወልደ ዐቢየ እግዚእ አስረከቧቸው። በዚያም በአጐታቸው ቁጥጥርና መምህርነት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በሚገባ ከተማሩ በኋላ የዲቁናን መዓርግ ተቀበሉ።

ትምህርታቸውን በመቀጠል ጸዋትወ ዜማን ለመማር ያደጉበትን ገዳም ለቀው ወደ ጎንደር ሲያቀኑ ሲሉ ርእሰ ደብር ወልደ ማርያም የተባሉ የድጓ መምህር ወደ ዚያው ወደ ደብረ ዳሞ ስለመጡ ያሰቡትን የዜማ ትምህርት እየተማሩ ቆዩ። የዜማ ትምህርታቸውን በሚገባ ጨርሰው ከተጠቀሱት መምህር የምስክር ወረቀት ካገኙ በኋላ ይህም በማኅበረ መነኮሳቱ በመታወቁ በዚያው በደብረ ዳሞ ገዳም የድጓ መምህር እንዲሆኑ ተፈቀደላቸው። ይሁን እንጂ የዜማውን ትምህርት ከዳር አድርሰው ለመምህርነት ቢበቁም በውስጣቸው የነበረው የመማር ፍቅር በጉባኤያቸው እንዲቆዩ አላደረጋቸው አለ። በመሆኑም የሞቀ ጉባኤያቸውን በመተው የገዳሙን ማኅበር ካበፈቀዱ በኋላ ቅኔን ከምንጩ ሊማሩ ወደ ጎጃም ጉዞዋቸውን ቀጠሉ። ይሁን እንጂ ጉዟቸውን በማፋጠን ዓድዋ ላይ ሲደርሱ በደብረ ብርሃን ሥላሴ የቆዩትንና በሞያው የታወቁትን የኔታ ክፍሌን በማግኘታቸው አሳባቸውን በመቀየር ከየኔታ ክፍሌ ጉባኤ በመግባት የቅኔ ትምህርታቸውን ፈጸሙ።

ብፁዕነታቸው ዓድዋ ላይ ለሦስት ዓመት ከመንፈቅ ከየኔታ ክፍሌ ቅኔን ሲማሩ ወደ አክሱምና ሌሎች በአካባቢው ወደ ሚገኙ ቅዱሳት መካናት በመዘዋወር ያገለግሉ ነበር። በዚህም ከአካባቢው ካህናት ጋር የጠበቀ ወዳጅነት ነበራቸው። የቅኔውን ትምህርት በዚህ በይነት የተማሩት ብፁዕ አቡነ ማቴዎበ ወደ ደብረ ዳሞ በመመለበ የታወቁ የመጻሕፍት መምህር ከነበሩትና በወቅቱ የገዳሙ አበ ምኔት ከነበሩት መ/ር ኪዳነ ማርያም ዘንድ የብሉያትንና የሐዲሳትን ትርጓሜ ተማሩ።



ብፁዕ አቡነ ማቴዎበ በዚህ ዓይነት ከቦታ ቦታ በመዘዋወር መንፈሳዊን ዕውቀት ክቀሰሙ በኋላ ልክ በ34 ዓመታቸው በዚያው ገዳም መዓርገ ምንኩስናን ተቀበሉ። ከመነኰሱም በኋላ በጸሎትና በትኅርምት ሆነው ድጓ እያበተማሩ ቆዩ። ዕድሜያቸው 36 ዓመት ሲደርስም በማኅበሩ በሙሉ ድምፅ ተመርጠው የገዳሙ አበ ምኔት በመሆን በአቡነ አረጋዊ ወንበር ለመቀመጥ በቁ። እግዚአብሔር ገና በሰባት ዓመታቸው ገብተው ፊደል ቆጥረው ባደጉበት ገዳም ላይ በታላቅ ሐላፊነት ስለ ሾማቸው እያመሰገኑ፣ በመልካም አበተዳደራቸውም ከማኅበረ መነኰሳቱ፣ ከአካባቢው ካህናትና መኳንንት ጋር በመበማማት ማገልገል ቀጠሉ። በዚህም ምንም እንኳን የገዳሙ ሕግ በገዳሙ ላይ አበ ምኔት ሆነው የሚሾሙ አበው ባምስት ባምበት ዓመት ከሹመታቸው እየተነሡ ሌላው እንዲተካ ቢያዝም ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ በግብረ ገብነታቸውና በመልካም አበተዳደራቸው ባተረፉት የመነኰሳቱ አክብሮትና ፍቅር የተነሣ በተደጋጋሚ ሹመታቸው እየጸናላቸው ለ21 ዓመታት በአበ ምኔት ወንበራቸው ላይ ተቀምጠው ገዳሙን መሩ።

ይህ የብፁዕነታቸው ደገኛ ተግባር ከአካባቢው አልፎ አዲበ አበባ ከንጉሡ ቤተ መንግሥት ድረስ ተሰማ። በዚህም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አዲሰ አበባ ተቀምጠው ለአገሪቱ ሰላምና ደኅንነት እንዲጸልዩ ወደ አዲበ አበባ አስመጧቸው። ይሁን እንጂ ብፁዕነታቸው ወደ አዲበ አበባ መጥተው ብዙም ሳይቆዩ ወራሪው የኢጣልያ ፋሺስት ጦር አዲበ አበባን ተቆጣጠረ። በጠላት ድርጊት ክፉኛ ያዘኑት ብፁዕነታቸውም ወደ እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም በመግባት ለአንድ ዓመት ያህል ዘግተው ለአገሪቱ ሰላም መመለበ ሲጸልዩ ቆዩ። ይሁን እንጂ ከዓመት በኋላ በራሰ ሥዩም አማላጅነት ከዘጉበት ቦታ ወጥተው በሰላም ወደ ጥንት ገዳማቸው ደብረ ዳሞ እንዲመለሱ ተደረገ።

በርካታ አባቶች በግፍ በሚጨፈጨፉበት፣ ለእስራትና ለእንግልት በሚዳረጉበት በዚያ ቀውጢ ዘመን ብፁዕነታቸው ያለ ምንም ሰቃይና እንግልት ያስተዳድሩት ወደ ነበረው ገዳም በመግባታቸው ተደሰቱ። በአንድ ጐን ግን በሕዝባቸውና በሃይማኖት ወንድሞቻቸው ላይ እየደረሰ ያለውን ጭፍጨፋና እንግልት እየሰሙ ማዘናቸው አልቀረም። ስለ ሁሉም ከገዳሙ መነኰሳት ጋር ለአንድ ዓመት

www.ethiopianorthodox.org

ሲጸልዩ ከቆዩ በኋላ የኢጣልያ መንግሥት ሳያስቡት ወደ አሥመራ ወሰዳቸው:: ከዚያም በአውሮፕላን ወደ አዲስ አበባ አስመጣቸው::

ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ከገዳሙ ወደ አሥመራ ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ሲወሰዱ እርሳቸውንም እንደ ሌሎች ወንድሞቻቸው ሊገድሏቸው ነው በሚል የገዳማቸው መነኰሳትና የአካባቢው ሕዝብ በእጅጉ አዝነው ነበር:: ይሁን እንጂ ቆይቶ ብፁዕነታቸው የተወሰዱት ለከፍተኛ መዓርግ በመታጨታቸው እንጂ ሊገደሉ እንዳልሆነ ተሰማ::

የተባለው እውነት ሆኖ ብፁዕነታቸው ኅዳር 2 ቀን 1930 ዓ.ም ከሌሎች ወንድሞቻቸው ጋር በብፁዕ አቡነ አብርሃም ሊቀ ጳጳሳት አንብሮተ እድ የጵጵስና መዓርግ ተሾሙ:: የተሰጣቸው ሀገረ ስብከትም ወሎ ነበር:: እግዚአብሔር በክብር ላይ ክብር ጨምሮ በስተርጅና እዚያ ስላደረሳቸው ቢደሰቱም ሰላሟ ጸንቶ የኖረው አገራቸው በመታወኳና መሪዋ ለስደት፣ ሕዝቧ ለከፋ ችግር መዳረጉን እያዩ ሲያዝኑ ቆዩ:: ከአምስት ዓመት በኋላም የሀገሪቷ ሰላም ተመልሶ ነጻነቷን አገኘች:: ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም ወደ ሀገራቸው ተመለሱ::

የብፁዕነታቸውን ደግነትና ፍጹም መንፈሳዊነት ቀድሞ ያውቁ የነበሩት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱም የሚያስፈልጋቸውን ማንኛውም ርዳታ እያደረጉ በደኅና ይኖሩ ጀመር:: ይሁን እንጂ ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ዕድሜያቸው እየገፋ፣ እርጅናም የበለጠ እየተጫናቸው በመሔዱ ወደ ጥንት መካናቸው ደብረ ዳሞ ሔደው በዚያው ማረፍ ትልቅ ምኞታቸው ሆነ:: ይኽን ፍላጐታቸውን ንጉሠ ነገሥቱ በእሺታ በመቀበላቸው ወደ ደብረ ዳሞ ተሸኝተው መጋቢት 30 ቀን 1939 ዓ..ም ደብረ ዳሞ ገቡ::

ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ላደጉበት ገዳም ያበቃቸውን አምላክ አመስግነው፣ ደብረ ዳሞ በገቡ በ50 ቀናቸው ግንቦት 27 ቀን 1939 ዓ.ም በተወለዱ በ77 ዓመታቸው የንግሀ ጸሎታቸውን አድርሰው ውዳሴ አምላክ በመድገም ላይ እንዳሉ ነፍሳቸው ከሥጋቸው በሰላም ተለየች:: እንደ ተመኙት ሥርዓተ ቀብራቸውም በዚያው ተፈጸመ:: የብፁዕነታቸው በረከት ይደርብን:: አሜን::



# 3.9. ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ቀዳማይ ጳጳስ

## /1837 - 1940 ዓ.ም/

መዓርገ ጵጵስና ከማግኘታቸው በፊት መምህር አካሉ ይባሉ ነበር:: መምህር አካሉ በ1837 ዓ.ም በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት፣ እናርጅ እናውጋ ወረዳ፣ ደብረ ወርቅ ከተማ ከአባታቸው ከአባ ኪዳነ ማርያምና ከእናታቸው ከወ/ሮ ወለተ መስቀል ተወለዱ::

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ወላጆቻቸው በዚያው በደብረ ወርቅ ማርያም ገዳም ዜማ ሲያስተምሩ ለነበሩት ለመሪ ጌታ ይግዛው ያስተምሩልን ብለው ሰጧቸው:: መምህር አካሉም በሕፃንነት አእምሮአቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በፍጥነት ጨርሰው ሁለተኛ ደረጃ የሆነውን ጸዋትወ ዜማን ቀጠሉ:: ዕድሜያቸው 17 ዓመት ሲሆን በሚያስደንቅ ሁኔታ ጸዋትወ ዜማን በብቃት አጠናቀው በድጓ መምህርነት ተመረቁ::

መምህር አካሉ በመምህርነት ከተመረቅሁ ይበቃኛል፤ ጉባኤዬን ዘርግቼ እያስተማርኩ ልኑር አላሉም:: ትምህርታቸውን በመቀጠል እዚያው ጎጃም መጋቢ አይቼህ ከተባሉ ሊቅ ቅኔ መቀጸል ጀመሩ:: የቅኔውንም ትምህርት በሚያስገርም ፍጥነት ተምረው በ23 ዓመት ዕድሜያቸው ቅኔን ለማስተማር ተመረቁ:: ከዚህ በኋላ ምስክርነት ባገኙባቸው ሁለት ሞያዎች /ቅኔና ድጓ/ ጉባኤ ዘርግተው ማስተማር ጀመሩ:: የጉባኤያቸውን መስፋት፣ የእርሳቸውንም ሊቅነት የሚሰማው ተማሪ ራቅ ካለ ቦታ ድረስ እየመጣ ጉባኤያቸውም ከዕለት ወደ ዕለት እየሰፋ ሔደ::

መምህር አካሉ ከማስተማር ጋር ከዘጌ መጥተው በደብረ ወርቅ ሲያስተምሩ ከነበሩት ከመምህር ኃይለ ማርያም ሐዲስን ያሔዱ ነበር:: በዚህ መካከል በወቅቱ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት ዐፄ ዮሐንስ ከግብፅ ያመጡአቸው ጳጳሳት ከመቀሌ ወደ ደብረ ታቦር መምጣታቸው ተሰማ:: ይህንን የሰሙት መምህር አካሉም ሃያ አምስት ደቀ መዛሙርታቸውን በማስከተል ወደ ደብረ ታቦር ገሠገሡ:: ከተማሪዎቻቸው ጋር ሞጣ ሲደርሱ አንድ በጎንደር ይኖሩ የነበሩና ሞኝ ገብረ ማርያም የተባሉ ደገኛ መነኩሴ

www.ethiopianorthodox.org

አገኙአቸው:: መነኩሴውም በብቃታቸው ኃላፊያትና መጻእያት የተገለጡላቸው ነበሩና ወደ መምህር አካሉ ቀርበው «ወዴት ትሔደላችሁ?» ሲሉ ጠየቋቸው:: መምህር አካሉም በትሕትና «ለልጆቼ ሥልጣነ ዲቁናን ላስጥ ወደ ደብረ ታቦር እሔዳለሁ» አሏቸው::

እኒያ ግሑስ መነኩሴ ግን ከዚያ አስቀድሞ ለኢትዮጵያውያን ያልተሰጠ መዓርገ ጵጵስና ለመምህር አካሉ እንዲ ሰጣቸው በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦላቸው «አቡን ከእናንተ ጋር ሳለ እናንተ አቡን ፍለጋ ትሔዳላችሁ?» አሏቸው:: መምህር አካሉ ምንም እንኳን ከመነኩሴው ይህን ቢሰሙም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «አንስ ኢየሐሥሥ ተድላ ለርእስየ» ብሎ ያስተማረውን ትምህርት ገንዘብ በማድረግ የዚህን ዓለም ክብር አይሹትም ነበርና ግሑሱ ይህ ነገር በኋላ ዘመን ለእርሳቸው እንዲደርስ መናገራቸውን አላወቁም ነበር:: ወዬው እውነት በሆነልኝ ብለውም አልጓጉም ነበር:: ሌሎች ይህን የመሰሉ ትንቢቶችም በሌሎች የበቁ አባቶች ተነግረውላቸው እንደ ነበር ይተረካል::

መምህር አካሉ ከተማሪ ቤታቸው ጀምሮ እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው ድረስ የዕለተ ዓርብ ምግባቸውን ለነዳያን እየሰጡ፣ እንግዳ እየተቀበሉ፣ በጸሎትና በትኀርምት ይኖሩ ነበር:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ወበከመ ሠራዕከዎሙ ለቤተ ክርስቲያን ዘገላትያ ከማሁ እንትሙኒ ግበሩ በበእሑድ» ብሎ ለቆሮንቶስ ሰዎች ያስተማረውን ሕግ ለመፈጸም እሑድ እሑድ በደብራቸው ወደ ሚኖሩ ድሆች በመሔድ በመካከላቸው በመቀመጥ ምሳ ያበሉ፣ መጠጥም ያጠጡ ነበር::

መምህር አካሉ በዚህ ዓይነት ለ24 ዓመታት በደብረ ወርቅ ማርያም ገዳም ድጓን፣ ቅኔንና መጻሕፍተ ሐዲሳትን ካስተማሩ በኋላ አዲስ አበባ ይኖሩ የነበሩትንና አለቃ አልያስ ይባሉ የነበሩትን የተማሪ ቤት ጓደኛቸውን ለመጠየቅ ወደ አዲስ አበባ መጡ:: በለውቀታቸውና በምግባራቸው የተመሰከረላቸውን የመምህር አካሉን ወደ አዲስ አበባ መምጣት የሰሙት ንጉሥ ዐፄ ምኒልክ የጉባኤ ቦታ ቢሰጧቸውና አዲስ አበባ ላይ ጉባኤ ዘርግተው ለመኖር ፈቃዳቸው እንደሆነ በመግለጽ ለመምህር አካሉ መልእክት ላኩባቸው:: ይሁን እንጂ በከተማ መኖር ለያዝኩት የምንኩስና ሕይወት አይስማማኝም በማለት ፈቃዳቸው እንዳልሆነ ከይቅርታ ጋር ለንጉሡ ላኩባቸው::

የትምህርት ቤት ባልንጀራቸውን ለመጠየቅ በ1882 ዓ.ም ከደብረ ወርቅ ወደ አዲስ አበባ የመጡት መምህር አካሉ ፊታቸውን ወደ ጎጃም ሳይመልሱ ወደ ይፋት ሔዱ:: በይፋት አውራጃ ጣርማ በር ጊዮርጊስ አንድ ዓመት ከኖሩ በኋላ ወደ ሰላ ድንጋይ ቅዱስ



ማርቆስ ደብር ገብተው ቅኔ እያስተማሩ ከአለቃ ኃይለ ማርያም ወልደ ሐና የሃይማኖተ አበውና የፍትሐ ነገሥት ትርጓሜን ማሔድ ጀመሩ:: መጽሐፉ ሊቃውንቱን በሚገባ ካጠናቀቁ በኋላ ሀሳባቸው እንደ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ከሰው ተለይተው፣ ጠለ ገዳም ተመግበው፣ በተባሕትዎ ለመኖር ነበረና ደቀ መዝሙራቸውን አለቃ ኃይለ ሥላሴን አስከትለው ከሰላ ድንጋይ ወደ ጀር ገዳም በመሔድ ለረጅም ጊዜ በዚያ ኖሩ::

ይህን የመምህር አካሉን ንጽሕናና ቅድስና የሰሙት በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት የነበሩት ግብፃዊው አቡነ ማቴዎስ በ1892 ዓ.ም ከነበሩበት ገዳም ወደ አዲስ አበባ አስጠርተዋቸው መዓርገ ቅስናንና ቁምስናን በአንድ ጊዜ ሰጥተው የሰላ ድንጋይ ቅዱስ ማርቆስን ደብር በመሾም ላኳቸው:: ረዘም ላለ ጊዜ ሰላ ድንጋይ ቅዱስ ማርቆስን ከማስተማር ጋር በብቃት ሲያስተዳድሩ የቆዩት መምህር አካሉ ከዚያ በመነሣት የሞረት ደብረ ብሥራት ዜና ማርቆስ ገዳም አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ:: ነገር ግን ብዙም ሳይቆዩ ወደ ቀደመ ቦታቸው ሰላ ድንጋይ ተመለሱ::

ከላይ በሌሎች አባቶች እንዳየነው ወራሪው የፋሺስት ኃይል ኢትዮጵያን ወሮ እንደ ማታለያ ቤተ ክርስቲያኗ የራሷን ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንድትሾም ባደረገ ጊዜ መምህር አካሉ በብፁዕ አቡነ አብርሃም አንብሮተ እድ «ብፁዕ አቡነ ሉቃስ» ተብለው ምዕራብ ኢትዮጵያን ተሾሙ:: ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ከዲቁና ጀምሮ ሲያገለግሏት የኖሯትን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በጵጵስናም መዓርግ የበለጠ ከማስተማር ጋር በጥሩ ሁኔታ እያስተ ዳደሩ ማገልገል ጀመሩ:: እርሳቸው የተሾሙበት ዘመን ሀገሪቷ ለከፋ ችግር የተዳረገችበት ስለ ነበር ሕዝቡን በማጽናናት፣ የሀገሪቷ ሰላምም እንዲመለስ አብዝቶ በመጸለይ፣ ካህናቱ የሕዝበ ክርስቲያኑን ችግር ችግራቸው አድርገው በጸሎትም በማስተማርም እንዲተጉ ማድረግ ጀመሩ:: ይሁን እንጂ ዕድሜ ዘመናቸው ብዙ ስለሆነና፣ በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት፣ በትሩፋት ሥራ ሁሉ ተወስነው ነዋሪ ስለሆኑ እርጅና እየተጫናቸው መጣ:: በዚህም የተለመደው ትሩፋ ትና ጸሎት ባይቀርባቸውም ለረጅም ዘመን የቆዩበት ጉባኤ ሠርቶ ማስተማርና በዐውደ ምሕረት ቃለ እግዚአብሔርን መስበክ አቆሙ::

እግዚአብሔር የኢትዮጵያውያንን መበደል ተመልክቶ አገሪቷን ከወራሪው የፋሽስት ጦር ነጻ ካወጣና ንጉሡ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ ብፁዕ አቡነ ሉቃስን እንደ ሌሎች አባቶች በክብር አኑረው በየጊዜው ሲያስጠይቋቸው ኖሩ:: በመጨረሻም ታኅሣሥ 30 ቀን 1940 ዓ.ም በ103 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም ውጣ ውረድ በክብር ዐረፉ:: የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን:: አሜን::

www.ethiopianorthodox.org

# 3.10. ብፁዕ አቡነ ማትያስ ቀዳማይ ጳጳስ

## /1860 ዓ.ም - ?/





አባ ማትያስ ተብለው ከመጠራታቸው በፊት መምህር ሣህሌ ተብለው ይታወቁ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ማትያስ በያኔው ሸዋ ጠቅላይ ግዛት አንኮበር ወረዳ ጠለሳ ከሚባል ቦታ በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ ተከብረው ከሚኖሩት ወላጆቻቸው በ1860 ዓ.ም ተወለዱ:: ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ከቤታቸው ሳይወጡ በአባታቸው አማካይነት የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን በሚገባ አጠናቀቁ:: ከዚያም ግብፃዊው አቡነ ማቴዎስ ለአገልግሎት አፈር ባይኔ ወደ ተባለው ወደ ብፁዕነታቸው የትውልድ ሀገር አካባቢ ሔደው ነበርና ዲቁና ተቀበሉ:: ከዚያም በዲቁና ተወልደው ያደጉበትን የጠለሳ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር ለጥቂት ጊዜያት ሲያገለግሉ ቆዩ::

ይሁን እንጂ ትምህርታቸውን መቀጠል የእሳቸውም ሆነ የአባታቸው ፈቃድ ነበርና ከወላጆቻቸው ቤት ወጥተው ወደ ሚጣቅ ሀማኑኤል ሔዱ:: በዚያም የጸዋትወ ዜማ ትምህርታቸውን በሚገባ ተምረው አጠናቀቁ:: አሁንም ትምህርታቸውን ለመቀጠል ወደ አዲስ አበባ መጥተው ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ሳይ ሰፈ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት መምህር ዘንድ የቅኔ ትምህርታቸውን በሚገባ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ::

ብፁዕ አቡነ ማትያስ ምንም እንኳን የቅኔውን ሞያ በአግባቡ በመያዝ በመምህርነት ቢመረቁም አሁንም ትምህርት በቃኝ አላሉም:: በመሆኑም የመጻሕፍትን ምሥጢር ለማወቅ ከአዲስ አበባ ተነሥተው ወደ አንኮበር ወረዱ:: በዚያም ጉባኤ ዘርግተው ሲያስተምሩ ከነበሩት መምህር ወልደ ሚካኤል ሐዲሳትን አሔዱ:: ከዚያም ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ከመምህር ደስታ /በኋላ አቡነ አብርሃም/ ዘንድ መጻሕፍተ ሊቃውንትን በተለይ አፈ ወርቅን በሚገባ ተማሩ::

በዚህ ዓይነት መንፈሳዊ ዕውቀትን በመሰብሰብ ራሳቸውን ያጠነከሩት ብፁዕነታቸው በ1910 ዓ.ም ወደ ደብረ ሊባኖስ ወርደው ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጸሙ:: ከዚያም ወደ ትውልድ ሀገራቸው አንኮበር ወርደው ቅኔንና ሐዲሳትን ማስተማር ጀመሩ:: በዚያም ለአራት ዓመታት በማስተማር ደቀ መዛሙርትን ካፈሩ በኋላ በ1910 ዓ.ም. ወደ ሐረር በመውረድ በጥምቀተ ባሕር ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ዘርግተው ቅኔንና ሐዲሳትን ሲያስተምሩ ቆዩ::

ብፁዕነታቸው ምንም እንኳን ከተማሪነት አልፈው ማስተማር ከጀመሩ ዓመታት የተቆጠሩ ቢሆንም የሚቀራቸው ዕውቀት እንዳለ በመገንዘብ በ1914 ዓ.ም ሐረር ላይ የዘረጉትን ወንበር በማጠፍ ወደ አሰቦት ገዳም በመግባት አለቃ ገብረ መድኅን ከተባሉ ሊቀ ሃይማኖተ አበውን አሔዱ:: ትምህርታቸውን እየተማሩ፣ ሌሎች

www.ethiopianorthodox.org

ተማሪዎችን እያስተማሩና በገዳሙ ውስጥ ካሉ መነኮሳት ጋር በትኅርምት እየኖሩ ሳሉ በ1920 ዓ.ም ድሬዳዋ ከተማ ለሚገኘው የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን መምዐር ሆነው ተሾሙ:: ሹመቱን በአኮቴት ተቀብለው ወደ ድሬዳዋ የሔዱት ብፁዕነታቸው በዚያም ጉባኤ ዘርግተው አያሌ ደቀ መዛሙርትን ከማፍራት ጋር በዐውደ ምሕረት ለምእመናኑ ወንጌልን በማስተማር ሰፋ ያለ አገልግሎት ሰጥተዋል::

የብፁዕነታቸውን ሰፊ አገልግሎት የተገነዘበው ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት ብፁለነታቸው ከፍ ያለ ወንበር ቢሰጣቸው የበለጠ አገልግሎት እንደ ሚያበረክቱ በመገንዘቡ በ1924 ዓ.ም. ከድሬዳዋ ምንጃር ወደ ሳማ ስንበት ገዳም /አሁን ብሔረ ሕያዋን እግዚአ ለሰንበት ተብሏል/ ተዛውረው በመምህርነት እንዲያገለግሉ ሾሟቸው:: ይሁን እንጂ በገዳሙ ብዙም ሳይቀዩ በ1925 ዓ.ም ወደ ሐረር ተመልሰው ከምዕልሻ ማርያም በተባለችው ደብር በመምህርነት ተሹመው እንዲሔዱ ተደረጉ:: በዚያም የተለመደ አገልግሎታቸውን በለፉት በመለጠት ላይ እንዳሉ የጣሊያን ወራሪ ኃይል ቀድሞ የተሾሙትን እነ አቡነ ጴጥሮስንና አቡነ ሚካኤልን ገድሎ ሌሎች ይሾሙ የሚል የተዛባ ዐዋጅ ሲያወጣ ብፁዕነታቸው በወቅቱ ተሠይመው በነበሩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ተመርጠው መስከረም 1 ቀን 1932 ዓ.ም በወቅቱ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው በተመ ረጡት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ አንብሮተ እድ «ብፁዕ አባ ማትያስ ጳጳስ ዘሸዋ ተብለው ተሾሙ::


ብፁዕነታቸው የቀደሙት ሁለት ብፁዓን ጳጳሳት በግፍ ተገድለው፣ የሀገሪቱ ንጉሥና ታሳሳቅ ሹማምንት ተሰደውና ተግዘው፣ ሕዝቡ በችግር እየተሰቃየ ይህ ሹመት በመምጣቱ ባይደሰቱም በሊቃውንቱ ግፊትና ምክር ሹመቱን በጸጋ ተቀብለው ሀገረ ስብከታቸውን ማስተዳደር፣ ለሀገሪቷ ሰላምና መረጋጋት መጸለይ ጀመሩ::

ከአምስት ዓመታት በኋላ ሀገሪቷ ነፃነቷ ተመልሶ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ሀገራቸው ሲመለሱና ቀድሞ የነበረው ሁኔታ ሲመለስ ብፁዕነታቸው በወረራው ወቅት እንደ ተሾሙት ሌሎች ብፁዓን አባቶች ከወረራ በፊት ወደ ነበሩበት ቦታ ተመልሰው የቀደመ አገልግሎታቸውን እንዲለጡ ተደረጉ:: ይሁን እንጂ ብዙም ሳይቀዩ ባደረባቸው ሕመም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን:: አሜን::



# 3.11. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ካልአይ ጳጳስ

## /1878 - 1952 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

መምህር ገሪማ ወልደ ኪዳን ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ከአባታቸው ከመሪ ጌታ ወልደ ኪዳንና ከእናታቸው ወ/ሮ /በኋላ እማሆይ/ ደስታ ወልደ ገብርኤል ግንቦት 7 ቀን 1878 ዓ.ም በወሎ ክፍለ ሀገር ግሸን ማርያም ተብሎ በሚጠራው ቦታ ተወለዱ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ከርስትና በተነሡባት ግሸን ማርያም ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ማለትም ንባብና የቃል ትምህርት በትጋት አጠናቀቁ። ትምህርታቸውን በመቀጠልም ከአባታቸው ከመሪ ጌታ ወልደ ኪዳን ሥር ሆነው ጸዋትወ ዜማን ተከታተሉ። የእርሳቸው ቀለም የመያዝ ብቃት ከአባታቸው የቅርብ ክትትል ጋር ተዳምሮ መምህር ገሪማ ሁለቱንም የትምህርት ደረጃ በፍጥነት አጠናቀቁ።

ብፁዕነታቸው ከዚህ በኋላ ቅኔ ለመማር ያደጉባትን ደብር ትተው ወደ ቦሩ ሔዱ። በዚያም የቅኔ ትምህርታቸውን አቀላጥፈው ተማሩ። በመምህር ገሪማ የረቀቀውን የማመሰጠር፣ የተሰወረውን መርምሮ የማግኘት ብቃት መምህራቸው ይደነቁ ነበር። በሚያስደንቅ ፍጥነት ቅኔን ከነአገባቡና ሞያው የተማሩት መምህር ገሪማ የመጻሕፍትን ትርጓሜ ለመመርመር በ1898 ዓ.ም መርጦ ከተባለው ቦታ ሰፊ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ወደ ነበሩት መምህር ደስታ /በኋላ አቡነ አብርሃም/ ሔዱ።

በዚያም መጻሕፍተ ሐዲሳትን ለሦስት ዓመታት አጠኑ። ከመምህር ደስታ የጀመሩትን ትምህርት ሳይጨርሱ ወደ ጎንደር በመሻገርም ከአለቃ ዮሐንስ ዘንድ ፍትሐ ነገሥትን አጠኑ። ከዚያም የዐሥራ አራቱን መጻሕፍተ ቅዳሴ ትርጓሜ መካነ ኢየሱስ ላይ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት አለቃ ወልደ ሚካኤልና ከደረስጌው ከአለቃ ብሩ ጠንቅቀው ተማሩ። ከዚህ በኋላ ባገኙት የዜማ መምህርነት ማረጋገጫ በ1910 ዓ.ም ጉባኤ ዘርግተው ቅዳሴ ያስተምሩ ጀመር።

የመምህር ገሪማን የማስተማር ብቃትና የጉባኤያቸውን በረከት የሰማው ተማሪ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል እየመጣላቸው ጉባኤያቸው እያደር እየሰፋ ታዋቂነታቸውም እየጨመረ ሔደ። በንጽሕናና በድንግልና ተወስነው የማስተማር ተግባራቸውን ለማጠናከር ጉባኤያቸውን ለሌላ መምህር አስረክበው ወደ ደብረ ሊባኖስ በመሔድ ሥርዓተ ገዳምን የበለጠ ካጠኑ በኋላ ጥር 7 ቀን 1916 ዓ.ም ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጸሙ። ብዙም ሳይቆዩ የካቲት 12 ቀን በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ግብፃዊው አቡነ ማቴዎስ ቅስናን ተቀበሉ።

ከዚህም በኋላ መምህር ገሪማ ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም



በመጋቢት ወር ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ሔዱ። እንዳሰቡት በቅድስት ሀገር ለስድስት ወራት ያህል ተዘዋውረው ቅዱሳት መካናቱን ከተሳለሙ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው በያኔው ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ አዲስ ተተክሎ በነበረው መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን የመጻሕፍተ ሐዲሳ ትና መጻሕፍተ ቅዳሴ መምህር ሆኑ። መምህር ገሪማ በተመደቡበት የመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በትጋት ማስተማር ጀመሩ። ቀድሞ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ሲፈጽሙ ወደ ደብረ ሊባኖስ በሔዱ ጊዜ የተለዩአቸው ተማሪዎቻቸው ወደ አዲስ አበባ እንደ ተመለሱ ሲሰሙ ከየነበሩበት መሰባሰብ ጀመሩ። ይህን የመምህሩን የማስተማር ብቃትና ዕውቀት በቅርበት ሆነው ያዩት ግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ዓፄ ኃይለ ሥላሴም መምህር ገሪማን ከማስተማር ጋር ከጉባኤያቸው አልፎ ለሌሎች ጉባኤያትና ትውልድ የሚጠቅም ሥራን እንዲሠሩ አዘዟቸው። ይኸውም ለረጅም ዘመናት በቃል ሲተላለፍ የቆየውን መጽሐፈ ቅዳሴ ነጠላ ንባቡን ከነትር ጓሜው እንዲያዘጋጁ ነበር።

የንጉሡን ትእዛዝ በፍጹም እሺታ የተቀበሉት መምህር ገሪማም በታዘዙት መሠረት የመጽሐፈ ቅዳሴን ነጠላ ንባብ ከነትርጓሜው አዘጋጁ። በሊቁ የተደሰቱት ዓፄ ኃይለ ሥላሴም ከቤተ መንግሥታቸው መጽሐፉ የገንዘብ ካዝና ወጭ ሆኖ በ1918 ዓ.ም እንዲታተም አደረጉ። ይህ መጽሐፍ ዛሬ ድረስ በተለያዩ ጊዜያት እንደገና እየታተመ በማገልገል ላይ ይገኛል።

ከንጉሡ የተሠጣቸውን ሥራ ከመሥራት ጋር ወደ ጉባኤያቸው የመጡ በርካታ ተማሪዎችን በማስተማር ለአራት ዓመታት የቆዩት መምህር ገሪማ በ1921 ዓ.ም ተወልደው ሳደጉባት ግሸን ማርያም ገዳም መምህር ሆነው ተሳኩ። በዚያም ለስምንት ዓመታት ያህል በትጋት ሰያገለግሉ ቆዩ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ጳጳሳት የመሾም ነጻነት ተቀዳጅታ ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት የመጀመሪያው ሊቀ ጳጳስ ከመሆናቸው በፊት ቤተ ክርስቲያኗም ሆነች የሀገሪቱ መንግሥት በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ያሏትን ገዳማት የሚያስተዳድር አንድ የታወቀ አባት ወደ ዚያው ትልክ ነበር። ይህ አባትም ሐላፊነቱን ተቀብሎ ወደ ዚያው ሲላክ የሚሰጠው የሹመት ስም «ራእስ /ረኢስ/ » የሚባል ነበር።

ምንም እንኳን ቀደም ሲል በራእስነት ወደ ኢየሩሳሌም የተላኩትን ኢትዮጵያውያን የቤተ ክርስተያን አባቶች ስም ዝርዝር ለማግኘት ባይቻልም ከዓፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ

www.ethiopianorthodox.org

ወዲህ እስከ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ጵጵስና መሾም ድረስ በራእስነት ያገለገሉ አባቶች ስም ዝርዝር የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ. መ/ር ወልደ ሰማዕት

2ኛ. መ/ር ገብረ ኢየሱስ

3ኛ. መ/ር ፈቀደ

4ኛ. መ/ር ማኅፀንቱ

5ኛ. መ/ር ይርዳው

6ኛ. መ/ር ወልደ ሚካኤል /አቡነ ሚካኤል/

7ኛ. መ/ር ገብረ ኢየሱስ

በ1928 ዓ.ም በተደረገው የራእሶች ምርጫ መምህር ገሪማ ተመርጠው በዚያው ዓመት መስከረም 24 ቀን «መ/ር ገሪማ፣ በኢየሩሳሌም ላሉት ለአራቱ የኢትዮጵያ ገዳማት ራእስ» ተብለው በመሾም ወደ ዚያው ተላኩ።

መምህር ገሪማ የተሰጣቸውን ሐላፊነት ይዘው ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ሔደው ብዙም ሳይቆይ ፋሺስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን ወረረ። ይህን የግፍ ዜና ኢየሩሳሌም ሆነው የሰሙት መምህር ገሪማ ወደ ሀገራቸው መመለስ ባይችሉም ከሌሎች በዚያ ከሚኖሩ ማኅበረ መነኰሳት ጋር በመተባበር የርቀት ትግላቸውን ቀጠሉ። ከጦርነቱ ሸሽተው ወደ ኢየሩሳሌም የተሰደዱትን ኢትዮጵያውያን በመቀበልና በማስተናገድ፤ የኢትዮጵያን በግፍ መወረርም ለአካባቢው መንግሥታት በማስማትና በሌሎች መንገዶች ሁሉ ትግላቸውን ያፋፍሙ ጀመር።

ፋሺስት በወረራው ዘመን በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ይውለበለቡ የነበሩት የኢትዮጵያ ባንዲራዎች ወርደው በኢጣሊያ ባንዲራዎች እንዲተኩ እንዳደረገ ሁሉ፤ ይህ ተግባሩ ዓለም ዐቀፋዊ መልክ ይዞ በኢየሩሳሌም ገዳማት ይውለበለቡ የነበሩት የኢትዮጵያ ባንዲራዎች ወርደው በኢጣሊያ ባንዲራዎች እንዲተኩ አድርጎ ነበር። ይህንን ከልክ ያለፈ የግፍ ተግባር በዓይናቸው ያዩት መምህር ገሪማ በቆራጥነት የኢጣልያንን ባንዲራ አውርደው በማቃጠል በቦታው የሀገራቸውን ባንዲራ ሰቅለዋል።

ከመራራ የአምስት ዓመት ትግል በኋላ የኢትዮጵያ ነጻነት በ1933 ዓ.ም ሲመለስ መምህር ገሪማም ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው በመስከረም ወር 1937 ዓ.ም. መጡ። በመጡ በዓመታቸውም ታኅሣሥ 16 ቀን 1937 ዓ.ም እንደ ገና በትውልድ ቦታቸው ግሸን



ማርያም ተሹመው ወደ ዚያው ሔዱ። በዚያም ሆነው ገዳማቸውን በመልካም አባትነት ጥቂት እንዳስተዳደሩ ሚያዝያ 19 ቀን 1938 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ በተደረገው የጳጳሳት ምርጫ ለጵጵስና ተመረጡ። ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም ከሌሎች አባቶች ጋር ወደ ግብፅ ካይሮ ሔደው በወቅቱ የአስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ከነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ 2ኛ አንብሮተ እድ መዓርገ ጵጵስናን ተቀብለው «አባ ሚካኤል ጳጳስ ዘጎንደር» ተብለው በቤጌምድርና ስሜን ሀገረ ስብከት ተሾሙ።

ብፁዕነታቸው ሹመቱን በአኰቴት ተቀብለው ወደ ሀገረ ስብከታቸው በመሔድ የተቀበሉትን ታላቅ ሐላፊነት ሲወጡ ቆዩ። ቃለ እግዚአብሔር ለተራበው ምግበ ነፍሱን፣ ምግበ ሥጋን ለሚሻው ደግሞ ከምግበ ነፍሱ ጋር ምግበ ሥጋውን ከግል ኪሳቸው እያወጡ ሲመግቡ ቆይተዋል። የሀገረ ስብከታቸውን ሕዝብ ቀድሞ ከተማረኑታቸው ጀምሮ የሚያውቁት በመሆኑ ጥናትና የመግባቢያ ጊዜ ሳያስፈልጋቸው የሚያውቁትን ጋራና ወንዝ በማቋረጥ ሕዝቡን አስተምረዋል፤ ገዳማትን፣ አድባራትንና አብነት ት/ቤቶችን አጠናክረዋል።

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ምንም እንኳን ሀገረ ስብከታቸው በጌምድር ቢሆንም በየዓመቱ መስከረም 21 ቀን ተወልደው ባደጉባት ግሼን ደብረ ከርቤ እየተገኙ በዓለ እግዝእትነ ማርያምን ማክበር ልማዳቸው ነበር። በዚህም መሠረት በ1952 ዓ.ም መስከረም ወር እንደተለመደው የእመቤታችንን በዓል ለማክበር ወደ ግሸን ሄዱ። በዓሉንም በሰላም አከበሩ። ነገር ግን የአሳቸው ሐሳብ ወደ ሀገረ ስብከታቸው መመለስ ቢሆንም ሳያስቡት ባደረባቸው ሕመም ለጥቂት ቀናት ከሰነበቱ በኋላ ጥቅምት 4 ቀን 1952 ዓ.ም በተወለዱ በ74 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

ዜና ዕረፍታቸው እንደ ተሰማም ብፁዕ አቡነ ገብርኤል በወቅቱ የወሎ ሊቀ ጳጳስ ከደሴ፣ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ፣ ብፁዕ አቡነ ያዕቆብና ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ከአዲስ አበባ ገሥግሠው በተገኙበት ሥርዓተ ቀብራቸው በዚያው በግሼን ደብረ ከርቤ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል። ዕረፍታቸውን በማስመልከትም ጥቅምት 7 ቀን 1952 ዓ.ም. ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ግርማዊት እቴጌ መነን እንዲሁም ንጉሣውያን ቤተ ሰቦች በተገኙበት በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በመገኘት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መሪነት በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ካህናትና የደብር አስተዳዳሪዎች ጸሎተ ፍትሐት ተደርጎላቸዋል። ከሥርዓተ ፍትሐቱና ቅዳሴው በኋላም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ስለ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል

www.ethiopianorthodox.org

ማንነት ሰፋ ያለ ንግግርና የኃዘን መግለጫ አሰምተው የጸሎተ ፍትሐት ፍጻሜ ሆኗል፡፡

የብፁዕነታቸውን አገልግሎት በተለይ ጣሊያን ሀገራችንን በግፍ በወረረ ጊዜ ያደረጉትን የአርበኝነት ሥራ ትውልድ ሲያዘ ክረው ይኖር ዘንድም በንጉሠ ነገሥቱ፣ በግርማዊት እቴጌ መነን፣ በንጉሠውያን ቤተ ሰብና በአምስቱ የመከራ ዘመናት የስደት ተካፋዮቻቸው በነበሩት ኢትዮጵያውያን የገንዘብ ርዳታ በመንበረ ፀባዮት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቅጽር ግቢ የመታሰቢያ ሐውልት ቆሞላቸዋል፡፡ ይኸው ሐውልት ዛሬም በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽረ ግቢ ቆሞ ይገኛል፡፡ የብፁዕነታቸው ረድኤት ከሁላችን ጋር ይሁን፡፡ አሜን፡፡



## 3.12. ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ቀዳማይ ሊቀ ጳጳስ

## /1888 - 1980 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

በስመ ጵጵስናቸው « አባ ያዕቆብ » ተብለው ከመጠራታቸው በፊት አባ ዘፈረ ብርሃን ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ታኅሣሥ 8 ቀን 1888 ዓ.ም በቀድሞው የሸዋ ጠቅላይ ግዛት፣ በሰላሌ አውራጃ፣ በእንሳሮ ወረዳ ልዩ ስሙ ሳላይሽ ኪዳነ ምሕረት በሚባለው ቦታ ተወለዱ። አባታቸው ባሻ ገብረ ጻድቅ ህብተ ማርያም፣ እናታቸው ወ/ሮ በየነች ወንድም ተገኝ ይባሉ ነበር።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው ከርስትና በተነሡበት ደብር ያስተምሩ ከነበሩት መምህር ገብረ ሕይወት ዘንድ ፊደል ቆጥረው ዳዊት ደገሙ። ትምህርታቸውን በመቀጠልም አለቃ ብርሃኑና መሪ ጌታ ዐጽመ ጊዮርጊስ ከተባሉ መምህራን ጸዋትወ ዜማን፣ ወደ ጎንደር በመሻገርም በጎንደር ማኅደረ ማርያም ስመ ጥር ከነበሩት ከመሪ ጌታ ወርቁ ዘንድ ድጓን፣ ጾመ ድጓንና ምዕራፍን ተምረው አስመሰከሩ።

ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ በትጋት ተምረው ለመምህርነት የሚያበቃ ዕውቀት ቢጨብጡም በቃኝ አላሉም። ለቀጣዩ ትምህርት ጎንደርን ለቀው ወደ ወሎ ተሻገሩ። በወሎ ክፍለ ሀገር፣ በላስታ አውራጃ፣ በቡግና ወረዳ ብርኳኳ ማርያም በምትባለው ደብር ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት ከመምህር ጽጌና መምህር መንበሩ ቅኔ ከነ ዕርባ ቅምሩ ተምረው ለመምህርነት ተመረቁ።

ቅኔን ተምረው በተመረቁባት በዚያችው ደብር ቅኔ እያስተማሩ የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ ከመምህር ኪዳነ ማርያም ጠንቅቀው አሔዱ።

ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር እንዳ መለከታቸው በትግራይ ክፍለ ሀገር እንደርታ አውራጃ ወደ ሚገኘው ማይ ወይኒ ቅዱስ ሚካኤል ገዳም ሔዱ። በዚያም ሥርዓተ ገዳምን እያጠኑ፤ በተጓዳኝ ቅኔን ከነአገባቡ በማስተማር በዚህ ዓለም የተሰጣቸውን ዕድሜ በንጽሕናና በድንግልና ሲያሳልፉ ከአምስት ዓመታት አመክሮ በኋላ ወስነው በዚያው ገዳም ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጸሙ።

ወደ ትግራይ የሔዱበትን ዓላማ ከግብ ካደረሱ በኋላ አሁንም ትምህርታቸውን ለማስፋፋት እንደ ገና ወደ ወሎ ተመልሰው ዓምደ ወርቅ ቅዱስ ቂርቆስ ከተባለው ደብር ከአለቃ ካሣ ተክሌ አቋቋምን፣ ከመሪ ጌታ በሰጠ ደግሞ የጎንደርን አቋቋም አጥንተው በመምህርነት ተመረቁ።

ብፁዕነታቸው በዚያው ደብር ለስድስት ዓመታት ቅኔንና ዜማን ሲያስተምሩ ከቆዩ በኋላ ደቀ መዛሙርታቸውን በማስከተል



ወደ አዲስ አበባ መጥተው በጽርሐ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ዘርግተው ማስተማር ጀመሩ። በወቅቱ በአዲስ አበባ አሉ ከሚባሉ ጉባኤያት የብፁዕ አቡነ ያዕቆብ አንዱና ዋናው ነበር። ይሁን እንጂ አሁንም መማር ይበቃኛል አላሉም። የቀራቸውን የሐዲሳት ትርጓሜ ለማስተካከል በወቅቱ አዲስ ዓለም ላይ ሰፊ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ወደ ነበሩት ሐዲስ ተክሌ /በኋላ አቡነ ዮሐንስ/ ደቀ መዛሙርታቸውን አስከትለው ሔዱ። በዚያም ለስድስት ዓመታት ያህል ሐዲሳትን እየተማሩ አስተማሩ።

በዚህ ዓይነት ሁሉንም መንፈሳዊ ትምህርት በብቃት ያጠናቀቁት ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ከማስተማር ጋር የማስተዳደር ሐላፊነት እየተሰጣቸው በርከት ላሉ ዓመታት አገልግለዋል። በአለቅነትና በመምህርነት ካስተዳደሯቸው ታላላቅ አድባራትና ገዳማት ውስጥ የመናገሻ ቅድስት ማርያም ገዳም፣ የበላ ድንጋይ ቅዱስ ማርቆስ ደብር፣ የፍርኩታ ኪዳነ ምሕረት ደብር፣ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ይጠቀሳሉ። በእነዚህ ገዳማትና አድባራት ሁሉ በብቃት ከማስ ተዳደር ጋር ወንበራቸው የታጠፈበት ጊዜ አልነበረም።

ጠላት ሀገራችንን በወረረ ጊዜም ኢትዮጵያውያን ለእናት ሀገራቸው ልባቸውንና ይሁንታቸውን ለጠላት እንዳይሰጡ፣ በቆራጥነትም የሰማዕትነት ተጋድሎ እንዲያደርጉ፣ በእናት ሀገራቸው ፍቅርም ልባቸው እንዲሞቅ ያደርጉ ነበር። በጠላት የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናትንም ሕዝቡን በማስተባበር ያድሱና እንደ አዲስ ያሠሩ ነበር።

ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ በስተ መጨረሻም በዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም በአበ ምኔትነት ተሹመው ሳለ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ያገኙትን ኢትዮጵያውያን አባቶቻቸውን ለጵጵስና የመምረጥ ነጻነት ተጠቅመው ለመዓርጉ የሚበቁ አባቶችን በመረጡ ጊዜ ብፁዕነታቸው አንዱ ሆነው ተመረጡ። ወደ እስክንድርያ በመሔድም ሢመተ ጵጵስና ተቀበሉ።

ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ መዓርጉን ከተቀበሉ በኋላ በተሰጣቸው በኢሉባቦር አህጉረ ስብከት ለሁለት ዓመታት ሲቆዩ በአካባቢው ወንጌል በስፋት እንዲሰበክ፣ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነፁ አድርገዋል። በመጨረሻም ኢሉባቦር ሀገር ስብከት ተቀንሶላቸው የወለጋን ሀገረ ስብከት ለ31 ዓመታት በብቃት መርተዋል፣ አስተምረዋል። በየወረዳዎቹና አውራጃዎቹ በመዘዋወር ከሁለት መቶ በላይ አብያተ ክርስቲያናትን አሠርተዋል። ለእያንዳንዱም ንዋያተ ቅድሳት እንዲሟሉ አድርገዋል። ምእመናኑም ለቀና ሃይማኖትና በንጹሕ ምግባር ጸንተው ሀገራቸውን እንዲጠብቁ ያልተቋረጠ ጥረት

www.ethiopianorthodox.org

ሲያደርጉ ኑረዋል። ለካህናትና መምህራንም ትርጓሜ መጻሕፍትንና ቅኔን ሲያስተምሩ ቆይተዋል።

ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ አንድ የተለየ ጸጋ ነበራቸው። ይኸውም እብዝቶ የመጸለየ፣ የመስገድ እንዲሁም የመጾም ጸጋ ነው። በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ሌሊት አልጋ ላይ ተኝተው አያውቁም ነበር። ማረፊያ ክፍላቸው ውስጥ አንዲት ደረቅ የእንጨት ወንበር ነበረቻቸው ይባላል። ብፁዕነታቸው በዚያች ወንበር ተቀምጠው ሲጸልዩ እንቅልፋቸው ከመጣም እዚያው እንደ ተቀመጡ ያሸልቡ ነበር። በሕይወት በነበሩ ጊዜ እንደ ተናገሩት ከዕለታት አንድ ቀን በእንቅልፍና በመንቃት መካከል እንዳሉ ጥንተ ጠላት ሠይጣን ይጠ ጋና ወደ አንገቴቸው አካባቢ ነካ ያደርጋቸዋል። በዚህ ጊዜ ይነቁና መስቀላቸውን ይዘው «እኔ የክርስቶስ ባሪያ፤ እንዴት ትቀርበኛለህ አንተ?» ብለው በመገሰጽ ከእላቸው ያርቁታል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሠይጣኑ የነካቸው አፋቸው አካባቢ በመጠኑ ጠመም ብሎ፣ ከፊት ጥርሶቻቸውም አንዱ ወጣ ብሎ እስከ ሚያርፉ ድረስ ይነቃነቅ ነበር ይባላል።

ብፁዕነታቸው በዐውደ ምሕረት ቆመው ሲያስተምሩ ምሥጢ ር ዐዋቂ ነበሩ ይባላል። በዚህ ሊቅነታቸው የተነሣ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስሙነ ሕማማቱ የተቀበለውን ዐዋትወ መከራ የሚያዘክረው መጽሐፍ ከብሉያቱ፣ ከሐዲሳቱ፣ ከድርሳናቱና፣ ከገድላቱ ወዘተ. ተውጣጥቶ እንዲዘጋጅ ሲደረግ የማስተጋባቱንና የማቀናጀቱን ህቢይ ሥራ የወሰዱት እሳቸው ነበሩ ይባላል።

ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ተወልደው ባደጉበት አካባቢ ለሚገኘው ደብረ ፍሥሐ ሸንኩርት ሚካኤል ደብር ሲሾሙ ከጃንሆይ የተሸለሙትን ከብርና ከወርቅ የተሠራ መስቀል ሰጥተው ነበር ይባላል። ይህንንም ያደረጉበት ምክንያት ቦታው የደብረ ሊባኖስን መነኮሳት ወራሪው የኢጣልያ ጦር የጨፈጨፈበት ቦታ በመሆኑ ለስማዕታቱ መታሰቢያ እንዲሆናቸው በማሰብ ነበር። ይህ መስቀል ዘራፊዎች በ1994 ዓ.ም ጠባቂውን አርደው ገድለው ደብሩን በዘረፉ ጊዜ የተዘረፈው መስቀል በፖሊስ ክትትል ተመልሷል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸውን ከዲቁና ጀምሮ እስከ ሊቀ ጵጵስና ድረስ ለረጅም ዘመናት ካገለገሉ በኋላ ዕድሜ እየለገሳቸው፣ ዐቅማቸው እየቀነሰ በመሔዱ ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ ከአስተዳደር ሥራ ተለይተው ዳዊት እየደገሙ በጸሎት ተወስነው እንዲኖሩ ሆኑ። በመሆኑም በ92 ዓመት ዕድሜያቸው እስካረፉበት ጊዜ ድረስ ለሀገራችን ሰላምና ለሕዝቧም ደኅንነት በመዓልትና በሌሊት በጾም፣ በጸሎትና በስጊድ ተወስነው ፈጣሪያቸውን በመለመን ቤተ



ክርስቲያንን በማገልገል፣ ሥልጣነ ክህነትን በመስጠት ቆይተዋል።

ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ከላይ በመጠኑ በተገለጠው ዓይነት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸውን ሲያገለግሉ ቆይተው ጥቅምት 24 ቀን 1980 ዓ.ም በዚያው በመንበረ ጵጵስናቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

የብፁዕነታቸው አስከሬን በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ በአድባ ራት አስተዳዳሪዎች፣ በሊቃውንቱና በካህናቱ እንዲሁም በሀገረ ስብከቱ ሠራተኞችና በአውራጃዎቹ ሊቃነ ካህናት፣ በነቀምቴ ከተማ ነዋሪ ሕዝብ፣ በእምስቱ አድባራት ሰንበት ት/ቤቶችና መዘምራን ታጅቦ በነቀምቴ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ህርፏል። በሥርዓተ ቀብሩ ላይ ከታበረከቱት ቅኔዎች መካከል የሚከተለው ይገኝበታል።

*ለትምክሕተ ኵሉ ያዕቆብ ኢይደልዎ ማኀደር*

*እንዘ በቀለ ፀር ቃየል ኢይዜክር*

*አምጣነ ድኅሪተ ገደፈነ ለዉለደ እሙ ምሥጢር*

*ሙሴኒ ወአልዓዛር*

*አመ ጸውዕዎ ይርአይ ኅዕኅዌ ብሔረ ካህናት አብትር*

*ተጽዕነ ሠረገላ ዕዝራ ወኤልያስ ኄር*

*ካህናተ ሰማይ ርእዩ መዐርጊሁ*

*ለሞተ ፍጡራን በኵር*

*ዘፈረ ብርሃን ረስየ አኮኑ ፈቃረ ሥልጣኑ ዘክብር*

*ጥበበ ሥላሴሰ ዓምደ ፍቅር*

*ለቀበላሁ ቀደመ እንዘ ይሴወር*

*ፍናዊሃ ለዘኤዶም ምድር።*

ለብፁዕነታቸው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በኑዛዜያቸው መሠረት ሀገረ ስብከቱ መጻሕፍታቸውን፣ አልባሳታቸውን፣ በየጊዜው የተሸለሚቸውንና ሌሎች የግል ዕቃዎቻቸውን በማሰባሰብ በነቀምቴ ከተማ አንድ መለስተኛ ሙዝየም ተሠርቶላቸው በክብር ተቀምጠ ዋል። የብፁዕነታቸው በረከት ይደርብን። አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

# 3.13. ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ቀዳማይ ሊቀ ጳጳስ

## /1889 - 1970 ዓ.ም/





የቀድሞ ስማቸው መምህር ጌታሁን ወልደ ሐዋርያት ነበር። ጥቅምት 7 ቀን 1889 ዓ.ም በቀድሞው የሸዋ ጠቅላይ ግዛት ቡልጋ ወረዳ መርፌታ ወለሴ ሚካኤል በሚባል ቦታ ተወለዱ። የአባታቸው ስም አቶ ወልደ ሐዋርያት ዓለምነህ፡ የእናታቸው ደግሞ እመት ወለተ ሐና አብዩ ሆይ ይባል ነበር።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ እዚያው ከወላጆቻቸው ቤት ሆነው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን /ዜማን/ ቀጥለውም ለደረጃው የሚበቃውን ያህል ዕውቀት ገበዩ። በወላጆቻቸው ቤት የጀመሩት ትምህርት በውሰጣቸው ፍቅርን ስላሳደረባቸው የቅኔ ትምህርት ለመማር ወደ ጐጃም ተሻገሩ።

ብቸና ቅዱስ ጊዮርጊስ ላይ ሰፊ ጉባኤ ዘርግተው የቤተ ክርስቲያን ተረካቢ የሆኑ ወጣት ሊቃውንትን ሲያፈሩ ወደ ነበሩት ዕውቁ የቅኔ ሊቅ መምህር ውብሸት ዘንድ ሔደው የቅኔ ዕውቀት ገበዩ። ከዚያም ዕውቀት በቃኝ፥ ወደ መካነ ትውልዴ ልመለስ ሳይሉ ወደ ቤጌምድር ተሻገረው ጋይንት ማኅበረ በኮር በተባለ ቦታ ከአለቃ ምሥራቅና ከአለቃ ዓምደ ብርሃን የቅኔ ትምህርታቸውን ካስፋፉ በኋላ የዜማውን ትምህርት እንደገና ጀመሩ።

በሚያስደንቅ ቅልጥፍና ጾመ ድጓ፣ ድጓና ምዕራፍ፣ ዝማሬና መዋሥዕት፣ ቅዳሴና አቋቋም ተምረው በዚሁ ትምህርት በመምህርነት ተመረቁ። ከዚያም በዚያው በቤጌምድር ውስጥ አንዳቤት በተባለ ቦታ ዘበየ ሚካኤል ደብር ለሰባት ዓመታት ያህል የተማሩትን ሲያስተምሩ ቆዩ። ከዚህ በኋላ የሕይወት አቅጣጫቸውን በመወሰን ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም መጥተው መዓርገ ምንኩስናን ተቀበሉ። ወዲያውኑም ከብፁዕ አቡነ አብርሃም ኢትዮጵያዊ መዓርገ ቅስናን ተቀበሉ።

እንደ ቅድሰት ቤተ ክርስቲያን ትእዛዝ ከላይ በተገለጠው ዓይነት ሥርዓተ ምንኵስናን ከፈጸሙ በኋላ ወደ ትውልድ ወረ ዳቸው ቡልጋ ሔደው ወለሴ ሚካኤል በሚባል ደብር ዜማ ማስተ ማር ጀመሩ። ለተወሰኑ ዓመታት በተጠቀሰው ቦታ ካስተማሩ በኋላ የካቲት 18 ቀን 1938 ዓ.ም የእቲሳ ተክለ ሃይማኖት ገዳም አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ። በዚያው ዓመት ሚያዝያ 19 ቀን አዲስ አበባ ላይ በተደረገው የጳጳሳት ምርጫ ለጵጵስና ተመረጡ። በዚህም ከሌሎች አባቶች ጋር ወደ እስክንድርያ በመሔድ ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም በወቅቱ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ከነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ መዓርገ ጵጵስናን ተቀበሉ።

ከዚያም «ጳጳስ ዘሲዳሞ» ተብለው ወደ መንበረ ጵጵስናቸው

www.ethiopianorthodox.org

ደርጋ ዓለም ሔዱ። ወደ ሀገረ ስብከታቸው ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነፅ፣ ምእመናንን በማስተማር፣ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ካህናትን እየሾሙ ሰፊ አገልግሎትን አበርክተዋል።

ብፁዕነታቸው ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ጋር በእጅጉ የጠበቀ ወዳጅነት ነበራቸው። እንዲያውም ግንኙነታቸውን በቅ ርብ የሚያውቁ ሰዎች እንደሚናገሩት ቅዱስ ፓትርያርኩ አንድ ሥራ ሊሠሩ ሲያስቡ ብፁዕነታቸውን ሳያማክሩ አይሠሩም ነበር ይላሉ። ብፁዕነታቸውም ሊሠሩ ያሰቡትን ለቅዱስነታቸው ሳያማክሩ አይጀም ሩትም ነበር ይባላል።

ብፁዕነታቸው የሰዎችን ሥነ ልቡና በቀላሉ የሚረዱ፣ ሰዎች ለምን እንደ እኔ አልሆኑም ብለው ሌላ ዓይነት አስተያየት የማይሰነዝሩ ነበሩ። አንድ ሰው በስሕተትም ሆነ ሆን ብሎ ጥፋት ቢሠራ ሰው መሆኑ ያመጣው ነው ብለው ከመምከር ያለፈ ሌላ ሰምም ሆነ አስተያየት አይሰጡትም ነበር ይባላል። ሰውን ከነድካሙ የሚቀበሉት እኒህ አባት ጸሎተኛ ነበሩ። ከሀገረ ስብከታቸው ደርጋ ዓለም ለጉባኤም ሆነ ለሌላ ጉዳይ ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ መንበረ ፓትርያርክ እስከ ሚደርሱ ድረስ ዓይናቸው ከመጽሐፍ እንደ በታቸውም ከጸሎት አይታቀብም ነበር። ይሁን እንጂ እሳቸው ቢጸልዩም ሾፌራቸውን በየቦታው «ዕረፍት አድርግ፣ ቁርስ፣ ምሳ፣ አድርግ» እያሉ ይከባከቡት ነበር። ምክንያቱም በእሳቸው አባባል «እሱ እንደሳቸው አይደለምና»።

ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር በሚመለከት ትውፊቱን እንደያዘ መሻሻል እንዲደረግበት ይጥሩ ነበር ይባላል። በተለይ የአብነት ት/ቤቶች ዘመናዊ መልክ ይዘው ተጠ ናክረው እንዲቀጥሉ አስተያየት ይሰጡና የቻሉትን ያደርጉ ነበር። በዚህ ረገድ በተወለዱበት አካባቢ በሚገኘው ወለሌ ሚካኤል ላይ መምህሩም ሆነ ተማሪዎች ለቀለባቸው ሳያስቡ እንዲማሩ ለሁለቱም ራሳቸው ቀለብ ሰፍረው ሁሉን በቀፍ አንድ መንፈሳዊ ት/ቤት አቋቁመው ነበር። ይህ ት/ቤት ቀደም ሲል ሀገረ በብከቱ የተመሠረ ተበትን ዓላማ ጠብቆ እንዲንቀሳቀስ ቢያደርግም በአሁኑ ወቅት ብዙም ትኩረት የተሰጠው አይመስልም።

ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ከዲቁና ጀምሮ ቅድስት ቤተ ክር ስቲያንን ለረጅም ዘመናት ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት ሲታከሙ ቆይተው በ81 ዕድሜያቸው የካቲት 15 ቀን 1970 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። የቀብራቸው ሥነ ሥርዓትም በሀገረ ስብከታቸው በደርጋ ዓለም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በወቅቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን



ፓትርያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና የጠቅላይ ቤተ ክህነት የመምሪያ ሐላፊዎች በተገኙበት ተፈጽሟል። የብፁዕነታቸው በረከት በሁላችን ላይ ይደርብን። አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

# 3.14. ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ቀዳማዊ ሊቀ ጳጳስ

## /1888 - 1957 ዓ.ም/

የቀድሞ ስማቸው መምህር ሐረገ ወይን ይባል ነበር:: ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ የተወለዱት በቀድሞው ወሎ ጠቅላይ ግዛት፣ የጁ አውራጃ፣ ገነተ ልዑል ማርያም በተባለው ቦታ ሲሆን ከእስልምና እምነት ተከታይ ቤተሰቦች እንደተገኙ ይነገራል:: ዕድሜያቸው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ በተወለዱበት አገር ከፈደል እስከ ዳዊት ተማሩ:: ከዚያም ወደ ቤጌምድር በመሻገር አዛውር ኪዳነ ምሕረት ተብሎ በሚታወቀው ቦታ ጸዋትወ ዜማ ተማሩ:: ብፁስነታቸው አሁንም እዚያው ጎንደር መርጦ ኢየሱስ ወደ ተባለው ቦታ ሔደው ጸበላት ማርያም ተብሎ በሚታወቀው ቦታ ቅኔ ተማሩ:: ቀጥሎም ወደ ደብረ ታቦር ሔደው ከሐዲስ ተክሌ /በኋላ አቡነ ዮሐንስ/ ሐዲሳትን፣ ፍትሐ ነገሥት፣ አቡሻህርን /የቁጥር መጽሐፍ/ ተማሩ:: ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ አሁንም ትምህርት ነገር በቃኝ ሳይሉ ጎሩይ ጊዮርጊስ ወደ ተባለ ቦታ ሔደው ከብሉይ ተክሌ ብሉያትን በሚገባ አሔዱ:: ከዚህ በኋላም እንደ ገና ወደ ሐዲስ ተክሌ ተመልሰው ፍትሐ ነገሥትንና አቡሻህሩን አጠናቀው ዐወቁ::

በ1920 ዓ.ም ሐዲስ ተክሌ ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ አብረዋቸው መጥተው በመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ እያስተማሩ ጥቂት ጊዜ ከቆዩ በኋላ በግርማዊት እቴጌ መነን መልካም ፈቃድ ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው በኢየሩሳሌም በሚገኘው ገዳም በረድእነትና በመጋቢነት ሲያገለግሉ ቆዩ:: በመጨረሻም የብፁዕነታቸው የአገልግሎት ትጋትና እሺ ባይነት በቤተ መንግሥቱ በመሰማቱ እዚያው ባሉበት ራእስ ተብለው፣ የገዳሙ አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ::

ብፁዕነታቸው ሹመቱን በጸጋ ተቀብለው ከማኅበረ መነኮሳቱ ጋር በመስማማት በትጋት እያገለገሉ ሳሉ ኢትዮጵያ በወራሪው የኢጣሊያ ፋሽስት ተወረረች:: በዚህ ጊዜ ከሌሎች መነኮሳት ጋር በመሆን በሀገር ፍቅር ተቃጥለው በተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ኢትዮጵያ በግፍ መወረሯን ለዓለም ሕዝብ ሲያሰሙ በጸሎት ሀገራቸውን ሲረዱ ቆዩ::

ከአምስት ዓመታት መራራ ትግል በኋላ ብፁዕ አቡነ ታዴ



ዎስ አገልግሎታቸውን ቀጥለው ማኅበሩንና ገዳሙን በደንብ ሲረዱና ሲያገለግሉ ቆዩ:: ከዚህ በኋላም ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ተጠሩ:: በዚሁም በተደረገው የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ በከፍተኛ ድምፅ ተመርጠው በ1943 ዓ.ም ነሐሴ 27 ቀን በብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ አንብሮተ እድ ብፁዕ አባ ታዴዎስ ተብለው የጎሬ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ሆነው ተሾሙ::

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ቤተ ክርስቲያን የጣለችባቸውን ሐላፊነት ይዘው ወደ ሀገረ ስብከታቸው ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ ከማኅበረ ካህናቱና ምእመናኑ ጋር በመስማማት ሰፋ ያለ አገልግሎት አበርክተዋል:: ብፁዕነታቸው ቃለ እግዚአብሔር በሀገረ ስብከቱ እንዲዳረስ ከማድረጋቸው በተጨማሪ በልማት ሥራ በመሳተፍ ቤተ ክርስቲያን በአካባቢው የልማት አርአያ እንድትሆን ያደርጉ እንደ ነበር በቅርብ የሚያውቋቸው ይመሰክራሉ:: በተለይ ካህናት እየሠሩ ምእመናኑን እንዲያሠሩ ይመክሩና ያስተምሩ ነበር ይባላል:: ራሳቸውም በመንበረ ጵጵስናቸው ጓሮ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በማከናወን የልማት ሥራዎች ቀጥተኛ ተሳታፊ እንደ ነበሩ ይነገራል:: የብፁዕነታቸው ሥራ ወዳድነት ሲነሣ አንድ የሚነገር ታሪክ አላቸው::

እሳቸው የጎሬ ሀገረ ስብከት ጳጳስ በመሆን ሲያገለግሉ የጠቅላይ ግዛቱ ገዥ ደጃዝማች ገረሱ ነበሩ:: ታዲያ እኒህ ደጃዝማች ብፁዕነታቸውን ያከብሯቸውና በየጊዜውም ከመንበረ ጵጵስናቸው ድረስ በመሔድ ይጠይቋቸው ነበር ይባላል:: አንድ ቀን በማይጠበቅ ሰዓት ደጃዝማች ገረሱ አጀቢ ሳያበዙ ብፁዕነታቸው ግቢ ይደርሳሉ:: ወደ ግቢው ዘልቀው ቤት ውስጥ ቢያስጠሯቸው አቡነ ታዴዎስ የሉም:: ደጃዝማቹ ተመልሰው ከግቢው ሊወጡ ሲሉ አንድ መነኩሴ ጓሮ ውስጥ ሲቆፍሩ ያያሉ:: ደጃዝማች ገረሱ ወደ መነኩሴው ይቀርቡና «አባ! ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ወደ ዬት ሔዱ?» ብለው ይጠይቃሉ:: መነኩሴውም ለደጃዝማቹ ሰላምታ ይሰጡና «ወደ ጸሎት ቤት ይኖራሉ፤ ቆይ ልጥራቸው» ይሉና ገብተው እጃቸውን አረጋግ ፈው ወንበራቸው ላይ ይቀመጡና «ሒዱ ግቡ ይላሉ ብሏቸው» ብለው ሰው ልከው ደጃዝማቹ እንዲገቡ ያደርጋሉ:: ደጃዝማች ገረሱ ከቤት ሲገቡ ተራ መነኩሴ መስለው ሲቆፍሩ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ መስቀል ያሳልሟቸውና እንዲቀመጡ ይጋብዟቸዋል:: ደጃዝማች ግን ሲቆፍሩ ያዩአቸው ብፁዕነታቸው መሆናቸውን ስለ ተረዱ «ምነው አባታችን ካልጠፋ አሽከር እስዎ ይቆፍራሉ?» ብለው ማዘናቸውን ቢገልጹላቸውም ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ «እኔን የሚመስል መነኩሴ አለ:: እሱ እንጂ እኔ አልነበርኩም የምቆፍረው» ብለው ለማስተባበል ቢሞክሩም ደጃዝማች ባለመቀበል «እርስዎ ሲቆፍሩ አንዱ ቢገድልዎ በገረሱ ግዛት ተገደሉ

www.ethiopianorthodox.org

ያስብሉብኝ?» ብለው የሚጠብቃቸው ወታደር መደቡላቸው ይባላል።

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ከዚሁ ከሥራ ጋር በተያያዘም ሌላ የሚነገር አንድ ታሪክ አላቸው። ከላይ በተገለጸው ዓይነት ኀሮአቸውን አልምተው ምርቱን በመሸጥ ለአደኩባት ደብር ቤተ ክርስቲያን ማሠሪያ ይሆነኛል ብለው ያጠራቀሙትን 7000 ብር ይዘው በእውሮፕላን ከጎሬ ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ አንድ በወቅቱ የታወቀና ሸዌ ከለቻ የተባለ ሌባ ቀስ ብሎ ኪሳቸውን ቀዶ ይወስድባቸዋል። በዚህ በእጅጉ አዝነው «እኔ ቤቷን እሠራለሁ ብዬ ያጠራቀምኩትን ለቀማኛ ከሰጠችብኝ እህልም ውሃም አልቀምስ፤ ብሞት ይሻለኛል» ብለው ነበር ይባላል። በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ቢማልዷቸውም እንቢ በማለታቸው ጉዳዩ ንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ደርሶ ንጉሡም «እኔ የጠፋውን ገንዘብ ልስጥዎና ያሰቡትን ቤተ ክርስቲያን ያሠሩ» ብለው ቢማልዷቸውም «አልፈልግም፤ እኔ የደከምኩበት ገንዘቤ ከጠፋ ሌላው የደከመበት ምን ያደርግልኛል?» ብለው በውሳኔያቸው ጸኑ። ንጉሠ ነገሥቱም ያ የታወቀ ሌባ ገንዘባቸውን እንደወሰደ ስለደረሱበት ሌባው እንደ ተቋጠረ እንዲያመጣ አስደርገው ያችው እሳቸው ያሠሩባት ከረጢትና ብሩ መሆኑን ሲመለከቱ ተደስተው እኽልም ውኃም ቀመሱ፣ ያሰቧትን የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን የጁ ላይ እሠሩ ይባላል።

ብፁዕነታቸው በተሰጣቸው ሀገረ ስብከት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የጣለችባቸውን አደራ በትጋት ሲወጡ ከቆዩ በኋላ በሽታ እየጠቃቸው፣ ዐቅማቸው እየደከመ ሲመጣ ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ሔደው በምናኔ ተቀመጡ።

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ በ1953 ዓ.ም በየካቲት ወር ከደብረ ሊባኖስ ተነሥተው ቀደም ሲል ከረድእነት እስከ ራእስነት ሲያገለግሉ ወደ ኖሩባት ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ሔደው እንደ አንድ ተራ መናኒ ሆነው በሚገባ ጸሎታቸውን እየጸለዩ ኖሩ። ከምናኔያቸውም ጽናት የተነሣ ጫማቸውን አውልቀው በእግራቸው ወደ ዴር ሡልጣን እየወጡ ወደ ኢየሩሳሌም እየወረዱ በጾምና በጸሎት ተወስነው ፈጣሪያቸውን ያገለግሉ ነበር። ሰው ሆኖ ከሞት የሚቀር የለምና ባደረባቸው የስኳር በሽታ በተወለዱ በ69 ዓመታቸው ታኅሣሥ 10 ቀን 1957 ዓ.ም ከቀኑ በ12 ሰዓት ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ሥርዓተ ቀብራቸውም በዚያው በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ተፈጽሟል። ዐጽማቸውን ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ካልእ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ሊቀ ጳጳስ በነበሩ ጊዜ ከቢታንያ የኢትዮጵያውያን የመቃብር ሥፍራ አስወጥተው በቢታንያ ምስካበ ቅዱሳን ተ/ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን በክብር እንዲያርፍ አድርገዋል። የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን። አሜን።



# 3.15. ብፁዕ አቡነ ማርቆስ ቀዳማይ ሊቀ ጳጳስ

/1877 - 1953 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

ቀድሞ መምህር ገብረ አምላክ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ማርቆስ በኤርትራ ጠቅላይ ግዛት በአካለ ጉዛይ አውራጃ ሰላሕ በተባለች መንደር ከአባታቸው ከአቶ ተስፋ እግዚእ ዘጊዮርጊስና ከእናታቸው ከወ/ሮ ወርቁ ኤልሣቤ በታኅሣሥ ወር 1877 ዓ.ም ተወለዱ:: ለድሜያቸው ለትምህርት ቢደርስ ወደ አቡነ ቡሩክ አምላክ ገዳም /መራጉዝ/ ገብተው ከፊደል እስከ ግብረ ዲቁና ተማሩ:: ብፁዕነታቸው የአንደኛ /ንባብ/ና ሁለተኛ /ዜማ/ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ቅኔን ለመማር ወደ መኻል ኢትዮጵያ ሊሔዱ ተነሡ:: ይሁን እንጂ ሐሳባቸውን በመቀየር ለረጅም ዓመታት ወዳገለገሉበትና ተጋድሎ ወደ ፈጸሙበት ደብረ ቢዘን ገዳም ሔዱ:: በዚያም ከገዳማውያኑ ጋር ተዋውቀው በተለ ማቸው አረጋውያንን የመርዳትና የመንከባከብ ጸጋ ማገልገል፤ ማኅበሩ ያዘዛቸውን ሁሉም መፈጸም ጀመሩ::

በዚህ ዓይነት ሳቅ ያለ አገልግሎታቸውን እየፈጸሙ ሥርዓተ ገዳምን በሚገባ ካጠኑ በኋላ ልክ ሃያ ዓመት ቢሆናቸው የገዳሙ አበምኔት በነበሩት መምህር ዓምደ ማርያም መዓርገ ምንኩስና ተፈጸመላቸው:: ይሁን እንጂ ብፁዕነታቸው ይመኙት የነበረውን መዓርገ ምንኩስና እስኪማ ቢቀበሉም የትምህርት ፍላጎታቸው ስላስገደዳቸው በእምላክ ፈቃድ ያስቡት ሁሉ ከተሳካ በኋላ እንደ ሚመለሱ ለማኅበረ መነኮሳቱ ቃል ገብተው ከደብረ ቢዘን ገዳም በመውጣት ወደ ትውልድ አካባቢያቸው አቡነ ቡሩክ እምላክ ገዳም ሔዱ:: በዚያም መምህር ተክለ ሃይማኖት ከተባሉ ሊቅ ዘንድ ቅኔን በሚገባ ተማሩ:: በዚያውም ዓዲ ኳላ ወደ ተባለው ቦታ ወርደው ቀድሞ ጀምረውት የነበረውን ጾዋትወ ዜማን ከመምህር ገ/ሕይወት ዘንድ ተማሩ::

ብፁዕነታቸው ትምህርታቸውን በመቀጠል በዚያው አካባቢ አሉ ወደ ተባሉ የመጻሕፍት መምህራን በመዘዋወር የመጻሕፍትን ምሥጢር በሚገባ ተማሩ:: በመጨረሻም በገቡት ቃል መሠረት ወደ ሚወዷቸው ማኅበረ መነኮሳት ደብረ ቢዘን ተመለሱ:: በዚያም ከመንፈስ ወንድሞቻቸው ጋር በተጋድሎ እየጸኑ በተለመደ ጸጋቸው በፍጹም ትሕትና ገዳሙን ማገልገል ጀመሩ:: የብፁዕነታቸውን ለውቀትን ከትሕትና ጋር አቀናጅቶ መያዝ የተመለከተው ማኅበረ መነኮሳትም የገዳሙ አፈ መምህር አድርጎ ሾማቸው:: በዚህ ሥልጣናቸው በርከት ላሉ ዓመታት ሲያገለግሉ ቆዩ::

ብፁዕ አቡነ ማርቆስ በዚህ ዓይነት በገዳሙ በማገልገል ላይ ሳሉ የቆብ አባታቸው መምህር ዓምደ ማርያም ተጋድሎአቸውንና አገልግሎታቸውን ሁሉ ፈጽመው ከዚህ ዓለም ወደ ማይታየው ዓለም አለፉ:: ከዚህ በኋላ በመምህሩ ወንበር ተተክቶ የሚያገለግል አባት



ከማኅበረ መነኮሳቱ ቢመረጥ ብፁዕ አቡነ ማርቆስ ክፍ ባለ ድምጽ የታላቁ ደብረ ቢዘን ገዳም አበ ምኔት ሆነው በጥር ወር 1923 ዓ.ም ተመረጡ::

ይህንን ታላቅ አደራ ከገዳማውያኑ ማኅበር የተቀበሉት ብፁዕነታቸው አገልግሎታቸውን በስፋት ማከናወን ጀመሩ:: ከማኅበረ መነኮሳቱ ጋር በቅርብ በመነጋገርና በመወያየት ስለ ገዳሙ ሁሉን በቀፍ ብልጥግና፣ በአካባቢው ቤተ ክርስቲያን የምትስፋፋበትን ሁኔታ እያቀዱ አገልግሎታቸውን በስፋት ቀጠሉ:: የገዳሙ አበምኔት ሆነው በቆዩባቸው ጥቂት ዓመታት ካበረከቷቸው አስተዋጽኦዎች ውስጥ የእስልምና እምነት በሚበዙባቸውና ቤተ ክርስቲያን ብዙም ባልተስፋፋችባቸው አካባቢዎች በርከት ያሉ አብያተ ክርስቲያናት እንዲቋቋሙ ማድረጋቸው ይጠቀሱላቸዋል::

ብፁዕነታቸው የገዳሙ አበምኔት ሆነው በተሾሙ በሰባተኛ ዓመታቸው ወራሪው የኢጣልያ ጦር አዲስ አበባ ላይ ባስለፈፈው ሀዋጅ መሠረት ኢትዮጵያውያኑ ሊቃውንት የራሳቸውን ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙ ሲደረግ ብፁዕነታቸው ተመርጠው ኅዳር 21 ቀን 1930 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ በብፁዕ አቡነ አብርሃም ሊቀ ጳጳሳት እንብሮተ እድ «አባ ማርቆስ የኤርትራና የትግራይ ክፍላተ ሀገር ጳጳስ» ተብለው ተሾሙ::

የሀገሪቷ ነጻነት ከተመለሰም በኋላ ኤርትራ በእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ሥር ሆና «ኤርትራ ለማን?» በሚል ፖለቲካዊ ውኅርንብር በሕዝቡ መካከል አለመግባባት ተከስቶ በነበረበት ጊዜ ሕዝቡ ከእናት ሀገሩ በሐሳብም በተግባርም እንዳይለይ በሰፊው ያስተምሩና ይመክሩ እንደ ነበር የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ:: «የኤርትራ ሕዝብ ሆይ አገሬ ኢትዮጵያ በል አትሳሳት ... ስንኳን እንተ ባለ አእምሮው የአርባ ቀን ሕፃን እንኳን እናቱንና አባቱን ያውቃል:: እንተማ የአርባና የሰማንያ ዓመት በዋቂ አይደለህምን?» እያሉ በስፋት ይሰብኩ የነበሩት ብፁዕነታቸው በአንድ ወቅት የአሜሪካ፣ የሩስያ፣ የእንግሊዝና የፈረንሳይ መንግሥታት የሕዝቡን ፍላጎት ለመስማት ወደ አስመራ እንደ ሚመጡ ሲሰማ «አቡነ ጴጥሮስ» ተብሎ ይጠራ በነበረው ሜዳ ላይ ሕዝቡን ሰብስበው «ሕዝቤ ሆይ ስማ ቁስሉን የደበቀ መድኃኒት አይገኝለትም እንደ ተባለው እነዚህ አራት ሐኪሞች መታመምህን በውቀው ሊፈውሱህ መጥተዋልና አሁን ቁስልህን አትደብቅ:: መድኃኒትህ ኢትዮጵያ ሀገሬ፡ እግዚአብሔር ፈጣሪዬ ነው ብለህ አስረዳቸው...» በማለት ሰፋ ያለ ትምህርት ሰጥተው ነበር ይባላል::

ብፁዕ አቡነ ማርቆስ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትዋሐድ ሕዝቡን ከማስተማርና ከመምከር ጋር ወደ እግዚአብሔርም ከሰንበ

www.ethiopianorthodox.org

ጋር ያመለክቱ እንደ ነበር የታሪክ መዛግብት ይመሰክራሉ። በዚህ ረገድ በወቅቱ ሕዝቡ ሁሉ እንዲያነበው በትግርኛ ቋንቋ የደረሱት ጸሎት የሚከተለው ነበር። ይህ ጸሎታቸው ፍሬ ሃይማኖት በተሰኘች የብፁዕ አቡነ ፊልጶስ መጽሐፍ ታትማለች።

*«እና ሰማይን ናይ ምድርን ጎይታ፣ እናይ ነገሥታት ንጉሥ፤ እናይ ኩሉ ዓለም ገዛኢ፤ እናይ ኩሉ እስትንፋስ ፈጣሪ፣ እን ኩሉ ፍጥረት እተናብርን እትሐልን አምላክ ነዛ ድንግል ዝኾነት ኢትዮጵያ ሀገርና ብቱ መወዳእታ ዘይብሉ ምሕረትካ ተዓረቐና። እንካብ ሠለስተ ሽሕ ዓመት ዚአክል ነአኻ ኡነተይና አምላክ ዘምለኽትን ዘሰገደትን ዝተገዝኤትን ኢያም፤ ንእኻ እትአምን ሀገር ኣብ ኢድ ጸላእቲ ኣይተእትዋ «ዘተወከለ ኪያከ አልቦ ዘተሐፍረ» /መከብብ/ ቅድም ሎሚ እውን መወዳእታ ብዘይብሉ ጥበብካን ፍልጠትካን ኢኻ እትሕልዋን እተናብራን ዝነበርካ እምበር እንካብ ክእለትናን ኃይልናን ኣይኮነን። ከም ናይ ቀደም ኪዳንካ ተኻየደና ድኻምነትናን ድንቀቁርናናን በይኑ ረኤ። ፍርሐትካን ቅዱስ ስምካን ምጽዋስ ግን ልምድናን ግብርናን እዩም በአኡጠሚትካ ራርኃልና ከንጸር ዘይንኽእል አርሁት ባዕዲ ኣይተሸከመና ባሕርያዊ ነፃነትና ምለሰልና ንስኻ ናይ ርትዒ ንጉሥ ኢኻም ነቱ ዘይገንዘቡ ዚደሊ ብኢዱ ሃዞ ንዓመጸይና አርሕቆ፣ ንትዕቢተይና አውድቆ፣ ንበዓል ትሕትና አጽድቆ፣ ንገበር ድሙስ መርቆ። ንስኻ ብገዛእ ኃይልካን ሥልጣንካን ምእንቲ ኃጢአት ሰብ ጸርፍን ግፍዕን ተቀቢልካ ኢኻም ንሕና ከአ ብገዛእ ሀገርና ብናይ ባዕድ አፍ ውርደትን ንዕቀትን ንቅበል ኣሎና እሞ ናብ ክብርን ናብ ናዕነትን ለውጠልና።*

*ለአምላኽና ናይ ይቅርታኻ ቃል አስምዓና ንሕና ሽሕኳ እንተበደልናካ ኣይከኸድ ናን ንአብን ንወልድን ንመንፈስ ቅዱስን ንአምንን ንሰግድን ኣሎና። «እምነ ማዕዱተ እፍላገ ኢተዮጵያ የመጽኡ ሊተ መስዋዕተ» እንካብ ማዕዶ ሩባ ናይ ኢትዮጵያ አምሃ የምጽኡለይ ቢልካ ብአፍ ነብይ ሶፎንያስ ትእዝዘና ኣሎኻም እንካብና ትሑታን ሕዝቢ መስዋዕቲ ክትቅበል ደስ እንካብ በለካ ናይ ምሉእ ኢትዮጵያ መስዋዕትን ጸሎትን ማኅሌትን ጾምን ምጽዋትን ንስሐን ምህልላን ነትረበልካ ኣሎናም ብብሩህ ገጽ ተቀበለልና።*

*ናይ ድኻ ጸሎት አብ ልዕል ደመና ወጺአ ናብ ልዑል አምላክ ትብጽሕ እዮ ንሱ ኪይ ሰምዓ ከአ እኳ ኣይትምለስን /ሲራ/። ናይ ትሑትን ንዑቅን ጸሎት ብታሕንስ ከም ትቅበል ኢየሱስ ወድካ አስተምሂሩና ኣሎ። ነዛ ኢትዮጵያ ሀገርና ብሕጋን ብሥርዓታን ብሐሩ ንጉሥ ተጠቅሊላ ነእኻ ልዑል ገዛኢ አምልኮን ሰግደትን ከም ትሀብ ግበራ ሥምረት ሐደ ሐድ ሀብና ትንአት አምላክናን ሀገርናን አኑሮረልና ፍቅሪ ብጻይ አብዚኁልና ንትሥና ምስ ሠራዊቱ*



*ሐልወልና ንመሬትና ጥልላትን ፍርያትን ሀባ ገንዘብና ሲሳይና አበርከልና።*

*እአምላክ ኢትዮጵያ እንካብ ጥንቲ ዝነበርካ ሎሚ እውን ዘሎካ ንወትሩ እውን እትነብርን እትነግሥን ንዘለዓለም ዓለም አሜን።»*

ብፁዕነታቸው ወራሪው የኢጣልያ ጦር ከሀገር ከወጣ በኋላ በወረራው ጊዜ የተሾሙት ብፁዓን አባቶች ከሥራቸው ታግደው ቆይተዋል። በዚህ ዓይነት ብፁዕነታቸው በ1943 ዓ.ም በተደረገው ሢመተ ኤጲስ ቆጶሳት ይቅረቡና ሹመትዎ እንደ ገና ተከልሶ በመንበረ ሥልጣንዎ ይቀመጡ ቢባሉ «የእኔ የቀደመ ሥልጣን ትክክለኛ ነው፤ ሕገ ወጥ አይደለም። የሾሙኝም ኢትዮጵ ያውያን ሊቃውንት መርጠው ያስቀመጧቸው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ናቸው። የማይደገመውን ክህነት ድገሙልኝ ብዬም አልቀርብም፤ አገልግሎቱ ይቅርብኝ» ብለው ነበር። ነገር ግን እሳቸው እንዲህ ቢሉም እንደ ሌሎቹ እንደ ገና ሳይሾሙ በነበራቸው ሹመት እንዲያገለግሉ ተብለው ሀገረ ስብከታቸው ተሰጧቸው እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው ድረስ ሲያገለግሉ ቆይተዋል።

ብፁዕ አቡነ ማርቆስ በሀገረ ስብከታቸው ቃለ እግዚአብሔር እንዲዳረስ፣ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነፁ፣ ገዳማት እንዲጠናከሩ ሲያደርጉ ከቆዩ በኋላ ኅዳር 7 ቀን 1953 ዓ.ም በደረሰባቸው ድንገተኛ የመኪና መገልበጥ አደጋ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። የመኪና አደጋ በደረሰባቸው ቦታ ከዚያ በፊት ያልነበረ ውሃ ፈልቆ ውሃው ማይ አቡን /የአቡን ውሃ/ ተብሎ ይጠራ እንደ ነበር ይተረካል።

ብፁዕነታቸው ካረፉበት ጊዜ ጀምሮ ለአንድ ብፁዓዊ አባት የሚገባው ጸሎተ ፍትሐት በመላው ሀገረቱ ከተደረገላቸው በኋላ ሥርዓተ ቀብራቸው ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ቀዳማይ፣ ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ቀዳማይ፣ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ካልአይ እና ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ቀዳማይ በተገኙበት በደብረ ቢዘን ገዳም ተፈጽሟል። የብፁዕነታቸው በረከት አይለየን። አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

# 3.16. ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ቀዳማዊ ሊቀ ጳጳስ

## /1889 - 1971 ዓ.ም/





መዓርገ ጵጵስናን ከመቀበላቸው በፊት አባ ተክለ ጊዮርጊስ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ገብርኤል በሰሜን ሸዋ፣ መርሐ ቤቴ አውራጃ፣ በላይ ቤት ወረዳ ውስጥ ልዩ ስሙ አምባ ወንዝ ከተባለው ቀበሌ ከአባታቸው ከመምህሬ ገብረ መስቀል ወልደ ማርያምና ከእናታቸው ከወ/ሮ አስካለ ደርጉ በ1889 ዓ.ም ተወለዱ።

ብፁዕነታቸው በወላጆቻቸው ቤት በሥነ ምግባር እየተኮተኮቱ ካደጉ በኋላ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በመርሐ ቤቴ አውራጃ በቆፍና ሚካኤል ደብር ከአለቃ ኃይሉ ዘንድ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በሚገባ አጠናቀቁ። በመቀጠልም ወደ ደብረ ሊባኖስ በመሔድ መምህር ገብረ ኢየሱስ ከተባሉ ጸዋትወ ዜማን ተማሩ። ከዚያም ለቀጣዩ ትምህርት ወደ ጎጃም ተሻግረው በታላቁ የመርጡለ ማርያም ደብር ሰፊ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት ከመምህር ተክለ ማርያም የቅኔን ትምህርት ከነአገባቡ አጠናቀው በመማር ተመረቁ።

ብፁዕ አቡነ ገብርኤል በመቀጠል ወደ ሸዋ ተመልሰው ወደ ታላቁ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ገቡ። ከገቡበት ጊዜም ጀምሮ ለሰባት ዓመታት በረድኤትነት ሲያገለግሉ ቆዩ። ከዚያም በቅዳሴ ተመድበው ለሰባት ዓመታት እንዳገለገሉ የብፁዕነታቸውን በጎ ትሩፋትና ሰፊ አገልግሎት የተረዳው የገዳሙ ማኅበር በገዳሙ በመስቀል አጣኝነት እንዲያገለግሉ መረጣቸው። የተሰጣቸውን ኃላፊነትም በአኩቴት ተቀብለው ለዘጠኝ ዓመታት በታማኝነት አገለገሉ። ከዚህ አገልግሎታቸውም ጎን ለጎን በትርፍ ሰዓታቸው አለቃ አምኃ ከተባሉ ሊቅ ሐዲሳትን አሒደዋል።

ብፁዕ አቡነ ገብርኤል በዚህ ዓይነት ገዳሙን ረዘም ላለ ጊዜ ካገለገሉ በኋላ በ1922 ዓ.ም የገዳሙ ጸባቴ በመሆን በማኅበረ መነኮሳቱ ሙሉ ድምፅ ተሾሙ። በዚህ ታላቅ ኃላፊነታቸውም ወራሪው የፋሺስት ኢጣልያ ጦር አገራችንን እስከ ወረረበት 1929 ዓ.ም ድረስ አስተዳደሩ። ብፁዕነታቸው በወረራው ወቅት የታላቁ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ንብረቶች እንዳይዘረፉ ስውር በሆነ ዋሻ ውስጥ አኑረው ለተተኪው ትውልድ እንዲቆዩ አድርገዋል።

ወራሪው የኢጣልያ ጦር የካቲት 16 ቀን 1929 ዓ.ም ብፁዕነታቸውን ሊይዝ ገዳሙን በከበበ ጊዜ በእግዚአብሔር አጋዥነት አምልጠው ወደ መርሐ ቤቴ በመሸገር ለኢትዮጵያ ነጻነት ከወራሪው ጦር ከሚታገሉት አርበኞች ጋር ተቀላቀሉ። በዚያም በቆራጥነት ከጠላት ጋር የሚታገለውን አርበኛ «ኃይልህን እንግ፤ ክንድህንም አጠናክር። እናት አገርህን ለወራሪ ጠላት አሳልፈህ እንዳትሰጥ በርታ፤ ታገል፤ ኃይል የእግዚአብሔር ነው» እያሉ ማትጋታቸውን ቀጠሉ። ይሁን እንጂ በዚህ የሀገር ፍቅር ወኔ በተሞላበት ሥራ እንደ

www.ethiopianorthodox.org

ተሰማሩ በጠላት ጦር ተያዙ:: ከዚያም ወደ አምቦ ተወስደው እስከ 1933 ዓ.ም ድረስ በግዞት ቆዩ::

በኢትዮጵያውያኑ አርበኞች ቆራጥ ተጋድሎ ወራሪው የኢጣልያ ፋሽስት ድል ተመትቶ ከአገር ሲወጣ ብፁዕነታቸው ወደ ደብረ ሊባኖስ ተመልሰው በጸባቴነት ሹመታቸው እስከ 1938 ዓ.ም ድረስ አስተዳደሩ:: ከዚያም በግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ወደ አዲስ አበባ መጥተው የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም አስተዳዳሪና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ የመንፈሳዊ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆነው እስከ 1943 ዓ.ም አገለገሉ::

ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ከዲቁና ጀምሮ በቅድስና ቤተ ክርስቲያንን ለረጅም ዘመናት ካገለገሉ በኋላ በ1943 ዓ.ም በነሐሴ ወር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስተያን በተደረገው የጳጳሳት ምርጫ በድምፅ ብልጫ ተመርጠው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ አንብሮተ ዕድ «ጳጳስ ዘወሎ» ተብለው ተሾሙ:: ከዚህ ታላቅ አደራ ጋር ወደ ወሎ የሔዱት ብፁዕነታቸው ከሔዱ ጀምሮ ረዘም ላለ ጊዜ ሰፊ አገልግሎትን ሲያበረክቱ ቆይተዋል::

ብፁዕ አቡነ ገብርኤል የመገሠጽና የመምከር ጠባይ ነበራቸው ይባላል:: በዚህም ሕግ በሀገሪቱ ይከበር፣ አባቶችም የሚገባቸውን ክብርና ሞገስ ይሰጣቸው ዘንድ ከጃንሆይ ጀምሮ እስከ ተራ ባለሥልጣናት ድረስ ይገሥጹ እንደ ነበር ይነገራል:: በተለይ በሀገረ ስብከታቸው ሥር ያገለግሉ የነበሩ ካህናት ለሕግ ለሥርዓት ተገዝተው አገልግሎታቸውን እንዲፈጽሙ ጠንከር ያለ መመሪያ ይሰጡ፤ በመመሪያ የማይሔደውን ከሥራው ያግዱና እስከ ማባረር ይደርሱ ነበር ይባላል::

ብፁዕነታቸው፤ ግብጻውያን አባቶች የተማረውን ካልተማረው ለመለየት የቋንቋ ችግር ስለ ነበረባቸው ሁሉንም እየሾሙ ለዘመናት ቤተ ክርስቲያኗ ሊቃውንት ካህናት እጥታ ቆይታለች ብለው ያምኑ ነበር ይባላል:: በዚህ የተነሣ ለአንድ ሰው ክህነት ሲሰጡ የሚገባውን ትምህርት በሚገባ መማሩን አረጋግጠውና ፈተና ፈትነው ነበር:: ብፁዕነታቸው በነበራቸው ሥርዓትን የማክበርና የማስከበር ጠባይ የተነሣ የትኛውም የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሲጣስ ካዩ ዝም አይሉም ነበር ይባላል:: በዚህ ረገድ ብፁዕ አቡነ ፊልጳስ ቀዳማዊ ባዘጋጁት መጽሐፍ ላይ የኑፋቄ አስተሳሰብ አለበት ተብሎ ጉዳዩ በቅዱስ ሲኖዶስ ሲታይ ብፁዕነታቸው ግንባር ቀደም ተቃዋሚ ነበሩ፤ በዚህም ብፁዕ አቡነ ፊልጳስን በአደባባይ ሳይቀር ይተቹ ነበር ይባላል::

ምንም እንኳን መገሥጽነታቸውና ተናጋሪነታቸው በይፋ ቢታወቅም በእሳቸው ንግግር ማንም ቂም በቀል አይዝም ነበር



ይባላል:: በስብሰባም ሆነ ሲያስተምሩ እውነቱን ከመናገር ወደ ኋላ አይሉም ነበር:: በሚያስተምሩበትም ጊዜ «እናንተ ዓለማዊ ተድላን ወዳችሁ ነው ንስሐ ገብታችሁ ሥጋ ወደሙን የማትቀበሉት» ብለው በይፋ ይገሥጹ ነበር:: ይህን ይበሉ እንጂ ማንም ክፉ ናቸው፣ አስቀይመ ውኛል ብሎ የሚናገርባቸውና የሚከሳቸው አልነበረም ይባላል::

ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን በእጅጉ ይወዱ እንደ ነበር የሚያውቋቸው ሁሉ ይመሰክራሉ:: በአንድ ነገር የተነሣ «ተክልዬን» ካሉ ወደ ኋላ አይሉም ነበር:: በአንጻሩ እሳቸው በአንድ ነገር እንዲስማሙ «በተክለ ሃይማኖት» ሲባሉ የአሰረኛ ያህል ይሸነፉ ነበር:: ብፁዕነታቸው ለጻድቁ ከነበራቸው ፍቅር የተነሣ ገድሉን ሳያስነብቡና ሳያነቡ ጸሀል አይቀምሱም ነበር:: በዓመታዊ በዓላቸውም ሰፊ ዝክር አድርገው ነዳያንን ያበሉ ነበር::

ብፁዕነታቸው በ1971 ዓ.ም ጡረታ ከወጡት ሊቃነ ጳጳሳት አንዱ ነበሩ:: ይሁን እንጂ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት በነበራቸው ቆራጥ አቋም ውሳኔውን አልቀበልም ብለው ነበር:: ነገር ግን የእንቢታቸውን መልስ ሳያውቁ ብዙም ሳይቆዩ ሀርፈዋል::

ብፁዕ አቡነ ገብርኤል በሀገረ ስብከታቸው በነበሩበት ጊዜ በትውልድ ቦታቸው እፍና /ዓለም ከተማ/ የእጋእዝተ ዓለም ሥላሴን ቤተ ክርስቲያን በራሳቸው ገንዘብ አሠርተው ከነ መተዳደሪያው ሰጥተው ነበር ይባላል::

በመጨረሻም ባደረባቸው ሕመም ምክንያት በሕክምና ሲረዱ ቆይተው በ83 ዓመታቸው ነሐሴ 15 ቀን 1971 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: ሥርዓተ ቀብራቸውም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና የገዳሙ ማኅበር በተገኙበት ረዘም ላለ ጊዜ ባገለገሉበት የደብረ ሊባኖስ ገዳም ተፈጽሟል:: የብፁዕነታቸው በረከት በሁላችን ላይ ይደር:: አሜን::

www.ethiopianorthodox.org

# 3.17. ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ቀዳማይ ሊቀ ጳጳስ

## /1872 - 1958 ዓ.ም/





አባ ገብረ ጊዮርጊስ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ከአባታቸው ከአቶ ናይዝጊ ንጉሤና ከእናታቸው ከወ/ሮ መስቀል ክብራ ደብረ ኤርትራ በኤርትራ ጠቅላይ ግዛት፣ በአካለ ጉዛይ አውራጃ በደቀ መሐሪ ወረዳ፣ ጉደይቲ በተባለው መንደር በ1872 ዓ.ም ተወለዱ። በቤተ ለቦቻቸው እንክብካቤ ካደጉ በኋላ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ አቡነ ብፁዕ አምላክ ተብሎ በሚታወቀው ጥንታዊ ገዳም ሲማሩ አደጉ። በተወለዱ በ19 ዓመት ዕድሜያቸው የትምህርት ብቃታቸውና ግብረ ገብነታቸው ተመስክሮላቸው በደብረ ቢዘን ገዳም መምህር ዓምደ ማርያም ሐጎስ ይባሉ ከነበሩት የገዳሙ አበምኔት ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጸሙ።

የእንጦንስንና ጳኩሚስን አሠረ ፍኖት ለመከተል ከመነኮሱ በኋላ ወደ አደጉበት ገዳም ሳይመለሱ በዚያው በደብረ ቢዘን ገዳም እየተማሩ በረድእነት ማኅበረ መነኮሳቱን ማገልገል ጀመሩ። ብፁዕነታቸው ትኅትናን ከግብረ ገብነት ጋር አዋሕደው የያዙ አባት ስለ ነበሩ ያለምንም ድካምና መሰልቸት ሁሉንም በአሆ በሀሊነት ሲያገለግሉ ያየው ማኅበረ መነኮሳት በየጊዜው ከቅዳሴ መምህርነት ጀምሮ በመጋቢነት፣ በእፌ መምህርነትና ቄሰ ገበዝነት እንዲያገለግሉ አድርጓቸዋል። የብፁዕነታቸውን አገልግሎት የሚመለከቱት አንዳንድ የበቁ ገዳማውያን «ይህ ልጅ የሚጠብቀው ታላቅ ወንበር አለ» ይሉ ነበር ይባላል።

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ከላይ በተጠቀሱት የሹመት ደረጃዎች ገዳሙንና እግዚአብሔርን በትጋት በማገልገል ላይ ሳሉ በብፁዕነታቸው አገልግሎት ከሚደሰቱት የገዳሙ አባቶች አንዱ አበምኔቱ መምህር ዓምደ ማርያም ሐጎስ ነበሩና ብፁዕነታቸው ወደ ኢየሩሳሌም ተሻግረው ቅዱሳት መካናትን ተሳልመው ቢመለሱ መልካም እንደሆነ በማመን በወቅቱ የኤርትራን ጠቅላይ ግዛት በቁጥጥር ሥር አውሎ ለነበረው የኢጣሊያ መንግሥት አመለከቱ። መንግሥቱም ጥያቄውን በመቀበል በራሱ ወጪ ብፁዕነታቸው ወደ ኢየሩሳሌምና ግብፅ ተሻግረው ቅዱሳት መካናትን እንዲሳለሙ ፈቀደላቸው። ብፁዕነታቸውም ግብዣውን በደስታ በመቀበል በ1919 ዓ.ም በመጀመሪያ ወደ እስክንድርያ በመሔድ ገዳማትን ጎበኙ። ከዚያም ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ተሻግረው ቅዱሳት መካናትን ተሳልመው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ።

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ቅዱሳት መካናትን ተሳልመው ወደ ገዳማቸው ከተመለሱም በኋላ ከሚወዷቸው ማኅበረ መነኮሳት ጋር በመሆን የተለመደ አገልግሎታቸውን መፈጸም ጀመሩ። በዚህ ዓይነት ለተወሰኑ ዓመታት ከቆዩ በኋላ እንደ ገና ወደ ውጭ የሚሔዱበት አጋጣሚ መጣ። ይኸውም በወቅቱ የኢጣሊያ

www.ethiopianorthodox.org

መንግሥት አልጋ ወራሽ የነበረው ልዑል ኡምቤርቶ ዲ ሳቮያ «ለሰርጌ ወደ ኤርትራ መጥቼ በነበረ ጊዜ በክብር የተቀበሉኝ መምህራንና መኳንንት እንዲገኙ ጋብዣለሁ» በማለት መልእክት ባስተላለፈ ጊዜ መምህር ዓምደ ማርያም ሐጎስ የኤርትራን ታላላቅ ሹማምንትና መኳንንት ቡድን በመምራት ወደ ሮማ ሲሔዱ ብፁዕነታቸው የመምህራቸው ጸሐፊና የክብር ተከታይ በመሆን በ1922 ዓ.ም ወደ ሮማ አቅንተው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ ጴጥሮስ ሰማዕትነት የተቀበሉባቸውን ቦታዎች ጎብኝተው ተመለሱ::

ከሮማ ተመልሰው ብዙም ሳይቆዩ የኢጣሊያ መንግሥት ኤርትራን የራሱ ግዛት ሲያደርግ ቤተ ክርስቲያኗን ሙሉ በሙሉ በመለየት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋር ለማገናኘት የኢጣሊያ መንግሥት ለቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ወደ ካይሮ ልኳቸው ነበርና ወደ ዚያ ተጉዘው ከወቅቱ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ዮሐንስ ጋር ተወያይተው ተመልሰዋል:: ውይይቱን ጨርሰው ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ ሊቀ ጳጳሳቱ ለብፁዕነታቸው ክብር ለእደባባይ እንዲያገለግላቸው አንድ ጥቁር ልብስና ለቤተ መቅደስ ሁለት ነጫጭ ልብሶች አልብሰው መዓርገ ቁምስና ሰጥተው ሸኝተዋቸዋል::

ብፁዕነታቸው ወደ ገዳማቸው ተመልሰው የተለመደ አገልግሎታቸውን በመፈጸም ላይ ሳሉ በሰውቀት መንፈሳዊ ወልደው ያሳደጓቸውና በእጅጉ ይወዷቸው የነበሩት አባታቸው መምህር ዓምደ ማርያም የኢትዮጵያ ሊቃውንት ጉባኤ ጠርቷቸው ወደ አዲስ አበባ እንደ መጡ በድንገተኛ ሕመም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: መምህሩ ወደ አዲስ አበባ ሲሔዱ ብፁዕነታቸውም አብረዋ ቸው ሔደው ነበረና አስከሬናቸውን ወደ ደብረ ቢዘን አምጥተው በዚያ እንዲያርፍ ካደረጉ በኋላ ገዳማቸውን በመተው ወደ ሸዋ ተመለሱ:: ወደ አዲስ አበባ ከመጡም በኋላ ማረፊያቸውን በወዳጅ ዘመዶቻቸው ቤት አድርገው ሲኖሩ ደግነታቸውና ትሩፋታቸው በቤተ መንግሥቱ በመሰማቱ የፉሪ ቅድስት ሐና ደብር መምህር ሆነው ተሾሙ::

ብፁዕነታቸው ከቤተ መንግሥቱ ጋር በተለይ ከእቴጌ መነን ጋር የቀረብ ግንኙነት ነበራቸው:: በዚህ ቀረቢነታቸው የተነሣ በወቅቱ ከበዓታው ሊቀ ሊቃውንት ሌላ በቤተ መንግሥቱ ጓዳ በር የሚገቡት እሳቸው ብቻ ነበሩ::

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በተሰጣቸው ገዳም በማገልገል ላይ እያሉ ሀገሪቱ በኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተያዘች:: በወረራው ወቅትም የመታሰቢያ ቤት መምህር ሆነው ተሾሙ:: ከዚያም በ1932 ዓ.ም ከሁሉም ጠቅላይ ግዛት በተመረጡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አማካይነት በተደረገው የጳጳሳት ምርጫ አልፈው «አባ ጎርጎርዮስ ጳጳስ ዘወሎ» ተብለው ተሾሙ::



ምንም እንኳን ጊዜው በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ጦርነት ተጋግሎ የቆየ ቢሆንም ወደ ሀገረ ስብከታቸው በመሔድ ለጥቂት ወራት ቆዩ:: የሀገሪቱ ነፃነት ሲመለስም በወረራው ወቅት እንደ ተሾሙ ሌሎች አባቶች ከጵጵስና አገልግሎታቸው ታግደው ቆዩ:: በእርግጥ እንደ ሌሎች አባቶች ከሀገረ ሰብከታቸው ቢነሱም ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር የቀረበ ግንኙነት እንደ ነበራቸው ይነገራል::

በዚህ የተነሣም ጣሊያን ሀገሪቱን ወርሮ በነበረበት ጊዜ የተሾሙት አንዳንድ አባቶች ሥልጣናቸው እንደ ገና ሲመለስ ብፁዕነታቸውም ነሐሴ 27 ቀን 1943 ዓ.ም በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት በነበሩት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ «አባ ጎርጎርዮስ ጳጳስ ዘከፋ» ተብለው ተሾሙ::

ሹመቱን በእኮቴት የተቀበሉት ብፁዕነታቸው ወደ ጅማ በመሔድ አገልግሎታቸውን ሲያበረክቱ ቆዩ:: ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ቀዳማዊ በመጽሐፋቸው ባካተቱት ሐሳብ የተነሣ ከሀገረ ስብከታቸው እንዲነሡ በቅዱስ ሲኖዶስ ሲወሰን በመጀመሪያ ማረፊያነት የተሳኩት ወደ ጅማ ሀገረ ስብከት ነበር:: በመሆኑም ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ እሳቸውንና በወቅቱ ለማጽናናት በሚል ወደ ዚያ ሔደው የነበሩትን መምህር ቀጸላን /በኋላ አቡነ እንድርያስ/ ተቀብለው ሲያስተናግዱ ቆይተዋል ይባላል::

ብፁዕነታቸው በኋላ በሀገረ ስብከታቸው ሲያገለግሉ ቆይተው በዕድሜና በሕመም የተነሣ ዐቅማቸው እየደከመ መጥቶ፤ በመጨረሻም ባደረባቸው በሽታ የተነሣ ሰኔ 4 ቀን 1958 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: ዜና ዕረፍታቸው እንደ ተሰማም ለአንድ ሊቀ ጳጳስ የሚገባው ጸሎተ ፍትሐት ከተደረገላቸው በኋላ ሥርዓተ ቀብራቸው በጅማ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ቤተ መቅደስ ውስጥ ተፈጽሟል:: የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን:: አሜን::

www.ethiopianorthodox.org

# 3.18. ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ቀዳማዊ ሊቀ ጳጳስ

## /1888 - 1974 ዓ.ም /





በስመ ጵጵስናቸው አቡነ ፊልጶስ ተብለው ከመጠራታቸው በፊት «ሊቀ ሊቃውንት ገብረ አብ» በሚል ስም ይጠሩ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ በኤርትራ ክፍለ ሀገር፣ ሐማሴን አውራጃ፣ ሳምዛ ሠሐርቲ ተብሎ በሚጠራው ወረዳ ዓዲ ቀሺ ቀበሌ ከአባታቸው ከአቶ መንግሥተ አብ በዕደ ማርያምና ከእናታቸው ከወ/ሮ ወለተ ኪዳን ወልደ ሚካኤል በ1888 ዓ.ም ተወለዱ::

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በተወለዱበት ቀበሌ የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን በጥሩ ሁኔታ ተምረው በ1901 ዓ.ም ዓዲ አቡን ከነበሩት ግብፃዊው አቡነ ጴጥሮስ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ:: በዲቁናቸውም ሀብተ ጥምቀትን ባገኙበት በቅዱስ ሚካኤል አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ማገልገል ጀመሩ::

ከተወሰነ አገልግሎት በኋላ ትምህርታቸውን በመቀጠል በሠራዬ አውራጃ ወደ ሚገኘው የአቡነ እንድርያስ ገዳም በመሄድ ጾዋትወ ዜማንና መዝገብ ቅዳሴን አለቃ ገብሩ ከተባሉ ባለሞያ በሚገባ ተማሩ:: ከዜማ ትምህርቱም ጋር ሥርዓተ ገዳምን በቃልም በመጣፍም ሲያጠኑ ቆዩ:: በመጨረሻም በዚህ ዓለም ተወስኖ የተሰጣቸው ዕድሜ እስከ ሚያበቃ ድረስ ቤተ ክርስቲያ ናቸውን በንጽሕና በድንግልና ሊያገለግሉ ቃል በመግባት በዚያው ገዳም በወቅቱ ከነበሩት አበ ምኔት መምህር ገብረ አብ ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጽመው አባ ገብረ አብ ተባሉ::

በመነኰሱበት የአቡነ እንድርያስ ገዳም ለአምስት ዓመታት ያህል እንደ ገዳሙ ሥርዓት ሌሊት በሰዓታቱ ቁመት፣ ቀን በእርሻውና በተግባረ ዕዱ ተጠምደው ሲያገለግሉ ቆዩ::

በኋላም አባ ገብረ አብ ቀደም ሲል በዚያው ገዳም የጀመሩትን የዜማ ትምህርት ለማስፋፋት ፈለጉ:: በመሆኑም በማኅበረ መነኰሳቱ ፈቃድ በ1911 ዓ.ም ወደ ታወቀው የቅዳሴ ቤት ደብረ ዓባይ ሔዱ:: በዚያም በወቅቱ ያስተምሩ ከነበሩት ከመምህር ገብረ ማርያም የቅዳሴውን ዜማ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ:: ከዚህም ጋር ሦስተኛውን የትምህርት ደረጃ ቅኔን ከነሞያው አጠኑ::

በዚህ ዓይነት ትምህርታቸውን ያስፋፉት አባ ገብረ አብ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ከግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ መዓርገ ቅስናን ተቀበሉ:: ከተቀበሉም በኋላ የአባ ገብረ አብን ትምህርትና ግብረ ገብነት የተረዱት ሊቀ መምህር ገብረ መድኅን ስቤተ መንግሥቱ የነበራቸውን ቅርበት በመጠቀም ለንጉሡ ሁኔታ ውን አስረድተው የደብረ ወገግ አባ ሳሙኤል ገዳምን የቀኑ ዘንድ የቅድስት ሥላሴን ታቦት ይዘው ወደ አሰቦት ገዳም እንዲሔዱ አደረጉ::

www.ethiopianorthodox.org

አባ ገብረ እብ ወደ አሰቦት ከሔዱ በኋላ የተሰጣቸውን አደራ በብቃት መወጣት ጀመሩ:: በጥረታቸውም ገዳሙ እየተስፋፋ ሔደ:: ይህንን የመነኩሴውን ደገኛ ተግባር የተመለከቱት የቤተ መንግሥት ሰዎችም አሁንም በእባ ገብረ መድኅን ይሁንታ በቅድስት ሀገር የኢትዮጵያ ገዳማትን እንዲያገለግሉ፤ ይልቁንም በወቅቱ ወደ ከፋ ደረጃ ደርሶ በነበረው በደብረ ሡልጣን የግብፅና የኢትዮጵያ የይገባኛል ጭቅጭቅ ላይ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ ከሌሎች መነኩሳት ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ላኳቸው::

ቤተ ክርስቲያናቸው የሰጠቻቸውን ሐላፊነት በብቃት መወጣትን የተካኑት አባ ገብረ አብም በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ለአምስት ዓመታት ያህል በመጋቢነትና በእንደራሴነት አገለገሉ:: ከዚህ በኋላ በ1918 ዓ.ም እንደ ገና ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ቀድሞ ያቀኑትን የደብረ ወገግ አሰቦት ገዳም አበ ምኔትነት ተሾሙ:: አባ ገብረ አብ አሰቦትን ያውቁት ነበርና እንደ ሔዱ መግቢያው በየት ነው? መውጫውስ? ሳይሉ በቀጥታ ወደ ሥራ በመሠማራት ገዳሙን በሁለንተናዊ መልኩ ማስፋፋት፣ በክብት እርቢነት ተወስኖ የነበረውን የአካባቢውን ሕዝብም ወንጌል በመስበክ አምኖ እንዲጠመቅ በማድረግ ሰፋ ያለ አገልግሎት ሊያበረክቱ ቆዩ::

አባ ገብረ እብ በዚህ ዓይነት ገዳሙን ለሰባት ዓመታት በሚገባ ካገለገሉ በኋላ በ1925 ዓ.ም ወደ እዲስ አበባ መጥተው በታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም ሊቀ ሊቃውንትነት ተሾሙ:: የተሾሙበት ቦታ ለቤተ ክህነቱም ሆነ ለቤተ መንግሥቱ የቀረበ መሆኑ ከእርሳቸው ትጋት ጋር ተደምሮ ለአገልግሎት ጥሩ ሁኔታን ፈጠረላቸው:: በመሆኑም ወደ ገዳሙ ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ ሥራቸውን በቅልጥፍና ማከናወን ጀመሩ::

እኒህ ትጉህ እባት ምንም እንኳን በገዳሙ የሠሯቸው ሥራ ዎች አያሌ ቢሆኑም ከዋና ዋናዎቹ እንዱ በገዳሙ የሚገኘውንና ዛሬም ታላላቅ ሊቃውንትን እያፈራ ለቤተ ክርስቲያን የሚያበረ ክተውን የካህናት ማሠልጠኛ መመሥረታቸው አንዱ ነው:: ከዚህም ጋር ብዙም ግልጽና ለአሠራር እመቺ ያልነበረውን የገዳሙን የአስ ተዳደር መዋቅር መልክ እንዲይዝ አድርገዋል::

ሊቀ ሊቃውንት ገብረ አብ በዚህ አገልግሎታቸው ላይ ሳሉ የኢጣልያ ጦር ኢትዮጵያን በመውረሩ ከንጉሠ ነገሥቱና ሌሎች እባቶች ጋር ወደ ማይጨው ሄደዋል:: ወደ እዲስ አበባ ከተመለሱም በኋላ ገዳማቸውን በማስተ ዳደር፣ በወረራው ሽብር ላይ የነበረውንም ሕዝብ በማረጋጋት ላይ እንደ ነበሩ አንድ ነገር ተከሰተ:: ይኸውም የኢጣልያኑ የጦር አዛዥ ግራዝያኒ የካቲት 12 ቀን የአዲስ አበባን ሕዝብ ዛሬ የሰማዕታት ሐውልት ተብሎ በሚጠራው ስድስት ኪሎ



አደባባይ ላይ ሰብስቦ በሚደሰኩርበት ጊዜ በቁርጠኞቹ የኢትዮጵያ ልጆች በተወረወረበት ቦንብ ቆሰለ:: በዚህ የተነሣም በግዳጅ ተሰብስቡ የተባሉት ኢትዮጵያውያን በግፍ በጥይት ተደበደቡ:: ሕዝብ ቀስቅሰዋል የተባሉ ታላላቅ አባቶችም ወደ ኢጣልያ እንዲጋዙ ተደርጎ ኢጣልያ ውስጥ ዚናራ ከተባለ ቦታ እንዲታሰሩ ተደረገ:: በዚህ ቦታ ከታሰሩት አባቶች መካከልም ሊቀ ሊቃውንት ገብረ እብ አንዱ ነበሩ::

ከዚህ ክስተት በኋላ ብዙም ሳይቆይ የኢጣልያ መንግሥት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ጳጳሳት ትመርጥ ዘንድ መብት አላት ብሎ በ1930 ዓ.ም ዐዋጅ አስማ:: ኢ ትዮጵያውያን ሊቃውን ትም ጉዳዩን ቀድመውም ይፈልጉት ነበረና በአስቸኳይ ጉባኤ በመጥራት በምግባራቸውና በትምህርታቸው የተመሰከረላቸውን ሊቃውንት በመምረጥ በወቅቱ የሊቀ ጵጵስናውን መንበር ይዘው በነበሩት በኢትዮጵያዊው ብፁዕ አቡነ አብርሃም እንዲሾሙ አደረጉ:: ከተሾሙት አምስት አባቶች መካከልም አንዱ ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ነበሩ::

የሀገሪቱ ነጻነት ከተመለሰም በኋላ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን በወረራው ወቅት የተሾሙትን ጳጳሳት መዓርግ እንደ ማትቀበል አሳወቀች:: ጉዳዩን ለመፍታትም ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ውይይት ተጀመረ:: ከውይይቱም ጋር ሰኔ 21 ቀን 1936 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉባኤ ውግዘቱን ታነሣ ዘንድ ለእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን እቋሙን ገልጾ ደብዳቤ ላከ:: ይሁን እንጂ ለሁለቱ ሀገሮች ግንኙነት በሚል በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና በመንግሥታቸው ተጽዕኖ ተሹመው የነበሩት ጳጳሳት ያለ ሥራ እንዲቀመጡ ተደረገ::

በኋላ ግን የቆዩት ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ፤ በ1943 ዓ.ም በብፁዕ አቡነ ባስልዮስ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የመጀመሪያው ሊቀ ጳጳስ ሆነው ተሹመው ሔዱ:: ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ሊቀ ጳጳስ ሆነው ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1957 ዓ.ም ድረስ የተለያዩ ድንቅ ድንቅ ሥራዎችን ሠርተዋል:: ከእነዚህም ውስጥ ዋናው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በገፋእያን ስትቸገርበት የቆየችውን የዴር ሡልጣን ገዳም ባለቤትነት ለማስከበር በፍትሕ አካላት ፊት ቀርበው በመከራከር ግብፃውያኑን በመርታት ይዞታችንን አረጋግጠውልናል:: እንዲሁም በኢየሩሳሌም እልዓዛር የሚባለውን የኢትዮጵያውያንን ሰፊ መካነ መቃብር አስከልለውና በጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ስም ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ቦታውን የመጐብኘት ዕድል ያገኘ ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንዲያርፍበት አድርገዋል::

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕነታቸው እንደ ቀደምት አባቶቻቸው ባመኑበት የሚጸኑ፣ ለጸኑበትም የሚጋደሉ በመሆናቸው ከግብፆች ጋር በፍርድ ቤት ካደረጉት ክርክር፣ በታውን በማስከበር ከሠሩት ተጋድሎ በተጨማሪ ጉዳዩን በተመለከተ በጥልቅ ምርምርና ትንተና የተዘጋጁ መጻሕፍት ጽፈዋል። በተለይ ኢየሩሳሌምን ዕወቁና ኢትዮጵያ በሀገረ ቅድስት ኢየሩሳሌም በተባሉ መጻሕፍታቸው ኢትዮጵያውያን በቅድስት ሀገር ያላቸውን ሀብት እንዲያውቁ አድርገዋል። የሰነድ ማስረጃዎች በተባለው መጽሐፋቸው ደግሞ ዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሆኑን የሚያረጋግጡ ጥንታውያት ማስረጃዎችን በአማርኛና በተጻፉበት ቋንቋ ጠርዘው አቅርበዋል። ከእነዚህም ጋር ለምእመናን የመንፈሳዊ ሕይወት ጥንካሬ የሚረዱ የእግዚአብሔር ሕገ መንግሥት፣ ቃለ እግዚአብሔርና ሕጋዊ ጋብቻ የተሰኙ ሌሎች መጻሕፍትን ለምእመናን አበርክተዋል። ብፁሰነታቸው እነዚህን መጻሕፍት እንዲታተሙ ያለቻላቸው የሚያስተምሩትን ትምህርት ሁሉ ቀድመው በወረቀት አስፍረው እያነበቡ የማስተማር ልምዳቸው እንደ ነበር በቅርብ የሚያውቋቸው ይመሰክሩላቸዋል። በመጻሕፍት መልክ ያሳተሟቸው መጻሕፍትም በዚሁ መልክ በታበታተነ መልኩ የተዘጋጁ ጽሑፎች ተሰባስበው ነው ይባላል።

ብፁዕነታቸው ክድርስት ሥራዎቻቸው ውስጥ በአንዱ ከቤተ ክርስቲያኗ ትምህርት የወጣ ሐሳብ አካተው እስከ ውግዘትና ግዞት ደርሰው እንደ ነበር ይነገራል። በዚህ መጽሐፋቸው የተነሣ ምንም እንኳን የወር ቀለባቸውን ባይነፈጉም ከሀገረ ስብከታቸው ተነሥተው ዘወር እንዲሉ፣ ወዲያውም ቢጽናኑ በሚል በመጀመሪያ ወደ ጅማ ሀገረ ስብከት፣ ቆይቶ ደግሞ ወደ አስቦት ገዳም ተግዘው ቆይተዋል። አስቦት ገዳም ላይ አርፈውባት የነበረችዋ ቤት ዛሬም «የአቡነ ፊልጶስ ቤት» በመባል ትጠራለች።

ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ መሬት ላራሹ የሚለውን አቋም ቀደም ብለው ጀምሮ ያራምዱና ለተግባራዊነቱም ጥረት ያደርጉ ነበር ይባላል። ይህንን አቋማቸውን ሲገልጹ «ሰው እንዴት ከመሬት ተፈጥሮ መሬት ይነፈገዋል?» ይሉ ነበር። በዚህ የተነሣም ወደ አስቦት ተግዘው በነበረ ጊዜ የገዳሙ መሬት ለገበሬው እንዲከፋፈል ግፊት ያደርጉ ነበር ይባላል። በገዳሙ ተግዘው ከቆዩ በኋላ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ተጻጽፈው ወደ አዲስ አበባ መጥተው በግላቸው ባሠሩት ቤት እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ቆይተዋል።

ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ከላይ በተገለጠው ዓይነት በጥምቀት ወልዳ አስተምራ ለወግ ለማዕርግ ያበቃቻቸውን ቤተ ክርስቲያን እያገለገሉ ሳሉ በነበረባቸው የልብ ድካም ጤና እየሸሻቸው መጣ። በዚህም የተነሣ ኤርትራ ወደ ሚገኘው ገዳማቸው ቤተ ማኅበር



ሔደው በዚያው ሲረዱ ቆዩ። ይሁን እንጂ እያደር በሽታው እየጸናባቸው በመሔዱ ወደ እሥራኤል ሀገር ኢናይል በተባለው ሆስፒታል ገብተው ሲታከሙ ቢቆዩም ከሕመሙ ሊያገግሙ ባለመቻላቸው ኅዳር 11 ቀን 1974 ዓ.ም በተወለዱ በ87 ዓመት ዕድሜያቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ሥርዓተ ቀብራቸውም ብዙ ጊዜ ባገለገሉባት በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ተፈጽሟል። የብፁዕ አባታችን የድካማቸው በረከት ይደረብን። አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

# 3.19. ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ካልአይ

## ሊቀ ጳጳስ

## /1900 - 1984 ዓ.ም/





መምህር ወ/ሚካኤል ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሉቃስ በቀድሞው የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት፣ በሠራዬ አውራጃ፣ በመንደፈራ አካባቢ ልዩ ስሙ አዲ ቀባይ ተብሎ በሚጠራው ቀበሌ በ1900 ዓ.ም ተወለዱ:: የአባታቸው ስም ቄሰ ብርሃነ መስቀል፤ የእናታቸው ደግሞ ወ/ሮ ብሬ ይባል ነበር:: ዕድሜያቸው ሰባት ዓመት ሲሆን በወላጆቻቸው ቤት ከፊደል እስከ ዳዊት ያለውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ::

ከዚያም በአባታቸው ግፊት ወደ ደብረ ዓባይ ገዳም ሔደው በዚያ ከሚኖሩ መምህራን በየተራ ጸዋትወ ዜማ፣ ቅኔ ከነአገባቡ፣ ሐዲሳት፣ ቅዳሴና አቡሻኽር ተምረዋል:: ከተማሯቸው ትምህርቶች ውስጥም በመዝገብ ቅዳሴ በመምህርነት ተመርቀዋል:: ገና ከልጅነ ታቸው ጀምሮ የገዳምን ሕይወት ከአባቶች እግር ሥር ተቀምጠው የተማሩት ብፁዕነታቸው ባስመሰከሩበት ሞያ እዚያው ጉባኤ ዘርግ ተው አያሌ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል::

ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ገና ተማሪ ሆነው ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ ገዳማውያኑን በእሆ በህሊናት፣ የደከሙትን በመርዳት፣ ለገዳሙ ሕግና ሥርዓት ታዛዥ በመሆን ለረጅም ዓመታት የትሩፋትን ሥራ ፈጽመዋል:: በመጨረሻም «ዘኢያረ መስቀለ ሞትየ ኢይክል ይጸመደኒ» የሚለውን አምላካዊ ቃል በመቀበል በገዳሙ ሕግና ሥርዓት መሠረት ሥርዓተ ምንኩስናን ተቀበሉ:: ረዘም ላለ ጊዜ የብፁዕነታቸውን የትሩፋት ሥራ በቅርብ ሆኖ ያየው የገዳሙ ማኅበረ መነኩሳት በመጨረሻ ለታላቁ ክብር በመብቃታቸው ደስታውን ገለጠላቸው::

ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ከዚህ በኋላ በዚያው በገዳማቸው ጉባኤያ ቸውን አስፋፍተው እያስተማሩ ቅስናንና ቁምስናን በየተራ ተቀበሉ:: በዚህ ዓይነት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ከፈጸሙ በኋላ ከልጅነታቸው ጀምሮ ሲያልሙት የነበረውን ሐሳባቸውን ተግባራዊ ሊያደርጉ ተነሡ:: ይኸውም ገና «መልአክተ ሐዋርያ» ብለው መቁጠር ሲጀምሩ ጀምሮ በአእምሮአቸው እየሣሉ የኖሩትን ቅዱሳት መካናት ለመሳለም ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም መሔድ ነበር::

ሕልማቸውን እውን ለማድረግ ካደጉበት፣ አድገውም ለመዓርግ ከበቁበት ደብረ ዓባይ ገዳም ደቀ መዛሙርቶቻቸውን አስከትለው ወደ አዲስ አበባ መጡ:: ይሁን እንጂ ለደጅ ጥናት ወደ አዲስ አበባ የመጡት ወራሪው የኢጣልያ ጦር ወደ ሀገራችን በሚመጣበት ዋዜማ ስለ ነበር ያሰቡት ሊሳካ አልቻለም:: ይልቁንም የሚወዷት ሀገራቸው በጠላት መወረር፣ ሕዝባቸውም የግፍ ቀማሽ መሆን ሰላበሳጫቸው አስከትለው ያመጧቸውን ተማሪዎች በትነው

www.ethiopianorthodox.org

ከመንፈሳውያን አባቶቻቸውና ከአርበኞች ወንድሞቻቸው ጋር በመቀላቀል ወደ ማይጨው ዘመቱ::

የጠላትን ወረራ ለመመከት ጦርነት ውስጥ የገቡትን አርበኛ በጸሎት እያበረቱ በመዋጋት ላይ ሳሉ ከጠላት በተተኮሰ ጥይት ቀኝ እጃቸውን ተመቱ::

በዚህ የተነሣም ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው በቅድስት ሥላሴና በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም አብያተ ክርስቲያናት እየተዘዋወሩ በመቃብር ቤት ተቀምጠው አቋርጠውት የነበረውን የቅዳሴ ማስተማር አገልግሎት ቀጠሉ:: ፋሺስት ኢጣልያን በኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ላይ እያደረሰ ያለውን የግፍ ጭፍጨፋ በቅርብ ዐይተው የተመለሱት ብፁዕነታቸው ከማስተማር ጋር የመከራ ዘመኑ አልፎ ሀገሪቱ ሰላሟ እንዲመለስ ከመሪር እንባ ጋር ይጸልዩ ነበር:: በመጨረሻም እግዚአብሔር የብፁዕ አቡነ ሉቃስንና የሌሎች አባቶችን ጸሎት ተቀብሎ ከአምስት ዓመታት የከፋ ችግር በኋላ ኢትዮጵያ ነጻነቷን ተቀዳጀች::

በወረራው ወቅት የብፁዕ አቡነ ሉቃስን ተሳትፎ የተገነዘቡት መኳንንት ከነጻነት በኋላ ከማስተማር ሥራቸው በተጨማሪም በማስተዳደርም እንዲያገለግሉ በጽርሐ ጽዮን ሐዋርያት ጉላ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ:: በዚያም ብዙ ሊቃውንትን ከማፍራት ጋር በመልካም አስተዳደራቸው ቦታውን አቅንተዋል:: ከሠሯቸው ሥራዎች ውስጥም በአጥቢያው አንድ ዘመናዊ ት/ቤት በማቋቋም በቤተ ሰዎቻቸው ኢኮኖሚያዊ ድካም የተነሣ መማር ያልቻሉ በርካታ ያሉ ልጆች እንዲማሩ አድርገዋል::

ከዚያም መምህር ተብለው በታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ:: በጉላ ቅዱስ ሚካኤል በነበሩ ጊዜ እንዳደረጉት ሁሉ በበኣታም የተለያዩ ሥራዎችን መሥራት ጀመሩ:: ከሠሯቸው ዐበይት ሥራዎች ውስጥ ሁለቱን ለመጥቀስ ለገዳሙ መተዳደሪያ ሊያስገኝ የቆየውን ጽርሐ ምኒልክ /በተለምዶ መሐሙድ ሙዚቃ ቤት ተብሎ የሚታወቀው ሙዚቃ ቤት ያለበትን/ የተሰኘውን አንድ ትልቅ ሕንፃ ፒያሳ መሐል ከተማ ላይ አሠርተዋል:: ከዚህም ጋር በገዳሙ ስም የተመዘገቡትን የከተማ ቦታዎችና የመሳሰሉትን ሁሉ ካርታ በማስነሳት በሕግ እንዲታወቁ አድርገዋል:: ብፁዕነታቸው በጉባኤ ቀጥ ብለው ከማስተማራቸው በተጨማሪ በሥነ ጽሑፉም ቤተ ክርስቲያንን አገልግለዋል:: በዚህ ረገድ ድርሳነ ማኅየዊ የተባለውን መጽሐፍ ከግእዝ ወደ አማርኛ እንደ ተረጎሙ ይነገራል::



ብፁዕ አቡነ ሉቃስ መምህር ወ/ሚካኤል ተብለው ለባዕታ አስተዳዳሪነት ቢሾሙም ሌሎች አባቶች ያገኙትን «የሊቀ ሊቃውንት ትነትን» ስያሜ አላገኙም ነበር:: ጉዳዩን በቅርበት የሚያውቁ ሰዎች እንደ ሚናገሩት ይህ የሆነበት ምክንያት ነበረው::

የታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን የተሠራችው በቤተ መንግሥቱ ይልቁንም በንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ስለ ነበር ላቅ ያለ ገንዘብ ነበራት:: ታዲያ ግንባታው ሲጠናቀቅ የተረፈው ወደ 700,000 የሚጠጋ ማሪያ ትሬዛ ብር በባንክ ተቀማጭ ሆኖ ነበር:: ይህ በእንዲህ እንዳለ ሀገሪቷ በፋሺስቱ የኢጣሊያ ጦር ትወረራለች:: በዚህ የተነሣ ንጉሡና ሌሎች መኳን ንት ከሀገር ሲሸሹ በገዳሟ ስም ባንክ ተቀምጦ የነበረውን ማሪያ ትሬዛ ይዘው ነበር:: በዚህም ምንም እንኳን ላቅ ያለውን ንጉሠ ነገሥቱ ቢወስዱም የተወሰነ መጠን ያህል በወቅቱ የቤተ ክርስቲያኗ ቄስ ገበዝ የነበሩት ራስ ካሣም ወስደው ነበር::

ከዓመታት በኋላ ሀገሪቷ ነፃ ወጥታ ንጉሡም ሆኑ ራስ ካሣና ሌሎች መኳንንት ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ:: ይሁን እንጂ የሀገሪቱ ሰላም ተመልሶ ቀን ቀንን ቢወልድም በዘመነ አጸባ ከባንክ ወጥቶ የተወሰደው የገዳሟ ገንዘብ ይመለስ ዘንድ ማንም አልጠየቀም ነበረ:: በመጨረሻ ግን ከነጻነት በኋላ በቦታው የተሾሙት መምህር ወ/ሚካኤል /ብፁዕ አቡነ ሉቃስ/ ጥያቄውን ያነሣሉ:: ይሁን እንጂ በተለይ ከራስ ካሣ የእምንታ መልስ አላገኙም ነበር:: ከዚያ ገንዘቡ የሚመለስበትን መንገድ ሲያፈላልጉ ቆይተው በመጨረሻ አንድ መላ ፈጠሩ::

በታሪክ እንደ ሚታወቀው ኢትዮጵያ ነጻ ትወጣ ዘንድ የእንግሊዝ መንግሥት ለሀገሪቱ ድጋፍ ሲያደርግ ጃንሆይ ቃል እንዲገቡለት ካደረገባቸው ነጥቦች ውስጥ አንዱ የፍርድ መጓደል በሀገሪቱ ላይ እንዳይታይ የሚል ነበር:: ለዚህ ይረዳ ዘንድም አቦቴ የተባለ እንግሊዛዊ የሕግ ባለ ሞያ ኢትዮጵያ እንዲመጣና በወቅቱ የዳኝነት ሥራ እንዲሠራ ተደርጎ ነበር:: ብፁዕነታቸው አንድ ቀን በገዳሙ የተሟላ ዝግጅት ያደርጉና «ና በዓታን ጎብኝ» ብለው ይጋብዙታል:: እሱም ግብዣውን ተቀብሎ ከባለቤቱ ጋር ሲመጣ ተማሪዎች፣ የገዳሙ ጡረተኞችና ሊቃውንቱ በሰልፍ እንዲቀበሉት ያደርጋሉ:: ከዚያ ለክብሩ ያዘጋጁለትን መብልና የውስኪ መጠጥ በሚገባ እየጋበዙ «ይኸውልህ ይኸ ሁሉ ተማሪና ጡረተኛ ይመገብ የነበረውን የገዳሟን ገንዘብ ንጉሡና ራስ ካሣ ወስደው ባለመመለሳቸው ችግር ላይ ወድቋል፤ የሚበላውም ሆነ የሚጠጣው አጥቶ ሊበተን ነው» ይሉታል:: ይህን የሰማው እንግሊዛዊ ዳኛም የተወሰደውን ገንዘብ በፍጥነት እንደ ሚያስመልስላቸው ቃል ገብቶ፣

www.ethiopianorthodox.org

ለግብዣውም አመስግኖ ይሔዳል::

በነጋታው እንግሊዛዊው ዳኛ ራስ ካሣ ቀርበው ስለ ተከሰሱበት ጉዳይ ቃላቸውን እንዲሰጡ መጥሪያ ይልክላቸዋል:: ይሁን እንጂ ተከሳሹ ጥሪውን ባለመቀበል አልቀርብም ይላሉ:: በዚህ እንቢታቸው የተበሳጨው እንግሊዛዊ ግን በፖሊስ ተገደው እንዲቀርቡ ትእዛዝ ያስተላልፍና ያሳስራቸዋል:: ጉዳዩም ከንጉሠ ነገሥቱ ጆሮ ይደርሳል:: ነገር ግን እንግሊዛዊው ዳኛ ተጠሪነቱ ለእንግሊዝ መንግሥት በመሆኑ ንጉሡ ማዘዝ አይችሉምና የገዳሟን ገንዘብ በውሳኔው መሠረት እሳቸውም ሆነ ራስ ካሣ እንደ ሚከፍሉ ቃል ገብተው አስፈቷቸው:: ንጉሡ በገቡት ቃል መሠረትም እሳቸው የወሰዱትን ገንዘብ፣ ገንዘብ ሚኒስቴር እንዲከፍል፣ ራስ ካሣም በግላቸው እንዲከፍሉ ትእዛዝ አስተላለፉ:: በዚህ ዓይነት በብፁዕነታቸው ብርታት ገዳሟ ገንዘቧን አግኝታለች::

ብፁለነታቸው በጥረታቸው ባስገኙት በዚህ ገንዘብም ከወራት በኋላ በገቢው ገዳሟ እንድትጠቀም ጽርሐ ምኒልክ የተሰኘውን ሕንፃ መኻል ፒያሳ ላይ አሠርተው እንዲመርቁላቸው ንጉሡን ጋብዘው አስመርቀዋል::

በዚህ የተነሣ ብፁዕነታቸው፣ ምንም እንኳን ከመልካም ሥራና አስተዳደር ጋር ለዓመታት የበዓታ አለቃ ሆነው ቢያገለግሉም «ሊቀ ሊቃውንት» የሚለው ሥያሜ ከቤተ መንግሥቱ ሳይሰጣቸው እንደ ቆየ ይነገራል::

በነዚህና በመሳሰሉት በጐ ሥራዎቻቸው በቤተ ክህነቱም ሆነ በቤተ መንግሥቱ ለውቅናን እያገኙ የሔዱት ብፁዕ አቡነ ሉቃስ በመጨረሻ ጥር 13 ቀን 1944 ዓ.ም የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው ተሾሙ:: በሥራ አስኪያጅነት ተቀምጠውም በአንድ ዓመት ውስጥ ባካበቱት የማስተዳደር ጥበብ ሌሎች አኩሪ ሥራዎችን ሠርተዋል:: ከእነዚም ውስጥ ዛሬ ቤተ ክህነቱ የሚገለገልበትን ትልቅ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ አሠርተዋል:: ብፁለነታቸው ከዚህ አዳራሽ ጋር ተያይዞ የሚነገር አንድ ታሪክ አላቸው:: ሥራ የመውደዳቸውን ያህል የሠሩትን ለሰው መናገር ይወዱ ነበር ይባላል:: ለዚህም የሚሰጡት ምክንያት «እኔ መሥራቴን ተመልክቶ ሌላውም እንዲሠራ ነው» ይሉ ነበር:: ከዕለታት አንድ ቀን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ብፁዓን አባቶችን አስከትለው የጠቅላይ ቤተ ክህነትን ግቢ ሲጎበኙ ብፁለ አቡነ ሉቃስ ከቅዱስነታቸው ጋር ከነበሩት አባቶች አንዱ ነበሩና ቅዱስነታቸው ስብከተ ወንጌል አዳራሽ ካለበት አካባቢ ሲደርሱ ብፁለ አቡነ ሉቃስ ወደ አዳራሹ እያመለከቱ «ቅዱስ አባታችን! ይህንን



አዳራሽ ያሠራሁት እኔ ነኝ፤ ሥራ አስኪያጅ በነበርኩበት ጊዜ» ይሏቸዋል:: ብፁለ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም የብፁዕነታቸውን ንግግር ካስጨረሱ በኋላ «አቡነ ሉቃስ፣ ሁል ጊዜ ይህን ያሠራሁት እኔ ነኝ እያሉ ለምን ይናገራሉ?» ቢሏቸው ብፁዕነታቸውም «እርስዎም ይህ እኔ ያሠራሁት ነው እንዲሉ ይሥሩ» አሏቸው ይባላል::

ብፁለነታቸው ቤተ መንግሥታዊ ጠባይ ነበራቸው ይባላል:: ራሳቸውን ብዙም አያስጨንቁም ነበር:: ፍል ውሃ ወርደው በመታጠብ ወደ እንጦጦ ተራራ ወጣ እያሉ በአገልግሎት የተወጠረ አዕምሮአቸውን ዘና የማድረግ ልማድ ነበራቸው ይባላል:: በዚሁ ላይ እጀ ሰፊ እንደ ነበሩ በቅርብ የሚያውቋቸው ሁሉ ይመሰክሩላቸዋል:: የገንዘብ ችግር ስላልነበረባቸው ለተቸገሩት ይመጸውቱ ነበር:: ራሳቸው ከመመጽወትም በተጨማሪ ባዕለ ጸጎች እንዲመጸውቱ «በሚጠፋ ገንዘብ የማይጠፋ ቤት ግዙበት» እያሉ ይመክሩ ነበር ይባላል::

በሥራ አስኪያጅነት ብዙም ሳይቆዩ በ1945 ዓ.ም በተደረገው የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ ከፍተኛ ድምፅ በማግኘት ግንቦት 18 ቀን 1945 ዓ.ም. በብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ አንብሮተ እድ መዓርገ ጵጵስናን ተቀበሉ:: የተሾሙበት ሀገረ ስብከትም አርሲ ነበር::

እንኳን ሰፊ ሀገረ ስብከት ተሰጥቷቸው በተወሰነች ቦታም ሥራን አቀላጥፎ መሥራት የተካኑት ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ወደ ሀገረ ስብከታቸው ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ መንፈሳዊና ማኀበራዊ ሥራቸውን በስፋት ቀጠሉ:: ከሠሯቸው ሥራዎች ውስጥ የተሾሙበት ሀገረ ስብከት አዲስ በመሆኑ እሰላ ላይ መንበረ ጵጵስና አሠርተው እዚያው ግቢ የመድኃኔ ዓለምን ቤተ ክርስቲያን አሳንፀዋል:: በሀገረ ስብከቱ ውስጥም በየአውራጃውና በየወረዳው በመዘዋወር እዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነፅ፣ የፈረሱትን በማሳደስ፣ መምህራንንና ሰባክያንን ቀጥሮ በማሠማራት፣ ድልድዮችንና መንገዶችን በማሠራት ከነዋሪው ሕዝብ ጋር በመተባበርና በመግባባት ለሀገርና ለወገን የሚጠቅሙ እያሌ ሥራዎችን ሠርተዋል::

ወደ አሰላ ከሔዱበት 1945 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1955 ዓ.ም ድረስ በዚህ ዓይነት በርካታ ሥራዎችን የሠሩት ብፁዕነታቸው በየካቲት ወር 1955 ዓ.ም ከአርሲ ሀገረ ስብከት ወደ ኤርትራ ሀገረ ስብከት ተዛወሩ:: ይሁን እንጂ በዚያ ብዙ ሳይቆዩ ከሁለት ዓመት በኋላ እንደ ገና ወደ ቀደመ ሀገረ ስብከታቸው ወደ አርሲ ተመለሱ::

ብፁለ አቡነ ሉቃስ በመጀመሪያው ሀገረ ስብከታቸው ቀድሞ

www.ethiopianorthodox.org

የወጠኗቸውን ሐሳቦች ተግባራዊ እያደረጉ፣ የሠሯቸውንም እያጠናከሩ እስከ 1969 ዓ.ም ቆዩ። ቤተ ክርስቲያን የስጣቻቸውን ሐላፊነት የሚወጡት ከሕዝቡ ጋር በመተባበር ነበርና በ1969 ዓ.ም በመላ ሀገሪቱ ተከስቶ በርካታ ወጣቶችን በሞት የነጠቀውን የቀይ ሽብር ሀዋጅ በይፋ በየሀውደ ምሕረቱ በስፋት ይናገሩና ድርጊቱን ይቃወሙ ነበር። በዚህ የተነሣም በደርግ ታጣቂዎች ተይዘው ለአራት ዓመታት /ከ1969 - 1972 ዓ.ም/ ታስረው ነበር።

እንደ አሳቸው ሁሉ ታስረው ከነበሩ ሌሎች አባቶች ጋር በ1972 ዓ.ም ከእስር ከተፈቱ በኋላ በወታደራዊው መንግሥት ተጽዕኖ እርሳቸውም እንደ ሌሎች በጡረታ እንዲገለሉ ተደረገ። ብፁዕነታቸውም ምንም እንኳን ሀገረ ስብከቱ ቢቀርባቸውም በጾምና በጸሎት ተወስነው እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ቆዩ። በመጨረሻም ኅዳር 9 ቀን 1984 ዓ.ም ልክ ከቀኑ 10:30 ላይ ሕመመኛና ደከመኝ ሳይሉ ከአባቶች ወንድሞቻቸው ጋር መንፈሳዊ ጭውውት በመጫወት ላይ ሳሉ ነፍሳቸው ከሥጋቸው ተለየች።

ለሊቀ ጳጳስ የሚገባው ጸሎተ ፍትሐት በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሁም የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎችና ካህናት ከተደረገ በኋላ ሥርዓተ ቀብራቸው በአሰላ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል። የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን። አሜን።



# 3.20. ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ካልአይ ሊቀ ጳጳስ

## /1885 - 1959 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

ቀድሞ ንቡረ እድ ገብረ ሚካኤል ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የካቲት 16 ቀን 1885 ዓ.ም ከአባታቸው ከቄስ ኃይለ ሥላሴ ኮነብ ከእናታቸው ከወ/ሮ እበባ በያኔው ትገሬ ጠቅላይ ግዛት፣ በሽሬ እውራጃ ደብረ ዓባይ ከተባለው ቦታ ተወለዱ::

በወላጆቻቸው ቤት በመልካም እንክብካቤ እየተማሩ ካደጉ በኋላ ዕድሜያቸው ሰባት ሲሆን ስመ ክርስትና ወደ አገኙበት ደብረ ዓባይ ገዳም ገብተው የሁለተኛ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን መማር ጀመሩ:: በነበራቸው ቀለም የመያዝ ችሎታ በመምህ ራቸውም ሆነ በባልንጀሮቻቸው ክብርና ሞገስ ሳይለያቸው ጸዋትወ ዜማንና ቅኔን እየተማሩ አደጉ:: ዕድሜያቸው ሃያ ዓመት ሲሆን ብቃታቸው በማኅበረ መነኮሳቱ ተመስክሮላቸው በዚያው ገዳም መዓርገ ምንኩስናን ተቀበሉ::

ከዚህ በኋላ ለመዓርገ መቅርስና ጳኩሚስ በበቁበት ገዳም በአሆ በሀሊነት የዕድሜ ባለጸጋ የሆኑትን አበው እየረዱ ከቆዩ በኋላ በሃያ ሁለት ዓመታቸው ከግብፃዊው ብፁዕ እቡነ ጴጥሮስ መዓርገ ዲቁናንና ቅስናን በአንድነት ተቀበሉ::

ብፁዕ እቡነ ሳዊሮስ ዕውቀታቸውንና ትኅርምታቸውን የሚገልጹ መዓርጋትን በዚህ መልኩ ካገኙ በኋላ ማኅበረ መነኮሳቱ በሙሉ ድምጽ መርጧቸው የጥንታዊውና የቅደሴ ምስክር የሆነው የደብረ ዓባይ ገዳም ገበዝ በመሆን ለዘጠኝ ዓመታት በትጋት አገለገሉ:: ከዚያም የብፁዕነታቸውን ብቃት የተመለከተው ማኅበሩ በዚያው ገዳም ሥር ታቅፎ ይተዳደር ለነበረው አቡነ ዮሐንስ ገዳም እስተዳዳሪ አድርጎ ሾማቸው:: ሹመቱን በአኮቴት የተቀበ ሉት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ገዳሙን በአበምኔትነት በብቃት ማስተ ዳደር ጀመሩ:: ከማኅበረ መነኮሳቱ ጋር በመተባበር የገዳሙ ሥርዓት የሚጠ ናከርበትን፣ መናንያኑም ከጸሎትና ከትርኅምት ጋር ገዳሙን በማልማት የሚተጉበትን መንገድ እየቀየሱ በማገ ልገል ላይ ሳሉ የገዳሙን ጉዳይ ለማስፈጸም ወደ አዲስ አበባ መጡ::

ነገር ግን ደብረ ዓባይ ሳይ ሆነው የሚፈጽሙት አገልግሎ ትና ትሩፋት አዲስ እበባ በቤተ መንግሥቱና በቤተ ክህነቱ ይሰማ ኖሮ ብፁዕነታቸው እንዳሰቡት ጉዳያቸውን ፈጽመው ሊመ ለሱ አልቻሉም:: ይኸውም በግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ ፈቃድና ትእዛዝ እዚሁ አዲስ አበባ እንዲቆዩ ተደርጎ የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራልን መምህርነት ተሾሙ::

ብፁዕነታቸው ምንም እንኳን ከማኅበረ መነኮሳቱ መለየታ ቸው ቢያሳዝናቸውም፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተቀበሉትን ከፍተኛ ሐላፊነት በመቀበል የተጣለባቸውን አደራ ለመወጣት የተለመደ



ትጋታቸውን ማሳየት ጀመሩ:: ይሁን እንጂ ብዙም ሳይቆዩ ኢትዮጵያ በፋሺስት የኢጣልያ ጦር ተወረረች:: በዚህ የተነሣም ንጉሠ ነገሥቱ ከተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብለው ወደ ማይ ጨው ሲዘምቱ እሳቸውም እንደ ሌሎች አባቶች አብረው ዘመቱ:: ጦርነቱ በፋሺስት ሠራዊት አጥቂነት ሲጠናቀቅ ብፁዕነታቸው ከሌሎች ጥቂት እባቶችና እርበኞች ጋር ተማርከው በቀይ ባሕር እካባቢ ወደ ሚገኘው ደሴተ ናኩራ ተጋዙ::

የአምስት ዓመቱ ዘግናኝ ወረራ በኢትዮጵያውያን የበሳይ ነት ተጠናቆ ሁሉም ነገር ወደ ነበረበት ሲመለስ ብፁዕነታቸው እንደ ሌሎች በርካታ አርበኞች ለሻርክ /የባሕር አውሬ/ ከመጣል ተርፈው ከጥቂት እባቶችና አርበኞች ጋር ከግዞት ወጡ:: ከዚያም እግዚአብሔርን በማመስገን በገዳማቸውና ሌሎች ቦታዎች እየተዘ ዋወሩ ሐዋርያዊ ተግባር ሲያከናውኑ ቆዩ:: የብፁዕነታቸውን አገልግ ሎት ከቀድሞ ጀምሮ የሚያውቁት ቤተ ክህነቱና ቤተ መንግሥቱ በ1943 ዓ.ም መስከረም ወር ላይ መልእከ ብርሃን በማለት የአድዋ ደብረ ብርሃን ሥላሴ አለቅነት ሾሟቸው:: ይሁን እንጂ ብዙም ሳይቆዩ በዚሁ ዓመት ሰኔ 24 ቀን ለገዳሟ ወንበር የሚገባውን ራስ ወርቅ አሥረው የአዲስ ዓለም ማርያምን ንቡረ እድነት ተሾሙ::


በእግዚአብሔር ፈቃድ ከወንበር ወንበር ከፍ እያሉ ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ የቆዩት ብፁዕነታቸው በ1945 ዓ.ም በተደረገው የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ ይበቃሉ ተብለው ከተመረጡት አባቶች መካከል እንዱ በመሆን በብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ አንብሮተ እድ «ብፁዕ እቡነ ሳዊሮስ ጳጳስ ዘጋሞ ጎፋ» ተብለው ተሾሙ::

በተሰጣቸው ሀገረ ስብከት ከማኅበረ ካህናትና ምእመናን ጋር በመተባበር ያላመኑትን በማሳመን፣ ያልተጠመቁትን በማጥ መቅ የምእመናንን ቁጥር በማብዛት ላቅ ያለ ሐዋርያዊ አገልግሎ ታቸውን ሲያበረክቱ ቆዩ:: አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነፅ፣ በሀገረ ስብከቱ ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች እንዲሠሩ በማድረግ የካህናት ገቢ እንዲጨምር፣ በአገልግሎታቸውም እንዲተጉ በማድረግ ላይ እንዳሉ ባደረባቸው ሕመም ጥር 17 ቀን 1959 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: ሥርዓተ ቀብራቸውም ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ የሀገረ ስብከቱ ካህናት፣ በርካታ ምእመናንና የብፁዕነ ታቸው ቤተሰቦች በተገኙበት የሀገረ ስብከታቸው ርዕሰ ከተማ በሆነው አርባ ምንጭ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል:: የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን::

www.ethiopianorthodox.org

# 3.21. ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ካልአይ ሊቀ ጳጳስ

## /1887 - 1983 ዓ.ም/





ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ አጅግ የተከበሩና የታወቁ ከነበሩት ወላጆቻቸው ቄስ ገብረ ኢየሱስ ፈቃዱ እና ከእናታቸው ከእመት ዓመተ ኢየሱስ ምሕረተ አብ በኤርትራ ደቡባዊ ዞን ልዩ ስሙ ኩርባርያ በሚባለው ቦታ ነሐሴ 12 ቀን 1887 ዓ.ም ተወለዱ::

ወላጆቻቸው ለብዙ ጊዜ ልጅ ሳይወልዱ በመቆየታቸው ከረጅም ጊዜ ኀዘንና ተማኅፅኖ በኋላ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስን በስዕለት በማግኘታቸው እነርሱም ሆኑ መላ ቤተሰባቸው ተደሰቱ:: እንደ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መስከረም 17 ቀን 1988 ዓ.ም በሰለተ በዓለ መስቀል ተጠምቀው ስማቸውም «ገብረ መስቀል» ተብሎ ተሠየመ::

የብፁዕነታቸው እናት አግዚአብሔርን ልጅ እንዲሰጣቸው ሲለምኑ ልጅ ካገኙ ለቤተ መቅደስ አገልግሎት ሲፈጽም ይኖር ዘንድ ለቤተ ክርስቲያን እሰጣለሁ በሚል ስዕለት ነበርና ቃላቸውን በማክበር ዕድሜያቸው ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ሲሆን እዚያው ኤርትራ ውስጥ ይገኝ ወደ ነበረው አቡነ ብፁዕ አምላክ ገዳም ወስደው አስረከቧቸው:: የገዳሙ ማኅበር ግን በእምነታቸው የገቡትን ቃል መፈጸማቸውን አድንቀውና አመስግነው እስከ ስድስት ዓመት ድረስ ከአነርሱ ጋር እንዲቆዩ ምክር ሰጥተው ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ አደረጉ:: የብፁዕነታቸው ወላጆችም የማኅበረ መነኩሳቱን ምክር በመቀበል መልሰው በመውሰድ ስድስት ዓመት እስኪሆናቸው ድረስ በእንክብካቤ አሳደጓቸው:: ስድስት ዓመት እንደ ሞላቸውም ወደ ዚያው ገዳም በመመለስ በሐላፊነት አባ ኪዳነ ማርያም ይባሉ ለነበሩት ታላቅና የተከበሩ መነኩሴ ሰጧቸው::

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ወደ ገዳሙ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ማኅበረ መነኮሳቱንም እንደ ልጅነታቸው እየተላላኩ ማገልገል ጀመሩ:: ቀለም ፈጥኖ የመያዝ ችሎታ የነበራቸው ብፁዕነታቸው አገልግሎታቸውን በትጋት ከመፈጸም ጋር ትምህርታቸውን በሚገባ ተምረው ልክ ዘጠኝ ዓመት ሲሆናቸው ንባብ፣ ዳዊትና ግብረ ዲቁና በሚገባ አጥንተው መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ::

ከዚህ በኋላ ከወላጆቻቸው በአደራነት የተቀበሏቸው ባሕታዊ ኪዳነ ማርያም የብፁዕነታቸውን የትምህርት ፍላጐትና ትምህርት የመቀበል ችሎታ በመመልከት ከፍተኛ ትምህርት ወደ ሚገኝበት ቦታ ይዘዋቸው ለመሔድ በመወሰን በትግራይ ክፍለ ሀገር ተምቤን አውራጃ ወደ ሚገኘው ተንስሐ ገዳም አመጧቸው:: በዚያን ጊዜ ዕድሜያቸው 12 ዓመት ከ10 ወር ነበር:: በዚያም እርሳቸውም በአደራነት እንደ ተቀበሏቸው የገዳሙ መምህር ለነበሩት ለመሪ ጌታ ወልደ ትንሣኤ «አደራ» ብለው በመስጠት ከጥቂት ቀናት ቆይታ

www.ethiopianorthodox.org

በኋላ ወደ ገዳማቸው ተመለሱ::

ምንም እንኳን ፊደል አስቆጥረው ያሳደጓቸው መምህራቸው አባ ኪዳነ ማርያም ትተዋቸው በመሔዳቸው ለጊዜው ቢደናገጡም፣ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ እየዋሉ እያደሩ ግን ከቦታው ጋር እየተለማመዱና ትምህርቱም እየተስማማቸው ሔደ:: በመሆኑም ትምህርታቸውን በንቃት በመከታተል በአጭር ጊዜ ከመሪ ጌታ ወልደ ትንሣኤ የውዳሴ ማርያምን ዜማና የቃል ትምህርት ተማሩ:: ብፁዕነታቸው በነበራቸው ከፍተኛ የመማር ፍላጎት የተነሣ በተንስሐ ገዳም አሐዱ ብለው የጀመሩትን ዕውቀት መንፈሳዊ ለማስፋፋት ወደ ጭኾ ሥላሴ ገዳም ሔዱ:: በዚያም ሁለተኛውን ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን እንደ ጀመሩ ከመምህራኑ ብቃትና፣ ከተማሪዎች ብዛትና ከጉባኤው ድምቀት አንጻር «ደብረ ኃይል» ወደ ተባለው ገዳም ቢሔዱ የበለጠ ዕውቀት እንደ ሚያተርፉ ሰሙ:: በመሆኑም ወደዚያው ገዳም አቀኑ::

በዚያም ሰፊ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት የድጓ ሊቅ መምህር ወልደ እግዚእ የጾዋትዎ ዜማ ትምህርታቸውን ተምረው በሚገባ አጠናቀቁ:: ትምህርታቸውን በመቀጠልም በዚያው ገዳም የኔታ ሀብተ ሥላሴ ከሚባሉት የቅዳሴ መምህር የቅዳሴውን ትምህርት አጠናቀቁ:: ብፁዕነታቸው ከመማር ጋር አገልግሎቱን ከልጅነታቸው ጀምሮ ይፈልጉት ነበርና በተማሩት ትምህርት በቅዳሴና በሌሎች መንገዶች የቤተ መቅደሱን አገልግሎት ያበረክቱ ነበር::

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በዚህ ዓይነት ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ከተማሩ በኋላ በ1910 ዓ.ም ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ከወላጆቻቸውና ከዘመዶቻቸው ጋር ለጥቂት ወራት ቆዩ:: ከዚያም የጀመሩትን ትምህርት ለማስፋፋት ወደ ጎንደር ለመሔድ ወላጆቻቸውንና ዘመዶቻቸውን በንብት ጠየቁ:: በተለይ እናታቸው ዳግም የልጃቸውን ርቆ መሔድ ባለመቀበል ቢያለቅሱም እንደ ምንም አግባብተው ዕድሜያቸው ልክ 23 ሲሆን በ1911 ዓ.ም ለትምህርት ወደ ጎንደር ሔዱ::

ብፁዕነታቸው እግረ መንገዳቸውን ቅዱሳት መካናትን እየተሳለሙ እግዚአብሔርን እየተማፀኑ ተጉዘው ጎንደር ማኅበረ ቅዱስ ሚካኤል ከሚባለው ደብር ደረሱ:: በዚያም የኔታ ቢሰጥ ከተባሉ መምህር ዘንድ ለሁለት ዓመታት አቋቋምንና ዝማሬ መዋሥዕትን ተማሩ:: ከዚህ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ለብዙ ዓመታት ይመኙት የነበረውን ትርጓሜ መጻሕፍት ለመማር አዲስ አበባ በሚገኘው መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ዘርግተው ወደ ነበሩት ታላቁ ሊቅ መምህር ደስታ /በኋላ



ብፁዕ አቡነ አብርሃም/ በ1914 ዓ.ም ገቡ::

በመምህር ደስታም /ብፁዕ አቡነ አብርሃም/ ሆነ በመላ ጉባኤያቸው መልካም አቀባበል የተደረገላቸው ብፁዕነታቸው ንጉቶው የሐዲሳትን የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርት በስፋት ቀጠሉ:: ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ አዲስ ዕውቀትን ለመያዝ ከነበራቸው ጉጉትና ፍላጎት እንዲሁም ቀለም የመቀበል ፍጥነት የተነሣ በመምህራቸው ዘንድ ከፍተኛ አድናቆትና ተቀባይነት ነበራቸው ይባላል:: በዚህም የተነሣ መምህራቸው ብፁዕ አቡነ አብርሃም ከቤተ መንግሥትና ከቤተ ክህነት እንግዶች ሊጠይቋቸው ወደ እሳቸው ሲመጡ ደቀ መዝሙራቸው ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ከጐናቸው ተቀምጠው በአስተውሎት የተመላ አስተያየታቸውንና ምክራቸውን እንዲበነዝሩ ያደርጉ ነበር ይባላል:: እንግዳ ሲመጣም ብቻ ሳይሆን ጉባኤያቸውን ዘርግተው የመጻሕፍትን ምሥጢር ሲተነትኑ ቀድሞ ሐሳብንና አስተያየትን የመግለጽ ዕድል ለብፁዕነታቸው እየሰጡ እንዲናገሩና እንዲገልጹ ያደርጉ ነበር ይባላል:: ይህ የመምህራቸው እንክብካቤና የራሳቸው ብቃት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስን እስከ ቤተ መንግሥቱ ድረስ እንዲታወቁ አደረጋቸው::

ብፁዕ አቡነ አብርሃም የደቀ መዝሙራቸውን ችሎታ በማድነቅ ከንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱ ጋር አስተዋወቋቸው:: ንግሥቲቱም ካዩትና ከሰሙት አስተዋይነታቸው በመነሣት መዝነውና አድንቀው ያለ አንድ ችግር ትምህርታቸውን እንዲማሩ የሚገባቸው ድርጐ ከቤተ መንግሥቱ እንዲበፈርላቸው አደረጉ:: ከዚህም ጋር ከሁሉም አብልጠው የሚወዱት መጽሐፍ መሆኑን ተገንዝበው በብራና የተጻፈ አንድ ትልቅ መጽሐፈ መነኰሳትና ሌሎችንም መጻሕፍት ሸለሟቸው:: በዚህ ዓይነት ከዕውቁ መምህራቸው መምህር ደስታ /ብፁዕ አቡነ አብርሃም/ ወንበር ሥር ቁጭ ብለው ሐዲሳትን፣ ብሉያትን፣ ሊቃውንትንና መጽሐፈ መነኰሳትን ተምረው አጠናቀቁ::

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በአዲስ አበባው መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል በመማር ላይ ሳሉ በነበራቸው ተለሚነትና ነገርን አራቆ የማቅረብ ችሎታ ለ1600 ዘመናት የዘለቀው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን አባቶች በኢትዮጵያ ላይ መሾም ቀርቶ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ላይ እንዲሾሙ ከፍተኛ ትግል አድርገዋል:: በትግላቸውም ድልን ተቀዳጅተዋል:: በብፁዕነታቸው አስተባባሪነት በኢትዮጵያውን ሊቃውንት ትግል አጣብቂኝ ውስጥ የገቡት ግብፃውያን የያኔውን መምህር ገብረ መስቀልን «ገብረ መስቀል ነቀል» በማለት ይጠሯቸው ነበር ይባላል::

በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ በስፋት እንደ ተተረ

www.ethiopianorthodox.org

ከው የጵጵስና ለኢትዮጵያውያን ይገባል ክርክሩ ውስጥ ለውስጥ ሲካረር ቆይቶ በ1919 ዓ.ም እና በ1920 ዓ.ም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ:: የኢትዮጵያ መንግሥትም ለእንቅስቃሴው ሙሉ ድጋፉን ሰጠ:: በመጨረሻም ግብፃውያኑ በኢትዮጵያ ጥያቄ ተስማሙና «የምንሾማቸውን አባቶች መርጣችሁ ላኩ» ብለው ወደ ኢትዮጵያ መልእክት አስተላለፉ::

በግብፃውያኑ ጥያቄ መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስተያን ሊቃውንት ተሰብስበው መምህር ደስታን /በኋላ አቡነ አብርሃም/፣ መምህር ኃይለ ማርያምን /በኋላ አቡነ ጴጥሮስ/፣ መምህር ኃይለ ሚካኤልን /በኋላ አቡነ ሚካኤል/ና መምህር ገብረ ኪዳንን /በኋላ አቡነ ይስሐቅ/ መርጠው ከሌሎች መልእክተኞች ጋር በግንቦት ወር 1921 ዓ.ም ወደ ግብፅ ላኩ:: ከአባቶች ጋር ከሔዱት መልእክተኞች አንዱና የልዑካኑ መሪ የያኔው አባ ገ/መስቀል /ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ/ ነበሩ::

ሊቃውንቱ ግብፅ እንደ ደረሱ ግብፃውያን «የጵጵስና ሹመት እንዳይናቅ ለኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ሙሉ ሥልጣን አንሰጥም» ብለው በመምከር የግብፃውያኑ ስምምነት ኢትዮጵያውያኑ እንዲያጸድቁት በጽሑፍ አድርገው ሰጧቸው:: በማታለል ታሪካዊ ስሕተት ሊያሠሯቸው እንደሆነ ለኢትዮጵያውያኑ ከታደሰው ወረቀት የተገነዘቡት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ወረቀቱን ከወንድሞቻቸው ሰብስበው ከያዙ በኋላ የሚከተለውን ታሪካዊ ንግግር አሰሙ::

«እኛ ወደዚህ የመጣነው እንሾማለን፣ ሥልጣን እንጨምራለን ብለን እንጂ ውል ልንገባ፣ የነበረንንም ሥልጣን አሳልፈን ልንሰጥ አይደለም:: እናንተም የሚሾሙትን አባቶች መርጣችሁ ስደዱ ባላችሁት መሠረት መጥተናል::… በመሠረቱ መዋዋል መፈራረም ሥጋዊ እንጂ መንፈሳዊ አይደለም:: ሐዋርያት ሲሾሙ ውል ነበራቸውን? እስኪ ማርቆስ የተዋዋለውን ውል ፎርማውን አሳዩን? እኛኮ ጥንታውያን አባቶቻችንን እንዳናስቀይም ግንኙነታችን እንደ ነበረው በፍቅር እንዲቀጥል ብለን ነው እንጂ እናንተ አባትነታችሁን ብትነሱን ከሌሎች እንደምናገኘው ልባችሁ ያውቀዋል:: … ደግሞም ትዝ ይበላችሁ፤ ሀገራችሁ አሸዋ በረሃ ነው:: ቁማችሁ የምትኼዱት ከሀገራችን በሚፈልቀው በዓባይ ውኃ ነው:: እናንተ መንፈሳዊ ምግባችንን፤ መብታችንን ብትገድቡ እኛም አባቶቻችን ይሉት እንደ ነበረ ሥጋዊ ምግባችሁን የዓባይን ውኃ መገደብ እንችላለን:: ውል ግቡልን የምትሉ ከሆነ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ተዋዋሉ እንጂ ከእኛ ጋር አይደለም:: አሁንም ትሾሙ እንደሆነ ሾማችሁ ስደዱን:: የማትሾሙን ከሆነ ደጎና ሁኑ ብላችሁ አሰናብቱንና ወደ ሀገራችን እንመለስ::»



ቁርጠኛ ንግግራቸውን የሰሙት ግብፃውያን አባቶችም ጉዳዩን ሊቀለብሱ እንደማይችሉ ተገንዝበው ተመርጠው የመጡላቸውን ኢት ዮጵያውያን አባቶች በወቅቱ ፓትርያርካቸው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ እንብሮተ ዕድ ሾመው ወደ ኢትዮጵያ ላኳቸው::

ብፁዕ አቡነ አብርሃም መዓርገ ጵጵስና ተሾመው ወደ ኢትዮጵያ እንደ ተመለሱ የተሰጣቸው ሀገረ ስብከት ጐጃም ነበር:: በመሆኑም ብፁዕነታቸው ወደ ዚያ ሲያቀኑ ጸሐፊ መዝሙራቸው የነበሩት መምህር ገብረ መስቀልም /ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ/ አብረዋቸው ሔዱ:: በዚያ በማስተማርም ሆነ በማስተዳደር ሥራው የሰውቀት መንፈሳዊ አባታቸውን እያገዙ እርሳቸውም ሥነ አስተዳደሩን ያጠኑ ጀመር:: ይሁንና በዚህ ደገኛ ተግባር ላይ እያሉ ግፈኛው የኢጣልያ ጦር ሀገራችንን ወረረ:: የኢትዮጵያን በግፍ መወረር ያዩት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስም አቡነ አብርሃምን በዚያው በጎጃም ትተው ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ጋር ወደ ማይጨው ዘመቱ:: የማይጨው ዘማች ጦር ሲበታተንም ወደ ደሴ በመመለስ የመድኃኔ ዓለም አስተዳዳሪ በመሆን የወሎ አርበኞችን በማስተባበር አኩሪ ሥራን ሲሠሩ ቆዩ::

ጠላት ከኢትዮጵያ ከወጣ በኋላ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በሊቀ ሊቃውንት መዓርግ የታሰካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ:: ሹመቱን በአኮቴት በመቀበል አገልግሎታቸውን በትጋት እየተወጡ ሳሉ ሥልጣናቸውን እንደያዙ የሰጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ /በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባሰልዮስ/ እንደራሴ፣ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የመንፈሳዊ ጉባኤ ምክትል ሰብሳቢ ሆነው በመሾም ሰፋ ያለ አገልግሎት አበርክተዋል:: ብፁዕነታቸው በተለይ በምክትል ሰብሳቢነታቸው የጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደራዊ መዋቅር መልክ እንዲኖረው አድርገዋል፡ በየሀገረ ስብከቱ፣ አውራጃውና ወረዳው መንፈሳዊ ጉባኤያትን አቋቁመዋል፡ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የምትተዳደርበት የቃለ ዐዋዲ ደንብ ንድፍ መሠረቱ እንዲጣል አድርገዋል::

በነበራቸው የማስተዳደርና የማስተባበር ብቃት ከሹመት ወደ ሹመት እያደጉ የመጡት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በ1940 ዓ.ም በርእሰ አድባራት ወገዳማት ዘኢትዮጵያ አክሱም ጽዮን ንቡረ እድና የአውራጃው አስተዳዳሪ በመሆን ተሹመው ሄዱ:: ከመንፈሳዊው አስተዳደር ጋር የሥጋዊውን አስተዳደር እንዲመሩ ሥልጣን የተሰጣቸው ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ከበታች ካሉት የአውራ ጃው ዳኞችና አስተዳዳሪዎች ጋር በመተባበር በአውራጃው ድኻ እንዳይበደል፣ ፍርድ እንዳይጓደል አድርገዋል::

www.ethiopianorthodox.org

በአክሱም ጽዮን ንቡረ እድነትና በአውራጃው አለተጳዳሪነት ለ10 ዓመታት ያህል አኩሪ ተግባር የፈጸሙት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በወቅቱ የትግራይ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ሲያርፉ ሐምሌ 18 ቀን 1948 ዓ.ም በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ አንብሮተ እድ ሁለተኛው የትግራይ ጳጳስ ሆነው ተሾሙ::

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስም ሹመቱን በፍጹም ፍርሀትና ታላቅ ትሕትና ተቀብለው እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው ድረስ ምእመናን የሚገለገሉባቸውን አብያተ ክርስትያናትን፣ ትምህርት ቤቶችን ከማሠራት ጋር እንደበታቸውን ከጸሎትና ከማለተማር፣ ዓይናቸውን መጽሐፍ ከመመልከትና የክርስቶስን መከራ መስቀል እያሰቡ ከማልቀስ፣ እጃቸውን ለድሆች ከመዘርጋት፣ በኅሊናቸው ፈጣሪያቸውን ከማሰብ ሳያቋርጡ መዋዕለ ሕይወታቸውን ሁሉ በቁም ነገር አሳልፈውታል::

ብፁዕነታቸው በትግራይ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው ባገለገሉባቸው ዓመታት በርካታ ጠቃሚ ሥራዎችን አከናውነዋል:: ከእነዚህም ውስጥ ቅዱስ ያሬድ መንፈሳዊ ት/ቤት፣ ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ት/ቤት፣ አብርሃ ወአጽብሐ መንፈሳዊ ት/ቤት፣ በመቀሌ ማኅበራዊ ኑሮ፣ የካህናት ማሠልጠኛ ት/ቤት፣ ቤተ መጻሕፍትና ምንጣፍ ሥራ፣ ሌሎች ዘመናዊ ት/ቤቶች በአድዋ፣ አዲ አቡን፣ የሐ፣ ውቅሮ፣ ዒጋሜ /ጉለ መኻጸ/፣ ተንቤን /ሀቢይ ዓዲ/፣ ሽሬና ዓዲ አውዓላ ተጠቃሾች ናቸው::

ዛሬ በዲግሪና በዲፕሎማ ደረጃ ደቀ መዛሙርትን እያፈራ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚያስማራው የከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ እሳቸው መሠረቱን የጣሉለትና ምኞታቸው እንደ ነበረም ይነገራል::

ሁለተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከመንበራቸው በደርግ መንግሥት በተነሡ ጊዜ እርሳቸውን የሚተካ ፓትርያርክ ተመርጦ እስኪሾም ድረስ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በሌሎች አባቶች ብቃታቸው ተመስክሮ ተመርጠው ተጠባባቂ ፓትርያርክ ሆነው በ1971 ዓ.ም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እስከ ሚሾሙ ድረስ በብቃት አገልግለዋል::

ብፁዕነታቸው የደርግን መንግሥት በሚመለከት አንድ የሚነገር ታሪክ አላቸው:: ይኸውም መንግሥቱ ሙሉ በሙሉ ሥልጣኑን ጨብጦ ሀገሪቷን መምራት ከጀመረ በኋላ የሕዝቡን አመለካከት ይቀይሩብኛል ያላቸውን ሰዎች እየመረጠ ከእሱ ጋር እንዲሰለፉ፣ የማይስማሙ ከሆነ ደግሞ እንዲገደሉ ያደርግ ነበር::



በዚህ ረገድ የቤተ ክርስቲያናችንን አባቶችም ክሱ ለማለለፍ ጥረት አድርጓል:: የወደቀውን ዘውዳዊ መንግሥት ረስተው ከአዲሱ ወታደራዊ መንግሥት ጋር እንዲጓዙ፣ ሕዝቡንም እንዲያስተምሩ ከተጠየቁ አባቶች ውስጥ ብፁዕነታቸው አንዱ ነበሩ:: ጉዳዩን በቅርብ ሲከታተሉ የነበሩ ሰዎች እንደ ሚናገሩት ከደርጉ ተወክለው የተላኩት ሰዎች ሔደው ሲጠይቋቸው ብፁዕነታቸው በነበራቸው ጥብአት «እኔ የማውቀው የዚች ሀገር ንጉሥ ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴን ብቻ ነው፣ ሌላ ንጉሥ አላውቅም፣ እንዳውቅም አልፈልግም» ብለው በድፍረት ተናግረዋል:: በዚህም ደርግ የብፁዕነታቸውን ጥንካሬና ግልጽ አቋም አድንቆ ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወስድባቸው «ባይሆን ሕዝቡን እንዲሀ ብለው እንዳ ይሰብኩብን» ብሎ ማሳሰቢያ ሰጥቶ አልፏቸዋል::

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ለ87 ዓመታት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸውን ያለ ድካምና መሰልቸት ካገለገሉ በኋላ የተወለዱ ላቸው ዕድሜ ሲደርስ በተወለዱ በ 96 ዕድሜያቸው ነሐሴ 12 ቀን 1983 ዓ.ም ከሌሊቱ 6:00 ላይ ዐረፉ::

ሥርዓተ ቀብራቸውም ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ቆሞሳት፣ ካህናትና ምእመናን በተገኙበት መቀሌ በሚገኘው የደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል ተፈጽሟል:: የብፁዕነታቸው ሐያው ስም የሚጠራበት፣ ታሪካቸው የሚታወስበት ቤተ መዘክር መቀሌ በሚገኘው የደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን መቅደስ ውስጥ በሀገረ ስብከቱ ካህናትና ምእመናን ትብብር ተሠርቶ ከኅዳር 12 ቀን 1991 ዓ.ም ጀምሮ በሕዝብ በመጐብኘት ላይ ይገኛል:: የብፁዕነታቸው በረከት ይደርብን:: አሜን::

www.ethiopianorthodox.org

# 3.22. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ካልአይ

## ሊቀ ጳጳስ

## /1901 - 1961ዓ.ም/





በቀድሞው ጎጃም ጠቅላይ ግዛት ደብረ ኤልያስ ተብሎ በሚታወቀው ቦታ ከአባታቸው ከመምህር ትርፌና ከእናታቸው ከወ/ሮ ትሑት ወልደ አካውሃ ነሐሴ አምስት ቀን 1901 ዓ.ም ተወለዱ:: የቀድሞ ስማቸው ሊቀ ሊቃውንት መሐሪ ይባል ነበር::

ወላጅ አባታቸው የልጃቸውን በትምህርት ሰው የመሆን ሕልም ሰውስጣቸው ቢይዙም ብፁዕነታቸው ተወልደው ገና ስድስት ዓመት ሲሆናቸው በድንገተኛ ሕመም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: አንኳን ለእርሳቸው ለሌላ የሚበቁት አባታቸው በሞት የተለዩአቸው ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስም የአባታቸው አደራ ነበረና ስመ ክርስትና ባገኙበት ደብረ ኤልያስ ያስተምሩ ከነበሩት መሪ ጌታ ሣህሉ ከፊደል ጀምሮ ሙሉ ጸዋትወ ዜማን አጠናቀቁ:: የብፁዕነታቸውን አስደናቂ የመማር ችሎታ ያዩት የደብሩ ማኅበርና አለቃ ገና በልጅነታቸው በዚያው ደብር የካህናት አጋፋሪና የቤተ መዛግብት ሹም አደረጓቸው::

በደብሩ የተሰጣቸውን ሐላፊነት በብቃት እየተወጡ በዚያው ደብር ዕውቅ የቅኔ መምህር ከነበሩት መሪ ጌታ ገብረ ሥላሴ ዘንድ የቅኔን ትምህርት አጠናቀቁ:: በብፁዕነታቸው አስደናቂ ቀለም የመያዝ ብቃት የተገረሙት መምህራቸውም ቀደም ሲል በደብሩ ከተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር ጋር በጉባኤያቸው ይገኙ በነበሩት ከ200 በላይ ተማሪዎቻቸው ላይ ሐላፊ አድርገው ሾሟቸው:: ከዚህም ብልህነታቸውንና ወደ ፊት የሚደርሱበትን ትልቅ ቦታ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦላቸው ከሥራቸው አድርገው፤ የሚበ ሉትን እያበሉ፣ የሚጠጡትን እያጠጡ፤ የውዳሴና የቅዳሴ ማርያምን፣ የትምህርተ ኅቡዓትንና የኪዳንን ትርጓሜ በሚገባ አስጠኗቸው:: እንደ ተለመደው ትምህርቱን ሲያጠናቅቁም ከደብሩ አስተዳደርና ካህናት ጋር መክረው ፈቃድ ካገኙ በኋላ በወቅቱ አዲስ አበባ ላይ ስፊ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ወደ ነበሩት ዕውቁ አለቃ ኅሩይ በደብሩ ማንተም የአደራ ደብዳቤ አስይዘው ወደ አዲስ አበባ ላኳቸው:: ሲልኳቸው ግን ለአምስት ዓመታት ያህል ከተማርክ በኋላ ወደ ደብርህ ተመልሰህ ሌሎችን እንድ ታስተምር በሚል የአደራ ቃል ነበር::

ታላቁ ሊቅ አለቃ ኅሩይም የማኅበሩንና የወዳጃቸውን የመምህር ገብረ ሥላሴን የአደራ ደብዳቤ ተቀብለው ከተመለከቱት በኋላ ብፁዕነታቸው ወደ ጉባኤው ገብተው የሐዲሳትን ትርጓሜ ይማሩ ዘንድ ፈቀዱላቸው:: በመምህሩ ፈቃድ እጅግ የተደሰቱት ብፁዕነታቸውም የሚወዱትንና መቼም ቢሆን ወደ ኋላ ብለውበት ማያውቁትን ትምህርታቸውን ጀመሩ::

[illegible] ሀገራችንን የኢጣሊያ ጦር በግፍ የወረረበት፣ በዚህ

www.ethiopianorthodox.org

የተነሣም የሕዝቡም ሆነ የሀገሪቷ ሰላም ከፉኛ ተናግቶ የነበረበት ቢሆንም ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በአምስቱ ዓመታት የመጻሕፍተ ሐዲሳትንና የሃይማኖተ አበውን ትርጓሜ አጠናቀቁ:: ከማጠናቀቅም አልፈው ማስተማር ጀመሩ:: በዚህ ጊዜም የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ አስተዳደርና ካህናት ዕውቀታቸውንና ግብረ ገብነታቸውን በመመልከት በደብሩ የሐዲስ መምህር ሆነው እንዲያስተምሩ መረጣቸው::

የአዲሱ የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሕንፃ በተፈጸመ ጊዜ እንደ ሌሎች ሸማግሌ ካህናት ከፍ ያለ ሽልማት ተቀበሉ:: በመካነ ሥላሴ ደብር ከዘረጉት ጉባኤ ጋር በየዓመቱ መላ አርባ ጾምን ወደ ታላቁ ደብር ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በመሔድ የሐዲሳትን ትርጓሜ ያስሙ ነበር:: በዚህና በሌሎች የእልቅና አገልግሎታቸው የተነሣም ስማቸው ከደብራቸው አልፎ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ምእመናንና በቤተ መንግሥቱ አካባቢ እየገነነ መጣ:: ከግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ዓፄ ኃይለ ሥላሴም በተለያዩ ጊዜያት ሽልማት አግኝተዋል::

ከዚህ ቀጥሎም መደበኛ ጉባኤያቸውን ሳይበትኑ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ት/ቤት የሐዲስ መምህር በመሆን ከ1936 ዓ.ም እስከ 1943 ዓ..ም ድረስ በማስተማር ብዙ ደቀ መዛሙርትን ለመምህርነት አብቅተዋል:: በ1935 ዓ.ም ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ የቤተ ክህነት ሊቃውንት የእንግሊዝኛ ቋንቋንም ትምህርት መቅሰም አለባቸው በሚል በላይኛው ቤተ መንግሥታቸው ቦታ መድበው፣ መምህር ቀጥረው እንዲማሩ ባደረጉ ጊዜ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ከተመ ረጡት አባቶች አንዱ በመሆን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በብቃት አጠናቀዋል::

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የአጎት ልጅ እንደ ነበሩ የሚነገርላቸው ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ጋርም የጠበቀ ግንኙነት እንደ ነበራቸው ይነገራል:: በዚህም የቅዱስነ ታቸው አቡነ ቀሲስ በመሆን አገልግለዋል፤ ፀጉራቸውንም የሚላ ጩ ቸው እሳቸው ነበሩ ይባላል:: ብፁዕነታቸው ወንበር ዘርግቶ ከማስ ተማር በተጨማሪ በነበራቸው የመሰበክ ጸጋ በዐውደ ምሕረት ላይ ቃለ እግዚአብሔርን በሚጣፍጥ ሁኔታ በማቅረብ ቤተ ክርስቲያንን በለፊው እንዳገለገሉ ይነገራል:: በዚህም ለመጀመሪያ ጊዜ ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ሠራተኞች እሑድ እሑድ የስብከተ ወንጌል መርሐ ግብር ሲጀመር ሊቀ ጉባኤ የሚል ማዕረግ ተሰጥቷቸው ያስተምሩ ነበር:: ይህንን የመሰለው ጉባኤ ወደ መንፈሳዊ ኮሌጅና ሌሎች ቦታዎችም እንዲስፋፉ ብፁዕነታቸው ትልቅ ሚና ነበራቸው::

በ1938 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ወደ ትውልድ አካባቢያቸው



እንዲሔዱ ተደርጐ የደልማ መድኃኔ ዓለምን ቤተ ክርስቲያን ገዳም በመምህርነት፤ አውራጃውንም በሊቀ ካህናትነት እንዲያስተዳድሩ ተሾሙ:: በዚያም ለተወሰኑ ዓመታት ካገለገሉ በኋላ በ1943 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ተመርጠው የሀረብኛን ቋንቋ ተምረው የጥንት መጻሕፍትን ለመመርመርና ለማስተማር እንዲችሉ በሚል ወደ ግብፅ ካይሮ ተላኩ:: ብፁዕነታቸው በዚሁ ጉዟቸው በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማትንና ሌሎችንም የታሪክ ቦታዎች ጐብኝተዋል::

ወደ ግብፅ የሔዱበትን የዐረብኛ ቋንቋ ትምህርት ለሦስት ዓመታት ተከታትለው፣ በቋንቋው መናገር፣ ማንበብና መጻፍ ከቻሉ በኋላ በ1936 ዓ.ም በግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ተጠርተው ወደ አዲስ አበባ መጡ:: እንደ መጡም በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም ሊቀ ሊቃውንት መሐሪ ትርፌ ተብለው ተሾሙ::

ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በሊቀ ሊቃውንትነታቸውም የተለያዩ ታላላቅ ሥራዎችን በመሥራት ውጤት ማስመዝገብ ጀመሩ:: ከሠሯቸውም ሥራዎች ውስጥ በነበራቸው የሥነ ጽሑፍ ጸጋ በርከት ያሉ መጻሕፍትን አዘጋጅተው ለንባብ አብቅተዋል:: እነዚህም <u>ርቱዕት ፍኖት ዘባስልዮስ በባሕረ ጣና</u> /1948 ዓ.ም/፣ <u>መጽሐፌ በቀኖኔት ዘጸም ወዘበዓል</u> /1946 ዓ.ም/፣ <u>ቃለ ምዕዳን</u> /1948 ዓ.ም/፣ <u>የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው</u> /1948 ዓ.ም/፣ <u>መዝገበ ሃይማኖት</u> /1950 ዓ.ም/፣ ከመጻሕፍተ ሐዲሳት ውስጥ ግብረ ሐዋርያትን፣ የሰባቱን መልእክታተ ሐዋርያትና የዮሐንስ ራእይን ትርጓሜ ከጥንት አባቶች ሲወርድ ሲወራረድ እንደ መጣው የአንድምታ ትርጓሜ - /1951/፣ <u>የኦርቶዶክሳውያን እምነት</u> /1951 ዓ.ም/ ናቸው::

ብፁዕነታቸው ጥሩ ነው ያሉትን ሥራ ሁሉ ከመሥራት ወደ ኋላ አይሉም ነበር:: በዘመነ ሊቀ ሊቃውንትነታቸው በደርግ ዘመነ መንግሥት ወደ ብሔራዊ ቤተ መንግሥቱ ተጠቃሎ እስከ ዛሬ በዚያው የሚገኘውን የሊቀ ሊቃውንቱን ቤት አሠርተዋል:: ይህን በዘመናዊ መልኩ የተሠራውንና 7 መኝታ ቤቶች፣ 70 ሰዎች በወንበር ተቀምጠው የሚያበላ አዳራሽ፣ ምድር ቤቱን ከመኝታ ቤቱና ሳሎኑ ጋር ስምሥጢር የሚያገናኙ መንገዶች ያሉትን መኖሪያ ቤት በከፍተኛ ወጪ ካሠሩ በኋላ ጃንሆይንና እቴጌዪቱን እንዲመርቁላቸው ይጋብዛሉ:: ጃንሆይም ግብዣውን በመቀበል ከእቴጌ ጋር ሆነው ቤቱን ሲመርቁ፤ የቤቱን አጠቃላይ ድርጅትና ታላቅነት ካዩ በኋላ «ግሩም ቤት ነው፤ ነገር ግን ለአንድ መነኩሴ ይኸንን የሚያኽል ቤት ምን ይሠራለታል? ለአንድ ቤት ይኸን

www.ethiopianorthodox.org

ያህል ገንዘብስ ለምን ወጣ?» ብለው ቅሬታቸውን ገልጸው ነበር ይባላል:: በዚህም ንጉሡ «ይኸን ያኸል ገንዘብ አውጥተው አንድ ቤት ላይ ያዋሉት ከላይ ሆኖ የሚቆጣጠራቸው ሰው ባለመኖሩ ነው» ብለው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሚኒስትሮች ያሉበት ነገር ግን ሊቀ ሊቃውንቱ በሰብሳቢነት የሚመራው «ባለ አደራ ቦርድ» የተለኘ ተቆጣጣሪና ወሳኝ አካል አቋቋሙ::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በነበሩ ጊዜ « 'አሐዱ አብ'፣ 'ሀበነ' እና 'አግዚአ' ሲባል ብቻ ካልሆነ በስተቀር በቅዳሴ ጊዜ መጋረጃ ተገልጦ ሥርዓተ ቅዳሴ እንዲከናወን» በሚል በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ እስከ ተቀየረበት ጊዜ ድረስ በሀገሪቱ ተጀምሮ እስከ ሚፈጸም ድረስ የቅዳሴ ሥነ ሥርዓት የሚከናወነው መጋረጃ ተዘግቶ ነበር:: ነገር ግን ምንም አንኳን በሲኖዶስ ቢወሰንም የአዲስ አበባ ታላላቅ አድባራትና ገዳማት አለቆች ውሳኔውን በቶሎ ወደ ተግባር ለመለወጥ ፈርተው ነበር:: በዚህ ጊዜ መልካም ነገር የሆነን በፍጥነት ወደ ተግባር የመለወጥ ብቃት የነበራቸው ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ያለምንም ፍርሀት በበዓታ ላይ ፈጥነው ተግባራዊ አድርገውታል::

ይህ የብፁዕነታቸው ፈጥኖ የመወሰን ችሎታ ምንም እንኳን በርካታ ሥራዎችን እንዲሠሩ ቢያደርጋቸውም ለአሳቸው ግን የሚቃወሟቸውን ያበዛባቸው ነበር:: በዚህ ረገድ አንድ በስፋት የሚነገር ታሪክ አላቸው:: የታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን መንበር በእጅጉ ጠባብና ለአገልግሎት የተመቸ አልነበረም:: ይህንን ችግር ያጤኑት ብፁለነታቸው የቤተ መንግሥት ቤተ ክርስቲያን ነው፣ ተቃዋሚ ይመጣብኛል ሳይሉ ጉበኑን አፍርሰው በሩን በማስፋት የነበረችዋን መንበር አውጥተው ሌላ ሰፊ መንበር ያስገባሉ:: ምንም አንኳን የፈረሰውን ጉበንና በር አንደ ገና የነበረውን መልክ ጠብቀው ቢያሠሩትም በወቅቱ ለቤተ መንግሥቱ እንቀርባለን ይሉ የነበሩ ሊቃውንት በቍላቻ ተነሥተውባቸው ስማቸውን በጥሩ ሁኔታ አያነሡትም ነበር::

ይሁን እንጂ በሊቅነታቸውም ሆነ በደፋርነታቸው በቤተ መንግሥቱም ሆነ በቤተ ክህነቱ ይወደዱ ስለ ነበር ከመሸለምና ከመወደስ በስተቀር ምንም ዓይነት እርምጃ አልተወ ሰደባቸውም ነበር::

በዚህና በሌሎች ሀበይት ሥራዎቻቸው በ1947 ዓ.ም ታኅሣሥ ሦስት ቀን ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በራስቻ መዓርግ የራስ ወርቅና ሙሉ ሽልማትን ተቀብለዋል:: ዳግመኛም በ1948 ዓ.ም የኒሻን ሽልማት ተሸልመው የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ሆነዋል::



ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በሊቀ ሊቃውንትነት መዓርግ ተቀምጠው ልዩ ልዩ አኩሪ ሥራዎችን እየሠሩ ሳለ ሐምሌ 12 ቀን 1952 ዓ.ም በተደረገው የጳጳሳትና የኤጲስ ቆጳሳት ምርጫ ተመርጠው ሐምሌ 17 ቀን 1952 ዓ.ም በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ገዳም በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ባስልዮስ አንብሮተ ዕድ «ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የስሜንና የቤጌምድር ጳጳስ» ተብለው ተሾሙ::

ብፁዕነታቸው ሹመቱን በአኮቴት በመቀበል ወደ ጎንደር ከሔዱም በኋላ የተለመደ አገልግሎታቸውን በስፋት ቀጥለዋል:: ዛሬ የአቋቋም ማስመስከሪያ የሆነችውና ጎንደር ከተማ የምትገኘው የደብረ ኃይል ወደብረ ጥበብ በዓታ ቤተ ክርስቲያን ቅድስትና መቅደስ ብቻ ነበራት:: አሳቸው ወደ ቦታው ከሔዱ በኋላ ግን በራሳቸው ገንዘብ ቅኔ ማሕሌቱንም አሠርተው ለአገልግሎት እንዲበቃ አድርገዋል:: ከዚህም በተጨማሪ በነበራቸው የሥራ ችሎታ ገቢው ለሀገረ ስብከቱ መጠቀሚያ ይሆን ዘንድ አዲስ አበባ ከመንበረ ፓትርያርኩ አካባቢ የሚገኘውንና በደርግ መንግሥት ተወርሶ የነበረውን በኋላ በቅርቡ ቤተ ክርስቲያኗ የተረከበችውን አንድ ባለ ሦስት ፎቅ ሕንፃ አሠርተዋል::

ብፁሉ አቡነ ጴጥሮስ በሕይወታቸው መጨረሻ መንፈስ ቅዱስ አነሳስቷቸው በመላ ጎንደር በበቅሎ እየዞሩ ቅዱሳት መካናትን ይጎበኙ ነበር ይባላል:: በጉዞ ሰንብተው በሀቢይ ጾም መግቢያ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ደርሰው በዚያው ሁለቱን ወር ሱባኤ ይዘው ቆዩ:: ብፁዕነታቸው በገዳሙ የሁለት ወር ቆይታቸው አግዚአብሔር ገልጾላቸው ዕለተ ዕረፍታቸው አንደ ደረሰ ተረድተዋል:: ሱባኤውን እንደ ጨረሱም ወደ ሀገረ ስብከታቸው ተመልሰው ከግል ንብረታቸው ጀምሮ መልክ መያዝ ያለበትን ነገር ሁሉ መልክ አስይዘው ለሞታቸው ምክንያት በሆነው ደዌ ዘአሴት ተያዙ::

በዚህም ምንም አንኳን የሐኪም ርዳታ እንዲያገኙ ቢደረግም የጤናቸው ሁኔታ የበለጠ በመታወኩ ለከፍተኛ ሕክምና በዚያውም ቅድስት ሀገርን ተሳልመው እንዲሰናበቱ እግዚአብሔር ስለ ፈቀደ ወደ ኢየሩሳሌም ተሳኩ:: በዚያም ሊሻላቸው ባለመቻሉ ሐምሌ 4 ቀን 1961 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ::

ቀብራቸውም ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በወቅቱ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ እንደራሴና የሐረር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፣ ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ በወቅቱ የሲዳሞ ሀገረ ሰብከት ሊቀ ጳጳስ፣ ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ በወቅቱ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ኤጲስ ቆጳስ፣ ክቡር ንቡረ እድ ዲሚጥሮስ ገብረ ማርያም በወቅቱ በሚኒስትርነት መዓርግ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ በተገኙበት

www.ethiopianorthodox.org

ሐምሌ 6 ቀን 1961 ዓ.ም በዚያው በኢየሩሳሌም ገዳማችን ተፈጽሟል:: ብፁዕነታቸው ነፍሳቸው ከሥጋቸው ከመለየቷ በፊት ያለ ንብረታቸው በሙሉ ለቤተ ክርስቲያን እንዲሰጥ በተናዘዙት መሠረት እንደ ተፈጸመ ይነገራል:: የብፁዕነታቸው በረከት ይደርብን:: አሜን::



# 3.23. ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ ካልአይ ሊቀ ጳጳስ

/1888 - 1968 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

ቀድሞ ገብረ እግዚአብሔር ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ የካቲት 29 ቀን 1888 ዓ.ም በያኔው የኤርትራ ክፍለ ሀገር ጸዓዳ ክርስቲያን በተባለው ቀበሌ ከአባታቸው ከአቶ ወልደ ማርያም እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ወለተ መድኅን ተወለዱ:: እንደ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በተወለዱ በአርባ ቀናቸው ስመ ክርስትና ሀብተ ወልድና ተቀብለው ገብረ እግዚአብሔር ተብለው ተሠየሙ::

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስም እዚያው ኤርትራ ክፍለ ሀገር መርቆሬዎስ ተብሎ በሚጠራው ታላቅ ገዳም ለዲቁና የሚያበቃቸውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት አጠናቀቁ:: ከዚያም በዚያው በትግራይ ክፍለ ሀገር ዓድዋ ዓዲ አቡን ተብሎ በሚታወቀው ቦታ ይኖሩ ከነበሩት ግብፃዊው አቡነ ጴጥሮስ የዲቁናን መዓርግ ተቀበሉ::

ትምህርታቸውን ለማስፋፋት ወደ ደብር ዓባይ ገዳም በመሔድ ጸዋትወ ዜማንና የዓሥራ እራቱን ቅዳሴያት ዜማ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ:: ከዚያም ፈደል ቆጥረው ወዳደጉበት የአቡነ መርቆሬዎስ ገዳም በመመለስ ጉባኤ ዘርግተው ሲያስተምሩ፣ በጎንም ሥርዓተ ገዳምን ሲያጠኑ ቆዩ:: በዚህ ዓይነት ቀን በጉባኤ ውለው ማታ በተለያዩ ሥራዎች ማኅበረ መነኰሳቱን ሲያገለግሉ፣ እያገለገሉም ሥርዓተ እንጦንስንና ጳኲሚስን ሲማሩ ከቆዩ በኋላ ሚያዝያ 16 ቀን 1915 ዓ.ም በዚያው ገዳም በወቅቱ እበ ምኔት በነበሩት መምህር ሀጽመ ጊዮርጊስ ሥርዓተ ጸሎት ተደርሶላቸው መዓርገ ምንኩስናን ተቀበሉ::

ከዚህ በኋላ ንጽሕ ጠብቆ በትኅርምት ከመኖር ጋር አእም ሮአቸውን በመንፈሳዊ ዕውቀት የበሰጠ ለማነፅ ያሰቡት ብፁዕነታቸው ከገዳማቸው በመነሣት ወደ በጌምድርና ሰሜን ክፍለ ሀገር ሔዱ:: በዚያም ከልዩ ልዩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ጸዋትወ ዜማን በማጠናቀቅ የፍትሐ ነገሥትን፣ ሃይማኖተ አበውንና የሐዲሳትን መጻሕፍት ትርጓሜ ጠንቅቀው በመማር በመምህርነት ተመረቁ::

በዚህ ዓይነት ዕውቀታቸውን ያስፋፉት ብፁዕ አቡነ መርቆ ሬዎስ ወደ ጎንደር ከተማ በመሔድ ጉባኤ ዘርግተው ደቀ መዛሙርትን በማስተማር ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አድርሰዋል:: ይሁን እንጂ በዚያው በማስተማር ላይ ባሉ ጠላት ኢትዮጵያን በግፍ በመውረሩ በታላቅ ኀዘን ተውጠው ሲጸልዩና ሕዝቡንም ሲያጽናኑ ቆዩ:: ይባስ ብሎም ጠላት በወረወረው ቦምብ ተመትተው ስለ ቆሰሉ ብዙ ጊዜ በሕመም ሲሰቃዩ ቆይተዋል::

ግፈኛው የፋሺስት ጦር ኢትዮጵያን ለቅቆ የሀገሪቱ ሰላም ከተመለሰም በኋላ በወቅቱ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ /በኋላ ብፁዕ



ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ/ ታሪካቸውን ሰምተው ኖሮ ከጎንደር አስመ ጥተው በሐረር ሀገረ ስብከት በሊቀ ካህናትነትና በዚያው የጥምቀተ ባሕር ቅዱስ ሚካኤልና የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሆነው እንዲያገለግሉ ሾሟቸው:: በዚህ ዓይነት ሹመት ወደ ሐረር ያቀኑት ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ የተለያዩ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች በመስጠት ላይ ሳሉ ሐምሌ 12 ቀን 1952 ዓ.ም በተደረገው የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ በአንደኛነት ተመርጠው ሐምሌ 17 ቀን 1952 በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ አንብሮተ እድ «አባ መርቆሬዎስ» ተብለው የባሌ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ሆነው ተሾሙ::

ወደ ባሌ ሀገረ ስብከት ከሔዱ ጀምሮም ከአካባቢው ምእመ ናንና ካህናት ጋር በመተባበር በአካባቢው ወንጌል እንዲ ሰበክ፣ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነጹ፣ ያረጁት እንዲታደሱ አድርገዋል:: ጎባ ላይ መንበረ ጵጵስናውንና የጎባ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያንን አሠርተዋል::

ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ ባሌ ሀገረ ስብከት ሳሉ በ1964 ዓ.ም ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም በመሔድ የኢትዮጵያን ገዳማት ጎብኝተው ተመልሰዋል:: እግረ መንገዳቸውንም በወቅቱ የአሰከን ድርያ ፓትርያርክ ከነበሩት ብፁዕ እቡነ ዮሳብ ለክብራቸው የሚገባ የወርቅ መስቀል ከነሐብሉ ተሸልመዋል:: እንደዚሁም ሁሉ በ1965 ዓ..ም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስተያን ወደ ሮም ካቶሊክ ልዑካን በላከች ጊዜ የልዑካኑ መሪ በመሆን ከሮማው ርእስ ለቃነ ጳጳሳት ጳውሎስ ስድስተኛ ጋር በመገናኘት ሐዋርያዊ ተልእኮአቸውን በአጥጋቢ ሁኔታ ፈጽመው ተመልሰዋል::

በቅርብ የሚያውቋቸው እንደ ሚናገሩት ብፁዕነታቸው ላመኑበት ነገር ወደ ኋላ የማይሉ፤ የቁጡነት ጠንካራ አቋዋም ነበራቸው::

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸውን ረዘም ላሉ ዓመታት ያገለ ገሉት ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ በመጨረሻ ባደረባቸው የጤና መታወክ በሕክምና ሲረዱ ቢቆዩም ሊሻላቸው ባለመቻሉ ነሐሴ 29 ቀን 1968 ዓ.ም ከዚህ ዓለም ድካምና እንግልት ዐረፉ:: እስከሬ ናቸውም በብፁዕ ወቅዱስ እቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና በቤተ ክህነት ባለሥልጣናትና በምእመናን ታጅቦ ወደ ሀገረ ስብከታቸው ባሌ ጎባ ከተማ ከተወሰደ በኋላ ራሳቸው ባሠሩት መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በተዘጋጀለት ቦታ ላይ ዐርፏል:: የብፁዕ እቡነ መርቆርዮስ በረከት አይለየን:: እሜን::

www.ethiopianorthodox.org

# 3.24. ብፁዕ አቡነ ሰላማ ካልአይ

## ሊቀ ጳጳስ

## /1898 - 1970 ዓ.ም/





ከመሾማቸው በፊት አባ መዘምር ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሰላማ በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በ1898 ዓ.ም ተወለዱ:: ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ በዚያው በትውልድ ሀገራቸው የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን በሚገባ ተምረው ጥር 12 ቀን 1916 ዓ.ም ከግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ::

ከዚያም የትውልድ አጥቢያቸውን ቤተ ክርስቲያን ጥቂት ካገለገሉ በኋላ ትምህርታቸውን ለማስፋፋት ወደ ጎንደር በመሔድ አለቃ ምሕረቴ ከሚባሉ መምህር ጸዋትወ ዜማን ጠንቅቀው ተማሩ:: እንደ ገና ወደ ጎጃም ቀደም ሲል በመሻገርም ዋድላና ደላንታ ከነበሩት ከአለቃ ተበማ ዘንድ ቅኔ አጠኑ:: አሁንም ትምህርታቸውን በመቀጠል ጎንደር ከመምህር ወልደ ዮሐንስ ዘንድ አቋቋምን፣ ወደ አዲስ አበባ በመምጣትም ከብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ሐዲሳት ትርጓሜን፣ ከመምህር በላይና አለቃ አየለ ደግሞ ሊቃውንትን በሚገባ ተማሩ::

በዚህ ዓይነት በትምህርት መንፈሳዊ አዕምሮአቸውን ውስጣቸውን የገነቡት ብፁዕ አቡነ በላማ ኅዳር 1 ቀን 1932 ዓ.ም በብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ሥርዓተ ጸሎት ተደርገላቸው መዓርገ ምንኩስናን ተቀበሉ:: እንደ ገና በዚያው ዓመት ሰኔ 21 ቀን መዓርገ ቅስናን ተቀበሉ:: ከዚያም በኋላ በዚሁ በአዲስ አበባ በስብከተ ወንጌል አገልግሎት ተሰማርተው ረዘም ላለ ጊዜ አገልግለዋል::

ብፁዕ አቡነ ሰላማ ባላቸው የስብከተ ወንጌል ጸጋ ከአዲስ አበባም ውጭ በደቡቡ የሀገራችን ክፍል እየተዘዋወሩ ወንጌልን ሲያዳርሱ ቆይተዋል::

በመጨረሻም ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያበረከቱት የረጅም ጊዜ አገልግሎት በቤተ መንግሥቱና ቤተ ክህነቱ ከግንዛቤ ውስጥ ገብቶ በ1950 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው የደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል ቤተክርስቲያንን እንዲያስተዳድሩ ተሾሙ:: በዚሁ ደብር በማስተዳደር ላይ ሳሉ ሐምሌ 12 ቀን 1952 ዓ.ም በተደረገው የጳጳሳት ምርጫ ተመርጠው ሐምሌ 17 ቀን 1952 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ አንብሮተ እድ «አባ ሰላማ ኤጲስ ቆጶስ» ተብለው ተሾሙ::

እንደ ተሾሙም የተሰጣቸው ሀገረ ስብከት ጉፋና ሐመር ባኮ ነበር:: በወቅቱ አካባቢው ገና ስብከተ ወንጌል በወግ ያልተዳረሰበት ስለ ነበረ ብፁዕነታቸው ወደ አካባቢው ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ በትጋት የሠሩት ስብከተ ወንጌል በአካባቢው እንዲዳረስ በማድረግ ነበር:: አካባቢውን ቀድሞም ያውቁት ነበረና ተራራ ሸለቆው ሳይበግራቸው፣ የሕዝቡ እንግዳ ባሕልና ቋንቋ ሳያስቸግራቸው እንደ

www.ethiopianorthodox.org

አሁኑ የትራንስፖርት ዘዴ ባልተስፋፋበት በዚያ ጊዜ ወጥተው ወርደው አስተምረዋል። በትምህርታቸውም በርካታዎችን ወደ ክርስትና መልሰው የክርስቶስ ተከታዮች አድርገዋል።

ብፁዕ አቡነ ሰላማ ተጎራሚ፣ ደግና በሰዎች መካከል ሰላም እንዲጸና በእጅጉ የሚፈልጉና የሚጸልዩ ለዚህም የቻሉትን ሁሉ ያደርጉ የነበሩ እስታራቂ አባት እንደ ነበሩ የሚያውቋቸው ሁሉ በአንድ ቃል ይመሰከሩላቸዋል። የተሰጣቸው ጸጋ ይህንንና ይህን የመሳሰለው ነበር።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ሁለተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በወታደራዊው መንግሥት ከመንበራቸው በተነሡ ጊዜ ለቤተ ክርስቲያኗ ምትክ የሚሆን ፓትርያርክ ስትመርጥ በሐዋርያዊ ተግባራቸው፣ በንጽሕናቸውና በቅድስናቸው ብቁዎች ናቸው ተብለው ከተመረጡት ዕጩ ፓትርያርኮች መካከል ብፁዕነታቸው አንዱ ነበሩ።

ብፁዕ አቡነ ሰላማ ለቆሙለት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መሳካት ከቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር ጋር ለመምከር ከሀገረ ስብከታቸው ወደ አዲስ አበባ ሲገሠግሉ ለኅልፈታቸው ምክንያት የሆነ የመኪና አደጋ ደረሰባቸው። መላ ዘመናቸውን በጾምና በትኅርምት የኖሩት ብፁዕነታቸው የደረሰባቸውን አሠቃቂ የመኪና መገልበጥ አደጋ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ለመቋቋም የሚችል ሰውነት አልነበራቸውም። አደጋው እንደ ደረሰባቸው ወዲያውኑ ወደ ሆስፒታል ተወስደው ዕርዳታ እንዲያገኙ ቢደረግም ጥረቱ አልሳካ ብሎ በተወለዱ በ72 ዕድሜያቸው ነሐሴ 15 ቀን 197ሀ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። የቀብራቸው ሥነ ሥርዓትም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት ነሐሴ 17 ቀን 1970 ዓ.ም በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተፈጽሟል።

ምንም እንኳን በሀገረ ስብከታቸው የሚኖረው ምእመን በረከት እንዲያገኝ በሚል ሊቃነ ጳጳሳት ሲያርፉ በሀገረ ስብከታቸው መቀበር አለባቸው ብሎ ቅዱስ ሲኖዶስ በወሰነው መሠረት ይኸው በሌሎች ብፁዓን አባቶች ሲፈጸም ቢቆይም ብፁዕነታቸው የተቀበሩት ደብረ ሊባኖስ ነበር። ጉዳዩን በቅርበት የሚያውቁት እንደ ሚገልጹት ይሀ የሆነበት ምክንያት ነበረው። ብፁዕነታቸው በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ የሚመኙትና ስዕለት ሲሳሉለት፣ በጸሎታቸውም ለእግዚአብሔር ሲያሳስቡት የነበረ ነገር ቢኖር ባረፉ ጊዜ ደብረ ሊባኖስ ገዳም መቀበርን ነበር። ምንም እንኳን እሳቸውም ያጸደቁት የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ቢኖርም ይህንን ፍላጎታቸውን በየጊዜው እያነሱ ለወንድሞቻቸው ይናገሩ ነበር ይባላል። እንዲያውም በንግግራቸው «እንዲየው ያንን ውሳኔ ማን በሻረልኝ?» እያሉ ከቀልድ ጋር አምርረው ይናገሩ ነበር አሉ። ይህንን ፍላጎታቸውን ይዘው ከላይ እንደ ተገለጠው ከሀገረ ስብከታቸው ተነሥተው ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ በደረሰባቸው የመኪና አደጋ አዲስ አበባ በሕክምና ሲረዱ ቆይተው እዚሁ ያርፉሉ። በእርግጥ እዚህ ላይ መገለጥ ያለበት ብፁዕነታቸው በደረሰባቸው የመኪና አደጋ በውጭ የሚታይ ጉዳት በሰውነታቸው ላይ አልደረሰባቸውም ነበር። ይሁን እንጂ የመኻል እናታቸውን ተገጭተው ኖሮ ደም ወደ አዕምሮአቸው የውስጥ ክፍል በመፍሰሱ እንደሆነ ይነገራል። ግጭቱ ከደረሰባቸው ከቀናት በኋላ ሆስፒታል የገቡበትም ምክንያት ራሴን እመመኝ ብለው ነው ይባላል።



ዕረፍታቸው በክረምት ስለ ነበር ለአንድ ሊቀ ጳጳስ የሚገባው ጸሎተ ፍትሐት በመንበረ ትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሲፈጸም ካደረ በኋላ በነበረው ውሳኔ መሠረት እስከሬናቸው በመኪና ተጭኖ ወደ ሀገረ ስብከታቸው ጉዞ ተጀመረ። ነገር ግን ምንም እንኳን መንበረ ጵጵስናቸው ያለበት የአርባ ምንጭ ከተማ ሕዝብ መቃብራችውን ቆፍሮ ሰፊ ዝግጅት አድርጎ በመጠባበቅ ላይ ቢገኝም አዋሽ ወንዝ በመሙላቱ መንገድ ላይ መኪናው መሻገር አልቻለም። እስከ ሚጎድል ቢጠበቅም መጉደል ባለመቻሉ የመልስ ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ይደረጋል። ችግሩን ያጤነው ቤተ ክህነቱም ኤሊኮፍተር ከመንግሥት በመጠየቅ እስከሬናቸው በሰማይ እንዲሔድ ለማድረግ ይሞከራል። ነገር ግን አሁንም በክረምቱ የተነሣ ኤሊኮፍተሩ የሚያርፍበት ቦታ በጉም በመሸፈኑ ሲሳካ አልቻለም። በዚህ ጊዜ የብፁዕነታቸውን የረጅም ጊዜ በደብረ ሊባኖስ የመቀበር ፍላጎትና ጉጉት የሚያውቁ አባቶች ነገሩን በማድነቅ ደብረ ሊባኖስ እንዲቀበሩ አደረጉ። የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን። አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

# 3.25. ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ቀዳማይ

## ሊቀ ጳጳስ

## /1892 - 1979 ዓ.ም/





ሊቀ ሥልጣናት ቄርሎስ ተስፋይ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ በቀድሞው ትግሬ ጠቅላይ ግዛት አጋሜ አውራጃ ቅልዓት መንበሮ በሚባል ቦታ በ1892 ዓ.ም ተወለዱ:: የአባታቸው ስም አቶ ተስፋይ በፈቃዱ፣ የእናታቸው ስም እመት ለምለም ገብረ ሚካኤል ይባል ነበር::

ወላጆቻቸው ገና በሕፃንነታቸው ስለተለያዩ ዓዲኧላ ወረዳ ጋዕቤን ተብሎ በሚታወቅ መንደር ከእናታቸው ጋር አድገው ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ወደ ኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ተሻግረው አባ ወልደ ሚካኤል ከሚባሉ መምህር ንባብና ጸዋትወ ዜማ እየተማሩ አደጉ:: ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ሔደው ከግብፃዊው ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ:: በተቀበሉት ክህነትም ባደጉበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለሦስት ዓመት ያህል ሲያገለግሉ ቆዩ:: ከዚያም በ1913 ዓ.ም ትምህርታቸውን ለማስፋፋት ወደ ታላቁ የደብረ ቢዘን ገዳም ሔደው አባ ወልደ እናንያ ይባሉ ከነበሩ መምህር የቅዳሴ ትምህርታቸውን ቀጠሉ:: ከትምህርቱም ጋር በገዳሙ መነኰሳት የሚሰጣቸውን ሥራ እየሠሩ ሲያገለግሉና ሥርዓተ ገዳምን ሲማሩ ቆዩ::

በዚህ ዓይነት የጀመሩትን የቅዳሴ ትምህርት ወደ ማጠናቀቅ ሲደርሱ በ1916 ዓ.ም ወደ ግብፅ ሔደው ገዳማትን ለመጎብኘት አሰቡ:: እንዳሰቡትም በእግራቸው እስከ ከሰላ፤ ከዚያም በባቡር በፖርት ሰዒድ አድርገው ወደ እስክንድርያ ሔደው ጥንታውያኑን የግብፅ ገዳማት በመጎብኘት በተለይ ዲር ቦርሞስ በሚባለው ገዳም ለአንድ ዓመት ያህል በመቆየት ሥርዓተ ገዳማቸውንና ቋንቋቸውን ተማሩ::

ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ከግብፅ ወደ ሀገራቸው ከመመለሳቸው በፊት በወቅቱ የእስክንድርያ ፓትርያርክ የነበሩት አባት ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን የመሳለሙን አጋጣሚ ስለፈጠሩላቸው በዚያው ወደ ኢየሩሳሌም አቀኑ:: በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ቅዱሳት መካናትን ከተሳለሙ በኋላ በዴር - ኤል - ሡልጣን ገዳም ለአንድ ዓመት ያህል በዲቁና ሲያገለግሉ ቆዩ:: ከዚያም በ1918 ዓ.ም ከቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ወደ ሀገራቸው ተመለሱ:: እንደ ተመለሱም ወደ ቀደመ ገዳማቸው ደብረ ቢዘን በመሔድ በ27 ዓመት ዕድሜያቸው መጋቢት 13 ቀን 1918 ዓ.ም. መዓርገ ምንኩስናን ተቀበሉ:: በዓመቱም ኅዳር 12 ቀን 1919 ዓ.ም ከአቡነ ማቴዎስ መዓርገ ቅስናን ተቀብለው በደብረ ቢዘን ገዳም ሽማግሌዎችን በመጦር፣ ደካሞችን በመርዳት፣ በአጣኝነት ለአራት ዓመታት ያህል ቆዩ:: በዚህ ቆይታቸው በገዳሙ ያስተምሩ ከነበሩት መምህር ወልደ ሥላሴ ዘንድ ቅኔን ከነአገባቡ በሚገባ አጠናቀቁ::

www.ethiopianorthodox.org

ማኅበሩም የብፁዕነታቸውን ቅንና ደገኛ ተግባር ተመልክቶ በ1923 ዓ.ም በትግሬ ጠቅላይ ግዛት ይገኝ የነበረውን የደብረ ቢዘን ርስተ ጉልት ደብረ ገነትን እንዲያስተዳድሩ ሾማቸው:: ሹመቱን በአኰቴት የተቀበሉት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስም በተሾሙበት ደብር በቅንነት ሲያገለግሉ ቆዩ:: ስለ አገልግሎታቸውም በአካባቢው ባለሥልጣኖች የተለያዩ ሽልማቶች ተበርከተውላቸው ነበር::

ወራሪው የኢጣሊያ ጦር ሀገራችንን በትግራይ በኩል በግፍ በወረረ ጊዜ በአጋጣሚ ብፁዕነታቸው ከንጉሠ ነገሥቱ ለደብረ ቢዘን ገዳም የተበረከተውን የገንዘብ ርዳታ ለመወሰድ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ነበር:: የርዳታውን ገንዘብ ይዘው ወደ ደብረ ቢዘን ገዳም ሲመለሱ የኢጣልያ ጦር ይዟቸው ኖሮ አንተ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለላይ ነህና ከገዳሙ እንዳትወጣ ብሎ ለተወሰኑ ዓመታት ከገዳማቸው እንዳይወጡ ተደርገው እንደ ነበር ይነገራል:: በመጨረሻ ግን በወራሪው የኢጣሊያ መንግሥት ትእዛዝ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የራሳቸውን ጳጳሳት እንዲሾሙ በተደረገ ጊዜ መስከረም 6 ቀን 1932 ዓ.ም ከተመረጡት ኤጲስ ቆጶሳት አንዱ በመሆን «ጳጳስ ዘኤ ርትራ» ተብለው ወደ ዚያው በመሔድ አገልግሎታቸውን ቀጠሉ:: ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ በኤርትራ በቆዩባቸው ዓመታት ለሕዝበ ክርስቲያኑ ሰፋ ያለ አገልግሎት ሲያበረክቱ እንደ ቆዩ ይነገራል:: ከእነዚህም ውስጥ አስመራ በምትገኘው ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ አንድ መንፈሳዊ ት/ቤት አሠርተዋል፣ በአስመራ ከተማ ምንም እንኳን በጊዜው የተጠናከረ ባይሆንም «ፍኖተ ሐዋርያት» በሚል ሥያሜ የካህናት ማኅበር አቋቁመዋል:: ይህ ማኅበር በኋላ በብፁዕ አቡነ ማርቆስ ለብሳቢነት «ማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት» በሚል እንደ ገና ተቋቁሞ ሰፋ ያለ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል::

ኤርትራ ከኢጣልያ ቅኝ ግዛት ወጥታ በእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ሥር በቆየችባቸው ዓመታት የእንግሊዝ መንግሥት ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ ጋር ተዋሕደው መኖር እንደ ሚፈልጉ ስለ ተገነዘበ ሕዝቡን በመከፋፈል በራሱ ችግር ብቻ ታጥሮና ተዳክሞ እንዲኖር የማድረግ ሥልት ተከትሎ ነበር:: በዚህ ጊዜ ሕዝቡ በቅኝ ገዥው መንግሥት ከፋፍሎ የመግዛት ሥልት ሳይደናገር አንድነቱን አጠናክሮ ወደ እናት ሀገሩ ኢትዮጵያ እንዲቀላቀል ከፍተኛ አባታዊ ምክርና ትምህርት ይሰጡ ነበር ይባላል:: የእንግሊዝ መንግሥትም ያሰራቸውን እንዲፈታ፣ «ኢትዮጵያ ወይም ሞት» በማለት ከእናት ሀገራቸው ጋር ለመዋሐድ ትግል የጀመሩትንም ማሳደዱን እንዲያቆም ከባለሥልጣናቱ ጋር በርከት ያሉ ደብዳቤዎች ተጻጽፈዋል::

ብፁዕነታቸው በዚህ ዓይነት ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ በኅዳር



ወር 1944 ዓ.ም ቀድሞ በደብረ ቢዘን ገዳማቸው፣ በወረራውም ወቅት ቢሆን የውስጥ አርበኛነታቸውን ቤተ ክህነቱም ሆነ ቤተ መንግሥቱ በመረዳቱ በ1944 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው በግርማዊ ጃንሆይ መልካም ፈቃድ የአሰቦት ገዳምን እንዲያስተዳድሩ ተሾሙ:: ሹመቱን በአኰቴት የተቀበሉት ብፁዕነታቸውም ወደ ገዳሙ ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ ለሁለት ዓመታት ልዩ ልዩ ደገኛ ተግባራትን አከናውነዋል::

ከሁለት ዓመታት አገልግሎት በኋላ አሁንም በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈቃድ በ1946 ዓ.ም ከአሰቦት ወደ መናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ተዛውረው በአስተዳዳሪነት እንዲያገለግሉ ሆኑ:: በዚያም እንደ ተለመደው ልዩ ልዩ ጠቃሚ ሥራዎችን በመሥራታቸው በ1948 ዓ.ም የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ኒሻን ከግርማዊ ጃንሆይ ተሸልመዋል::

ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ በነበራቸው ሠርቶ የማሠራት ብቃት በቤተ መንግሥቱም ሆነ በቤተ ክህነቱ ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኙ በመሔዳቸው በ1949 ዓ.ም የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሊቀ ሥልጣናት ሆነው ተሾሙ:: በከፍተኛ ድምፅ ተመርጠው በ1950 ዓ.ም የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አማካሪ ሆነው ሠርተዋል:: ከዚህም ጋር በዚሁ ዓመት በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤትና በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ገዳም በተቋቋመው የአስተዳደር ቦርድ በአባልነት እንዲሠሩ ተደርጓል:: በአባልነታቸው ባሳዩት ብቃትም በግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፈቃድ የቦርዱ ፕሬዚዳንትና የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ገዳም ሊቀ ሥልጣናት ሆነው ተሾሙ::

በመጨረሻም ሊቀ ሥልጣናትና የአስተዳደር ቦርዱ ፕሬዚዳንት ሆነው በመሥራት ላይ ሳሉ ሐምሌ 12 ቀን 1952 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ አንብሮተ ዕድ የከፋና ማጂ ጳጳስ በመሆን እንደ ገና በጵጵስና ተሾሙ::

ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ በሀገረ ስብከታቸው ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋ፣ ያላመኑ እንዲጠመቁ፣ ያመኑ እንዲጸኑ በማድረግ ተላል የማይባል ሥራን ሠርተዋል:: በዚህ ደገኛ አገልግሎታቸውም የሀገረ ስብከታቸውን ሕዝብ ፍቅር አትርፈው ይኖሩ ነበር:: በተለይ በሀገረ ስብከቱ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ከነበራቸው ጉጉት የተነሣ በ1958 ዓ.ም «የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናን ስብከተ ወንጌል ማኅበር» የተሰኘ ማኅበር በማቋቋም ስብከተ ወንጌል ያልደረሰው ሕዝብ እንዲደርሰው አድርገዋል:: በመላው ሀገረ ስብከቱ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች እንዲሠሩ

www.ethiopianorthodox.org

በማድረግም የካህናት የገቢ ሁኔታ ተሻሽሎ አገልግሎታቸው ላይ እንዲያተኩሩ አድርገዋል።

ብፁዕነታቸው የወጣቱን ትውልድ የቤተ ክርስቲያን ተረካቢነት በውል በመረዳታቸው በሀገረ ስብከታቸው ወጣቶች በልዩ ልዩ ማኅበራት እንዲደራጁ ከፍተኛ ምክርና ድጋፍ ይሰጡ ነበር ይባላል። በዚህም በ1960 ዓ.ም የጎሬ ደብረ ገነት ቅድስት ማርያም ወጣቶች ክርስቲያናዊ ማኅበርን፣ በ1963 ዓ.ም የመቱ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን «ብርሃነ ወንጌል» ማኅበርን፣ በ1970 ዓ.ም የበደሌ መድኃኔ ዓለም «ፍኖተ ብርሃን» ማኅበርን፣ በዚያው ዓመት በያዩ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን «ፍሬ ተዋሕዶ» ወጣቶች ማኅበርን አቋቁመዋል። ካቋቋሙም በኋላ አዳራሽ እንዲሠራላቸው፣ የሚማማሩበት መጽሐፍ ቅዱስ በብዛት እንዲያገኙና መምህራን እንዲመደቡላቸው በማድረግ አሳቸውም እየተገኙ ይመክሯቸውና ያስተምሯቸው ነበር ይባላል።

ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ በሌሎች አባቶች ብዙም ያልተለመደ አንድ አርአያነት ያለው ልምድ ነበራቸው ይባላል። ይኸውም የዕለት ከዕለት ውሏቸውን እየመዘገቡ ያስቀምጡ ነበር። በሕይወት ዘመናቸው በመጻፍ ያጠራቀሙት የዕለት ከዕለት ውሎ ዘገባ /diary/ ባሬ አቶ አብርሃ ገ/ሕይወት በተሰኙ የብፁዕነታቸው ተማሪ እጅ ይገኛል።

ብፁዕነታቸው በሕይወት ዘመናቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያንንና ሀገርን በማገልገል ላበረከቱት ሰፊ አስተዋጽኦ በተለያዩ ጊዜያት ልዩ ልዩ ሽልማቶችን አግኝተዋል። በመጨረሻም በዕድሜያቸው መግፋት የተነሣ በአደባባይ ይሰጡት የነበረውን አገልግሎት በማቆም ከአዲስ አበባ ወደ አስመራ ሔደው በጸሎት ቆይተው ጥር 23 ቀን 1979 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ሥርዓተ ቀብራቸውም ተምረው ባስተማሩበትና ልብሰ ምንኩስና በለበሱበት ታላቁ የደብረ ቢዘን ገዳም ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ የገዳማት አበምኔቶች፣ የመንግሥት ባለ ሥልጣኖችና በርካታ ምእመናን በተገኙበት ተፈጽሟል። የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን። አሜን።



# 3.26. ብፁዕ አቡነ አብርሃም ካልአይ ሊቀ ጳጳስ

## /1905 - 1995 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

የቀድሞ ስማቸው መምህር ጥበቡ ምሕረቴ ይባል ነበር:: ብፁዕ አቡነ አብርሃም ከአባታቸው ከብላታ ምሕረቴ ትርፌና ከእናታቸው ከወ/ሮ በሰጠች ጸዳል ኅዳር 13 ቀን 1905 ዓ.ም በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ደብር ቅዱስ እንድማጣ ኢየሱስ ከተባለ ቦታ ተወለዱ::

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ በተወለዱበት ደብር ከፊደል እስከ መዝሙረ ዳዊት ያለውን የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርት አባ ተገኝ ወልደ ጊዮርጊስ ከተባሉ አባት ተማሩ:: ከዚያም ትምህርታቸውን በማስፋፋት እዚያው ትውልድ ሀገራቸው አካባቢ ንጎት ኢየሱስ ከተባለ ደብር መምህር በትሩ፣ መምህር አገሩና መምህር ከንፉ ከተባሉ መመህራን ምዕራፍን፣ ጾመ ድጓንና ድጓን ተማሩ:: ከዚህ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ከግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ ከብፁዕ አቡነ ማቴዎስ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ::

ከዚህ በኋላ ወደ ጎጃም ተመልሰው ወደ ቅኔ ትምህርት ቤት በመግባት በየረዝ ቅዱስ ሚካኤል ከመምህር ልሳነ ወርቅ፣ በብቸና ቅዱስ ጊዮርጊስ ከመምህር ውብሸት፣ በደብረ ኤልያስ ከመምህር ገብረ ሥላሴ ከንፌ በመዘዋወር ቅኔን ከነአገባቡ ጠንቅቀው ተማሩ::

ቅኔውን በተገለጠው ሁኔታ ያጠናቀቁት ብፁዕ አቡነ አብርሃም እንደ ገና ወደ ዜማ ቤት በመግባት በደብረ ማርቆስ ከርእሰ ደብር ጸጋ ገብረ ሥላሴ ድጓውን ሦስት ጊዜ ዘልቀው በመምህርነት ተመረቁ:: ቀጥለውም በደብረ ኤልያስ ከመምህር እንደሻው አቋቋም ከተማሩ በኋላ ወደ ጎንደር ተሻግረው በአፈረ ዋናት በላና ቅዱስ ጊዮርጊስ ከመሪ ጌታ ፍሥሐ መንገሻ ዝማሬንና መዋሥዕትን አጠኑ::

ከዚህ በኋላ ትምህርታቸውን በመቀጠል ግንቦት 21 ቀን 1924 ዓ.ም ወደ ጎንደር ከተማ ገብተው በመካነ ስማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ከመሪ ጌታ አካሉ የአቋቋም ትምህርት ከአነ ሙሉ ይትበሃሉ ተምረው ተመረቁ:: በዚያውም በደንቀዝ ማርያም ከመምህር ተክለ ማርያም ቅዳሴን ተማሩ::

ብፁዕ አቡነ አብርሃም አሁንም ትምህርታቸውን ለማስፋፋት በ1928 ዓ.ም ወደ ትርጓሜ መጻሕፍት ቤት በመግባት በጎንደር ግምጃ ቤት ማርያም ከመምህር ክፍለ ማርያም ይመር የኪዳንና የትምህርተ ኅቡአትን፣ የሐዲሳትን ትርጓሜ በሙሉ ከአለቃ ገብረ ኢየሱስ፣ የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜ፣ ከመምህር ተመስገን፣ ሃይማኖተ አበውንና ቄርሎስን፣ ከመምህር ጌታሁን፣ የዳዊት ትርጓሜን ከመ/ር አፈ ወርቅ ገብረ ሥላሴ የኢሳይያስ ትርጓሜን ተምረው በመምህርነት ተመረቁ::



ብፁዕ አቡነ አብርሃም ከላይ በቀረበው ዓይነት በዕውቀት መንፈሳዊ ከተገነቡ እና ማንነታቸውን ከመረመሩ በኋላ የአባቶቻቸውን ሥርዓት ለመፈጸም ወደ ዋልድባ በጻር ኪዳነ ምሕረት በመሔድ እንደ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የአመክሮ ጊዜያቸውን አጠናቀው በወቅቱ በገዳሙ አበ ምኔት መዓርገ ምንኩስናን ተቀበሉ:: ከዚያም ወደ ሐረር በመምጣት በወቅቱ የሐረር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ እንደ ራሴ ከነበሩት ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ መዓርገ ቅስናን ተቀበሉ::

ቅስናን ከተቀበሉ በኋላ በዚያው በሐረር ሀገረ ስብከት የዓለማያ ቅዱስ ማርቆስ፣ በሐረር ከተማ የደብረ ገነት መድኃኔ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት አስተዳደሪ በመሆን በየተራ ተሹመው አገልግለዋል:: ከዚህም ጋር ሐረር ይገኝ በነበረውና በቤተ ክርስቲያኗ ተቋቁሞ በነበረው በልዑል ራስ መኰንን መንፈሳዊ ት/ቤት በግእዝ ሰዋስውና የቅዱሳት መጻሕፍት መምህር በመሆን አገልግለዋል::

ብፁዕ አቡነ አብርሃም በዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል ላይ ሳሉ ሐምሌ 18 ቀን 1952 ዓ.ም ሰባት ቆሞሳት ተመርጠው ኤጲስ ቆጶሳት ሆነው በተሾሙ ጊዜ እርሳቸው አንዱ በመሆን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ አንብሮተ እድ በጊዜው አጠራር ከምባታ፣ ሐይቆችና ቡታጅራ አውራጃ ኤጲስ ቆጶስ ሆነው ተሾሙ::

ብፁዕነታቸው ወደ ተሾሙበት ሀገረ ስብከት ከሔዱ ጀምሮ የተለያየ እምነትና ስብከት እምልኮት የነበራቸውን በማስተማር፣ በማሳመንና በማጥመቅ የቤተ ክርስቲያናችን አባላት እንዲሆኑ አድርገዋል:: በወቅቱም ይህ መልካም አገልግሎታቸው በጋዜጣ፣ በሬድዮና በመሳሰሉት የመገናኛ ብዙኃን በሰፋት ይሠራጭ ነበር::

በ1955 ዓ.ም ወደ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት እንዲዛወሩ ተደርጎ እስከ 1976 ዓ.ም ድረስ በእንደራሴነትና በሊቀ ጵጵስና ተገቢውን አባታዊ አገልግሎት አበርክተዋል:: ይህም አገልግሎት ሰበካ ጉባኤያትን በማቋቋምና በማጠናከር፣ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን በማሠራት፣ ኢ አማንያንን አስተምሮና አሳምኖ በማጥመቅ የሰጡትን ያልተቆጠበ አገልግሎት ያጠቃለለ ነው:: ከዚህም ጋር ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ መመሪያን በመቀበል በሐረር ከተማ የነበረው መንፈሳዊና ዘመናዊ ት/ቤት በአቋሙ እንዲሰፋፋና እንዲያድግ አድርገዋል::

ብፁዕነታቸው ከመስከረም 15 ቀን 1976 ዓ.ም ጀምሮ ከሐረርጌ መንበረ ጵጵስና ወደ አዲስ አበባ መንበረ ፓትርያርክ ተዛውረው የመላ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

www.ethiopianorthodox.org

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ ሥራ የበላይ ሐላፊ ሆነው ሠርተዋል:: በዚህም ጊዜ ሰኔ 8 ቀን 1980 ዓ.ም በቅዱስ ሲኖዶስ ተመርጠው ለዓርባ ቀናት ያህል ዐቃቤ መንበረ ፓትርያርክ ሆነው አገልግለዋል:: ከዚህም በኋላ ከየካቲት 1 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤልና የታዕካ ነገሥት በኣታ ለማርያም አድባራት የበላይ ሐላፊ ሆነው እንዲሠሩ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ፈቃድ ተሹመው ለተወሰኑ ዓመታት አባታዊ አገልግሎት ሰጥተዋል::

ብፁዕነታቸው ሀብተ ዜማ የተሰጣቸው አባት ነበሩ:: በዚህም በዕድሜ ምክንያት ሀቅማቸው እስከ ደከመበት ጊዜ ድረስ በሀበይት በዓላት ማሕሌት፣ በአጽዋማት ጊዜ ደግሞ ሰዓታት ደከመኝ ሳይሉ ይቆሙ ነበር:: በቅርብ የሚያውቋቸው እንደ ሚናገሩት ብፁዕ አቡነ አብርሃም ደግነትና ትሕትና ያበዙ ነበር::

ብፁዕ አቡነ አብርሃም የጤና መታወክ ካጋጠማቸው ጊዜ ጀምሮ በመኖሪያ ቤታቸው ቢወሰኑም አእምሮአቸው ሳይዛባ፣ እንደበታቸው ሳይረታ እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው ቆይተዋል:: አልፎ አልፎም በቅርብ ረዳቶቻቸው ድጋፍ ወደ መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመሔድ ተወዳጁን ጣዕመ ዜማቸውን ያሰሙ ነበር::

ብፁዕነታቸው አብሯቸው የሚቀድስ ቄስም ሆነ ዲያቆን ቀለም ቢገድፍ የተሳሳተውን እያስተካከሉ ይሔዱ ነበር::

ብፁዕ አቡነ አብርሃም በዚህ ዓለም ይኖሩበት ዘንድ ተሰፍሮ የተሰጣቸው ዕድሜ ሲጠናቀቅ ነሐሴ 29 ቀን 1995 ዓ.ም በተወለዱ በ90 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞተ ሥጋ ተለዩ:: ዕርጅና ያሳሸነፈው የብፁዕ አቡነ አብርሃም በያሬዳዊ ጣዕመ ዜማ የታሸ አንደበት ዳግም ላንሰማው ተዘጋ::

የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ነሐሴ 30 ቀን 1995 ዓ.ም በመን በረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ፣ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት ወኤጲስ ቆጶሳት፣ የጠቅላይ ቤተ ክህነት የየመምሪያውና የየድርጅቱ ሐላፊዎች፣ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች፣ ካህናት፣ መዘምራንና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች እንዲሁም ምእመናን በተገኙበት ተፈጽሟል:: የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን:: አሜን::



# 3.27. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ሣልሳይ ሊቀ ጳጳስ

## /1903 - 1995 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

መምህር ወልደ ሚካኤል ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ከአባታቸው ከአቶ /በኋላ አባ/ ገብረ እግዚአብሔር እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ዓምባነሽ መርሻ ታኅሣሥ 2ሀ ቀን 1903 ዓ.ም ተወለዱ። ቦታውም በቀድሞው በጌምድር ጠቅላይ ግዛት በስሜኑ ክፍል ሳንግ ቆላ ወገራ ልዩ ስሙ እየሩ በአታ ማርያም ይባላል።

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በወላጆቻቸው ቤት በእንክብካቤ አድገው ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በተወለዱበት አካባቢ በሚገኘው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አለቃ ተካልኝ ከተባሉ መምህር ዘንድ የንባብ ትምህርታቸውን ተማሩ። ልክ በ12 ዓመታቸው ከግብፃዊው ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ። ከዚያም ትምህርታቸውን ከዚያው አለቃ ተካልኝ ጋር በመቀጠል ውዳሴ ማርያም፣ ጸዋትወ ዜማ፣ ጾመ ድጓ፣ አቋቋምና መስተጋብዕ ጠንቅቀው ተማሩ።

ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት ወደ ዋልድባ አብረንታት ገዳም ወረዱ። በእርግጥ ወደዚያ ከጓደኞቻቸው ጋር ሲሔዱ እንመነኩሳለን ብለው አልነበረም። ከዚያ ሲደርሱ ግን የመነኩሳቱ በተለይ የወጣት መነኩሳት ሕይወት በእጅጉ ማረካቸው። በዚህ የተነሣም ብፁዕነታቸውና ጓደኞቻቸው የገዳሙን አባቶች ካላመነኩሳችሁን ብለው ጠየቁ። የገዳሙ አባቶችም ምንም እንኳን ሕፃናት ናቸውና እንዲቆዩ ቢነግሯቸውም ሐሳባቸውን ባለመቀበላቸው እንደ ፈቀዳችሁ ይሁን ብለው አመነኮሷቸው።

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ከትውልድ ሀገራቸው ወደ ዋልድባ አብረዋቸው ከሔዱት ወንድማቸው ጋር መዓርገ ምንኩስናን ከተቀበሉ በኋላ ከዚያው ዋልድባ አካባቢ ወደ ሚገኘው እንደልሻ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ሔደው ገዳሙንና በአካባቢው የሚገኙ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን ሲያገለግሉ ቆዩ። ከዚያም ትምህርታቸውን ለማስፋፋት ወደ ደብረ ዓባይ ሔዱ።

በዚያም የቅዳሴ ትምህርታቸውን የኔታ ገብረ ኪዳን ከተባሉ መምህር ዘንድ መከታተል ጀመሩ። ይሁን እንጂ ትምህርታቸውን በጥሙና እየተከታተሉ ሳለ ቀድሞም ከገዳማቸው ወጥተው እንዲሔዱ ያልወደዱት የእንዳልንሻ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አባቶች መልሰው ወደ ጎንደር ይዘዋቸው ሔዱ።

የቅዳሴ ትምህርታቸውን አቋርጠው የተመለሱት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል እንደ ቀድሞው ሁሉ ከሚወዷቸው ማኅበረ መነኮሳት ጋር በመሆን የተለመደ አገልግሎታቸውን እንደ ቀጠሉ በ1925 ዓ.ም ልዕልት ዘነበ ወርቅ ሲሞቱ የገዳሙ አበምኔት ጃንሆይን እግዚአብሔር ያጥናዎት ለማለት ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ ብፁዕነታቸ



ውም የአበምኔቱ ተከታይ ሆነው ወደ አዲስ አበባ መጡ።

አዲስ አበባ እንደ ደረሱም ደብረ ዓባይ ላይ በእንደልሻ ኪዳነ ምሕረት ወንድሞቻቸው አማካይነት ተለይተዋቸው የሔዱትን የቅዳሴው ምስክር የኔታ ገብረ ኪዳንን በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት በአታ ለማርያም ገዳም ጉባኤ ዘርግተው ሲያስተምሩ አገኙዋቸው። ቀድሞም ሲማሩ የጓጉለት ትምህርት ነበረና ተከትለዋቸው ወደ አዲስ አበባ የመጡትን አበ ምኔት ትተው ወደ የኔታ ገብረ ኪዳን ጉባኤ በመግባት ትምህርታቸውን እንደ ገና ቀጠሉ። የቅዳሴውን ትምህርት በአጭር ጊዜ አጠቃለው በመምህርነት ከተመረቁ በኋላ የእርሳቸው ረዳት ሆነው ማስተማር ጀመሩ።

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ከሊቁና ደጉ መምህራቸው ጋር በማስተማር ላይ ሳሉ የኢጣልያ ጦር ኢትዮጵያን ወረረ። በዚህን ጊዜ የቀድሞው ሊቀ ሊቃውንት ገብረ አብ /በኋላ ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ/ የበአታ ለማርያም ገዳም አስተዳዳሪ ነበሩና ማይጨው ከጃንሆይ ጋር ሲዘምቱ አብረው እንዲዘምቱ አደረጓቸው። ከዚያም የጦርነቱ ሁኔታ አልሆን ብሎ ንጉሡና የተከተሏቸው ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ብፁዕነታቸው ላስታ ላይ ታመው ቀሩ። ከወራት ቆይታ በኋላ ምንም እንኳን ከሕመማቸው ቢያገግሙም አካባቢውን ለለ ተላመዱትና እንዲሁ ባሕታዊም ከዚያው እንዲቆዩ ለለ ነገራቸው ወደ አዲስ አበባ መምጣታቸውን ትተው በዚያው ባረፉበት ደብር ጉባኤ ዘርግተው ማስተማር ጀመሩ።

በመምህርነት የተመረቁበትን የቅዳሴ ትምህርት እያስተማሩ በአንድ ጎን ቅኔን፣ ሐዲሳትንና ባሕረ ሐሳብን ያሄዱ ነበር። በዚህ ዓይነት አምበቱ የመከራ ዘመን አልፎ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ወደ አዲስ አበባ እንደ ተመለሱ ሲሰሙ ደቀ መዛሙርቶቻቸውን አስከትለው ወደ አዲስ አበባ መጡ።

አዲስ አበባ እንደ ደረሱም ያኔ በበአታ ተሹመው የነበሩት ሊቀ ሊቃውንት ገብረ መስቀል /ኋላ አቡነ ዮሐንስ/ በአታ ላይ ቅዳሴ እንዲያስተምሩ ጋበዟቸው። ብፁዕነታቸውም ግብዣውን በአኩቴት በመቀበል ከመሸምገላቸው የተነሣ ወደ አገሬ ሔጄ እሞታለሁ ብለው ወንበራቸውን አጥፈው ወደ ደብረ ዓባይ በሔዱት የቀድሞ መምህራቸው የኔታ ገብረ ኪዳን ቦታ ተተክተው ቅዳሴ ማስተማር ጀመሩ።

ለዐሥር ዓመታት ቅዳሴ በማስተማር በርከት ያሉ ደቀ መዛሙርትን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ካበረከቱ በኋላ ምንም እንኳን ለረጅም ዓመታት ሲያስተምሩት ቢቆዩም የተረጣ የተገደፈ ያጥራል በሚል ሲከልሱት ወደ ደብረ ዓባይ ሔዱ። በዚያም ለሦስት

www.ethiopianorthodox.org

ወራት ያህል ከከለሉ በኋላ እግረ መንገዳቸውን ወላጆቻቸውንና ዘመዶቻቸውን ለመጠየቅ ወደ ትውልድ ሀገራቸው አቀኑ።

ከተለዩአቸው 14 ዓመት ያህል ከሆናቸው ወላጆቻቸው ጋር ሲገናኙ እናታቸውም ሆኑ አባታቸው መንኩሰው አገኙዋቸው። ከእነሱም ጋር ለአርባ ቀናት ከቆዩ በኋላ ተመልሰው ወደ አዲስ አበባ መጡ። አዲስ አበባ እንደ ደረሱም የተመደቡት በቀድሞው ቦታቸው ታዕካ ነገሥት በኣታ ለማርያም ሳይሆን የመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳምን እልቅና ነበር። ከእልቅናውም ጋር የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው አቡነ ቀሲስም ነበሩ።

በዚህ ዓይነት ለስድስት ዓመታት ያህል ካገለገሉ በኋላ ወደ መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም በእልቅና ተመድበው ተዛወሩ። በተሰጣቸው የማስተዳደር ጸጋም ገዳሙን በግሩም ሁኔታ በማገልገል ላይ ሳሉ በሐምሌ ወር 1952 ዓ.ም በተደረገው የጵጵስና ምርጫ ተመርጠው ከሌሎች ስድስት አባቶች ጋር በብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት አንብሮተ እድ መዓርገ ጵጵስናን ተቀበሉ።

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል መዓርጉን ከተቀበሉ በኋላ የተመደቡበት ሀገረ ስብከት ቦረና ነበር። በተሰጣቸው ሀገረ ስብከት ገቆዩባቸው አምስት ዓመታት ሕዝቡን አስተምሮ በማጥመቅ፣ አብያተ ክርስቲያናት ባልነበሩባቸው ቦታዎች በማሳነፅ፣ የሀገረ ስብከቱ መንፈሳውያን ወጣቶችን በማስተማር ክህነት በመስጠት ወደ አገልግሎት እንዲሠማሩ አድርገዋል። ከዚያም ወደ አርሲ ሀገረ ስብከት በመዛወር ለአንድ ዓመት አገልግለዋል።

ከአርሲ ቀጥሎ የተመደቡት ረዘም ላለ ጊዜ ወደ ቆዩበትና ከሀገረ ስብከቱ ካህናትና ምእመናን ጋር በመተባበር በርካታ ሥራዎችን ወደ ሠሩበት ኤርትራ ሀገረ ስብከት ነበር። ከ1959 ዓ.ም እስከ 1971 ዓ.ም በሀገረ ስብከቱ በሊቀ ጵጵስና ሲያገለግሉ አስተዳደራዊው መዋቅር መልክ እንዲኖረው፣ ቁጥራቸው ውስን የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት እንዲበራከቱ አድርገዋል።

ዋልድባ ሰቋር ኪዳነ ምሕረት ገዳም ምንም እንኳን በአንድ ስም ቢጠራም ዘጠኝ ደወል /ዘጠኝ ማኅበር/ ነበረው ይባላል። በዚህ የተነሣ እልፎ አልፎ ስይጣን በሚያበነሳባቸው ፈተና ማኅበራቱ እርስ በርስ ይጣሉ ነበር። ቅዱስ ሲኖዶስ ገዳሙ በአንድ ደወል /በአንድ ማኅበር/ ይጠቃለል ዘንድ ሲወስን ውሳኔውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የተመረጡት ብፁዕነታቸው ነበሩ። ታዲያ ብፁዕነታ ቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የጣለችባቸውን አደራ ይዘው ወደ ቦታው በመሔድ የተጣመመውን አቃንተው ማኅበራቱን እርስ በርስ አስማምተው በአንድ ገዳማዊ አስተዳደር እንዲተዳደሩ አድርገው መጥተዋል።



ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በእርጅና ምክንያት በስተ መጨረሻ ቤት ቢውሉም ለብዙ ዓመታት ወደ አስተዳደሯት መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመሔድ ሕዝቡን ይባርኩ ነበር። ምክርና ታሪክ ፈልጎ ወደ በኣታቸው ለሔደም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ይመክሩና ያስተምሩ ነበር። በዕድሜያቸው መጨረሻ ባደጉበት አካባቢ ደባርቅ ከተማ ላይ አዲስ የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በራሳቸው ገንዘብ አሠርተው ለሕዝቡ አበርክተዋል።

ዕድሜ እየተጫናቸው የሔዱት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በዚህ ዓለም ይኖሩበት ዘንድ የተሰጣቸው ዕድሜ ሲፈጸም ጥር 26 ቀን 1995 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። የቀብራቸው ሥነ ሥርዓትም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች፣ ካህናት፣ የሰንበት ት/ቤት መዘምራንና ምእመናን በተገኙበት ጥር 27 ቀን 1995 ዓ.ም በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ምድር ቤት ውስጥ በሚገኘውና በቁመተ ሥጋ ሳሉ እየሔዱ ውዳሴ ማርያም ሲደግሙበት በነበረው ሥፍራ መካነ መቃብራቸው ተፈጽሟል። የብፁዕነታቸው በረከት ይደርብን። አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

# 3.28. ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ቀዳማይ ሊቀ ጳጳስ

## /1911 - 1991 ዓ.ም/





ቀድሞ መምህር ገብረ ማርያም ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ በሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት ልዩ ስሙ ሰቀልት ምቅዋመ ማርያም በተባለ ቦታ ሰኔ 12 ቀን 1911 ዓ.ም ተወለዱ። አባታቸው መምህር ፈንታ ስምስም እናታቸው ደግሞ እመት ድንቅነሽ ውብነህ ይባሉ ነበር። እናታቸው የዓፄ ቴዎድሮስ የእኅት ልጅ እንደ ነበሩ ይነገርላቸዋል።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በተወለዱበት ደብር መምህር አፈ ወርቅ ከተባሉ ሊቅ ዘንድ እስከ ጸዋትወ ዜማ ተማሩ። ከዚያ በኋላ ግንቦት 16 ቀን 1927 ዓ.ም ከብፁዕ አቡነ አብርሃም ቀዳማዊ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ። ከዚያም ጎንደር ወደ ሚገኘው ማኅበረ ሥላሴ ገዳም በመሔድ ሥርዓተ ገዳምን ሲያጠኑ ቆይተው ነሐሴ 16 ቀን 1930 ዓ.ም የገዳሙ አበ ምኔት ከነበሩት መምህር ወልደ ሚካኤል የምንኩስናን መዓርግ ተቀበሉ።

ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ በዘመነ ወረራ ወደ ማኅበረ ሥላሴ ሲገቡ መልከ ቀና ነበሩና አንዳንድ መነኮሳት «ወረራውን ሸሽቶ የመጣ ከነገሥታት ዘር የሆነ ልጅ ይሆናል፤ እሱን ፈልጎ የመጣ ጠላት እንዳይፈጀን» በማለት ወደ ማኅበሩ እንዳይገቡ ከልክለዋቸው ነበር ይባላል። ይሁን እንጂ ብፁዕነታቸው በጥርጣሬም ቢሆን በገዳሙ ተቀባይነት አግኝተው በኋላ መናኝነታቸው ተረጋግጦ ሊመነኩሱና ቆይቶም የገዳሙ አበምኔት ሊሆኑ ችለዋል።

በነበራቸው ትምህርታቸውን የማስፋፋት ፍላጎት ከማኅበረ ሥላሴ በመነሣት ወደ ደብረ ዓባይ ወርደው በወቅቱ የታወቁ መምህር ከነበሩት መምህር ኪዳነ ማርያም ዘንድ ቅዳሴ ተማሩ። በመቀጠልም ከመምህር ተክለ መድኅንና ከእስቃ ዳዊት ዘንድ ትርጓሜ ዳዊትን ተማሩ። በመጨረሻም ጥር 20 ቀን 1938 ዓ.ም ከግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ መዓርገ ቅስናና ቁምስና ተቀበሉ።

ከዚያም በ1940 ዓ.ም ሥርዓተ ምንኩስና የፈጸሙበት የማኅበረ ሥላሴ ገዳም አበ ምኔት ይሆኑ ዘንድ በማኅበረ መነኮሳቱ ተመረጡ። እርሳቸውም ማኅበሩ የሰጣቸውን ሐላፊነት በእሺታ ተቀብለው ለስድስት ዓመታት አገልግለዋል። በዚህ ወቅት በገዳሙ አካባቢ የሚገኙትን የጉምዝ ብሔረሰብ አባላት በማስተማር አጥምቀዋል።

ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ከንጉሡ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቁት ኢትዮጵያ ከወራሪው የኢጣልያ መንግሥት ቁጥጥር ነጻ በወጣች ጊዜ ንጉሡ በሱዳን አድርገው ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ እግረ መንገዳቸውን ወደ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም በሄዱ ጊዜ ነበር። ከዚያ

www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ ጀምሮ ብፁዕነታቸው የንጉሡ ቀራቢ ነበሩ:: እንዲያውም በነገር ሁሉ እስከ መገበጽ ደርሰው ነበር ይባላል:: በእርግጥ ንጉሡ በተለይ መጀመሪያ አካባቢ ያለምንም ፍርሐት ይገበጿቸው ስለ ነበረና በመልከ ቀናነታቸው «የኢያሱ ልጅ ሳይሆን አይቀርም» እያሉ በጥርጣሬ ይመለከቷቸው ነበር ይባላል:: በኋላ ግን ዪት መጣቸውን በሚገባ ካወቁ በኋላ በእጅጉ ያቀርቧቸውና የጠየቁትን ሁሉ ይፈጽሙላቸው ነበር:: ብፁዕነታቸውም ይህንን ቀራቢነታቸ ውን በመጠቀም በአበምኔትነታቸው ንጉሡ ለገዳሙ እንዲያስቡ ያደ ርጉ እንደ ነበር ይነገራል:: በእርግጥ በወረራው ጊዜ ከኢትዮጵያ ገዳማት በፋሺስቱ ጦር ያልተደፈረና የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማም ያልወረደበት ገዳም በመሆኑ ንጉሡ ራሳቸው ለገዳሙ ልዩ አመለካ ከት ነበራቸው::

ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ በማኅበረ ሥላሴ ገዳም አበ ምኔት ነታቸው የሠሯቸው ጠቃሚ ሥራዎች ዜና ንጉሡም በቅርብ ያውቁ ነበርና በ1940 ዓ.ም በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ከማኅበረ ሥላሴ ወደ ጎጃም ጠቅላይ ግዛት በመሔድ በወቅቱ በሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር የጎጃም ጠቅላይ ግዛት መተከል አውራጃ የነገደ ጉምዝ የሕዝብ ዕድገት ሥራ አስኪያጅ በመሆን ተሾሙ:: በዚያም በቤተ መንግሥቱ የተሰጣቸውን ሐላፊነት ባለ መዘንጋት በርካታ ሰዎችን በማስተማር አጥምቀው የክርስትና እምነት ተከታይ እንዲሆኑ አድርገዋል:: ብዙ አብያተ ክርስቲያናትንና ት/ቤቶችንም አሠር ተዋል::

ይህንና የመሳሰለውን አገልግሎት በትጋት ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸውና ሀገራቸው ሲያበረክቱ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ሐምሌ 12 ቀን 1952 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ እንብሮተ ዕድ የኤጲስ ቆጳስነት መዓርግ ተቀበሉ:: የተሾሙትም በንጉሡ መራጭነትና አቅራቢነት እንደ ነበረ ይነገራል::

ከሹመቱም በኋላ የአሶሳ፣ የመተከልና የደንቢ ዶሎ ጳጳስ ሆነው ተመደቡ:: ወደ አህጉረ ስብከታቸው ከሔዱ ጀምሮም ቦታው ስብከተ ወንጌል በሚገባ ያልተስፋፋበት፣ አብያተ ክርስተያናት በደንብ ያልተስፋፉበት መሆኑን በመገንዘብ ቅድሚያውን ለእርሱ በመስጠት መንቀሳቀስ ጀመሩ:: ምንም እንኳን አህጉረ ስብከታቸው የተበታተነና ለቅኝት የማያመች ቢሆንም ብፁዕነታቸው ግን ደከመኝ ሠለቸኝ ሳይሉ ረጅም መንገድ በእግራቸውና በከብት ተጭነው እየተዘዋወሩ በርካታ ኢ አማንያንንና መናፍቃንን በማስተማር በጥም ቀት ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን አንድነት እንዲቀላቀሉ አድርገዋል:: በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን፣ የልማት ቦታዎችን አሳንፀዋል፣ አስፋፍተዋል::



በዚህ ደገኛ ተግባራቸው በንጉሠ ነገሥቱ ፊት የበለጠ ከፍ ከፍ ያሉት ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ በ1957 ዓ.ም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትእዛዝ ወደ ቅድስት ሀገር እየሩሳሌም በመሔድ የኢትዮጵያ ገዳማት ሊቀ ጳጳስ ሆነው እንዲሠሩ ተደረገ:: ብፁዕነታቸውም ወደ ኢየሩሳሌም ከሔዱ ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያናችን ከግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋር ለረጅም ዘመናት በትከራከርበት የነበረውን የዴር - ኤል - ሡልጣን ጉዳይ በማንቀሳቀስ ኢትዮጵያ የቦታው ባለቤት እንድትሆን በሕግ አስፈርደውላታል:: ከዚህም ጋር ለገዳሙ መተዳደሪያ የሚሆን የገቢ ምንጭ በመፍጠር ልዩ ግምት የሚሠጠው ሥራ ሠርተዋል::

ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ከኢየሩሳሌም የሰባት ዓመታት ፍሬያማ ቆይታ በኋላ በ1964 ዓ.ም ከኢየሩሳሌም ወደ ድሮው ሀገረ ስብከታቸው ከፋ ጅማ ተዛወሩ:: በዚያም ከሚያውቁት ሕዝብ ጋር እስከ 1970 ዓ.ም ድረስ በመቆየት አገለገሉ:: ይሁን እንጂ በ1970 ዓ.ም ወቅቱ ወታደራዊው የደርግ መንግሥት ቀይ ሽብር በሚል ወጣቱን የሚጨፈጭፍበት ይባስ ብሎም የወቅቱን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በግፍ የገደለበት በመሆኑ ብፁሰነታቸው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ተቃውሞአቸውን ማሰማት ጀመሩ::: በዚህም በወቅቱ ከነበሩት ባለሥልጣናት ጋር በመቃቃራቸው ጡረታ ወጥተዋል በሚል ከሥራ እንዲገለሉ ተደረጉ::

ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ምንም እንኳን ከመንበረ ጵጵስናቸው ቢነሡም ወደ ትውልድ ሀገራቸው ጎንደር በመሔድ ምእመናንን በማስተባበር የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታደሱ፣ አዳዲሶችም እንዲታነፁ አድርገዋል:: በአካባቢው ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን በማስፋፋት አብያተ ክርስቲያናቱ እንዲገለገሉ አድርገዋል:: በተለይ ጣና ሉስንዮስ በተባለው ቦታ የእርሻ መሬት ወስደው በማልማት የአካባቢው ሕዝብ እንዲጠቀም ከማድረጋቸው በተጨማሪ የሥራ እርአያ ሆነዋል:: ይሁን እንጂ በመጨረሻ ከአካባቢው ሕዝብ የተወሰኑ ሰዎች ሸፍተው ብፁዕነታቸው ገንዘብ የተረፋቸው ናቸው በማለት ቤታቸው ገብተው የከብር ልብሶቻቸውን ሳይቀር ዘርፈ ዋቸው፤ በመጨረሻ እሳቸውን ሊገድሏቸው ሲሉ በባርካ ወንዝ አቋርጠው ሕይወታቸውን ሊያተርፉ ችለዋል:: በዚህም እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ ያዝኑ ነበር ይባላል::

ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ከሀገረ ስብከቴ እንድለቅ ተደረግሁ ብለው ለአንዲት ቀንም ሳይከፋቸው ከላይ በተገለጠው ዓይነት በአገልግሎት ሲተጉ ቆይተው በ1980 ዓ.ም በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ውሳኔ ወደ ቀድሞ ቦታቸው እንዲመለሱ ተደርጎ ሀገረ ስብከታቸውን

www.ethiopianorthodox.org

ይዘው እስከ 1988 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ሲሰጡ ቆዩ።

ከሐምሌ ወር 1988 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የድሬዳዋና የምሥራቅ ሐረርጌ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በመሆን አገልግሎት መስጠት ጀመሩ። ወደ ድሬዳዋ ከሔዱ ጊዜ ጀምሮም ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ ከነበሩት አገልግሎታቸው ባሻገር በርካታ የልማት ሥራዎችን ሲያከናውኑ ቆይተዋል።

ወደ መጨረሻም ምንም እንኳን ዛሬ ታትሞ ለማየት ባይታደሉም ግብረ ሕማማት የተሰኘው ከግእዝ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ብፁዓን አባቶች እንዲታይ እንዲታተም ቤተ ክርስቲያን ስትወስን የጉባኤው ሰብሳቢ እሳቸው ሆነው በመመረጣቸው ሲያገለግሉ ቆይተዋል።

ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ በባሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሰላማ ጋባቸንት የኖሩበትንና ይንጉሰት የነበረውን ስብከተ ወንጌል ለሕዝቡ ለማዳረስ ግንቦት 12 ቀን 1991 ዓ.ም ከብፁዕ አቡነ ኤልያስና ሌሎች ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ጋር ሲጓዙ በደረሰባቸው ድንገተኛ የመኪና አደጋ በ80 ዓመት ዕድሜያቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ሥርዓተ ቀብራቸውም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ፣ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፣ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት አስተዳዳሪዎች፣ መምህራንና ካህናት፣ የሰንበት ት/ቤቶች አባላትና ምእመናን በተገኙበት ግንቦት 14 ቀን 1991 ዓ.ም በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተፈጽሟል። በእርግጥ ብፁዕነታቸው እንዲቀበሩ የሚፈልጉት አሰቦት ገዳም ነበር ይባላል። የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን። አሜን።



# 3.29. ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ቀዳማይ ሊቀ ጳጳስ

/1878 - 1953 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

መምህር ግርማ ጽዮን ገብረ ኤዎስጣቴዎስ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ በቀድሞው የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት አካለ ጉዛይ አውራጃ ኩርባርያ ከተባለው ሥፍራ በ1878 ዓ.ም ተወለዱ። በተወለዱ በዓሥራ አራት ዓመታቸው ዓዲኳላ ከተማ ከነበሩት መምህር ገብረ ሕይወት የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ተማሩ። እስከ 19 ዓመት ዕድሜያቸው በዚህ ዓይነት ከቆዩ በኋላ ከዚህ ዓለም ርቆ ለመኖር ፈቃዳቸው ስለሆነ፣ ከፃዕዳ እምባ ሥላሴ ገዳም በምናኔ ለመኖር ቆርጠው ገቡ።

መምህር ገብረ ማርያም የተባሉ ሊቅ ቅኔንና መጻሕፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ እያስተማሩ በዚሁ ፃዕዳ እምባ ገዳም በምናኔ ይኖሩ ስለነበረ ከኒሁ ሊቅ መጻሕፍተ ሊቃውንትን ሲማሩና ገዳማውያኑን ሲረዱ ቆዩ። ለ11 ዓመታት በትጋት እየተማሩና እያገለገሉ ከቆዩ በኋላ 30 ዓመት ሲሞላቸው መምህር ተብለው የዚሁ ገዳም አበ ምኔት እንዲሆኑ በመነኮሳቱ ተመርጠው ተሾሙ።

የገዳሙ አበ ምኔት ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በቆዩበት 45 ዓመት ዕድሜ የተለያዩ መንፈሳውያን አገልግሎቶችን አበርክተዋል። በአበ ምኔትነት የተሾሙበት ፃዕዳ እምባ ገዳም በዓፄ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት በጣም ከፍ ካለ ተራራ ላይ የተገደመ በመሆኑ ገዳማውያኑ የከፋ የውኃ ችግር ነበረባቸው። በዚህ የተነሣም መነኮሳቱ ገደሉን ወርደው አምስት ሰዓት ያህል ተጉዘው ውኃ ቀድተው ወደ ገዳሙ ይመለሱ ነበር። ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ይህንን የገዳማውያኑን ችግር ለማስቀረት ሲሉ ከገዳሙ ውስጥ አለቱን እየቆፈሩ የውኃ ማጠራቀሚያ ኩሬ ጉድጓድ አሠርተው ለገዳሙ የሚበቃ ውኃ አስገኝተዋል።

እንዲሁም ከገዳሙ ውጭ መነኮሳቱ ከብት በማርባት፣ እርሻን በማስፋፋት የሚጠቀሙበት ማዕዳዋይና ደንጊያ ወርቅ ከተባለው ቦታ ውኃ ለማጠራቀም የሚያገለግል ግድብ ገድበው ለገዳሙ መጠቀሚያ ሆኗል። በ1981 ዓ.ም አቆርዳት ከተባለው ከተማ ቤተ ክርስቲያንና ቤተ መነኮሳት አሠርተው መነኮሳቱ በገዳማዊ አስተዳደር እንዲኖሩ አድርገዋል።

ከዚህም ጋር ብፁዕነታቸው በአውራጃው የክርስትናን ትምህርት ለማስፋፋት ሰፊ ያለ ሐዋርያዊ አገልግሎት አበርክተዋል። በ1920 ዓ.ም ተከዜ ላይ ከሚገኘውና እምኒ ሐጀር ከተባለው ከተማ ቤተ ክርስቲያንና አብያተ መነኮሳት እንዲኖሩና መንፈሳዊ ሥራቸውን እንዲያስፋፉ ሥርዓት በመሥራት እንዲተዳደሩ አድርገዋል።

ምንም እንኳ አካባቢው በእስልምና እምነት የተዋጠ ቢሆንም በ1923 ዓ.ም ከሩን በተባለው ከተማ ቤተ ክርስቲያን አሳንፀውና ሰፊ



አጥር አሳጥረው፣ አብያተ መነኮሳትም አሠርተው ገዳሙ የተዋሕዶ ሃይማኖትን ባሕልና ሥነ ሥርዓት ተከትሎ እንዲሔድ የአካባቢውን ሕዝቦችም እንዲያስተምር አድርገዋል።

በ1933 ዓ.ም ተሠነይ በተባለው የሱዳን አዋሳኝ ከተማ ቤተ ክርስቲያን አሳንፀውና ቤተ መነኮሳት አሠርተው ያስቀመጧቸው መነኮሳት ከገዳሪፍና ከከሰላ እየመጡ ለሚኖሩት ሰዎች መነኮሳትን እየላኩ በማጥመቅና በማስተማር አገልግሎታቸውን እንዲያበረክቱ አድርገዋል።

ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ በ1943 ዓ.ም የኤርትራን ሊቃውንት ካህናትንና ምእመናንን በማስተባበር «ማኅበረ ሐዋርያት» ይሰኝ የነበረውን ማኅበር እንዲቋቋም አድርገዋል። እርሳቸው የመሠረቱት ማኅበር ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መጠናከር ከፍተኛ አገልግሎትን አበርክቷል። እኒህ ብፁዕ አባት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል ሰፊ አስተዋጽኦ ካደረጉት አባቶች አንዱ ናቸው።

በዚህ ሁሉ አገልግሎታቸው በ75 ዓመት ዕድሜያቸው ሚያዝያ 12 ቀን 1953 ዓ.ም ብፁዕ አባ አትናቴዎስ ጳጳስ ዘኤርትራ ተብለው ተሹመዋል። ብፁዕነታቸው ቀድሞም ቢሆን ለረጅም ዘመናት የቆዩበት አካባቢ እና አገልግሎት ቢሆንም ሥራው ሳያሸንፋቸው ዕድሜ እያሸነፋቸው በመምጣቱ ብዙም ሳይቆዩ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ሥርዓተ ቀብራቸውም በዚየው በክብር ተፈጽሟል። የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን። አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

# 3.30. ብፁዕ አቡነ እንድርያስ ቀዳማይ ሊቀ ጳጳስ

## /1906 - 1987 ዓ.ም/





ቀድሞ መምህር ቀፀላ ሠይፈ ሥላሴ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ እንድርያስ በያኔው ወሎ ጠቅላይ ግዛት መቄት ወረዳ ልዩ ስሙ ገረገራ ቅዱስ ጊዮርጊስ /ደብረ ሃይማኖት/ በተባለው ጥንታዊ ደብር ጥር 27 ቀን 1906 ዓ.ም ተወለዱ:: አባታቸው ካህን ገላው ገብረ ማርያም እናታቸው ወ/ሮ አበበች ካሣ ይባሉ ነበር::

ዕድሜያቸው አምስት ዓመት ሲሆን በተወለዱበት ደብር መሪ ጌታ መንክር ከሚባሉት ስመ ጥር መምህር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ:: ትምህርታቸውን በመቀጠልም ከእኒያው መምህር ጸዋትወ ዜማን እንደ ጀመሩ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ከግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ::

ገና በልጅነታቸው የትምህርትን ጥቅም የተረዱት ብፁዕ አቡነ እንድርያስ ዲቁና ከተቀበሉ በኋላ ወደ ትውልድ ደብራቸው በመመለስ የጀመሩትን የጸዋትወ ዜማ ትምህርት አጠናቀቁ:: ከዚያም ትምህርታቸውን ለማስፋፋት ሲሉ በሰሜን ወሎ ዋድላ ቤተ ዮሐንስ በተባለው ደብር ከመምህር ገብረ መስቀል፣ በደቡብ ጎንደር ስማዳ ወረዳ ልዩ ስሙ ጉጠ ማርያም በተባለው ደብር ከመምህር ወልደ ስማዕት፣ በሰሜን ወሎ ደላንታ ገላ ነአኩቶ ለአብ በተባለው ደብር ከመምህር ብርሌ ውቤ፣ በደቡብ ጎንደር በእስቴ ወረዳ ልዩ ስሙ ዘገራ ገብርኤል በተባለው ደብር ከመምህር ተወልደ ብርሃን፣ እንዲሁም በሞያው ስመ ጥር ከነበሩትና በመቄት ወረዳ ያስተምሩ ከነበሩት ከአለቃ ቦወቀ በላይ ዘንድ በመዘዋወር ቅኔንና የቅኔን ሀዋጅ ከነ እርባ ቅምሩ አጠናቀው ተማሩ::

ከዚያም በ1926 ዓ.ም መጻሕፍትን ሲመረምሩ ለመኖር በነበራቸው ፍቅርና ጉጉት በእጅጉ ይወዷቸው ወደ ነበሩት መምህራቸው መምህር ሠይፈ ሥላሴ ዘንድ ሔደው የመጻሕፍተ ሐዲሳትን፣ የማር ይስሐቅን፣ የአረጋዊ መንፈሳዊን፣ የዳዊትንና የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜ ተማሩ:: በእርግጥ የመጻሕፍትን ምስጢር የመመርመርን ፍቅር በውስጣቸው ከመስነቃቸው በፊት ፍላጎታቸው በዜማው ትምህርት መግፋት ነበር:: ነገር ግን የብፁዕነታቸውን ጸጋ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተረዱት መምህራቸው «የአንተ ዕጣ ፈንታህ የመጻሕፍትን ምስጢር መመርመር ነው» ስላሏቸው ወደ ትርጓሜው ትምህርት ሙሉ በሙሉ አትኩረዋል::

ብፁዕነታቸው ከመምህራቸው ወንበር ሥር ቁጭ ብለው ሐዲሳትን በማሔድ ላይ ሳሉ ሀገራችን በፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ተወረረች:: በዚህ ጊዜ ከመምህራቸው ሳይለዩ በተደበቁበት ዋሻ ስንቅ እየቀረበ የማር ይስሐቅን፣ የአረጋዊ መንፈሳዊን፣ የዳዊትንና የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜ ተማሩ:: ቀጥሎም ከመምህር ፈላታዎስ የመጽሐፈ ኢሳይያስን ትርጓሜ ከተማሩ በኋላ ከመጀመሪያው

www.ethiopianorthodox.org

መምህራቸው ከመምህር ሠይፈ ሥላሴ ዘንድ ተቀምጠው የመምህራቸውን ደቀ መዛሙርት በማስተማር ላይ እንዳሉ በ1935 ዓ.ም ምንኩስናንና ቅስናን ከብፁዕ አቡነ ይስሐቅ እጅ ተቀበሉ።

ከዚህ በኋላ የቀለም አባታቸው የነበሩት መምህር ሠይፈ ሥላሴ አብርሃም በ1938 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። በዚህ የተነሣም መምህሩ ያስተዳድሩት የነበረውን የገረገራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር እንዲያስተዳድሩ የአጥቢያው ምእመን ብፁዕነታቸውን መረጠ። መንግሥትም ምርጫውን አጸደቀ። ብፁዕ አቡነ እንድርያስም የመምህራቸው ግዝት ነበረባቸውና ሹመቱን በአኰቴት ተቀብለው የአካባቢው ምእመንም ሆነ መምህራቸው መምህር ሠይፈ ሥላሴ የጣሉባቸውን አደራ በብቃት ሲወጡ ቆዩ።

በጉባኤ በማስተማርም ሆነ በማስተዳደር ላቅ ያለ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ሳሉ በ1943 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መልካም ፈቃድ በወሎ ሀገረ ስብከት ለብፁዕ አቡነ ይስሐቅ እንደራሴ ሆነው ተሾሙ። በተሰጣቸው ሐላፊነት መሠረት ከብፁዕ አቡነ ይስሐቅ በወቅቱ የወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ጋር በመሆን ለአምስት ዓመታት ያህል ሰፊ አገልግሎት እንደ ሰጡ በ1948 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ሀረፉ። በዚህ የተነሣም ወደ ቀደመ ቦታቸው ገረገራ ጊዮርጊስ ተመልሰው የተለመደ ጉባኤያቸውን ዘርግተው ማስተማር ጀመሩ። በትምህርታቸውም በርካታ ደቀ መዛሙርትን ለአገልግሎት ብቁ እንዲሆኑ አድርገዋል። ብፁዕ አቡነ እንድርያስ ገረገራ ጊዮርጊስ ጉባኤ ዘርግተው በሚያስተምሩበት ጊዜ ከመደበኛ ጉባኤያቸው በተጨማሪ የአካባቢውን ምእመናን እያስተማሩ በሕግ እንዲጸኑ፣ በሥጋ ወደሙ እንዲወሰኑ አድርገዋል።

በአጋጣሚ የገረገራ ቅዱስ ጊዮርጊስን ደብር ጉዳይ ለማስፈጸም በ1952 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው የነበሩት ብፁዕነታቸው ሳያስቡት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ አቅራቢነት በግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፈቃድ የአዲስ አበባ መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ። ሳያስቡት ለታላቅ ሐላፊነት የደረሱት ብፁዕ አቡነ እንድርያስ ደብሩን ከተረከቡበት ጊዜ ጀምሮ ካህናት ሕዝበ ክርስቲያኑን በትጋት እንዲያገለግሉ፣ ወጣት የቤተ ክርስቲያን ልጆችም ወደ እናታቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተሰባስበው እንዲያገለግሉና እንዲገለገሉ በማድረግ ሰፊ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

በተለይ የወደ ፊቱ የቤተ ክርስቲያን ተረካቢ ወጣቱ መሆኑን በውል የተረዱት ብፁዕነታቸውን በዚያው ደብር «ዓምደ ሃይማኖት» በሚል ስያሜ ወጣቶች ተሰባስበው እንዲማሩ በ1957 ዓ.ም ሰንበት ት/ቤቱን መሥርተዋል። ከዚህ ሰንበት ት/ቤት ተምረውና ሠልጥነው



የወጡ ወጣቶች ዛሬ በየቦታው ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶችን በማበርከት ለቤተ ክርስቲያን አለኝታ ሆነዋል። እየሆኑም ነው።

ብፁዕ አቡነ እንድርያስ በደብሩ የአስተዳዳሪነት ቆይታቸው ወቅት ቃለ እግዚአብሔር ለተጠሙት በትጋት ከማዳረስ ጋር በደብሩ ከወልደ አብ ወልደ ሚካኤል፣ ከመምህር አካለ ወልድና ከብፁዕ አቡነ አብርሃም እንዲሁም ከመምህር ሠይፈ ሥላሴ ሲያያዝ የመጣውን ጉባኤ በማስፋፋት በርካታ ደቀ መዛሙርትን ለቤተ ክርስቲያን አበርክተዋል። ከእርሳቸው ጉባኤ ተምረው ከፍ ላለ ደረጃ ከደረሱት አባቶች ውስጥም ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል፣ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ፣ ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ይገኙበታል። ብፁዕነታቸው ከነበራቸው የማስተማር ጸጋና ጉጉት መንገድ ላይም የሚያሳልሙትን ሰው በአጭሩም ቢሆን ቃለ እግዚአብሔር ሳያስተምሩት አያልፉም ነበር ይባላል።

ብፁዕነታቸው የዚህ ታላቅ ገዳም አስተዳዳሪ ሆነው ባገለገሉባቸው ዓመታት የገዳሙ ገቢ እንዲያድግና አስተዳደሩም ዘመናዊ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ነበር። ገዳሙን በገቢ ራሱን ለማስቻል ፒያሳ አካባቢ እንድ ዘመናዊ ባለ አራት ፎቅ ሕንፃ አሳንፀዋል።

ከ1952 ዓ.ም ጀምሮ በመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ደብር በአስተዳዳሪነት የቆዩት ብፁዕነታቸው በ1964 ዓ.ም በተደረገው የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ ከተመረጡት ስድስት አባቶች አንደኛ በመውጣት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አንብሮተ እድ የጎንደር ሀገረ ስብከት ጳጳስ ሆነው ተሾሙ። በጎንደር ሀገረ ስብከታቸውም ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ በየአብያተ ክርስቲያናቱ የሰበካ ጉባኤ በማቋቋም፣ እንደ አዲስ አበባው ሁሉ የወጣቶች መንፈሳውያት ማኅበራትን በማስፋፋት፣ ከሀገረ ስብከቱ ጀምሮ እስከ ወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ድረስ በሙሉ ጊዜ የሚያገለግሉ ሠራተኞች ቋሚ ደሞዝ እንዲመደብላቸው በማድረግ፣ የቀለምና የሞያ ት/ቤቶች እንዲቋቋሙ በማድረግ ላቅ ያለ አገልግሎት አበርክተዋል። ከዚህም ጋር በሀገረ ስብከቱ የሚገኙትን የከይላ ብሔረሰብ አባላት በማስተማር ተጠምቀው የቤተ ክርስቲያን አባላት እንዲሆኑ አድርገዋል። ብፁዕነታቸው እነዚህንና ሌሎች በርካታ ያልተጠቀሱ አገልግሎቶችን ሁሉ ሲያበረክቱ በነበራቸው የመግባባትና የማሳመን ችሎታ በተለይ በወቅቱ በሀገረ ስብከታቸው አካባቢ ይንቀሳቀሱ የነበሩ የውጭ ድርጅቶችን በማሳመንና የርዳታ እጆቻቸውን እንዲዘረጉ በማድረግ ነበር።

ብፁዕ አቡነ እንድርያስ ላመኑበት ነገር ወደ ኋላ የማይሉ

www.ethiopianorthodox.org

ጥብእትን ከእግዚአብሔር የተቀበሉ አባት ነበሩ። በዚህ ጠባያቸውም ዛሬም የሚያውቋቸው ሁሉ «መምህር ወመገስጽ ዘኢያደሉ ለገጽ» ነበሩ በማለት ይገልጿቸዋል። ከሰዎች ሕግ ቀድሞ የእግዚአብሔር ሕግ ተግባራዊ እንዲሆን፣ የሰውም ሕግ ከእግዚአብሔር ሕግ ያልወጣ መሆን ስላለበት ማንኛውም ሕዝብ ይተዳደርበት ዘንድ የሚወጣ ሕግ በሕገ እግዚአብሔር የተደገፈ ለእሱም የተገዛ እንዲሆን ከፍተኛ ፍላጎትና እምነት የነበራቸው አባት ነበሩ።

በነበራቸው ቃለ እግዚአብሔርን እምልቶና አስፍቶ የማቅ ረብ ጸጋ በዐበይት በዓላት ጊዜ ሊያስተምሩ ሲቆሙ ለቤተ መንግ ሥቱም ሆነ ለቤተ ክህነቱ ሰዎች በዚህ በኩል ይኽ ጎድሏል፣ በዚህኛው ደግሞ ይኽ ይቀራል ይስተካከል እያሉ የሚገባቸውን ትምህርት ካለምንም ፍርሐት ይሰጡ ነበር። በዚህ ሊቅነታቸው ከንጉሠ ነገሥቱ ጀምሮ በቤተ መንግሥቱ ሰዎች ዘንድ አክብረሮት በሰፊው ይቸራቸው ነበር። ሊቀ ሊቃውንት በነበሩ ጊዜ የዓመት ልብሳቸውን በቅዱስ ገብርኤል ስም የሚችሏቸው ልዕልት ተናኘ ወርቅ ነበሩ።

በአንድ ታላቅ ዓመታዊ የበዓል ቀን ንጉሡን እንኳን አደረስዎ የማለቱ ተራ የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ሆኖ ብፁዕነታቸው የደብሩን መዘምራን አስልፈው ለበዓሉ የሚገባውን ወረብ ለንጉሡ፣ ለልዑላኑና ለልዕልታቱ እንዲሁም ለመኳንንቱ ሲያቀርቡ ከበሮውን የያዘው ሰው የመዘምራኑን ጣዕመ ዜማና ከበሮ ምቱን በማቀላቀል አጠቃላይ ዜማውን ያበላሻል። በዚህ ጊዜ ብፁዕነታቸው ከበሮውን ከያዘው ሰው ተቀብለው ምቱን ከዜማው ጋር በሚያስገርም ሁኔታ እያስማሙ እንደ እንዝርት ያሽከረክሩት ጀመር። በዚህ ጊዜ ንጉሡ በስሜት ከዙፋናቸው ተነስተው ወደ መዘምራኑ በመግባት ካባቸውን አውልቀው ለብፁዕነታቸው አለበሷቸው ይባላል።

ብፁዕ አቡነ እንድርያስ ደርግ ዘውዳዊውን መንግሥት በኃይሉ ጥሎ መንበረ መንግሥቱን በመያዝ ሀገሪቱን ሲመራ የተፈጠ ረውን ቀውስ በግልጽ በአደባባይ ይተቹ ነበር። በዚህ የተነሣም በተለያዩ ጊዜያት ልዩ ልዩ ፈተናዎች ደርሰውባቸው ነበር። በተለይ የቀይ ሽብር ዘመቻ በሚል በወቅቱ ተፋፍሞ በነበረው የወጣቶች እልቂት «ሰውን ያለፍርድ ገድሎ በመንገድ ላይ መጣልን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታወግዛለች፤ ሰው በዘፈቀደ መገደልና በየመንገዱ መጣል የለበትም» በማለት የደርግን ርምጃ በግልጽ ተቃውመው ነበር። በዚሁ እንቅስቃሴም በጎንደር ከተማ የሚገኙ መኖሪያ ቤቶች በወታደሮች ሲፈተሹ የብፁዕነታቸውን ቤት ለመፈተሽ ወታደሮች ወደ እሳቸው ቤት



መጥተው ነበር። የወታደሮችን ቤት መግባት የተመለከቱት ብፁዕነታቸውም «ከእኔ ቤት መስቀል እንጂ ሌላ ምን ይገኛል? የእኛ መሣሪያ እናንተ ከታጠቃችሁት የጦር መሣሪያ የሚበልጠው ይህ መስቀል ነው፤ ውጡልኝ» በማለት ሲገስጿቸው አንዱ ወታደር ሊገድላቸው ሲል ሌላው ከልክሎ የብፁዕነታቸው ነፍስ ተርፋለች ይባላል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ብፁዕነታቸው በየትኛውም ጉባኤ ጸሎት ሲያሳርጉ «ከቀሳፊ መልአክ ይሰውራችሁ፤ ይሰውረን» ይሉ ነበር። በወቅቱ የደርግን ፖሊሲ በአካባቢው ያስፈጽም ዘንድ በቦታው የተቀመጠው ሰው «መልአኩ ተፈራ» ተብሎ ይጠራ ስለነበር የብፁዕነታቸው የተለመደና ከሥርዓት ያልወጣ ጸሎት ከእሱ ጥይት ይሰውረን እንደ ማለት ተቆጥሮባቸው ከመጋቢት 1971 ዓ.ም ጀምሮ ከመንበረ ጵጵስናቸው ተነሥተው ሙሉ ደሞዛቸውን እያገኙ በአዲስ አበባ እንዲቀመጡ ተደርጎ ነበር። ብፁዕነታቸው ግን «ያለፍርድ እነ ወንጀለኛ ነህ ከተባልኩ የኢትዮጵያን ሕዝብ ገንዘብ መብላት የለብኝም፤ በልቼ ብገኝ ዕፀ በለስን እንደመብላት ይቆጠርብኝ» ብለው ከሁለት ዓመታት በላይ በመንፈስ ልጆቻቸው እየተረዱ ተቀምጠው ነበር። ቆይቶ ግን የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ የመምህራንና የቀሳውስት ማሠልጠኛ ት/ቤትን ይመራ በነበረው ባለ አደራ ቦርድ የት/ቤቱ የበላይ ጠባቂ አድርጎ በሰኔ ወር 1973 ዓ.ም ሾማቸው። ብፁዕነታቸውም ሹመቱን በደስታ ተቀብለው እስከ ኅዳር 1985 ዓ.ም ድረስ በበላይ ጠባቂነት ሲያገለግሉ ቆይተዋል።

ብፁዕነታቸው በሀገረ ስብከታቸው በማገልገል ላይ እንዳሉ በ1965 ዓ.ም ከፍተኛ የጤና መታወክ አጋጥሟቸው ነበር። ይህ ደዌ ዘዕቤት ብፁዕነታቸው ምን ያህል ቅዱስ አባት እንደሆኑ መስክሮ ያለፈ ነው። አዲስ አበባ በሚገኘው የየካቲት 12 ሆስፒታል በሕክምና ሲረዱ ቢቆዩም ሊሻላቸው ባለመቻሉ ለከፍተኛ ሕክምና ወደ ኢየሩሳሌም ይሔዳሉ። በዚያም በሠለጠኑ ዶክተሮች ጤናቸው እንዲመለስ ጥረት ቢደረግም በሐኪሞቹ አባባል «ተስፋ ሲያገኙ» አልቻሉም። በመሆኑም ሐኪሞቹ ወደ ሀገራቸው ይዘዋቸው እንዲመለሱ ለአሳካሚዎቻቸው ይመክራሉ። ነገር ግን ብፁዕነታቸው እዚሁ ቅድስት ሀገር እቀበራለሁ እትውሰዱኝ ብለው ይቀራሉ። በዚህም ወደ ዴር ሱልጣን መድኃኔ ዓለምና ደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት የኢትዮጵያ ገዳማት እየተመላለሱ ሥጋ ወደሙን ሲቀበሉ ወስነው በመጀመሪያው ቀን አልጋ ላይ እንዳሉ ሲቀበሉ ዓይናቸው ተገለጠ። በሁለተኛው ቀን ደግሞ ያለማንም ድጋፍ ከአልጋ ተነሥተው ተቀበሉ። በሦስተኛው ቀን ራሳቸው ገዳሙ ድረስ በእግ ራቸው ሔደው ተቀብለው ተመለሱ ይባላል። በዚህ ዓይነት ሐኪሞቹ ተስፋ የላቸውም ቢሉም ብፁዕነታቸው በክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ደም

www.ethiopianorthodox.org

ክቡር ጤናቸው ሙሉ በሙሉ ተመልሶ ከሦስት ወራት ቆይታ በኋላ ጥር 18 ቀን 1965 ዓ.ም ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል ::

ብፁዕ አቡነ እንድርያስ በተሰጧቸው ሥልጣን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸውን እያገለገሉ ሳለ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ በተደረገ ጊዜ የመኖሪያ በአታቸው በፈንጅ ተከቦ ኖሮ በደረሰው የመፈንዳት አደጋ ጉዳት ደርሶበት ነበር:: ይሁን እንጂ ቤታቸውና ንብረታቸው ቢቃጠልም በእሳቸው ላይ ምንም ዓይነት አደጋ ሳይደርስ ተርፈዋል:: ብፁዕነታቸው ይህ አደጋ ከመድረሱ በፊት ግንቦት 19 ቀን ቤቱን ለቀው እንዲወጡ በወዳጆቻቸው ተመክረው ነበር ይባላል:: ብፁዕነታቸው ግን «አንድጠ ራጠር አታድርጉኝ፤ ሞት ሲመጣ ወደ እግዚአብሔር ቤት ይኬዳል እንጂ እንዴት ወደ ግለሰብ ቤት ይኬዳል? እመቤቴ ቅድስት ድንግል ማርያም ከምድራዊው እሳት በሰባት እጅ ከሚበልጠው እሳት ታድነኛለች ብዬ ዘወትር የምለምናት ታወጣኛለች» ብለው በእም ቢታ በቤታቸው አድረው ነበር ይባላል::


ብፁዕ አቡነ እንድርያስ አብረውት የቆዩትን የጎንደርን ሕዝብ እንደ ገና ለማግኘት ጉጉት ስለ ነበራቸው ከ14 ዓመት ቆይታ በኋላ በኅዳር ወር 1985 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ መልካም ፈቃድ እንደ ገና ወደ ጎንደር ተሳኩ:: በዚያም የተለመደ አገልግሎታቸውን በማበርከት ከሚወዱት የሀገረ ስብከታቸው ሕዝብ ጋር ለሁለት ዓመት ከቆዩ በኋላ በ1987 ዓ.ም በጥቅምት ወር ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ተደርጎ የታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳምና የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል አብያተ ክርስቲያናት የበላይ ጠባቂ ሆነው ተሾሙ:: ይሁን እንጂ ብዙም ሳይቆዩ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት ሐምሌ 27 ቀን 1987 ዓ.ም በ81 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: አስከሬናቸውም በአዲስ አበባ መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተገቢው ጸሎትና አሸኛኘት ከተደረገለት በኋላ በሕይወት ዘመናቸው ደጋግመው በሰጡት ኑዛዜ መሠረት ሐምሌ 29 ቀን 1987 ዓ.ም በሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ወደ ሚገኘውና ተወልደው ወዳ ደጉበት፣ ተምረው ወዳ ስተማሩበት ደብረ ሃይማኖት ገረገራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተሸኝቶ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና የአካባቢው ምእመን በተገኙበት ሐምሌ 30 ቀን 1987 ዓ.ም የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ተፈጸመ:: የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን:: አሜን::



# 3.31. ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ሣልሳይ

## ሊቀ ጳጳስ

## /1904 - 1991 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

ቀድሞ ንቡረ እድ አበበ ሻውል ይባሉ ነበር:: በቀድሞው ሸዋ ጠቅላይ ግዛት ተጉለትና ቡልጋ አውራጃ መሰኖ ማርያም በምትባል ቀበሌ ከአባታቸው ከአቶ ወልደ ሐዋርያት እና ከእናታቸው ከወ/ሮ /በኋላ አማሆይ/ ጻዲቁ ተወለዱ:: ዘመኑም 1904 ዓ.ም ነበር::

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ እዚያው ተወልደው ክርስትና ተነሥተው ባደጉበት አጥቢያ አባ ገብረ ኪዳን ከተባሉ መምህር የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ማለትም የንባብና የቃል ትምህርታቸውን ተማሩ:: ከዚህ በመቀጠልም በዚያው ቦታ አባ ረዳ ከተባሉ መምህር መዝገብ ቅዳሴውን አጠናቀው ሀወቁ:: ከዚሁም ጋር አለቃ ገብረ ጻድቅ ከተባሉት መምህር ሁለተኛውን ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርት ማለትም ምዕራፍና ጾመ ድጓ አጠቃላይ የጸዋትወ ዜማውን ትምህርት በሚገባ ሀወቁ::

የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን በዚህ ዓይነት አቀላጥፈው የተማሩት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ለቀጣዩ ትምህርት ከትውልድ ሀገራቸው በመውጣት ወደ በላሌ ሔደው ፍቼ ጊዮርጊስ ላይ በሬ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት ስመ ጥር ሊቅ ከመምህር ጥበቡ ገሜ የቅኔ ትምህርታቸውን ቀጠሉ:: ይሁን እንጂ ከመምህር ጥበቡ ገሜ የቅኔ ትምህርታቸውን ሲያገባድዱ ለቅኔ ሀገሩ ጎጃም ነው የሚባለውን ወሬ በመስማታቸው ትምህርቱን አጠናቆ መምህር የመሆን ታላቅ ሕልማቸውን በንቀው ወደ ጎጃም ተሻገሩ:: በዚያም እንደ ደረሱ መምህር ከብካብ ከተባሉ ሊቅ ዘንድ የቅኔ ትምህርታቸውን አስፋፉ:: በዚያው መምህር ማርቆስ ወደ ተባሉ ስመ ጥር የቅኔ መምህር ዘንድ ሔደው የቅኔ ዕውቀታቸውን የበለጠ በማስፋፋት እስከ አገባቡና እርባ ቅምሩ ቀጽለው በመምህርነት ተመረቁ::

ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ለመምህርነት ከበቃሁ ዘንድ ዐርፌ ልቀመጥና አፎይ ብዬ እያስተማርኩ ልኑር አላሉም:: ከፍተኛውን ደረጃ የመንፈሳዊ ትምህርት ለመማር ወደ ጎንደር አቀኑ:: ዳት ጊዮርጊስ ተብሎ በሚጠራው ደብር በሬ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ወደ ነበሩት አለቃ የማነ ብርሃን ዘንድ ሔደው ከብሉያት መጻሕፍት ውስጥ የዳዊትን ትርጓሜ ተማሩ:: ቀጥሎም በእንዳ ቤት ወረዳ ጂማር ቅዱስ ሚካኤል ደብር ወደ ነበሩት መምህር ገብረ እግዚአ ብሔር ዘንድ በመሔድ የሐዲሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ተማሩ::

የመጻሕፍትን ትርጓሜ የበለጠ ለመመርመር ጽኑዕ ፍላጐት የነበራቸው ብፁዕነታቸው አሁንም ወደ ታወቁት ሊቅ መምህር ሠይፈ ሥላሴ ዘንድ ሔደው የሐዲሳትንና የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜ አጠናቀው በመማር በመምህርነት ተመረቁ:: ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ አሁንም በቃኝ አላሉም:: አራቱንም ጉባኤያት የማዳረስ ጽኑዕ



ፍላጎት ስለ ነበራቸው አስቴ መካነ ኢየሱስ የመጻ ሕፍተ ሊቃውንት መምህር ወደ ነበሩት መምህር ወልደ ሚካኤል ዘንድ በመሔድ የመጻሕፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ አጠኑ::

በዚህ ዓይነት ከሀገር ሀገር፣ ከጉባኤ ቤት ጉባኤ ቤት፣ ከመምህር መምህር እየተዘዋወሩ በፋ ያለ ትምህርት ያካበቱት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ በመጨረሻ በአዲስ አበባ መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም በቅኔና በሐዲስ መምህርነት ተቀጥረው ማስተማር ጀመሩ:: እያደር በሚደምቀውና በሚሰፋው ጉባኤያቸው ለአምስት ዓመታት ያህል ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን ሲያፈሩ ከቆዩ በኋላ በሊቅነ ታቸው በመጀመሪያ የአንኮበር ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ፣ ቀጥሎም የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም አስተዳዳሪ፣ በመጨረሻም የርእሰ አድባራት ደብረ ጽዮን አዲስ ዓለም ማርያም ንቡረ እድ ሆነው በመሾም ለረጅም ዓመታት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አገለገሉ::

ከዚያም በ1964 ዓ.ም በተደረገው የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ ከተመረጡት አባቶች አንዱ በመሆን «ብፁዕ አባ ሳዊሮስ ጳጳስ ዘቦረና ነገሌ» ተብለው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ እንብሮተ እድ መዓርገ ጵጵስናን ተሾሙ:: ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ በተሾሙበት ሀገረ ስብከት በረሃነት ሳይበቀቁ፣ ወባውን ሳይፈሩ ከአውራጃ ወደ ወረዳ በመዘዋወር ሕዝቡን አስተምረዋል:: ከዚያም ወደ ሸዋ በመምጣት በጡረታ እስኪገለሉ ድረስ በሊቀ ጳጳስነት አገልግለዋል:: አዲስ አበባ የነበረው የሸዋ ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና በሲኖዶስ ውሳኔ ወደ ደብረ ብርሃን ሊዛወር ብፁዕነታቸው የመጀመሪያው በመሆን የሀገረ ስብከቱን መንበረ ጵጵስና ከነ ሙሉ ድርጅቱ እንዳ ሠሩ ይነገርላቸዋል::

ብፁዕነታቸው የወቅቱ መንግሥት በቤተ ክርስቲያኗ ላይ ተሐድሶ አመጣለሁ በሚል ካወጣቸው ሕግጋት አንዱ ዕድሜያቸው የገፉ ጳጳሳት በጡረታ እንዲገለሉና በገዳም እንዲቀመጡ የሚል ስለ ነበር ሕጉ በቀጥታ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጸመባቸው አንዳንድ አባቶች ጉዳዩን አንቀበልም፤ ጳጳስ ጡረታ ሊወጣ አይገባም በማለት ሲቃወሙ ብፁዕነታቸው ጉዳዩን በቸልታ በማየት ለጥቂት ጊዜያት ባሳደጓቸው የመንፈስ ልጆቻቸው ቤት ከቆዩ በኋላ ቀሪ ሕይወታ ቸውን በትግሐ ጸሎትና በሱባኤ ሊሸኙ ወደ ደብረ ሊባኖስ ወረዱ:: በዚያም በፍጹም ብሕትውና ዕለት ዕለት በጸሎት ከአምላካቸው ጋር እየተገናኙ ቆዩ:: በመጨረሻም የደርግ መንግሥት በአሁኑ ሊተካ ቅዱስ ሲኖዶስ ቀደም ሲል በጡረታ ተገልለው በየቦታው ያሉ አባቶች ወደ ቀደመ አገልግሎታቸው እንዲመለሱ ወሰነ:: በዚህም ብፁዕነታቸው ከገዳሙ ወጥተው የቀደመ አገልግሎታቸውን እንዲ

www.ethiopianorthodox.org

ያበረክቱ ሲጠየቁ «ከአሁን በኋላ ክበአቴ ወጥቼ ዬት እሔዳለሁ? እዚሁ ቆይቼ ቀሪ ሕይወቴን እሸኛለሁ እንጂ እንደ ገና ወደ ሹመት አልሔድም» በማለት ጥያቄውን ሳይቀበሉት ቀሩ:: ቅዱስ ሲኖዶስም በብፁዕነታቸው አሳብ ተስማምቶ ባሉበት ሙሉ ደሞዛ ቸውን እያገኙ በዚያው በበላይ ጠበቂነት እንዲያገለግሉ ወሰነላቸው::

በመሆኑም በበላይ ጠበቂነት ከዓሥራ ሁለት ዓመት በላይ ሲያገለግሉ ቆዩ:: በገዳሙ በነበሩበት ጊዜም ከዓመት እስከ ዓመት ከቅዳሴ ሳይለዩ፣ በጾም በጸሎት በትኅርምት ተወስነው እግዚአብ ሔርን ሲያገለግሉ እንደ ነበረ በቅርብ የሚያውቋቸው ሁሉ ይመሰክሩላቸዋል::

ብፁዕነታቸው ለሥራ ቀጠሮ የማይሰጡ ፈጣን አባት እንደ ነበሩ ይነገርላቸዋል:: የደርግ መንግሥት ሥልጣን ላይ በወጣ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት «ሕዝብ ወሳኝ ኃይል ነው» የሚል ፈሊጥ ስለ ነበረው ብዙ ነገር በሕዝብ ውሳኔ ይከናወን በሚል ሰፋ ያለ ነጻነት ሰጥቶ ነበር:: የዚህን ነጻነት አይዘልቄነት ቀድመው የተረዱት ብፁዕነታቸው ነበሩ ማለት ይቻላል:: በዚህም «ይኸ መንግሥት እስከ ሚጠናከር ነው ሕዝብ ሕዝብ የሚለው፤ ትንሽ ከቆዬ ይኸ ዕድል አይገኝምና ሥራን መሥራት አሁን ነው» እያሉ በአካባቢያቸው ያሉ የሥራ ባልደረቦቻቸውን ይመክሩና ያነሳሱ ነበር ይባላል:: በመሆኑም ሕዝቡ ወሳኝ ነው በተባለበት በዚያ ጊዜ በማስተማርና በማስተባበር በርካታ ሥራዎችን ሠርተዋል:: ከእነዚህም ውስጥ ቡሉልታ አካባቢ ይገኝ የነበረውን የደጃዝማች ይልማ ደሬሳን የከብት እርባታ ቦታ ሕዝቡ እንዲቀበል አድርገው የሥላሴን ታቦት በፍጥነት አስገብተው ቤተ ክርስቲያን እንዲሆን አድርገዋል:: በተጨማሪም በአካባቢው የሚገኘውን ሌላ የዶሮ እርባታ ግቢያ በመውሰድ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ታቦት አስገብተው ቤተ ክርስቲያን አድርገዋል:: በዚህ ጠባያ ቸውም ሕዝቡም ሆነ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ይወዷቸው ነበር::

በመጨረሻም ብፁለ አቡነ ሳዊሮስ ክሽምግልናቸው ጋር ለተወ ሰኑ ጊዜያት ለዕረፍታቸው ምክንያት በሆነ በሽታ ተይዘው ክቆዩ በኋላ ጳጉሜን 6 ቀን 1991 ዓ.ም ዕረፍተ ቅዱሳን በሆነ ዕረፍት ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: አስከሬናቸውም በቤተ ክርስቲያን ዐርፎ ለሊቀ ጳጳሳት የሚገባው ጸሎተ ፍትሐት ሲደረግ ከቆየ በኋላ መስከረም 2 ቀን 1992 ዓ.ም ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት የጠቅላይ ቤተ ክህነት የየመምሪያውና የየድርጅቱ ሐላፊዎች የገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች በተገኙበት በሕይወተ ሥጋ እያሉ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ባዘጋጁት መካነ መቃብር ዐረፈ:: የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን:: አሜን::



## 3.32. ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ቀዳማይ

## ሊቀ ጳጳስ

## /1924 - 1967 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

አባ ገብረ እግዚአብሔር ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል በቀድሞው ቤጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት በ1924 ዓ.ም ተወለዱ:: በቤተሰባቸው እንክብካቤና ቁጥጥር በሥነ ምግባር ተኮትኩተው ከአደጉ በኋላ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ወቅቱ የሚጠይቀውን የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርት በዚያው በተወለዱበት አጥቢያ ተማሩ::

ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ትምህርታቸውን በመቀጠል የጸዋትወ ዜማ ትምህርታቸውን ጥቂት እንደ ተከታተሉ ወደ አዲስ አበባ መጡ:: ወቅቱ በመንግሥት በኩል ዘመናዊ ትምህርት በሀገሪቷ ይስፋፋ ዘንድ ወጣቶችና ቤተሰቦቻቸው የሚበረታቱበት ነበር:: ብፁዕነታቸውም ወደ ዘመናዊው ት/ቤት በመግባት የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኘውና ተፈሪ [illegible]ንን እየተባለ በሚጠራው ት/ቤት አጠናቀቁ:: ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውንም በወቅቱ በርካታ ወጣቶችን አስተምሮ ለከፍተኛ ትምህርት ባደረሰው ያኔ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት /ዛሬ ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ/ በጥሩ ውጤት አጠናቀቁ::

ብፁዕነታቸው ወደ ፊት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ሊያበረክቱ የሚችሉትን በጎ አገልግሎት የተረዳው የወቅቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርም በግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፈቃድ ለከፍተኛ የነገረ እግዚአብሔር ትምህርት ወደ ሶቪየት ኅብረት ላካቸው:: በመሆኑም በዚያ በሚገኘው ሌኒን ግራድ መንፈሳዊ አካዳሚ ትምህርታቸውን ተከታትለው በነገረ መለኮት ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አገኙ:: የጀመሩትን ትምህርት በመቀጠልም በዚያው ወደ ጀርመን ሐምቡርግ ዩኒቨርሲቲ በመሔድ ተምረው በነገረ መለኮት የማስትሬት ዲግሪያቸውን ያዙ::

ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል በዚህ ዓይነት ዕውቀታቸውን ካስፋፉ በኋላ በዚያ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያንና የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን እናትነት ለሚፈልጉ ሰዎች ትምህርቷን በማስተማር፣ አማንያንን በማጠንከር፣ ኢአማንያንን በማስተማር አጥምቀው የቤተ ክርስቲያን አባል እንዲሆኑ ለማድረግ ወደ አሜሪካ ተላኩ:: በዚህም የተነሣ በአሜሪካ፣ በትሪኒዳድና በዌስት ኢንዲስ በመዘዋወር ለረጅም ዘመናት በማገልገል የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ዓለም አቀፋዊነት አስመስክረዋል::

ከዚያም ወደ ሀገራቸው ተጠርተው ከመጡ በኋላ በ1961 ዓ.ም በጠቅላይ ቤተ ክህነት የሰብከት፣ የታሪክና ድርሰት እንዲሁም የትምህርት ክፍል ሐላፊ ሆነው ተሹመው ባካበቱት ዕውቀት ቤተ ክርስቲያናን የጠቀመ አስተዋጽኦ አበርክተዋል:: በዚሁ ዓይነት ለአራት ዓመታት ካገለገሉ በኋላ በ1964 ዓ.ም ቅዱስ ሲኖዶስ



ባደረገው የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ ተመርጠው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አንብሮተ ዕድ «አባ ሳሙኤል» ተብለው በሸዋ ክፍለ ሀገር የሐይቆችና ቡታጅራ፣ የከምባታ አውራጃዎች ጳጳስ በመሆን ተሾሙ::

ብፁዕነታቸው ባካበቱት ዓለም ዐቀፋዊ ዕውቀት የቤተ ክርስቲያናን ክብርና መብት ያስጠብቃሉ ተብሎ ስለታሰበ እንደ ተሾሙ ከሀገረ ስብከታቸው ጋር በኢትዮጵያ ፓርላማ የቤተ ክርስቲያኗ ተወካይ ሆነው እንዲሠሩ ተመርጠው ነበር:: አንድ ቀን በፓርላማው በሀገሪቱ ተከብረው ስለ ሚውሉ የሃይማኖት በዓላት አስመልክቶ ከእስልምና በኩል ቀርቦ በነበረው «የእኛ በዓላትም ይከበሩልን» ጥያቄ ላይ ፓርላማው ውይይት ካደረገ በኋላ አንድ የውሳኔ ሐሳብ በአመያዮቹ ቀረበ:: ይኸውም «በእስልምናው በኩል የቀረቡትን ሦስት ቀናት ብሔራዊ በዓላት አድርጎ ለመውሰድ በክርስትናው በኩል ከተያዙት የበዓላት ቀናት ሦስቱን እንቀንስ፣ ለዚህም ረመዳንን በቃና ዘገሊላ፣ አረፋን በማስዶት፣ መውሊድን በነሐሴ 16 እንተካ» የሚል ነበር:: ይህንን የሰሙት ብፁዕነታቸውም ጉባኤው በቀረበው የይሁንታ ሐሳብ ላይ ተወያይቶ ወደ ውሳኔ ከመድረሱ በፊት «እኔ የእመቤቴን የትንሣኤ መታሰቢያ ቀን በማላምንበት ሰው የልደት ቀን ይተካ ብዬ አልፈርምም» ብለው ጉባኤውን ረግጠው ወጡ:: ይህ በደርጉ ተሰምቶ ኖሮ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ብፁዕነታቸውን እንዲመክሯቸው፣ ላጠፉትም ጥፋት እንዲቀጧቸው ትእዛዝ ይሰጧቸዋል::

ነገር ግን ሁሉም ሳይሆን ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ዝዋይ በሚገኘው መንበረ ጵጵስናቸው ግንቦት 23 ቀን 1967 ዓ.ም ራሳቸውን አጥፍተው ተገኙ ተባለ:: ስለ አሟሟታቸው በርካታ የሚሰጡ መላምቶችና አስተያየቶች በመኖራቸው ጠለቅ ያለ ጥናት ያስፈልጋል:: ሥርዓተ ቀብራቸውም በሀገረ ስብከታቸው በምትገኘው የዝዋይ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል:: የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን:: አሜን::

www.ethiopianorthodox.org

# 3.33. ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ካልአይ ሊቀ ጳጳስ

## /1896 - 1975 ዓ.ም/





መዓርገ ጵጵስና ከመቀበላቸው በፊት አባ ገብረ ኢየሱስ ይባሉ ነበር። ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ በቀድሞው የወሎ ጠቅላይ ግዛት ዋግ አውራጃ ልዩ ስሙ ወይብላ ማርያም በተባለው ቀበሌ በ1896 ዓ.ም ተወለዱ። ብፁዕነታቸው እንደ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ከዚያው በተወለዱበት አጥቢያ ክርስትና ከተነሡ በኋላ ገና ሕፃን ሳሉ እናታቸው ከወሎ ተነሥተው ወደ አክሱም ሔዱ። ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስም ከእናታቸው ጋር ከወሎ ተነሥተው ወደ አክሱም በመሔድ እዚያው አክሱም ከተማ በምትገኘው አክሱም ጽዮን ደብር የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ተማሩ።

ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ አክሱም ከተማ መኖር ከጀመሩት እናታቸው ጋር ሆነው ለዲቁና መዓርግ የሚያበቃውን ትምህርት እንዳጠናቀቁ ይወዷቸው የነበሩትንና ከትውልድ ቦታቸው ይዘዋቸው አብረዋቸው ተሰደው የነበሩትን እናታቸውን በሞት ምክንያት አጡ። በዚህ ክፉኛ ያዘኑት ብፁዕነታቸው ሕይወታቸውን በሙሉ ቃለ እግዚአብሔርን በመማርና በማስተማር ሊኖሩ ወሰኑ። እንደ ወሰኑም እዚያው አክሱም ከተማ የጀመሩትን ትምህርት በመቀጠል ድጓ፣ ቅዳሴ፣ ዝማሬ መዋሥዕት፣ አቋቋም፣ ከዚያም አልፎ ቅኔን ተምረው በሚገባ አጠናቀቁ።

በቃለ እግዚአብሔር የወጣትነት ልቡናቸውን ካስገዙና እንዲ ሰበር ካደረጉ በኋላ ቅዱስ ወንጌል «ምንት ይበቁዖ ለሰብእ ለእመ ኩሎ ዓለመ ረብሀ ወነፍሶ ሐጕለ» እንዳለ በቀድሞው የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ሠራዬ አውራጃ ሰፍአ ወረዳ ወደ ሚገኘው የአቡነ እንድርያስ ገዳም መነኑ። ከማኅበረ መነኮሳቱ ጋር ከተቀላቀለበት ጊዜ ጀምሮም ለማኅበሩ በመታዘዝና የደከሙትን በመርዳት ሥርዓተ ገዳም ሲማሩ ቆዩ። ይህንን መንፈሳዊ አገልግሎት በትጋት ሲያበረክቱ ያያቸው የገዳሙ ማኅበርም ወዶና ፈቅዶ በወቅቱ የገዳሙ አበምኔት በነበሩት መምህር ኃይለ ሥላሴ የምንኩስናን መዓርግ እንዲቀበሉ አደረገ። በኋላም ገዳሙን በመንፈሳዊ ተልእኮ በማገልገል ላይ ሳሉ በገዳሙ ማኅበር ተመርጠው በአፈ መምህርነት ለአንድ ዓመት ከስድስት ወር አገለገሉ።

ከዚህ በኋላ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ በዚያ የሚገኙ ቅዱሳት መካናትን ለመጐብኘት ወደ ግብፅ በእግራቸው በመሔድ ቁስቋም ገዳም ገብተው የዓረብኛ ቋንቋን ማጥናት ጀመሩ። የግብፃውያኑን ሥርዓተ ገዳም ከማጥናት ጋር የዓረብኛን ቋንቋ በሚገባ ተማሩ። ከዚያም በ1926 ዓ.ም ከደብረ ቁስቋም ተነሥተው ወደ ቅድስት አገር ኢየሩሳሌም አቀኑ። በዚያም እየተዘዋወሩ ቅዱሳት መካናትን በመሳለም የእንግሊዝኛን ቋንቋን እያጠኑ ለብዙ ጊዜ ተቀመጡ።

በዚህ ዓይነት ወደ ባሕር ማዶ በመሻገር ቅዱሳት መካናትን

www.ethiopianorthodox.org

ከተሳለሙና ቋንቋ ካጠኑ በኋላ በ1940 ዓ.ም ወደ ሀገራቸው ተመለሱ። እንደ ተመለሱም የትምህርታቸውን ደረጃና መንፈሳዊነታቸውን በመመልከት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የቅዱስ ጳውሎስ ሰዋስወ ብርሃን የትምህርት ቤቱና የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ አድርገው ሾሟቸው።

በተሾሙበት ቦታ ለሁለት ዓመታት ያህል በሚገባ ካገለገሉ በኋላ የብፁዕነታቸውን ትጋት የተመለከቱት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ወደ ቅዱስ ፓትርያርኩ ጽ/ቤት ተዛውረው የውጭ ሀገር እንግዶች ተቀባይና አስተርጓሚ አድርገው ሾሟቸው። አሁንም በተሾሙበት ቦታ በቅንነትና በትጋት በማገልገል ላይ ሳሉ በ1945 ዓ.ም መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲሰጡና ቤተ ክርስቲያንን እንዲያስፋፉ ወደ አሜሪካ ተላኩ። በዚያም በዌስት ኢንዲስ፣ በጉያና፣ በትሪኒዳድና በቶቤጎ በጠቅላላው ሃያ የሚሆኑ አብያተ ክርስቲያናትን መሥርተዋል። ከ30 ሺ በላይ የሚሆኑ ምእመናንንም አስተምረው በማጥመቅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባላት እንዲሆኑ አድርገዋል።

ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ በዚህ ዓይነት በስብከተ ወንጌልና መንፈሳዊ አገልግሎት አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነጽ ለ19 ዓመታት ያህል ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ የካቲት 5 ቀን 1964 ዓ.ም በተደረገው የኤጲስ ቆጶሳት ሹመት የደቡብና የሰሜን አሜሪካ ጳጳስ ተብለው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ አንብሮተ እድ ተሾሙ። በዚህ ሹመት ወደ አሜሪካ ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1971 ዓ.ም በጠቅላላው ለስምንት ዓመታት ያህል ሰፊ አገልግሎት ሲሰጡ ቆዩ።

በ1971 ዓ.ም ቅዱስ ሲኖዶስ ዕረፍት እንዲያደርጉ በወሰነው መሠረት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው መደበኛ ባልሆነ መልኩ አገልግሎት በመስጠት ላይ እንዳሉ ባደረባቸው ሕመም የካቲት 25 ቀን 1975 ዓ.ም ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ሲሆን ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

ልክ በ79 ዓመት ዕድሜያቸው ያረፉት የብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ አስከሬን ወደ አሥመራ ተወስዶ የካቲት 28 ቀን 1975 ዓ.ም ባደጉበትና የምንኩስና መዓርግ በተቀበሉበት በአቡነ እንድርያስ ገዳም ተፈጽሟል። የብፁዕነታቸው ረድኤት ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን።



# 3.34. ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ካልአይ

# ሊቀ ጳጳስ

## /1919 - 1996 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ በቀድሞው አጠራር በሸዋ ጠቅላይ ግዛት እንሳሮ ወረዳ ልዩ ስሙ ወረንጨፌ በተባለው ቦታ መጋቢት 29 ቀን 1919 ዓ.ም ተወለዱ። የአባታቸው ስም መምህር ገብረ መድኅን ተክሌ፤ የእናታቸው ደግሞ ወ/ሮ ወለተ ማርያም ባዩ ይባል ነበር። በሰመ ጵጵስናቸው ማቴዎስ ተብለው ከመጠራታቸው በፊት ሊቀ ሊቃውንት ኃ/መስቀል ይባሉ ነበር።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመኼድ አባ ተሰፋ ጊዮርጊስ ከተባሉ መምህር ንባብና ሰዓታት፤ ከመምህር ንጉሤ ገብረ ሥላሴ ጸዋትወ ዜማ ተማሩ። ከዚያም ትምህርታቸውን ለማስፋፋት ወደ ሰሬ መድኃኔ ዓለም በመኼድ ከታወቁት ሊቅ ከመምህር ጥበቡ ገብረ ማርያም ዓለሙ ትርጓሜ ሐዲሳትን፣ ከመሪ ጌታ አንዳርጌና ከመሪ ጌታ አበራ ታቦር የፍትሐ ነገሥትንና የመጽሐፈ መነኩሳት ትርጓሜን አሒዱ። በኋላ ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ከተባሉት መምህር ወልደ ሚካኤል ብርሃን መስቀልም የቅዳሴ ዜማን በሚገባ ተማሩ።

ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ በ1925 ዓ.ም ከግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ መዓርገ ዲቁናን፣ በ1937 ዓ.ም ከዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ምንኩስናን፣ በ1938 ዓ.ም ከብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ቅስናን ተቀበሉ።

ብፁዕነታቸው ዲቁና እንደ ተቀበሉ በታላቁ የደብረ ሊባኖስ ገዳምና በወይባ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ለሰባት ዓመታት፣ በደብረ ሊባኖስ ሜጋል በማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ለሦስት ዓመታት፣ እንደ ገና ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመመለስ ለአራት ዓመታት ያህል በትጋት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አገለገሉ።

በዚህ ዓይነት ትምህርታቸውን ሲያስፋፉና ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ የቆዩት ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ገና ከሕፃንነታቸው ጀምሮ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ራሳቸውን መስጠታቸውን የተመለከቱት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ወደ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በማቅረብ የታላቁ ገዳም የደብረ ሊባኖስ ገዳም ጸባቴ ሆነው እንዲሾሙ አደረጉ። ሹመቱን በአኰቴት የተቀበሉት ብፁዕነታቸውም ከተሾሙበት ጊዜ ጀምሮ ለስድስት ዓመታት ያህል ገዳሙን በፍቅርና በሰላም አስተዳድረዋል።

ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ በደብረ ሊባኖስ ገዳም በጸባቴነታቸው ዘመናት ባሳዩት ፍሬያማ ሥራ የተነሣ ለበለጠ ሥልጣንና መዓርግ ተመረጡ። በዚህም በ1952 ዓ.ም በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ በአታ ለማርያም ገዳም ከነሙሉ መዓርጉና ሽልማቱ ሊቀ ሊቃውንት ሆነው ተሾሙ።



ብፁዕነታቸው ከሀብተ ክህነት ጋር የአስተዳደር ዕውቀት የተሰጣቸው አባት ነበሩ። በመሆኑም ታላቁን አደራና ሐላፊነት ተቀብለው ወደ ታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም ከመጡም በኋላ የተሰበረውን በማስጠገን፣ ያረጀውን በማሳደስ፣ የጐደለውን በማሟላት ከሠሯቸው በርካታ ሥራዎች በተጨማሪ በመታሰቢያ ቤቱ ያለው ነባር መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በየዘርፉ እንዲስፋፋና ሊቃውንትን በብዛት እንዲያወጣ አድርገዋል። ከዚህም በተጨማሪ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤትን በመክፈት ዘመናዊና መንፈሳዊ ዕውቀት እንዲገበይበት፣ በተለያዩ ቦታዎች ዘመናውያን ሕንፃዎችንም በማሠራት የገዳሙ አስተዳደር የሚረዳበትን ከፍተኛ የገቢ ምንጭ አስገኝተዋል። በዚህም የገዳሙ ሊቃውንትና ካህናት ተገቢ ደመወዝ እንዲያገኙና የኑሮ አቋማቸው እንዲሻሻል አድርገዋል። ብፁዕነታቸው ካሠሯቸው ዘመናውያን ሕንፃዎች ውስጥ መኻል ፒያሳ የሚገኘውና ዘውዲቱ ሕንፃ ተብሎ የተሰየመው ሕንፃ አንዱ እንደሆነ ይነገራል።

ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ በዘመነ ሊቀ ሊቃውንትነታቸው ለዘመናት ካለ ቤተ ልሔም የቆየችዋን ታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም ቤተ ልሔምን አሠርተውላታል። ከዚህም በተጨማሪ በጣልያን ወረራ ዘመን ከገዳሟ የወጡትን ቅርሶች እንዲመለሱ በማድረግ ረገድ የሚመሰገን ጥረት አድርገዋል። ወደ ገዳሙ እንዲመለሱ ካደረጓቸው ቅርሶች ውስጥ ጣልያን እንጦጦ አካባቢ ቀብሮት የነበረውን የቤተ ክርስቲያኗን ጉልላት ዘውድ ከተቀበረበት በጠቋሚ አስወጥተው እንዲመለስ አድርገዋል።

ብፁዕነታቸው በነበራቸው አስተዳደራዊ ስልት ዛሬ በቦታው አሻራቸው የሚታዩ በርካታ ደንቦችንና መመሪያዎችን አውጥተው አልፈዋል። ከእነዚህም ውስጥ ሕጋውያን ካህናት ወጥተው ቦታዎ በደናግል መነኮሳትና ያላገቡ ዲያቆናት እንድትቀደስና እያንዳንዱ አገልጋይም የየራሱ ምድብና ስም እንዲኖረው ያደረጉት ይጠቀሳሉ።

እሳቸው ለንጽሕናቸው ተጨናቂ የመሆናቸውን ያኽል አከካባቢያቸውም የጸዳ በተለይ ሁሉም የሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ ክፍል ዕለት ዕለት እንዲጸዳ ያደርጉ ነበር ይባላል። አንድ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያኗ ሲገቡ ከላይ ከጾሙ ላይ አንዲት ሸረሪት ድሯን እየገመደች ወደ ታች ስትመጣ ያያሉ። ይኸንን የተመለከቱት ብፁዕነታቸው የጽዳት ሐላፊውን ይጠሩና «ያቺ ምንድን ናት?» ይሉታል። ሠራተኛውም ደንግጦ «ሊቀ ሊቃውንት፡ እኔ አሁን አጽድቼው ዘወር ስል እሷ ትመጣለች፤ ምን ላድርግ?» ይላቸዋል። በዚህ ጊዜ እሳቸውም «እሷ ሥራዋን አክብራ ስትመጣ አንተ ዬት እየሔድክ ነው?»። ቢሉ ተናገሩ ይባላል።

በዚሁ ገዳም ለዐሥራ ሁለት ዓመታት ካገለገሉ በኋላ በ1964

www.ethiopianorthodox.org

ዓ.ም በተደረገው የኤጲስ ቆጳሳት ምርጫ ተመርጠው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ እንብሮተ እድ «ብፁዕ አባ ማቴዎስ» ተብለው በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ ሆነው ተሾሙ::

ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ጳጳስ ሆነው ወደ ቦታው ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ ለአጠቃላይ ገዳማቱ አስተዳደር መጠናከር ከማኅበረ መነኮሳቱ ጋር በመግባባት እያሌ ሥራዎችን አከናውነዋል:: በተለይ ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ነገሥታትና ንግሥታት ለገዳማቱ የገቢ ምንጭ ይሆኑ ዘንድ በኢየሩሳሌም ከተማ እየገዙ የሰጧቸው፣ ነገር ግን ከጊዜ በኋላ በሀገሪቱ መንግሥት የተወረሱ ሕንፃዎችን በነበራቸው የአስተዳደር ስልት አስመልሰዋል:: የገዳሙን ገቢ ብቻ እየተጠባበቁ ይኖሩ የነበሩ መነኮሳትም ትምህርት ተምረው ለገዳሙ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ እንዲያስገኙ ያደርጉ ነበር::

በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ጳጳስ በመሆን ለአምስት ዓመታት ያህል ካገለገሉ በኋላ በ1970 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው ለአንድ ዓመት አገለገሉ:: ወቅቱ የቀይ ሽብር ዘመቻ በሚል በርካታ ወጣቶች ይጨፈጨፉበት የነበረ በመሆኑ ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ጉዳዩ አገርን ከመጉዳት በስተቀር ጥቅም እንደ ሌለው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ተቃውሞአቸውን ያሰሙ ነበር:: በዚህ የተነሣ በደርግ ባለ ሥልጣናት ከሥልጣናቸው እንዲነሡ ተደረገ:: ብፁዕነታቸው በዚህ ጊዜ ወዳደጉበትና ወደ ተሾሙበት ታላቁ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ሔደው የተለመደ አገልግሎታቸውን ሲያከናውኑ ቆዩ::

በ1982 ዓ.ም ምንም እንኳን እርሳቸው ለመመለስ ባይፈልጉም በአባቶች ምክርና አስገዳጅነት ከደብረ ሊባኖስ ገዳም ወጥተው ወደ አዲስ አባባ በመምጣት በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳምና ት/ቤት የበላይ ሐላፊ ሆነው ተሾሙ:: ገዳሙን ለስድስት ዓመታት በማስተዳደር ካገለገሉ በኋላ በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ በ1985 ዓ.ም ወደ መጀመሪያ መንበረ ጵጵስናቸው ኢየሩሳሌም ተመልሰው እንዲያገለግሉ ተደረገ:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ 1991 ዓ.ም በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማት ሊቀ ጳጳስ በመሆን ካገለገሉ በኋላ በ1991 ዓ.ም ወደ ሀገራቸው ተመልሰው እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው ድረስ የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤልና የታዕካ ነገሥት በኣታ ለማርያም አብያተ ክርስቲያናት የበላይ ሐላፊ በመሆን አገልግለዋል::

ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ቤተ ክርስቲያን በሐላፊነት ባስቀመጧቸው ቦታዎች ሁሉ ያለ ምንም ድካምና መሰልቸት ቤተ ክርስ-



ቲያንን አገልግለዋል:: በደብረ ሊባኖስ ገዳም ጸባቴ ሆነው በሚያገለግሉበት ወቅት የገዳሙ ት/ቤቶች ተጠናክረውና ተስፋፍተው ታዋቂ መምህራንን እንዲያስገኙ፣ የገዳሙ የቆየ ሥርዓትና ትውፊት ተጠብቆ እንዲኖር፣ የገዳሙ መተዳደሪያ ሀብትና ንብረት ተከብሮ በአግባቡ ለተፈላጊው አገልግሎት እንዲውል ከፍተኛ ጥረት በማድረግ የተሳካ አገልግሎት አበርክተዋል::

ከዚህም ጋር ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለ29 ዓመታት የጸለዩበትንና አጽማቸው ያረፈበትን የደብረ አስቦን ዋሻ ለዕይታና ለጥበቃ በሚያመች ሁኔታ በማሠራት ቅድስናውን ጠብቆ እንዲኖር አድርገዋል::

ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ሔደው በሚያገለግሉበትም ጊዜ የገዳሙ ሥርዓተ ማኀበር ተከብሮና ተጠብቆ እንዲኖር ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል:: በየዘመኑ የነበሩ ደጋግ የኢትዮጵያ ነገሥታት፣ ንግሥታት፣ መኳንንት፣ መሣፍንት፣ ወይዛዝርት፣ ምእመናንና ምእመናት ለገዳሙ አስተዳደር ሕልውና ድጋፍ እንዲሆኑ ያወረሷቸው ንብረቶች፣ የለገሡት ሀብት ሁሉ እንዲከበር፣ በቁልፍ የተወሰዱት እንዲመለሱና በሥርዓት አገልግሎት እንዲሰጡ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል:: የዴር ሡልጣንን የኢትዮጵያ የባለቤትነት መብትና ሕጋዊነት ባለው ተጨባጭ ማስረጃ መሠረት እንዲከበር ታላቅ ሐላፊነት የተመላበት እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ቆይተዋል:: ከዚህም በተጨማሪ በአልዓዛር ቢታንያ በምስካበ ቅዱሳን የሚገኘውን የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ቤተ ክርስቲያን አሠርተዋል::

በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም በበላይ ሐላፊነት በቆዩበትም ጊዜ የገዳሙ መንፈሳዊ ሕይወት እንዲጠበቅ፣ የቤተ ክርስቲያኑ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ሥርዓትን ጠብቆ እንዲመራና ምእመናን በሥነ ሥርዓት እንዲገለገሉ መልካም ምሳሌነት ያለውን አመራር ሰጥተዋል:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል ዘመኑን በመዋጀት ለሀገርና ለወገን አስተዋፅኦዋን እየሰጠች እንደ ሆነ ቋሚ ምስክር የሆነው በገዳሙ ቅጽረ ግቢ የሚገኘው ዘመናዊና መንፈሳዊ ት/ቤት ዕድገት እንዲኖረውና ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርስ ብርቱ ጥረት አድርገዋል:: ከዚህም ጋር ለገዳሙ ሁለንተናዊ አገልግሎት የሚሰጥ አንድ ክሊኒክና ልዩ ልዩ የገቢ ምንጭ የሚያስገኙ ሌሎች ተቋማትን አቋቁመዋል:: በእነዚህና በሌሎች አገልግሎታቸው ከተለያዩ ታላላቅ ግለሰቦችና ካገለገሉባቸው ቅዱሳት መካናት የተለያዩ ስጦታዎች ተበርክተውላቸዋል::

ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ የሚያውቁትን ለማሳወቅ ከነበራቸው ጉጉትና ቸርነት የተነሣ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ከቃለ ስብከት ጋር በመጽሐፍም ለምእመናን አስተላልፈዋል:: በተለያዩ ጊዜያት

www.ethiopianorthodox.org

በዓላትና አጽዋማት፣ የሃይማኖተ አበው ተዋጽኦ በግእዝና በአማርኛ፣ ሥርወ ሃይማኖት፣ የሰባቱ ጊዜያት ጸሎት፣ ስምከ ሕያው /የዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ ታሪክ/፣ ኩኩሕ መንፈሳዊ የደብረ ጽጌ ገዳም ታሪክ፣ ታሪክህን አስታውስ /ስለ ኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ታሪክ/፣ ዝክረ ጻድቅ ለዓለም ይሄሉ /የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ታሪካዊ ማስታወሻ/ የተሰኙ መጻሕፍትን እሳትመው ለምእመናን አበርክተ ዋል፡፡ ሌሎች መጻሕፍትንም አዘጋጅተው ለማሳተም በዝግጅት ላይ ነበሩ፡፡

ብፁዕነታቸው ገና ልጅ ሆነው በገዳም ማገልገል ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ሹመት አያጣቸውም ነበር ይባላል፡፡ በዚህም ገና ከአናኮዕ /የገዳም እንጨት ለቃሚዎች/ አለቃነት ጀምሮ እስከ ከፍተኛው የቤተ ክርስቲያን ሹመት ድረስ ቤተ ክርስቲያናቸውን በትጋት አገልግለዋል፡፡

ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ከረጅም ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አገልግ ሎት በኋላ ጥቅምት 30 ቀን 1996 ዓ.ም በተወለዱ በ77 ዓመት ዕድሜያቸው በድንገት ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡ በማግሥቱ ኅዳር 1 ቀን 1996 ዓ.ም በጠቅላይ ቤተ ክህነት የስብከተ ወንጌል አዳራሽና በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ጸሎተ ፍትሐት ሲደረ ግላቸው ከዋለና ካደረ በኋላ አስከሬናቸው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ልዩ ልዩ የመምሪያ ሐላፊዎች፣ የብፁዕነታቸው ቤተሰቦችና ወዳጆች፣ እንዲሁም በርካታ የገዳሙ መነኮሳትና ተማሪዎች በተገኙበት ታኅሣሥ ኅዳር 2 ቀን 1996 ዓ.ም በደብረ ሊባኖስ ገዳም በሕይወት በነበሩ ጊዜ ባዘጋጁት መካነ መቃብር ዐረፉ፡፡ የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን፡፡ አሜን፡፡



# 3.35. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ሣልሳዊ ሊቀ ጳጳስ

## /1921 - 1993 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

አባ ክፍለ ዮሐንስ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በሰሜን ሸዋ በመንዝና ግሼ አውራጃ በጌራ ምድር ወረዳ ልዩ አካባቢው አራድማ ግራርያ ሚካኤል በተባለው ቦታ ሰኔ 30 ቀን 1923 ዓ.ም ተወለዱ። የአባታቸው ስም አቶ ሽንቁጥ፣ የእናታቸው ደግሞ ወ/ሮ በላይነሽ ሀብተ ማርያም ይባል ነበር።

በወላጆቻቸው እንክብካቤ በሥርዓት አድገው ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ በአካባቢው ከነበሩ መምህራን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ተምረው አጠናቀቁ። ከዚያም ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከብፁዕ አቡነ ቄርሎስ መዓርገ ዲቁና ተቀበሉ።

ከዚያም ትምህርታቸውን ለመቀጠልና በመንፈሳዊ ሕይወት ለመኖር በነበራቸው ፍላጎት ወደ ሰላሌ አውራጃ ሔደው በፍቼ ከተማ ከአለቃ አሸቴ ጸዋትወ ዜማ ተማሩ። በመቀጠልም ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ገብተው የደብረ ዓባይ ቅዳሴ ከአባ ይትባረክና ከመሪ ጌታ ወርቁ ፣ ቅኔ ከነአገባቡ ከመሪ ጌታ ዓምዴ፣ ውዳሴና ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ከአባ ገብረ ማርያም ተማሩ።

ከዚህ በኋላ ወደ መንፈሳዊነቱና ገዳማዊ ሕይወት በማምራት በተማሩበት የደብረ ሊባኖስ ገዳም አንጨት በመሸከም፣ ውኃ በመቅዳት፣ ንፍሮ በመቀቀል፣ እንጀራ በመጋገር ደካሞችን በመርዳት ለገዳሙ አገልግሎት ሲሰጡ ቆዩ። በዚሁ ጊዜ የሰጡትን አገልግሎትና ያላቸውን የግብረ ገብነት ዝንባሌ በማየት በማኅበሩ ፈቃድ የምንኩስና መዓርግ በማከታተልም የቅስናና የቁምስና መዓርጋት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ተሰጣቸው።

በእነዚሁ መዓርጋት ገዳሙን በማገልገል ላይ እንዳሉ በማኅበሩ ፈቃድና ምርጫ የገዳሙ ሊቀ ዲያቆናት ሆነው ተሾሙ። በዚሁ ገዳሙን ብዙ ሲያገለግሉ ቆይተው ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በመንበረ ፓትርያርክ በላአካነ አርድዕትነት ተመድበው በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ከመምህር ገብረ ማርያም ዓለሙ፣ በመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ከመምህር ብርሃኑ ትርጓሜ ሐዲሳትን ተማሩ። ከዚህም ጋር በታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም የዳዊትን ትርጓሜ ከመጋቤ ምሥጢር ጌራ አሔዱ። ከዚህም ጋር የትምህርተ ኀቡዓትን የኪዳንንና የባሕረ ሐሳብን ትርጓሜ ከመምህር ወልደ ሰንበት ተማሩ። ፍትሐ ነገሥቱንም ከእኚሁ መምህር ቀጽለዋል።

ከዚህ በላይ በተገለጸው ዓይነት የቤተ ክርስቲያን ትምህርታቸውን ካጠናቀቁና በታላቁ ገዳም በደብረ ሊባኖስ የሚገባውን አገልግሎት ሲሰጡ ከቆዩ በኋላ ከመስከረም ወር 1955 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 1955 ዓ.ም በአሰቦት ገዳም በመምህርነት፣ ከሐምሌ 1955



ዓ.ም - መስከረም 1959 ዓ.ም በደብረ ሊባኖስ ገዳም በጸባቴነት፣ ከየካቲት ወር 1959 ዓ.ም - ሰኔ 1967 ዓ.ም በደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤልና የእንጦጦ ደብረ ኤልያስ አስተዳዳሪ ሆነው ሁለቱን አድባራት እያስተዳደሩ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የመንፈሳዊ ጉባኤ ምክር ቤትና የፍትሕ መንፈሳዊ ስብሳቢ ሆነው ሰፋ ያለ አገልግሎት ሲሰጡ ቆዩ። በተጨማሪም ከሰኔ ወር 1966 ዓ.ም ጀምሮ በሊቀ ሊቃውንትነት መዓርግ በዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ መታሰቢያ በአታ ለማርያም ገዳም በአስተዳዳሪነት በማገልገል ላይ እያሉ ለታላቁ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና መዓርግ ተመረጡ። በመሆኑም መስከረም 16 ቀን 1968 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አንብሮተ እድ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ተብለው የወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ረዳት ጳጳስ ሆነው ተሾሙ።

ብፁዕነታቸው ቀደም ሲል ይዘውት በነበረው የሊቀ ሊቃውንትነት መዓርግ የዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ መታሰቢያ በአታ ለማርያም ገዳምን በማስተዳደርና የረዳትነት አገልግሎታቸውን ገና ሲጀምሩ ባላወቁት ሁናቴ በወቅቱ በነበረው የደርግ መንግሥት ከዛሬው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተ/ሃይማኖት እና ከብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ጋር ታሰሩ። ከ1968 ዓ.ም - 1975 ዓ.ም ድረስ ለሰባት ዓመታት ያህል የግፍና የመከራ ጊዜ ካሳለፉ በኋላ በ1976 ዓ.ም ተፈተው በሐረርጌ ሀገረ ስብከት የሰሜንና ምዕራብ አውራጃዎች ጳጳስ በመሆን እስከ 1981 ዓ.ም አገለገሉ። ከ1981 ዓ.ም - 1984 ዓ.ም ደግሞ ቀድሞ ረዳት ጳጳስ ሆነው ተመድበውበት በነበረው የወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፣ ከ1985 ዓ.ም ጀምሮም በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የፍትሕ መንፈሳዊ ጉባኤ የበላይ ሐላፊ ሊቀ ጳጳስ ሆነው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸውን አገልግለዋል።

ብፁዕነታቸው ሁለተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ርእሰ መንበርነታቸው ሲያቆም ቤተ ክርስቲያኗን በጊዜያዊነት ይመራ ዘንድ በቅዱስ ሲኖዶስ ተቋቁሞ የነበረውና አምስት ሊቃነ ጳጳሳት አባላት የነበሩት ኮሚቴ አባል ሆነው ተመርጠው አገልግለዋል።

ብፁዕነታቸው በስተመጨረሻ ለሰባት ዓመታት የደረሰባቸው ባደልና መንገላታት የተነሣ ጤናቸው እየተጓደለ ሔደ። ምንም እንኳን ያገግሙ ዘንድ በጠበልና በሕክምና ሲረዱ ቢቆዩም ሕመማቸው እየባሰባቸው በመሔዱ ኅዳር 20 ቀን 1989 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ሥርዓተ ቀብራቸውም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ

www.ethiopianorthodox.org

ዘአክሱም ወሰጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፣ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ልዩ ልዩ የመምሪያና የድርጅቶች ሐላፊዎች በተገኙበት በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተፈጽሟል። የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን። አሜን።



# 3.36. ብፁዕ አቡነ ሰላማ ሣልሳይ ሊቀ ጳጳስ

/1931 - 1996 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

መዓርገ ጵጵስና ከመቀበላቸው በፊት አባ ሐዋዝ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሰላማ በያኔው አጠራር ሸዋ ጠቅላይ ግዛት ሰላሌ አውራጃ ጎሐ ጽዮን ተብሎ በሚታወቀው ወረዳ ከአባታቸው ከአቶ በየነ ገብረ ሕይወትና ከእናታቸው ከወ/ሮ መርዓተ መድኅን ኅዳር 12 ቀን 1931 ዓ.ም ተወለዱ።

በቤተ ሰቦቻቸው የቅርብ እንክብካቤ ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ ከዚያው ተወልደው ባደጉበት አካባቢ አባ እንግዳ ከተባሉ መምህር የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ማለትም ፊደልንና ንባብን በሚገባ አጠናቀቁ። ከዚያም ትምህርታ ቸውን በመቀጠል መምህር ዘገየ ከተባሉ ሊቅ ሁለተኛውን ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን /ጸዋትወ ዜማን/ በአጭር ጊዜ ተምረው አጠናቀቁ። ከዚህ በኋላ በ1947 ዓ.ም ያኔ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መዓርገ ዲቁና ተቀበሉ።

የመንፈሳዊውን ትምህርት ነገር ከዳር ሳያደርሱ ላለመቀመጥ ለራሳቸው ቃል የገቡት ብፁስነታቸው አሁንም ጊዜ ሳያጠፉ በዲቁና ቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸውን እያገለገሉ መምህር ጥበቡ ጋሜ ከተባሉት የቅኔ ሊቅ ቅኔን በሚገባ ተማሩ።

ብፁዕ አቡነ ሰላማ በተማሪነታቸው ከጓደኞቻቸው ጋር የሚግባቡና በመምህሮቻቸውም ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው እንደ ነበሩ በቅርብ የሚያውቋቸው ይመሰክሩላቸዋል። ለዜማ ትምህርት ከፍተኛ ፍላጎትና ጉጉት የነበራቸው ብፁዕነታቸው በዚያው በትውልድ አካባቢያቸው የቅኔውን ትምህርት እንዳጠናቀቁ በመምህ ሮቻቸውና ታላላቅ ጓደኞቻቸው ይሰሙት በነበረው መሠረት ወደ ጎንደር በመሸገር የዜማ ዕውቀታቸውን ለማስፋፋት ወሰኑ። በመሆኑም ጎንደር ውስጥ ፋርጣና ጋይንት አውራጃዎች በሚገኙ ልዩ ልዩ ቅዱሳት መካናት በመዘዋወር አለቃ ቀለመ ወርቅ ከተባሉ መም ሀር ቁም ዜማን፣ መሪጌታ ወልደ ሰንበት ከተባሉት ሊቅ ዘንድም አቋቋምን በሚገባ ቀጸሉ። ከዚህ በኋላ ወደ ሀገሬ ልመለስ ሳይሉ ጎንደር ከተማ ወደ ሚገኘው ዕውቁ የአቋቋም ማስመስከሪያ መንፈ ሳዊ ዩኒቨርሲቲ በመሔድ የአቋቋሙን ይትበሃል በሚገባ አጠኑ።

የዜማውን ትምህርት እስከ ከፍተኛው ደረጃ ድረስ በዚህ ዓይነት በሚገባ ያጠናቀቁት ብፁዕ አቡነ ሰላማ በመቀጠል ወደ አራተኛውና የመጨረሻው መንፈሳዊ የትምህርት ደረጃ ተሸጋገሩ ይኸውም እሳቸውም እንደ አባቶቻቸው የመጻሕፍትን ምሥጢር በመመርመር ቤተ ክርስቲያንን በተጠያቂነት ለማገልገል የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ትምህርት መጀመር ነበር። በመሆኑም የአቋቋም ትምህርቱን በሚገባ ካጠናቀቁ በኋላ ወላጆቻቸውንና



ዘመዶቻቸውን በመተው ምናኔ የወጡለትን ትምህርት ከዳር ሊያደርሱ እዚያው በጎንደር ከተማ በሚገኘው ዓቢየ እግዚእ ቤተ ክርስቲያን ብሉያትን ያስተምሩ ወደ ነበሩት መምህር ወልደ ሰንበት ዘንድ በመሔድ ብሉይ ኪዳንን ማሔድ ጀመሩ። ይሁን እንጂ ጥቂት እንደተማሩ መምህራቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ነገር ግን ወንበራቸው ለረጅም ጊዜ ሳይታጠፍ መምህር ጸጋ፣ ቀይቶም መምህር ኃይለ ማርያም የተባሉ ሊቃውንት በመተካታቸው የብሉያት ትምህርታቸውን በሚገባ አጠናቀቁ።

መንፈሳዊ ትምህርት ሊያሸንፉት እንጂ ሊያሸንፋቸው የማይችል እንደሆነ በተግባር ያስመሰከሩት ብፁስነታቸው በነበራቸው ቀለም የመያዝ ብቃት ብሉያቱን ከተጠቀሱት መምህራን በአጭር ጊዜ አጠናቀው የእነ አባ እንጦንስንና አባ መቃርስን አሠረ ፍኖት ለመከተል በ1961 ዓ.ም ወደ ታላቁ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም በመውረድ ሥርዓተ ምንኩስናን ፈፀሙ። ከዚያም የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትር ጓሜ በመቀጠል ጎንደር ውስጥ መምህር ክፍሌ ከተባሉ ሊቅ ዘንድ በሚገባ ተምረው አጠናቀቁ።

ከዚያም በ1964 ዓ.ም በወቅቱ የጎጃም ሀገረ ስብከት ጳጳስ ከነበሩት ብፁዕ አቡነ ማርቆስ ማዕርገ ቅስናን ተቀበሉ። ከዚህ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በወቅቱ በአብነት ትምህርቱ ረጅም መንገድ ለተጓዙ ሊቃውንት በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ይሰጥ የነበረውን የኮርስ ትምህርት ለመከታተል ዕድል ስላገኙ ወደ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤቱ ገቡ። ብፁዕነታቸው ይሰጥ የነበረውን ኮርስ እየወሰዱ በትርፍ ጊዜያቸው በአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት እየተዘዋወሩ ቃለ እግዚአብሔርን ለምእመናኑ ያስሙ እንደ ነበር የሚያስታውሱ ይናገራሉ። በወቅቱ በከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤቱ የሚሰጠውን ኮርስ ይከታተሉ የነበሩ ደቀ መዛሙርት ያደርጉት እንደነበረውም ብፁዕነታቸው ከአዲስ አበባው በተጨማሪ በርከት ወዳሉ አህጉረ ስብከትና አውራጃዎች በመዘዋወር የተማሩትን ቃለ እግዚአብሔር በሰፊው አስተምረዋል።

ብፁዕነታቸው በዚህ ዓይነት ብዙ ተንገላተው የተማሩላትን ቤተ ክርስቲያን በማገልገል ላይ ሳሉ ትጋታቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ችሎታቸውን ያየው ጠቅላይ ቤተ ክህነት ኮርሳቸውን እንዳጠናቀቁ የገነተ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ አድርጎ ሾማቸው። ብፁዕነታቸው ሹመቱን በአኮቴት በመቀበል የተሰጣቸውን ሐላፊነት ከማኅበረ ካህናቱና የአጥቢያው ምእመናን ጋር በመሆን ለጥቂት ዓመታት እንደ ተወጡ ወደ ደብረ አሚን ተከለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ተዛውረው አገልግሎት እንዲሰጡ ተደረጉ። በዚያም አገልግሎታቸውን በትጋት እየፈጸሙ ሳለ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ

www.ethiopianorthodox.org

ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በ1971 ዓ.ም ለከፍተኛው ሐዋርያዊ ተልእኮ ከመረጠቻቸው 13 ኤጲስ ቆጶሳት መካከል አንዱ ሆነው ተመረጡ::

በዚህም መሠረት የካቲት 2 ቀን 1971 ዓ.ም በተደረገው የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ «ብፁዕ አባ ሰላማ የባሌ ሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጶስ» ተብለው በሦስተኛው የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እንብሮተ እድ ተሠየሙ::

በዚህ ዓይነት ለከፍተኛው የቤተ ክርስቲያኒቱ ሥልጣንና ሐላፊነት የደረሱት ብፁዕነታቸው ሹመቱን በእኩቴት ተቀብለው ወደ ሀገረ ስብከታቸው በመሔድ አገልግሎታቸውን መፈጸም ጀመሩ:: ወደ ቦታው ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ ምንም እንኳን በወቅቱ በሀገሪቱ የነበረው ርዕዮተ ዓለም መንግሥተ እግዚአብሔርን እንደ ልብ ለመስበክ የማይቻልበት ቢሆንም ዛቻውንና ማስጠንቀቂያውን ሳይሰቀቁ ለወንጌል ስብከት ቅድሚያ በመስጠት በየ አውራጃውና ወረዳው በመዘዋወር ቃለ እግዚአብሔርን ለሀገረ ስብከታቸው ምእመናን በሰፊው አዳርሰዋል:: በልማትም ረገድ ከሀገረ ስብከቱ ካህናትና ምእመናን ጋር በመተባበር ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን አከናውነዋል::

እነዚህንና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች በመፈጸም እስከ 1974 ዓ.ም ድረስ በባሌ የቆዩት ብፁዕነታቸው በ1975 ዓ.ም በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ጳጳስ ሆነው በመሾም ወደ ዚያው እቀኑ:: በዚያም ከማኅበረ መነኮሳቱና በአካባቢው ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ምእመናን ጋር በመስማማት ለሦስት ዓመታት ከፍተኛ አገልግሎት ሲያበረክቱ ቆዩ:: ቅዱስ ሲኖዶስ ኅዳር 17 ቀን 1977 ዓ.ም በወሰነው መሠረት ብፁዕነታቸው ከኢየሩሳሌም ተመልሰው ወደ ቀደመ ሀገረ ስብከታቸው ባሌ በመሔድ ሐዋርያዊ ተልእኮአቸውን እንዲፈጽሙ ተደረጉ:: ወደ መጀመሪያ ሀገረ ስብከታቸው መመለሳቸውን በደስታ የተቀበሉት ብፁዕ አቡነ ሰላማ ወደ ሚያውቁትና ወደ ሚያውቃቸው ሕዝበ ክርስቲያን በመመለስ ሰፊውንና ከ13 ዓመታት በላይ የዘለቀ አገልግሎታቸውን ቀጠሉ::

ብፁዕ አቡነ ሰላማ በነበራቸው የስብከት ጸጋና ቤተ ክርስቲያኗ በምንም ያልተበረዘውን ቃለ እግዚአብሔር ሳልደረሳቸው ታዳርስ ዘንድ በየስብሰባው ያቀርቧቸው በነበሩ ጠቃሚ አሳቦች የተነሣ ከያዙት ሀገረ ስብከት ጋር በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ የበላይ ሐላፊ ሆነው እንዲሠሩ ተመርጠው ከየካቲት 1 ቀን 1989 ዓ.ም እስከ 1991 ዓ.ም ድረስ አገልግለዋል:: ከዚህም በተጨማሪ ቅዱስ ሲኖዶስ ሰኔ 5 ቀን 1990 ዓ.ም በወሰነው መሠረት ወደ አውሮፓ ክፍለ



ዓለም በመሔድ ለሦስት ወራት ሐዋርያዊ አገልግሎትን ሰጥተው ተመልሰዋል::

ብፁዕ አቡነ ሰላማ በባሌ ሀገረ ስብከት ለረጅም ዘመናት ካገለገሉ በኋላ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ከሰኔ 1 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት ተዛወሩ:: ብፁዕነታቸው ወደ ጎንደር ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ ያለምንም ድካምና መሰልቸት ጉባኤያት እንዲስፋፉ፣ ቅርሶች እንዲጠበቁ፣ ቃለ እግዚአብሔር በዐውደ ምሕረት በሰፊው እንዲነገር አድርገዋል:: ቀድሞ በጎንደር ከተማ የነበሩትንና በተለይ በግራኝ አሕመድ ወረራ ዘመን የተቃጠሉት አብያተ ክርስቲያናት የነበሩባቸው ቦታዎች በተመራማሪዎች ተጠንተው ቦታቸው እንዲከበር ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል:: በተለይ በሕይወታቸው መጨረሻ አካባቢ «ድህነት የሰው ልጅ ጠላት ነው» የሚለውን አቋማቸውን በመያዝ በሀገረ ስብከታቸው በመዘዋወር ሕዝቡን ስለ ልማት፣ ስለ እርከን ሥራ፣ ስለ ሠፈራ አስፈላጊነት በስፋት እያስተማሩ መንግሥትን ተራድተው ነበር ይባላል::

ብፁዕነታቸው ሕይወታቸውን ሁሉ የላመ የጣመ ሳይመገቡ በትኅርምት ለማሳለፍ ከፈጣሪያቸው ጋር ቃል ኪዳን የገቡበትን ቅናተ ዮሐንስ እስረው ነበር ይባላል:: በመሆኑም በቅርቡ ሕይወታቸው እስከ ሚያልፍ ድረስ በሀገሪቱ ቅናተ ዮሐንስ ካሰሩ ጥቂት አባቶች አንዱ ነበሩ ይባላል:: በመሆኑም ቃል ኪዳኑ እንደ ሚያዝዘው ሥርዓቱን ከፈጸሙበት ጊዜ ጀምሮ መላ ስድሜያቸውን ከጥሉላት ምግብ ርቀው፣ ማንኛውንም የአልኮል መጠጥ ወደ አፋቸው ሳያስጠጉና በአልጋ ሳይተኙ ቆይተዋል:: የሚያስገርመው ይህንን ገድላቸውን ማንም ሰው እንዲያውቀው ሳይፈልጉ ማለፋቸው ነው::

ብፁዕ አቡነ ሰላማ በዚህ ዓይነት አገልግሎታቸውን በመፈጸም ላይ ሳሉ ለኅልፈታቸው ምክንያት በሆነ ደዌ ዘእሴት ተያዙ:: ብፁዕነታቸው ሕማማቸውን በመቻል አገልግሎታቸውን ለመፈጸም ቢሞክሩም እየዋለ እያደረ እየባሰባቸው መጣ:: በዚህም በሀገር ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ሕክምና መከታተል ጀመሩ:: ይሁን እንጂ የብፁዕነታቸው በሽታ በሀገር ውስጥ ሊታከም የማይችል መሆኑ ይከታተሏቸው ከነበሩ የሕክምና ባለሞያዎች በመገለጡ በሰኔ 1995 ዓ.ም ለከፍተኛ ሕክምና ወደ ኢየሩሳሌም ሔዱ:: በዚያም ለአንድ ዓመት ያህል ሕክምናቸውን ሲከታተሉ ቆዩ:: ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ያገኙት ሕክምና ዘመናዊነቱ የተመሰከረለት ቢሆንም ከበሽታቸው ሊፈውሳቸው አልቻለም:: በመሆኑም የሕክምናውን ነገር ተስፋ ቆርጠው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ:: ብፁዕነታቸው በኢየሩሳሌም ለአንድ ዓመት ሲቆዩ እንደምንም አዝግመው ቤተ

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር በማስቀደስ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን በተከታታይ ይቀበሉ ነበር ይባላል:: ወደ ሀገራቸውም እንደ ተመለሱም በቀጥታ ሬሳዬ ያርፍበታል ወዳሉት የደብረ ሊባኖስ ገዳም ነበር የሔዱት:: ይሁን እንጂ ሁኔታው እንደ ተስማ በማግስቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተ/ሃይማኖት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትን አስከትለው ወደ ደብረ ሊባኖስ በመሔድ ከጠየቋቸው በኋላ ሕመማቸው በቤተ ሰብ ደረጃ ለማስታመም የሚከብድና የባለ ሞያዎችን እገዛ የሚጠይቅ ጽኑ ደዌ በመሆኑ እስከ ሰለተ ዕረፍታቸው ሕክምና ያገኙ ዘንድ ወደ አዲስ አበባ አመጧቸው:: በዚህም ሐያት እየተባለ በሚጠራው ሆስፒታል በሕክምና ሲረዱ ቆይተው በዚህ ዓለም ይኖሩበት ዘንድ ተለክቶ የተሰጣቸው ዕድሜ ሲጠናቀቅ ሰኔ 18 ቀን 1996 ዓ.ም ልክ ከቀኑ 7:20 ሲሆን በተወለዱ በ66 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ::

የብፁዕነታቸው ዜና ዕረፍት እንደ ተሰማም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ጋር በመሆን ወደ ሆስፒታሉ በመሔድ አስከሬኑን እጅበው በማምጣት በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን እንዲያርፍ ካደረጉ በኋላ ጸሎተ እኩቴትን አደረሱ:: ቀጥሎም ሌሊቱን በሙሉ በመዘምራኑ ማኅሌት፣ በመነኮሳቱና ቀሳውስቱ ሰዓታት ጸሎተ ፍትሐት ሲከናወን አድሯል:: ሲነጋም አስከሬናቸው ወደ ደብረ ሊባኖስ ተሸኝቶ ሥርዓተ ቀብራቸው ሰኔ 20 ቀን 1996 ዓ.ም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት፣ አበው ቆሞሳት፣ የጠቅላይ ቤተ ክህነት የየመምሪያው ሐላፊዎች፣ የገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች፣ የብፁዕነታቸው ዘመዶችና ምእመናን በተገኙበት ተፈጽሟል:: የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን:: አሜን::



# 3.37. ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልአይ ሊቀ - ጳጳስ /1932 - 1982 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ መዓርገ ጵጵስናን ከመቀበላቸው በፊት አባ መዝገበ ሥላሴ ይባሉ ነበር:: ብፁዕነታቸው በ1933 ዓ.ም በያኔው የወሎ ጠቅላይ ግዛት ደሴ ከተማ ከአባታቸው ከአቶ ገበየሁና ከእና ታቸው ከወ/ሮ አሰለፈች ካሣ ተወለዱ::

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ ተወልደው ባደጉበት ደሴ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ:: ከዚያም ትምህርታ ቸውን ለማስፋፋት ወሎ ውስጥ ሳይንት ነአኩቶ ለአብ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ወደ ነበሩት አባ ክፍሌ ዘንድ በመሔድ የውዳሴና ቅዳሴ ማርያምን ትርጓሜ፣ አዕማደ ምሥጢርና ባሕረ ሐሳብ የተሰኙትን ትምህርቶች ተማሩ::

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ቀለም በፍጥነት የመያዝ ችሎታ ባለ ነበራቸው ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ባስተማሯቸው መምህራን እንዲ ሁም ደቀ መዛሙርት ፍቅር አይለያቸውም ነበር:: በዚህም የተነሣ ትርጓሜ መጻሕፍትን ያስተማሯቸው አባ ክፍሌ የተነገራቸውን በፍጥነት የመያዝ ችሎታቸውን ለመግለጽ ወላጆቻቸው ያወጡላቸ ውን ስም በመቀየር «መዝገበ ሥላሴ» የሚል ስም አውጥተውላቸው አባ ጎርጎርዮስ እስከ ሚባሉ ድረስ በዚሁ ስም ይጠሩ ነበር::

ከዚህ በኋላ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በወቅቱ የወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ:: ከዚያም በዲቁናቸው ጥቂት እንዳገለገሉ ከወሎ በመነሣት ወደ አዲስ አበባ መጥተው በመታሰቢያ ቤት በታላካ ነገሥት በኣታ ለማርያም ገዳም ገብተው ሐዲሳትን ተማሩ:: ከዚያም ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመውረድ መዓርገ ምንኩስናን ተቀበሉ::

በዚህ ዓይነት የሕይወት አቅጣጫቸውን የወሰኑት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ መዓርገ ምንኩስናን ከተቀበሉ በኋላ ወደ ተወለዱበት አካባቢ ሳይመለሱ ወደ አዲስ ዓለም ሔዱ:: በዚያም መምህር አፈ ወርቅ መንገሻ ከተባሉ ሊቅ ቅኔን ከነአገባቡ በሚገባ ጠንቅቀው ተማሩ:: ከዚያም እንደ ገና ወደ ደብረ ሊባኖስ በመመለስ መምህር ፍሥሐ ከተባሉ ሊቅ የሐዲሳትን ትርጓሜና ትምህርተ ሃይማኖትን፣ መምህር ቢረሳው ከተባሉ ሊቅ ደግሞ መጽሐፈ ሊቃውንትን ተማሩ:: እንደ ዚሁም በደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ማርያም ሰፊ ጉባኤ ከነበራቸው መምህር ገብረ ሕይወት ዘንድ በመሔድ የሐዲሳ ትን ትርጓሜ አደላድለው ተመረቁ:: ከሐዲሳቱም ጋር በዚሁ ደብር ቅዳሴን ከነሥርዓቱ አጠናቀው ተማሩ::

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በዚህ ዓይነት ከጉባኤ ጉባኤ ተዘዋ ውረው ሰፊ ዕውቀትን ከሰበሰቡ በኋላ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ



መዓርገ ቅስናን ተቀበሉ:: በዚህ መዓርጋቸው ጥቂት እንዳገለገሉ ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት ወደ ሐረር ተላኩ:: በዚያም በተሰጣ ቸው የማስተማር ጸጋ የአካባቢውን ምእመናን ቃለ እግዚአብሔር እየመገቡ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ዘመናዊ ትምህርታቸውን በጥሩ ውጤት አጠናቀቁ:: ከዚህ በኋላ የብፁዕነታቸውን ትጋትና አስተዋይነት የተመለከተው የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር በዚያው አካባቢ የሚገኘው የቀልቢ ገብርኤል ገዳም አስተዳዳሪ በማድረግ ሾማቸው:: ብፁዕነታቸውም ሹመቱን በአኮቴት በመቀበል በነበራቸው የማስተዳደር ጥበብ ገዳሙን ማስተዳደር ጀመሩ::

በቁልቢ ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ለሁለት ዓመታት ከቆዩ በኋላ ብፁዕነታቸው ወደ ውጭ ሀገር በመሔድ ያለውን ባሕልና የትምህርት አሰጣጥ ሁናቴ ተመልክተው ቢመጡ የነገዋን ቤተ ክርስቲያን በመረከብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክቱ ስለ ታመነበት በ1963 ዓ.ም ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ግሪክ ተላኩ:: በዚያም ደሴተ ፍጥሞ በተባለችው ቦታ በሚገኘው ከፍተኛ የነገረ ሃይማኖት ት/ቤት ለሁለት ዓመታት ተምረው ዲፕሎማ ተቀበሉ:: ትምህርቱን በመቀጠልም በዚያው ወደ አቴና ዩኒቨርሲቲ በመግባት ለአራት ዓመታት የነገረ መለኮት ትምህርታቸውን በመከታተል በማስትሬት ዲግሪ ተመረቁ:: ወደ ሀገራቸው ከመመለሳቸው በፊት ስለ ውጭው ዓለም ያላቸውን ዕውቀት በሚገባ አዳብረው መምጣት እንዳለባቸው ስላመኑ የአቴና ዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን በዚህ ዓይነት ካጠናቀቁ በኋላ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ስዊዘርላንድ አቀኑ:: በዚያም ፍሪቦንግ በሚል ስያሜ በሚጠራው ዩኒቨርሲቲ የፈረንሳይኛ ቋንቋ አጥንተው ዲፕሎማ አገኙ::

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በዚህ ዓይነት የአውሮፓ ትምህር ታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ፣ ወቅቱ በኢትዮጵያ የመንግሥት ለውጥ የነበረበት፣ ቀይ ሽብር በሚልም ወጣቶች በገፍ አያለቁ የነበረበት፣ ይልቁንም ቤተ ክርስቲያንን እንድታገለግል ሒድና ተምረህ ና ብለው የሰደዷቸው አርቆ አሳቢ አባት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ እስር ቤት የሚገኙበት ወቅት ስለ ነበር ወደ ሀገራቸው መምጣታቸውን ትተው ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም አቀኑ:: ብፁዕነታቸው በእንግድነታቸው በቆዩባቸው ጊዜያት በአካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሕፃናትን ሰብስበው ሲመክሩና ሲያስተምሩ፣ ከማኅበረ መነኮሳቱም ጋር በመስማማትና በመተጋገዝ ሕፃናቱን የአማርኛ ቋንቋና ባሕል ከመንፈሳዊ ትምህርት ጋር አያስተማሩ ቆዩ:: ከዚህም ጋር ብፁዕነታቸው በኢየሩሳሌም ቆይታቸው ለማኅበረ ካህናቱ እንደ ዕጣን ቅመም ዓይነት ልዩ ልዩ ሞያዎችን በማስተማር ገዳሙ ራሱን በገንዘብ እንዲደጉም ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ አበርክተዋል:: የሚወዱትን ትምህርት በመቀጠልም በዚያ ከሚገኘው

www.ethiopianorthodox.org

የግሪክ የነገረ መለኮት ኮሌጅ የሀረብኛ ቋንቋን አጥንተው ሰርቲፊኬት ተቀብለዋል::

የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስን ከቦታ ቦታ ተዘዋውሮ ዕውቀትን መገብየት የተመለከተው የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር በሀገሪቱ አንጻራዊ ሰላም ከመጣ በኋላ በ 1971 ዓ.ም ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ጥሪ አደረገላቸው:: ብፁዕነታቸውም መማራቸው ለእናት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መሥመርና መፋጠን ስለ ነበር ምንም እንኳን ባለፉት ዓመታት ቤተ ክርስቲያኗ የደረሰባት መደፈር ቢያሳዝናቸውም ጥሪውን በደስታ ተቀብለው ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ:: ብፁዕነታቸው ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ በማግባባቱና በማሳመኑ ረገድ በወቅቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከፍተኛ ሚና እንደ ነበራቸው ይነገራል::

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ወደ ኢትዮጵያ እንደ ተመለሱ በጠቅላይ ቤተ ክህነት በተሰጣቸው ቦታ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎቶችን ማበርከት ጀመሩ:: ነገር ግን ብዙም ሳይቆዩ ሲታሳቁ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ሥልጣን ታጩ:: በምርጫውም ሙሉ ድምፅ አግኝተው በጥር ወር 1971 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አንብሮተ ዕድ ከተሾሙት አባቶች አንዱ በመሆን መዓርገ ጵጵስናን ተቀበሉ:: መዓርጉን እንደ ተቀበሉ የተሰጣቸው ሀገረ ስብከት መላው ሸዋ ሲሆን ከዚሁ ጋር የቅዱስ ፓትርያርኩ እንደራሴና የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ሆነው ነበር::

ብፁዕነታቸው በሀገር ውስጥም ሆነ በባሕር ማዶ ባካበቱት ዕውቀት በመጠቀም ከሀገረ ስብከታቸው ጋር የእንደራሴነታቸውንና የቅዱስ ሲኖዶስ ጸሐፊነታቸውን ተግባራት በብቃት መወጣት ጀመሩ:: በተለይ በነበራቸው ሐላፊነት የቤተ ክርስቲያንን ሁለንተናዊ አስተዳደር እንዳጠናከረ የሚነገርለትን ምቅዋመ ሕግ /ሕገ ቤተ ክርስቲያን/ አርቅቀዋል:: ብፁዕነታቸው ቤተ ክርስቲያን የጣለጠ ችባቸውን አደራዎች ደራርበው በማገልገል ላይ ሳሉ ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ጋር በሥራ ምክንያት አለመግባባት ተፈጠረ:: በዚህ የተነሣ የእንደራሴነታቸውንና የዋና ጸሐፊነት ሥራቸውን አስረክበው ትኩረታቸውን ሙሉ በሙሉ ብዙ ሥራ ወደ ሠሩበት የዝዋይ ገዳም እንዳደረጉ ይነገራል::

ብፁዕነታቸው የሀገረ ስብከታቸውን ጽ/ቤት ሙሉ በሙሉ ወደ ዝዋይ ከማድረጋቸው በፊት በወቅቱ የሸዋ ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና አዲስ አበባ ላይ ስለ ነበር ብፁዕነታቸው የተሰጣቸውን ሐላፊነት ሁሉ በነበራቸው የአስተዳደር ጥበብና ዕውቀት በብቃት ማስተዳደርና ፍሬን ማሳየት ጀመሩ:: ብፁዕነታቸው ምንም እንኳን በቦታው ያቀዷቸውን ሁሉ ከዳር ለማድረስ ባይፈቀ... ሁናቴ በጀመሩት የዝዋይ ካህናት ማሠልጠኛ በርካታ ሥራዎችን



ሠርተዋል:: ቦታው እርሳቸው ወደ ዚያ ከመሔዳቸው በፊት በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ርዳታ የተሠራ ቢሆንም የታሰበውን ያህል አገልግሎቱን በብቃት እያከናወነ አልነበረም:: እርሳቸው ከተረከቡት በኋላ ግን የትምህርት ዓላማውን ሳይተው በገዳም ሥርዓት እየተዳደረ ሥራውን በተሻለ ሁናቴ እንዲቀጥል አድርገዋል:: ከዚህም ጋር ቦታው ገዳም ሲሆን ተማሪዎች የተማሩትን በተግባር የሚያሳዩበትና የጸሎት ሕይወት የሚለምዱበት ቤተ ክርስቲያን ያስፈልግ ነበርና ቤተ ክርስቲያን አሠርተው የቅዱስ ገብርኤልን ጽላት አስገብተው የገዳሙን ስም የዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ብለው ሠይመዋል::

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በዚህ ዓይነት ገዳሙንና በውስጡ ያለውን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ካስፋፉና መሠረት ካስያዙ በኋላ ከተለያዩ አህጉረ ስብከት ተማሪዎች እንዲመጡ እያደረጉ በአዳሪነት፣ እንዲሁም ካህናት በኮርስ እንዲማሩ በማድረግ ለቤተ ክርስቲያኗ ንቁ እና ዕውቀት ያለው ትውልድ እንዲገኝ አድርገዋል:: በገዳሙ ይማሩ ከነበሩትና ዛሬ በልዩ ልዩ መስክ ተሠማርተው ቤተ ክርስቲያናቸውንና ሀገራቸውን እያገለገሉ ከሚገኙት ምሁራን ውስጥ ብዙዎቹ እናትና አባት የሌላቸው እንዲሁም መማር የማይችሉ ነበሩ:: በገዳሙ ውስጥ የሚኖሩ መነኮሳትም ልዩ ልዩ የቀለም እና የሞያ ዕውቀት እንዲኖራቸው በማድረግ ቀላል የማይባል ሥራ እንዲሠራ አድርገዋል::

ብፁዕነታቸው በነበራቸው ወጣቱን ትውልድ የመያዝ ፍላጎትና ችሎታ በወቅቱ በተለያዩ የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ይማሩ የነበሩ ተማሪዎችን በክረምት ወደ ገዳሙ እንዲገቡ በማድረግ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በመማር ዘመኑን እንዲዋጁ አድርገዋል:: ምንም እንኳን በዚህም ረገድ የነበራቸው ሕልም ተግባራዊ ሲሆን ለማየት ባይታደሉም እርሳቸው ለሁለት ሦስት ክረምቶች ሰብስበው ያስተማሯቸውና የመከሯቸው ተማሪዎች ዛሬ ቁጥራቸውን አበራክተው በማኅበር ደረጃ በመሰባሰብ ከልዩ ልዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚመረቁ ወጣቶች በዕውቀታቸውና በገንዘባቸው ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲያገለግሉ በማድረግ ላይ ይገኛሉ::

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ቤተ ክርስቲያን ጥንት የነበራት አቋም ተመልሶ በልማት ራሷን ችላ ሌሎችን መርዳት አለባት የሚል የጸና እምነት ስለ ነበራቸው በገዳሙ የሚማሩ ተማሪዎች እንዲሁም መነኮሳት ገዳሙን በማልማት ራሳቸውን እንዲችሉ የሚደነቅ ጥረት ያደርጉ ነበር:: በዚህም መሠረት በርካታ የባሕር ዛፍ፣ የአርዘ ሊባኖስ፣ የትሪ ማንተሪ፣ የሙዝ ፣ የብርቱካን ፣ የቡና እና የፓፓያ ተክሎች በገዳሙ ግቢ እንዲተከሉ አድርገው ዛሬም ከቡናው በስተ

www.ethiopianorthodox.org

ቀር ሌሎች ለገዳሙ ፍሬ እየሰጡ ይገኛሉ:: በዚህ ገዳም አርአያነት በሀገረ ስብከታቸው የሚገኙ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትንም ራሳቸ ውን በማልማት እንዲጠቀሙና እንዲጠቅሙ ይመክሩ እና ያስተ ምሩ ነበር::

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ከላይ በአጭሩ በተገለጠው ዓይነት ወንጌልን በተግባር ከመስበክ ጋር በነበራቸው ግሩም የማስተማር ጸጋ በየአጥቢያው እየተዟዟሩ ምእመናን በሕገ እግዚአብሔር ጸንተው እንዲኖሩ ያስተምሩ ነበር:: መጻሕፍትንም በመጻፍ አስተምረዋል:: ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በፀጸደ ሥጋ በነበሩበት ጊዜ ካዘጋጇቸው መጻ ሕፍት መካከል <u>መሠረተ እምነት</u>፣ <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ</u> ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ <u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ</u> በዓለም መድረክ የተሰኙት ለኅትመት እንዲበቁ አድርገዋል:: ትምህርተ ሃይማኖት /ዶግማ/፣ የስብከት ዘዴ /ኦርቶዶክሳዊ/፣ ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ፣ ሥርዓተ ኖሎት፣ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የተሰኙት ሌሎች ደግሞ አዘጋጅተዋቸው ሳያሳትሟቸው የቀሩ ናቸው:: ብፁዕነታቸው በእነዚህ ድርሰቶቻቸው ብዙዎች በቃልም ይሁን በመጣፍ በብዛት ያልዳሰሷቸውን እንደ ጾም፣ በዓላት አከባበርና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ዘርዘር ባለ መንገድ በመጻፍ አስተምረዋል::


ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ለዐሥራ አንድ ዓመታት በዚህ ዓይነት ከፍተኛ እና አርአያነት ያለው አገልግሎት ካበረከቱ በኋላ ሐምሌ 22 ቀን 1982 ዓ.ም በመቂ ቅዱስ ሚካኤል ለሚገኙ ምእመናን የተለመደ አባታዊ ትምህርታቸውን ለመስጠት ሲገሠግሱ በድንገት በደረሰ ባቸው የመኪና አደጋ በተወለዱ በኀምሳ ዓመታቸው ዐረፉ:: ሥርዓተ ቀብራቸውም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ይወዷቸውና ያከብሯቸው የነበሩ ደቀ መዛሙርት እንዲሁም የዝዋይ እና የአካባ ቢው ምእመናን በተገኙበት በጥሩ ሁኔታ ባደራጁት የዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ መቅደስ ውስጥ ተፈጽሟል:: የብፁዕ ነታቸው በረከት አይለየን::



# 3.38. ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ካልአይ

## ሊቀ ጳጳስ

## /1922 - 1993/



www.ethiopianorthodox.org

ቀድሞ ሊቀ ጉባኤ ገብረ ሚካኤል መንገሻ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል በያኔው የወሎ ጠቅላይ ግዛት በየጁ አውራጃ በሚገኘው መርጦ ኢየሱስ ደብር መስከረም አንድ ቀን 1922 ዓ.ም ተወለዱ:: ወላጆቻቸው አቶ ወልደ ሚካኤልና ወ/ሮ አማረች መንገሻ ይባሉ ነበር::

ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል በወላጆቻቸው ቤት በመልካም ሥነ ምግባር ተኮትኩተው ካደጉ በኋላ ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ በተወለዱበት ደብር ቀኝ ጌታ መንግሥቱ ቢያበይን፣ መሪ ጌታ ገብረ ኢየሱስ እና የኔታ ሐዋዝ ከተባሉ መምህራን የመጀ መሪያና የሁለተኛ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ:: በመቀጠልም ከመምህር ወልደ መስቀል ቅዳሴን ተምረዋል:: ብፁዕነታቸው ትምህርታቸውን የማስፋፋት ልዩ ጉጉት ባለ ነበራቸው በዚህ ዓይነት በትውልድ አጥቢያቸው ሁለቱን የትምህርት ደረጃዎች ካጠናቀቁ በኋላ ሦስተኛውን መንፈሳዊ ትምህርት ለመቀጠል ወደ ዋድላ ድላንታ አውራጃ ዳውንት ሔደው ቅኔን ከመሪ ጌታ ሄኖክ በሚገባ ተማሩ::

ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ትምህርታቸውን ለመቀጠል ወደ ላስታ አመሩ:: በዚያም መቄት ከተባለው አካባቢ ገረገራ ጊዮርጊስ ላይ ሰፊ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት መምህር ቀፀላ ስይፈ ሥላሴ /ብፁዕ አቡነ እንድርያስ/ የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ:: ከዚያም ባስመሰከሩበት ሞያ ጥቂት ጊዜ ካስተማሩ በኋላ በ1946 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ መምህራንና ቀሳውስት ማሠልጠኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ገብተው የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜና አቡሻህር /የቁጥር ትምህርት/ ከመምህር ገብረ ሕይወት ሠይፈ ሥላሴ ተማሩ:: ብፁዕነታቸው በዚህ ጊዜ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ዘመናዊ ትምህርታቸውን ተከታትለው የአንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ::

ከላይ በአጭሩ ባየነው ዓይነት መንፈሳዊ ዕውቀትን በሚገባ አደላድለው የያዙት ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ከዚህ በኋላ ረዘም ላሉ ዓመታት ያካበቱትን ዕውቀት ለሌላው ሊያካፍሉ ጉባኤ ዘረጉ:: በዚህም ከ1948 ዓ.ም እስከ 1954 ዓ.ም ድረስ ትርጓሜ መጻሕፍትን በማስተማር ብዙ ደቀ መዛሙርትን አፈሩ:: ከመደበኛ ጉበኤያቸው ጋር በ1954 ዓ.ም ሊቀ ጉባኤ ተብለው በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ት/ቤት የመንፈሳዊ እና የዘመናዊ ትምህርት የስብከተ ወንጌል ሐላፊ በመሆን እስከ 1965 ዓ.ም አገለገሉ:: በእነዚህ የአገልግሎት ዘመናቸው ብፁዕነታቸው በነበራቸው ካህናትንና ሕዝብን አስተባብሮ የማሠራት ልዩ ችሎታ ለዘመናዊውና ለመንፈሳዊው ትምህርት



አገልግሎት የሚሰጡ 10 ተጨማሪ ክፍሎችን አሠርተዋል:: እነዚህ ክፍሎች ዛሬም አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ::

ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል በዚህ ዓይነት ራሳቸውን በትምህርትና በአገልግሎት ካጠነከሩ በኋላ ሥርዓተ አበውን ሊፈጽሙ ወደ ታላቁ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ወረዱ:: በዚያም ግንቦት 12 ቀን 1955 ዓ.ም መዓርገ ምንኩስናን ተቀበሉ:: በዓመቱ በ1956 ዓ.ም ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ የቅስናን መዓርግ ተቀብለዋል::

በ1965 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ መልካም ፈቃድ በግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ ትእዛዝ ወደ ሐረርጌ ክፍለ ሀገር ተዛውረው በሐረር ቅድስት ሥላሴ ደብር አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ:: በየሔዱበት መልካም ሥራን እንዲሠሩ የሚያስ ችላቸው መልካም ጠባይና ሕዝብን የማስተባበር ችሎታ ገንዘባቸው ነበርና ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ የአጥቢያቸውን ካህናት በማስተባበር ከወትሮው ላቅ ባለ ሁናቴ በአካባቢው ስብከተ ወንጌልን አስፋፍተዋል:: እንዲሁም ደብሩ በዘመን ብዛት የተነሣ ተጐሳቁሎ ባለ ነበር እንዲጠገን አድርገዋል::

ብፁዕነታቸው በተመደቡበት ቦታ ለሦስት ዓመታት በትጋት ካገለገሉ በኋላ በ1968 ዓ.ም መጨረሻ ወደ አዲስ አበባ ተዛውረው የጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ:: በዚያም በወቅቱ የቤተ ክርስቲያኗ ማዕከላዊ አስተዳ ደር አጽድቆ በሥራ ላይ እንዲውል አዝዞት የነበረውን የሰበካ ጉባኤ ማቋቋሚያ መመሪያ በትጋት ወደ ሥራ ተርጉመው አሳይተዋል::

ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል በእነዚህ ከላይ በአጭሩ በተጠቀሱት እና በሌሎች ባልተጠቀሱ በርካታ አገልግሎታቸው የተነሣ ለታላቁ የቤተ ክርስቲያን ሹመት ታጩ:: በምርጫውም የድምፅ ብልጫ በማ ምጣት በጥር ወር 1971 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖ ት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ አንብሮተ እድ ጳጳስ ዘወሎ ተብለው መዓርገ ጵጵስና ተቀበሉ:: ብፁዕነታቸው ተሾመው በሔዱ በት ሀገረ ስብከትም አገልግሎታቸውን በትጋት ቀጠሉ:: ያለ ምንም ድካ ምና መሰልቸት በየወረዳው እየተዘዋወሩ ኢ አማንያንን በማስተማር በጥምቀት የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አባል እንዲሆኑ አድርገዋል::

ከዚህም በመቀጠል ከ1976 ዓ.ም እስከ 1987 ዓ.ም ድረስ ወደ ሐረርጌ ተዛውረው በሀገረ ስብከቱ የሚገኙትን ገዳማትና አድባራት በመዘ ዋወር ካህናቱ ካለባቸው ችግር እንዲላቀቁ፣ ምእመናኑን በማስተማር ከማገልገላቸውም በላይ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አሳንፀዋል::

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት መልካም ፈቃድ ከኅዳር 1 ቀን 1987 ዓ.ም እንሥቶ ወደ ጅማ ሀገረ ስብከት ተዛውረዋል::

ብፁዕነታቸው በጅማ ለተከታታይ ሰባት ዓመታት ካገለገሉ በኋላ የነበራቸውን ትጋት በመመልከት ከሐምሌ 15 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ በያዙት ሀገረ ስብከት ላይ የከፋችና ሸክቾ ቤንችና ማጂ አገረ ስብከት ተደርቦላቸው ለሁለት ዓመታት በርካታ ሐዋርያዊና መንፈሳዊ ሥራዎችን አከናውነዋል:: እርሳቸው ወደ እገረ ስብከቱ ሲሔዱ በነበሩት 170 አብያተ ክርስቲያናት ላይ ምእመናንን በየጊዜው በማስተማርና ካህናቱን በማስተባበር 50 ተጨማሪ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነፁ አድርገዋል::

ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ቅድሚያ የሚሰጡት ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት ነበር:: በመሆኑም በመድረክ ሲያስተምሩ ውለው ቢያድሩ የማይሰለቹ አባት ነበሩ:: የትምህርት አሰጣጣቸውም የማይሰለችና የሰውን መንፈሳዊ ሕይወት የሚያድስ ነበር::

ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል አርቆ አሰተዋይ በመሆናቸው ዕውቀታቸው በሳቸው ብቻ ተወስኖ እንዳይቀር 1992 ዓ.ም ለተከታታይ አራት ወራት በጅማ ከተማ የሚገኙትን መምህራን ካህናትንና ዲያቆናትን በማሰባሰብ አሠልጥነው ዘመኑ ካመጣቸው ልዩ ልዩ እምነቶች ምእመናንን እንዲጠብቁና ጸንተው በእምነታቸው እንዲኖሩ አድርገዋል:: የብፁዕነታቸው የካህናት ሥልጠና ፕሮግራም በጅማ ከተማ ብቻ ተወስኖ የቀረ ሳይሆን በሁሉም ወረዳዎች መካሔድ ያለበት በመሆኑ በሀገረ ስብከቱ በሚገኙት የተለያዩ ወረዳዎች የካህናት ሥልጠና እንዲሰጥ አድርገዋል::

በዚህም የተነሣ ነባሩን የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርት ለማጠናከር ባደረጉት ጥረት ከሰሜን፣ ከምሥራቅና ከመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ከ50 በላይ ለሆኑ ተማሪዎች በርእሰ ከተማው በሚገኘው ደብር ወንበር ዘርግተው ለሚያስተምሩ የአብነት መምህራን ዘወትር አባታዊ ምክር በመስጠት ከኪሳቸውም የማበረታቻ ድጎማዎች እየሰጡ ያበረታቷቸው ነበር::

ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ከሕፃንነታቸው ጀምሮ ቤተ ክርስቲያናቸውን በትጋት ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ሕማም ዐቅማቸውን እየነሣቸው በመምጣቱ ጤናቸው እየታወከ መጣ:: ምንም እንኳን ከሕመማቸው ያገግሙ ዘንድ በሀገር ውስጥ በሕክምና እና በጠበል ሲረዱ ቢቆዩም ጤናቸው ሊመለስ ባለመቻሉ ለከፍተኛ ሕክምና ወደ እስራ

www.ethiopianorthodox.org



ኤል ሔዱ:: በዚያም ያገኙት ሕክምና ጤናቸውን ሊመልስላቸው አልቻለም:: ሰኔ 23 ቀን 1993 ዓ.ም ከጧቱ በሦስት ሰዓት ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: ሥርዓተ ቀብራቸውም በዚያው በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ተፈጸመ:: የብፁዕነታቸው በረከት አይለየን:: አሜን::

# 3.39. ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ካልአይ

## ሊቀ ጳጳስ

## /1921 - 1981ዓ.ም/





መዓርገ ጵጵስና ከመቀበላቸው በፊት አባ ጸገዬ ቢሆነኝ ይባሉ ነበር። ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ በቀድሞው የበጌምድር ጠቅላይ ግዛት በደብረ ታቦር አውራጃ በእስቴ ወረዳ ልዩ ስሙ ቆማ ፋሲለደስ ተብሎ በሚታወቀው ቦታ በ1921 ዓ.ም ተወለዱ። የአባታ ቸው ስም ቀኝ ጌታ ቢሆነኝ ዋሴ፤ የእናታቸው ስም ወ/ሮ ውዴ መሸሻ ይባል ነበሩ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በመካነ ልደታ ቸው በቆማ ፋሲለደስ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን መምህር ሐዲስ ከሚባሉ የድጓ ምስከር ተማሩ። ከዚያም በጥር ወር 1935 ዓ.ም ወደ አዲስ አባባ መጥተው በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ከብፁዕ አቡነ ቄርሎስ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ። ከዚያም በ1940 ዓ.ም በታላቁ ገዳም በደብረ ሊባኖስ መዓርገ ምንኩስናን ተቀበሉ።

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ በነበራቸው የትምህርት ፍላጐት የተነሣ ከትውልድ ቦታቸው ወጥተው በልዩ ልዩ ክፍላተ ሀገር በመዘዋወር ከአያሌ ኢትዮጵያውያን መምህራን የቤተ ክርስቲያናችንን ከፍተኛ ትምህርት ቀሰመዋል። በዚሁም መሠረት ከደቡብ ጎንደር ወደ ምሥራቅ ጎጃም ሔደው ሞጣ አውራጃ ውስጥ ድቦ ኪዳነ ምሕረት ከምትባል ቦታ ያስተምሩ ከነበሩት አለቃ አድማሱ ዘንድ ቅኔን ከነ አገባቡ ከተማሩ በኋላ እንደ ገና ወደ ደቡብ ጎንደር ተመልሰው በጋይንት አውራጃ በስማዳ ወረዳ ደብረ ዕንቁ ላይ ጉባኤ ዘርግተው ከነበሩት ከመምህር ጌጡ ተሰማ በተጨማሪ ቅኔ በመማር ዕውቀታቸውን አስፋፉ። አሁንም የቅኔውን ትምህርት ለማጠናከር ወደ ደቡብ ወሎ በመሔድ በአማራ ሳይንት ወረዳ በሮ ሚካኤል ከነበሩት ከአለቃ ከበደ ቀደም ሲል የተማሩትን የቅኔ ትምህርት ከነ አገባቡ በመማር ከአጠናቀቁ በኋላ በመምህርነት ተመረቁ።

የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ለመማር የጸና ፍቅር የነበራቸው ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ በቅኔው ትምህርት ከተመረቁ በኋላ ወደ ቀጣዩ የትምህርት ደረጃ ገሠገሡ። ይኸውም የመጻሕፍትን ትር ጓሜ ለመማርና ለማወቅ ነበር። ለዚህም በዚያው የቅኔን መምህርነት ባገኙበት በወሎ ክፍለ ሀገር፣ በቦረና ሳይንት አውራጃ፣ መካነ ሰላም ተብሎ በሚጠራው ቦታ ከአለቃ ታመነ አግደው ትርጓሜ ነገሥትን፣ በደሴ መድኃኔ ዓለም ከአባ ገብረ ማርያም ገብረ ሐና የዳዊት፣ የውዳሴና የቅዳሴ ማርያም ትርጓሜን አጠኑ። በመቀጠልም በዚያው ቦታ መምህር ገብረ እግዚአብሔር ሐጐስ ከተባሉ ሊቅ የትምህርተ ኅቡአት፣ የኪዳንና የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜ አሔዱ። መዓርገ ቅስናን የተቀበሉት በዚያው በደቡብ ወሎ በትምህርት ላይ በነበሩበት ጊዜ መስከረም 21 ቀን 1944 ዓ.ም ነበር።

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ መዓርገ ቅስናን ከተቀበሉ በኋላ ጀምረውት የነበረውን የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርት አቁመው ወደ አዲስ አበባ መጡ። እንደ መጡም በታዕካ ነገሥት በአታ መታሰቢያ ቤት የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርታቸውን ቀጠሉ። በዚህም መሠረት ሐዲሳትን ከመምህር ገብረ ሕይወትና ከመምህር ሥምረተ አብ ቀጸላ፣ ብሉያትን ከአለቃ ጌራ፣ አቡሻህርን ከመምህር ገብረ ሕይወት በሚገባ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ።

በዚህ ዓይነት ራሳቸውን በትምህርተ ሃይማኖት ያነፁት ብፁዕነታቸው ሊቅነታቸው በቃልም በተግባርም በመመስከሩ በ1956 ዓ.ም ታላቁ መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በሐዲሳት ትርጓሜ መምህርነት ተመደቡ። ከተመደቡበት ጊዜ ጀምሮም ጉባኤያቸውን በማስፋት እስከ 1971 ዓ.ም ድረስ በትጋት በማስተማር በርካታ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል። ብፁዕነ ታቸው በካቴድራሉ በቆዩባቸው ዓሥራ አምስት ዓመታት በጉባኤ ቃለ እግዚአብሔርን ከማስተማር በተጨማሪ የካቴድራሉ ቄሰ ገበዝም በመሆን በትጋት አገልግለዋል። የእጥቢያውን ምእመናንና ወጣቶችን ዘወትር ቅዳሜና እሑድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና ነገረ መስኮት በማስተማር አገልግለዋል።

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ በደቀ መዛሙርቱም ሆነ በምእመናን ጉባኤ በመገኘት በቃል ከማስተማራቸውም በተጨማሪ በቃል ያለ ይረሳል በመጽሐፍ ያስ ይወረሳል የሚለውን ልብ በማለት የፍትሐ ነገሥትን፣ የዳዊትን፣ የሐዲሳትንና የትንቢተ ኢሳይያስን ትርጓሜ በእጃቸው ጽፈው ለቤተ ክርስቲያናችን ቅርስ አስቀምጠው አልፈዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በወሰነው መሠረት ጥር 5 ቀን 1971 ዓ.ም ከተመረጡት ዓሥራ ሦስት ኤጲስ ቆጳሳት መካከል ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ አንዱ ሆነው በመመረጥ «ብፁዕ አባ ታዴዎስ ጳጳስ ዘኢሉባቦር» ተብለው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መዓርገ ጵጵስናን ተሾሙ።

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ወደ ተሾሙበት ሀገረ ስብከት ከሔዱ ጀምሮ ያለ ምንም ድካም ቤተ ክርስቲያን የምትስፋፋበትን፣ የሀገረ ስብከቱ ምእመናን በሃይማኖት የሚጐለብቱበትን፣ የሀገረ ስብከቱ ካህናት የኑሮ አቋም የሚስተካከልበትን መንገድ ሁሉ በመሻት ስፊ አገልግሎትን አበርክተዋል።

ብፁዕነታቸው ከነበሩበት ሀገረ ስብከት ወደ ሰሜን ጎንደር እንዲዛወሩ ተደርጎ በአዲሱ ሀገረ ስብከታቸው ጥቂት እንዳገለገሉ ባደረባቸው ሕመም የተነሣ ቅዳሜ መጋቢት 16 ቀን 1981 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞተ ሥጋ ተለዩ። የቀብራቸው ሥነ ሥርዓትም ጎንደር



ከተማ በሚገኘው መንበረ መንግሥት መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስ ቲያን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና በርካታ ምእመናን በተገኙበት ተፈጽሟል። የብፁዕነታቸው በረከት ይደርብን። አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

# 3.40. ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ካልአይ

## ሊቀ ጳጳስ

## /1920 - 1981 ዓ.ም/





በ1920 ዓ.ም በሸዋ ሀገረ ስብከት ልዩ ስሙ ስምበሌጥ ገብርኤል በተባለው ሥፍራ ተወለዱ:: የአባታቸው ስም አቶ ገብረ ክርስቶስ እውነቱ፣ የእናታቸው ስም ወ/ሮ ጊዜ ባንጃው ይባል ነበር::

አባ ገብረ እግዚአብሔር ገብረ ክርስቶስ ይባሉ የነበሩት ብፁዕነታቸው ለድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ መርሐ ቤቴ ላይ ትምህርት ቤት ገብተው በዚያ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ተከታተሉ:: ከዚያም ወደ ወሎ ሀገረ ስብከት አማራ ሳይንት ሔደው ከመምህር ገብረ መድኅን ወልደ ኪዳን ዜማን ተማሩ:: ከዚያ ቀጥሎም በ1939 ዓ.ም ደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ማርያም ተብላ ወደ ምትጠራዋ ገዳም በመምጣት አለቃ /በኋላ መልአክ አርያም/ ይትባረክ መርሻ ከተባሉት መምህር ቅኔ በሚገባ ተማሩ::

ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ትምህርታቸውን በመቀጠል በዚሁ ገዳም አባ ደብረ ጽዮን ከተባሉት መምህር ዘንድ መዝገበ ቅዳሴን አጠናቀው ተማሩ:: በዚሁ በደብረ ጽጌ ገዳም ይህንኑ ትምህርት እንደ ፈጸሙ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ መልካም ፈቃድና ትእዛዝ የቅዳሴ መምህር ሆነው ማስተማር ጀመሩ::

ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ በዚህ ዓይነት በማስተማር ላይ እንደ ነበሩ ሕይወታቸውን በታላቅ ቅድስና ሊመሩ ወስነው ነሐሴ 24 ቀን 1942 ዓ.ም በደብረ ሊባኖስ ገዳም መዓርገ ምንኵስናን ተቀበሉ:: ቀጥሎም በ1943 ዓ.ም በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን የወሊጋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ከብፁዕ አቡነ ያዕቆብ መዓርገ ቅስናን ተቀበሉ::

ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ትምህርታቸውን በማስፋፋት ከመምህር ሐረገ ወይን ገብረ ሥላሴ የውዳሴ ማርያምና የቅዳሴ ማርያም፣ የዳዊትን ትርጓሜና ባሕረ ሐሳብን ጨምረው ተምረዋል:: እንዲሁም ከአለቃ ወልደ ዮሐንስ የመጽሐፈ ኢሳይያስንና ዳንኤልን ትርጓሜ ተምረዋል::

ከዚህ በኋላ ከ1951-1963 ዓ.ም በደብረ ጽጌ ገዳም በልዩ ልዩ የሞያ ዘርፍ ተሠማርተው ሲያገለግሉ ቆይተዋል:: ከዓመታት ቆይታ በኋላ ግን በ1963 ዓ.ም ሚያዝያ 25 ቀን በሸዋ ሀገረ ስብከት በመናገሻ አውራጃ በሚገኘው የደብረ ጽሞና ገዳም በመምህርነት ተሾመው አስተዳደሩ:: ብፁዕነታቸው በዚህ ጊዜ ከማስተዳደር ጋር ወንበር ዘርግተው በማስተማር አያሌ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል:: ምእመናንንም የወንጌልን ትምህርት በማስተማር አበረታተዋል::

ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ከዚህ በኋላ በ1967 ዓ.ም ኅዳር 30 ቀን በሸዋ ሀገረ ስብከት በየረርና ከረዩ አውራጃ በሚገኘው የሳማ ሰንበት ገዳም በአስተዳዳሪነት ተሾመዋል:: በአስተዳዳሪነት በቆዩበት ጊዜ ከፋ

www.ethiopianorthodox.org

ጳሚቸው አያሌ ተግባራት አንዱ 226 ዕድሜ ያለውን ቤተ ክርስቲያን ከዘመን ብዛት የተነሣ ለመውደቅ ተቃርቦ ስለነበር ምእመናንን በማስተባበር አዲስ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ አድርገዋል።

ለሰባት ዓመታት በሳማ ሰንበት በአስተዳዳሪነት በመቆየት ስፊ አገልግሎት ሲያበረክቱ የቆዩት ብፁዕነታቸው በ1974 ዓ.ም እንደገና ወደ ደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ገዳም በመዛወር መልአከ ጽጌ ተብለው የገዳሟ ዋና አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ። ይሁን እንጂ በደብረ ጽጌ ብዙም ሳይቆዩ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ለኤጲስ ቆጳስነት ምርጫ ውድድር እንዲገቡ ተደረገ። በውድድሩም ከፍተኛ የድምፅ ብልጫ አግኝተው በሁለተኛ ደረጃ ተመረጡ።

በዚሁም መሠረት ሐምሌ 17 ቀን 1975 ዓ.ም አባ ፊልጳስ ተብለው በመሠየም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ አንብሮተ በመላዋ ኢትዮጵያ ለሚገኙት ገዳማት ኤጲስ ቆጳስ ሆነው ተሾሙ። ወዲያ ውም በ1976 ዓ.ም ግንቦት 11 ቀን የመላው የኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት ኤጲስ ቆጳስነትን እንደ ያዙ በደምቢዶሎ የቄለም አውራጃ ኤጲስ ቆጳስ ሆነው ሠርተዋል።

እንደ ሚታወቀው በደርግ ዘመነ መንግሥት ሰንበተ እሑድ የገበያ ቀን እንዲሆን ታውጆ ይኸው ዐዋጅ በብዙ ቦታዎች ተግባራዊ መሆን ጀምሮ ነበር። ብፁዕነታቸው ግን በሀገረ ስብከታቸው ሕዝብ ዘንድ ይህች ቀን ተከብራ ትውል ዘንድ ከመንግሥት ባለ ሥልጣናት ጋር ተደራድረው እንድትከበር አድርገው ነበር ይባላል።

ብፁዕ አቡነ ፊልጳስ በተሰጣቸው መንፈሳዊ ተልእኮ በአሳዩት ቅን ተግባርና የሥራ ትጋት ከግንቦት 7 ቀን 1980 ዓ.ም ጀምሮ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሆነው ተሾሙ።

ከዚህ በኋላ የካቲት 4 ቀን 1980 ዓ.ም ብፁዕነታቸው የገዳማት ሐላፊነታቸውን እንደ ያዙ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የአሰብ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው እንዲሠሩ ተደርጐ በዚሁ ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ ተልእኮአቸውን በማከናወን ላይ እንዳሉ በድንገት በተወለዱ በ61 ዓመታቸው ሰኔ 12 ቀን 1981 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ያረፉበት ምክንያትም ሙቀት እንደ ሆነ ይነገራል። ብፁዕነታቸው በነበራቸው የትኅርምት ሕይወት ምግብ በሚገባ ስለማይመገቡ የብርድ ሕመም ነበረባቸው። በዚህ የተነሣ ነፋስ በእጅጉ ይፈሩ ነበር ይባላል። በአሰብ ሀገረ ስብከት ተመድበው ሲያገለግሉ ምንም እንኳን ሀገሩ ሙቀት ቢሆንም ከነበረባቸው የነፋስ ፍርሐት የተነሣ ልብስ

www.ethiopianorthodox.org



ይደራርቡ ነበር ይባላል። ሲተኙም ልብሶቻቸውን እንደ ደረቡ መስኮቶቻቸውና በሮቻቸው ያሏቸው ቀዳዳዎች ሁሉ እንዲጠቀጠቁ አድርገው ነበር። ታዲያ አንድ ቀን በዚህ ሁናቴ ተኝተው ሳሉ አየር አጥሯቸው በዚያው እስከ መጨረሻው እንዳሸለቡ ይነገራል።

የብፁዕነታቸው ሥርዓተ ቀብር አሰብ ከተማ በሚገኘው ሐመረ ኖኅ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ የደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፣ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የከተማው ምእመናን በተገኙበት ተፈጽሞአል። የብፁዕነታቸው በረከት ይደርብን። አሜን

# 3.41. ብፁዕ አቡነ በርናባስ ቀዳማዊ

## ሊቀ ጳጳስ

## /1917 - 1980 ዓ.ም/





ቀድሞ አባ ብርሃኑ ካሣ ይባሉ ነበር። በጎጃም ሀገረ ስብከት፣ በባሕር ዳር አውራጃ፣ በይልማና ዴንሣ ወረዳ፣ እነጋዴ ቅዱስ ሚካኤል ከተባለው ደብር ተወለዱ። አባታቸው ብላታ ካሣ አሳምነህ፤ እናታቸው ደግሞ ወ/ሮ ቀኑብሽ /በኋላ እማሆይ ቀኑብሽ/ ይባሉ ነበር።

የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ከወላጆቻቸው ሳይርቁ በ40 ቀናቸው በተጠመቁበት ቤተ ክርስቲያን ያስተምሩ ከነበሩት መሪ ጌታ ዘውዴ ዘንድ ተማሩ። ሁለተኛ ደረጃ /የዜማ/ ትምህርታቸውንም በዚያው አጠናቀቁ። ትምህርታቸውንም ለመቀጠል ወደ ቋሊሳ ሔደው ሸዋ ጽዮን ከምትባለው ደብር ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት መምህር አክሊሉ ዘንድ ቅኔን ከነ አገባቡ በሚገባ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ።

ብፁዕ አቡነ በርናባስ የጀመሩትን ዕውቀትን የመፈለግ ጉዞ በመቀጠል በዚያው ደብር ቅኔ ካስተማሯቸው መምህር የውዳሴና ቅዳሴ ማርያም እንዲሁም የስባቱ ኪዳናትን ትርጓሜ ካሔዱ በኋላ ወደ ጎንደር ተሻግረው ደብረ ታቦር አውራጃ ከምትገኘው ማደበረ ማርያም በምትባለው ቦታ ከዚያ በፊት ተምረውት የነበረውን ቁም ዜማ በመከለስ አጠናቀቁ። ከዚያም ወደ ጎንደር ከተማ በመሔድ ደብረ ፀሐይ ቁስቋም ከነበሩት ከመሪ ጌታ መዘምር የአቋቋም ትምህርትን በሚገባ ቀሰሙ። ይሁን እንጂ የአቋቋም ዕውቀታቸውን በማስረጃ ማረጋገጥ ስለ ነበረባቸው ወደ ደንቢያ በመሔድ ዓረቢያ መድኃኔ ዓለም ከነበሩት ለመ ጥር መምህር መሪ ጌታ አስናቀው የተማሩትን አቋቋም በመከለስ በመምህርነት ተመረቁ። ከዚህ በኋላ ከዚያው ጎንደር ውስጥ ጎርጎራ ደብረ ሲና ማርያም ከተባለችው ደብር ጉባኤ ዘርግተው ሲያስተምሩ ቆዩ።

ብፁዕ አቡነ በርናባስ ምንም እንኳን ጉባኤያቸው እየሞቀና እየሰፋ ቢሔድም የጉባኤው ፍቅር ከትምህርቱ ስላልበለጠባቸው ወደ ዙር አባ አቡነ አረጋዊ /ጽርሐ አርያም/ ሔደው ዝማሬና መዋሥዕት ተምረው በመምህርነት ተመረቁ። ከዚያም አሁንም በነበራቸው የመማር ፍላጎት የተነሣ እንግዲህስ ጉባኤ ልዘርጋ ሳይሉ መምህር ወልደ ሚካኤል ወደ ተባሉ መምህር ዘንድ ሔደው የቅዳሴን ዜማ በሚገባ ተማሩ። ከዚያም ወደ ቅዳሴው ምስክር ቤት ደብረ ዓባይ ወርደው መዝገበ ቅዳሴን ጽፈው በመማር አስመሰከሩ።

ብሁዕነታቸው በዚህ ዓይነት ራሳቸውን በቃለ እግዚአብሔር ካኮለበቱ በኋላ ወደ ታላቁ ገዳም መንዳባ መድኃኔ ዓለም በመውረድ ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጸሙ። ከዚህ በኋላ ወደ ጎጃም በመመለስ እነጋዴ ቅዱስ ሚካኤል ከተባለው ቦታ ጉባኤ ዘርግተው አቋቋም፣

www.ethiopianorthodox.org

ዝማሬ መዋሥዕትና ቅዳሴ ማስተማር ጀመሩ። ይሁን እንጂ ቦታው ለተማሪዎች ምቹ አልሆነም። በመሆኑም ደቀ መዛሙርታቸውን አስከትለው በባሕር ዳር አውራጃ በአቸፈር ወረዳ ወደ ሚገኘው ታላቁ ደብር ይሰማላ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሔዱ። በዚያም ወንበራቸውን ዘርግተው፣ ጉባኤያቸው ከዕለት ወደ ዕለት እየሰፋ ለስድስት ዓመታት ያህል በትጋትና በንቃት ሲያስተምሩ ቆዩ።

ብፁዕ አቡነ በርናባስ ከዚህ በኋላ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ቀደም ሲል ጉባኤ ዘርግተውባት ወደ ነበረችው ጎርጎራ ደብረ ማርያም በመመለስ ጉባኤያቸውን በንቃትና በትጋት ሲያስተምሩ በትርፍ ጊዜያቸውም መምህር ጳውሎስ ከተባሉ ሊቅ ዘንድ የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ ተማሩ። በዚህ ጊዜ የብፁዕነታቸው ሊቅነት፣ የጉባኤያቸውም ስፋት በወቅቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ከነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ጆሮ ደረሰ።

ቅዱስ ፓትርያርኩም ይህንኑ እንዳረጋገጡ ሊቁ ወደ አዲስ አባባ መጥተው በሚሰጣቸው ቦታ ተቀምጠው ቢያስተምሩ ጥቅሙ የበለጠ መሆኑን በመረዳት ብፁዕነታቸውን ጋበዟቸው። ብፁዕ አቡነ በርናባስም ግብዣውን በመቀበል ከሰፊው ጉባኤ ለመምህርነት የበቁትን 38 ደቀ መዛሙርት ይዘው ወደ አዲስ አባባ መጡ ። እንደ መጡም ወዲያውኑ የጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ደብር አስተዳዳሪነትን ተሾሙ።

በተሾሙበት ደብር ለዐሥር ዓመታት ያህል የቆዩት ብፁዕነታቸው ለአንዲት ቀንም ያህል ጉባኤያቸውን ሳይፈቱ፣ ምእመናንንም በማስተማር በማታው ክፍለ ጊዜ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ዘመናዊ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ።

ከዚህ በኋላ የብፁዕነታቸውን ሁለንተናዊ ብቃትና ትጋት ያየው የወቅቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ መልካም ፈቃድ ከፍተኛውን መንፈሳዊ ትምህርት ተምረው ለበለጠው አገልግሎት የተዘጋጁ ይሆኑ ዘንድ ወደ ግሪክ ቆጵሮስ የነገረ መለኮት ት/ቤት ላካቸው። ብፁዕ አቡነ በርናባስም ትምህርትን ፈጥኖ በመያዝ ችሎታቸው የቀረበላቸውን ትምህርት በመማር በዲፕሎማ ተመረቁ። በዚያውም ወደ ግሪክ ዋና ከተማ አቴና በመዛወር ከዚያ በሚገኘው የነገረ መለኮት ዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን በትጋት ከተከታተሉ በኋላ በማስትሬት ዲግሪ ተመረቁ።

ብፁዕ አቡነ በርናባስ በተገለጠው ዓይነት የማስትሬት ዲግሪ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም በመሔድ በዚያ



በሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳም ት/ቤት ማስተማር ጀመሩ። ይሁን እንጂ በገዳሙ ት/ቤት ለሦስት ዓመታት ብቻ እንዳስተማሩ በወቅቱ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አለቃኪይ ጥሪ ተደርጉላቸው ወደ እናት ሀገራቸው ኢትዮጵያ ተመለሱ። ከዚያም ወደ ዝዋይ የካህናት ማሠልጠኛ ተልከው ለተወሰኑ ዓመታት ካህናትን በማሠልጠን አገለገሉ።

ወንጌልን በማስፋፋት ረገድ ብፁዕነታቸው ትጋታቸውን በሔዱበት ቦታ ሁሉ ያስመሰከሩ ነበርና በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ መልካም ፈቃድ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ሐላፊ በመሆን ተሾሙ። ብፁዕነታቸው በዚህ ሥልጣናቸው በትጋት በማገልገል ላይ እንደ ነበሩ በ1973 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አንብሮተ እድ «ብፁዕ አባ በርናባስ ኤጲስ ቆጶስ» ተብለው የፓትርያርኩ ረዳትና የመንፈሳዊ ኮሌጅ ዲን በመሆን ተሾሙ።

ብፁዕ አቡነ በርናባስ በተሾሙበት ቦታ ቤተ ክርስቲያንን በትጋት ካገለገሉ በኋላ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ሊቀ ጳጳስ በመሆን ተሹመው ወደ ቅድስት ሀገር ሔዱ። ሹመቱን በአኮቴት ተቀብለው ወደዚያ ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ ከማኅበረ መነኮሳቱ ጋር በመተባበር ገዳሙን ሲያገለግሉ ቆዩ። ከዚያም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በባሌ ሀገረ ስብከት በመሾም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በማስተማር በርካታ ኢ-አማንያንን አጥምቀዋል።

ከዚህ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ የመንፈሳዊ ኮሌጅ ዲን ሆነው ወደ አዲስ አባባ መጡ። በዚያም ጥቂት ካገለገሉ በኋላ ከቦታው በመነሣት የቅዱስ ሲኖዶስ ጸሐፊና የአሰብ አውራጃ ሊቀ ጳጳስ ሆኑ። በአሰብ በነበሩባቸው ዓመታት በርካታ መንፈሳዊ አገልግሎቶችን ሲያበረክቱ ቆይተዋል። በመጨረሻም ባደረባቸው ሕመም ምክንያት በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ነሐሴ 3 ቀን 1980 ዓ.ም በሞት ተለዩ። ዜና ዕረፍታቸውም እንደ ተሰማ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሠራተኞች፣ የአዲስ አባባ አድባራትና ገዳማት ካህናት በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም በመሰባሰብ ጸሎተ ፍትሐት ሲያደርሱ ካደሩ በኋላ ሥርዓተ ቀብራቸው ነሐሴ 4 ቀን 1980 ዓ.ም በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተፈጸመ። የብፁዕነታቸው ረድኤት ይደርብን። አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

# 3.42. ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ቀዳማዊ ሊቀ ጳጳስ

## /1911-1989 ዓ.ም/





መምህር ወልደ ትንሣኤ ግዛው ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ በሰሜን ሸዋ፣ ተጉለትና ቡልጋ አውራጃ፣ ከሰም ወረዳ ልዩ ስሙ ደብረ ጽላልሽ አቲሳ ገዳም እየተባለ በሚጠራው ቦታ መጋቢት 24 ቀን 1911 ዓ.ም ተወለዱ። ወላጆቻቸው መምህሬ ግዛው ዘዮሐንስና ወ/ሮ ዘነበች የሺ ጌታ ይባሉ ነበር።

ብፁዕነታቸው በወላጆቻቸው እንክብካቤ አድገው ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ በዚያው በደብረ ጽላልሽ አቲሳ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ከነበሩት አባ ምንዋልሁስት ዘንድ ከፊደል እስከ ቃል ትምህርት ያለውን የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርት በሚገባ ተማሩ። ከዚያም በ1921 ዓ.ም ከግብፃዊው አቡነ ቄርሎስ መዓረገ ዲቁናን ተቀበሉ። ከዚህ በኋላ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ወደ መናገሻ ሔዱ። በዚያም ዕውቅ የድጓና የአቋቋም መምህር ከነበሩት አለቃ ገብረ እግዚአብሔር ዘንድ ሁለተኛውን ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርት ማለትም የጾዋትወ ዜማን ትምህርት ተማሩ።

ገና በሕፃንነታቸው የመማር ፍቅር የነበራቸው ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ በጥሩ ሁኔታ እየተማሩት የነበረውን ትምህርታቸውን በመቀጠል የቅኔን ዕውቀት ደግሞ ሊቀስሙ ከመናገሻ ተነሥተው ወደ ጎጃም ተሻገሩ። በዚያም ደብረ ማርቆስ ላይ ሰፊ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት አለቃ ሣህሌ ዘንድ ቅኔን ከተማሩ በኋላ ቆላ ቀርቀስና ዲማ ጊዮርጊስ በተባሉ ታላላቅ ገዳማት በመዘዋወር መጻሕፍተ ትርጓሜን በመጠኑ ተማሩ።

ብፁዕነታቸው በዚህ ዓይነት ዓባይን ተሻግረው ዕውቀት መንፈሳዊን ከሰበሰቡ በኋላ ወደ ትውልድ ሀገራቸው ተመለሱ። በዚያም መምህር በላይ ከተባሉ ሊቅ ዘንድ ተቀምጠው ቀደም ሲል ያካበቱትን ትምህርት በማጠናከር ላይ ሳሉ የኢጣልያ ወራሪ ኃይል ሀገራችንን በግፍ ወረረ። በዚህ የተነሣም ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ በሀገር ፍቅር ስሜት ተነሣሥተው ትምህርታቸውን በማቆም ከሌሎች አርበኞች ጋር በመቀላቀል ወራሪውን ኃይል በመቃወም ከቡልጋ ጫካ ገቡ።

ለአራት ዓመታት ያህል ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ጋር በመሆን በአርበኝነት ለሀገራቸው መብት መከበር እንደ ተጋደሉ አንድ ቀን ጠላት ድንገት ደርሶ በእሳቸውና በሌሎች ወንድሞቻቸው ላይ አደጋ አደረሰ። በዚህም የሞተው ሞቶ በሕይወት የተረፈው ሲበተን ብፁዕነታቸውም በአቃቂ አድርገው አዲስ ዓለም ወደ ነበረች እኅታቸው ሔዱ።

ይሁን እንጂ ወራሪው የኢጣልያ ጦር አዲስ ዓለምን አጥቅቶ በዚያ ከሕዝቡ ጋር ነበሩ ያላቸውን አርበኞች ለመያዝ ጥቃት

www.ethiopianorthodox.org

በስነዘረ ጊዜ ብፁዕነታቸው በጣልያን ወታደሮች ተይዘው ለእስር ተዳረጉ። ለአንድ ዓመት ያህል በእስር እንደቆዩ ወራሪው ኃይል በኢትዮጵያውያን ቆራጥ ተጋድሎ ድል ተመቶ ከሀገር ወጣ። ብፁዕነታቸውም ከነበሩበት እስር ቤት ተፈቱ።

ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ የሀገሪቷ ነፃነት ተመልሶ ከእስር ከተፈቱ በኋላ በቀጥታ ወደ ታላቁ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ገብተው ጥቂት ጊዜያት ቆይተው ነሐሴ 24 ቀን 1933 ዓ.ም መዓርገ ምንኩስናን ተቀበሉ።

ከዚህ በኋላ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በቤተ መንግሥት ፈቃድ በደብረ ሰላም ቀጨኔ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ለምእመናን በብሉተ ወንጌልን መስጠት ጀመሩ። በዚህም ወቅት መጋቢት 24 ቀን 1934 ዓ.ም በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ከብፁዕ አቡነ ቄርሎስ እጅ ቅስናን ተቀበሉ። ከዚያም ከቀጨኔ ወደ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ቆይቶም ወደ መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ በመዛወር በስብከተ ወንጌልና ቅዳሴ አገልግሎት ተሠማርተው ሲያገለግሉ ቆዩ። በዚህ አገልግሎታቸው ላይ እንደ ነበሩም መጋቢት 24 ቀን 1940 ዓ.ም በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ መታሰቢያ ታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም ከኢትዮጵያዊው ሊቀ ጳጳስ ከብፁዕ አቡነ ይስሐቅ መዓርገ ቁምስናን ተቀበሉ።

ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ በዚህ ዓይነት በአዲስ አበባ ለሰባት ዓመታት ያህል ሲያገለግሉ ዘመናዊ ትምህርታቸውን በመጀመር እስከ ስምንተኛ ተምረዋል።

በዚህ ዓይነት አዲስ አበባ ለተወሰኑ ዓመታት ከቆዩ በኋላ በ1940 ዓ.ም በሐረርጌ ሀገረ ስብከት ስባቱ ወንጌል የድሬዳዋ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አለቃ ሆነው ወደዚያው ተላኩ። በዚያም የተሰጣቸውን ሐላፊነት በብቃት በመወጣት ለአራት ዓመታት ያህል ቆዩ። ብፁዕነታቸው ከሀብተ በብኩት ጋር ሀብተ ፈውስ ከባለቤቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቸራቸው አባት በለ ነበሩ በአካባቢው ባበረከቱት አስተዋጽኦ ከምእመናን ዘንድ ታላቅ ፍቅርንና አክብሮትን አትርፈው ነበር።

በ1944 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መልካም ፈቃድ ተወልደው ፊደል ቆጥረው ወደ አደጉበት ደብረ ጽላልሽ እቲሳ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ተዛውረው በመምህርነት እንዲያስተዳድሩ ተሾሙ። በዚያም ለአንድ ዓመት ያህል በፍቅርና በትጋት አገለገሉ። ከመስከረም 1 ቀን 1945 ዓ.ም ጀምሮም የሸዋ ክፍለ ሀገር የጨቦና ጉራጌ አውራጃ ሊቀ ካህናት ተብለው ከዚህም ጋር የፍርድና የአስተዳደር ዳኝነት ሥራ እንዲሠሩ በቁምስናም ሆነ



በጽጽበና ላቅ ያለ አገልግሎት ወደ አበረከቱበት ቦታ ሔዱ። በዚያም በአታቸውን በአውራጃው ዋና ከተማ ላይ አጽንተው በአውራጃው ውስጥ ወደ ሚገኙት ዐሥራ ሦስቱም ወረዳዎች በመዘዋወር በተስጧቸው ሀብተ ስብከትና ሀብተ ፈውስ የአካባቢውን ምእመን በነፍሱም ሆነ በሥጋው ከመጣበት በሽታ ሁሉ ነጻ ማድረግ ጀመሩ። ከዚህም ጋር እናትና አባት የሌላቸውን እጓለ ሙታን በመሰብሰብ እየረዱና እያስተማሩ ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን እንዲጠቅሙ ያደርጉ ነበር።

ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ከዚህ በላይ በተገለጸው መንፈሳዊ ተግባራቸው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ በኤጲስ ቆጶስነት ተመርጠው ግንቦት 30 ቀን 1979 ዓ.ም በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ እድ «ብፁዕ አባ ዲዮስቆሮስ» ተብለው የጨቦና ጉራጌ አውራጃ ኤጲስ ቆጶስ ሆነው ተሾሙ።

ቀደም ሲል ጀምሮ ሲሰጡት የነበረውን መንፈሳዊ አገልግሎት በማጠናከር ለዐሥር ዓመታት ያህል በማገልገል ቅድስት ቤተ ክርስ ቲያን የጣለችባቸውን አደራ ሲወጡ ከቆዩ በኋላ ባደረባቸው ሕመም በ1989 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ሥርዓተ ቀብራቸውም ቅዱስ ፓትርያርኩ አቡነ ጳውሎስ፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ እንዲሁም ምእመናን በተገኙበት ተፈጸመ። የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን። አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

# 3.43. ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ካልአይ ሊቀ ጳጳስ

## /1917 - 1996/





ከመሾማቸው በፊት መምህር ተክለ ማርያም ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ በኤርትራ ክፍለ ሀገር ለንጊት ከረን አውራጃ ልዩ ስሙ አድርባ ሚካኤል ተብሎ በሚታወቀው ቦታ በ1917 ዓ.ም. ተወለዱ። የአባታቸው ስም አቶ ዓምደ ጊዮርጊስ ዕቁበ ጽዮን፤ የእና ታቸው ደግሞ ወይዘሮ ወለተ ቅዱሳን ዓምደ ሚካኤል ይባል ነበር።

ብፁዕነታቸው በወላጆቻቸው እንክብካቤ ካደጉ በኋላ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በአቅራቢያቸው በሚገኘው የጻዕዳ ዓምባ ሥላሴ ገዳም የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህ ርታቸውን ማለትም ንባብና ዳዊት ከቃል ትምህርት ጋር አጠ ናቀው ተማሩ። ከዚያም ትምህርታቸውን በመቀጠል ስዓታት ንና ግብረ ዲቁናን በሚገባ ከተማሩ በኋላ በወቅቱ የኤርትራ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ከነበሩት ግብፃዊው አቡነ ማርቆስ መዓርገ ዲቁና ተቀበሉ። በተቀበሉት መዓርግ በተወለዱበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በቅዳሴ ሲያገለግሉ ቆዩ።

ብፁስ አቡነ ያዕቆብ ሀብተ ዉልድና ስመ ክርስትና ባገኙበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለጥቂት ዓመታት ካገለገሉ በኋላ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ወስነው በሡራዬ አውራጃ ወደ ሚገኘው ደብረ ድኀሃን አቡነ ዮናስ ገዳም ገቡ። በዚያም አረጋውያን መነኮ ሳትን በመርዳት ከፍ ያለ ትሩፋትንና መንፈሳዊ አገልግሎትን እያበ ረከቱ ትምህርታቸውን ቀጠሉ። በዚህም ቅኔን፣ አቋቋምን በበለጠ ደግሞ መዝገበ ቅዳሴን ለመምህርነት በሚያበቃ ሁኔታ ተምረው ተመርቀዋል።

በገዳሙ ያበረከቱት በነበረው ላቅ ያለ መንፈሳዊ አገልግሎት ከማኅበረ መነኮሳቱ ከፍ ያለ ተወዳጅነትን ያገኙት ብፁዕነታቸው ከታላላቅ አባቶቻቸውና ወንድሞቻቸው ትምህርትን በማግኘት በአርዑተ ምንኩስና ተጠምደው ለመኖር በመወሰን በዚያው ሥርዓተ ምንኩስና ፈጸሙ። በመምህርነት በተመረቁበት ሞያም በዚያው ገዳም ወንበር ዘርግተው ለ10 ዓመታት ያህል ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል። ተማሪዎቻቸውን እያስተማሩ በ1938 ዓ..ም. መዓርገ ቅስና ከብፁስ አቡነ ማርቆስ፡ እንደዚሁም ከብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ መዓርገ ቁምስና ተቀብለዋል።

ብፁዕነታቸው በማኅበረ መነኮሳቱ በነበራቸው ተወዳጅነት የተነሮ ለገዳሙ አበምኔት ሆነው በመመረጥ ለአራት ዓመታት ያህል አገልግለዋል። ከዚያም የኤርትራ ሀገረ ስብከት ዋና ጸሐፊ ሆነው በመመረጥ ወደ አስመራ ሄደው ለዓመታት ከዋና ጸሐፊነታቸው በተጨማሪ በመንፈሳዊ ደኛነትና በሰባኬ ወንጌልነት ላቅ ያለ አገልግሎት አበርክተዋል። ከዚህም በተጨማሪ በወቅቱ በክፍለ ሀገሩ

www.ethiopianorthodox.org

ተከስቶ በነበረው የስሳም መደፍረስ የተነሣ መፍትሔ ለመፈለግ በተቋቋመው የሰላም ጉባኤ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በመወከል የጉባኤው አባል ሆነው ክፍ ያለ አስተዋጽኦ አበርክተዋል:: ከዚህም በተጨማሪ በወቅቱ መንግሥት አውጆት ለነበረው የመሠረተ ትምህርት ተግባራዊነት ከፍተኛ አስተ ዋጽኦ በማድረጋቸው የምስጋና ምስክር ወረቀት አግኝተው ነበር:: ቤተ ክር ስቲያንን ለማስፋፋት ሃይማኖትንም ለማጽናት በሚደረገው መንፈሳዊ ጉባኤም በኤርትራ ሀገረ ስብከት በሚገኙት አውራጃዎች ከሀገረ ስብከቱ እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ድረስ በመዘዋወር ሰበካ ጉባ ኤን በማቋቋምና በማጠናከር የሰንበት ተማሪዎችን ባማሰባሰብና በማ ስተማር የሚደነቅ ጥረት አድርገዋል::

የብፁዕነታቸውን መንፈሳዊ ተልእኮና ውጤት የተገነዘበው ቅዱስ ሲኖዶስ ጵጵስና ይገባቸዋል ብሎ ስለ መረጣቸው ግንቦት 7 ቀን 1980 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አንብሮተ እድ «አባ ያዕቆብ ጳጳስ ዘአዲስ አበባ» ተብለው ተሾሙ::

ሹመቱን በአኰቴት የተቀበሉት ብፁዕነታቸው በተሰጣቸው ሀገረ ስብከት ይልቁንም ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ አጠገብ በመሆን ቤተ ክርስቲያናቸውን በትጋት ማገልገል ጀመሩ:: ይሁን እንጂ ብዙም ሳይቀዩ ወደ ጎንደር ሀገረ ስብከት ተዛወሩ:: በዚያም አገልግሎታቸውን በመስጠት ላይ እንዳሉ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ሣልሳይ ፓትርያርክ ሥልጣናቸውን ሲለቁ ዐቃቤ መንበር ሆነው እንደ ገና ወደ አዲስ አበባ መጡ:: የተሰጣቸውን ከፍተኛ ሐላፊነት በብቃት ሲወጡ ከቆዩ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት አራተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው ሲሾሙ ቤተ ክርስቲያን ያስረከበቻቸውን አደራ አስረከቡ:: ከዚያም ብዙም ሳይቆዩ ወደ ኤርትራ ሔደው በዚያ ሲያገለግሉ ቆዩ:: በኤርትራም ከዚሁ ተሹመው የሔዱት ብፁዕ አቡነ ፊልጳስ በፓትርያርክነት ቆይተው ሲያርፉ ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ፓትርያርክ ሆነው ተሹመው እስካረፉበት 1996 ዓ.ም ድረስ አገልግለዋል:: የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን::



# 3.44. ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ካልአይ ሊቀ ጳጳስ

/1938 - 1983ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

መልአከ ፀሐይ አባ ሀብተ ማርያም ደምሴ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በሸዋ ክፍለ ሀገር በተጉለት አውራጃ በባሶ ወረዳ ልዩ ስሙ እንዲትጥድ በተባለው ሥፍራ ከአባታቸው ከአቶ ደምሴ ወልደ ጻድቅና ከእናታቸው ከወ/ሮ ትርፌነሽ ይመኑ ጥቅምት 21 ቀን በ1938 ዓ.ም ተወለዱ::

ብፁዕነታቸው ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በተጠመቁበት ደብር መሪ ጌታ ኩራ ከተባሉ መምህር ዘንድ የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ተማሩ:: ከዚያም ወደ ደብረ ጽሙና ገዳም በመሔድ ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስ ዘንድ ዳዊት፣ ጾመ ድጓና የዘወትር ምስራፍ ተማሩ:: ብፁዕነታቸው ትምህርታቸውን በመቀጠል በዚሁ ቦታ አቋቋም፣ ዝማሬና መዋሥዕት ከተማሩ በኋላ ከየኔታ ወልደ ማርያም ገብረ ኢየሱስ ሐዲሳትን፣ ዳዊትን፣ ትምህርተ ኅቡዓትን፣ የውዳሴ ማርያምና የቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ተማሩ::

ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በተጠቀሰው ዓይነት ትምህርታቸውን ካስፋፉ በኋላ በ1950 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ደብር እያገለገሉ በታዕካ ነገሥት ከታወቁት መምህር ከየኔታ ጊራ ቅኔን እንዲሁም ከየኔታ መንግሥቱ መዝገበ ቅዳሴን እንዲሁም ከመልአከ ገነት ጥሩ ነህ አቋቋም ተማሩ:: ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላም ከጥንታዊው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር የዘመናዊውንም ትምህርት በመጀመር እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ አጠናቀቁ::

በ1951 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከብፁዕ አቡነ ያዕቆብ መዓርገ ዲቁናን የተቀበሉት ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፡ በ1960 ዓ.ም በደብረ ጽላልሽ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መዓርገ ምንኩስናን፣ ከአራት ዓመት በኋላ በ1964 ዓ.ም ደግሞ ከብፁዕ አቡነ ገብርኤል መዓርገ ቅስናን ተቀበሉ:: ከዚያም አዲስ አበባ በሚገኘው በደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ደብር በቅስናና በቁስ ገበዝነት አገልግለዋል:: በዚሁ ጊዜ ከብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ መዓርገ ቁምስናን ተቀብለዋል::

ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በ1970 ዓ.ም በታላቁ /እንጦጦ/ ደብር ቀራንዮ መድኃኔ ዓለም በአስተዳዳሪነት ተሹመው እስከ 1972 ዓ.ም አገልግለዋል:: ከዚያም በመመለስ ቀድም ሲል ያገለግሉበት በነበረው ደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ደብር «መልአከ ሰላም» ተብለው ተሾሙ:: በዚያም ለሁለት ዓመታት እንዳገለገሉ ወደ ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ ደብር ተዛውረው ከ1974 - 1975 ዓ.ም አገለገሉ:: ከዚያም ወደ ታወቀው ደብር ቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ተዛውረው ከ1975 - 1981 ዓ.ም ለሰባት ዓመታት በፍቅርና በሰላም ሲያስተዳድሩ ቆዩ::



በመጨረሻም ወደ ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ደብር ተዛውረው በማስተዳደር አገልግሎት ላይ እንዳሉ በ1983 ዓ.ም በተደረገው የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ ተመርጠው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ አንብሮተ ዕድ «ብፁዕ አባ ተክለ ሃይማኖት ኤጲስ ቆጶስ» በድሬዳዋ ሀገረ ስብከት ተሾሙ::

ወደ ሀገረ ስብከቱ ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮም ቀደም ሲል በቦታው በነበሩ አባቶች ተጀምረው የነበሩ ሥራዎችን በማጠናቀቅ፣ አዳዲስ ሥራዎችንም በመፍጠር ከሀገረ ስብከቱ ካህናትና ምእመናን ጋር በመተባበር ሰፋ ያለ አገልግሎት አበርክተዋል:: ይሁን እንጂ በተቀበሉት ሥልጣን የተፈቀደላቸውን ያህል ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ካገለገሉ በኋላ ባደረባቸው ሕመም በሀገር ውስጥና በውጭ በሕክምና ሲረዱ ቆይተው መጋቢት 7 ቀን 1989 ዓ.ም ሀርፈው ሥርዓተ ቀብራቸው በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ተፈጽሟል:: የብፁዕነታቸው በረከት ይደርብን:: አሜን::

www.ethiopianorthodox.org

# 3.45. ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ካልአይ

## ሊቀ ጳጳስ

## /1903 - ?/





አባ ተወልደ ብርሃን ወ/ሥላሴ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ በ1903 ዓ.ም ተወለዱ:: ወላጅ እናታቸው ገና በሕፃንነታቸው ስላረፉ አባታቸው በምናኔ ወደ ደብረ ቢዘን ገዳም ሲገቡ ብፁዕነታቸውንም ይዘዋቸው ገቡ:: በመሆኑም የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ከግብረ ገብ ትምህርት ጋር ተማሩ::

ለቀጣዩ መንፈሳዊ ትምህርትም ወደ ሠራዬ አውራጃ ዓዲ ጠፉ ወደ ተባለ ቦታ ሔደው መምህር ወልደ ሥላሴ ከተባሉ ሊቀ ዘንድ ቅኔ ተቀኙ:: በመቀጠልም ይህንኑ የቅኔን ትምህርት ለማጠናከር ወደ ትግራይ ተሻግረው አምባ ሰነዪቲ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በሚገኘው የቅድስት ሥላሴ ገዳም ያስተምሩ ከነበሩት መምህር አፈ ወርቅ ከሚባሉ ሊቅ ዘንድ ቅኔን ከነአገባቡ አጠናቀቁ:: ቀጥሎም የትምህርት ፍላጎታቸውን ለማርካት ከኚሁ የቅኔ አስተማሪ ከመምህር አፈ ወርቅ ጋር ወደ አክሱም ሔደው የመጽሐፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ ተማሩ::

ብፁዕነታቸው በዚህ ዓይነት መንፈሳዊ ዕውቀትን በመገብየት ላይ እንዳሉ ትጋታቸውን እና መንፈሳዊነታቸውን ያዩትና ፊደል ቆጥረው ያደጉበት የደብረ ቢዘን ገዳም አበ ምኔት የነበሩት መምህር ዓምደ ማርያም ወደ ደብረ ቢዘን መልሰው ወሰዷቸው:: በዚያም በማኅበረ መነኮሳቱ ምርጫ እና ትእዛዝ ገዳሙን የሚጠቅሙ ልዩ ልዩ ሥራዎችን ሲሠሩ ቆይተው በ1922 ዓ.ም በአበ ምኔቱ በመምህር ዓምደ ማርያም እጅ ሥርዓተ ምንኩስና ተፈጸመላቸው:: ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ በአባቶቻቸው ፍኖት ለመጓዝ ቆባቸውን ከጫኑ በኋላ ገዳሙን በማገልገል በዕድሜና በበሽታ የተነሣ አልጋ ላይ የዋሉ መናንያንን ሲረዱ ቆዩ:: ከዚያም መዓርገ ቅስናን ለመቀበል ቀድሞ እንደ ሚደረገው ወደ መኻል ሀገር ለመምጣት ቢያስቡም በወቅቱ አገሪቱን ወርሮ የነበረው የኢጣልያ ኃይል ማንኛውም የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ሰው ወደ መኻል ሀገር መሔድ አይችልም ብሎ ከልክሎ ነበርና አልቻሉም:: ይሁን እንጂ ወደ ግብፅ በመሻገር በወቅቱ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ከነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ እጅ መዓርገ ቅስናን ተቀብለው መጡ::

ከዚህ በኋላ ለአንድ ዓመት ያህል ዶሳም ወደ ተባለው የገዳሙ ቦታ መንፈሳዊ ትምህርትን ሲሰጡ ከቆዩ በኋላ በማኅበረ መነኮሳቱ ጥያቄ እና ጥሪ ወደ ደብረ ቢዘን ገዳም ተመልሰው በቄስ ገበዝነት እንዲያገለግሉ ተመረጡ:: ብፁዕነታቸውም ምርጫውን በአክብሮት በመቀበል ለሦስት ዓመት ከስድስት ወር ያህል በቅንነት እና በትጋት አገለገሉ:: ከዚያም በትግራይ ክፍለ ሀገር በዓድዋ አውራጃ ዓዲ ጉደ ወረዳ በሚገኘው የደብረ ቢዘን ሁለተኛ ገዳም ወደ ሆነው ደብረ ገነት ተልከው ገዳሙን በመጠበቅና በማገልገል ለዓሥር

www.ethiopianorthodox.org

ዓመታት ያህል ሲያገለግሉ ቆዩ:: ሆኖም ከሠላሳ አራት ዓመት መንፈሳዊ አገልግሎት በኋላ በገዳሙ በአበ ምኔትነት ሲያገለግሉ የቆዩት መምህር ወልደ ሰማዕት በሞት ተለዩ:: በመሆኑም በአበው መነኮሳት ሕግና ሥርዓት ለዚሁ መንፈሳዊ ሐላፊነት በዕውቀት መንፈሳዊ እና በግብረ ገብነት ከታነጹት መካከል መምህር ተብለው በድምፅ ብልጫ ተመስክሮላቸው ወዲያው የገዳሙ አበ ምኔት ተብለው እንዲያስተዳድሩ በማኅበረ መነኮሳቱ ተመረጡ::

ብፁዕነታቸው በተሰጣቸው ሥልጣንና ሐላፊነት አገልግሎታቸውን በገዳሙ ብቻ ሳይወስኑ የአካባቢው ሕዝብ ትምህርተ ሃይማኖት እንዲማር፣ እብያተ ክርስቲያናት እንዲታነፁ፣ የገዳሙ ይዞታዎች እንዲከበሩ እና እንዲስፋፉ በማድረግ አገልግሎታቸውን በስፋት ቀጠሉ:: የብፁዕነታቸው ትምህርት፣ ምግባር እና አገልግሎት ታውቆ አባቶች ሲመሰክሩ እና ሲጠቆሙም ለታላቁ የቤተ ክርስቲያናችን ሥልጣንና ሐላፊነት ተመረጡ:: በምርጫውም ከፍተኛ ድምፅ በማግኘት ጥቅምት 18 ቀን 1983 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ አንብሮተ ዕድ ብፁዕ አባ ፊልጶስ የመላ ኢትዮጵያ ገዳማት ኤጲስ ቆጶስ ሆነው ተሾሙ::

ብፁዕነታቸው የኢትዮጵያ ገዳማት ሊቀ ጳጳስ ሆነው ሲሾሙ መቀመጫቸው ኤርትራ አስመራ ነበር:: በዚያ እንዳሉ ሀገሪቷ ከኢትዮጵያ ስትገነጠል በዚያው በአስመራ ቆይተዋል:: በዚህም ቤተ ክርስቲያኗ ራሷን ቻለች ሲባል ፓትርያርክ ሆነው እንደ ነበር ይነገራል:: በመጨረሻም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ሥርዓተ ቀብራቸው በደብረ ቢዘን ገዳም ተፈጽሟል:: የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን:: አሜን::



# 3.46. ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ሣልሳይ

## ሊቀ ጳጳስ

## /1936 - 1990 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

የቀድሞ ስማቸው አባ አረጋዊ ይባል ነበር። ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በሰሜን ሸዋ በመንዝና ግሼ አካባቢ ልዩ ስሙ ቃጥላ ቅድስት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን እየተባለ በሚጠራው ቦታ ተወለዱ። የተወለዱበት ዘመን 1936 ዓ.ም ሲሆን የአባታቸው ስም አቶ ወልደ ገብርኤል አብቤ፤ የእናታቸው ስም ወ/ሮ ይታይሽ ወልደ ገብርኤል ይባል ነበር።

በመልካም የወላጅ እንክብካቤ ያደጉት ብፁዕነታቸው ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በተወለዱበት አካባቢ በሚገኘው በከለርቦ ቅድስት ማርያም ደብር መምህር ንዋይ ከተባሉ መምህር ዘንድ የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ተማሩ። ከዚያም ትምህርታቸውን በመቀጠል በዚያው አካባቢ ወደ ምትገኘው መዞሪያ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመሔድ ከአለቃ ወልደ ጻድቅ ንዋይ ዘንድ የጾዋትወ ዜማን ትምህርት ተማሩ።

የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በዚህ ዓይነት ያጠናቀቁት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በ1950 ዓ.ም ወደ አዲስ አባባ መጥተው ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ። ከዚያም ወደ ሀገራቸው ሳይመለሱ በሰሜን ምዕራብ ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት ወደ ምትገኘው ደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመሔድ ከመሪ ጌታ ልዑል በደብረ ዓባይ ሥርዓተ ዜማ መዝገብ ቅዳሴን፤ ከመምህር ቶማስም ቅኔ፤ ከታወቁት ሊቅ ከመምህር ገብረ ሕይወት ደግሞ መጻሕፍተ ሐዲሳትን፣ የቅዳሴ ማርያምንና የውዳሴ ማርያምን ትርጓሜ፤ እንዲሁም የአቡሻኽር ትምህርታቸውን ተማሩ።

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በዚህ ዓይነት በመንፈሳዊው ትምህርት ከበሰሉና ከተደላደሉ በኋላ በ1954 ዓ.ም በታላቁ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጸሙ። ከዚያም በኋላ እንደ ገዳሙ ሥርዓት በዚያው ቆይታ አድርገው የሚጠበቅባቸውን ቀኖና ከፈጸሙ በኋላ ዘመናዊውንም ትምህርት ለመማር ፍላጐት ነበራቸውና ወደ አዲስ አበባ መጡ። እንደ መጡም በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል መንፈሳዊውን አገልግሎት እያበረከቱ በዚያው ዘመናዊ ውን ትምህርት መከታተል ጀመሩ።

ይሁን እንጂ አዲስ እባባ ላይ የጀመሩትን ትምህርት ሳይጠ ገቁበት በ1956 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ እቡነ ባስልዮስ አባታዊ ፈቃድ ወደ ሐረር ለመንፈሳዊ አገልግሎት ተላኩ። ነገር ግን ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ የዘመናዊውን ትምህርት የመማር ፍላጐት ተከትሏቸው ሐረር ድረስ ሔዶ ስለ ነበር በሐረር ከተማ በሚገኘው የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን እያገለገሉ እዚያው በሚገኘው



ልዑል ራስ መኰንን መንፈሳዊ ት/ቤት ዘመናዊውን ትምህርት በመከ ታተል የመጀመሪያ ደረጃ ዘመናዊ ትምህርታቸውን አጠ ናቀቁ።

ከዚህ በኋላ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ከሐረር ወደ ስዋስው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት መጥተው በዚያ የሚሰጠ ውን የነገረ መለኮት ትምህርት እንዲከታተሉ ተፈቅዶላቸው ወደ አዲስ አባባ መጡ። በመሆኑም በከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤቱ የሚሰጠ ውን የሃይማኖት ትምህርት በትጋት ከመማር ጋር የሁለተኛ ደረጃ ዘመናዊ ትምህርታቸውንም ጎን ለጎን በመማር አጠናቀቁ።

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በቅዱስ ጳውሎስ የነገረ መለኮት ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ የመማር ፍላጐታቸውን በቅርብ ይከታተሉ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መልካም ፈቃ ዳቸው ሆኖ በ1962 ዓ.ም ለከፍተኛ የነገረ መለኮት ትምህርት ወደ ሩስያ ተላኩ። በዚያም በሌኒን ግራድ የሩሲያ እርቶዶክስ ቤተ ክርስ ቲያን ዩኒቨርስቲ ለስድስት ዓመታት ያህል ትምህርታቸውን ተከታ ትለው በነገረ መለኮት ትምህርት የማስትሬት ዲግሪ ተቀበሉ። ከዚያም ባገኙት ዕውቀት ያስተማረቻቸውን ቤተ ክርስቲያን ለማገ ልገል ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው መጡ።

እንዳሰቡትም እናት ቤተ ክርስቲያናቸውን በየተመደቡበት ቦታ በትጋት በማገልገል ላይ ሳሉ በዚያ የሚያበረክቱት አገልግሎት ብልጫ እንደ ሚኖረው በመገንዘብ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ መልካም ፈቃድና ቡራኬ በ1969 ዓ.ም በለንደን ለምትገኘው ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሆነው በመሾም ወደ ዚያው ተላኩ።

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ይህንን ታላቅ ኃላፊነት ተሸክመው ወደ ለንደን ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮም በስደት ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ቅን አባትና ታዛዥ በመሆን በቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸው ዙሪያ እንዲሰባሰቡ፣ እንደ ቤተ ክርስቲያናቸው ሥርዓት ስደተኞቹ ምእመ ናን በሰበካ ጉባኤና በሰንበት ት/ቤቶች በመታቀፍ የሚጠበቅባቸውን እንዲያበረክቱ በማድረግ የምእመናንን ፍቅር በማትረፍ ሐላፊነታ ቸውን በብቃት ቢወጡ ቆዩ።

ይህንን የብፁዕነታቸውን በተግባር የተመሰከረ ስፊ አገልግ ሎት የተመለከተው ቅዱስ ሲኖዶስም ለታላቅ ሐላፊነት ቢበቁ ቤተ ክርስቲያናቸውን የበለጠ እንደሚያገለግሉ በማመን ለኤጲስ ቆጳስነት ተመረጡ። በመሆኑም ጥር 30 ቀን 1985 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ አንብሮተ እድ ብፁዕ አባ ዮሐንስ በመ ላው አውሮፓ የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

www.ethiopianorthodox.org

ኤጲስ ቆጶስ ተብለው ተሾሙ:: ከዚህም በኋላ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ቀድሞም ወደ ሚያውቁት ቦታ በመሔድ በለንደን የመጀመሪያውን የቅድስት ቤተ ክርስቲያን መንበረ ጵጵስና በመመሥረት አገልግ ሎታቸውን በስፋት ቀጠሉ::


ብፁዕነታቸው ወደ ሀገረ ስብከታቸው ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ የአውሮፓ ከተሞች ያለ ምንም ድካም በመዘዋወር ምእመናንን በማስተማር ከቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸው ጋር ያላቸ ውን ግንኙነት በተግባር እንዲጠብቁ አድርገዋል:: ከዚህም ጋር በዚያ የሚገኙትን በርካታ ጥቁር አሜሪካውያንን በማሰባሰብ አስተ ምረው የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አባላት እንዲሆኑ አድርገዋል:: የተወሰኑትም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተምረውና ሥልጣነ ክህነት በመያዝ ተመልሰው ለአገልግሎት እንዲበቁ አድርገዋል::

ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣቸውን ዕድሜ በሙሉ ሥራ ሠርተው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንድትጠቀም ያደረጉት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ እንደ ተለመደው የተቀደሰ ሐዋርያዊ አገልግሎታ ቸውን በማከናወን ላይ እንዳሉ ታኅሣሥ 16 ቀን 1990 ዓ.ም በደረሰባቸው ድንገተኛ አደጋ በተወለዱ በ53 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል:: ሥርዓተ ቀብራቸውም አስከሬናቸው ከለንደን ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዞ ብፁዕ አቡነ አረጋዊ በወቅቱ የሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የቅዱስ ሲኖዶስ ተወካይ በተገኙበት በቢታንያ አልዓዛር አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ለብፁዓን አበው በተዘጋጀው መካነ መቃብር ሀረፈ:: የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን:: አሜን::



# 3.47. ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ሣልሳይ ጳጳስ

/1938 - 1991 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

ቀድሞ አባ ኪዳነ ማርያም አለባቸው ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ በደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት በሳስታ አውራጃ ልዩ ስሙ መዳጌ አቦ በተባለው ቦታ በ1938 ዓ.ም ከአባታቸው ከአቶ አለባቸው ወልዴና ከእናታቸው ከወ/ሮ ዓለሚቱ እንደሻው ተወለዱ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ እዚያው ከወላጆቻቸው ቤት እየተመላለሱ ከአጐታቸው ከቄስ አስምረው እንደሻው ከፊደል እስከ ንባብ ተማሩ። ከዚያም ትምህርታቸውን በመቀጠል መሪ ጌታ አበጀ ከተባሉ የድጓ መምህር ዘንድ የሁለተኛ ደረጃ /የዜማ/ ትምህርታቸውን አጠኑ። ከዚህ በኋላ በ1949 ዓ.ም በወቅቱ የወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ብፁዕ አቡነ ገብርኤል መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ።

ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ከዚህ ቀጥሎ የጀመሩትን ትምህርት ለማስፋፋት ትውልድ አካባቢያቸውን በመተው ወደ ጎጃም ተሻገሩ። በዚያም ደብረ ጽላሎ በመባል በሚታወቀው የቅኔ ትምህርት ማዕከል ታዋቂ ከነበሩት ከወ/ሮ ገላነሽ ሐዲስ /እማሆይ ገላነሽ ሐዲስ/ ዘንድ ቅኔን ከነአገባቡ ተማሩ። ከዚያ ቀጥሎም ከእማሆይ ገላነሽ የጀመሩትን ትምህርት ለማስፋፋት በድጋሚ አለቃ መንክር ወደ ተባሉት ሊቅ በመሔድ ቅኔን በሚገባ አጠናከሩ።

ከዚህ በኋላ ወደ ወሎ በመመለስ ብዙ ሊቃውንት ወደ ሚገኙበት ገረገራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በመሔድ ከታወቁት ሊቅ ከመሪ ጌታ መንግሥቱ ጐሹ ዘንድ ጾመ ድጓና ምዕራፍ በሚገባ ተማሩ። ይሁን እንጂ አሁንም በተለመደው የተማሩትን ደግሞ በመማር የማጠናከር ብቃታቸው በነፋስ መውጫ አውራጃ ልዩ በሙ ማይደርፉ ወደ ተባለው ቦታ በመሔድ ከመሪ ጌታ ኀሩይ /ዘውዱ ጨቡዴ/ ዘንድ ጾመ ድጓንና ምዕራፍን እንደ ገና በመከለስ አጠናቀቁ።

ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ አሁንም በነበራቸው የመማር ፍላጐት የቀራቸውን መንፈሳዊ ትምህርት ለመማር በ1956 ዓ.ም ወደ አዲስ አባባ መጡ። በመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ገዳም በፊ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ወደ ነበሩት መምህር ቀጸላ ሠይፉ /በኋላ አቡነ እንድርያስ/ በመሔድ መጻሕፍተ ሐዲሳትን፣ ውዳሴ ማርያምንና ቅዳሴ ማርያምን እንዲሁም የኪዳንንና ትምህርተ ኅቡአትን ትርጓሜ፤ እንዲሁም ባሕረ ሐሳብን በሚገባ አጥንተው በመምህርነት ተመረቁ።

በዚህ ዓይነት ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ መምህራቸው መምህር ቀጸላ ብፁዕ አቡነ እንድርያስ ተብለው ወደ ጎንደር ሀገረ ስብከት ሲሔዱ ተከትለው ወደ ጎንደር ሔዱ። በዚያም ደቀ መዛሙ



ርትን እያስቀጸሉና የአቡነ ቀሲስነቱን ሥራ በመሥራት ለሁለት ዓመት አገለገሉ። በ1967 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መልካም ፈቃድና ትእዛዝ በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ት/ቤት ገብተው የ11 ወራት ሁለ ገብ ኮርስ በመከታተል የምስክር ወረቀት ተቀበሉ።

ከዚያም በኋላ በመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በሰብከተ ወንጌልና በመዘምርነት ተመደቡ። በተመደቡበት ቦታም በቅንነት በማገልገል ላይ ሳሉ እንደገና በ1969 ዓ.ም በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድዖ ኮሚሽን አማካይነት በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ከየካቲት 15 እስከ ግንቦት 15 ድረስ በተዘጋጀው ሁለ ገብ ኮርስ ተሳትፈው በጥሩ ውጤት በማጠናቀቅ የምስክር ወረቀት ተቀበሉ። ከዚያም በተመደቡበት የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ምእመናንን በማስተማር ለአምስት ዓመታት ያህል አገለገሉ።

ከዚያም በ1977 ዓ.ም ወደ ደብረ ነጐድጓድ ቅዱስ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን በመዛወር በአስተዳዳሪነት ማገልገል ጀመሩ። ከአጥቢያው ካህናትና ምእመናን ጋር በመተባበርም አያሌ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን አከናወኑ። በ1984 ዓ.ም እንደ ገና ወደ ደብረ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን በመዛወር የተለመደውን አገልግሎታቸውን ሲያበረክቱ ቆዩ። በ1985 ዓ.ም እንደ ገና ወደ ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ተዛውረው ለጥቂት ዓመታት ሲያገለግሉ ቆዩ።

ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ በዚህ አገልግሎታቸው ላይ እንደ ነበሩ በ1987 ዓ.ም በቅዱስ ሲኖዶስ ተመርጠው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ አንብሮተ ዕድ መዓርገ ኤጲስ ቆጶስነትን ተቀብለው በደቡብ ኦሞ ሀገረ ስብከት ተሾሙ። በዚያም የተጠሩበትን አገልግሎት በማፋጠን ላይ ሳሉ ኅዳር 5 ቀን 1991 ዓ.ም በደረሰባቸው ድንገተኛ የመኪና መገልበጥ አደጋ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ሥርዓተ ቀብራቸውም በአዋሳ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል። የብፁዕነታቸው ረድኤት አይለየን። አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

# 3.48. ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ቀዳማዊ ሊቀ ጳጳስ

## /1933 - 1991 ዓ.ም/





መዓርገ ጵጵስና ከማግኘታቸው በፊት ሊቀ ጉባኤ ሀብተ ዮሐንስ ቤተ ይባሉ ነበር። ብፁዕ አቡነ ኤልያስ በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በአንኮበር ወረዳ ልዩ ስሙ ዋሻ ገብርኤል ከሚባለው ቀበሌ ከአባታቸው ከመምህሬ ቤተ ሣህሌና ከእናታቸው ከወ/ሮ ባሕሬቱ ሙሉ ሸዋ ተወለዱ። ዘመኑም 1933 ዓ.ም ነበር። ብፁዕነታቸው በደጋግ ወላጆቻቸው ክብካቤ አድገው ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በተወለዱበት ሆማ ተክለ ሃይማኖት ደብር ከአባ ወልደ ሥላሴ ዘንድ የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ።

ከዚያም ወደ አዲስ አባባ መጥተው ደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ላይ ጉባኤ ዘርግተው ሲያስተምሩ ከነበሩት መሪ ጌታ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ ሚካኤል ጸዋትወ ዜማን ተማሩ። በዚህ ጊዜም ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መዓርገ ዲቁናን ተቀበሉ። ከዚያም በዲቁናቸው በደብሩ እንዲያገለግሉ ተፈቅዶላቸው በዚያው በደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት በመዘምርነትም ጭምር ማገልገል ጀመሩ። ከአገልግሎትም ጎን በወቅቱ የደብሩ አስተዳዳሪ ከነበሩት ከአለቃ አያሌው ታምሩ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በሚገባ አጠኑ።

ብፁዕ አቡነ ኤልያስ በደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ለአምስት ዓመታት ያህል በመማርና በማገልገል ከቆዩ በኋላ ለበለጠ ትምህርት ወደ ወሎ አቀኑ። በዚያም ገረገራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ላይ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት መምህር ምናሴ ዘለቀ የጸዋትወ ዜማ ትምህርታቸውን በማስፋፋት አጠናቀቁ። በመቀጠልም በዚያው ሀገረ ስብከት ሆብል እንጦጦ መድኃኔ ዓለም ያስተምሩ ከነበሩት ሊቀ ኅሩያን ወልደ ሰንበት እንዲሁም ወደ ደቡብ ጎንደር በመሔድ ነፋስ መውጫ ልዩ ስሙ መንጮ ቂርቆስ በተባለው ደብር ያስተምሩ ከነበ ሩት ከመምህር ኪነ ጥበቡ ቅኔን ከነ አገባቡ ተማሩ።

ብፁዕነታቸው አሁንም ትምህርታቸውን በመቀጠል ወደ መካነ ኢየሱስ በመሔድ ባሕረ ሐሳብ፣ ሐዲሳትና ፍትሐ ነገሥት ከመምህር ኃይለ ሚካኤል ገብረ ጊዮርጊስ ተማሩ። ከዚህ በኋላ እንደ ገና ወደ አዲስ አበባ በመመለስ በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ የመምህራንና የቀሳውስት ማሠልጠኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ገብተው ከመምህር ሳእለ ማርያም ዓሥራት /በኋላ አቡነ ሕርያቆስ/ መጻሕፍተ ሐዲሳትን አጠናቀው በመማር ዲፕሎማ ተቀበሉ።

ብፁዕ አቡነ ኤልያስ በዚህ ዓይነት ዕውቀታቸውን ካስፋፉ በኋላ ከፍጹም ትሕትና ጋር ቤተ ክርስቲያንን በሰፋትና በትጋት ሲያገለግሉ ቆዩ። በዚህም ከ1964 - 1969 ዓ.ም በታዕካ ነገሥት በኣታ ለማርያም የሐዲስ መምህር፣ ከ1969 - 1976 ዓ.ም በሊቀ ጉባኤነት እንዲሁም የስብከትና የድርሰት ሐላፊ በመሆን አገልግለዋል።

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕነታቸው ከነበራቸው የመማር ፍላጐት የተነሣ በአገ ልግሎት ላይም እያሉ ቅኔን ከመጋቤ ምሥጢር ጌራ ወርቅ ጥበቡ፣ መዝገብ ቅዳሴን ከመጋቤ ኅሩያን መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በመማር በመምህርነት ተመርቀዋል። እንዲሁም ከንቡረ እድ መኩሪያ አብየ ሆይ የመዝገብ ቅዳሴን አንድምታ ትርጉም ተምረዋል።

ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ከፍ ሲል ከተዘረዘሩት ትምህርቶች በተጨ ማሪም ዛሬ የካቲት 6 ትምህርት ቤት በሚባለው የቀድሞው ዘነበ ወርቅና የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ዘመናዊ ትምህርታቸውን በመማር በጥሩ ውጤት አጠናቀ ዋል። ብፁዕነታቸው በዚሁ ወቅት በነበራቸው ምሥጢራትን በዘመና ዊ አቀራረብ ለምእመናን የማቅረብ ችሎታ በአዲስ አባባ ልዩ ልዩ አድባራትና ገዳማት በመዘዋወር በትጋት ሲያስተምሩ ቆይተዋል።

ይህንን የብፁዕነታቸውን ትጋት በአንክሮ የተከታተለውና ያጤነው ቅዱስ ሲኖዶስም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ መልካም ፈቃድና ትእዛዝ ከጥቅምት 1 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ በምዕራብ ሐረርጌ የሊቀ ጳጳሱ ረዳት ቆሞስ ሆነው እንዲያገለግሉ ተላኩ። በዚያም በተቀበሉት አደራ መሠረት በትጋት ለአንድ ዓመት እንዳገለገሉ በ1987 ዓ.ም በተደረገው የኤጲስ ቆጳሳት ምርጫ ተመርጠው ኅዳር 4 ቀን 1987 ዓ.ም በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድና በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ እንብርተ እድ የኤጲስ ቆጳስነትን መዓርግ ተቀበሉ።

ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ይህን ታላቅ መዓረግ እንደ ተቀበሉ የተሾሙት በምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ነበረ። ወደዚያ ከሔዱ በት ጊዜ ጀምሮም በጣዕመ ስብከታቸው የሀገረ ስብከቱን ምእመናን እስተምረው ያላመኑትን እንዲያምኑ፣ ያመኑትም በእምነታቸው በር ትተው ራሳቸውን ከመናፍቃን እንዲጠብቁ አድርገዋል። በተለይ እርሳቸው በሔዱበት ዘመን በሐረርና አካባቢው የተሐድሶ መናፍቃን እንቅስቃሴ እግሩን መስደድ የጀመረበት በመሆኑ ብፁዕነታቸው ባደረጉት ትግል መናፍቃኑ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር ተጠልለው የቅሰጣ ሥራቸውን ከመሥራት እንዲታገዱ አድርገዋል። ከምዕራብ ሐረርጌ ጋር የምሥራቅ ሐረርጌንና የአጋዴን አህጉረ ስብከ ትንም ደርበው እንዲያስተዳድሩ በተደረገ ጊዜ የመናፍቃኑን ማንነት በስብከት የማጋለጥ ስፊ እንቅስቃሴያቸውን ቀጥለዋል።

ብፁዕነታቸው በዚህ ዓይነት በመላ ሀገረ ስብከታቸው በመዘ ዋወር ሰፊ አገልግሎት ሲሰጡ ከቆዩ በኋላ ከሰኔ 25 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ ከሐረርጌ ወደ ወለጋ ሀገረ ስብከት እንዲዛወሩ ተደረገ። የማስተማር ሀብት በእጅጉ የተሰጣቸው ብፁዕ አቡነ ኤልያስ በወለ



ጋም ከሔዱበት ጊዜ ጀምሮ የሀገረ ስብከቱን ምእመናን በማስተማር፣ የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናትን በማሳደስ፣ ባልተሠራባቸውም እያሠሩ ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተዋል።

ብፁዕ አቡነ ኤልያስ በዚሁ ሀገረ ስብከት በማገልገል ላይ እንደ ነበሩ በባሌ ሀገረ ስብከት ሊደረግ በታቀደው የስብከተ ወንጌል መርሐ ግብር ላይ እንዲገኙ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሰላማ ተጋብዘው ከብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ጋር ሲጓዙ በደረሰባቸው ድንገተኛ የመኪና አደጋ በተወለዱ በ58 ዓመታቸው ግንቦት 12 ቀን 1991 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ሥርዓተ ቀብራቸውም ግንቦት 14 ቀን 1994 ዓ.ም በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድ ራል ተፈጽሟል። የብፁዕነታቸው በረከት ይደርብን። አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

# 3.49. ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ካልአይ ሊቀ ጳጳስ

## /1932 - 1992 ዓ.ም/





አባ ገብረ ሥላሴ ኃይለ ማርያም ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ በጎንደር ክፍለ ሀገር በአብናት አውራጃ በምትገኘው ደብረ ይባቤ ገዴ ማርያም አጥቢያ በ1932 ዓ.ም ተወለዱ:: ወላጆቻቸውም አቶ ኃይለ ማርያም አበበና ወ/ሮ ወይኒቱ ትኩዬ ይባሉ ነበር:: በወላጆቻቸው ክብካቤ በመንፈሳዊ ሥርዓትና ሥነ ምግባር /ትምህርት/ እየታነጹ ካደጉ በኋላ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በአካባቢያቸው አጃ ጊዮርጊስ ተብሎ በሚታወቀው ቦታ ላይ ያስተምሩ ከነበሩት መሪ ጌታ ይግዛው የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ /ከፊደል እስከ ጸዋትወ ዜማ/ ትምህርታቸውን በሚገባ አጠናቀቁ::

ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ወደ ደንቢያ በመሔድ በዘርፉ ስመ ጥር ከነበሩት መምህር አክሊሉ ብርሃን ቅኔን ከነ አገባቡ ተማሩ:: ከዚያም ወደ ርእሰ አድባራት አክሱም ጽዮን በመሔድ ከመምህር ገብረ ጊዮርጊስ ገብረ አምላክ ሐዲሳትን ተማሩ::

በዚህ ዓይነት ከቦታ ቦታ ተዘዋውረው ከተማሩ በኋላ የሕይወት አቅጣጫቸውን በመወሰን ወደ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ገቡ:: በዚያም ለበርካታ ዓመታት ሥርዓተ ገዳምን በመማር፣ ማኅበረ መነኮሳቱንም በረድእነት እያገለገሉ ከቆዩ በኋላ በማኅበረ መነኮሳቱ ፈቃድ በ 1957 ዓ.ም የገዳሙ አበ ምኔት ከነበሩት ከመምህር ገብረ ማርያም ተስፉ ሥላሴ መዓርገ ምንኩስናን ተቀበሉ:: ሥርዓተ ምንኩስናን ከፈጸሙም በኋላ በዚያው ገዳም በትጋት በማገልገል ላይ እንዳሉ በ1961 ዓ.ም በማኅበሩ ምርጫ የገዳሙ አበ ምኔት ሆነው ተመረጡ:: በገዳሙ ላይ የተሾሙት ብፁዕነታቸው ማኅበረ መነኮሳቱን በማስተባበር የገዳሙን ልማትና ዕድገት በማጠናከር፣ ሥርዓተ ገዳሙን በመጠበቅ፣ በማስጠበቅ እስከ 1969 ዓ.ም ድረስ በታማኝነትና በቅንነት ሲያገለግሉ ቆዩ:: ከዚያም የተሰጣቸውን ሐላፊነት በፈቃዳቸው ለማኅበሩ በማስረከብ በዚያው ገዳም በትርጎምት ተወስነው ቆዩ::

ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ በ1983 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የታላቁ ገዳም መናገሻ ማርያምና የጋራ መድኃኔ ዓለም ገዳም አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ:: በዚያ ገዳምም ምእመናንን በማስተባበር የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በማከናወን እስከ 1985 ዓ.ም ድረስ በቅንነት ሲያገለግሉ ቆዩ:: በ1986 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ መልካም ፈቃድ ወደ አዲስ አባባ ተዛውረው በደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣ በብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ፣ በማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም፣ በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም፣ በደብረ ሰላም ቀጨኔ መድኃኔ ዓለምና በታዕካ

www.ethiopianorthodox.org

ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም በመዘዋወር ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ ቆዩ።

በመጨረሻም በሕይወት ዘመናቸው ለቅድስት ቤተ ክርስ ቲያን ያደረጉትን አስተዋጽኦና ትርጎምት የተመላውን ሕይወታቸውን በመመልከት በየካቲት ወር 1990 ዓ.ም ቅዱስ ሲኖዶስ የአጋዴን ሀገረ ስብከት ቆሞስ ሆነው እንዲያገለግሉ ሾማቸው። ነገር ግን ብዙም ሳይቆዩ ቅዱስ ሲኖዶስ ባደረገው የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ እርሳቸው አንዱ እንዲሆኑ በመወሰኑ ሐምሌ 5 ቀን 1991 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ አንብሮተ ዕድ የአጋዴን ሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጶስ ሆነው ተሾሙ። ብፁዕነታቸው የተሰጣቸውን ታላቅ ሐላፊነት በመያዝ ወደ ሀገረ ስብከታቸው በመሔድ አገልግሎት ጀመሩ። ከዚያም ወደ ድሬዳዋ ሀገረ ስብከት ተዛውረው የተለመደ አገልግሎታቸውን ማበርከት ጀመሩ። ይሁን እንጂ ሀገረ ስብከ ታቸውን ብዙም የማገልገል ዕድል ሳይገጥማቸው ባደረባቸው ሕመም ኅዳር 24 ቀን 1992 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። የብፁዕነታቸው ረድኤት ከሁላችን ጋር ይኑር። አሜን።



# 3.50. ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ሣልሳይ ጳጳስ

## /1937 - 1995 ዓ.ም/



www.ethiopianorthodox.org

ቀድሞ አባ ኃይለ ኢየሱስ እጅጉ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሉቃስ በሰሜን ወሎ በቡግና ወረዳ በቅዱስ ላል ይበላ አጥቢያ በ1937 ዓ.ም ተወለዱ:: ወላጆቻቸው ስም መሪ ጌታ እጅጉ በለውና ወይዘሮ በፍታ መብራቱ ይባሉ ነበር::

ብፁዕ አቡነ ሉቃስ በወላጆቻቸው ቤት በመንፈሳዊ ሥነ ሥርዓትና በሥነ ምግባር ታንጸው አድገው ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ በዚያው ህብተ ዉልድና በጥምቀት ባገኙበትና ከላል ይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት አንዱ በሆነው በቤተ ጉልጉታ አባ ኃይለ ሚካኤል ከተባሉት መምህር ዘንድ የመጀመሪያ ደረጃ /ከፊደል እስከ ንባብ/ ትምህርታቸውን፣ ከሊቀ ትጉሃን አባ ቢተው ደግሞ ሁለተኛ ደረጃ /ጸዋትወ ዜማ/ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ተማሩ::

ብፁዕነታቸው ትምህርታቸውን ለማስፋፋት ወደ ገረገራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር በመውረድ ከመሪ ጌታ መንግሥቱ ውሂብ ዘንድ የጀመሩትን የዜማ ትምህርት በመቀጠል ምዕራፍና ጾመ ድጓ በሚገባ ተማሩ:: ከዚህም በተጨማሪ በዚያው ደብር መሪ ጌታ ፍሥሐ ከተባሉ መምህር ዘንድ አቋቋም ተማሩ::

ብፁዕ አቡነ ሉቃስ በነበራቸው የመማር ፍላጎት የዜማ ትምህርታቸውን በዚህ ዓይነት ካጠናቀቁ በኋላ ለቀጣዩ ትምህርት ወደ ጎጃም ተሻገሩ:: በዚያም ዋድላ የንጃ ቅዱስ ሚካኤል ከተባለው ደብር የኔታ መዝሙር ከተባሉ መምህር ቅኔን ከነ አገባቡ ተማሩ:: ነፋስ መውጫ ሥላሴ ወደ ተባለው ቦታ በመሔድም ከመሪ ጌታ ይትባረክ ዘንድ የቅኔ ትምህርታቸውን አስፋፉ::

በዚህ ዓይነት ወደ ጎጃም ሔደው የቅኔን ዕውቀት የቀሰሙት ብፁዕ አቡነ ሉቃስ በዚያው ወደ ጎንደር በመሻገር መሪ ጌታ መዝሙር፣ መሪ ጌታ እራጌ፣ መሪ ጌታ ለይኩንና መሪ ጌታ ፍቅሬ ከተባሉ ሊቃውንት አቋቋምን በሚገባ ተማሩ:: ከዚህ በኋላ ብፁዕነታቸው በ1966 ዓ.ም ከጎንደር ወደ አዲስ አበባ መጡ:: የብፁዕነታቸውን ዕውቀት የተገነዘበው የወቅቱ የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደርም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ መልካም ፈቃድ በምዕራብ ሸዋ ተጂ ከተማ ወደ ሚገኘው ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በመዘምርነት እንዲያገለግሉ መደባቸው:: በዚያም ለሰባት ዓመታት ያህል በቅንነት መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ሲያበረክቱ ቆዩ::

በዚህም ጊዜ ሕይወታቸውን በድንግልና ሊመሩ ወስነው ነሐሴ 24 ቀን 1970 ዓ.ም ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመሔድ በብፁዕ አቡነ ሚካኤል ጸሎተ ቡራኬ ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጸሙ:: ከዚያም መስከረም 26 ቀን 1971 ዓ.ም በወቅቱ የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ከብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ መዓርገ ቅስናንና ቁምስናን ተቀበሉ:: በዚህ ዓይነት መዓርጋቸውን የተቀበሉት ብፁዕ አቡነ ሉቃስ አዲስ አበባ በሚገኘው አስኮ ደብረ ገነት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎት ተመደቡ:: በዚያም ለአንድ ዓመት ያህል በቅስናና በመዘምርነት ካገለገሉ በኋላ በ1972 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መልካም ፈቃድ የቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ደብር አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ:: በደብሩ ባበረከቱት የአምስት ዓመታት አገልግሎት የአጥቢያውን ምእመናን በማስተባበር ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑን አስጠግነዋል:: ቤተ ልሔሙም በዘመናዊ መልኩ እንዲታነጽ አድርገዋል:: ከዚህም በተጨማሪ የደብሩ መካነ መቃብር ተጠናክሮ እንዲሠራ፣ በደብሩ ስምም የእርሻ ልማት ሥራ እንዲስፋፋና ሰበካ ጉባኤው ተጠናክሮ የካህናቱ ደሞዝ እድገት እንዲያሳይ አድርገዋል::



ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ከተሾሙበት ደብር በ1977 ዓ.ም የጽርሐ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን አለቃ ሆነው ወደ ዚያው ተዛወሩ:: ብፁዕነታቸው በዚህም ደብር የተለያዩ አገልግሎቶችን አበርክተዋል:: ከአገልግሎታቸው ውስጥ የቤተ ክርስቲያኑ ክልል በማዘጋጃ ቤት እንዲታወቅና የይዞታ ማረጋገጫ እንዲያገኝ ማድረጋቸው በዐቢይነት ይጠቀሳል:: ብፁዕ አቡነ ሉቃስ በጽርሐ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ለሁለት ዓመታት ካገለገሉ በኋላ በ1979 ዓ.ም እንደ ገና ወደ አስኮ ደብረ ገነት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ተዛወሩ:: በዚያም ለሰባት ዓመታት ያሀል በቅንነት ሲያገለግሉ ቆይተዋል:: በመጨረሻም በ1985 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ,በጐ ፈቃድ ወደ ላስታ ቅዱስ ላል ይበላ ደብር ተዛወሩ:: ወደ ዚያ ከሔዱ ጊዜ ጀምሮም በታሪካዊውና ጥንታዊው የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት የአካባቢውን ምእመናን በስፋት አገልግለዋል:: ካበረከቱት አገልግሎት ውስጥም ቤተ ዐማኑኤል፣ ቤተ መድኃኔዓለም፣ ቤተ መስቀልና ቤተ ሊባኖስ የተባሉትን አብያተ መቅደስ ጊዜያዊ መጠለያ ቆርቆሮ በማልበስ ካጋጠማቸው በዝናብ የመታጠብ አደጋ አትርፈዋል፤ የቤተ ክርስቲያኑን ገቢ ብማሳደግ የካህናቱ ደሞዝ እንዲያድግ አድርገዋል::

ብፁዕነታቸው በላል ይበላ ደብር ለአምስት ዓመታት ካገለገሉ በኋላ ወደ ደቡብ ኦሞ ሀገረ ስብከት ተዛወሩ:: በዚያም የተለመደ አገልግሎታቸውን በመቀጠል በአካባቢው ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋ አድርገዋል፣ ዘጠኝ ክፍል ያለው መንበረ ጵጵስና አሠርተዋል፣ በበጎ አድራጊዎች እርዳታ የአገልጋይ ካህናት እጥረት ባሉባቸው አካባቢዎች ካህናት እንዲቀጠሩ አድርገዋል::

www.ethiopianorthodox.org

በመጨረሻም ብፁዕነታቸው ለረጅም ዘመናት በትጋት ያበረከቱትን አገልግሎት ከግንዛቤ ውስጥ የከተተው ቅዱስ ሲኖዶስ ለኤጲስ ቆጶስነት መርጧቸው ሐምሌ 5 ቀን 1991 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ አንብሮተ ዕድ «አባ ሉቃስ ጳጳስ ዘደቡብ ኦሞ» ተብለው ተሾሙ:: ብፁዕነታቸው ሀገረ ስብከቱን ቀድሞም ያውቁት ነበርና አገልግሎታቸውን ከዕለት ወደ ዕለት በማስፋፋት ሐላፊነታቸውን መወጣት ጀመሩ:: በዓመቱ ሐምሌ 13 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ ከአገረ ስብከታቸው ጋር የስሜን ኦሞን ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና ሥራ ደርበው እንዲሠሩ ተደረገ::

ብፁዕ አቡነ ሉቃስ በሁለቱም አህጉረ ስብከት እየተዘዋወሩ በስብከተ ወንጌልና ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን በማስተባበር ከቆዩ በኋላ ከታኅሣሥ 15 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ ወደ አዲስ አባባ ተዛውረው የሀገረ ስብከቱ ጳጳስ እና የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ረዳት ጳጳስ ሆነው ተመደቡ:: ብፁዕነታቸው በዚሁ አገልግሎት ላይ እንዳሉ ስንልፈት ባበቃቸው ሕመም ከፉኛ ተያዙ:: ብፁዕነታቸው ከያዛቸው በሽታ ድነው ወደ ተለመደ አገልግሎታቸው ይሠማሩ ዘንድ በሀገር ውስጥ በተለያዩ ሆስፒታሎች፣ ከሀገር ውጭም ወደ እስራኤልና ሮም በመሔድ በሕክምና ሲረዱ ቢቆዩም ከሕመማቸው ሊድኑ አልቻሉም:: ነሐሴ 27 ቀን 1995 ዓ.ም በተወለዱ በ58 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: ሥርዓተ ቀብራቸውም ነሐሴ 28 ቀን 1995 ዓ.ም በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የልዩ ልዩ መመሪያ ሐላፊዎች፣ በአዲስ አባባ ሀገረ ስብከት የልዩ ልዩ አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች፣ ካህናትና ምእመናን በተገኙበት ተፈጸመ:: የብፁዕነታቸው በረከት ይደርብን :: አሜን::



# ዋቤ መጻሕፍት

## I. የታተሙ

### ሀ/ መጻሕፍት

#### ሀ.1/ እንግሊዝኛ


Abir M. 1980. Ethiopian and the Red Sea. London: Frank Cass and Company Ltd.

Aymero Wondimagegnehu. 1965. A Short Introduction of the Ethiopian Orthodox Church. Addis Ababa: Berhanena Selam Publishing Press.

---. 1970. The Ethiopian Orthodox Church. Addis Ababa: Berhanena Selam Printing Press.

Aziz, A.S. 1968. History of Eastern Christianity. Nortre Dame: University of Notre Dame.

Bahiru Zewde. 1992. A History of Modern Ethiopia. Addis Ababa: Addis Ababa University Press.

Clapham, C. 1988. Transformation and Continuity in Revolutionary Ethiopia. New York: Cambridge University Press, 1988.

Ephrem Isaac. 1968. The Ethiopian Church. Boston: Henry N. Sawyer Company.

General Staff Intelligence. 1917. A Hand Book of Abyssinia. Khartoum:

Greenfield, Richard. 1965. Ethiopia: A New Political History. New York: Frederick A. Praeger.

Hyatt, Harry M. The Chrch of Abyssinia. London:

Kefele Zeleqe. 1971. About the History of Independence of Ethiopian Church. Addis Ababa: Berhanena Selam Publishing Press.


www.ethiopianorthodox.org

Mara, Y. 1972. The Church of Ethiopia: the National Church in Making. Asmara: Il Poligrafico Press.

Michael Geddes. 1694. The Church History of Ethiopia. London:

Nicolas of Aksum. 1951. Church's Revival, Emancipation from 1600 Guardianship Free Church in Free State. Cairo: Costa Tsoumas and co. Press.

Sergew Hable Sellase. 1972. The Church of Ethiopia. Addis Ababa: Ethiopian Orthodox Church Press.

Solomon Gashaw. "Power Struggle in Addis Ababa 1906 - 1916," BA Thesis in History, Haile Sellase I University, 1971.

Taddesse Tamrat. 1972. Church and State in Ethiopia 1270 - 1527. Oxford: Oxford University Press.

Tensa'e Za Goubae. 1963. The First Ethiopian Patriarch. Addis Ababa: Berhanena Selam Printing Press.

---. Zena Mewa'el of Tekle Haymanot. 1985. Addis Ababa

Abrha Gebre Hiwot. "The History of Dabra Bizen Monastery from Its Foundation to Date" Asmara: 1991.

ሀ.2/ አማርኛ

መርስኤ ኀዘን ወ/ቂርቆስ:: 1938 ዓ.ም:: የዘመን ትዝታ፣ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት:: አዲስ አበባ

--- :: 1956 ዓ.ም:: የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

መንፈሳዊ ጉባኤ ዋና ጽ/ቤት:: 1938 ዓ.ም:: አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት::

--- :: 1943 ዓ.ም:: ሢመተ ሊቀ ጳጳሳት ኢትዮጵያዊ:: አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት::

--- :: 1951 ዓ.ም:: የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት::



መንግሥቱ ለማ:: 1959 ዓ.ም:: መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ወልደ ጻድቅ:: አዲስ አበባ፣

ማኅተመ ሥላሴ ወ/መስቀል:: 1942 ዓ.ም:: ዝክረ ነገር፣ አዲስ አበባ፣ ነፃነት ማተሚያ ቤት::

ስርግው ሐብለ ሥላሴ:: 1970 ዓ.ም:: «የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ረቂቅ እንዲሻሻል የተባዛ»፣ ቁ. 3፣ ገጽ 96 - 97:: አዲስ አበባ::

አባ ቄርሎስ:: ሊቀ ጳጳስ:: 1969 ዓ.ም.:: ፍሬ ሃይማኖት:: አስመራ፣ ኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት::

--- :: 1961 ዓ.ም:: ፍሬ ከናፍር 5ኛ መጽሐፍ:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

ትንሣኤ ዘጉባኤ:: 1963 ዓ.ም:: የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

ኅሩይ ወ/ሥላሴ:: 1921 ዓ.ም:: ዋዜማ :: አዲስ አበባ፣

አበራ ጀንበሬ:: 1985 ዓ.ም:: የእስር ቤቱ አበሳ በታላቁ ቤተ መንግሥት ከ1966ጠ1974 ዓ.ም::

ከበደ ተሰማ:: 1962 ዓ.ም:: የታሪክ ማስታወሻ:: አዲስ አበባ፣

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ /አለቃ/:: «አንዳንድ ነጥቦች ስለ ሀገር፣ ቋንቋና ነገድ የመግቢያ ክፍል::» የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም፣ Acc. No. 1908::

ኅብረ ሥላሴ :: 1959 ዓ.ም:: ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ:: አዲስ አበባ፣

ጎርጎርዮስ /አባ/:: 1981:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ:: አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት::

ለ/ ጋዜጦችና መጽሔቶች

ለ.1/ አማርኛ

ስምዐ ጽድቅ፣ ቅጽ ? ቁጥር ?፣ 1989

--- ፣ ቅጽ 9 ቁጥር 5፣ 1994 ዓ.ም::

--- ፣ ቅጽ 8 ቁጥር 10፣ 1993 ዓ.ም::

www.ethiopianorthodox.org

ተክለ ሃይማኖት፣ ቅጽ 18፣ ቁጥር 21::

ትንሣኤ፣ የሃያ አምስት ዓመት መንፈሳዊ ርምጃ

--- ፣ ቁጥር /?/ መጋቢት 1972 ዓ.ም::

--- ፣ ቁጥር 58፣ 1978 ዓ.ም::

--- ፣ ቁጥር 117፣ 1979 ዓ.ም::

--- ፣ ቁጥር 127 ፣ 1980 ዓ.ም::

--- ፣ ቁጥር /?/ ፣ ሐምሌ 1980 ዓ.ም::

--- ፣ ቁጥር /?/ ፣ ነሐሴ 1980 ዓ.ም::

ድምፀ ተዋሕዶ፣ መስከረም 1972 ዓ.ም::

--- ፣ ኅዳር 1974 ዓ.ም::

--- ፣ መጋቢት 1975 ዓ.ም::

--- ፣ ጥቅምት 1976 ዓ.ም::

--- ፣ ሐምሌ 1976 ዓ.ም::

--- ፣ ነሐሴ 1978 ዓ.ም::

--- ፣ መጋቢት 1979 ዓ.ም::

--- ፣ መስከረም 1980 ዓ.ም::

--- ፣ ኅዳር 1980 ዓ.ም::

--- ፣ ሐምሌ/ነሐሴ 1983 ዓ.ም::

አዲስ ዘመን፣ ነሐሴ 1፣ 1940 ዓ.ም::

አኮቴት፣ ቁጥር 2፣ 1985 ዓ.ም::

--- ፣ ጥቅምት 8፣ 1952 ዓ.ም::

ዜና ቤተ ክርስቲያን፣ ግንቦት፣ 1940 ዓ.ም::

--- ፣ ሐምሌ፣ 1961 ዓ.ም::

--- ፣ ጥቅምት፣ 1969 ዓ.ም::

--- ፣ መጋቢት፣ 1981 ዓ.ም::

--- ፣ ጥቅምት፣ 1980 ዓ.ም::

--- ፣ ሰኔ፣ 1968 ዓ.ም::





--- ፣ ጥቅምት፣ 1992 ዓ.ም::

--- ፣ ኅዳር፣ 1987 ዓ.ም::

--- ፣ ጥር፣ 1990 ዓ.ም::

--- ፣ መጋቢት፣ 1981 ዓ.ም::

--- ፣ መስከረም፣ 1969 ዓ.ም::

--- ፣ ጥቅምት፣ 1980 ዓ.ም::

--- ፣ ጳጉሜን፣ 1982 ዓ.ም::

--- ፣ ጥር፣ 1985 ዓ.ም::

--- ፣ ግንቦት፣ 1974 ዓ.ም::

--- ፣ ሐምሌ፣ 1952 ዓ.ም::

--- ፣ ሰኔ፣ 1980 ዓ.ም::

ዝክረ ቴዎፍሎስ ሰማዕት 2ኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ፣ ሐምሌ 4 ቀን 1989 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ::

ዝክረ ጻድቅ ለዓለም ይሄሉ /ታላቁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ሐዋርያ ብፁዕ አቡነ እንድርያስ እኚህ ነበሩ/። ጥር 1988 ዓ.ም::


### ለ.2/ እንግሊዝኛ


The Ethiopian Herald. Vol. 6, No. 6, 1948.


## II. ያልታተሙ

### ሀ/ ሰነዶች


Archive of the Ethiopian Orthodox Church. "Abuna Basilios." File No. 171, Folder No. 2680.

Archive of the Ethiopian Orthodox Church. "Debre Tsige Mariam Church." File No. 1009, Folder No. 6096.

Archive of the Ethiopian Orthodox Church. "Debre Tsige Mariam


www.ethiopianorthodox.org

Church," File No. 1009, Folder No. 9075.

Archive of the Ethiopian Orthodox Church. "Menagesha Amba Mariam Monastery," File No. 493, Folder No. 4508.

Archive of the Ethiopian Orthodox Church. "Abuna Takla Haymanot," File No. 100, Folder No. 4382.

Archive of the Ethiopian Orthodox Church. "Abuna Takla Haymanot," File No. 200, Folder No. 10936.

Archive of the Ethiopian Orthodox Church. "Abuna Tewoflos," File No. 100, Folder No. 755.

Archive of the Ethiopian Orthodox Church. "Dabra Mankerat Monastery," File No. 200, Folder No. 742.

### ለ/ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች

Abate Kassa. "The History of Lideta Church (1926 - 1974)," BA Thesis in History, Addis Ababa University, 1991.

Adugnba Amenu. "The Ethiopian Orthodox Church Becomes Autocephalous," BA Thesis in History, Hile Sellase I University, 1971.

Andualem Mulaw. "Begemeder and Semen," BA Thesis in History, HSIU, 1971.

Beletu Mengistu. "A Short Biography of Abuna Matewos (1881 - 1926)," BA Thesis in History, AAU, 1972.

Derese Beyene. "Ethio-Egyptian Relations," BA Thesis in History, AAU, 1986.

Tareqegn Yibabe. "The History of Mahdere Mariam," BA thesis in History, AAU, 1988.

Wudneh Almaz. "The Foundation, Growth and Development of Soddo Town Untill the Revolution 1974," BA Thesis in History, AAU, 1974.



# ምዕራፍ አራት

## አባሪዎች

### አባሪ 1

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ለአቡነ ቄርሎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

እስከ አሁን ድልድሉንና መተዳደሪያውን ያቆየንባችሁ ከኛ አገር የተሾሙት ጳጳሳት አዲስ ስለሆኑና ሕዝቡ አዲስ ነገር ስለሆነበት ባለማወቅ ክፉ ነገር እየተናገረ እንዳይጎዳ እነርሱም በሥራው እንዲለምዱ በማለት ነው።

አሁን ግን እንግዲህ ሥራው ከተለመደ ሥራውን ከዚህ እንደሚከተለው አድርጋችሁ ሥሩ።

አንደኛ።

ስለ ስብከታችሁ ስም።

የኢትዮጵያ የመላው ሊቀ ጳጳሳት በአቡነ ቄርሎስ ሆኖ ከውስጡ ከፍል ስብከትም ኢትዮጵያ መኻል ሆኖ ደቡቡ ለአቡነ ሳዊሮስ፣ ምዕራቡ ለአቡነ አብርሃም፣ ምሥራቁ ለአቡነ ጴጥሮስ፣ አዜቡ፤ ለአቡነ ሚካኤል፤ ሰሜኑ፤ ለአቡነ ይስሐቅ ይሁን። ይኸውም በስም በስሙ ተቆጥሮ በወረቀት ተጽፎላችኋል።

ሁለተኛ።

ርክበ ካህናት።

በመራራቅም አሳባችሁ እንዳይለያይ ባመት አንዳንድ ጊዜ መጽሐፍ እንደሚያዘው እየተገናኛችሁ ለሕዝበ ክርስቲያኑ የሚሆንለትን ምግባር ሃይማኖት እየተመካከራችሁ እንድታቀኑስት ይሁን።

ሦስተኛ።

ስለምታስተምሩበት ቦታ።

አሁን ስበካችሁን የከፈልነው በስፊ በሰፊው ነውና ለሕዝቡ

www.ethiopianorthodox.org

ትምህርታችሁ እንዳይርቀው የዐይን መጐበኘታችሁም እንዳይለየው እያንዳንዳችሁ ጳጳሶች ሁለት ሁለቱን ታላላቅ አውራጃ ነውና የሰጠናችሁ መንፈቁን ካንዱ መንፈቁን ካንዱ ከተማ ላይ እየተዛወራችሁ እንድታስተምሩ።

አራተኛ።

ስለ መተዳደሪያ ልክ።

እንደዚያው እንደ ተማከርነው ማደሪያችሁ በገንዘብና በማረፊያ ጉልት ስለ ሆነ በያዙት በመናገሻ ላይ በቾ ከሚባለው መቶ ገባርና የወር ደመወዝ ሁለት ሺህ ብር ለአቡነ ሳዊሮስ ባፈር ባይኔ ልክ አገር ደመወዝ እንደ ወንድሞቻቸው አምስት መቶ ብር ተቀብለው በእጨጌነታቸው ግን የሚያስፈልገውን ማደሪያ መዝነን ለብቻ ይቀበሉ። ለአቡነ አብርሃም፣ ለአቡነ ሚካኤል፣ ለአቡነ ጴጥሮስ፣ ለአቡነ ይስሐቅ መዠመሪያ አቡነ ማቴዎስ ሲገቡ ይዘውት በነበረው ባፈር ባይኔ ልክ ከየቦታቸው ላይ ጉልት እየተቀበሉ ለቤት ጉዳይ ማሰናጃ በወር 500 500 ብር አድርገንላቸዋል።

አምስተኛ።

ይኸንኑም የታዘዘላችሁን ገንዘብ መዠመሪያ ከየሰበካችሁ ላይ እንድትቀበሉ።

ሲያንስም ከየቤተ መንግሥቱ እንዲሞላላችሁ በፊት ሰበካችሁን ከመረመራችሁት በኋላ ለዚሁ ለታዘዘላችሁ ልክ ሆኖ የማይሞላላችሁ ሲሆን ከቤተ መንግሥቱ እየሞላ ይሰጣችሁ። ሲጒድልም እኛ እንፈልግም የምትሉ እንደ ሆነ በየሰበካችሁ በናንተው ሹም እየሰበሰባችሁ ራሳችሁን ቻሉ ትርፍም ቢገኝ ለተማሪ ቤት ይሁን።

ስድስተኛ።

ከየሰበካችሁ ላይ ወደ እናንተ በግብር የሚገባ የገጸ በረከትም አቀባበል ለምና ጠፍንቱ እየተመዛዘነ ግብሩ እስኪተካከል ድረስ ላሁን እንደዚያው እንደ ተለመደው ይውጣ።

ሰባተኛ።

እናንተ ስለ ምትገቡበት ዳኝነት ሕግ ከምትገዙትም ከጉልታችሁ ከምታስተምሩትም ከሰበካችሁ እናንተም በሥጋዊ ዳኝነት እንግባ እንዳትሉ፤ ሥጋዊ ዳኞችም በመንፈሳዊ ዳኝነት እንግባ እንዳይሉ፤ ይኸውም እናንተ የማትገቡበት ሥጋዊ ዳኝነት ሰው በርስቱ፤ በገንዘቡ፣ በአካላቱ የተነጠ በሚነጋገርበት ነገር ጨዋም ካህንም ቢሆን ነገሩ ሥጋዊ ከሆነ በዚሁ በሥጋዊ ዳኝነት ይለቅ።



ለየጉልታችሁም ደኅና ደኅና ሹም እያደረጋችሁ ከዋየት ወዲህ ካዋሽ በመለስ ያለ ጉልት ሲሆን ሰበሩ አዲስ አበባ ወደ ክፍሉ ወንበር እየመጣ ይታይ። ከዚህ የሚርቀው አገር ግን ስለ ርቀቱ ድኻው እንዳይበደል ሰበሩ ከዚያው ከዋናው አገረ ገዥ ላይ ይታይ። መንፈሳዊ ዳኝነት የሚባለው ግን ካህንም ምእመናንም ቢሆኑ ነገሩ የሃይማኖት የሥልጣንና የሕግ የገረገራ ግቢውና የዳስ ዳኝነት ሲሆን የሥጋዊ ዳኞች ሳይገቡባችሁ እናንተው እየያዛችሁ በላይም በንጉሠ ነገሥቱ በታችም በጳጳሳቱም ሥርዓት ይለቅ። የምትሾሙትም ወንበር መንፈሳዊ ይሁን፤ በዚህም ምክንያት የሚመጣ ዳኝነት ቢገኝ ወደ ደመ ወዛችሁ ሒሳብ ይቀላቀል።

ስምንተኛ።

ለጊዜው በሥልጣን መስጠት ምክንያት ስለሚገባው ገቢ ገንዘብ የክህነት ጨው የሚባለው ፈጽሞ ይቅር። ሰውም ዲቁናና ቅስና ሲቀበል የሚመለክርለት አንዳንድ ጉርድ ወረቀት ይቀበል። ሲቀበልም ለወረቀቱ ዋጋ አንዳንድ ብር ብቻ ይከፈል። ይኸውም ገንዘብ ለወረቀቱና ለጸሐፊው ዋጋ ችሎ የሚተርፍ ሲገኝ ወደ ደመ ወዛችሁ ይቀላቀል።

ዘጠነኛ።

ስለ ቅዳሴ በሚገባ እክል ሳያገኘው እዳፋኝ ስለሚከፍል። እስካሁን ታቦቱ እየተዳፈነ ሹማምንት ወይም ጳጳስ ብቻ እዳፋኙን እየበሉ ታቦቱ ምንም ሳያገኝ በመቅረቱ አላግባብ እንዳይሆን አለቃና ገበዝ ፈልገው ያስቀደሱ እንደ ሆነ ሁለቱን እጅ እዳፋኝ እነሱ እየበሉ ሲሶውን ጳጳሱ ይብላ። እነሱ ፈልገው ያላስቀደሱ እንደ ሆነ ግን ሁለት ዕጅ ለታቦቱ ጉዳይ እየሆነ ሲሶውን ጳጳሱ ይብላ።

/ሀ/ አቡነ ሳዊሮስ ዘደቡብ ኢትዮጵያ

ራሱ የወበሪ ድንበር እግሩ የጐጃም ድንበር።

የደብረ ሊባኖስ ቆላው ላም ዋሻ ሞረት

| | |
|---|---|
| እንጠሮ | አዳብርጋ |
| መርሐ ቤቴ | ሜታ ሮቢ |
| ጉረኒ | ሜጫ |
| ግምብቹ | ሩፋ |
| ውጫሌ | ጊዳ |
| ሙሎ | ጥቁር |
| ጨቦ | ሶዶ |
| ጉራጌ | ሥልጢ |

www.ethiopianorthodox.org

| | |
|---|---|
| ማረቆ | መስቃን |
| ውርባረግ | እነሞር |
| እነቆር | ሲዳሞ |
| ክምባታ | ገሙ |
| ሊሙ | ቦረና |
| ወላሞ | አመያ የፈታውራሪ |
| | ሀብተ ጊዮርጊስ |
| | ይዞታ:: |

ስለ አቀማመጥና አስተዳደር::

መንፈቁን ደብረ ሊባኖስ ወላሞ፤ መንፈቁን አዲስ አበባ ላይ ተቀምጠው ያስተምሩ:: ሲዛወሩም በበታችዎ ሊቀ ካህናት ሆነው የሚጠብቁልዎ ለግማሹ ክፍል የደብረ ሊባኖስ ጸባቴ ለግማሹ ክፍል የወላሞ የዳሞት ተክለ ሃይማኖት መምህር ይሁንልዎ:: የጵሕፈት አድራ፮ዎ ጳጳስ ዘደቡብ ኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ ተላዌ አሡሩ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት ይበል:: ጥር 22 ቀን 1923 ዓ . ም::

/ለ/ አቡነ ይስሐቅ ዘሰሜነ ኢትዮጵያ::

ራሱ ጨጨሆ እግሩ እስከ ኤርትራ ወሰን::

| | |
|---|---|
| ዋግ | ገረአልታ |
| ላስታ | ሐራማት |
| የጁ | እንደርታ |
| ደላንታ | አይባ |
| ዋድላ | 2 አውላዕሎ |
| ዳውንት | ዋጅራት |
| ሸደሆ | ሠራዬ |
| ዋሮ | አበርገሌ |
| መቄት | ቦራ |
| ዐድዋ | ዕንዳመሆኔ |
| ሽሬ | አዘቦ |
| አክሱም | ጨርጨር |
| አጋሜ | ራያ |
| ተንቤን | ዞብል |

ስለ አቀማመጥና አስተዳደር::

መንፈቁን ላሊበላና መርጦ፤ መንፈቁን አክሱምና መቀሌ ላይ ተቀምጠው ያስተምሩ:: ሲዞሩም በበታችዎ ሆነው ሕግ የሚጠብቁልዎ የላሊበላው መምህር የአክሱሙ ንቡረ እድ ይሁንልዎ፤



አድራሻዎም ጳጳስ ዘሰሜነ ኢትዮጵያ ተላዌ አሡሩ ለአቡነ ሳሙኤል ይባል::

/ሐ/ አቡነ አብርሃም ዘምዕራብ ኢትዮጵያ::

ራሱ ጎንደር እግሩ መተማ እንግሊዞች ወሰን ድረስ::

| | |
|---|---|
| ግንደ በረት | ጎዣም |
| ሰላሌ | አገው |
| ደራ | ዳሞት |
| ቦረና | ሜጫ |
| ሜዳ | አቸፈር |
| በጌምድር በሞላ | ወንድዬ |
| ስሜን | ይልማና ዴንሳ |
| ቋራ | |

<u>ስለ አቀማመጥና አስተዳደር</u>

መንፈቁን በጌምድር ደብረ ታቦርና ጉንደር፤ መንፈቁን ጎጃም መርጠለ ማርያምና ማርቆስ እየተቀመጡ ያስተምሩ:: ሲዛወሩም በበታችዎ ሊቀ ካህናት ሆነው ሕግ የሚጠብቁልዎ የጣና ቂርቆስ መምህር የመርጠለ ማርያም መምህር ይሁንልዎ አድራ፮ዎም ጳጳስ ዘምዕራብ ኢትዮጵያ ተላዌ አሡሩ ለአቡነ ሐራ ይባል::

/መ/ አቡነ ጴጥሮስ ዘምሥራቅ ኢትዮጵያ

ራሱ በሸሉ በመለስ እግሩ አቦከ ፈረንሳዊ ወሰን ድረስ::

| | |
|---|---|
| መንዝ | ደራ |
| ግሼ | ቦረና |
| ወረይሉ ጃማ | አንጾኪያ |
| ይፍራታ | ዉይንት |
| ግድም | ወረሂመኖ |
| አምባሰል | ወረበቾ |
| ወረባቡ | ተኩለደሬ |
| ወረዋዩ | ዓባይ ቤት |
| ወረቃሉ | ለጋምቦ |
| ጨረቻ | ለገ ሂዳ |
| ለገ ጐራ | |

ስለ አቀማመጥና አስተዳደር::

መንፈቁን ወረይሉ መንፈቁን ደሴ እየተቀመጡ ያስተምሩ:: ሲዛወሩም በበታችዎ ሊቀ ካህናት ሆኖ ሕግ የሚጠብቅልዎ የተድባበ ማርያምና የሐይቁ መምህር ይሁንልዎ አድራ፮ዎም ጳጳስ ዘምሥራቅ

www.ethiopianorthodox.org

ኢትዮጵያ ተሳዬ አሠረ ለአቡነ ኢየሱስ ሞዓ ይበል።

/ሠ/ አቡነ ሚካኤል ዘአዜበ ኢትዮጵያ

ራሱ ጉደር ወንዝ እግሩ እንግሊዝ ወሰን ድረስ።

| | |
|---|---|
| የሸኖገሌ | ጉማይ |
| የጆቴ አገር | ቶኪን ጨርሮ |
| ዱሬኒ | ቡኖ |
| የደጃች ገብረ እግዚአብሔር | ጊሚራ |
| አገር | ኢሉባቦር |
| ጉማ | ጉራ ፈርዳ |
| ወለጋ የራስ ደምስው ይዞታ | ትቤ |
| ሲቡ | ጩለያ |

ስለ አቀማመጥና አስተዳደር።

መንፈቁን ኢሉባቦር መንፈቁን ወለጋ እየተቀመጡ ያስተምሩ። ሲዛወሩም በበታችዎ ሊቀ ካህናት ሆኖ የሚጠብቅልዎ ወለጋ ያርጅው አለቃ ይሉባቦር የጉሮ ማርያም አለቃ ይሁንልዎ፤ አድራሻዎም ጳጳስ ዘአዜበ ኢትዮጵያ ተሳዬ አሠሩ ለአቡነ ዜና ማርቆስ ይባል። ስለ ስበካውም ርቀት በርክበ ካህናት ጊዜ እንዳ ይቸገሩ ስምዎም መሠረት እንዲሆንዎ ከመኻል ሸዋ ቦታ እናደርጠ ግልዎታለን ተብሎ በጃንሆይ ማኅተም ከታተመ በኋላ እንደ ገና በጸሐፌ ትእዛዙ ማኅተም ተጉለት ወደሳቸው ይሁን ተባለ።

/ረ/ አባ እንጌ ጳጳስ ዘመስዐ ኢትዮጵያ። /ተጂሚ ያልተደረገበት ተመድቦ የሚጠበቅ ቦታ/።

ራሱ ከምባታ ዛንጅሮ አግሩ እንግሊዞች ድንበር ድረስ።

| | |
|---|---|
| ጐፋ | ኮንታ |
| ባኮ | ጅማ |
| ቁጫ | ኖኖ |
| ቦረዳን ጨምሮ | ከፋ |
| ኩሎ | ሊሙ |
| ዛንጅሮ | ማጂ |

ስለ አቀማመጥና አስተዳደር

መንፈቁን ከፋ መንፈቁን ጐፋ ሲዛወሩ የሚከተልዎ . . . አድራሻዎም ጳጳስ ዘመስዐ ኢትዮጵያ ተሳዬ አሠሩ ለአቡነ ሕፃን ሞዓ ይባል። ስለ ስበከውም ርቀት በርከበ ካህናት ጊዜ እንዳይቸገሩ ስምዎም መሠረት እንዲሆንዎ ከመኻል ሸዋ ጠራ ወደ ርስዎ ይሁን።



# አባሪ 2

# ሁለተኛ ክፍል

## በኢትዮጵያና በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ስላለው ጉዳይ የተደረገ ንግግር።

### ከታሪኩ ባጭሩ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በቋንቋዋ የሚለብከላትና በመከራዋ ጊዜ የማይለያት ሊቀ ጳጳሳት ከተወላጆቿ ለማግኘት ስታስብበት የቆየ ነገር ነው። በ1929 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሕዝብና በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ብርቱ መከራ ደርሶ ሳለ ሊቀ ጳጳሱ ወደ አገራቸው ወደ ግብፅ ገብተው ነበር። በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስዋን በመከራ ጊዜ ከማይለይዋት ከተወላጆቿ ከመንፈሳውያን አባቶች መካከል ለማግኘት ከማያከራክረው ለዓት ላይ ደረሰች።

ሊቀ ጳጳሱ ወኪል ያደረጓቸው ጳጳሱ አቡነ አብርሃም በ1930 ዓ.ም ኅዳር 29 ቀን በሊቃውንት ሲኖዶስ ጉባኤ ተመርጠው ሊቀ ጳጳሳት ሆኑ። ጳጳሳትንም ሾሙ። እርሳቸውም ሲያርፉ ተከታያቸው አቡነ ዮሐንስ በሊቃውንት ሲኖዶስ ጉባኤ ተመርጠው የያውራጃው ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጳሳት ቆሞሳትም ባሉበት ሊቀ ጵጵስናውን ተሾሙ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓይነት አስተዳደር በተወላጆቿ ተጠብቃ ሳለች ኢትዮጵያ ነጻነቷንና ንጉሠ ነገሥቷን ለማግኘት በቃች።

በ1933 ዓ.ም በመጋቢት ወር ፓትርያርኩ አቡነ ዮሐንስ የሁለቱን ቤተ ክርስቲያኖች ግንኙነት ለማቃረብ መልክተኛ ይልኩ ዘንድ አስበው ጥያቄ ቢያቀርቡ ለጥያቄአቸው የቅንነት መልስ ተሰጣቸው። እሳቸው ግን የስምምነቱ ጉዳይ ከመፈጸሙ አስቀድሞ የፊተኛው ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ መልክተኛ ሆነው ከሌሎች ተከታዮች ጋር እንዲመጡ አደረጉ። ከንግግሩም በኋላ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስተያን ያሳት የስምምነት አሳብ ተገልጾላቸው የቀሩት መልክተኞች ሲመለሱ አቡነ ቄርሎስ ከዚሁ ቆዩ።

በዚህ ጊዜ ከግብፃውያን በኩል በቀረበው አሳብ መሠረት ስምምነቱን ያለ ቅርታ በፍጥነት በመፈጸም ምክንያት ይሆናል ተብሎ ታስቦ ስለ ነበረ የሊቀ ጳጳሳቱን መንበርና ግቢውን ይዘው በሥራው ላይ የነበሩት ኢትዮጵያዊው ሊቀ ጳጳሳት በ1934 ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

በስኔ ወር ግቢውን እንዲለቁ ተደረገ። ቀጥሎም ስለ ትሕትና ሊባል የፊተኛው ሊቀ ጳጳስ እንዲገቡ ከተደረገ በኋላ የጳጳሳቱም ከሥራ መቈየት የስምምነቱን ፍጻሜ እንዲጠብቅ ሆነ።

ከዚህ በኋላ ነገሩን የሚያረዝመው ምክንያት እየበዛ ሄደ። እንደ አጋጣሚም ፓትርያርኩ አቡነ ዮሐንስ በ1934 ዓ.ም በስኔ ወር ስላረፉ ሌላው ፓትርያርክ እስኪሾሙ ብዙ ወሮች አለፉ። በሁለተኛው ዓመት በ1936 ዓ.ም ሁለቱም ወገኖች አዲስ አበባ ላይ ስብሰባ አድርገው ንግግሩን እንደ ገና ጀመሩ።

በዚህ ጊዜ የተደረጉት ንግግሮችና ከዚያም በኋላ የተሳሳኩዋቸው አንዳንድ ደብዳቤዎች ወደ ፊት ተጽፈው የሚገኙት ናቸው።

የስብሰባው ቃለ ጉባኤ

ስብሰባው በስኔ 12 ቀን 1936 ዓ.ም ከቀኑ በ10 ሰዓት አዲስ አበባ በቤተ መጻሕፍት ወመዘክር ዉሉን በብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ሰብሳቢነት ተደረገ።

ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ከተከታዮቻቸው ጋር ቀረቡ።

ስለ እስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ዋናው መልክተኛ ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስና ተከታዮቻቸው ቀረቡ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች

ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ። በኢትዮጵያና በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ስላለው ጉዳይ ካሁን በፊት ከብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ተልከው ለመጡት መልክተኞች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትፈልገውና መልክተኞቹም ሊያውቁት የሚፈልጉት ነገር በዝርዝር ተሰጥቷቸው ሄደው ነበር። ይኸውም ጥያቄ በአቡነ ዮሐንስ ሞትና በአዲሱ ጳጳስ አለመሾም ምክንያት ዘግይቶ ስለ ነበረ ሳይፈጸም ቈየ። አሁን የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች የሆናችሁ እናንተ ለፊተኛው ጥያቄያችን ምን መልስ አመጣችሁልን? ብለው ጠየቁ።

<u>የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች መልስ</u>

«ካሁን በፊት የመጡት ሰዎች አቡነ ቄርሎስን እንዲከተሉና የግዛቱን ጉዳይ እንዲመረምሩ ነው እንጂ ከዚህ የተሰጣቸውን ጉዳይ ለመቀበል አልተላኩም ነበር። ይሁን እንጂ እዚህ በነበሩበት ጊዜ የተሰጣቸውንና ያገኙትንም ለብፁዕ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት



አስታውቀዋል።

ያንኑ ጉዳይ የሚነጋገሩ ሰዎች እንዲላኩ ሲሉ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትን ጠይቆ ይምጡ የሚል መልስ ካገኘን በኋላ ነው የመጣነው። ይሁን እንጂ የፊተኞቹ መልክተኞች የቤተ ክህነትን ጉዳይ የማያውቁ ስለ ነበሩ አሁን በጉዳዩ ሊነጋገሩ የሚችሉትን አቡነ ጢሞቴዎስን ፓትርያርኩ ልከዋቸዋል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንንም ጥያቄ ያጠናነው ስለ ሆነ አሁን ንግግሩን ለመቀጠል ይቻላል። ብለው ንግግራቸውን በመቀጠል እንዲህ አሉ።

በቀረበው ሪፖርት እንደ ተመለከትነው 1ኛ ጥያቄ ከኢትዮጵያውያን አንድ ሊቀ ጳጳስ እንዲሾም ነው። ለዚሁም የተሰጠው ምክንያት ያገሩን ቋንቋና ልማዱንም ሁሉ የሚያውቀው ስለሆነ ኢትዮጵያውያንን በልዩ ልዩ ሃይማኖት ከኦርቶዶክስ ሃይማኖታቸው እንዳይለውጡ ለማድረግ የሚቀናው በመሆኑ ነው ተብሏል።»

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች የተናገሩት

«ከዚህም ከተነገረው ምክንያት በቀር ሌላም አለ። 1ኛ/ ቋንቋውንና የሕዝቡን ዝርዝር ጉዳይ ሁሉ በማወቅ የቤተ ክርስቲያናችንን አስተዳደር ለማሻሻል የሚቻለው ያገር ተወላጅ ሊቀ ጳጳስ ሲገኝ ነው። 2ኛ/ ባለፉት የመከራ ዘመኖች እንደ ተደረገው ሁሉ ለምሳሌ እንደ አቡነ ጴጥሮስና እንደ አቡነ ሚካኤል፣ እንደ ደብረ ሊባኖሶችና እንደ ዜና ማርቆሶች፣ እንደ ማኅበረ ሥላሴዎችም ለሕዝቡ በመንፈስ መጽናኛ የሚሆኑና ለሃይማኖታቸውም ለኢትዮጵያ መሥዋዕት የሚሆኑላት በመከራ ጊዜ የማይለዩ ያገር ተወላጆች ጳጳሳት ኢትዮጵያ እንዲኖሯት ያስፈልጋል። 3ኛ/ እንዳለፈው ጊዜ አደጋ ሆኖ መንገድ ሲቋረጥ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጠባቂ ካገሯ የማያስወጣው የራስዋ ሊቀ ጳጳሳት ሊኖራት ይገባል። 4ኛ/ በብዙ የሃይማኖት ወረራ ስትፈተን ከ1600 ዘመን ይበልጥ ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያላትን አንድነት ሳታቋርጥ በታማኝነት የኖረች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አንድ ሊቀ ጳጳስ ከቤተ ሰቦቿ ለማግኘትና ይኸውም ሊቀ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሾም ሥልጣን የተሰጠው እንዲሆን ትፈልጋለች። ይኸውም ሲሆን የኢትዮጵያና የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በሃይማኖት አንድ ነታዛዡ [illegible]ና ሆኖ ስለ ሚኖር የምንጠይቀው ሊቀ ጳጳስ በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ሥልጣን እንዲሾም ነው።»

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች የሰጡት መልስ

ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ሊቀ ጳጳስ የመሾሙ ጉዳይ የተባለ [illegible] ውሳኔ የሚነካ በመሆኑ የሁለታችንንም ቤተ ክርስቲያኖች መሠረት የሚያፈርስ ስለ ሆነ እጅግ አስቸጋሪ ጉዳይ

www.ethiopianorthodox.org

ነው::

ስኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስነት የሚሾመው ግብፃዊ የአማርኛን ቋንቋ አጥርቶ የሚያውቅ እንዲሆን በመታሰቡ በውስጡ ሆነው ስሚሾሙት ኢትዮጵያውያን ጳጳሶች ጋር በኅብረት የሚሠሩ ሲሆን ልጆቹን ከሃይማኖት መስወጥ ለማዳንና የቤተ ክርስቲያናችንንም ደንብ ለማሻሻል የሚበቃ ችሎታ ይኖረዋል::

1600 ዘመን ያህል በኢትዮጵያ የነበሩት ጳጳሶች ባገሩ ላይ ከደረሰው ፈተና ተካፋይ በመሆን በጦርነትም የሞት ተካፋይ መሆናቸው ይዘነጋ አይመስለንም:: በጠላትም አስገዳጅነት ግብፃዊው ጳጳስ ካገር እንዲወጣ ቢሆን በውስጡ ካሉት የኢትዮጵያ ጳጳሳት አንዱን በወኪልነት እንዲሠራ ሥልጣን ሰጥቶታል ብለው መለሱ::

<u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች</u>

ባለፉት ጊዜያት ኢትዮጵያን የወረራት ፋሺስት አቡነ ቄርሎስን ካገር ሲያስወጣና በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ የተሾሙትን የኢትዮጵያን ጳጳሳት ከአቡነ እብርሃም በቀር ሲገድል የአቡነ ቄርሎስ ወኪል የነበሩት እቡነ እብርሃም ዓይናቸው ተሰውሮ በሕመማቸው ምክንያት የዕድሜያቸው ፍጻሜ መቅረብ ሲሰማቸው ከእስክንድርያው ጳጳስ ጋር ለመገናኘት በፍጹም የማይቻል በመሆኑ ሃይማኖታቸውን ለማዳን የሲቃውንት ስብሰባ አድርገው ጳጳሳትን ከውስጣቸው ቢመርጡ የእስክንድርያ መንፈሳዊ ጉባኤ በውግዘት ከመለየት በቀር ስተደረገባቸው ችግር ዕርዳታ ሲያደርግላቸው አልቻለም::

<u>የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች መልስና ጥያቄ</u>

የአቡነ ቄርሎስ ወኪል የነበሩት አቡነ አብርሃም ከእስክንድርያው ጳጳስ ጋር የሚገናኙበትን መንገድ ስማጣታቸው የተነሣ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በሃይማኖት አባት እጦት ምክንያት ከባዕድ ሃይማኖት ወረራ ለማዳን ጉባኤ አድርገው ጳጳሳትን ሾሙ:: ይህንስ ባያደርጉ ምን መንገድ ይገኝለት ኖሯል? በነሱስ ቦታ እናንተ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ኖሯል?

<u>የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች መልስ</u>

በእውሮፕላን ወይም በነፋስ ስልክ መገናኘት ይቻል ነበር እሉ::

<u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች መልስ</u>

በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ባትኖሩ ነው እንጂ፡ የነበሩት አውሮፕላኖችና የነፋስ ስልኮች የኢጣልያኖች ብቻ እንደ ነበሩ ትረዱት ነበር እኳቸው::



ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ሳይገኝ ቀርቶ በጉባኤ ኒቅያ ተወሰኗል በተባለው ጉዳይ ንግግራቸውን ሲቀጥሉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች በጉባኤ ኒቅያ ውሳኔ ሳይ ኢትዮጵያውያኖች ሊቀ ጳጳስ አይሹሙ ይላል እንጂ ራሳቸው አይሾሙ አይልም አሉ::

<u>የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች</u>

በዓረብኛ በተጻፈው ላይ አይሹሙ ደግሞ አይሾሙ ነው የሚለው እሉ::

<u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች</u>

እናንተ በዓረብኛ የተጻፈውን ቃል መሠረት ስታደርጉ እኛም በግእዝ የተጻፈውን መሠረት በማድረግ የተለያየ ቃል ቢኖርበት ጥንታዊ ጽሑፍ በግሪክ ስለ ሆነ ከግሪክ ሊቅ መርጠን እናስተርጉመው::

<u>የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች</u>

ለ1600 ዘመን በኢትዮጵያውያን ሊቀ ጳጳስ ሳይሾም መኖሩ ጉባኤ ኒቅያ የማይፈቅድ መሆኑን ያስረዳል ሲሉ መለሱ::

<u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች</u>

እስከ ዛሬ ሳንጠይቅም ብንቈይ ዛሬ በማወቅና ለጊዜውም አስፈላጊ በመሆኑ ጳጳስ እንዲሾምልን ብንጠይቅ የጊዜው መቈየት የጉባኤ ኒቅያን ጽሕፈት የሚለውጠው አይደለም::

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች

የሁለት አገሮች ቤተ ክርስቲያኖች ባንድ ጳጳስ መተዳደር ያገሮቹን ክፍታና ዝቅታ የሚያሳይ አይደለም:: ይህም ሲታወቅ ፈረንሳይ፤ እስፓኝ፤ ፖርቱጋልና ሌሎችም አገሮች በሮማ ጳጳስ ይተዳደራሉ ሲሉ ምሳሌ አደረጉ::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች

እኛም ከነዚህ ከተቈጠሩት አገሮች የተለየ መብት ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አልጠየቅንም:: ፈረንሳዊ፣ እስፓኝና ፖርቱጋል የሚያስፈልጓቸውን ጳጳሶች ካገራቸው ሰዎች በሮማ ጳጳስ ያሾማሉ እንጂ የሮማው ጳጳስ የኢጣልያን ተወላጅ የሆነውን ሰው እየሾመ አይልክባቸውም ብለው መለሱ::

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች

www.ethiopianorthodox.org

የሮማ ጳጳስ በያገሩ እንደራሴዎች አላቸው እኮ ::

<u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች</u>

የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ሆኖ አንድነታችንን የሚያጸና መልከተኛ ቢኖራቸው ችግር ነገር ያለበት መስሉ አይታየንም::

<u>የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች</u>

ሊቀ ጳጳስ ይሾም መባሉ ለክብር ብቻ ነው እንጂ እርሱ የሚያደርገውን ጳጳሳት ሊያደርጉት ይችላሉ:: ስለዚህ ኢትዮጵያውያን የሆኑ ጳጳሶች ቢኖሩ ለቤተ ክርስቲያኑ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሁሉ ለማድረግ ይችላሉ አሉ::

<u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች</u>

1600 ዘመን ያህል በመከራና በዓለምም ጊዜያት በማርቆስ ሃይማኖት ጸንተው ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋራ ያላቸውን ግንኙነት ጠብቀው ለኖሩት ለኢትየጵያውያን ልጆቻቸው ሊቀ ጳጳሱ ለግብፃውያን በሚያደርጉት እኩልነት ለምን ይነፍገናል ብለው ጠየቁ::

የእስክንድርያ ቤተ <u>ክርስቲያን</u> መልክተኞች

ሊቀ ጳጳሱ ኢትዮጵያውያንን በመውደዳቸው በግብፅ ውስጥ ጳጳሳት አያሉ ሲሾሙ በኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ብለው ይሾማሉ ሲሉ መለሱ::

<u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች</u>

እንግዲህ የጠየቅነው ኢትዮጵዊ ሊቀ ጳጳስ በሰምምነትና በወዳጅነት የሚሾምልን ነውን? ወይስ አይቻልም ነው የምትሉን? ብለው ጠየቁ::

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች

ይህን ጉዳይ ሳንሲኖድ የተባለው የእስክንድርያ ቤተ ክርስተያን ታላቁ ጉባኤ መክሮበት የሚቈረጥ ነው እንጂ ይሆናል ወይም አይሆንም ማለቱ የኛ መብት አይደለም::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች

ጉዳዩ በሳንሲኖድ ጉባኤ የሚቈረጥ መሆኑ እርግጥ ነው:: ይኸውም ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ብርቱ ጉዳይ ስለ ሆነ የብፁዕ አባ ጢሞቴዎስና የናንተም የመልክተኞቹ መልካም አስተያየትና ዕርዳታ እንዲሰጠው ተስፋ እናደርጋለን አሉ::



<u>የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች</u>

የጉዳዩን ታላቅነት እናውቃለን:: ይህም ነገር በሚቈረጥበት ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች እንዲከራከሩበት በጉባኤው ላይ እንዲገኙ ተስፋ አለን ቢሉ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞች የኢትዮጵያ መልክተኛ ሄዶ እንዲነጋገር አስፈላጊ መሆኑ የታወቀ ነው:: ይሁን እንጂ በጉባኢ ኒቅያ ትርጉም የማንስማማ ቢሆን በጉባኤ ኒቅያ ከነበሩት ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ አማካይ ተርጓሚዎች ለመምረጥ ይቻል የለምን ሲሉ ጠየቁ::

<u>የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች</u>

የዚህ ዓይነት ትርጉምና የአሳብ መለያየት ቢያጋጥም ሁለታችንም ወገኖች በግሪክ ቋንቋ ሊቆች የሆኑ እርቶዶክሳውያን ሰዎች ለመምረጥ ይቻላል ሲሉ አስታወቁ::

ከዚህ በኋላ የሚቀረውን ጉዳይ በሰኔ 13 ቀን 1937 ዓ.ም በ10 ሰዓት ተኩል በዚሁ ቦታ ሁለቱም ወገኖች ተሰብስበው ንግግራቸውን እንዲቀጥሉ ቀጠሮ ተደረገ::

www.ethiopianorthodox.org

# አባሪ 3

የኢትዮጵያ መንፈባዊ ጉባኤ በ14 ሰኔ 1936 ዓ.ም ጽሮ ሰብፁሰ አቡነ መቃርዮስ የላክውና ስድስት ጥያቄዎች የተመለከቱበት ደብዳቤ

መንፈሳዊ ጉባኤ ዘመንግሥተ ኢትዮጵያ

አዮአ ሰኔ 21 ቀን 1937 ዓ.ም

የኦርቶዶክባዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ለብፁዕ አባታቸው ለሊቀ ጳጳሳት አቡነ መቃርዮስ የትሕትና ሰላምታቸውን እያቀረቡ በቅዱስ ማርቆስ መንበር ተቀምጠው ይባርኳቸው ዘንድ ስለ ተመረጡ ደስታቸውን ይገልጻሉ።

ከዚህ በኋላ ቀጥሎ ያለውን እሳብ ሲያቀርቡ ብፁዕ አባታቸው አቡነ መቃርዮስ በነገሩ በጣም እንዲያስቡበትና መልካም ፍጻሜ እንዲያስገኙለት ተማምነው ነው።

ብፁዕ አባታችን ሆይ

ኢትዮጵያ በፋሺስቶች መንግሥት በተወረረችበት ሰዓት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር መገናኛዋ እየተቋረጠባት የመከራው ዘመን እስኪያልፍ ድረስ ራሷን ችላ መኖሯ የታወቀ ነው። የመከራውንም ዘመን በሃይማኖቷ ጸንታ ወደ በላሙ ዘመን በደረሰች ቁጥር ከማርቆስ መንበር ላይ የተቀመጠውን አባቷን ከመፈለግ አቋርጣ አታውቅም፤ አሁንም ወደ ፊት ያላት ምኞት ይኸው መሆኑን ስትገልጽ ደስ ይላታል።

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብት ባለማግኘቷ ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ እደጋ በመጣ ቁጥር ለክርስቲያን የሚገባውን ሥርዓት ሁሉ ለኢትዮጵያ ምእመናን ለማድረግ እልቻሉም። በዚህም ምክንያት ወደ ሌላ ሃይማኖት የሄዱና የሌላውን ሃይማኖት ባሕል የለመዱ ብዙ አትዮጵያውያን ናቸው።

ስለዚህ ወደ ፊት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ማርቆስን አባትነት ሳትለቅ ሃይማኖቷ የሚጸናበትንና ምእመናኗም የሚጠቀሙበትን መንገድ ለመመሥረትና ለመከተል ግዴታ እንዳለባት ስለ ተገነዘበች የሚከተሉትን መብቶች እማርቆስ መንበር ላይ የተቀመጡት ቅዱስ አቡነ መቃርዮስ ባርከው እንዲሰጧት ትለምናለች።




# አባሪ 3

የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ በ14 ሰኔ 1936 ዓ.ም ጽፎ ለብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የላከውና ስድስት ጥያቄዎች የተመለከቱበት ደብዳቤ

መንፈሳዊ ጉባኤ ዘመንግሥተ ኢትዮጵያ

አዮአ ሰኔ 21 ቀን 1937 ዓ.ም

የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ለብፁዕ አባታቸው ለሊቀ ጳጳሳት አቡነ መቃርዮስ የትሕትና ሰላምታቸውን እያቀረቡ በቅዱስ ማርቆስ መንበር ተቀምጠው ይባርኳቸው ዘንድ ስለ ተመረጡ ደስታቸውን ይገልጻሉ።

ከዚህ በኋላ ቀጥሎ ያለውን አሳብ ሲያቀርቡ ብፁዕ አባታቸው አቡነ መቃርዮስ በነገሩ በጣም እንዲያስቡበትና መልካም ፍጻሜ እንዲያስገኙለት ተማምነው ነው።

ብፁዕ አባታችን ሆይ

ኢትዮጵያ በፋሺስቶች መንግሥት በተወረረችበት ሰዓት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር መገናኛዋ እየተቋረጠባት የመከራው ዘመን እስኪያልፍ ድረስ ራሷን ችላ መኖሯ የታወቀ ነው። የመከራውንም ዘመን በሃይማኖቷ ጸንታ ወደ ሰላሙ ዘመን በደረሰች ቁጥር ከማርቆስ መንበር ላይ የተቀመጠውን አባቷን ከመፈለግ አቋርጣ አታውቅም፤ አሁንም ወደ ፊት ያላት ምኞት ይኸው መሆኑን ስትገልጽ ደስ ይላታል።

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብት ባለማግኘቷ ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ አደጋ በመጣ ቁጥር ለክርስቲያን የሚገባውን ሥርዓት ሁሉ ለኢትዮጵያ ምእመናን ለማድረግ አልቻሉም። በዚህም ምክንያት ወደ ሌላ ሃይማኖት የሄዱና የሌላውን ሃይማኖት ባሕል የለመዱ ብዙ አትዮጵያውያን ናቸው።

ስለዚህ ወደ ፊት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ማርቆስን አባትነት ሳትለቅ ሃይማኖቷ የሚጸናበትንና ምእመናኗም የሚጠቀሙበትን መንገድ ለመመሥረትና ለመከተል ግዴታ እንዳለባት ስለ ተገነዘበች የሚከተሉትን መብቶች እማርቆስ መንበር ላይ የተቀመጡት ቅዱስ አቡነ መቃርዮስ ባርከው እንዲሰጧት ትለምናለች።


1ኛ. ከኢትዮጵያ ተወላጆች ውስጥ በቤተ ክህነት ክፍል አድገው፤ በሃይማኖቷ ጸንተው ከሚኖሩት ከመንፈሳውያን አባቶች ለሊቀ ጳጳስነት የሚገባው ሰው ተመርጦ በእስክንድርያው አባታችን ተባርኮና ተቀብቶ እንዲሾምላት፤

2ኛ. የእስክንድርያው ሲኖዶስ በሚመረጥበት መሠረት የኢትዮጵያም ሲኖዶስ ለጵጵስናና ለኤጲስ ቆጳስነት የሚገቡትን መንፈሳውያን አባቶች እንዲመርጥና ከእስክንድርያ አባታችን ተቀብቶ የመጣው ሊቀ ጳጳስ ባርኮ እንዲሾማቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

3ኛ. በማርቆስ መንበር ላይ የሚቀመጠው አባታችን በሚመረጥበት ጊዜ የቅዱስ ሲኖዶስ በር ለኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያን ክፍት እንዲሆንና መልክተኞቿ በምርጫው ውስጥ እንዲገኙ፤

4ኛ. የኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያን ዘወትር በእስክንድርያው ቅዱስ ሲኖዶስ ውስጥ መንበር እንዲኖራትና ሲኖዶሱ በተሰበሰበ ቁጥር መልክተኞቿ በሚገባቸው ደረጃ ተቀምጠው እንዲገኙ፤

5ኛ. ኢትዮጵያ በውድ ሳይሆን በግድ በጦር ኃይል ከእስክንድርያ ጋር እንዳትገናኝ ተከልክላ በተቋረጠችበት ጊዜ በሃይማኖቷ ጸንታ ወደ ሰላም ዘመን እስክትደርስ መርጣ የሾመቻቸውን ጳጳሳት ከግዝቱ እንዲፈቱላት፤

6ኛ. በኢትዮጵያና በእስክንድርያ መካከል ያለው መንፈሳዊ ግንኙነት አሁን ካለው የበለጠ እንዲሆን የእናትነትና የልጅነትም መሠረት የጠነከረ ሆኖ እንዲኖር የገዳም ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ እንዲከፈት፤ ስለዚሁም ተማሪ ቤት አቋቋምና አካሄድ ቅዱስ አባታችን አቡነ መቃርዮስ፤ ቅዱስ ቡራኬያቸውን እንዲሰጡን:: ከዚህ ተማሪ ቤት ተመርቀው ለጵጵስና፤ ወይም ለቁምስና የታዩት መምህሮች በምስር ገዳማት ውስጥ እየሄዱ ከወንድሞቻቸው ጋር በመንፈስ ተባብረው እንዲመለሱ እንደዚሁም ከምስር የሚመጡት ወንድሞቻችን በኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ ሲመጡ በመንፈሳቸው ሁሉ የተባበሩ ወንድሞች አግኝተው እንዲመለሱ::

ከዚህ በላይ በስድስቱ አንቀጾች የተመለከቱት ጉዳዮች ለእስክንድርያና ለኢትዮጵያ አንድነት ዘለዓለማዊ መሠረት መስለው የሚታዩን ናቸው:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሌሎቹ ኦርቶዶክሳውያን ብቸኝነትን አትፈልግም:: ከእስክንድርያ ጋራ በአንድነቷ ጸንታ ለመኖር ስለ ፈለገች ነው መለያየት የሚያመጡትን ምክንያቶች ሁሉ ለማስወገድ የወደደችው::

እነዚህን በስድስቱ አንቀጾች የተመለከቱትን ጉዳዮች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ሆኖባት የጠየቀችበት ምክን ያት፤ ከብፁዕ አባታችን ተልከው ከመጡት ሰዎች ጋራ በተደረገው ጉባኤ የንግግር ማስታወሻ ውስጥ ይገኛል::

ይልቁንም በአንደኛውና በሁለተኛው አንቀጽ ውስጥ የተመለከቱት ዋናዎቹ ጥያቄዎች ለቀድሞው ጊዜ አስፈላጊ አይደሉም ተብለው ተደንግገው እንኳን ቢሆን የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ መንፈስ በፍጹም አልተቀበለውም::

ስለዚህ ብፁዕ አባታችን እቡነ መቃርዮስ የአሳባችን ተካፋይ ሆነው፤ የኢትዮጵያንና የእስክንድርያን መሠረት ለማናወጽ የተነሡ ትን ነፋሳት በተሰጣቸው በታላቁ ረድኤት ለማስወገድ እንዲ ደክሙ በትና እንዲችሉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እጥብቃ ታሳስባለች::

እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ዘነበረ በመንበረ
አቡነ ተክለ ሃይማኖት

www.ethiopianorthodox.org